ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት

# ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት




ከሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org




ከሊቀ ሥ

www.ethiopianorthodox.org

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤ ንጉሠ ነገሥት ዘኢትዮጵያ የክርስትና ሃይማኖት ጠባቂ በ፴፰ኛው ዘመነ መንግሥት ይህ መጽሐፍ ብርሃንና ሰላም ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ማተሚያ ቤት ታተመ ።

በሙሉም በከፊልም ለማሳተም መብቱ የደራሲው ነው ።

www.ethiopianorthodox.org



ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ፤
የሃይማኖታችን ጠባቂና የሥነ ሥርዓታችን አስከባሪ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ግርማዊ ሆይ ፤

ሀገራችን ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር እንደመሆኗ በዘመን በዓይነት የተለያዩ ጥንታውያን የሆኑ ጥበቦችና የትምህርት ዓይነቶች አንድም አስደናቂዎች የሆኑ ቅርሶች አሏት ፤ እነዚህም ጥበባት ሁሉ ዘመን ሲያንገላታቸው ፥ ጠላትም ለማጥፋት ሲታገላቸው ኑሮ በማቸነፍ ርዝራዣቸው ፈጽሞ ሳይጠፋ ሁሉም ከኛ ዘመን የደረሱ ናቸው ። ይኸንም ሐተታ ስንሰጥ የዘመኑን ርዝመት የችግሩን ብዛት ለመናገር ያህል እንጂ ታዛቢ ሳይኖራቸው ጥበቃም ሳይደረግላቸው ኖሩ በማለት ጥንታውያን አባቶችን ለመውቀስ አይደለም ። እውነት ነው ፤ ጥበቃም ቢሆን አስፈላጊውን ያህል አልተደረገላቸውም ፥ እንዲሁ በዕድላቸው ተገኙ ኖሩም ለማለት ያስደፍራል ፤ ይሁን እንጂ ግርማዊነትዎ ገና አልጋ ወራሽና ባለሙሉ ሥልጣን እንደሆኑ ነገሩ አስቸኳይ መሆኑን በማመንና ጊዜም ባለመስጠት ጥበቦቻችን ሁሉ በየደረጃቸው መልክ ባለው አኳኋን እንዲጠበቁ ፥ ለትውልድም እንዲተላለፉ ለማድረግ ጀመሩ ። ስለዚህም በመጀመሪያ ሊቃውንቱን ሰብስበው እንዲማከሩ ፥ እንዲጽፉና እንዲተረጉሙ በጽሑፍም ወጥቶ ለልጅ ልጅ እንዲዳረስ የመወያያ የመሥሪያ በር ከፈቱላቸው ።

ሊቃውንት ያሉት አገርና ሕዝብ ሁሉም ሊቅ እንደሆነ የታመነ ነው ፤ ምክንያቱም ምንም ቢሆን ሊቃውንት ያሉት ሕዝብ ችግር አይፈጠርበትም ፥ ቁም ነገር አይጠፋበትም ፥ ለሁሉም ነገር ልክ መልክ ይሰጡታል ። ስለዚህ በሠለጠኑት ሀገሮች ሁሉ ባለሥልጣኖች ሊቃውንቱን ዘመኑ በፈቀደው መልክ መከባከብና መጠበቅ ተገቢ መሆኑን በማመን ለሊቃውንቱ ሕይወት ፤ ለዕውቀታቸው መስፋፋት ፤ ለትምህርታቸው አሰጣጥ ያስባሉ ፤ ማለት ሊቃውንት በነፃ እንዲያስቡ ፤ በነፃም እንዲሠሩ ልዩ ርዳታ ያደርጉላቸዋል ፤ ይከባከቧቸዋል ፤ በገንዘብም ቢሆን ከፍ ያለ ባጀት ይመድቡላቸዋል ፤ ስለዚህም በነፃ ይሠራሉ ፤ ዕውቀታቸውንም ለሁሉ በተገቢው መንገድ ያድላሉ ፤ ለተተኪውም ትውልድ ያስተላልፋሉ ።

## ግርማዊ ሆይ ፤

ይኸ ሁሉ ነገር እንግዳ አልሆነብዎም ፤ ማለት ከላይ እንደገለጥኩት ሁሉ ከሊቃውንቱ ጋር ሁልጊዜ አብረው እንደመዋልዎ የጉባኤውም ሁሉ ተካፋይ እንደመሆንዎ የዐዋቂዎችን መጠን ለመገመት ችለዋል ፥ ጥንታውያን ጥበባትን ቀስመዋል ፤ ስለዚህ እነርሱም እንዳይቸገሩ ጥበባቸውም በሜዳ እንዳይቀር በማለት ዘመኑን የተከተለ ዕቅድ በማውጣት ፥ ሊቃውንቱን ሰብስቦ መያዝ አስፈላጊ መሆኑን አምነው ጀመሩ ፤ ይኸም ብቻ ሳይበቃዎ ዕውቀታቸው በጽሑፍ እንዲቀረጽ ለማድረግ የመጀመሪያውን የማኅተም መኪና በግል ገንዘብዎ አስመጥተዋል ፤ በዚህም ምክንያት የመጀመሪያው የአማርኛ ሥነ ጽሑፋችን በር ከፋች ሁነውልናል ። የዘመኑን

www.ethiopianorthodox.org

ርኅቀት ፤ የችግሩን ብዛት ፤ የጥበባችንንም ዓይነት ስንመለከት ደግሞ ፤ ይኸን የመሳሰሉ ሌሎች የረቀቁ ጥበባት በጽሑፍ ሳይቀረጹ በሰውም እጅ ሳይደርሱ ከሊቃውንቱ ጋር አብረው ቀደም ብለው የጠፉ እንዳሉ በቀላሉ ልንረዳ ችለናል ።

በተደረገው ጥረት እንደሰት እንጂ በጠፋው ማሰባችን አይቀርም፤ሆኖም በጠፋው ምርምር እንድናደርግ አሁንም ግርማዊነትዎ የኢትዮጵያ ምርምር ጥናት ብለው በር ከፍተዋል ።

በጠቅላላውም አስተያየት ግርማዊነትዎ የሊቃውንት ፈጣሪ ሁነው በመገኘትዎ በዘመንዎ ብዙ ጥበባት ሊታደሱ ችለዋል ፤ የጠፋው ተገኝቷል ፤ የሞተው ተነሥቷል ፤ የኢትዮጵያም ጥናት በሰፊው ተጀምሯል ፤ የውጭ የውስጥ ሊቃውንት ተገናኝተው በነፃ የመወያየትን ዕድል ሰጥተዋል ።

ግርማዊነትዎ የሊቃውንት ችግርና የዕርምጃቸው ተሳታፊ በመሆንዎ ደግሞ ዕውቀታቸውን በሰፊው ለማበርከት ችለዋል ። ይኸን ከፍተኛ ጥረትዎን ያለው ትውልድ ቢያውቀውም መጭው ትውልድ እንዲገነዘበው ደግሞ በጽሑፍ ማስቀመጥ የሁላችን ግዴታ ነው ፤ ከዚህም ጋር በዘመንዎ የተነሡትን ፤ ቀደም ብለው የነበሩትን የሊቃውንቱን ችሎታ ፤ የትምህርቱን ዓይነት ፤ የትምህርትም አሰጣጥ ዘዴአቸውን ሌላም ይኸንና ይኸን የመሰለውን ሁሉ ለመግለጥ «ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት» በሚል አርእስት፤ጽሑፍ አዘጋጅቼ መታሰቢያነቱን ሕይወታቸውን ሙሉ ለዕውቀት ሰጥተው ኢትዮጵያችን የዕውቀት ምንጭ ለአደረጉ መምህራን እንዲሆን ፤ በዚህም መልክ መጽሐፉ እንዲታተም እንዲፈቀድልኝ ከዙፋንዎ ሥር ወድቄ እለምናለሁ ።

ትሑት አገልጋይዎ ፤

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org



ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

www.ethiopianorthodox.org

# መ ቅ ድ ም ።

ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር እንደመሆኗ ጥንታዊ የሆነ ከማንም ሀገር ጋር ግንኙነት የሌለው ፣ ራሱን የቻለ፣ኢትዮጵያዊም የሆነውን ሁሉ የሚያኰራ ልዩ ጥናትንም የሚጠይቅ ከዚህ ቀደም ያልተደረሰበት ባህል አላት ።

ይሁን እንጂ ቃል በቃል ከመተላለፉ በቀር ብዙውን ነገር በታወቀ መልክ ጽፎ ያስቀመጠው ለምርምርም በር የከፈተለት የለም ፤ ይኸም ነገር አስፈላጊ መሆኑን አምነው ብዙ የውጭ ሊቃውንት ለማጥናት መሞከራቸው አልቀረም ፤ ቢሆንም የሚመለከቱት በራሳቸው አስተሳሰብ ብቻ ስለሆነ በኢትዮጵያዊ አስተሳሰብ ሳይሆን እንደመሰላቸው አድርገው ያቀርቡታል ።

አንዳንዶች ደግሞ በቅን ልቡና ተመልክተው ለመጻፍ ሲነሡ እንደዛሬው የቋንቋ መገናኛ ስለአልነበረን ቅን ልቡና ይኑራቸውና ሥራውን ይጀምሩት እንጂ ረዳት በማጣት እነርሱን እንደመሰላቸው ብቻ በግምት ጽፈዋል ።

ጥልቅ ምርምር አድርገው አቃቂርም አውጥተው እውነቱን ፈልፍለው መነሻውንና መድረሻውን ለይተው ሊጽፉ የሠነዘሩ ብዙዎች ነበሩ ፤ ግን አልሆነላቸውም ። የችግሩም መነሻ ሆኖ የተገኘው ፣ አገራችን ከሌላው ዓለም ሁሉ ተለይታ በመኖሯ ምክንያት እንደሆነ ተደርሶበታል ፤ ይኸም ሊሆን የቻለው በጠላትና ልዩ ልዩ አስተሳሰብ ባላቸው ሕዝቦች በመከበቧ ነው ፤ ኢትዮጵያም ከዓለም የተለየችውን ያህል ከብዙ ጥበባት ተለይታ ኑራለች ።

ይኸንም ስንመለከት በጣም ያሳዝነናል ፤ ማለት ታላቅ ርምጃ ያላት አገራችን በአላት ብቻ በመወሰኗ ነው ፤ ይሁን እንጂ ራሱ ችግሩ ቅሉ የተለየ ባህል የተለየም ሥነ ጥበብ እንዲኖራት የተለየም ጥናት እንድትወስድ አድርጓታል ።

ይኸም ሁናቴ በዚያን ጊዜ ይጉዳን እንጂ ለአሁኑ ጊዜ በጣም የሚያኰራ ባህልን ይዛ እንድትገኝ አድርጓታል ፤ ነገር ግን ይኸ ጥንታዊና የሚያስከብረን ባህላችን ጥበባችን በየመልኩ እንዲገኝ ያሰበበት ባለመኖሩ ፤ በየጊዜውም ተከታትሎ በጽሑፍ ያስቀመጠው ባለመኖሩ ፤ ከማሳዘኑም በላይ አሁን ተመልሶ ለኛው ሳይቀር መነሻውና መድረሻው ጠፍቶ ዕንቈቅልሽ መሆን ሲጀምር ይገኛል ።

የሆነውንና የነበረውን በየጊዜው ተከታትሎ በየመልኩ በጽሑፍ ካላሰፈሩት በመዋልና በማደር የትመጣው ይረሳል ፤ ነው ከማለት ይልቅ ነበር ወደማለት ያዘነብላል ፤ ቆይቶ ደግሞ የትመጣው ፈጽሞ ጠፍቶ ተወዳጅነቱን አጥቶ ይቀራል ።

ይኸንም በማመን የዓለም ሊቃውንት በሥነ ጽሑፍ አደባባይ ተሰልፈው ይኸንኑ ጥናት ለማድረግ ሲሽቀዳደሙ ይገኛሉ ፤ በዚህም መሠረት የአገራቸውን ባህል ይቅርና የሌላውን አገር ታሪክ በብዙ ጥረት ይጽፋሉ ።

የባህሎቻችን ዓይነታቸውና ስማቸው ብዙ ሲሆን ከሌላው ዓለም የተለየ ሆኖ የሚያኰራን ጥንታዊ ሕዝብነታችንና ታሪክ ያለን ሕዝቦች መሆናችንን ከሚ

www.ethiopianorthodox.org

ያስረዱት ውስጥ ፤

፩ኛ በቅርጻቅርጽ በሥዕል በሥነ ጽሑፍ ረገድ ከማንም ያልተቀዳ ራሱን የቻለ ታላቅ ጥበብ ሁኖ ተጠብቆ የኖረ ነው ።

፪ኛ ሥርዓተ ትምህርታችን መልክ ያለው አሰጣጥ ኑሮት ተጠብቆ መኖሩ ነው ።

ኢትዮጵያውያን የትምህርት ሕዝብ ሁነው አገራቸውን የዕውቀትና የጥበባት አገር አስደርገው አስከብረዋት ኑረዋል ።

የትምህርቱ ሥነ ሥርዓትም መልክ ያለው ሆኖ እንዲሰጥ በማድረጋቸው ትምህርታችን ከሌላው ዓለም የትምህርት አሰጣጥ ያላነሰ ራሳችንንም የሚያስችል ከፍተኛም ዕውቀት አስደርገውት ኑረዋል ።

ስለትምህርት ያለንን ባህል ፤ ትምህርት በሚለው ወስነን ተናገርነው እንጂ ለእያንዳንዱ ሞያ ራሱን ያስቻልነው እንደሆን ከፍ ያለ ምሥጢር እናገኝበታለን ፤ ለምሳሌ ፤ በዜማ ፤ በቋንቋ ፤ በሥነ ጽሑፍ ፤ ይኸንም በመሳሰለ በሌላ ነገር ሁሉ ከፍተኛ ግምት የሚጣልበት ዕውቀት እንደነበረን የታመነ ነው።

በቋንቋ በኩል የሔድን እንደሆን ግዕዛችን ቅዱስ ቋንቋ ሆኖ በሥነ ጽሑፍ ረገድ ቅዱሳት መጻሕፍት ተጽፈውበት ተተርጕመውበት ብዙ ሥራ ተሠርቶበት ይገኛል ።

በግጥም በኩል የሔድን እንደሆነ ብዙ ሊቃውንት የቅኔ አብነት በመሆን አዳዲስ ብዙ ቅኔዎች ተቀኝተውበት ብዙ ሥራ ሠርተውበት እናገኘዋለን ።

ይኸም ቋንቋ፤ውዳሴ ቅዳሴ የሚደረስበት ታላላቅ ቁም ነገር የሚጻፍበት ራሱን የቻለ ሕያው ቋንቋ ነው ተብሎ የውጪ ሊቃውንት ሳይቀር ተምረው በዩኒቨርስቲያቸው እንደሚያስተምሩት የታወቀ ነው ።

በዜማ በኩል የሔድን እንደሆን ፤ ቤተ ክርስቲያናችን የምትገለገልበት ለእግዚአብሔር ምስጋና የሚቀርብበት ፤ ለደስታ ለኀዘን ፤ መግለጫ የሆነ ራሱን የቻለ ምልክት ያለው ደንበኛ መንገድን የተከተለ ዜማ አለን ፤ እርሱም ልዩ የምስክር ቦታ ተወስኖለት ብዙ ደቀ መዝሙር ሲወጣበት የኖረ ነው ።

በሒሳብም ትምህርት በኩል ራሱን የቻለ ትምህርትና የአቈጣጠር ስልት ነበረን ፣ እንዲያውም እስከ ኮከብ መቍጠር የሚያደርስ የራቀ ወይም የረቀቀ መንገድ እንደነበረን ይነገራል ፤ ይሁን እንጂ እንዴት እንደነበረ እንዴትስ እንዳለ እስከ አሁን ቀዋሚ የሆነ ጥናት ስለአልወሰድንበት ባህላችን ለሌላው ቀርቶ ለኛ አለመታወቁ ግልጥ ነው ።

ሞያችንን አለማወቅ ፤ ለማወቅም አለመጣጣር ብቻ ሳይሆን ያደረብን ጥላቻ ለሌሎች አስገራሚ ሳይሆን አልቀረም ፤ ይኸም የሚሆንበት ምክንያት አንድ ሰው በሌላው ትምህርት ፍጹም ዕውቀት ኑሮት ፤ ይኸን ባህልና ሌላውን ይኸን የመሳሰለውን ሳያጣራና ሳያጠናቅቅ በመቅረቱ እንዳላዋቂ ያስገምተኛል በማለት አላ

www.ethiopianorthodox.org

ዋቂ ሁኖ ከመገመት ይልቅ እኔ ካላወቅሁት ምን ያደርጋል ለምንስ አይጠፋም የሚል አስተያየትን ስለሚያቀርብ ነው ።

ይኸም ነገር እርግጥ ነው ፥ ሊሆንም ይገባዋል ፤ ምክንያቱም ለማያውቁት ነገር አይጓጉለትም ፤ ያላዩትንም ነገር አይሹትምና ነው ። ያስተማራቸው ያሰማቸው ያሳያቸው ስለሌለ ፤ እንዲሁም ሊያውቁ ስለማይችሉ ጥሩነቱን ወይም መጥፎነቱን ለይተው ሊያውቁ አልቻሉም ።

የትምህርታችን ሥርዓት በዘመኑ ወይም በጊዜው ልክ መልክ ያለው የታወቀ መነሻና መድረሻ ያለው መሆኑን ባለፈው ተናግረናል ፤ በመካከለኛው ዘመን ግን መልኩን ለውጦ በመገኘቱ የትምህርታችን ሥርዓት ተወዳጁ አስቀያሚ ፤ ሥርዓት ያለው ደግሞ እንዲሁ በዕድሉ የተገኘ መስሎ መታየቱ የታመነ ነው ።

በዚህም ምክንያት የአሁኑ ሕዝብ እንደንቀት አድርጎ «የቄስ ትምህርት» እስከ ማለት ደርሶ ይናገራል ።

ይኸም ማለት አቅድ የሌለው መነሻና መድረሻው ያልታወቀ ፤ ዘላቂ ያል ሆነ ዕውቀት እንደሆነ በመገመት ነው ። ይሁን እንጂ የትምህርታችን ሥርዓት ከአሁኑ ሥርዓተ ትምህርት የበለጠ የተመጠነ የተለካ የማስተማሪያዎችም መጻሕፍት እንደየጊዜው ሁናቴ በደንብ የተዘጋጁ ሊቃውንቱም በዕውቀት የበሰሉ የትምህርት አሰጣጥን ዘዴ ያውቁ እንደነበሩ የማያብለው ታሪክ ያስረዳናል ።

እውነት ነው እየዋለ እያደረ ምክንያቱ ሳይታወቅ ትምህርቱ መልኩን እየለወጠ ፥ ሥርዓቱም እየጠፋ ሔዷል ፤ ስለዚህም በውጭ አገር የትምህርት ሥርዓት ብቻ ስንጠቀም በመገኘታችን በአዲሱ ሕዝባችን ዘንድ ምንም የትምህርት ቅርስና ቀዋሚም ባህል ያልነበረን አድርጎ ሊያስገምተን ችሏል ።

አሁንም አንዳንድ ጊዜ የዚህ ዓይነቱ ዕውቀት ሲነሣ እንደተናቀ ሰውየውም እንደ አላዋቂ በመገመት ላይ እንደሆነ ጥርጥር የለውም ፤ እውነቱንና ሐሰቱን ለመለየት ግን አንብቦ መረዳት ያስፈልጋል ።

ጥንታዊው ትምህርት በአሁኑም ጊዜ በመጠኑ የሚሰጥ ቢሆንም ቅሉ በጣም ቀዝቅዞ ይታያል ፤ ለወጥ ያለ መልክም የያዘ ይመስላል ፤ በዚህም ምክንያት የአንዳንድ ነገር የትመጣው በመጥፋቱ ከባድ ጥያቄን አስከትሏል ፤ ጥያቄውንም ሁሉ በቀጥታ ለመመለስ የሚችሉ በቍጥር ያነሱ ከመሆናቸውም በላይ ለነርሱም ቢሆን ልዩ ምርምር አስፈልጓል ።

አንዳንድ የዩንቬርስቲ ተማሪዎችና የውጭ አገር ሊቃውንት በመጡ ጊዜ የሚመረምሩትና የሚጠይቁት ሁሉ በዚሁ መጽሐፍ የሰፈረውንና እርሱንም የመሰለውን ነው ።

ስለዚህም ጉዳይ ከዚህ ቀደም በመጽሐፍ የቀረበ ነገር ባለመኖሩ ፤ ማንኛውንም ዝርዝር ነገር ለማስረዳት ችግር ሲፈጥር ቆይቷል ።

አሁንም ቢሆን የየአንዳንዱ ትምህርት መምህራን ወይም ልዩ ዐዋቂዎች

www.ethiopianorthodox.org

በመጠኑ ይገኛሉ ፤ ይሁን እንጅ ዕውቀቱ ሳያንሳቸው የአገላለጥ ችሎታ የሌላቸው ስለሆኑ ፤ በጥያቄው መሠረት ሊመልሱ አልቻሉም ።

ይኽም ሁናቴ ዐዋቂዎችን እንደዐላዋቂዎች ከማስገመቱም በላይ ፤ ጥበቡ እንደጠፋ ዐዋቂም እንደሌለበት አስገምቷል ።

በቅርብ በመገኘቴ ፤ እንዲሁም ቦታውን በመመልከት እንደሆነ አላውቅም ፤ ይኽን ጥያቄ በመያዝ ሁሉም ወደኔ ይመጣል ፤ እኔም በበኩሌ ተገቢውን መልስ ለመስጠት ማሰብና መዘጋጀትም ግድ ሆነብኝ ፤ በጥያቄው ጊዜ የምችለውን ብቻ በቀጥታ መልሼ ሌላውን ጥያቄ ወደሚመለከተው ሊቅ ሳስተላልፍ በጠያቂዎች ላይ የቅርታ መልክ ይታይባቸው እንደነበር ተረድቻለሁ ፤ ምክንያቱም በመልስ አሰጣጥ በኩል ሌሎች እንደማያጠግቡን ዐውቀን ስንመጣ እንደምን ወደሌላ ትመራናለህ በማለት ነው ።

በዚህም ምክንያት አንዳንዱን እኔ ራሴ የማውቀው ሲሆን ፤ ሌላውን ግን አስቀድሜ ከሌሎች ጠይቄ በመረዳት መልሱን አዘጋጅቼ ለማስቀመጥ ቁርጥ ሐሳብ አደረግሁና ይኽን ሁሉ ጽሑፍ ለመሰብሰብ ቻልሁኝ ፤ በዚህም መልክ በመሰብሰቡ የአሁኑን ቅጽ ይዞ መጽሐፍም ሁኖ ሊወጣ ቻለ ።

ይኽንም ጽሑፍ ለማሳተም ሕሊናዬ ሲነሣሣ ሙሉ ዝግጅት ያለው እንዲሆን ፤ ማስፈለጉን በመረዳት እንደገና ጥናቴን ለመቀጠል በልዩ ልዩ ቦታ ፤ ወደሚገኙ ሊቃውንት ጥያቄዬን በማቅረብ ብዙ ጊዜ አሳልፌአለሁ ።

አንዳንድ ሊቃውንት ጥያቄውን የተከተለ መልስ በመመለስ ፈንታ ለፈተና ያዘጋጀሁት እየመሰላቸው የጥላቻ መልክ ያሳዩኝ ይገኛሉ ፤ አንዳንዶች ግን በሰፊው ርዳታቸውን አበርክተውልኛል ፤ ምስጋናቸውንም በሚያስፈልገው ቦታ ስማቸውን በመጥራት አነሣቸዋለሁ ።

አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ፤ ይኽ ጥናት ከዚህ ቀደም ያልተደረሰበት መሆኑንና ለጥናቱም ሰፊ ጊዜ ሊሰጠው የሚያስፈልግ መሆኑን ከመናገራቸውና ከማነቃቃታቸው ይልቅ የግል ሐሳባቸውን በመስጠት የረዱኝ ብዙ ናቸው «ችግርን የቀመሳት ችግርን ያውቃታል» እንደተባለው የእንደዚህ ያለው ጥናት አስፈላጊ መሆኑን ያወቁ ሁሉ ሥራየን በሚገባ እንድቀጥል በየጊዜው ያተጋትኝ ነበር ፤ እኔም ራሴ ከዚህ ቀደም ላይላዩን አጥንቼው የነበረውን ጠለቅ ብዬ ለመመርመር ዕድል ሲገጥመኝ ፤ ወደሥነ ጽሑፍ ስገባ ደግሞ እንደገና ተማሪ ቤት እንደገባሁ ቆጥሬዋለሁ ።

ይኽም ጽሑፍ እንደዚህ ከመረሳትና ከመጠየቅ እስኪደርስ ለትውልድ እንዲተላለፍ ሕይወታቸውን መሥዋዕት በማድረግ ያስተማሩ መምህራን ብዙዎች ከመሆናቸው የተነሣ ውኃ ቀጂው እንጨት ሰባሪው በቀላሉ ሊረዳው ይቻለው ነበር ።

እኔም ችግሩን ሁሉ ባለመመልከት መምህራኑ ፈጽመው ሳይጠፉ ዛሬ ጥያቄው መልስ ያላገኘ መቼ ሊያገኝ ነው በማለት ባለመሰልቸት ጥያቄዬንና

www.ethiopianorthodox.org

ምርምሬን በበለጠ ትጋት ለመቀጠል ተገደድኩኝ ፤ ምንም ከዚህ ቀደም ለመጻፍ የጀመርኳቸው ልዩ ልዩ ጥናቶች ቢኖሩኝ ለዚህኛው ቅድሚያ መስጠት ተገቢ መሆኑን በመረዳት እንደዚህ ያለ መልካም ፍጻሜን ለማስገኘት ረድቶኛል ።

የሊቃውንቶቻችን ዕውቀታቸው ወደብርሃን እንዲወጣ ስማቸውም በአዲሱ ትውልድ ዘንድ እንዲታወቅ ለማድረግ ስጽፍ የዚህንም ጽሑፍ መታሰቢያነት ለነርሱ ሰጥቼአለሁ ።

ይኸንንም ለማድረግ ያነሣሣኝ ሊቃውንቶቻችን ብሔራዊ ስሜት የነበራቸው በዕውቀት ባሕር የጠለቁ ሁሉንም መርምረው ያወቁ ስለነበሩ ፤ መታሰቢያቸው ዘለዓለማዊ እንዲሆን በማመን ነው ።

ሊቃውንቶቻችን ችግራቸውን ሳያስቡ ከመሥራታቸው የተነሣ ኢትዮጵያን ከአፍሪካ ለይተው የዕውቀት ደሴት ፤ የቅኔ አደባባይ ፤ የዜማ መዲና ፤ የንግግር ስልት መገኛ አድርገዋታል ።

ምንም ዛሬ ከኛ በሥጋ ቢለዩ በዓፀደ ነፍስ ሕያዋን ሁነው የሚገኙ ስለሆነ ሁላችንም ልናስባቸው ይገባናል ። እንዲሁም ጥንታዊ ጥበባችን ምን ዓይነት እንደሆነ ክፍል በክፍል ለመረዳት እንችል ዘንድ በዚህ መልክ አቀርባለሁ ።

የጥናቴም መነሻ ያደረግሁት የትምህርቱን አሰጣጥ ደረጃ በመከተል ቅደም ተከተሉንም በመጠበቅ ከፊደል ወደከፍተኛ ክፍለ ትምህርት በመሔድ ሲሆን ክፍሉንም ፤ በ፲፰ ክፍል ከፍየዋለሁ ። ስለዚህም ጥንታዊ ሥርዓተ ትምህርታችንን ዘርዝሬ ሳቀርብ አንባብያን ሁሉ ዋና ሐሳቡን ተረድተው የጥንት ባህላችን ደጋፊዎች ይሆኑ ዘንድ አሳስባለሁ ።

ይኸንም ጥናት በመጠኑ አጥንቼ ሳቀርብ ፍጹም ነው በማለት ሳይሆን ለወደፊት ጥናት መነሻ ይሆናል በማለት ነው ።

ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያም ወርቅነህ ።

# መግቢያ ።

ጥንታዊ የኢትዮጵያ ትምህርት በማለት መግለጫ የሰጠሁት ይኸ ጽሑፍ የጥንቱን ሁኔታ በታሪክ መልክ የሚገልጥ ሲሆን ለወደፊቱ ደግሞ ለጥናት መግቢያ በርን የሚከፍትና አሁንም ቢሆን እንዴት ልናጠናው እንደምንችል አቅዱን የሚያሳይ መጽሐፍ ነው ።

ምክንያቱም እየአንዳንዱ የትምህርታችን ዓይነት ጥንታዊ መልኩ ምን እንደነበር እንዴት ያስተምሩት እንደነበር ከተረዳን አሁን ካለው የትምህርት ይዞታችን ጋር በማነፃጸር ልንጠቀምበት እንችላለን ። በዚህም ሁኔታ ታላቅነታችን፤ ጥንታዊነታችን ፤ እንዴትስ ያለ የትምህርት አሰጣጥ እንደነበረን ልንረዳና የተሻለውን መንገድ በመያዝ ወደፊት ልንጠቀምበት እንችላለን ።

እውነት ነው በዚህ አርእስት ከገለጥኳቸው የትምህርት ዓይነት ውስጥ ይበልጠው ነበር በማለት ፤ የሚተርክለት እንጅ ፤ ነው ፤ በማለት የሚሰጠው አስረጅ በመጠኑ ነው ።

የቀረው ቀርቶ አሁን እንኳን በቅርቡ ለጠያቂ መልስ ፤ የማይገኝለት መሆኑ የታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጅ በታሪካዊ መንገድ ለመጠቀም ከፈለግን በነበር መልክም ቢሆን ልናጠናው ይገባናል ።

ይኸንም ጽሑፍ ሳዘጋጅ ጥንታዊ ትምህርታችን ምን ዓይነት እንደነበር ፤ በእንዴት ያለ መንገድ ይማሩት ያስተምሩት እንደነበር ፤ ለማስረዳት ስፈልግ በትምህርቱ ጥንታዊ መልክና በመሰል ሁኔታው ስለከፈልኩት ፤ ራሱን የቻለው ብቻ ፲፰ ክፍል ሆኖ ይገኛል ።

እያንዳንዱ የትምህርት ክፍል የተለየና ብዙ መልክ ስላለው ከፍ ያለ ጥናትን የሚጠይቅና ፩ኛው ብቻ እንኳን በሚገባ ቢሠራ ይኸን ያህል መጽሐፍ የሚወጣው መሆኑ የተመሰከረለት እውነት ነው ፤ ይሁን እንጅ ፤ ፩ኛውን ክፍል ከፍ ፤ ሌላውን ደግሞ ዝቅ በማድረግ ሁሉንም በአስተዋጽኦ በመጥቀስ በዚህ አነስተኛ መጽሐፍ አጠቃልዬ አውጥቼዋለሁ ።

በያንዳንዱ ሞያ ችሎታ ያላቸው ሊቃውንት ለዚያው ለያዙት ሞያ ዋጋ ሰጥተው ቢጽፉት ፤ አሁንም ከፍ ያለና የተጠናቀቀ ውጤትን እንደሚያቀርቡልን የታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጅ በዚህ በሀገራችን ሞያ የሠለጠኑ አባቶች በቊጥር ብዙዎች ሲሆኑ እነርሱም የቃል ጥናት እንጅ በጽሑፍ የማቀናበር ልምድ ከጥንት ጀምሮ ስላልቆያቸው በልባቸው ያለውን በጽሑፍ ሊያሠፍሩት አልቻሉም ።

አሁን ግን ይኸን የመሰለውን ጽሑፍ በመመልከት ፤ ለካስ ይኸም አለ በማለት መንፈሳዊ ቅንዓት አድሮባቸው ፤ በዚህም መንፈስ ተነሣሥተው አስፋፍተው እንዲጽፉ ፤ በር ለመክፈት ያህል ይኸን ጽሑፍ አበረክታለሁ ።

እንዲሁም የትምህርታችን ዘዴ ያልገባቸው ወገኖች በመንቀፍ ብቻ ስለሚ

www.ethiopianorthodox.org

ገኙ ፤ ጥንታዊ የትምህርት አሰጣጡ ሁኔታ በምን መልክ እንደነበር ለመገመትና ለመቀበል እንዲችሉ ነው ።

ማንኛውንም ነገር ለመውደድም ሆነ ለመጥላት ፤ ነገሩን አስቀድሞ ከሥሩ ከመሠረቱ ማወቅ ያስፈልጋል ፤ እንዲሁ መጥላት ፤ እንዲሁም መውደድ ተገቢ አይደለም ፤ ስለዚህ ጥንታዊ ሞያችን ምን ያህል ክብር አንድም ደረጃ እንደነበረው በዚህ መልክ ዐውቆ ሊወዱትና ሊያጠኑት ያስፈልጋል ፤ የሚርቁትና የሚጠሉት ቢኖሩም ከዚህ የተነሣ መሆን አለበት ፤ ደኅና አድርጎ ቀምሶ ጣዕሙንም ዐውቆ መቅረብም መራቅም የዐዋቂዎች ፈንታ ነው ።

ይኸንም የምንልበት ምክንያት የአሁኑ ወጣት እኛ ኢትዮጵያውያን ሁሉ አዲስ ትውልድ እንደሆን ፤ እንዴት እንደኖርን ያላወቀና ሥነ ሥርዓት የሌለን ፤ የትምህርትም ሥነ ሥርዓት አሁን የተጀመረ እየመሰላቸው ሞያችንን ንቀው አቅለው የሚመለከቱት ፥ እንዲሁ የሚያነቡት አንድም የሚረዱበት ባለመኖሩ እንደሆነ የተመሰከረለት እውነት ነው ።

በዚህ መልክና ይኸን በመሰለ መንገድ ቢዘጋጅ ግን የኛው ትውልድ ቀርቶ ሌላው ነገድ እንደሚያጠናው የተረጋገጠ ነው ።

ስለዚህ ሁላችንን ወደጥናት የምትመራ ይኸችን ጽሑፍ ለተመራማሪዎችና ለደቀ መዛሙርት ሳበረክት በዚህ መነሻነት ሌላውንም ጠለቅ ብለን እንድንመራመር በማስገንዘብ ነው ።

ደ ራ ሲ ው

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፩ ።

# ፊደል ከነጓዙ

## ምዕራፍ ፩ ።

# የፊደል ትምህርት ።

## ፩ኛ የፊደል የትመጣ ።

ስለፊደላችን የትመጣና ብሂል በየጊዜው ብዙ ሐተታ ይሰጥበታል ፣ ይኸውም ፊደል ማለት ጽሑፍ ማለት ነው ፣ ብለው «ፈደለ» ጻፈ ካለው ከግዕዝ ቋንቋ የሚያወጡ አሉ ።

እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት የሆነ እንደሆነ ደግሞ የፊደል ስልት አንድም አቅድ ተጀመረ የሚባለው በሄኖስ ዘመን ነው ። ነቢዩ እግዚአብሔርን በማገልገል የታወቀ ደግ ስለነበር ፣ ለደግነቱ መታወቂያ ይሆነው ዘንድ በቅዱስ እግዚአብሔር ፈቃድ የሕግ መሣሪያ የሚሆነው ፊደል በጸፍጸፈ ሰማይ ተገልጦ ታይቶታል ፤ ስለዚህ ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ፊደልን ለሥነ ጽሑፍ በር መክፈቻ በማድረግ ተጠቅሞበታል ፣ ስሙንም ጽሑፍ ለማለት ፊደል ብሎታል ። ይኸስ እውነቱ ምን ያህል ያገለግላል ?

በዚያን ጊዜም በጸፍጸፈ ሰማይ ታየ የሚባለው ፊደል የእብራይስጡ ፊደል እኛ አሁን አሌፋት እያልን የምንጠራው ነው ።

ስለዚህም ይኸ ፊደል ከፊደልነት ጥቅሙ ጋር እንደ ኀቡዕ ስም ይገመታል ፤ ይኸም ታሪክ ይኸም የስም አጠራር ቅሉ በኛ ቋንቋ እንጅ በሌሎች አይደለም ፤ ስለዚህ እኛ የሥነ ጽሑፋችን በር መክፈቻ የአሌፋቶችን ስም ፊደል ብለነዋል ።

እንዲሁም ከዚያን ጊዜ አያይዞ ማንኛውም ነገር መጻፍ ፤ ለመጪውም ትውልድ መተላለፍ ስለነበረበት ራሱ ፊደሉ የሥነ ጽሑፍ መጀመሪያ ስለሆነ ጽሑፍ ለማለት ፊደል ተብሏል ።

አንዳንድ ሊቃውንት ግን ፊደል ማለት ፍጡር አንድም መፍጠሪያ ማለት ነው ብለው ይናገራሉ ፤ ቃሉም የወጣው ፈደለ (አጥብቆ) ፈጠረ ብለው ነው፤ ይኸንም ከግዕዝ ቋንቋ እንደወጣ አድርገው ይናገራሉ ። ለአስረጅም ያህል ዛሬ በአማረኛችን አንድ ሰው ባልሠራው ነገር ሲከሰስ ሲወቀስ እንዲያው ነገሩን ፈድሎብኝ ነው እንጂ እኔ ሠርቼው አይደለም ይላል ፤ ትርጉሙም እንዲያው ጥፎብኝ አንድም ለጥፎብኝ ነው እንጅ እኔ ሠርቼው አይደለም እንደማለት ነው ። ይሁን እንጅ የሁለቱም ቃላት ትርጉማቸው አንድ ዓይነት ነው ፤ ምክንያቱም ለክፋም ሆነ ለደግ ነገር መፍጠሪያው መጣፊያው ፊደል ስለሆነ ፤ ጻፈብኝ ፤ ለጠፈብኝ ፤ ፈጠረብኝ ፤ ብሎ ይናገራልና ።



www.ethiopianorthodox.org

በደኅናውም ነገር ቢሆን ካለፊደል ሊነገር ስለማይቻል ጸፈብኝ በማለት ፈንታ ጸፈልኝ ሊል ይቻላል ፤ ማለት ለክፉ ብቻ ሳይሆን ለደግም ነገር ሊሆን ይችላል ።

ስለዚህም አባቶች ሲመስሉ ፤ «ዘእንበለ ፊደል ኢይትነገር ወንጌል» ይላሉ ፤ ማለት ወንጌል ሳይቀር የምትጻፈው የምትተረጐመው በፊደል አማካይነት ነው ። ከዚህ ሌላ ስለ ፊደል የሚሰጠውን ሐተታ በመጠኑ እንደሚከተለው እንገልጣለን።

፩— ፊደል ማለት መጽሔተ አእምሮ ማለት ነው ፤
ምክንያቱም ያለ ፊደል ምንም አይታወቅምና ፤
የአእምሮ መገመቻ የምሥጢር መመልከቻ ማለት ነው ።

፪— ፊደል ማለት ነቅዓ ጥበብ ማለት ነው ፤ ምክንያቱም የጥበብ ሁሉ ምንጭ መገኛ ፊደል ናትና ፤

፫— ፊደል ማለት መራሒ ዕውር ማለት ነው ፤ ምክንያቱም የሰውን ልጅ ሁሉ ከድንቁርና አውጥቶ ወደብርሃን ይመራልና ።

፬— ፊደል ማለት ጸያሒ ፍኖት ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ድንቁርናን ጠርጎ አጽድቶ ከፍጹም ዕውቀት ያደርሳልና ፤

፭— ፊደል ማለት ርእሰ መጻሕፍት ማለት ነው ፤ ምክንያቱም የመጻሕፍት ሁሉ ራስ እናት ፊደል ናትና ።

ያለ ፊደል ማንኛውም መጽሐፍ ሊነገር አይቻልም ፤ «ኢተወልደ መጽሐፍ ዘእንበሌሁ ለፊደል» ይላልና ። ሌላም ይኸን የመሰለ ልዩ ልዩ ሐተታ ይሰጣል ፤ ይሁን እንጅ በሌሎች ቋንቋዎች ሁሉ ፊደል የሚጠራው በዚያው በፊደሉ መጀ መሪያ ነው ፤ ለምሳሌ ፊደሉ ኤ ቢ ሲ ዲ ፤ አንድም አሌፍ ቤት ፤ አንድም ፤ አልፋ ቤታ ያለ እንደሆነ ስሙም በየቋንቋው ሁሉ እንዲሁ ነው ግን በኛ ቋንቋ ፊደሉ ሲጀመር ሀ ለ ሐ መ ፤ በማለት ሲሆን ስሙም እንደዚያው ሀ ለ ሐ መ በመሆን ፈንታ ፊደል ይባላል ።

የግዕዝ ቋንቋ ከሴማውያን ቋንቋዎች ሁሉ ፩ኛው ያውም ጥንታዊው ስለ ሆነ ጥሩ የሆነ ቃል ከነፍቹ ይዞልን ይገኛል ፤ ስለዚህም በእርግጥም ፊደል የሥነ ጽሑፍ ሁሉ እናት አንድም መገኛ መፍጠሪያ ስለሆነ ራሱን ጽሑፍ በማለት ፊደል ብለውታል ።

ሆኖም ጽሑፍ የማለትን ትርጒም ይያዝ እንጅ ፊደል እያልን በጠራን ቍጥር ራሱን ፊደሉን ብቻ መጥራታችን እንደሆነ ያለ ትርጒም የታወቀ ነው ።

## ፪ኛ የፊደል ቍጥር ።

ከሴማውያን ቋንቋዎች እንዲሁም ከአውሮፓውያን ፊደሎች ይልቅ ፤ የኛ ፊደ ሎች ብዙ ቍጥር የተለየም ድምፅ እንዳላቸው አድርገው የሚናገሩ ወይም የሚገ ምቱ ብዙ ናቸው ፤ እንዲያውም የሚገምቱ ብቻ ሳይሆኑ የሚጽፉ ብዙ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም የፊደሉን ቍጥር ፤ ፪፻፴፩ አድርገው ይጽፉሉ ፤ በአንድ በኩል ደግሞ እንደጀማሪ ሁነው ሲመለከቱት አሁንም በእውነት ፊደላችን የበዛ ይኸንም ያህል ቍጥር ያለው ያስመስላል ፤ ምክንያቱም ከሀ — ፐ ያለውን የግዕዙንም የአማርኛውንም ፊደል በቍጥር ፴፫ የሆነውን በ፯ ድምፅ ሰጪ ሲያበዙት ፪፻፴፩ (ሁለት መቶ ሠላሳ አንድ) ቍጥር ይመጣል ።

ነገር ግን በልከኛው አቈጣጠር የመጣን እንደሆነ አንድም እንደ ነርሱ መንገድ የሔድን እንደሆን ፊደላችን ፳፮ ቍጥር ብቻ ያለው ሆኖ ይገኛል ፤ ይኸውም እርግጠኛ የሆነውን የግዕዝ ፊደላችን ብቻ የቈጠርን እንደሆን ነው ። ይኸን ደግሞ በ፯ ያበዙት እንደሆነ ፻፹፪ ይሆናል ፤ ሌሎችን የግዕዙን ዲቃሎች ፳ ጊዜ ፩ = ፳ ይሆናል ፤ ከ፻፹፪ ፡ ላይ ፳ ፤ የደመሩ እንደሆነ ፪፻፪ ይሆናል ( ሁለት መቶ ሁለት ) ።

ነገር ግን ይኸ ሁሉ ድምፅ ሰጪ ይባላል እንጂ ፊደል አይባልም ፤ ተማሪው ፊደሉን ብቻ ያለ ድምፅ ሰጪ ሀ ለ ሐ መ ፤ እያለ ሊያጠናው ይችላል ፤ ነገር ግን በኋላ እንደ ሌሎቹ ቋንቋዎች በንባብ ጊዜ እንዳይቸገር በማለት ድምፅ ሰጪዎቹን አብሮ በፊደል መልክ ፤ አንድም ከፊደሉ ጋር ሊማራቸው ግድ ይሆናል ።

ይኸም ቢሆን የግዕዝን ፊደል ብቻ የያዘ እንደሆነ ነው እንጂ በየጊዜው የተጨመሩትን የዓረብኛ ፤ አንድም የአማርኛ ፊደሎች የተባሉትን ፤ አንድም የነርሱን ዲቃላዎች ሁሉ አይዝም ።

የግዕዝ ፊደል የሚባለው ጥንታውያን መጻሕፍቶቻችን ሁሉ የተጻፉበት ብዙ ድርሰቶች የተደረሱበት ፊደል ነው ።

አንዳንድ የውጭ ሊቃውንት ይኸንኑ ፊደል ብቻ ጽፈው የግዕዝ አንድም የኢትዮጵያ ፊደል ይሉታል ፤ ፪ኛውን ግን የዓረብኛ አንድም የአማርኛ ፊደል በማለት ስም ይሰጡታል ።

ይኸም ሲሆን ፊደላችን በሁለት ክፍል ይከፈላል ማለት ነው ፤ ፩ኛው የኢትዮጵያ አንድም የግዕዝ ፊደል የተባለው ሲሆን እርሱም የሚከተለው ዓይነት ነው ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | ሁ | ሂ | ሃ | ሄ | ህ | ሆ |
| ለ | ሉ | ሊ | ላ | ሌ | ል | ሎ |
| ሐ | ሑ | ሒ | ሓ | ሔ | ሕ | ሖ |
| መ | ሙ | ሚ | ማ | ሜ | ም | ሞ |
| ሠ | ሡ | ሢ | ሣ | ሤ | ሥ | ሦ |
| ረ | ሩ | ሪ | ራ | ሬ | ር | ሮ |
| ሰ | ሱ | ሲ | ሳ | ሴ | ስ | ሶ |
| ቀ | ቁ | ቂ | ቃ | ቄ | ቅ | ቆ |
| በ | ቡ | ቢ | ባ | ቤ | ብ | ቦ |
| ተ | ቱ | ቲ | ታ | ቴ | ት | ቶ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ኀ | ኁ | ኂ | ኃ | ኄ | ኅ | ኆ |
| ነ | ኑ | ኒ | ና | ኔ | ን | ኖ |
| አ | ኡ | ኢ | ኣ | ኤ | እ | ኦ |
| ከ | ኩ | ኪ | ካ | ኬ | ክ | ኮ |
| ወ | ዉ | ዊ | ዋ | ዌ | ው | ዎ |
| ዐ | ዑ | ዒ | ዓ | ዔ | ዕ | ዖ |
| ዘ | ዙ | ዚ | ዛ | ዜ | ዝ | ዞ |
| የ | ዩ | ዪ | ያ | ዬ | ይ | ዮ |
| ደ | ዱ | ዲ | ዳ | ዴ | ድ | ዶ |
| ገ | ጉ | ጊ | ጋ | ጌ | ግ | ጎ |
| ጠ | ጡ | ጢ | ጣ | ጤ | ጥ | ጦ |
| ጰ | ጱ | ጲ | ጳ | ጴ | ጵ | ጶ |
| ጸ | ጹ | ጺ | ጻ | ጼ | ጽ | ጾ |
| ፀ | ፁ | ፂ | ፃ | ፄ | ፅ | ፆ |
| ፈ | ፉ | ፊ | ፋ | ፌ | ፍ | ፎ |
| ፐ | ፑ | ፒ | ፓ | ፔ | ፕ | ፖ |

የኢትዮጵያ አንድም የግዕዝ ፊደል የተባለበት ምክንያት ከነዚህ ውጭ የሆነ የአማርኛ አንድም ፤ የዓረብኛ ፊደል አንድስ እንኳን በግዕዝ ቋንቋ በግዕዝም ሥነ ጽሑፍ ውስጥ ገብቶ የማይገኝ ነው ። ከጥንት ጀምሮ እስከ ፲፪ኛው መቶ ዘመን በዚህ መልክ በነዚህም ፊደሎች ብቻ ሲሠራ ቆይቷል ፤ እየዋለ እያደረ ግን የአማርኛ ቋንቋ ሲነግሥ የአማርኛም ፊደል ሊፈጠር ቻለ ። የሆነው ሁኖ ከነዚህ ብዙዎች ፊደሎች ውስጥ ድምፃቸው ሴማውያን ከተባሉት በተለይም በዓረብ ስለሚገኙ ዓረቢ ወይም ዓረብኛ የሚል ስም ተሰጥቷቸው ይገኛሉ ፤ ይሁን እንጅ ወደ አማርኛችን ቋንቋ መቼ እንደገቡ እንዴትም እንደገቡ ሳይታወቁ ይኖራሉ ፤ ዛሬ ግን የኢትዮጵያ ፊደሎች ሥር በቀል መስለው ጥንታዊ መልክን ይዘው ይገኛሉ ፤ ወጣቶችም እንደ ኢትዮጵያ ፊደል አድርገው ይማሯቸዋል ።

## የግዕዝ ፊደል ዲቃሎች ።

ከላይ ከቈጠርናቸው ፊደሎች የተለዩ አንድም የተደቀሉ ፊደሎች አንድም ብትን ፊደሎች የተባሉ አሉ ፤ እነርሱም ከዚሁ ከናቱ ፊደል ስለተወለዱና ግዕዝነት ስላላቸው የግዕዝ ፊደል ይባላሉ ፤ ነገር ግን በደንበኛው መንገድ ስለማይሔዱ ደግሞ ዲቃሎች ይባላሉ ፤ እየራስም በግዕዙ ሥነ ጽሑፎች በብዛት የሚገቡ ሲሆኑ በአማርኛ ግን አብዛኞቹ ጨርሶ የማያስፈልጉ ሁነው ተገኝተዋል ፤ ለመኪና ጽሑፍም በማስቸገራቸው ብዙዎቹ ከቦታቸው ወጥተው ይገኛሉ ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

| ግዕዝ | ሣድስ ፤ | ሣልስ ፤ | ራብዕ ፤ | ሐምስ ፤ |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኩ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጉ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቍ | ቁ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኍ | ኍ | ኋ | ኌ |

## ፫ኛ የፊደል መለወጥ ።

የኛ ፊደል ምን ጊዜም ቢሆን ጥንትነቱን ሳይለቅ ከሌላም ፊደል ሳይዋስ ጥቂት በጥቂት ለውጥ እያደረገ የመጣ ነው ፤ ምናልባት በግሪክ የሥልጣኔ ዘመን ኢትዮጵያ ከፍ ያለ ግንኙነት ስለነበራት ፤ በዚያን ጊዜም የኛ ፊደል ስለተሻሻለ ከግሪክ የመጣ ነው ይባላል ፤ ምናልባት ከቀኝ ወደግራ ማንበቡ ሌላም ይኸን የመሰለ ለውጥ በዚያን ጊዜ ተደርጎ እንደሆን እንጂ የግሪክኛው ፊደል ከኛ ጋር ምንም ግንኙነት የለውም ፤ ሆኖም ይነሱ እንጅ አንዳንድ ፊደሎች ከግሪክ መጡ ለማለት ይቻል ይሆናል ፤

ለምሳሌ Λ በኛ ለ θ በኛ ፀ የተባለው ፊደል ሲሆን ፤ ድምፁም መልኩም ከግሪክኛው ጋር ይመሳሰላል ፤ ይሁን እንጅ ከጥንት ከሳቢያቲክ የመጣ እንደ ሆነ የታወቀ ነው ። ሌላ ግን መልኩ መስሎ ድምፁ ልዩ የሆነ ϙ በነርሱ ፈ የሚሉት በኛ ግን ቀ የሚባለው ፊደል ነው ። ከሁሉም ይልቅ እንዳለ ግሪክኛው የገባ በአኃዛችን አጻጻፍ ብቻ ነው ፤ ለምሳሌ ፤

ግሪክ ፤ ግዕዝ ፤ ግሪክ ፤ ግዕዝ ፤



አኃዛችን በኛም በጥንት ጽሑፉችን ዕዝልና ቅጥል ሳይኖርበት በዚህ መልክ ይጻፍበት እንደነበር የጥንት መጽሐፎቻችን ይመሰክራሉ ፤ አሁን ግን ዕዝልና ቅጥል ስላደረግንበት የኛ የግላችን አኃዝ አስመስለን ይዘነዋል ፤ ለምሳሌ ፩፡ ፪፡ ፫፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ሲል ዕዝል ስላለበት ብቻ ከግሪክኛው ልዩ ይመስላል ።

ከጥንት ፊደላችን ላይ በአጣጣል ቅጥሉንም ለመለዋወጥ በየጊዜው እስካሁንም ድረስ ቢሆን መሻሻሉ አልቀረም ፤ የየጊዜውም ለውጥ በፊደሉ ሁሉ ይገኛል፤ የጥ

www.ethiopianorthodox.org

ንቱንና የመካከለኛውን ዘመን ጽሑፍ ሲመለከቱት ብዙ ልዩነት ይገኝበታል ፤ የሁሉም እንኳን ቢቀር የአንዱን ፊደል ለውጥ ለምሳሌ እገልጣለሁ ፤ ሰ የአሁኑ አጻጻፍ ሲሆን ፤ ሰ የጥንቱ አጻጻፍ ፤ ሰ በጣም ቀደም ያለ አጻጻፍ ነው። ለምሳሌ ያህል በለ ብቻ ፊደል ገለጥን እንጅ በያንዳንዱ ፊደል ላይ በዚህ መልክ ብዙ ለውጥ መደረጉን መጻሕፍትን አገናኝተው ሲያነጋግሯቸው ይመሰክራሉ ።

ሆኖም የቀረው የኛ ፊደል ከውጭ ፊደል ተወሰደ ከሚለው ይልቅ ከኛ ፊደል ላይ ሌሎች እንደወሰዱ አንድም በኛ ፊደሎች መልክ አሻሻሉ ተብሎ ይነገራል ፤ ለምሳሌ የአርመን ፊደሎች በ፭ኛው መቶ ዘመን ከግዕዝ የተወሰዱ መሆናቸውን የሌኒን ግራድ ዩኒቨረስቲ ፕሮፌሰር ድሚትሪ አሌክሲቪች አልዶሮገ የተባለው ሊቅ ሰፋ አድርጎ ገልጧል ። ከአርመን ፊደል ውስጥ በድምፅ የሚመስሉ እንኳን ባይኖሩ በመልክ የሚመሳሰሉ ብዙ ፊደሎች ይገኛሉ ።

## ፬ኛ የአማርኛ ፊደል ።

የአማርኛ አንድም የዓረብኛ ፊደል የሚባሉ ከግዕዝ የተለዩ ፊደሎች ናቸው ፤ እንዚህም የአማርኛ ፊደሎች የተባሉበት ምክንያት በግዕዝ መጻሕፍት የማይገኙና በጥንታዊ አነጋገርም የማይገቡ ስለነበርና በኋላ ዘመን የገቡ ስለሆነ ነው ።

አሁንም ቢሆን በጥንት ፊደል ሲያስተምሩ እነዚህን አይጨምሩም ፤ ይሁን እንጅ በአማርኛ ሥነ ጽሑፍ በጣም ስላስፈለጉ ወጣቶች ማጥናት ግድ ይሆንባቸዋል ።

እነርሱም ድምፅ ሰጪአቸው ሳይጨመር በቍጥር ፯ ናቸው ፤ ነገር ግን እንደሌላው ግዕዝ ፊደል ድምፅ ሰጪ አላቸው ።

እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ሸ | ሹ | ሺ | ሻ | ሼ | ሽ | ሾ |
| ቸ | ቹ | ቺ | ቻ | ቼ | ች | ቾ |
| ኘ | ኙ | ኚ | ኛ | ኜ | ኝ | ኞ |
| ኸ | ኹ | ኺ | ኻ | ኼ | ኽ | ኾ |
| ዠ | ዡ | ዢ | ዣ | ዤ | ዥ | ዦ |
| ጀ | ጁ | ጂ | ጃ | ጄ | ጅ | ጆ |
| ጨ | ጩ | ጪ | ጫ | ጬ | ጭ | ጮ |

ከነዚህ ሌላ በየጊዜው የተፈጠሩ ልዩ ልዩ ድምፅን የሚሰጡ አማርኛችን አንድም ጊዜያችን የፈጠራቸው ፊደሎች ይገኛሉ ፤ ግን ሙሉ ፊደል ሙሉም ድምፅ አንድም ስም የሌላቸው ቈናጽል ፊደሎች ሆነው ይገኛሉ ። አባቶች ከጊዜ ወደጊዜ በማሳጠር የሚጠቀሙበት ለመሻሻል ተብሎ የተደረገም ዘዴ ሳይ

www.ethiopianorthodox.org

ሆን አይቀርም ። ስለዚህ አልፈው አልፈው የሚገቡ ፊደሎች ይገኛሉ ፤ እነር ሱም የሚከተሉት ናቸው ።

## የአማርኛ ፊደል ዲቃሎች ።

አማርኛ ራሱን የቻለ ቋንቋ ሲሆን ፤ በዘመን ብዛት በድምፅ መስጠት ታስ ቦም ሳይታሰብም የገቡ ፊደሎች አሉ ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

ሏ ሟ ሯ ሷ ቧ ቷ ኗ ዟ ዷ ጧ
ጿ ኧ ጯ ዧ ጇ ቿ ኟ ፏ

እነርሱም በዐረፍተ ነገር ሲገቡ እንደሚከተለው ይሆናሉ ።

ልቧ ፥ ሆዷ ፥ ጧፍ ፥ ባሏ ፥ ሟች ፥ ዓይኗ ፥ ፏፏቴ ፥ ኧረ ፥ እጇ ፥ እግሯ ፥ ርሷ ፥ አባቷ እንዲህ እያለ የሚሄድ ሲሆን እነዚህ ፊደሎች በዐረፍተ ነገርም ሊገቡ የሚችሉት በሩቅ ሴት በዝርዝር ሲነገር ነው ።

እንዲሁም በተውላጠ ስም በቆሳቁስ ስም በመግባት ሊነገሩ ይቻላል ። ነገር ግን የዚህ ዐረፍተ ነገር አገባብ በጣም ያልተለመደ በብዙዎች ዘንድ እንግዳ የሆነ ነገር ነው።

ከላይ እንደገለጥነው በቅልጥፍና አንድም ለማሳጠር ተብሎ የገባ ይመስ ላል ፤ ምክንያቱም ልብዋ በማለት ፈንታ ልቧ ፤ ባልዋ በማለት ፈንታ ባሏ ለማ ለት ለማሳጠር የገባ ነው ።

በአሁኑ ጊዜ ግን ምንም ዝርዝር ፊደል ባይኖራቸው የቈጠርናቸውና ሌሎ ችም እነርሱንም የመሰሉ ሁሉ በየመጽሐፉ ይገባሉ ፤ በአዋጅም ከፊደል ጋር እየ ታተሙ መቅረብ ጀምረዋል ።

## ፫ኛ የፊደሎች ድምፅ ።

ፊደሎቻችን ቊጥራቸው ብዙ ፤ ቅርጻቸውም ልዩ ልዩ ነው ፤ እነዚህም ፊደላት ለብዙ ዘመናት ያህል እንደ መልካቸው እንደ ድምፃቸው አኳኋን ሲሠራባቸው እንደቆየ ፤ ሴማዊውንም ጠባይ ጠብቀው እንደኖሩ ታሪክ በሰፊው ይነግረናል ፤ እየዋለ እያደረ ግን መልኩ ብዙ አይለውጥ እንጅ ድምፁ እንደጥንቱ የተጠበቀ አይመስልም ፤

ምክንያቱም መልካቸው የተለያዩ ፊደሎች መኖራቸው ሲታወቅ ድምፃቸው አንድ ዓይነት ሆኖ ይገኛልና ፤ በሌሎች ሴማውያን በሆኑ ቋንቋዎች ግን ተመሳሳይ ድምፅ ያላቸው ፊደሎች ለጊዜው መሰል ድምፅ ያላቸው ይምሰሉ እንጅ በጉረሮ በት ናጋ በምላስ በመነገር ከፍ ያለ ልዩነት እንዳለው በሰዋስዋቸው ይገልጣሉ ።

በአሁኑ ጊዜ ያለው ፊደላችን ልዩ መልክ እንዲሁም ልዩ ልዩ ስም ይኑረው እንጅ በአነጋገር ደረጃ በልሳን በትናጋ ፤ በከንፈር ተከፍለው ሲረገጡ ይገኛሉ ። ብዙ ጊዜ እንደሚነገረው በመላ የግዕዝ ፊደላችን ፳፮ቱ ብቻ ናቸው ፤ እነዚህም ከላይ እንደገለጥነው በ፭ የድምፅ ደረጃ ይከፈላሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

፩ኛ/ በጉረሮ ብቻ የሚነገሩ ፊደሎች አሉ ፤ እነርሱም ፭ ናቸው ፤ ዝርዝራቸው
ሀ ፣ ሐ ፣ ኀ ፣ አ ፣ ዐ ።
፪ኛ/ በትናጋ ፣ ፬ ፣ ገ ፣ የ ፣ ከ ፣ ቀ ።
፫ኛ/ በምላስ ፭ ደ ፣ ለ ፣ ነ ፣ ጠ ፣ ተ ።
፬ኛ/ በከንፈር ፮ ፣ በ ፣ ወ ፣ መ ፣ ፈ ፣ ጰ ፣ ፐ ።
፭ኛ/ በጥርስ ፮ ፣ ዘ ፣ ሠ ፣ ሰ ፣ ጸ ፣ ፀ ፣ ረ ፣

ከዚህ ሌላ የአማርኛ ፊደሎች የሚባሉ ፯ ይገኛሉ ፤ እነርሱም መደበኛውን የግዕዝን ፊደል ድምፅ ተከትለው የሚሠሩ ስለሆኑ ሌላ ድምፅ አልሰጠነውም ።

የቀረው ቀርቶ ከግዕዙ እስከ ሳብዑ ያለው ሁሉ ትንሽ ለየት ያለ ድምፅ ያለው መስሎ ቢታይም ቅሉ መደቡን አይለቅም ።

በሌሎች ቋንቋዎች ዘንድ በትናጋ የሚነገሩ ፊደሎች የኛን የፊደል ድምፅ የመሰለ ክፍል አላቸው ፤ ይሁን እንጅ እንደ ቀ ያለው ድምፅ ያስቸግራቸዋል ፤ ማለት እንደ ከ የሚለውን ቀ እያሉ ያነቡታል ፤ እኛም ከ የሚለውን ቀ እያልን የተረጐምነው ብዙ ነገር አለ ።

## ፮ኛ የፊደል ትርጉም ።

ሀ— ግዕዙን በግዕዝ መተርጐም ፣ ፊደላችን ራሱን የቻለ ትርጉም አለው ፤ ግን ይኸን ዓይነት ትርጉም የሚማሩት በዚህ በፊደል ትምህርት ጊዜ ሳይሆን በግዕዙ ትምህርት ጊዜ ነው ።

በሴማውያን ቋንቋዎች ሁሉ እያንዳንዱ ፊደል ትርጉም አለው ፤ ለሕፃኑም አብረው ወዲያውኑ ትርጉሙን ከቅርጹ ጋር ያስተምራሉ ።

እንደ ግዕዙ ትምህርታችን የሆነ እንደሆነ ግን በግዕዙ ፊደል ብቻ ከዚህ የሚከተለው ትርጉም አለው ።

ሀ ፤ ብሂል ሀልዎቱ ለአብ እምቅድመ ዓለም ፤ የአብ አኗኗሩ ከዓለም በፊት ነው ።
ለ ፤ ብሂል ለብሰ ሥጋ እምድንግል ፤ ክርስቶስ ከድንግል ሥጋን ለበሰ ።
ሐ ፤ ብሂል ሐመ ወሞተ ፤ ታመመና ሞተ ።
መ ፤ ብሂል መንክር ግብሩ ለእግዚአብሔር ፤ የእግዚአብሔር ሥራው ድንቅ ነው ።
ሠ ፤ ብሂል ሠረቀ በሥጋ ፤ በሥጋ ተገለጠ ።
ረ ፤ ብሂል ረግዓት ምድር በቃሉ ፤ ምድር በቃሉ ረጋች ።
ሰ ፤ ብሂል ሰብአ ኮነ እግዚእነ ፤ ጌታችን ሰው ሆነ ።
ቀ ፤ ብሂል ቀዳሚሁ ቃል ፤ ቃል መጀመሪያ ነበር ።
በ ፤ ብሂል በትሕትናሁ ወረደ ፤ ጌታችን በትሕትናው ወደኛ ወረደ ።
ተ ፤ ብሂል ተሰብአ ወተሰገወ ፤ ጌታችን ሰው ሆነ ።
ኀ ፤ ብሂል ኃያል እግዚአብሔር ፤ እግዚአብሔር ኃያል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ነ ፤ ብሂል ነሥአ ደዌነ ወጾረ ሕማመነ ፤ ጌታችን ደዌያችንን ወሰደ ።
አ ፤ ብሂል አአኵቶ ወእሴብሖ ለእግዚአብሔር ፤ ጌታን ፈጽሜ አመሰግነዋለሁ ።
ከ ፤ ብሂል ከሃሊ እግዚአብሔር ፤ ጌታችን ቻይ ነው ።
ወ ፤ ብሂል ወረደ እምሰማይ ፤ ጌታ ከሰማይ ወረደ ።
ዐ ፤ ብሂል ዓርገ ሰማያተ ፤ ወደሰማይ ዐረገ ።
ዘ ፤ ብሂል ዘኵሎ ይእኅዝ እግዚአብሔር ፤ ጌታ ሁሉን የሚይዝ ።
የ ፤ ብሂል የማነ እግዚአብሔር ገብረት ኃይለ ፤ የጌታ ቀኝ እጅ ኃይልን አደረገች ።
ደ ፤ ብሂል ደመረ ሥጋነ ምስለ መለኮቱ፤ጌታ ሥጋችንን ከመለኮቱ ጋር አንድ አደረገ።
ገ ፤ ብሂል ገብረ ሰማያተ በጥበቡ ፤ ጌታ በጥበቡ ሰማዮችን ሠራ ።
ጠ ፤ ብሂል ጠዐሙ ወታእምሩ ፤ ከመ ኄር እግዚአብሔር ፤ ጌታ ቸር እንደሆነ ቅመሱና ዕወቁ ።
ጰ ፤ ብሂል ጰራቅሊጦስ መንፈሰ ጽድቅ፤ጰራቅሊጦስ እውነተኛ መንፈስ ቅዱስ ነው።
ጸ ፤ ብሂል ጸጋ ወክብር ተውህበ ለነ ፤ ጸጋና ክብር ተሰጠን ።
ፈ ፤ ብሂል ፈጠረ ሰማየ ወምድረ ፤ ጌታ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ።
ፐ ፤ ብሂል ፓፓኤል ስሙ ለአምላክ ፤ ፓፓኤል ማለት የአምላክ ስም ነው ።

## ለ| ፊደል በቊጥር መልክ ሆኖ ሲተረጐም ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ— | ማለት | ፩ኛ | አንድ |
| ለ— | ማለት | ፪ኛ | ሁለት |
| ሐ— | ማለት | ፫ኛ | ሦስት |
| መ— | ማለት | ፬ኛ | አራት |

እንደዚህም እያለ እስከ ፐ ይደርሳል ። እንደ ምዕራፍ ሁኖ የዐረፍተ ነገር መክፈያ ፤ የኃይለ ቃል መጀመሪያ ሁኖ ሲገኝም ፊደል ያለ ጥርጥር ቊጥርን ያመለክታል ፤ በቊጥርም መልክ ይተረጐማል ፤ ይኸም ዓይነት አቈጣጠር ጥንታዊ ይሁን እንጂ አሁንም እንደቀጠለ ነው ።

## ሐ· ፊደል በሌላ ቊጥር መልክ ሲተረጐም ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሀ— | ማለት | አንድ | ፩ኛ/ ይሆናል |
| ሁ— | » | ሁለት | ፪ኛ/ |
| ሂ— | » | ሦስት | ፫ኛ/ |
| ሃ— | » | አራት | ፬ኛ/ |
| ሄ— | » | አምስት | ፭ኛ/ |
| ህ— | » | ስድስት | ፮ኛ/ |
| ሆ— | » | ሰባት | ፯ኛ/ ማለት ይሆናል ። |

www.ethiopianorthodox.org

በዚህ መልክ እያንዳንዱ ፊደል ፤ እንዲሁ ሊሔድ ይችላል ፤ በዚህም መልክ ሊቈጠር ይችላል ፤ በዚህም መልክ ሊተረጐም ይችላል ።

በተለይም በ፪ቱ መልክ ለመተርጐም የሚያሻው በሐሳበ ፊደል በኩል የሔደ እንደሆነ ነው ፤ ሐሳበ ፊደሉን ለማወቅ የነዚህን የ፪ቱንም ትርጉም መንገድ ደኅና አድርጎ ለይቶ ማወቅ ሊያስፈልግ ነው ።

ስለዚህ ይኸን ዓይነት ጠንቅቆ ለማወቅ የተለየ ዕድል የተሰጣቸው ሰፊ አእምሮ ያላቸው ብቻ ነበሩ። በአሁኑ ጊዜ ግን ፫ቱን፤ ሀ፤ሐ፤ኀ በ፩ ቍጥር አናስገባም በማለት ሀ ለ መ እያሉ ይሄዳሉ ፤ ሌላውንም እንደ ሠ፤ ሰ፤ አ፤ ዐ፤ ያሉትንም እየዘለሉ የሚሄዱ አሉ ። ይኸም ልብ ወለድ መንገድ ከጥንታዊ ትምህርት ፤ አንድም የትርጓሜ ፤ አንድም ፤ የቍጥር ስልት የሚያፈናቅል መሆኑን በመላ የግዕዝ ሰዎች ሊያውቁት ይችላሉ ።

## ፫ኛ ጥንታዊ የፊደል ቅጽ ።

ይኸች ፊደል የምትባለው መጽሐፍ ከሌሎች ኢትዮጵያውያን መጻሕፍት ቅጽ የተለየች እንደ ጥንታውያን ነቢያት ጽሑፍ ነበረች ፤ በሌላው ሀገር መጻሕፍት ሁሉ በኛም እንዲሁ ይጻፍ እንደነበር ያስገምታል ፤ ማለት ፊደሏ የምትታጠፍና የምትዘረጋ ነበረች ፤ የፊደሏም ቁመት በግምት ፳፬ ሳንቲም ያህል ስትሆን ከታች ወደላይ የምትጠቀለልና ከላይ ወደታች የምትዘረጋ ነበረች ፤ ጽሕፈቱም ዝርዝር የሆነ ፤ በአንድ ፤ ባላ በሆነ በአነስተኛ እንጨት ተንጠልጥላ የምትያዝ በአስፈለገ ጊዜ የምትዘረጋ ነበረች ።

ቅጺም ለልጆች በሚመች አቅድ የተዘጋጀችና የተጻፈች ነበረች ። ሌላ የድግምት መጻሕፍት ግን ፤ በዚህ ዓይነት እስካሁን ይጻፍ ነበር ፤ ስለዚህም ይኸ ዓይነት አጻጻፍ ፊደል ይመስላል ይባላል ።

የፊደልም ዋጋ ቀለል ያለ ማንኛውም ሊያገኘው በሚችል አቅድ የተዘጋጀ ነበረ ፤ በክርታሱም ሆነ (አንድም) በእጁ ጽሕፈት ብዙ ዋጋ የማይከፈልበት ፤ እንዲሁ ደጋግ መምህራን ጽፈው ለተማሪዎች የሚሰጡት ስጦታ ነበር ፤ የማኅተም መኪና እስከመጣበት ፤ እስከኛ ዘመን ድረስ ፊደል በዚህ መልክ ሲሠራበት ቆይቷል።

## ፬ኛ የፊደል ሥርዓተ ትምህርት ።

ተማሪው ፊደሉን ከግዕዙ እስከ ሳብዑ ማለት ከሀ—ሆ ያለውን እያንዳንዱን ስም ከመልክ በመለየት ፊደልን ይቈጥራል ።

በዚህም መልክ ከሀ — ፐ ያለውን በዝርዝር ይቈጥራል ፤ ተማሪው ይኸን እየመላለሰ ከቈጠረ በኋላ የፊደሉን ቅርጽ ከድምፅ ጋር በሚገባ ሲለይ ግዕዙን ብቻ ለብቻ ከሁ — ፑ ወደታች በመውረድ ካዕቡንም እንዲሁ ፤ ከሆ — ፖ ፤ ሣልሱን

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁ ፤ በዚያው መልክ ሌላውንም እስከ ሳብዑ ድረስ የያንዳንዱን ድምፅ በመጠበቅ ያጠናል ፤ ይኸው ዓይነት ትምህርት የተለየ ዜማና የተለየ ድምፅ ያለው ነው ።

የትምህርቱም አቅድ የተለየ ስም አለው ፤ ይኸውም ቍጥር ይባላል ፤ ትርጉሙም የየፊደሉን ስም ከመልክ በመለየት መቍጠር ማለት ነው ። ተማሪውም ይኸን ዓይነት ትምህርት በሚገባ ሲጨርስ በሌላ ዜማ በሌላም ድምፅ ያንኑ ፊደል ከላይ በገለጥነው ዓይነት ይማረዋል ።

ነገሩ እንደመቍጠር ሲሆን ፤ ሁሉንም በየስሙ እየጠራ ሲናገር የትምህርቱ ስም ግን ግዕዝ ይባላል ፤ ትርጓሜውም ፩ኛ/ ማለት ነው ፤ ነገር ግን ቍጥር የተባለው ያልተቈጠረ ሆኖ ግዕዝ ፩ኛ/ የተባለ ይመስላል ፤ ሆኖም ግዕዝ ተባለና ፤ በግዕዝ ፊደል ይጀመር እንጅ ካዕቡንም ሣልሱንም እስከ ሳብዑ ድረስ በዚያው ግዕዝ በተባለው ድምፅ ይጨርሰዋል ።

ስለዚህ ስሙም በዚሁ ይጠራል ፤ በዚህም ሁኔታ ከላይ ወደታች ከታች ወደላይ ከቀኝ ወደግራ ፤ በመስቀልያ ዓይነት ተምሮ የፊደልን ስምና መልክ ይለያል።

## ምዕራፍ ፪ ።

# አቡጊዳ ።

## ፩ኛ የአቡጊዳ ትርጉም ።

አቡጊዳ ማለት የጥንታዊ ፊደላችን ስም የሚያመለክት ወይም የያዘ ነው ፤ ይኸውም አ ፤ በ ፤ ገ ፤ ደ ፤ የተባለበት በግዕዝ ድምፅና በግዕዝ ቅርፅ ብቻ የተዘጋጀ በዚህም መልክ የሚሄድና ፤ ይኸንም በመሰለ መልክ ሌላው ሁሉ ይሔድ ስለ ነበረ ነው ።

ይኸም ፊደል በግዕዝ ፊደል ብቻ በመሔድ ቋንቋው ሳይቀር ግዕዝ እንደተባለ ይነገራል ፤ ይኸም ጥንታዊ ፊደላችን ከሴማውያን ጋር ግንኙነት ያለው ብዙ የተሠራበት ብዙም ድርሰት የተደረሰበት ፊደል ነበር ፤ ለምሳሌ የሌሎች ሴማውያን ቋንቋዎች ፊደል ፤ አሌፍ ፤ ቤት ፤ ጋሜል ፥ እንደሚል የኛም እንዲህ እያለ ይሄዳል ፤ በዚህም መሠረት ስሙም አቡጊዳ ተብሏል ፤ ይኸ አቡጊዳ በግዕዝነቱ ብቻ እንደጥንቱ ሳይጠበቅ ስሙም ሳይጠራ የዛሬ ልጆች ፊደልን ከተማሩ በኋላ የሚማሩት አቡጊዳ እያሉ ስለሆነ ስሙም በዚያው ተጠርቷል ። በዚህ ፊደል አንድም በዚህ ዓይነት ትምህርት በሀገራችን መጠቀሙ ከክርስትና ዘመን አንሥቶ ተቋርጧል ይባላል ፤ ምክንያቱም በእርሱ እግር ሀ ለ ሐ መ እያለ የሚሔደው የዛሬው ዓይነት ፊደል አንድም መንገድ ስለገባበት ነው ፤ ይኸውም አክሱማዊ ለውጥ የተባለው የተደረገበት ነው ፤ አሁን ግን አቡጊዳ ከፊደሉ ጋር እየታተመ ስለሚወጣ እንደ ሁለተኛ መማሪያ ፤ የፊደል መለያ ሁኖ ይገኛል ። በአንዳንድ ጠቅ

www.ethiopianorthodox.org

ላይ ግዛቶች አሁንም ቢሆን ተማሪው ፊደል ከለየ ወደሌላ የመጽሐፍ ቊጥር በቀጥታ ያስገቡታል እንጂ ይኸን ደረጃ አይጠብቅም ፤ ምክንያቱም ፤ አቡጊዳ የሚባለው መጽሐፍ ስለማይገኝ ነው ። እንዲያውም አቡጊዳ የተባለው ትምህርቱ ብቻ ሳይሆን ስሙም ሳይቀር እንግዳ ሳይሆንባቸው የማይቀሩ አሉ ፤ አሁን ግን ከፊደሉ ጋር አብሮ ስለሚታተም ሁሉም በቀላሉ ሊያውቀው ችሏል ።

አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ አቡጊዳ ጥንታዊ የፊደል መንገድ ሳይሆን የአዲሱ ፊደል የማስተማሪያ ዘዴ ሆኖ ለዚሁ አሁን ለአልነው ፊደል ማስተማሪያ ሁኖ እንደወጣ ይናገራሉ ፤ በክርስትናም ጊዜ ተለወጠ የሚባለው ከሳቢያቲክ የፊደል ዓይነት ወደዛሬው ፊደል እንጂ ከአቡጊዳ ወደአሁኑ ፊደል አይደለም ። የሆነው ሁኖ ከተራው መለያየት በቀር አቡጊዳ እያለ በሳቢያቲኩም በአክሱማዊውም አቅድ ከግዕዝ እስከ ሳብዑ ይዞ ይገኛል ።

## ፪ኛ የአቡጊዳ ፊደል አቀማመጥ ።

አቡጊዳ የተባለችው ፊደል ለጀማሪዎች ሁሉ የፊደል መለያ ሁና የተዘጋጀች ስትሆን በመዘበራረቋ ደግሞ ልጆችን የምታስቸግር ሁና ተገኝታለች ፤ ስለዚህም «አቡጊዳ የተማሪዎች ዕዳ» ብለዋታል ።

ይኸ አቡጊዳ የተባለው ፊደል ግን ጥንታዊ አቀማመጡ ፤ አንድም መልኩ እንዴት እንደነበር ከሴማውያን ፊደሎች ጋር ምን ያህል ግንኙነት እንደነበረው እንዲሁም ከዕብራውያን ጋር የቀረው ቀርቶ ከጽርዕ ጋር ምን ያህል ይገናኝ እንደነበር በኛም ቢሆን ጥንት እንዴት እንደምንማረው ለመግለጥ ያህል ከዚህ እንደሚከተለው እናስቀምጣለን ።

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ | ቡ | ጊ | ዳ | ሄ | ው | ዞ |
| በ | ጉ | ዲ | ሃ | ዌ | ዝ | ሆ |
| ገ | ዱ | ሂ | ቃ | ዜ | ሕ | ጦ |
| ደ | ሁ | ዊ | ዛ | ሔ | ጥ | ዮ |
| ሀ | ዉ | ዚ | ሓ | ጤ | ይ | ኮ |
| ወ | ዙ | ሒ | ጣ | ዬ | ክ | ሎ |
| ዘ | ሑ | ጢ | ያ | ኬ | ል | ሞ |
| ሐ | ጡ | ዪ | ካ | ሌ | ም | ኖ |
| ጠ | ዩ | ኪ | ላ | ሜ | ን | ሦ |
| የ | ኩ | ሊ | ማ | ኔ | ሥ | ዖ |
| ከ | ሉ | ሚ | ና | ሤ | ዕ | ፎ |
| ለ | ሙ | ኒ | ሣ | ዔ | ፍ | ጾ |
| መ | ኑ | ሢ | ዓ | ፌ | ጽ | ቆ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ነ | ሡ | ዒ | ፉ | ጼ | ቅ | ሮ |
| ሠ | ዐ | ፊ | ጻ | ቄ | ር | ሶ |
| ዐ | ፋ | ጺ | ቃ | ሬ | ስ | ቶ |
| ፈ | ጹ | ቂ | ራ | ሴ | ት | ኖ |
| ጸ | ቁ | ሪ | ሳ | ቴ | ኅ | ዖ |
| ቀ | ሩ | ሲ | ታ | ኄ | ፅ | ጾ |
| ረ | ሱ | ቲ | ኃ | ዔ | ጽ | ፖ |
| ሰ | ቱ | ኂ | ፃ | ጼ | ፕ | አ |
| ተ | ኍ | ዒ | ጻ | ፔ | እ | ቦ |
| ኀ | ፁ | ጺ | ፓ | ኤ | ብ | ጎ |
| ፀ | ጹ | ፒ | ኣ | ቤ | ግ | ዶ |
| ጰ | ፑ | ኢ | ባ | ጌ | ድ | ሆ |
| ፐ | ኡ | ቢ | ጋ | ዴ | ህ | ዎ |

ይኸ ፊደል የአቀማመጡ ተራ ከመፋለሱ በስተቀር በአሁኑ ጊዜ ከምንጠቀምበት ፊደል ፤ በተለይም ከግዕዙ ፊደል ምንም ልዩነት የለውም ፤ በቍጥር የሐድን እንደሆነ አንድ ሳይቀነስ ያንኑ ቍጥር ይሰጠናል ።

ማለት ፳፮ ብቻ ሁኖ እናገኘዋለን ፤ በድምፅ በኩል የሔድን እንደሆን እንደ ዚያው ፯ ድምፅ ሰጪዎች እንዳሉት ሁኖ እናገኘዋለን ።

## ፫ኛ የአቡጊዳ ሥርዓተ ትምህርት ።

ለአቡጊዳም እንደ አሁኑ ፊደል የቍጥር ትምህርት አለው ፤ ማለት የፊደሎች ቅርጽ በተለያየ ቦታ ሲገኙ ተማሪው እንዴት ሊለያቸው እንደሚቻል ሆኖ የተዘጋጀ ስለሆነ ፤ ተማሪው አንድ በአንድ ፊደሎችን እየቈጠረ ከላይ ወደታች ከታችም ወደላይ ከቀኝ ወደግራ ከግራም ወደቀኝ እያለ እየመላለሰ ይማራቸዋል ። በዚህም መልክ ከተማረ በኋላ ወደ ግዕዝ (ማጋዝ) ትምህርት ይገባል ፤ የግዕዝም ትምህርት ትርጉም ፤ ፩ኛ ማለት ሲሆን ፤ ከዚህ ላይ ደግሞ ዜማ ያለው ንባብ እንደማለት ነው ።

የዜማውም ዓይነት ልክ እንደ ፊደሉ ትምህርት ነው ፤ በዚህም ድምፅ ልክ እንደ ቍጥሩ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደቀኝ ከላይ ወደታች ከታችም ወደላይ በማለት ድምፁንና መልኩን እስኪለየው ድረስ ይመላልሰዋል ።

ለማጋዝም እንዲመቸው ፪ቱን ፊደሎች ከአንድ ላይ እያገናኘ ያግዛል ፤ እርሱም እንደሚከተለው ነው ።

በማጋዝ ጊዜ ፤ አቡ ፤ ጊዳ ፤ ሄው ፤ ዞሐ ፤ ኀጠ ፤ የከ ፤ ለመ ፤ ነሠ ፤ ዐፈ ፤ ጸፀ ፤ ቀረ ፤ ሰተ ፤ ጰፐ እያለ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም ውስጥ

| | |
|---|---|
| አ—ብሎ | ግዕዙን ። |
| ቡ—ብሎ | ካዕቡን ። |
| ጊ—ብሎ | ሣልሱን ። |
| ዳ—ብሎ | ራብዑን ። |
| ሄ—ብሎ | ሐምሱን ። |
| ው—ብሎ | ሳድሱን ። |
| ዞ—ብሎ | ሳብዑን ያመለክታል ። |

ስለዚህም ስሙ ሳይቀር አቡጊዳ ይባላል ። የቀሩት ፊደሎች ግን ይኽን ሁሉ አይጠብቁም ፤ በግዕዙ ብቻ ይዘልቃሉ ፤ ያለ ድምፅ ሰጪ አቡጊዳ ግዕዙ ብቻ ሲገኝ እንደሚከተለው ይሆናል ።

| ግዕዙ | ዕብራይስጡ | ግዕዙ | ዕብራይስጡ |
|---|---|---|---|
| አ | አሌፍ | መ | ሜም |
| በ | ቤት | ነ | ኖን |
| ገ | ጋሜል | ሠ | ሳምኬት |
| ደ | ዳሌጥ | ዐ | ዔ |
| ሀ | ሄ | ፈ | ፌ |
| ወ | ዋው | ጸ | ጻዴ |
| ዘ | ዛይ | ፀ | ቆፍ |
| ሐ | ሔት | ቀ | ሬስ |
| | | ረ | ሳን |
| ጠ | ጤት | ሰ | ታው |
| የ | ዮድ | ተ | ቀ |
| ከ | ካፍ | ጸ | |
| ለ | ላሜድ | ፐ | |

ይኽ ከዚህ በላይ ያሳየነው ሠንጠረዥ ፤ ፊደላችን በተለይም አቡጊዳ ከዕብራይስጥ ጋር ያለውን ተመሳሳይነትና የቊጥሩንም ልክ የሚያመለክት ነው ።

ግን በአሌፋቱ ፤ አንድም ፤ በዕብራይስጡ ብዙኃኑ ኀ ፤ ፀሐዩ ፀ ፤ ጸ እንዲሁም ፐ የሌለበት ስለሆነ ከዕብራይስጡ ይልቅ የኛ ፊደል የበዛ ነው ለማለት ይቻላል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፫ ።

# የሒሳብ ትምህርት ።

## ፩ኛ የቍጥር ስልት ።

እንደ ዛሬው ሁሉ የመደመር የመቀነስ ወይም የ፬ቱ መደብ የሒሳብ ትምህርት በአሁኑ መልክ አንድም በደንበኛው መንገድ አይሰጥ እንጅ ፤ በመጠኑ ሕፃናት የቍጥርን ትምህርት ከፊደሉ ጋር አብረው መማር እንደ ነበረባቸው የታወቀ ነው ።

ይኸውም ሊሆን የሚገባው ከፊደሉ ጋር አብሮ በመዝለቅ እየመላለሱ እንደፊደሉ የአኃዝን (ቍጥሩን) መልክና ቅርጽ ማጥናት ነበረባቸው ። እንዲሁም ተማሪዎቹ በአኃዝ ብቻ ሳይወሰኑ በፊደልም መልክ ሒሳቡን ማጥናት መቍጠርም ነበረባቸው ።

እንዲሁም ቍጥሩን በቍጥር መልክ በመግለጥ መማር ነበረባቸው ፤ ለምሳሌ የቍጥሩን አኃዝ በመግለጥ ሲማሩ ፤ ፩ ፡ ፪ ፡ ፫ ፡ ፬ ፡ ፭ ፡ ፮ ፡ ፯ ፡ ፰ ፡ ፱ ፡ ፲ ፡ ፳ ፡ ፴ ፡ ፵ ፡ ፶ ፡ ፷ ፡ ፸ ፡ ፹ ፡ ፺ ፡ ፻ ፡ ፼ ፡ በሚል መልክ ነበር ፤ ግን በመጨረሻ ጊዜ ፤ ምዕት ፤ እልፍ ብለው ግጥም በመግጠም « የመምሬን ጠላት እንቆ ለጉድፍ ፡ በመምሬ ጉሮሮ ጠጅ ይንቆርቆርበት ፤ በጠላታቸው ግን አጥንት ይሰንቀርበት » በማለት መምህራንን መውደድ ማክበር እንዲገባ አብረው ያስተምሩት ነበር ።

የአኃዙ ቅርፃችን ከፊደላችን የተለየ ዕርአዊ መልክ ያለው ሁኖ ተገኝቷል ማለት ከአንድ ጀምሮ እስከ ፲ ያለው ቍጥር ምንም ለውጥ የሌለው ቅደም ተከተሉም ሳይሳሳት የዕርዕ ፊደል ሁኖ ተገኝቷል ፤ ይኸንም በገጽ ፲፰ ተመልከት ፤ ሌሎች ግን አንዳንዶች ቢመስሉ እንጂ ሁሉ አይደሉም ።

ይኸንን ቍጥር በማብዛት እስከ ዛሬው ሚሊዮን ድረስ ያስተምሩት ነበር ፤ በአኃዝ ሲቈጥሩ ከላይ እንዳየነው ነው ፤ ግን በአኃዝ ብቻ ሳይሆን በፊደልም ይቈጥሩት ነበር ፤ በፊደልም ሲቈጠር በዚህ መልክ እንደነበር ይገመታል ።

## ፪ኛ በአሁኑ ፊደል ሲቈጠር ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ | 1 | ፩ |
| ለ | 2 | ፪ |
| ሐ | 3 | ፫ |
| መ | 4 | ፬ |
| ሠ | 5 | ፭ |
| ረ | 6 | ፮ |
| ሰ | 7 | ፯ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ቀ | 8 | ፰ |
| በ | 9 | ፱ |
| ተ | 10 | ፲ |

በዚህ መልክ ሊቀጥል ይችላል ፤ ይሁን እንጅ ከ፲ በኋላ ፤ ፳ ፴ ፵ ፶ እያለ ይሄዳል ፡ ይኸም ቢሆን ቅሉ አንዳንዶች የዚህን ጥቅም ባለማወቅ ፤ ሀ- ለ- መ- እያሉ የሚደግመውን ፊደል እየተው ለመቍጠር ይፈቅዳሉ ፤ ይኸም ታላቅ ስሕተት ነው ፤ ምክንያቱም ፊደሎች ሁሉ ራሳቸውን የቻሉ መልክና ቍጥር አላቸውና ።

## ፫ኛ በአቡጊዳ ፊደል ሲቈጠር ።

| | | |
|---|---|---|
| አ | ፩ | 1 |
| በ | ፪ | 2 |
| ገ | ፫ | 3 |
| ደ | ፬ | 4 |
| ሀ | ፭ | 5 |
| ወ | ፮ | 6 |
| ዘ | ፯ | 7 |
| ሐ | ፰ | 8 |
| ጠ | ፱ | 9 |
| የ | ፲ | 10 |
| ከ | ፳ | 20 |
| ለ | ፴ | 30 |
| መ | ፵ | 40 |
| ነ | ፶ | 50 |
| ሠ | ፷ | 60 |
| ዐ | ፸ | 70 |
| ፈ | ፹ | 80 |
| ጸ | ፺ | 90 |
| ቀ | ፩፻ | 100 |
| ረ | ፪፻ | 200 |
| ሰ | ፫፻ | 300 |
| ተ | ፬፻ | 400 |
| ኀ | ፭፻ | 500 |
| ዐ | ፮፻ | 600 |
| ጸ | ፯፻ | 700 |
| ፐ | ፰፻ | 800 |

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ራሱ ፊደሉ ከ፩ እስከ ፲ ድረስ ስለሆነ በቍጥር መልክ እንደ ሚከተለው ያስተምሩታል ።

ሀ - ግዕዝ፤ ሁ - ካዕብ ፡-ሂ- ሣልስ ፡-ሃ- ራብዕ ፡- ሄ - ሐምስ ፤ ህ- ሳድስ ፤ ሆ- ሳብዕ እያሉ የግዕዝ አቈጣጠርን በፊደል መጻፍን በአኀዝ መቍጠርን አብረው ይማሩ ያስተምሩም ነበር ።

እንዲሁም

| | | |
|---|---|---|
| አሐድ | አንድ | አንደኛ |
| ካዕብ | ሁለት | ሁለተኛ |
| ሣልስ | ሦስት | ሦስተኛ |
| ራብዕ | አራት | አራተኛ |
| ሐምስ | አምስት | አምስተኛ |
| ሳድስ | ስድስት | ስድስተኛ |
| ሳብዕ | ሰባት | ሰባተኛ |
| ሳምን | ስምንት | ስምንተኛ |
| ታስእ | ዘጠኝ | ዘጠነኛ |
| አሥር | አሥር | አሥረኛ እያሉ ያጠኑት ነበር ። |

በተለይ ይኸ ዓይነት የአኀዝ መንገድ በሰፊው የሚጠናው በግዕዝ ትም ህርት በተለይም በአገባብ ትምህርት ጊዜ ነው ።

(መጽሔቱን ተመልከት)

ምዕራፍ ፬ ።

# ፊደለ ሐዋርያና ገበተ ሐዋርያ ።

## ፩ኛ ታሪኩ ።

ፊደለ ሐዋርያና ገበተ ሐዋርያ የተባሉት የትምህርት ዓይነቶች ከአቡጊዳ ቀጥለው የሚገኙ ሲሆኑ የመጠሪያ ስማቸው እንዲህ የተባለበት ምክንያት ምን እንደ ሆነ አይታወቅም ፤ በቤተ ክርስቲያን ግን የታወቀ ስማቸው ፤ መልእክተ ዮሐንስና ሌሎችም መልእክታት ናቸው ።

ተማሪው እነርሱን የዘር መለያ የንባብ መማሪያ አድርጎ ከፊደል ዓለም እንደወጣ የሚቈጥርባቸው የመማሪያ ዘዴዎች ናቸው ።

በዚህም መሠረት ዛሬም ቢሆን በሁሉም መልእክታት አይጠቀሙ እንጅ ፤ ፩ኛውን የቅዱስ ዮሐንስን መልእክት በተለይም መጀመሪያውን ምዕራፍ ከፊደ ልና ከአቡጊዳ ጋር አብረው አሳትመው ይማሩበታል ያስተምሩበታል ።


www.ethiopianorthodox.org

ተማሪውም የቀለሞችን አቀማመጥ የሚለይበት አፉንም የሚከፍትበት ይኸ ዓይነት ትምህርት ነው ፤ ምክንያቱም አቡጊዳ የተባለው ምንም የፊደሎቹ አቀማመጥ ለየት ብሎ ከፊደል የቀረውን ቅርጽ ለይቶ ማወቂያ ወይም ማጣሪያ ቢሆንም ፤ ተማሪው የሚቈጥረው አሁንም ፊደል እንደሆነና በፊደልም መልክ ነው።

ይኸ ፊደለ ሐዋርያ አንድም ገበተ ሐዋርያ የተባለው ግን ራሱን የቻለ መጽሐፍ ስለሆነ ፊደሎችም ሌላ የአቀማመጥ ስልት ያላቸው በመሆኑ ተማሪው ጠንቅቆ አንድ በአንድ እንዲያጠናው አቀማመጣቸው ያስገድደዋል ።

ስለዚህም መልካቸውን ቅርጻቸውን በመለየት ጠንቅቆ ይቈጥራል ፤ ያግዛል ውርድ ንባብም ያነባል ፤ በጣም መለየቱ ሲታወቅ ደግሞ ቁም ንባብ ያስነብበዋል ።

## ፪ኛ በብዛት የሚጠቀሙበት አገሮች ።

በዚህ ዓይነት ትምህርት ከጥንት ጀምሮ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሲጠቀሙበት እንደኖሩ ይነገራል ፤ እየዋለና እያደረ ግን በትግሬና በሸዋ ፤ እንዲሁም በስሜን ብቻ ይጠቀሙባቸው ነበር ።

እነርሱም ቢሆን በመጠኑ ነው እንጅ ለሁሉም የተዳረሰ አልነበረም ከዚያም በቀጥታ ወደ ልዩ ልዩ መጽሐፍ የሚሸጋገሩ ሁነዋል ።

በታሪክ መልክ ግን ሲቀርብ የትምህርቱ ዘዴ እንዲህ እንደነበር ለማወቅ ያስችላል ፤ ግን እንኳን በጥንት ዘመን ዛሬም ቢሆን በሁሉም ቦታ የታወቀ አይደለም ፤ ማለት ፤ ፊደለ ሐዋርያ ከፊደሉ ጋር አብራ በመታተሟ ባይማሯትም ስሟን ያውቃሉ ፤ ገበተ ሐዋርያ ግን እስካሁን ከነስሙ እንግዳ የሆነ ነገር ነው ፡ እንዲያውም በአንዳንድ ቦታ ፊደል ሳይቀር ማግኘት ችግር እየሆነባቸው በፊደል ያልተማሩ የፊደልን አቀማመጥ እንኳን በደንቡ የማያውቁ ፤ ግዕዙን ካዕቡን ሣልሱን ለይተው የማያውቁ ብዙዎች ናቸው ።

ምክንያቱም እንዲሁ ትምህርት ሲጀምሩ በደንበኛው ፊደል ሳይሆን ከማንኛውም መጽሐፍ በቀጥታ ገብተው ቍጥር ይጀምራሉ በዚያውም ንባቡን ጀምረው ይዘልቃሉና ።

ምዕራፍ ፫ ።

## የጽሕፈት ትምህርት ።

ጽሕፈት ለኢትዮጵያውያን ከፍ ያለ ሞያ ትልቅም ቁም ነገር ስለነበር ተማሪው ፊደል እንደጀመረ ከፊደሉ ቍጥር ጋር ጽሕፈቱን አብሮ ያጠና ነበር ፤ በዚህም ጊዜ ዳዊቱን እንደጨረሰ ከትምህርት ሲወጣ በጽሕፈት ሥራ ገብቶ ሲያገለግል ችግር አይገጥመውም ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም በቀር በቁም ጽሕፈት የሠለጠኑ እየሆኑና የዛሬውን ትውልድ
ወደ አድናቆት የመለሱትን ታላላቅ መጻሕፍት በቁም ጽሕፈት እየጻፉ ያቆዩን
በዚህ መልክ የተማሩ ሁሉ ነበሩ ። ብዙዎች መምህራን ከትምህርት ጋር
ይኸንኑ አስገብተው ደረጃም ሰጥተው የፊደሎችን ቅርጽ በመጠበቅ ጽሕፈት ያስ
ተምሩ ስለነበር ሁሉም ጸሐፊ ለመሆን በቃ ።

ማንኛውም ጸሐፊ ሊጠነቀቅላቸው የሚገቡ ግድፈተ ጸሐፊ ሁነው እንዳ
ይገኙ በጥብቅ የሚያሳስቧቸው ነገሮች የሚከተሉት ነበሩ ።

## ፩ኛ የፊደልን አቀማመጥ በመጠበቅ ።

የቁም ጽሕፈት ሲማሩ የብርዑን አጣጣል ማሳመር ብቻ ሳይሆን አርእስትን
ኀዳግን ይጠነቀቃሉ ፤ ለምሳሌ ፤

፩- አርእስት የተባለው ነው፤እርሱም የመጽሐፉ ራስ ያልተጻፈበት ቦታ ነው ።

፪- ኅዳግ የተባለው ነው ፤ ይኸ ደግሞ በግርጌው ያለው ሲሆን ኅዳግ ማለት
ያልተጻፈበት የተተወ ማለት ነው ።

፫- ግሌት የተባለው ነው ፤ ይኸውም ወደመጨረሻ ያለው ቦታ ነው ፤

፬- ሕላፍ የተባለው ነው ፤ ይኸውም ወደጫፉ ያለው ቦታ አንዳንድ ጊዜ
መመለስ እያቃታቸው አልፈው ስለሚጽፉበት ሕላፍ ተብሏል ።

፭- ዓምድ የተባለው ነው ፤ ይኸውም በሁለቱ ጽሑፎች መካከል የማይጻ
ፍበት ቦታ ነው ። አሁን ግን ዓምድ የሚሉት በአንዳንድ ላይ ተለያይተው የሚገ
ኙት የተጻፈባቸው ቦታዎች ናቸው ፤ ግን ልክ አይደለም ።

፮- ወስፈው ያለፈበት ወይም መሥመሩ ነው ፤ ይኸውም ሲራክ ይባላል ፤

፯- ምስማክ ፤ ይኸውም በመሥመርና በመሥመር መካከል ያለው ቦታ ፊደ
ልን በመጠበቅ የሚጻፍበት ነው ።

፰ - ማኅጸን የተባለው ነው ፤ እርሱም በፊደሉ መካከል የሚገኘው ቦታ
ነው ፤ ለምሳሌ ዓ መ ቀ ይኸንም የመሳሰሉ ናቸው ።

፱- ሕጽን የተባለው ነው ፤ እርሱም በፊደሉ መካከል የሚገኘው ክፍት
ቦታ ነው ፤ ለምሳሌ በ ለ ሰ እነርሱንም የመሳሰሉ ናቸው ።

፲- ሕጽንና ማኅጸን በአንድ ላይ ሲገኙና ይኸንም የመሳሰሉ ሌሎች
ይገኛሉ ።

እንዲሁም ፊደልን በመጠበቅ ሲጻፍ ፤ ለምሳሌ ፤ ሀ- ሃሌታው ሀ እና ሐመሩ ሐ
እንዲሁም ብዙኃኑ ኃ ፤ እንዳይጠፉ በማለት ለይቶ ጠንቅቆ ይጽፍ ነበር ፤ እንዲሁም
ንጉሡ ሠ እና እሳቱ ሰ ፤ አልፋው አ እና ዓይኑ ዐ ፤ ጸድቁ ጸ እና ፀሐዩ ፀ
የዋሉበትን ወይም የሚሆኑበትንና እንደ ነርሱም ያሉትን አሻሚ ፊደሎችን ሁሉ
በመጠበቅ በቁም ጽሕፈት መጻፍ ነበረበት ። ለምሳሌ ያህል እነዚህ ብቻ ተገ

www.ethiopianorthodox.org

ለጡ እንጅ እነዚህ ፊደሎች ፩ኛው ሊውልበት የሚገባው ከኋላው ማንኛው ፊደል ሲከተለው በፊቱም ማንኛው ፊደል ሲቀድመው እንደሆነ እያተቱ ስለሚያስተምሩ ተማሪው ጽሕፈቱን በሚገባ ይከታተል ነበር ፤ በተለይም ከፊደሎች ውስጥ ግዕዙና ራብው ቅርፃቸው ልዩ ይሁን እንጅ በድምፅ ስለሚመሳሰሉ ለይቶ ለመጻፍ ያስቸግራሉ ፤ ለምሳሌ ሀ እና ሃ ፤ ሐ እና ሓ ፤ ኀ እና ኃ ፤ እንዲሁም አ እና ኣ ፤ ዐ እና ዓ ፤ እንዲሁም ካዕቡና ሳድሱ ፤ በድምፅ አንድ መስለው በቅርጽ የተለያዩ ናቸው ። በምሥጢሩም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው ፦ሌላም ይኸን የመሰሉትን ያለቦታቸው እንዳይውሉ ማድረግ ቀዋሚ ትምህርት ነበር ለምሳሌ በሠ ፊንታ ሰ ፤ በሃ ፊንታ ኃ ፤ ሌላም ይኸን የመሰለ ችግር እንዳያጋጥመው ጠንቅቆ ያጠናል ፤ በዚህም መሠረት ይጽፋል ።

ከዚህም በቀር ከመሥመር በላይ የሚውሉ ከመሥመር በታችም የሚወርዱ ፊደሎች ባይኖሩንም እንኳ ሁሉም መሥመራቸውን ጠብቀው የሚሔዱ ቢሆኑም የያንዳንዳቸውን ቅርጽና አቀማመጥ ጠንቅቀው ይማሩ ነበር ።

እንዲሁም ይኸን የመሰለውን ሁሉ በመጠበቅ እንከን ሳያገኝ የመጽሐፉ ውጤት እንዲያምር ያስተምራሉ ።

## ፪ኛ የነጥቦችን አቀማመጥ በመጠበቅ ።

የነጥቦች አቀማመጥ ደንበኛውን ቦታ ሲይዝ ለሥነ ጽሑፍ መልክ ከመስጠቱ በላይ ለንባብም ይቀናል ። ነጥቦች ከአይደለ ቦታ የዋሉ እንደሆን ለትርጓሜ ያስቸግራሉ ፤ የቀረው ቀርቶ ለንባብ እንኳን በጣም ያስቸግራሉ ፤ ስለዚህ እንደ ግዕዙ ቋንቋ ትምህርት የሆነ እንደሆነ የነጥቦችም አቀማመጥ ብዙ ጥንቃቄ ሊደረግለት እንደሚገባ ያስተምራሉ ። ይኸንም ለሚጠብቅ ከፍተኛ ግምት ይሰጠው ነበር ፤ የነጥቦች አቀማመጥና ስማቸውም የሚከተሉት እንደሆኑ በቁም ጸሐፊዎች ዘንድ የታወቀ ነው ።

ነጥብ ( ፡ ) ነቁጥ ( ⁎ ) ነጠላ አንድም ንዑስ ሠረዝ ( ፣ ) ድርብ አንድም ዓቢይ ሠረዝ ( ፤ ) ሙሉ ነጥብ ( ። ) ናቸው ።

እንደ ጥያቄ ምልክት የሚሆነው ግን ራሱን የቻለ ምልክት እንደነበረን የታወቀ ነው ፤ እርሱውም ኑ የተባለው ፊደል ነው ፤ በርሱም ሲጠቀሙ እንዲህ ይላሉ «ሕያውኑ አቡክሙ» አባታችሁ ደኅና ነውን «ዘመኑ መልክኡ» ቅርጹ የማነው የሚል ነበር ።

በአማርኛ ቋንቋ ግን <u>በ</u>ኑ ፊንታ <u>ን</u> የተባለው ፊደል ተተክቶ ይገኛል ፤ ለምሳሌ ፤ ምንህ<u>ን</u> ያምሃል ፤ መጽሐፉ የማ<u>ን</u> ነው ይኸንንም በመሰለ መንገድ ይሄድ ነበር ።

ሊቃውንቱም ይኸን ሁሉ በመለየት ያስተምሯቸው ነበር ፦ መጻሕፍቱም በዚሁ መልክ በብዛት ለመጻፍ ቻሉ ፤ ዛሬ ግን ፩ኛ የፊደሉን መልክ በመለየት

www.ethiopianorthodox.org

ባለማስተማር ፤ ፪ኛም የጽሕፈትን ሥልት በሚገባ ባለማስተማር እንኳን ተማሪው አስተማሪው የሚጽፈው ከፊደልም ከነጥብም ውስጥ ማንኛውም ባለመጠበቁ ለአ ንባቢ ችግርን ፈጥሮ ይገኛል ።

ይኸውም ሀብት በማለት ፈንታ ሐብት አንድም ኀብት ያለ እንደሆን ለአ ዋቂ ሰው ማንበብ ያስቸግረዋል ፤ ምክንያቱም መጀመሪያውን ሀብት በማለት መጻፍ እንዳለበት ወይም እንደሚገባ አጥንቷልና ። ሁኖም አሁን ሁሉም በመል ኩና በአገባቡ ባለመማሩ ብዙ ሰው እንዳገኘ ከመጻፉ የተነሣ እንዳገኘ ሊያነበው ችሏል ፤ ወቀሳም ከሰሳም ስለሌለ እንዲሁ ሊጽፈው ችሏል ።

አንዳንዶች ግን የዚህን ሁሉ ችግር በመመልከት ሌላ የተሻለ መንገድ የተገኘ መስሏቸው ፊደሉ ቢለወጥ ወይም ቢያጥር ሌላም ዓይነት ቅርጽ ቢያገኝ የተሻለ ነው ፤ በማለት የተለያዩ ሐሳቦችን በየጊዜው ማመንጨታቸው አልቀረም ።

ሐሳቡ መልካም ሲሆንና ሊደገፍም ሲገባ ችግሩ ያንንም ቢሆን በወጉ ካልተማሩት ውሎ አድሮ የበለጠ እንቆቅልሽ ይሆንና ከዚህ የበለጠ ችግር እንደ ሚፈጥር ጥርጥር የለበትም ።

እንዲያውም አንዳንዶች ከጥንታዊው የጽሕፈት አጣጣል ያልተለየ አስተያ የትን አቅርበዋል ፤ ይሁን እንጅ ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው መሠረት ተማ ሪዎቻችንን ማስተማር ማሠልጠን የሁላችን ፈንታ በመሆኑ ሁላችን ልናስብበት የሚገባን በዚሁ በጥንታዊው ፊደል መሆን አለበት ።

## ፫ኛ የጽሕፈት ተቃውሞ ።

በጥንት ዘመን ሁሉም ጽሕፈት ይማሩ ነበር አልን እንጅ ጥቂቶች አስተ ማሪዎች ደግሞ የጽሕፈት ተቃዋሚ ሁነው ከትምህርት ቤታቸው ሲጽፍ ያገኙትን ተማሪ እንደነውር አድርገው ይቀጡት ፤ ከትምህርት ቤታቸውም ያስወጡት ነበር ፤ ሌላውም እንዳይጽፍ ይከለክሉ ነበር ፤ ምክንያቱንም ሲጠይቋቸው ርቀን አሰብን ብለው በሚመስላቸው መንገድ መልስ ይሰጣሉ ፤ የሚመልሱትም የጥንቁልና ሥራ እየተስፋፋ ስለአስቸገራቸው ተማሪው ሁሉ የእጁ መፍቻ ያደረገው የጥንቁልናን ሥራ በመሆኑ ነው ፤ ይኸውም ሊተላለፍ የሚችለው በመጽሐፍ ስለሆነ ነው ።

ስለዚህ ካህናት የሆኑ ሁሉ ጽሑፍ የጻፉ እንደሆን ይጠንቁላሉ እየተባሉ በጣም ይፈሩ ስለነበር እንዳይጽፉ ወይም ጽሕፈት እንዳይማሩ ያደርጓቸው ነበር ።

እንዲያውም ጽሕፈት የሚያውቅ እንዳይቀድስ ግዝት የሆነባቸው አብያተ ክርስቲያናት እስከ አሁን ይገኛሉ ፤ ለምሳሌ ፤ መካነ ኢየሱስ የተባለው ታላቁ ደብር (ቤጌምድር) ነው ፤ እስካሁን ይኸ ነገር እንደትልቅ ሕግ ሆኖ ይጠበቃል ፤ ማለት የሚጽፍ አይቀድስም ፦ በሌላም በብዙ አድባራትና ገዳማት እንዲሁ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የሆነ ሆኖ በዚያ አገር ደግሞ የቁም ጽሕፈት በየደብሩ የተለየ ትምህርት ቤት ያለው ሆኖ እስከ አሁን ተማሪዎች ይማሩበታል ታላላቅ መጻሕፍቶችም የሚጻፉ በዚያው አገር ነው ። በተለይም ፤ አንዳቤትና አፈረ ዋናት በተባሉ አገሮች የፊደል ቅርጽ የሚጠበቅበት የቁም ጽሕፈት አቃቂር የሚወጣበት ፤ ዘመናትን በመጠበቅ ልዩ ልዩ መሻሻል የሚደረግበት አገር ነው ።

እንደዚህም ለመሆን የቻሉት ለልጆች አስቀድሞ ጽሕፈትን ከፊደሉ ትምህርት ጋር በማስተዋወቅ የጽሕፈትንም ትምህርት ስልት በማስተማር ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፪ ።

# የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ።

### ምዕራፍ ፩ ።

## የንባብ ትምህርት ።

## ፩ኛ የንባብ መጻሕፍት ።

ከዚህ በፊት በገለጽነው መልክ ተማሪው የፊደሎችን ቅርጾችና ስሞች እንዲሁም ጠባዮች በደንብ ከለየና ፊደለ ሐዋርያን ገበተ ሐዋርያንም በሚገባ ከአነበበ በኋላ ፤ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን እያፈራረቀ ያነባል ፤ እንደ ዕድል ሆኖ ብዙ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን መጻሕፍት የሚገኙት በየመምህራኑ ቤት ስለሆነ በተአምሩ በድርሳኑ ይኸንም በመሳሰሉት መጻሕፍት ያለችግር ተማሪው ያነባል ።

ነገር ግን ለንባብ መለያ ይሆናሉ ተለብው በቤተ ክርስቲያን የተወሰኑት መጻሕፍት አርጋኖን ፤ ውዳሴ አምላክ ፤ መጽሐፈ አርድዕት ፤ የተባሉትና ይኸንም የመሳሰሉት ሌሎች መጻሕፍት ናቸው ። እነዚህም ለንባብ አስቸጋሪ መስለው የተገመቱ ስለነበሩ ተማሪው እነዚህን መላልሶ እንዲያነብ ያደርጉታል ። ይኸም የንባብ ክፍል እንደ ከፍተኛ ደረጃ ተቈጥሮ እገሌ ንባብ ገብቷል ንባብም ይማራል ሲባል ከፍተኛ ክፍል እንደደረሰ ከጀማሪነት ደረጃ እንደወጣ ይገመት ነበር።

## ፪ኛ የንባቡ ዓይነት ።

ንባብ የተባለው ትምህርት ፫ ዓይነት ዜማ አንድም መንገድ አለው ፤ ይኸውም

ሀ ፤ ግዕዝ ንባብ አንድም ማጋዝ ይባላል ፤

ይኸ ዓይነት ትምህርት ከዚህ ቀደም በፊደል ትምህርት እንዳመለከት ነው ሁሉ ፊደሎቹን በመቍጠር ያግዛል ፤ ያግዛል ማለትም ይድኃል ፤ ይንኳተታል እንደማለት ነው ፤ በተሻለ አገላለጥ ሲገለጥ ከቍጥር በተሻለ መንገድ ማጋዝ ይጀምራል ማለት ነው ። ሆኖም ነገሩ እንደቍጥር ያለ ነው ፤ ግን ዜማ ያለው ትምህርት ስለሆነና ከቍጥርም ትንሽ ለቀቅ ያለ ስለሆነ ግዕዝ ተብሏል ።

ለ ፤ ውርድ (ንዑስ) ንባብ ፤

እሱም ዜማ ያለው ንባብ ሲሆን ይኸውም የኀዘን መልክ ያለው ነው ፤ ስለዚህም የታላቁ የኀዘን ዕለት በዚህ ድምፅ አንድም ዜማ ይነበባል ፤ - ለምሳሌ የስቅለት ዕለት ብዙ ጊዜ የሚነበበው ንባብ ሁሉ በዚሁ ዜማ ነው ፤ - ፪ኛው ዓይነት የንባብ ስልት መሆኑ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

### ሐ ፤ ቁም (ዓቢይ) ንባብ ፤

ይኸውም ዓይነት ንባብ ቍጥሩን ማጋዙን ፣ ውርድ ንባቡን በደንብ ከለዩ በኋላ ያላንዳች ችግር በቀጥታ ማንበብ ማለት ነው ።

ግዕዙም ውርድ ንባቡም እንደ መገርደፍ ሲሆን ፤ ቁም ንባብ ግን እንደመ ሰለቅ ፤ እንደማላምም ይቈጠራል ።

ስለዚህም ንባቡን ደኅና አድርጎ ይሰልቀዋል በሚገባም ያነበዋል ፤ ከላይ የተገለጡትን መጻሕፍት ተራ በተራ እያፈራረቀ ካነበበ በኋላ ፤ እገሌ ንባብ ዐወቀ ይባላል ፤ ለምልክቱም ያገኘውን መጽሐፍ ሁሉ ሳይቈጥርና ሳያግዝ በቀጥታ እን ደቀረቡለት ተነሺውን ወዳቂውን በመለየት ያለምልክት አቃንቶ ያነባል ። ይኸ የን ባብ ክፍል ፤ ከላይ እንደገለጥነው ሁሉ ከፍተኛ ስለሆነ ጀማሪው ሁሉ እገሌ ትም ህርቱን ከምን እንደ አደረሰ ሲጠየቅ ንባብ ገብቷል ይባላል ፤- በዚህም መሠረት ገና ንባብ ያልጀመረ ሰው ከትምህርት ቤት ገብቶ ድጓ ሲማሩ አይቶ ተማሪዎ ቹንም ሰው ሲያከብራቸው ተመልክቶ ስለ ድጓ ሲያስብ ምን ትማራለህ ብሎ ቢጠይቀው የድጓ ንባብ ሲል መለሰለት ፤ ተመልካቹም እውነትህ ነው « ከነም ልክቱ ድጓ መነበቡ » አለው ይባላል ፤ ይኸም ማለት ።

ሀ/ የውሸቱ ምልክት ይኸ ነው ፤ ድጓ የንባብ መጽሐፍ መሆኑ ፤

ለ/ ድጓው ንባቡ ብቻ ሳይሆን ምልክቱ ሳይቀር ይነበባል በማለት እንደ መገረም ነው ።

በዚህም መልክ ተማሪው የንባቡን ትምህርት እንደፈጸመ ወደ ዳዊት ይገባል ።

## ምዕራፍ ፪ ።

## ዳዊት መድገም ።

የዳዊት መድገም ከጥንት ዘመን ጀምሮ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንደከፍ ተኛ ትምህርት ተቈጥሮ ፤ በጣም የከበረ ሥርዓት ነበረው ፤ ስለዚህም ዳዊት የትም ህርቱ መጨረሻ እንደሆነ ይገመት ስለነበር ልጆች ሁሉ ከዚህ ለመድረስ ይኸንንም ደረጃ ለማለፍ የሚያደርጉት ጥረት በጣም ከፍ ያለ ነበር ።

ዳዊት የተባለው መጽሐፍ ነቢዩ ወይም ንጉሡ ዳዊት የደረሰውና ያስደ ረሰው ፤ በኋላም እየመላለሰ ይዘምረው የነበር ሲሆን ፤ ከርሱ ጊዜ ጀምሮ እስካሁን በሀገራችን ይኸ መጽሐፍ ለጸሎትም ለትምህርትም ጊዜ ክብር ተሰጥቶት ሁሉም ይማረው ነበር ። በዚህም ምክንያት ወንድ ሴት የጨዋ ልጅ ካህን ሳይል ሁሉም በጧት በማታ በመድገም ሲጠቀምበት ይገኛል ። ስለጸሎትነቱ ፤ በዓለም ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ተወዳጅነት ያለው በየጊዜውም የሚደገምና የሚዘለቅ ልዩ ልዩ ቦታ ተሰጥቶት የሚጸለይ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ የትምህርት ዓይነት ።

ወጣቱ ተማሪ ምንም ቀደም ብሎ ልዩ ልዩ መጻሕፍትን ቢያነብ የንባብንም ስልት ጠንቅቆ ቢያውቅ ፤ ግዕዝ ንባብ ለመጀመሪያ ጊዜ ማንበቡ አይቀርም ፤ ግን ግዕዝነቱ የተለየ ነው ።

በዚህም መልክ እየመላለሰ አንዱን መዝሙር ከወጣው በኋላ እንደገና ውርድ ንባብ የተባለውን ፪ኛውን ዓይነት ትምህርት በዚያው መዝሙር ላይ ይቀጥላል ፤ እርሱንም በመመላለስ ከዘለቀው በኋላ ቁም ንባብ አንድም ዓቢይ ንባብ የተባለውን በቀጥታ ያነባል ።

፪ኛ ፤ ከላይ በተገለጠው መልክ ፫ ጊዜ ይዘልቀዋል የዚህንም ውጤት መምህሩ ሲመለከት አስደሳች ሆኖ ያገኘው እንደሆነ ወደ ፪ኛውና ወደ ሚቀጥለው መዝሙር እንዲተላለፍ ያደርገዋል ።

በዚህ መልክ ከፍካሬ እስከ ንዑስ አነ መቶ አምሳ አንዱን ዳዊት ያጠናል ።

ከዚያም አልፎ ነቢያት የተባሉትን ለጸሎት የተውጣጡትን ከዳዊት ጋር ሁል ጊዜ የሚጠረዙትን መጻሕፍት ያጠናል ።

እነዚህ መጻሕፍት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ለጸሎት ተውጣጥተው ከዳዊት ጋር አብረው የተጠረዙ በመሆናቸው ዳዊት የደረሳቸው ፤ አንድም የዘመራቸው እንደሆነ ያመለክታል ፤ ስማቸው እንደሚያመለክተው የተለያዩ ነቢያት በተለያየ ዓረፍተ ዘመን የደረሷቸው እንደሆነ ጥርጥር የሌለበት እውነት ነው ።

ይሁን እንጅ በብራናውም ፤ በእትማቱም ጊዜ ሳይለዩ በመገኘታቸው ተማሪው እንደ ዳዊቱ በፊት አብሮ ይማራቸዋል ፥ በኋላም እንደ ዳዊቱ ጊዜ ወስኖ አብሮ ይጸልያቸዋል ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

መኃልየ ነቢያት ።

ጸሎተ ሙሴ ቀዳማይ
ጸሎተ ሙሴ ዳግም
ጸሎተ ሙሴ ሣልስ
ጸሎተ ሐና
ጸሎተ ሕዝቅያስ
ጸሎተ ምናሴ
ጸሎተ ዮናስ
ጸሎተ ዳንኤል
ጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ
ኀበ ባረኩ አናንያ

www.ethiopianorthodox.org

ጸሎተ ዕንባቆም
ጸሎተ ኢሳይያስ
ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም
ጸሎተ ዘካርያስ
ጸሎተ ስምዖን

ከዚህ በኋላ ፭ቱን የሰሎሞን መኃልየ መኃልይን በዚያው መልክ ያጠናል ። እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

፩-/ ይስዕመኒ በስዕመተ አፉሁ
፪-/ ቃል ወልድ እኁየ
፫-/ መኑ ይእቲ ዛቲ
፬-/ ምንት ውእቱ ወልድ እኁኪ
፭-/ መኑ ይእቲ ዛቲ እንተ ትኄውጽ ፤ ናቸው ።

ውዳሴ ማርያምና አንቀጸ ብርሃን ሁልጊዜ ከዳዊቱ ጋር ይጠረዛሉ ፤ ግን በትምህርት ጊዜ ከላይ እንደገለጥናቸው ሁሉ አይማሯቸውም ፤ የሚማሩበትም ጊዜው በዚያው ዳዊት በሚደግምበት ጊዜ ሲሆን ፤ ጥናቱ ግን ማታ ማታ እየ ሆነ በቃሉ ስለሚያጠናው ፤ የቃል ትምህርት ተብለው ይጠራሉ ።

## ፪ኛ ዳዊት ለደገመ የሚሰጥ ሽልማት ።

የዳዊቱን ትምህርት ከዚህ በላይ በገለጥነው መልክ ከአጠናቀቀ በኋላ እገሌ ዳዊት ደገመ ይባላል፤ ልዩ ግምት ይሰጠዋል ፤ ማለት ትምህርት ጨረሰ እንደ ማለት ነው ። ይኸውም ማለት በዛሬው ጊዜ ፪ኛ ደረጃን እንዳጠናቀቀ ወጣት ይቈጠር ነበር ፤ በዚህም ምክንያት እንደጊዜው ሁናቴ ከፍተኛ ሽልማት ከወላጆቹ ከዘመ ዶቹ ከክርስትና አባቱ ለተማሪው ይሰጠው ነበር ።

ለመምህሩም ቢሆን እንዲሁ ከፍተኛ ስጦታ ይሰጠው ነበር ።

በቀለም ትምህርት ዳዊት መድገም እንደ መጨረሻ ሆኖ ብዙው ሰው በዚህ ሲወሰን ወደሥራም ሲሠማራ ፤ ከፍ ያለ ዕውቀት ለማግኘት የፈቀደ ግን ወደ ከፍተኛው ደረጃ ወደ ቃል ትምህርትና ወደዜማ ይዛወር ነበር ።

ቀን ዳዊት እንደመድገሙ ማታ ማታ ወይም በቀኑ ሰዓት ተወስኖለት የሃይማኖትና የቃል ትምህርት ይማር ነበር ።

ምዕራፍ ፫ ።

# የሃይማኖት ትምህርት ።

ኢትዮጵያውያን ከእምነት ውጭ የነበሩበት ጊዜ ከቶ የለም ፤ ስለዚህም በየጊዜው የተወሰነውን የሃይማኖት ትምህርት በልዩ ልዩ መልክ ማለት በስድ

www.ethiopianorthodox.org

ንባብ በግጥም እንዲሁም በጥያቄና መልስ ዓይነት እያደረጉ ወጣቶችን ያስተምሯ ቸው ነበር ።

ይኸውም በብሉይና በሐዲስ ዘመን የተወሰነ ትምህርት ሲሆን እንደ ግጼታ ሁኖ ሲሰጥ ቆይቷል ፤ እርሱም የሚከተለው ዓይነት ነው ።

## ፳፪ ሥነ ፍጥረት ።

እግዚአብሔር በቸርነቱ ዓለምን እንደፈጠረ ፥ ዓለምን እንደመገበ ሁሉም በእግዚአብሔር ፈጣሪነት እንደሆነ ፥ ያለ እግዚአብሔርም ፥ ምንም የሆነ እንደሌለ ቅዱስ መጽሐፍ «እግዚአብሔር በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ» በማለት የየ ዕለቱን ፍጥረት ተራ በተራ በመዘርዘር የተናገረውን የኛ ሊቃውንት አስፋፍተው ተርጒመው ሁሉንም በየወገኑ አድርገው ቆጥረው የሥነ ፍጥረት ክፍል ወይም ቊጥር ፳፪ እንደሆነ አምነው ያስተምራሉ ።

ይኸንም ትምህርት ሲያስተምሩ ከቅዱስ መጽሐፍ ሌላ አስፋፍተው ተር ጒመው የታወቀውን የቅዱስ ባስልዮስን እንድም የቅዱስ ኤጲፋንዮስን «አክሲ ማሮስ» የተባለውን መጽሐፍ በመከተል ነው ።

አክሲማሮስ የተባለውም ፥ ኤክስ—ኤሜራስ ፤ የስድስት ቀን ፍጥረት ማለት ነው ፤ እንደዚህም አገላለጥ በስድስት ቀን ብቻ ፍጥረቱ ሁሉ ተከናወነ ፍጥረቱ ሁሉ መልኩን ቅርጹን ያታውን ይዞ ተገኘ ማለት ነው ።

በስድስት ቀን የተፈጠሩት ፍጥረታት ሁሉ ፳፪ ዓይነት ናቸው ። የሥነ ፍጥረትም ቊጥራቸውና ስማቸው ተራቸውም ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

### ሀ) የዕለተ እሑድ ፍጥረት ፤

በዚህ ዕለት ስምንት ፍጥረታት ተፈጥረዋል ፤ እነዚህም ሰማይና ምድር ፤ ውኃና ፤ እሳት ፤ ነፋስ ፤ ሲሆኑ ፬ቱ ባሕርያት የሚባሉት ናቸው ።

ከሰማይ ጋር ፯ ይሆናሉ ፤ ብርሃንና ጨለማ መላእክትም ጭምር በዚሁ ዕለት ተፈጥረዋል ፤ ሁሉም ሲደመሩ ፰ ይሆናሉ ።

አንዳንድ ሊቃውንት ግን ፯ ብቻ እንደሆኑ አድርገው ይናገራሉ ።

### ለ) የዕለተ ሰኑይ ፤

በዚህ ዕለትም የዕለተ እሑድ ፍጥረት ተከናውኗል ፤ እነርሱም ዓለም ወጣ ገብ ስትሆን መልክ አግኝታበታለች « ለይትጋባእ ማይ ውስተ ምዕላዲሁ » በማ ለት ባሕርን ከሦስት ከፍሎ አንዱን እጅ ጠፈር አድርጐታል የብርሃን ፀሐይ መመ ላለሻ ነው ፤ ተብሎ የተገመተው ነው ።

አንዱን እጅ በዓለም ዙሪያ ወስኖታል ፤ ውቅያኖስ እየተባለ የሚጠራው ነው ፤ አንዱን እጅ ግን መሠረተ ምድር አድርጐታል ፤ ሐኖስ ይባላል ፤ እንዲህ አድ

www.ethiopianorthodox.org

ርጎ ለዓለም ቅርጽ መልክ ሰጥቶታል ፤ ግን ፍጥረቱ ወይም ሥራው አንድ ብቻ ተብሎ ይቈጠራል አንዳንዶቹ ግን ፪ ይላሉ ።

## ሐ) የዕለተ ሠሉስ ፍጥረት ፤

በዚህ ቀን ፫ ፍጥረታት ተፈጥረዋል ፤ እነርሱም ፤ በጥፍር የሚለቀሙ አትክልት ፤ በማጭድ የሚታጨዱ አዝርእት ፤ በምሣር የሚቆረጡ ዕፀዋት ናቸው ።

## መ) የዕለተ ረቡዕ ፍጥረት ፤

በዚህም ዕለት ፫ ታላላቅ ፍጥረቶች ተፈጥረዋል ፤ እነርሱም ፤ ፀሐይ ፤ ጨረቃ ፤ ከዋክብት ናቸው ። ከዋክብትና ፀሐይ እንኳን ገና ቢሆኑ ጨረቃ የተባለችው የብርሃን መገኛ በዚህ በኛ ዘመን በሰው እጅ የተዳሰሰች ፕላኔት ሁና ተገኝታለች ።

## ሠ) የዕለተ ሐሙስ ፍጥረት ፤

በዚህም ዕለት ፫ ታላላቅ ዓይነት ፍጥረቶች ተፈጥረዋል ፤ እነርሱም በባሕር ውስጥ የሚኖሩ ሲሆኑ በእግር የሚሽከረከሩ ፤ በክንፍ የሚበሩ ፤ በልብ የሚሳቡ ናቸው ። እነዚህም ሁሉ በደመ ነፍስ ጸንተው ሕያዋን ሆነው የሚኖሩ ፍጥረቶች ናቸው።

## ረ) የዕለተ ዓርብ ፍጥረት ፤

በዚህም ዕለት ደግሞ ፬ ዓይነት ፍጥረታት ተፈጥረዋል ፤ እነርሱም ለምግብ የሚሆኑ እንስሳት ሲሆኑ በእግር የሚሽከረከሩ ፤ በክንፍ የሚበሩ ፤ በልብ የሚሳቡ ፤ ናቸው ፤ እነርሱም ሁሉ በየብስ የሚኖሩ ናቸው ፤ ፬ኛው ግን የዓለም ገዥ የሆነው ታላቅ ፍጥረት ሰው ነው ።

በዚህ መልክ ሲናገሩት የሥነ ፍጥረትም ተራና ቊጥር ሲገለጥ ፳፪ ይሆናል።

እግዚአብሔር ታላቅና ገናና እንደሆነ ፤ ሁሉን ለማድረግ ችሎታ ያለው እርሱ እንደሆነ ፤ ስለዚህም ሁሉን እርሱ እንደፈጠረ ያስተምሯቸዋል ።

እነዚህም ሁሉ በእግዚአብሔር ፈጣሪነት መፈጠር ብቻ ሳይሆን በእርሱም መጋቢነት ጸንተው እንደሚኖሩ ያስተምራሉ ፤ በእግዚአብሔርም ፈጣሪነት እንደ ተፈጠሩ ያስረዳሉ ፤ ሁሉም የእግዚአብሔር ፍጥረት ስለሆኑ ሁሉም ለከፍተኛ ዓላማ እንደተፈጠሩ በማመን የሰው ልጅ ሁሉ ለፍጥረቱ እንዲያዝን እንዲራራ በከንቱም እንዳያጠፋቸው ያስተምሯቸዋል ።

ይኸንንም እያንዳንዱን ፍጥረት በመዘርዘር ከፍ ያለም አገላለጥ በማድረግ ያስተምሯቸዋል ።

## ፪ኛ ፲ቱ ቃላተ ኦሪት ።

በሥጋችንም በነፍሳችንም በኲል ጸጋን ሰጥቶ ኑሮውን አቃንቶ ይኖር ዘንድ እግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ ሁኖ ለሰው ልጅ የሰጠው የመጀመሪያው ሕግ ፲ቱ ቃላት ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ሕግ በኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ተከብሮ ይኖራል ፤ ሊከበርም የቻለበት ምክንያት ፤

ሀ) በጥንት ዘመን የተቀበልነው ሕግ ስለሆነ በሕዝቡ የደም ሥር ሠርጾ ስለሚገኝ የሕግ ሕዝብም በመሆኑ ነው ።

ለ) ለተማሪዎች ከሕፃንነታቸው ጀምረው ዘርዝረው በማስተማራቸው ሕጉም አብሯቸው ስለሚያድግ ነው ።

እነዚህ ፲ ቃላትም ከሁለት ይከፈላሉ ፤ ይኸውም ፩ኛው ክፍል ፤ ለእግዚአብሔር የሚሆንና ፤ የእግዚአብሔርን ክብር የሚመለከት ነው ። ፪ኛው ክፍል ግን ሰው ለሰው አንድም ባልንጀራ ለባልንጀራው ሊያደርገው ሊፈጽመው የሚገባው ነው ፤ አንድም ሰው ሊርቀውና ሊሸሸው የሚገባውን የሚገልጥ ነው ።

ለአምላክ የሚሆኑ የመጀመሪያዎቹ አንቀጾች ፫ ናቸው ፤ እነርሱም ፤ ፩ኛ ከኔ ከአምላክህ በቀር ሌላ አምላክ አይኑርህ ፤ ፪ኛ የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው ፤ ፫ኛ የአምላክህን ሰንበት አክብር የተባሉት ሲሆኑ የቀሩት ፯ቱ ግን የሰውን ነገድ ብቻ የሚመለከቱ ናቸው ። ማለት አንዱ ለሌላው እርሱም ለመሰሉ ሊፈጽመው የሚገባው ነው ፤ የ፲ቱ ቃላትም ተራ እንደሚከተለው ነው ።

ባዕድ አምላክ አታምልክ
የአምላክህን ስም ከንቱ አታድርገው
የአምላክህን ሰንበት አክብር
አባትህንና እናትህን አክብር
አትግደል
አታመንዝር ።
አትስረቅ ።
በሐሰት አትመስክር
የባልንጀራህን ሀብት አትመኝ ።
ባልንጀራህን እንደራስህ አድርገህ ውደድ የሚል ነው ።

ብዙ ጊዜ የታወቀ ተራ ይኸ ይሁን እንጅ በየጊዜው ተራቸው እየተለዋወጡ በየመጻሕፍቱ ይገኛሉ ።

## ፫ኛ ፯ቱ ቃላተ ወንጌል ።

በሐዲስ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ወገኖቹን እንደጐበኘና እንደ ጠበቀ ለማጠየቅ እንደገና ሐዲስ ሕግን ሰጠ ፤ ይኸውም ፲ቱ ቃላትን የሚያጸና አንድም የሚፈጽም እንጅ የሚቃወም አይደለም ። ክርስቲያናዊ እምነታችን ፍጹም እንደ ሆነ ትምህርቱም አንድም ሕጉም ፍጹም እንደሆነ ለማጠየቅ ይኸን አስተማረን ።

www.ethiopianorthodox.org

አባቶቻችንም ይኽንኑ አምላካዊ ትእዛዝ ከሌላው ትምህርት አስቀድመው ለሕፃናት ያስተምሩት ነበር፣ ሕፃናትም ከልጅነታቸው ጀምረው ተምረውት ያደጉ ስለሆነ በልቡናቸው ተቀርጾ የሕግ ፈጻሚዎች ሁነው ይኖሩ ነበር ።

<u>፮ቱ ቃላተ ወንጌል የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው ።</u>

፩ኛ/ በወንድምህ ላይ በከንቱ አትቆጣ ።
፪ኛ/ ወደሴት ዓይተህ አትመኝ ።
፫ኛ/ ያለአንድ ምክንያት ሚስትህን አትፍታ ።
፬ኛ/ ፈጽማችሁ አትማሉ ።
፭ኛ/ ክፉውን በክፉ አትቃወሙ ።
፮ኛ/ ጠላታችሁን ውደዱ የሚል ነው ። ( ማቴ- ፭. ፳፩-፵፫ )

እንደሊቃውንቱ አስተያየትና አነጋገር ፮ቱ ቃላተ ወንጌል የተባሉት እነዚህ ይሁኑ እንጂ ሕዝቡ የሚቀበላቸው አንድም የሚያውቃቸው ግዴታም አድርጎ እስ ካሁን የሚፈጽማቸው ሌሎች ናቸው ፤ እነርሱም ፤ የሚከተሉት ናቸው ፤

፩ኛ/ ተርቤ አብልታችሁኛልና
፪ኛ/ ተጠምቼ አጠጥታችሁኛልና ።
፫ኛ/ እንግዳ ሁኜ ተቀብላችሁኛልና ።
፬ኛ/ ታርዤ አልብሳችሁኛልና ።
፭ኛ/ ታምሜ ጠይቃችሁኛልና ።
፮ኛ/ ታሥሬ ወደኔ መጥታችኋልና የሚል ነው ። (ማቴ-፳፭-፴፭)

እነዚህም ቃላተ ወንጌል እንደአጋጣሚ ፮ በመሆናቸው በተለይም በመጨ ረሻ ጊዜ አምላክ የሰውን ልጅ የሚጠይቅ እነዚህን ስለሆነ በእውነት ሕዝቡ አም ኖበት በሥራ ሲፈጽመው በነገር ሲወያየው የኖረና ያለም ነገር ነው ።

ሕዝባችንንም ሰላማዊ ሕዝብ አድርጎ እርስ በርስ በፍቅርና በመተባበር አስ ተሳሥሮ ያቆየው ቅሉ ይኸው አምላካዊ ቃል ነው ።

## ፬ኛ ፭ቱ አዕማደ ምሥጢር ።

፭ቱ አዕማደ ምሥጢር የተባሉት የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን የእምነት ውሳኔ የሚገለጥበት በረጅሙ ሆነ አንድም በአጭሩ የተወጣጣ አዋቂም ልጅም የሚማርበት ከጥንት ዘመን ጀምሮ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ዶክትሪን ነው ።

በዚህም ሃይማኖት ውሳኔ መሠረት ጠቅላላው ትምህርተ ክርስትና እንደ ሚገለጥበት የታመነ ነበር ፤ ስለዚህም የሕፃንነት ዕድሜ ያላቸውን ተማሪዎች ሳይ ቀር በጥያቄና በመልስ መልክ ያስተምራቸው ነበር ። ፭ቱ አዕማደ ምሥጢር የሚ ባሉትም የሚከተሉት ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ሀ) ምሥጢረ ሥላሴ ፤

ምሥጢረ ሥላሴ በማለት የሚያስተምሯቸው ትምህርት የሥላሴን ፫ትነትንና አንድነትን ምልዓትን ስፋትን ርቀትን ዘርዝሮ የሚያስረዳ ትምህርት ነው ።

ሥላሴ በስም ፤ በአካል ፤ በግብር ፤ ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ በህልውና በአምላክነት አንድነታቸውን ለማስረዳት እንደሚከተለው በጥያቄና በመልስ መልክ ያስተምራሉ ።

ጥ- ማን ፈጠረህ
መ- ሥላሴ
ጥ- ሥላሴ ስንት ናቸው
መ- አንድም ሦስትም ናቸው ።
ጥ- አንድነታቸው እንዴት ነው ።
መ- በባሕርይ በመንግሥት በሥልጣን አንድ ነው ።
ጥ- አብ ማለት ምን ማለት ነው ።
መ- አባት ማለት ነው ።
ጥ- ወልድ ማለትስ ።
መ- ልጅ ማለት ነው ።
ጥ- መንፈስ ቅዱስ ማለትስ ምን ማለት ነው ።
መ- ሠራፂ ማለት ነው ።
ጥ- የሥላሴ ሦስትነታቸው እንዴት ነው ።
መ- በስም ፤ በአካል ፤ በግብር ፤ ፫ ናቸው ።
ጥ- የአብ ግብሩ ምንድን ነው ።
መ- የአብ ግብሩ መውለድ ።
ጥ- የወልድስ ምንድን ነው ።
መ- የወልድ ግብሩ መወለድ ።
ጥ- የመንፈስ ቅዱስስ ግብሩ ምንድን ነው ።
መ- የመንፈስ ቅዱስ ግብሩ መሥረፅ ነው ።
ጥ- አብ ወልድን ከወለደ ፤ መንፈስ ቅዱስን ካሠረጸ ፤ አይበልጣቸውም አይቀድማቸውም ።
መ- አይበልጣቸውም አይቀድማቸውም ፤ ምክንያቱም ቅድምናቸው አንዲት ስለሆነች ነው ። በዚህ መልክ ስለ ሥላሴ ያለውን ምሥጢር ዘርዝረው ያብራሩና ያስረዱ ነበር ።

## ለ) ምሥጢረ ሥጋዌ ፤

ምሥጢረ ሥጋዌ ማለት ሰው የመሆን ምሥጢር ማለት ነው ። አምላክ በቸርነቱ የሰውን ባሕርይ ገንዘብ እንዳደረገ ፤ ስለዚህም ፍጹም ሰው እንደሆነ የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ናገር ትምህርት ነው ። በዚህም ውስጥ ስለ እግዚአብሔር ወልድ አምላክነት ማለት ስለፍጹም አምላክነቱ ስለ ፍጹም ሰውነቱ ከማስረዳቱ በላይ በወልድ ላይ የተነሡ ትንም መናፍቃን በማውገዝ እንዳለፈው በጥያቄና መልስ መልክ ያስተምራሉ ።

## ሐ) ምሥጢረ ጥምቀት ፤

በዚህም ትምህርት የሰውን ጥንተ ተፈጥሮ ፣ የኋላውን በደል ፣ በጥምቀት ምክንያት የሚሠረየውን ኃጢአት ፤ በጥምቀት የሚገኘውን ልጅነት ፣ በጥምቀት ፣ የሚጠፋውን ፍዳ መርገም ገልጠው ያስተምሩ ነበር ።

የዚህም ትምህርት አቅድ ከላይ እንደተናገርነው በጥያቄና መልስ መልክ ሲሆን ምሥጢረ ሜሮንንም አጠቃሎ የሚይዝ ነው ።

## መ) ምሥጢረ ቊርባን ፤

በዚህም ምሥጢር ካህኑ የሚፈትተው ኅብስት ፍጹም የክርስቶስ ሥጋ ፤ የሚቀዳው ወይን ደግሞ ፍጹም የክርስቶስ ደም እንደሆነ በቄሱ ሥልጣን ፤ በእግ ዚአብሔርም ቃል ኅብስቱና ወይኑ እንደሚለወጥ ያስተምራሉ ።

የክርስቶስን ሥጋ ያልበላ ደሙንም ያልጠጣ ሕይወት እንደማያገኝ ስለ ዚህም የሰው ልጅ ሁሉ ከሥጋውም መብላት ከደሙም መጠጣት እንዳለበት ያስ ተምራሉ ።

እንዴት መቍረብ እንደሚገባ፤ ለሚቈርበው ጥንቃቄን ፤ ምሥጢረ ንስሐን አስ ፋፍተው ይናገራሉ ፤ እነማን መቍረብ እንደሚገባቸው ገልጠው ያስተምራሉ ። በምሥጢረ ቍርባንም አብረው ምሥጢረ ክህነትን ሲያስተምሩ ይኖሩ ነበር ።

## ሠ) ምሥጢረ ትንሣኤ ሙታን ፤

በዚህም ትምህርት ውስጥ ፪ ነገሮችን ያስተምሩበት ነበር ፤ ይኸውም ፩ኛ ሰው ከፈረሰ ከበሰበሰ በኋላ እንደገና አካል ገዝቶ ፣ ሕይወት አግኝቶ ፣ ከሙታን ተለይቶ ተነሥቶ እንደሚኖር ሲሆን ፤ ፪ኛው ደግሞ ስለዓለም ፍጻሜ ፤ ስለኢየሱስ ፪ኛ መምጣት ነው ።

በዚህም ትምህርት የሰውን የመጨረሻ ዕድሉን ገልጠው ያስረዳሉ ማለት ሕይወትም ሞትም እንደሆን የክብሩን ደረጃ በመዘርዘር ወይም የሐሣሩን ደረጃ በመከተል ያስተምራሉ ።

በዚህም መልክ ፍጹም ክርስቲያናዊ እምነትን ሲያስተምሩ ኑረዋል ፤ ይኸ ንም ዓይነት ትምህርት ያላወቀ ክርስቲያን አይባልም ፤ ስለዚህ ከተግባረ ሥጋ አስ ቀድሞ ተግባረ ነፍስ መማር ግዴታ እንደሆነ ከዚያውም ውስጥ የመጀመሪያው ፭ቱ አዕማደ ምሥጢር እንደሆኑ ይሰብካሉ ያስተምራሉ ፣ ከዚህም ጋር ልዩ ልዩ የሆነ የእ ምነት ምዕላድን ያስተምራሉ ፤ ለምሳሌ መንገደ ሰማይ ሌላም ይኸን የመሰለ ፤ ሆኖም ግን በግልጥ የታወቀ ፭ቱ አዕማደ ምሥጢር የተባለው የእምነት ድንጋጌ ብቻ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ የምግባረ ሠናይ ትምህርት ።

ምግባረ ሠናይ ወይም ግብረ ገብነት እየተባለ የሚጠራው ትምህርት መን ፈሳዊ ሕይወት በወጣቶች ላይ አድሮ ይኖር ዘንድ ልዩ ልዩ ምሳሌዎችንና ሕጎችን በመጥቀስ ያስተምሯቸው የነበር ትምህርት ነው ፤ ከምሳሌዎችም ውስጥ የሲራክን የሰሎሞንን ምሳሌ በማስፋፋት ያስተምሯቸው ነበር ።

በዚያም ውስጥ ያለውን መንፈሳዊ ፍልስፍና ይገልጡላቸው ነበር ፤ ከሕግ ጋትም ውስጥ የግብረ ገብነትና የእምነት አንቀጽ ያለበትን ዲዲስቅልያን ያስተም ሯቸው ነበር ፡ እነዚህ ትምህርቶች ግዴታ እንደነበሩና ሁሉም ሊማራቸው አስፈ ላጊ እንደነበር የሚያመለክተው አስረጅ « መቅድመ መሀርዎሙ ለውሉድክሙ መጽሐፈ ሲራክ ፤ ወሰሎሞን ወመዝሙረ ዳዊት » ሲል የቤተ ክርስቲያናችን ሕግ ያውጃል ።

በዚህም መሠረት አባቶች መምህራን እነዚህን መጻሕፍት በብዛት ይጠ ቀሙባቸው ነበር ፤ ሕዝቡም በግብረ ገብነት የታነፀ በሕግም የሚራመድ የነበረው ከልጅነቱ በዚህ መልክ ቢማርና በዚህም መንፈስ ቢመራ እንደሆነ ሳይታለም የተ ፈታ ሳይነበብ የተተረጐመ ነው ።

ይኸ ነገር ግን ፤ እየቆየ በተለይም በአሁኑ ጊዜ እየተዘነጋ የሔደ ይመስ ላል ፤ ምክንያቱም በትእዛዙ መሠረት የሚማርም የሚያስተምርም የለምና ፤ እን ዲህ ነበር ወይም እንዲህ መሆን ይገባው ነበር በማለት ብቻ ይጠቀሙበታል ።

ምዕራፍ ፬ ።

## የቃል ትምህርት ።

የቃል ትምህርት የሚባለው በቃል ብቻ የሚጠና በልብም የሚያዝ አስተ ማሪውም በቃል ብቻ የሚነገረው ፤ ተማሪውም በዚህ መልክ ያለ መጽሐፍ በቃል የሚቀበለው የሚያጠናውም ትምህርት ማለት ነው ።

ይኸንም እንዲሁ ብዙ ጊዜ ማታ ማታ መጽሐፍ በማይዘረጋበት ጊዜ በቃል ያስተምሩታል ፡ ነገር ግን ለሁሉ የማታው ጊዜ የማይስማማ ስለሆነ ከሰዓት በኋላ ጊዜ ተመርጦለት ቃል ትምህርት ይሰጥ ነበር ።

የቃል ትምህርትም የሚባሉት ብዙዎች ሲሆኑ ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

### ፩ኛ ከበስመ አብ እስከ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል ።

ሀ) በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ ፤

ይኸም ሁሉም ያጠናው የነበር ትምህርት ነው ፤ ለማንኛውም ጀማሪ የሚ ሆን በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን የሚባል ጸሎት ነው ።


www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም ቃል የጸሎቱ ሁሉ መጀመሪያ የድንገተኛም ነገር ሁሉ መግለጫ ነው ፤ ትምህርቱንም «በመቀጠል በቅድስት ሥላሴ እንዘ አአምን» እያለ ይሄዳል ። ይኸ ፪ኛው አረፍተ ነገር ግን በኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚባል ሲሆን ጸሎት በተደረገ ጊዜ ከመጀመሪያው እስከ መጨረሻው ሁሉም ይደገማል ።

ነገር ግን ማን እንደደረሰው መቼስ እንደተደረሰ ግልጥ የሆነ ማስረጃ የለም ።

## ለ) ነአኵተከ እግዚኦ ወንሴብሐከ ፤

ይኸም ትምህርት ከበስመ አብ ቀጥሎ የሚጠና ሲሆን በኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚጸለይ ነው ፤ ስለዚህም በኛ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚያስተምሩት ሁኖ ይገኛል ፤ እርሱውም ልዩ ምስጋና የሆነ በጸሎት ጊዜያት የሚደገም ነው ።

ይሁን እንጂ ይኸም ቢሆን ማን እንደደረሰው መቼ እንደተደረሰ አይታወቅም ። (ከቅዳሴ ሐዋርያት እንደተወሰደ ይናገራሉ) ።

## ሐ) አቡነ ዘበሰማያት ፤

(ማቴ- ፮- ፱-፲፫) ይኸም ጸሎት በቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት መሠረት የጸሎት ሁሉ ማሠሪያ ስለሆነ በማንኛውም ጊዜያት የሚጸለይ ሁሉም የሚማረው ነው ፤ እንዲሁም ከማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚያስተባብር ጸሎት ነው ።

## መ) በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል መልአክ ፤

ይኸም ጸሎት ወይም የቃል ትምህርት ከአቡነ ዘበሰማያት ጋር በምንም ምክንያት በማንኛውም ጊዜ ሳይለይ የሚጸለይ ነው ።

እርሱም ከቅዱስ ወንጌል የተውጣጣ መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ቅድስት ማርያምን ያመሰገነበት አንቀጽ ነው ፤ (ሉቃስ - ፩-፳፮-፴፰) ። ለቅድስት ማርያም ምስጋና ለማቅረብ ከጌታ ጸሎት ጋር በማስተባበር ሁል ጊዜ እንዲደገም ቤተ ክርስቲያናችን የወሰነችው ጸሎት ነው ። በብዙዎች አብያተ ክርስቲያናት ያልተለመደ ጸሎት ነው ፤ ካቶሊኮች « አበ ማርያ » ከሚሉቱ ጋር የሚመስል ነው ። (በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ እንደተወሰነ ይናገራሉ ።)

# ፪ኛ ከጸሎተ ሃይማኖት እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ።

## ሀ) ጸሎተ ሃይማኖት ፤

ይኸም ትምህርት ለጸሎትም ለሃይማኖትም መረጃ ጠቃሚ ስለሆነ ሁሉም ይማረዋል ፤ እርሱም የኒቅያ ሲኖዶስ ውሳኔ ነው ። ይኸም ትምህርት አንድም ይኸ ጸሎት የጸሎት ሁሉ ማሠሪያ ማጠቃለያ እንደሆነ በቤተ ክርስቲያናችን ይታመናል ፤ ስለዚህም በጸሎት መጀመሪያ በጸሎትም መጨረሻ ይጸለያል ።

ከዓለም ቤተ ክርስቲያን ጋር የሚተባበር ጸሎት ነው ፤ እንዲሁም የክርስ

www.ethiopianorthodox.org

ትና አባትና እናት ለመሆን በግድ ይኸን ማጥናት ያሻል ፤ ሁሉ በክርስትና ጊዜ የሚደግሙት ነውና ፤ ስለዚህም ሁሉም በደንብ በቃላቸው ያጠኑታል ።

## ለ) ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እግዚአብሔር ፀባዖት ፤

ይኸም የእግዚአብሔር ምስጋና በቃል ትምህርት መልክ በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚጠናና የሚጸለይ ነው ።

ይኸም ትምህርት ከመጀመሪያው ግድም ከኢሳይያስ መጽሐፍ የተውጣጣ ይመስላል (ኢሳ ፮-፫) ሌላው ግን በሀገር ሊቃውንት የተደረሰና የተቀናበረ ነው ፤ ግን ፡ መቼ ማን ደረሰው የሚለው ፤ ጥያቄ ፤ አሁንም መልስ አያገኝም ።

## ሐ) ስብሐት ለአብ ፤ ስብሐት ለወልድ ፤ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ፤ የሚል ነው፤

በማንኛውም ጊዜ የሚጸለይ በተለይም ከምግብ በኋላ የሚጸለይ ጸሎት ነው፤ይኸ ውም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚባል የምስጋና ጸሎት ነው ፤ በቃል ትምህርት መልክ ሁሉ አብሮ ይማረዋል ።

ይኸም ድርሰት ማን እንደደረሰው መቼ እንደተደረሰ ግልጥ የሆነ አስረጂ የለውም ።

## መ) ሰላም ለኪ ፤ እንዘ ንሰግድ ንብለኪ ፤

ይኸ ጸሎት ስለቅድስት ማርያም የሚጸለይ ጸሎት ሲሆን የተለየ የቅድስት ማርያምን ምስጋና የርሷንም አማላጅነት የሚገልጥ ጸሎት ነው ።

ይኸውም በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ የሚጸለይ ጸሎት ነው ።

ይኸም ትምህርት በንባብ ብቻ ሳይሆን የዜማም መጀመሪያ ሆኖ ይገኛል ፤ ማለት ዜማ የማያውቀውን ሰው ሲሰድቡት «ገና ሰላም ለኪ ያላለ» ይሉታል ፡ ይኸም ማለት ዜማ ያላወቀ ማለት ነው ፤ ዜማን የጀመረ ሁሉ እርሷን የማያውቅ የለምና ።

ይኸም ቢሆን ከላይ እንደተገለጠው ሁሉ ደራሲውና የተደረሰበት ጊዜ አይ ታወቅም ።

## ሠ) ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ፤

ይኸም ትምህርት ከሰላም ለኪ ቀጥሎ በንባብ መልክ የሚያጠኑት ነው (ሉቃስ ፩፡፵፮-፶፭) ሰላም ለኪ በዜማ ከተባለ በኋላ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም ሁልጊዜ በድጋም ብቻ የሚባል ጸሎት ነው ፤ ጸሎቱንም የደረሰችው ቅድስት ማርያም ናት ።

እነዚህ ከዚህ በላይ የተገለጡት የቃል ትምህርቶች ሁሉ በመጽሐፍ ቅዱስ ከተገለጡትና ከጸሎተ ሃይማኖት በቀር ማን እንደደረሳቸውና መቼ እንደተደረሱ ግልጥ የሆነ አስረጂ የለም ፤ የሚያስደንቀው ግን ፤ ከማንም ያልተወረሱ ኢትዮጵያውያን ድርሰቶች ሁነው በመላ ኢትዮጵያ ሕዝብ ኦርቶዶክስ እምነት ባለው ሁሉ በትክ ክል የሚጠኑ መሆናቸው ነው ። እንደዛሬ ሳይሆን ትንሽ ቀደም ብሎ ክርስቲያኑ

www.ethiopianorthodox.org

ሕዝብ ሁሉ እነዚህን ትምህርቶች ሁሉ ያጠናቸዋል ፤ ያለመጨመርም ያለመቀነስም ዳር እስከ ዳር ሁሉም በዚሁ መልክ ይማራቸው ይጸልያቸውም ነበር ።

## ፫ኛ ውዳሴ ማርያም ።

ይኸም ድርሰት የቃሉ ትርጉም እንደሚያስረዳው የቅድስት ማርያምን ምስ ጋና የሚናገር ነው ።

ውዳሴ ማርያም የተባለውን ጸሎት የደረሰው ቅዱስ ኤፍሬም ሲሆን ሀገራ ችን የቅድስት ማርያም አሥራት እንደሆነች በማመን ክርስቲያኑ ሕዝብ ሁሉ ያመ ሰግናት ዘንድ ተተርጉሞ ለሁሉም ተዳረሰ ።

ግን ማን ተረጐመው መቼ ተተረጐመ ለሚለው ጥያቄ አሁንም አጥጋቢ መልስ የለውም፤ይሁን እንጂ አሁን በዜማ፤በንባብ፤በትርጉም፤የሚደረስ የተከበረ ድርሰት ነው ።

ይኸ ውዳሴ ማርያም የተባለ ድርሰት የቅዱስ ኤፍሬም ሲሆን በግጥም መልክ የተደረሰ ነበር ፤ ወደ ግዕዝ ሲተረጐም ግን ግጥምነቱን አጥቷል ።

በጥንት ጊዜ በጸሎት ሶርያውያን ይጠቀሙበት ነበር ይባላል ፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ከኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በቀር በጸሎት የሚጠቀምበት የለም ፤ ለትርጉሙ ግን ከኮፕት ወደ እንግሊዝኛ ተተርጉሞ ይገኛል ።

ይኸም ውዳሴ ማርያም የተባለው ለጸሎት ለሃይማኖትም ተፈላጊ በመሆኑ ሁሉ ያጠናው ወይም ይጸልየው ዘንድ የተለየ የዕለት ጸሎት አለው ።

የየአንዳንዱ ቀንም ውዳሴ ማርያም በቍጥር የተለያየ ነው ማለት ፤ ረጅምና አጭር አለው ፤ ለሁሉም የተወሰነ ቍጥር የለውም በያንዳንዱ ውዳሴ ማርያም መጨረሻ ግን ሰአሊለነ ቅድስት (ቅድስት ለምኝልን) የሚል መርገፍ አለው ። ይኸውም መርገፍ የጸሎቱ ማሣረጊያ ወይም ማሠሪያ ነው ። ይኸንም የመሰለ በዳዊት መዝሙር መጨረሻ ላይ ስብሐት ለአብ ፤ ወወልድ ፤ ወመንፈስ ቅዱስ የሚል መርገፍ ወይም ማሠሪያ አለው ፤ ይሁን እንጅ ይኸን ሰአሊለነ ቅድስት የሚለውን ቃል ቅዱስ ኤፍሬም አልደረሰውም ለዜማ ስልት ለመስጠት ወይም ማስማሚያ ይሆነው ዘንድ ቅዱስ ያሬድ እንደደረሰው የሚናገሩ ሊቃውንት አሉ ፤ እንዲሁ ደግሞ ስለቅድስት ማርያም ፍቅር በየመጨረሻው የኋላ ሊቃውንት አስማሙት የሚሉ አሉ ።

የሆነ ሆኖ የሰባት ቀን ውዳሴ ማርያም የሚባለው ከዚህ የሚከተለው ነው ።

ሀ) የሰኞ ውዳሴ ማርያም ፱
ለ) የማክሰኞ ውዳሴ ማርያም ፲፩
ሐ) የረቡዕ ውዳሴ ማርያም ፳
መ) የሐሙስ ውዳሴ ማርያም ፯
ሠ) የዓርብ ውዳሴ ማርያም ፮
ረ) የቀዳሚት ውዳሴ ማርያም ፲
ሰ) የእሑድ ውዳሴ ማርያም ፱

www.ethiopianorthodox.org

ውዳሴ ማርያም ሁሉም ተጠቃሎ ሲደመር ፷፬ ይሆናል ፤ ይኸውም ቍጥር በቅድስት ማርያም ዕድሜ ልክ የተደረሰ መሆኑን ያመለክታል ፤ በዚህም ቍጥር ልክ እመቤታችንን ለማመስገን የተወሰነ ጸሎት ነው ።

ይኸ ጸሎት ግን የሚጸለየው እንደ ሰውየው ችሎታ ነው ፤ ማለት የሰባቱን ዕለታት በአንድ ጊዜ የሚጸልይ ሰው አለ ፤ የየዕለቱን ብቻ የሚጸልይ አለ ፤ በጧትና በማታ የሚጸልይ አለ ፤ በትምህርት ቤት ግን ሁሉም ለያንዳንዱ የግሉ ሁኖ እንደተቻለው ይጸልይ እንጅ የማታው ጸሎት የግድ የማኅበር ጸሎት ሁኖ በዜማ ይደረሳል ፤ ስሙም ማስታኰት (ማመስገን) ይባላል ።

## ፬ኛ አንቀጸ ብርሃን ።

አንቀጸ ብርሃን ማለት የብርሃን በር ማለት ነው ፤ የርሱም ቍጥሩ ፲፪ የሆነ ቅዱስ ያሬድ ስለመቤታችን ምስጋና የደረሰው ድርሰት ነው ።

፲፪ትም ቍጥር የሆነበት ምክንያት ቅዱስ ያሬድ በጥንት ዘመን በአክሱም ቤተ ክርስቲያን ዓምድ ልክ ስለደረሰው ነው ፤ በበሩም ቍጥር ስለደረሰው አንቀጸ ብርሃን፡ ተብሏል የሚሉ አሉ ።

ይኸን ጸሎት አንዳንዶቹ መምህራን ከውዳሴ ማርያም ቀጥሎ ያስተምሩታል ፤ ሌሎቹ ደግሞ በዚህን ጊዜ ያልፉትና በኋላ በምዕራፍ ትምህርት ጊዜ ከዜማው ጋር አብረው ያስተምሩታል ይማሩታል ። በጸሎት ጊዜ ግን ምንም ቢሆን ከእሑድ ውዳሴ ማርያም አይለዩትም አብረው ይጸልዩታል ፤ አንድም የሰባት ቀን ውዳሴ ማርያም በአንድ ጊዜ ከተደገመ ይኸንም አይተውትም አብረው ይጸልዩታል ።

## ፭ኛ መልክአ መልክ ።

መልክአ መልክም ማለት ፤ የአንዱን ቅዱስ አካል በመዘርዘር ምስጋና ማቅረብ ነው ።

የአንዱን ቅዱስ የራስ ጠጕር የእጁንና የእግሩን ጥፍር ሳይቀር እንዲሁም ንዋየ ውስጡን በመዘርዘር እየጠቀሱ ምስጋና ያቀርቡለታል ፤ በዚህም መልክ የሚጸለየው ሁሉ መልክአ መልክ ይባላል ።

ድርሰትነቱም የኢትዮጵያውያን ነው ፥ በዚህም መልክ የምትጠቀም የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ብቻ ናት ፤ ሌሎችም ቢሆን መልኩ ለወጥ ይበል እንጅ ስለ ጻድቁ ስለ ቅዱሱ ክብር በሌላም መልክ ምስጋና ያቀርቡለታል ፤ በኛ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ተብሎ ጽላት ተቀርጾለት ቤተ ክርስቲያን ታንፆለት ይኸ ዓይነት ምስጋና ያልተደረሰለት አይገኝም ።

ሆኖም ደራሲው የተለያየ ጊዜውም የተለያየ ነው ፤ ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን እንመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org

ከአንገት በላይ ያሉትን ሕዋሳት የሚመለከት ።

ለዝክረ ስምከ ።
ለሥዕርተ ርእስከ ።
ለርእስከ ።
ለገጽከ ።
ለቀራንብቲከ ።
ለአዕይንቲከ ።
ለአእዛኒከ ።
ለመላትሒከ ።
ለአእናፊከ ።
ለከናፍሪከ ።
ለአፉከ ።
ለአስናኒከ ።
ለልሳንከ ።
ለቃልከ ።
ለእስትንፋስከ ።
ለጕርዔከ ።

ከአንገት በላይ ያሉትን ክፍሎች ምንም ሳይቀላቅል ለይቶ ተናገረ ፤ ይኸም ክፍል የሰው ልጅ ሁሉ የማሰቢያው ክፍል ስለሆነ በፈላስፎችና በአዋቂዎች ይመሰላል ።

መካከለኛውን የአካል ክፍል በመለየት ሲናገር ደግሞ ።

ለክሣድከ ።
ለመትከፍትከ ።
ለዘባንከ ።
ለእንግድዓከ ።
ለሕጽንከ ።
ለአእዳዊከ ።
ለመዛርኢከ ።
ለዘርናዕከ ።
ለእመትከ ።
ለእራኅከ ።
ለአፃብዒከ ።
ለአጽፋረ እዴከ ።
ለገቦከ ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ክፍል ደግሞ ኃይል የሚገለጥበት ሥራ የሚሠራበት ክፍል ስለ ሆነ በኃያላኑ ፍጥረታት ይመሰላል ።

ንዋየ ውስጥን በመለየት ሲነገር ።

ለከርሦከ ።
ለልብከ ።
ለሕሊናከ ።
ለኅንብርትከ ፤ እያለ ይሄዳል ።

ይኸ ክፍል ደግሞ ያልታወቀውን ያልተመረመረውን ዓለም የሚያመለክት ሁኖ ይገኛል ።

ከሐቌ እስከ እግር ጥፍር ያለውን በመለየት ።

ለሐቌከ ።
ለአቍያጺከ ።
ለአብራኪከ ።
ለአእጋሪከ ።
ለሰኰናከ ።
ለመከየድከ ።
ለአጻብዒከ ።
ለአጽፋረ እግርከ ፤ እያለ የሚሔድ ነው ፤

ይኸም ክፍል ደግሞ ሠራተኛውን ዓለም የሚመለከት ሁኖ ይገኛል ።

ጠቅላላ አቋምና ሥነ ላህይን በመለየት ፤

ለቆምከ ።
ለመልክእከ ።

ይኸ ክፍል ግን ከላይ በልዩ ልዩ ክፍል የገለጥናቸውን ሁሉ አንድ አድርጎ አጠቃሎ የሚያሳይ ነው ።

ከየመልኩ ውስጥ አንዳንድ ለየት ያለ ይገኛል ፤ ማለት የሚጨምርም የሚቀንስም አለ ፤ ሁኖም ክፍሉ ይኸን በመሰለ መንገድ የሚሄድ ነው ። ድርሰቱም ፍጹም ኢትዮጵያዊ የሆነ ከማንም ያልተቀዳ ነው ።

በትምህርት ቤት ግን ጠንቅቀው የሚያስተምሩት ።

ሀ) መልክአ ማርያምን ።
ለ) መልክአ ኢየሱስን ብቻ ነው ።

ሌላውን መልክአ መልክ ግን እያንዳንዱ ተማሪ እንደ ቅዱሱ ፍቅር በግሉ ያጠናዋል እንጅ በትምህርት ቤት አይማረውም ።

www.ethiopianorthodox.org

በድጋም ወይም በንባብ መልክ ብቻ ማታ ማታ የሚጠናው የቃል ትምህርት አንድም የጸሎት ስልት በዚህ ይፈጸማል ። ማንኛውም ሰው ሁሉ ስለ ቃል ትምህርት የሚወሰነው በዚህ ብቻ ነው ፤ የቀረው ቀርቶ በጥንት ዘመን ዲቁና የሚቀበለው ወጣት እንኳን በቃል ትምህርትም በንባብም በጽሕፈትም እስከዚህ ከደረሰ በኋላ ነበር ፤ ከዚህ ሳይደርስ ዲቁና እንዳይቀበል ፈተና ነበረበት ፡ ስለዚህም ከዚህ ለመድረስ ታላቅ ጥረትን ያደርግ ነበር ፤ ይኸን ከፈጸመ በኋላ ግን ወደ የግል ዕድሉ አንድም ወደ ልዩ ልዩ ሥራው ይሠማራ ነበር ። በእርግጥም ትምህርታቸውን ለመግፋት ፍጹም ሊቅ ለመሆንም ዕድሜ ልካቸውን ከሀገር ወደ ሀገር እየተዘዋወሩ የሚያጠኑ ነበሩ በዚህም ብቻ ተወስነው የሚኖሩ እንደነበሩ የታወቀ ነው ።

## ልዩ አስተያየት ፤

፩- በቀንም በማታም ይማሩት የነበር ይኸ ትምህርት ከፍተኛ ተብሎ ይገመት ነበር ፡ ስለዚህም በጸሎት ጊዜ በቃል ትምህርቱም በዳዊቱም ተሳታፊ የማይሆን ሁሉ ያፍር ነበር ።

፪- ይኸን የመሰለ የጸሎት ስልት ለኢትዮጵያ ብቻ ነው ፡ በቤተ ክርስቲያንም ቢሆን ደንበኛው ጸሎት ይኸ ሁኖ ሳይፈጸም የቀረ እንደሆን ጸሎቱ እንደታጐለ ይገመታል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ።

# የዜማ ቃል ትምህርት ።

### ምዕራፍ ፩ ።

## ዜማ በጠቅላላው ።

ዜማ ማለት በጠቅላላ አነጋገር ጩኸት ፤ ድምፅ ማሰማት ማለት ነው፤ ከዚህ ላይ ግን ዜማ ባልን ጊዜ የምስጋና መዝሙር የደስታ ድምፅ ማለት ይሆናል ፤

ይኸውም ዘመረ አመሰገነ ፤ አዜመ ካለው ቃል ጋር ይመሳሰላልና ። የሆነው ሆኖ ዜማ ማለት ለምስጋና ብቻ ሳይሆን የልቅሶ ፤ የቀረርቶ ፤ የሽለላ ፤ የፉከራ ፤ የኀዘን ፤ የደስታ ይኸን የመሰለውን ስሜት ሁሉ መግለጫ የሆነው ድምፅ ነው ፤

ለቤተ ክርስቲያን ማገልገያ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቢያ የሆነው ይኸ ጩኸት አንድም ድምፅ ዜማ ይባላል ።

የዚህም የቤተ ክርስቲያን ዜማ ደራሲው ቅዱስ ያሬድ የተባለ የኢትዮጵያ ሊቅ እንደሆነ የታወቀ ነው ።

እርሱም መጀመሪያ ዜማውን በአርያም ጀምሮ እንደነበር ራሱ ሲመሰክር «ቀዳሚ ዜማ ተሰምዐ በሰማይ» እያለ ይሄድ ነበር ፥ በአሁኑ ጊዜ ግን የዜማው ትምህርት ሲጀመር በሰላም ለኪ አንድም በውዳሴ ማርያም ነው ፤

ይኸም ለውጥ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ ለምን እንደተለወጠ አይታወቅም ፤ ይሁን እንጂ ከዚህ ጀምሮ ያለው የዜማ ትምህርት ሁሉ የቃል ትምህርት ይባላል ። የዚህም የአርያም ዜማ አደራረስ በዓራራይና በግዕዝ ሲሆን ሰላም ለኪ ብሎ የመጀመሪያው ዜማ ግን ከሰኞ እስከ ቅዳሜ ያለው የውዳሴ ማርያም ዜማ ዓራራይ ብቻ ነው ፤ ሰላም ለኪ ግን ግዕዝም ዕዝልም ይሆናል ፤ ለምሳሌ የሰንበት ቀን ውዳሴ ማርያም ዜማ ዕዝል ይሆናል ፤ ከዚህ ከውዳሴ ማርያም በላይ ያለው ትምህርት ለምሳሌ የመወድስ የምዕራፍ ዜማ ሁሉ የቃል ትምህርት ሲባል የዜማው ዓይነት ግን በ፫ቱም ዓይነት ዜማዎች ይደርሳል ፤ ማለት ግዕዝም ዕዝልም ዓራራይም ይሆናል ፤ ቅደም ተከተሉ ግን የሚከተለው ነው ።

## ፩ኛ የውዳሴ ማርያም ዜማ ።

የዜማ ቃል ትምህርት መጀመሪያው ውዳሴ ማርያም ነው፤ይኸን ትምህርት ጀማሪዎች ሁሉ እርሱን በትጋት ካጠኑ በኋላ ወደሌላ ይተላለፋሉ።ውዳሴ ማርያምን በንባብ ከሚማሩትና ለጸሎት ከሚደግሙት ሌላ ሀ/ በማስታኮት ጸሎት ጊዜ በዜማ ያደርሳሉ ።

ለ/ የዓመት በዓል በተከበረበት አደራረስም በደረሰ ጊዜ እንደ አንድ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተቈጥሮ በዜማ ይደርሳል ።

www.ethiopianorthodox.org

የዚህም ዜማ ደራሲ እንደሌላው ሁሉ ቅዱስ ያሬድ ሲሆን ንባቡን የደረሰው ግን ቅዱስ ኤፍሬም ሶርያዊ እንደሆነ የታወቀ ነው ።

## ፪ኛ መስተጋብእ ።

መስተጋብእም ማለት እስትጉቡእ (ስብስብ) የተከማቸ ማለት ነው ፤ ይኸውም ከዳዊት መዝሙር ከ፩፻፶ው ውስጥ ከየዕለቱ ለጸሎትና ለዝማሬ ተስማሚ የሆነው እየተውጣጣ ለመዝሙር ተስማሚ የሆነው የተቀመረ ነው ። የዚህም ዜማ ደራሲ ያው የታወቀው ታላቅ ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ሲሆን እርሱም መስተጋብእን ሲጀምር «ወለቡ ጽራኅየ» ጩኸቴን ልብ አድርግ ብሎ ይጀምራል ።

ይኸንም ሁለተኛ የዜማ ትምህርት አድርገው ሊቃውንት ያስተምሩታል ፤ ተማሪዎችም በዚሁ መልክ ይማሩታል ፤ ለአገልግሎትም ጊዜ ቢሆን በዓቢይ ጾም ሁልጊዜ ከሰኞ እስከ ቀዳሚት ድረስ በጧት ይዘመራል ፤ የቀድሞ አባቶች ግን የቅድስት ማርያምን ክብር ለመግለጥ ሲሉ በፍልሰታ ጾምም ይዘምሩት ነበር ይባላል ።

ይኸም ዜማ ከሰኞ እስከ ቅዳሜ በየዕለቱ የተለየ የተወሰነም መዝሙር ስላለው የዕለቴ እየተለየ በየጊዜው ይዘመራል ። ዜማውም በግዕዝና በዕዝል ብቻ ይወሰናል ፤ ነገር ግን ከሐሙስ አንድ ፤ ከቅዳሜም አንድ ብቻ ዓራራይ ዜማ ይገኝበታል ፤ ይኸውም ከሐሙስ ውስጥ የሚገኘው « አንተስ እግዚኦ ለዓለም ትነብር ወዝክርከኒ ለትውልደ ትውልድ » የሚለው ሲሆን ከቅዳሜ ደግሞ « መንግሥትከሰ መንግሥት ዘለኵሉ ዓለም ወምኵናኒከኒ ለትውልደ ትውልድ » የሚል ነው ።

የመስተጋብእ ዜማ በመላ ከዳዊት መዝሙር የተውጣጣ ነው ብለናል ፤ ነገር ግን አንድ ብቻ በመስተጋብእ መጨረሻ ላይ የሚገኝ ልዩ ድርሰት አለ ፤ እርሱም ዳዊትን የማይነካ ሲሆን የሚከተለው ነው ፤ «አድኅነ ሕዝቦ በኃይለ መስቀሉ እስመ ብርሃን ሠረቀ» የሚል ነው ።

መስተጋብእ የተባለው የቃል ትምህርት ድምሩ ፩፻፶ ሲሆን በጠቅላላው የሚሰጠው አገላለጥ የአምላክን ምስጋና ለማቅረብ የሚደረስ መሆኑን ነው ፤ ብዙ ጊዜም የሚነገረው የዳዊት ቃል ብቻ ነው ።

መስተጋብእ የሚባሉበት ቀኖችና የዜማው ዓይነት የሚከተለው ነው ።

| ቀኖች | የዕዝል ቍጥር | የግዕዝ ቍጥር |
|---|---|---|
| ሰኞ | ፲፭ | ፳፬ |
| ማክሰኞ | ፲፭ | ፲፰ |
| ረቡዕ | ፲፭ | ፲፬ |
| ሐሙስ | ፲፭ | ፲፯ |
| ዓርብ | ፲፪ | ፲፫ |
| ቅዳሜ | ፲፭ | ፳ |

www.ethiopianorthodox.org

## ፫ኛ አርባዕት ።

አርባዕት ማለት አራት ፤ አራተኛ ማለት ነው ፤ ምክንያቱም በዳዊት መዝሙር በአራተኛው መሥመር ውስጥ እየገባ የሚዘመር ቅዱስ ያሬድ የደረሰው መዝሙርና ጸሎት ነው ፤ ይኸውም «ቃልየ አጽምእ እግዚኦ ፤ ወለቡ ጽራኅየ ፤ ወአጽምአኒ ቃለ ስእለትየ ፤ ንጉሥየኒ ወአምላኪየኒ » ብሎ አራቱን ቊጥሮች አንድም ፬ቱን መሥመሮች ዘምሮ ከፈጸመ በኋላ አርባዕት የተባለው የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ይገባል ፥ ስለዚህ ስሙን አርባዕት ብለውታል ።

አርባዕት ሲጀመር ፤ ቃልየ ፤ ከመ ያፈቅር ፤ ጐሥዓ ፤ ዓቢይ ፤ ተሠሃለኒ ፤ ብሎ ነው ፤ እርሱም በግጥም መልክ የተቀመረ ነው ፤ ለምሳሌ « ኮከብ መርሆሙ ፤ ቤተልሔም አብጽሆሙ ፤ ወቆመ መልዕልቴሆሙ ፤ ወዜነዎሙ ፥ ዓቢየ ዜና ዘይከውን ሎሙ ነገሮሙ » የሚል ነው ።

እንዲሁም በስድ ንባብ የሆነ ይገኛል ፤ ይኸም ምሳሌ አለው ፤ አራት መዝሙር መሆኑ የ፬ቱ ኪሩቤል ምሳሌ ነው ፤ በዳዊት መዝሙር እየገባ መባሉ ደግሞ ጌታ በዳዊት መዝሙርና ቃል ምስጋና ይገባዋል ለማለት ነው ። የአርባዕትም እንዲሁ የተለየ ዜማ ግዕዝ ዕዝል ዓራራይ አለው ፤ እንዲሁም የሚዘመርበት የተለየ ዕለት የተለየም በዓል አለው ፤ አርባዕት የተባለው ድርሰት ሲጀመር በዳዊት መዝሙር ይጀምር እንጂ በኋላ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ይቀጥላል ፤ እርሱም በግጥም መልክ የተዘጋጀ ነው ። ስሙና ቊጥሩ ግን እንደሚከተለው ነው ።

### የአርባዕት ስምና ቊጥር ።

የሰኞ ፤

፩ኛ/ አጥመቀ
፪ኛ/ ኮከብ መርሆሙ
፫ኛ/ ዘረሰዮ
፬ኛ/ እስመ አንተ ባሕቲትከ ንጉሥ
፭ኛ/ አፍቅር ቢጸከ
፮ኛ/ ዓርገ ሐመረ

የማክሰኞ ፤

፩ኛ/ አምላከ አዳም
፪ኛ/ አንትሙ ውእቱ
፫ኛ/ ወይቤሎሙ ዮሐንስ ለሕዝብ
፬ኛ/ ሐጸበሙ እገሪሆሙ
፭ኛ/ ሀቡ ስብሐተ

www.ethiopianorthodox.org

**የረቡዕ ፤**

፩ኛ/ ተንሥኡ ንሑር
፪ኛ/ ኒቆዲሞስ አምጽአ
፫ኛ/ ዘመጽአ እምድኅረ
፬ኛ/ ብፁዕ አንተ ዮሐንስ
፭ኛ/ ዘመራህከሙ ለሕዝብከ
፮ኛ/ ኃያላን ሰብእ

**የሐሙስ ፤**

፩ኛ/ ዛቲ ዕለት
፪ኛ/ ሰንበት አሜሃ
፫ኛ/ ወይሡዑ ሎቱ መሥዋዕተ ስብሐት
፬ኛ/ ንልበስ ወልታ ዘብርሃን
፭ኛ/ ዘይገለብቦ ለሰማይ በደመና
፮ኛ/ ናሁ ሠናይ

**የዓርብ ፤**

፩ኛ አብርህ ለነ
፪ኛ/ በከመ ይቤ
፫ኛ/ ለከ ስብሐት
፬ኛ/ ዘበዳዊት ተነበየ
፭ኛ/ ናሁ ብርሃናት

**የቅዳሜ ፤**

፩ኛ/ ብርሃን ዘይወጽእ
፪ኛ/ ሠርዓ ሰንበተ
፫ኛ/ አፃብኢሁ ፍሑቃት
፬ኛ/ ዘጌሠ ኃቤሃ
፭ኛ/ ለቤተ ክርስቲያን የሚለው ነው ።

የአርባዕት ጠቅላላ ድምሩ ፴፫ ይሆናል ። ነገር ግን ትርፍ የተባሉትን ሰባቱን የጨመርን እንደሆን ፵ ይሆናሉ ፤ ትርፍም የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው ።

## የአርባዕት ትርፍ ።

ሐጸቦሙ እገሪሆሙ ፤ ተፈሥሒ ጽዮን ፤ ቅኔ ደብተራ ፤ አእትት እከየ ፤ ጸርኀ ኢሳይያስ ፤ ዓራራተ ነበረት ታቦት ፤ በመስቀልከ አብራኅከ ለነ ፤ እነዚህ ፯ቱ ትርፍ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

አርባዕት የሚደረስበት ጊዜ ወይም የሚባልበት ቦታ መወድስ በደረስ በት ጊዜ በየሳምንቱ እሑድ ነው ።

## ፬ኛ አርያም ።

አርያም ማለት ልዑል አንድም ከፍተኛ ማለት ነው ፤ ነገር ግን ከዚህ በላይ በአርያም የተሰማ ድርሰት ስለሆነ አርያም ተብሏል ። ምክንያቱም ቅዱስ ያሬድ በተመስጦ ጽርሐ አርያም ወጥቶ መላእክት ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ እያሉ ሲያ መሰግኑ ሰምቶ ድርሰቱን በአርያም ጀምሯል ስለሚባል አርያም ተብሏል ይባላል ። እርሱም «ቀዳሚ ዜማ አንድም ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ» የሚል ነው ፤ እንዲ ሁም ከመላእክት ሰምቶ ስለአመጣው በአርያም የተገኘ ዜማ ለማለት ስሙን አር ያም ብለውታል ።

ይኸውም ሃሌ ሉያ ለአብ ፤ ሃሌ ሉያ ለወልድ ፤ ሃሌ ሉያ ለመንፈስ ቅዱስ ብሎ የግጥም መልክ ባለው አርያም በተባለው ይጀምራል ፤ ምሥጢሩም ቅድመ ዓለም ለነበሩ ዓለምን አሳልፈው ለሚኖሩ ሥላሴ ምስጋና ይገባል የሚል ነው ።

ይኸ አርያም የተባለው ድርሰት ከፍ ያለ የግጥም ሞያን የሚያሳይ ነው ፤ ለምሳሌ «ኃላፊ ንብረት ፤ ከመ ጽላሎት ፤ ወከመ ልብሰ ኅሰት ፤ የምኬ ሰብእ ወኄ ሰመ መሬት» ይላል ። እንዲሁም በስድ ንባብ ደግሞ ይገኛል ፤ ለምሳሌ «በዕን ንቈ ሰንፔር ትትሐነፅ ወበመረግድ ፤ ሃሌ ሉያ ለአብ ፤ ሐፁር የዐውዳ ትበርህ እም ከዋክብት ፤ ሃሌ ሉያ ለወልድ ፤ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ጽዮን ቅድስት ቤተ ክርስቲያን ደብተራ ፍጽምት» ሲል ይገኛል ።

አርያም በዕለት የተለየ ግዕዝ ዕዝል ዓራራይ ዜማ ያለው ጸሎት ሲሆን የሚባልበት ጊዜ ደግሞ በጾም ጊዜ በጾመ ድጓው እየገባ ነው ፤ በተለይም በክብረ በዓል ክሥተት አርያም ሲደረስ ይዘመራል ።

## የአርያም ስምና ቍጥር ።

የሰኞ ፤

፩ኛ/ ቀዳሚ ዜማ
፪ኛ/ ይገብሩ በዓለ
፫ኛ/ ቃለ ዓዋዲ
፬ኛ/ አክሊለ ሰማዕት
፭ኛ/ ተከሥተ አፉሁ
፮ኛ/ ዮሐንስ ስሙ

www.ethiopianorthodox.org

፯ኛ/ አጥመቆሙ ዮሐንስ
፰ኛ/ ዴግንዋ ለፍኖተ ሕይወት
፱ነኛ/ እስመ በትሕትና
፲ኛ/ እስመ ዋካ ይእቲ
፲፩ኛ/ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን
፲፪ኛ/ ኃላፌ ንብረት

<u>**የማክሰኞ**</u> ፤

፩ኛ/ ካህን ወነቢይ
፪ኛ/ ለዘገብርኤል
፫ኛ/ ተሰፍሐ ትፍሥሕት
፬ኛ/ ከመ ቀስተ ደመና
፭ኛ/ ግነዩ ለአምላክ አማልክት
፮ኛ/ ትጉሃን እለ ኢይነውሙ
፯ኛ/ ዘልዑል እምሰማያት
፰ኛ/ ይትዓየን መልአከ እግዚአብሔር
፱ነኛ/ ረኪቦሙ ሕፃነ

<u>**የረቡዕ**</u> ፤

፩ኛ/ ተበሃሉ በበይናቲሆሙ
፪ኛ/ ይቤ እስጢፋኖስ አንሰ ርኢኩ
፫ኛ/ ለዘዓርገ ውስተ ሰማያት
፬ኛ/ አዋልደ ንግሥት
፭ኛ/ አክሊሎሙ ለሰማዕት
፮ኛ/ ፃኡ ተቀበሉ መርዓዌ
፯ኛ/ ወሰኑ ወሠርዑ ሃይማኖተ
፰ኛ/ ጽድቅ ውእቱ ስምከ
፱ነኛ/ ዕዝራኒ ርእያ

<u>**የሐሙስ**</u> ፤

፩ኛ/ ፀወንነ ወኃይልነ
፪ኛ/ ይቤልዎ ሕዝብ ለዮሐንስ
፫ኛ/ አረጋዊ አንግሃ ገይሠ
፬ኛ/ መስቀልከ እግዚኦ
፭ኛ/ በመስቀሉ አተበነ
፮ኛ/ ሚካኤል ብሂል
፯ኛ/ በመዳልው ደለወ ዓለመ

www.ethiopianorthodox.org

**የዓርብ ፤**

፩ኛ/ ለካህናት አሠርገዎሙ
፪ኛ/ ጸለየ ዓዛርያ
፫ኛ/ ባረኮ ለሕፃን
፬ኛ/ ኃረየ አሠርተ ወክልኤተ
፭ኛ/ ሕንፄሃ ወሱራሬሃ አዳም
፮ኛ/ አዳም ወሠናይት
፯ኛ/ ሕንፄሃ ወሱራሬሃ
፰ኛ/ ሥላሴ ዋሕድ
፱ነኛ/ በእንቄ ሰንፔር

**የቅዳሜ ፤**

፩ኛ/ ንሴብሖ ወንዜምር
፪ኛ/ ከሠተ ለነ
፫ኛ/ ዋካ ወብርሃን
፬ኛ/ እምጽዮን ነበበ
፭ኛ/ ተዘከርኩ በሌሊት
፮ኛ/ መስቀል ሞዓ ፤ ሞት ተሞዓ
፯ኛ/ ይምጻእ ብርሃን
፰ኛ/ ሐዋዘ ብርሃነ
፱ነኛ/ ብርሃን ትእዛዝከ

የዓርያም ጠቅላላ ድምሩ ፶፮ ብቻ ነው ፤ ነገር ግን ፬ቱ ትርፍ ሲደመሩ ፷ ይሆናል።
የአርያም ትርፍ የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው

ዮሐንስኒ ሀሎ ፤
ንው ንትፈሣሕ
ዮሐንስ እምከርሠ እሙ አእመረ
ዓቢይ ዜማ ተሰምዐ በሰማይ
እነዚህ ፬ቱ ትርፍ ናቸው ።

## ፭ኛ ሠለስት ።

ሠለስት ማለት ሦስት ሦስተኛ ማለት ነው ፤ ምክንያቱም በዳዊት መዝሙር በሦስተኛው መሥመር እየገባ የሚዘመር ስለሆነ ነው ፤ አንድም ፫ መዝሙሮች ብቻ የሚዘመሩለት ማለት ነው ።

ይኸውም «ስምዐኒ እግዚኦ ጸሎትየ፥ ወይብጻሕ ቅድሜከ ገዓርየ ፥ ወኢትሚተ ገጸከ እምኔየ» ፥ ብሎ ከዘመረ በኋላ የያሬድን ድርሰት እያስገባ የሚሄድ ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

ሠለስት ሁል ጊዜ ሲጀምር ስምዐኒ ብሎ ነው ፤ ብዙ ሃሌታ አለው ፤ ብዙውም በግጥም መልክ የሚዘመር ነው ፤ ለምሳሌ «ተወልደ ኢየሱስ በቤተ ልሔም ዘይሁዳ ፤ አዋልደ ጢሮስ አሜሃ ይሰግዳ ፤ ሰብአ ሰገል አምጽኡ ሎቱ ጋዳ ፤ ወይት ሐሠያ አዋልደ ይሁዳ» እንዲሁም እያለ ይሄዳል ።

እንዲሁም በምዕራባውያን ግጥም መልክ የሚሄድ ይገኛል ፤

ለምሳሌ መርዓዊ በጽሐ ተቀበሉ------ይላል ። በስድ ንባብም ይገኛል ለምሳሌ ጽጌ አስተርአየ በውስተ ምድርነ -----ይላል ። ይኸ ሠለስት የተባለው ዜማ የሚደረስ በዋዜማ ፤ በስብሐተ ነግህ ፤ በአርያም ፤ በጾመ ድጓው ውሎ ፤ በአርያም ፤ በሰንበት ፤ በፍትሐት ጊዜ ነው ።

የሠለስት ስምና ቍጥር የሚከተለው ነው ።

<u>የሰኞ</u> ፤

፩ኛ/ እስመ ተሐውር
፪ኛ/ ርእዩ በግዓ
፫ኛ/ ሠርዓ ሰንበተ
፬ኛ/ ሶበ ይትነሣእ
፭ኛ/ በመንፈስ የሐውር
፮ኛ/ በከመ ሥምረቱ
፯ኛ/ ነያ ሀገር መድኀኒት
፰ኛ/ እስመ አልቦ ነገር
፱ነኛ/ ባረከ እግዚአብሔር
፲ኛ/ ረከብናሃ በአመ ገዳም
፲፩ኛ/ ዝንቱ ውእቱ ዮሐንስ
፲፪ኛ/ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያን
፲፫ኛ/

<u>የማክሰኞ</u> ፤

፩ኛ/ ማርያም ጽርሕ ንጽሕት
፪ኛ/ በጺሐሙ
፫ኛ/ ጾመ ሙሴ ፵ መዓልተ
፬ኛ/ ተወልደ ኢየሱስ
፭ኛ/ ወአንተሰ ብእሴ እግዚአብሔር
፮ኛ/ ደምፀ እገሪሁ ለዝናም
፯ኛ/ ይገንዩ አሕዛብ ለስምከ እግዚአ
፰ኛ/ እደ ወአንስተ ወሕፃናተ
፱ነኛ/ መርዓዊ በጽሐ ተቀበሉ

www.ethiopianorthodox.org

፲ኛ/ ጽጌ አስተርአየ በውስቴ ምድርነ
፲፩ኛ/ ጽጌ አስተርአየ
፲፪ኛ/ ጊዜ ገሚድ በጽሐ

**የረቡዕ ፤**

፩ኛ/ አብ መርሆሙ ወልድ መገቦሙ
፪ኛ/ ሶፍያ ንግሥት
፫ኛ/ ወገብረ ንጉሥ መድቅሐ
፬ኛ/ ቅንዋተ እንደዊሁ አርአዮሙ
፭ኛ/ ወሚካኤል አሐዱ እመላእክት
፮ኛ/ መዝራዕትየ ወኃይልየ
፯ኛ/ አጸውተ ሲኦል አድለው ሎቱ
፰ኛ/ ወበልዋ ለወለተ ጽዮን
፱ነኛ/ ዝንቱሰ ብእሲ መምህርነ
፲ኛ/ በከመ ይቤ እግዚእነ በወንጌል
፲፩ኛ/ የምስ ወለደት ቅድስት ድንግል
፲፪ኛ/ ወጸውአ ሊቀ ምርፋቅ

**የሐሙስ ፤**

፩ኛ/ ወመሀረ እስከ አመ ዓርገ
፪ኛ/ ወተቀበልዎ መላእክት
፫ኛ/ ሰብሐ ወዘምሩ
፬ኛ/ በከመ ይቤ ዕዝራ ነቢይ
፭ኛ/ ሰፍሐ እደዊሁ ቅዱሳተ
፮ኛ/ በመስቀሉ ወልድ ቤዘወነ
፯ኛ/ ነገሩነ በእንተ ወልድከ
፰ኛ/ ዕቀብዋ ለዛቲ ቃል
፱ነኛ/ ኢትርኃቁ እምኔሃ
፲ኛ/ ይእዜኒ ንዜንወክሙ
፲፩ኛ/ ዛቲ ዕለት ዓባይ ፋሲካ
፲፪ኛ/ ኀበሩ ቃለ

**የዓርብ ፤**

፩ኛ/ ርግብየ ይቤላ
፪ኛ/ ማርያምስ እሙኒ
፫ኛ/ ነጽረነ በአዕይንተ ምሕረትከ
፬ኛ/ ሖረ ኢየሱስ እምገሊላ
፭ኛ/ ዮሐንስ ስሙ ቅዱስ ውእቱ

www.ethiopianorthodox.org

፮ኛ/ ካህን ወነቢይ ድንግል ወሰማዕት
፯ኛ/ ካህን ወነቢይ ወሰማዕት
፰ኛ/ ሶፍያ ንግሥት
፱ነኛ/ ነያ ደብተራ

**የቅዳሜ ፤**

፩ኛ/ ኃይል ክርስቶስ
፪ኛ/ በለስ ዘይቤ ቤተ እስራኤል
፫ኛ/ ገብርኤል መልአክ መጽአ
፬ኛ/ ያፍ ፀዓዳ ትመስል
፭ኛ/ ወአመ ሰዱስ ነሥአሙ
፮ኛ/ ወሪዶሙ እምደብር
፯ኛ/ አዋልደ ንግሥት

የሠለስት ጠቅላላው ድምር ፹፯ ነው ፤ ነገር ግን ስድስት ትርፍ ስላለ እርሱ ሲደመር ፺፫ ይሆናል ።

የሠለስት ትርፍ የሚባሉትም የሚከተሉት ናቸው ።

ይትበደር ሰብእ
ትንሣኤሁ አግሀደ
ዘምሩ
በአይቴ እንከ ንረክብ
ክርሡ ሰሌዳ ከመ ቀርነ ነጌ ።
ሮማይ ብእሲሁ

እነዚህ ፮ቱ ትርፍ ናቸው ።

ትርፍ የተባሉት ሁሉ መቼ እንደ ገቡ ማን እንደደረሳቸው አይታወቅም ።

## ፮ኛ ክሥተት

ክሥተት ማለት የቃሉ ትርጒምና የሥራው ዓይነት በትክክል ያልተያዘ ነው ፤ ስለዚህም ቀጥተኛ ትርጒሙ እስካሁን አልታወቀም ፤ ሆኖም ግን በሰዓታተ መዓልት እግር የገባ እንደሆነ ሊቃውንቱ ይናገራሉ ። የኢትዮጵያ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንደሚያመለክተው በጾምና በበዓላት ጊዜ የሚባል የመዓልት ሰዓታት አለ ፤ ይሁን እንጅ ትልቅ በዓል ሁኖ በአርያም ቁመት ጊዜ ሰዓታቱን ማጎሌቱ ስለአስቀረው ክሥተት በርሱ ፈንታ ገብቶ ይዘመራል ፤ ይኸም ይታወቅ ዘንድ «በሌሊት አንሥኡ እደዊክሙ በቤተ መቅደስ ፤ ወዘሕጎ ያነብብ መዓልተ ወሌሊተ ፤ ሌሊተ ተዛዋእኩ ምስለ ልብየ ወአንቃሕክዋ ለነፍስየ» ሲል ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

የክሥተት ትምህርትም ሁል ጊዜ ፪ መዝሙር ብቻ ይዘምራል ፤ ምሳሌውም ከላይ እንደተመለከተው ይሆናል ። ክሥተት ብዙ ጊዜ የሚገባው ከዳዊት መዝሙር ነው ፤ ነገር ግን በቀዳሚት ላይ የነቢያት መዝሙር ይገኝበታል ፤ ለምሳሌ መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚአ ፥ ወመኑ ከማከ ሰቡሕ በውስተ ቅዱሳን ፤ መገቦሙ ወመርሆሙ ወዐቀቦሙ ከመ ብንተ ዓይን - - - - - - - ይላል ።

እንዲሁም ከዳዊት መዝሙርም ከነቢያት ቃልም ያልሆነ ንጹሕ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት እንደመርገፍ ሁኖ የገባ አለ ፤ እርሱም « እስመ ኪያከ ይሴብሑ ኵሉ ኃይለ ሰማያት ወምድር » ብሎ መንግሥቱ እስከሚለው ድረስ የሚገኘው ነው ። እርሱም ከምስጋና ቃልነቱ ጋር ዜማው ልብን የሚመስጥ ድርሰት ነው ፤ ስለዚ ህም ሁል ጊዜ በትልቅ ዓመት በዓል ሁሉ ይደርሳል ።

| የክሥተት ቀኖችና | ቍጥር |
|---|---|
| የሰኞ | ፳፪ |
| የማክሰኞ | ፲፭ |
| የረቡዕ | ፲፭ |
| የሐሙስ | ፲፭ |
| የዓርብ | ፲፭ |
| የቀዳሚት | ፴ |

የክሥተት ጠቅላላ ድምር ፩፻፳፪ ነው ነገር ግን የጥምቀተ ባሕር ክሥተት ለብቻው ፶፪ የሚሆን ስላለ ፤ ሁለቱም ዓይነት ሲደመር ፪፻፲፬ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፪ ።

## መወድስ ።

መወድስ ማለት ወደሰ አመሰገነ ካለው ከግዕዝ የወጣ ቃል ስለሆነ ምስ ጋና ወይም ማመስገኛ ማለት ነው ፤ ይኸውም ከክሥተት ቀጥሎ የሚማሩት ራሱን የቻለ ትምህርት ነው ።

እስከዚህ ያለው ትምህርት ሁሉ የቃል ትምህርት ይባላል ፤ ከዚህ ጀምሮ እስከ ክሥተት ዓርያም ያለው ግን መወድስ ይባላል መወድስ የሚባለው ወይም የሚደረሰው በዕለተ ሰንበት ነው ፤ ምክንያቱም መላእክት በዕለተ ሰንበት ሲፈጠሩ እንደበታቸው ከምስጋና ሳይለይ ቅዱስ ፤ ቅዱስ ፤ ቅዱስ እያሉ እያመሰገኑ ተገኝተዋልና የዚያ ምሳሌ ነው ይባላል ። ቅዱስ ያሬድም ከመላእክት ምስጋና ሰምቶ ይኸን መወድስን የዕለተ ሰን በት ማመስገኛ አድርጎ ሠርቶታል ። በዕለተ ሰንበት የሚደረሰው ጸሎት የሚያድረው

www.ethiopianorthodox.org

ማኅሌት ሁሉ በጠቅላላው መወድስ ይባላል ፤ ምክንያቱም ዕለተ ሰንበት የምስጋና መጀመሪያ ናትና ።

በዚህም በመወድስ ጊዜ ቅኔ በብዛት ይደርሳል ፤ የዳዊትም መዝሙር በልዩ ልዩ ዜማ ይደረሳል ። መወድስ በመባል በአንድ ዕለተ ሰንበት የሚደረሰው ምስጋና በጠቅላላው በአንድ ላይ ሲደመር ፶፪ ይሆናል ።

ይኸንንም የሚያረጋግጥ «ሃምሳ ወክልኤቱ ቅኔያቲሃ ለዕለተ ሰንበት» ሲል ራሱ ምዕራፉ ይመሰክርልናል ። መወድስ የተባለው ድርሰት ስምና ቍጥሩ እንደ ሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ ጸሎተ አኰቴት
፪ኛ/ ይእቲ ማርያም
፫ኛ/ እግዚእ ፀወነ ኮንከነ
፬ኛ/ እግዚእ ኵነኔከ
፭ኛ/ ግነዩ ብሎ ዛቲ ዕለት
፮ኛ/ መስተብቍዕ እስከ ወገኑ
፯ኛ/ ምስባኩ ንዑ ንትፈሣሕ
፰ኛ/ መዝሙር ተቀነዩ
፱ነኛ/ ዘአምላኪየ እስመ ከማሁ ይቤ
፲ኛ/ እግዚእ ሚበዝኁ
፲፩ኛ/ ቃልየ አጽምእ አርባዕት
፲፪ኛ/ ጸኒሐ
፲፫ኛ/ ብፁዕ ዘይሌቡ
፲፬ኛ/ ከመ ያፈቅር
፲፭ኛ/ ፍታሕ ሊተ
፲፮ኛ/ እግዚኦ ሰማዕነ
፲፯ኛ/ ጐሥዐ
፲፰ኛ/ አምላክነሰ
፲፱ነኛ/ ኵልክሙ
፳ኛ/ ዓቢይ
፳፩ኛ/ ስምዑ ዘንተ
፳፪ኛ/ አምላክ አማልክት
፳፫ኛ/ ተሣሃለኒ
፳፬ኛ/ ግነዩ ዛቲ ዕለት
፳፭ኛ/ ይኄይስ
፳፮ኛ/ እግዚአብሔር ነግሠ

www.ethiopianorthodox.org

## የሰንበት ስብሐተ ነግህ ።

፳፯ኛ/ ዕዝል
፳፰ኛ/ ንሴብሖ
፳፱ነኛ/ አጽምዕ ሰማይ
፴ኛ/ እስመ እሳት ትነድድ
፴፩ኛ/ ጸንዐ ልብየ
፴፪ኛ/ አንሰ እቤ
፴፫ኛ/ እግዚኦ አኃዜ ኵሉ
፴፬ኛ/ ጸራኅኩ በምንዳቤየ
፴፭ኛ/ ይትባረክ ዘዳንኤል
፴፮ኛ/ ይትባረክ ዘሠለስቱ ደቂቅ
፴፯ኛ/ ይባርክዎ
፴፰ኛ/ እግዚኦ ሰማዕኩ
፴፱ነኛ/ በሌሊት ትገይሥ
፵ኛ/ ተዐብዮ ነፍስየ
፵፩ኛ/ ይትባረክ ዘዘካርያስ
፵፪ኛ/ ይእዜ ትሥእሮ
፵፫ኛ/ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት
፵፬ኛ/ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲስ
፵፭ኛ/ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ
፵፮ኛ/ እስመ ለዓለም
፵፯ኛ/ አቡን
፵፰ኛ/ ሠለስት
፵፱ነኛ/ ሰላም
፶ኛ/ ክብር ይእቲ
፶፩ኛ/ ዝማሬ
፶፪ኛ/ ዕጣነ ሞገር

የዚህም ሁሉ ጠቅላላ ድምር ፶፪ ነው ።

«፶ወ፪ ቅኔያቲሃ ለዕለተ ሰንበት» ያለው ስለዚህ ነው ። ይኸ ሁሉ በአንድ ዕለተ ሰንበት ይዘመራል ፤ ይጸለያል ። አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ግን ፶ወ፪ ቅኔያቲሃ ያለው ፫፻፷፭ቱን ቀን ለ፯ ቀን ሲያድሉት ፶፪ ደርሷቸው አንድ ቀን ይተርፋል ፤ ይኸም ማለት የአንድ ዓመት መዝሙር ቢቈጥሩት ፶፪ ሁኖ ፩ ይተርፋል፤ አንዱን የዘመን መለወጫ አድርጎ በ፶፪ እሑድ ውስጥ በየአንዳንዱ መዝሙር ፶፪ ሥርዓት ይደርሳልና ፶ወ፪ ቅኔያቲሃ አለ ይላሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ ስብሐተ ነግህ ።

ስብሐተ ነግህ ማለት የነግህ ምስጋና ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ሁልጊዜ መዝሙሩ ምስጋናው በነግህ የሚባል ስለሆነ ነው ። ስብሐተ ነግህም በ፯ ዓይነት ይከፈላል ፤ ይኸውም ፤

### ሀ/ የዘወትር ስብሐተ ነግህ ነው ።

እርሱም የሚከተለው ነው ።

፩- ዕዝል ፤
፪- መስተብቍዕ እንዘ ነአኵቶ
፫- አምላኪየ ኦምላኪየ
፬- ይኄይስ
፭- ለከ ይደሉ
፮- የነርሱ ምቅናዮች ፲፩ ይባላሉ ።
፯- በእንተ ዱያን
፰- ተዐብዮ ነፍስየ እንደ በዓሉ ይባላል ።
፱- በእንተ እለ ይነግዱ
፲- ይትባረክ እግዚአብሔር
፲፩- ይባርክዎ ለእግዚአብሔር
፲፪- ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት
፲፫- ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ሰብሐተ ሐዲሰ
፲፬- ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ
፲፭- በእንተ ንጉሥ
፲፮- እስመ ለዓለም ሁለት
፲፯- አቡን አንድ
፲፰- ውዳሴ ማርያም
፲፱- ወንጌል
፳- ሠለስት
፳፩- ሰላም
፳፪- የስብሐተ ነግህ መርገፍ ።
፳፫- ሰላምታ
፳፬- ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከሙ ናምልኮ ።

### ለ/ የዕለተ ሰንበት ስብሐተ ነግህ ።

እርሱ ደግሞ በገጽ ፷፱ እንደተመለከተው ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ቤተ ፈቃዳ ቤተ ... ማኅበረ ...

ሐ/ የዓበይት በዓላት ስብሐተ ነግህ ።

የዓበይት በዓላት ስብሐተ ነግህ እንደዘወትሩ ሁኖ ልዩነቱ በየዳዊቱ መጨረሻ ቅኔ ይገባበታል እርሱንም በገጽ ፩፻፲፱ ተመልከት ።

መ/ በዘመነ ጽጌ የሰሎሞን ስብሐተ ነግህ ተብሎ የሚደርስ ነው ።

ሠ/ የተጽዒኖ ማግሥት የምህላ ሳኒታ የሚባለው ነው ።

ረ/ በሰሙነ ሕማማት የሚደርሰው ፤

የግብረ ሕማሙ ሥራ እንደ ስብሐተ ነግህ ይቈጠራልና ።

ሰ/ የቅዳሜ ሥዑር ስብሐተ ነግህ ነው ።

ይኸውም የሚባለው በዘወትር በበዓላት በሰንበትም ቀን ነው ። ስብሐተ ነግህም ሲጀመር አምላኪየ አምላኪየ ብሎ ነው ፤ ምክንያቱም የቅዱስ ዳዊት መጀመሪያው ድርሰት አምላኪየ ብሎ ነው እና የሚሉ አሉ ። መምህራን ለተማሪዎቻቸው ስብሐተ ነግህ ሁል ጊዜ በጧት እንዲያደርሱ ይመክሯቸው ነበር ፤ እነርሱንም እንዲህ ይሏቸው ነበር ፤ የክርስቶስን የሕይወት ታሪክ ሳትሰሙ ፤ በማየ ዮርዳኖስ ሳትጠመቁ ፤ የአበውን ሞት ሳትረዱ አትዋሉ ። የምሳሌው ትርጉም ዮርዳኖስ የተባለ ማየ ገቦ ነው ፤ የአበው ሞት የተባለ በስንክሳር ውስጥ የአሉቱ የቅዱሳን ዜና ነው ፤ ኢየሩሳሌም የተባለች ቤተ ክርስቲያን ናት በቤተ ክርስቲያን ተገኝታችሁ ስብሐተ ነግህ አድርሱ ስንክሣር አንብቡ ማለት ነው ።

ምዕራፍ ፫ ።

ምዕራፍ ።

ምዕራፍ ማለት ማረፊያ ማለት ነው ፤ ይኽ ስም በሌላ ቦታ ሲውል የመጻሕፍት ክፍል የኃይለ ቃል መለያ ሆኖ አዲስ መሥመር በሚጀመርበት ጊዜ አዲስ ምዕራፍ ይከፈትለታል ፤ ይኸም ምዕራፍ ይባላል ። በዜማ ቤት የሆነ እንደ ሆነ ግን ምዕራፍ ማለት በመላ ሰላም ለኪ ብሎ ጀምሮ የጾም ምዕራፍ እስ ኪፈጸም ድረስ ያለው ትምህርት ሁሉ ምዕራፍ ይባላል ። ራሱንም የቻለ ምዕራፍ የተባለ መጽሐፍ አለ ፤ እርሱም በቃል ትምህርት ጊዜ የተለየ ተራ ሲኖረው በመጽሐፉ አቀማመጥ ደግሞ የተለያየ ተራ ያለው ሁኖ ይገኛል ። የሆነው ሆኖ ምዕራፍ ሲል ልዩ ልዩ ክፍል ያለው የታወቀው የዘወትር ምዕራፍ የጾም ምዕራፍ በመባል አንድ ላይ ሆኖ ነው ።

ምዕራፍ በመባል በ፩ ስም የታወቀው ትምህርት በክፍል ግን የተለየ ስም አለው ፤ ይኸውም ሰላም ለኪ ብሎ እስከ ክሥተት ድረስ ያለው የቃል ትምህርት ይባላል ፤ እርሱም ከገጽ ፺፯—፩፻፫ ያለው መሆኑ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከመወድስ ጀምሮ ምቅናዩን ጨምሮ እስከ እምሥራቀ ፀሐይ ድረስ ያለው ትምህርት ሁሉ ዳግም መወድስ ይባላል ፤ እርሱንም በገጽ ፷፯—፷፱ ተመልከት።ከርሱ ቀጥሎ ያለው ትምህርት ደግሞ ከሥተት ዓርያም ይባላል ፤ እርሱም ፥ ተሣሃለኒ ብሎ ይጀምርና በእግዚአብሔር ነግሠ ይፈጸማል ፤ እርሱንም በገጽ ፻፲፱—፻፳፫ ተመልከት። እንዲሁም ቀጥሎ ያለው ዋዜማ ይባላል ፤ እርሱም ሲጀመር ቅዱስ ብሎ በኪዳኑ ይጀምራል ፤ ዋዜማ የተባለው ትምህርት ደግሞ ፳፪ አርእስት አሉት ፤ እነሱም የሚ ከተሉት ናቸው ።

፩- ዋዜማ
፪- በአምስት
፫- እግዚአብሔር ነግሠ
፬- ይትባረክ
፭- ሠለስት
፮- ሰላም
፯- መዝሙር
፰- ዘአምላኪየ
፱- አርባዕት
፲- ሚበዝኁ
፲፩- ብፁዕ ዘይሴቡ
፲፪- መወድስ
፲፫- ዞልክሙ
፲፬- ዕዝል
፲፭- ማኅሌት
፲፮- ዘይእዜ
፲፯- ስብሐተ ነግህ
፲፰- እስመ ለዓለም
፲፱- አቡን
፳- ክብር ይእቲ
፳፩- ዝማሬ
፳፪- ዕጣነ ሞገር

ድምር ፳፪ ያልነው ይኸ ነው ። የዜማም ሁሉ አርእስት ይኸ ነው ፤ በአ ምስት የሚለው ትርጓሜ በዳዊት መዝሙር በ፭ኛው መሥመር የሚባል ስለሆነ ብቻ ነው ፤ ይኸውም ፥

፩- ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ
፪- ዓለምኒ ወኵሎሙ እለ ይነብሩ ውስቴታ

www.ethiopianorthodox.org

፫- ወውእቱ በባሕር ማረራ
፬- ወበአፍላግኒ ውእቱ አጽንዓ
፭- መኑ የዓርግ ውስተ ደብረ እግዚአብሔር

የሚለውና ይኸንም የመሰለ ነው ፣ ከዚህ ላይ ግን ምዕራፍ ይገባል ፣ ይኸ ውም በአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ይመሰላል ። በጠቅላላው እስከአሁን የዘረዘር ነው የዜማ ትምህርት ሁሉ በስም ምዕራፍ ይባላል ፤ እርሱም የዘወትርና የጾም ምዕራፍ በማለት ይከፈላል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፩ ።

## ድጓ ።

### ምዕራፍ ፩ ።

# የድጓ ትምህርት ።

## ፩ኛ የድጓ ብሂል ።

ድጓ ማለት ረቂቅ ማለት ነው ፤ ይኸውም ከጽሕፈቱ ረቂቅነት ከምልክቱ ብዛት የተነሣ የወጣለት ስም ሳይሆን አይቀርም የማለት ግምት አለ ። አንዳንዶችም ደግሞ ድጓ ማለት እስትጉቡእ ማለት እንደሆነ ይናገራሉ፤ ምክንያቱም የዓመቱ መዝሙራት ተውጣጥተው ተሰብስበው ይገኛሉና ። ይኸ ስም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ የወጣ አንድም በኋላ ጊዜ ይሁን ግልጥ ሆኖ አይታወቅም ራሱ ቅዱስ ያሬድ ግን «ዋይ ዜማ» ሲል የዜማውን ስልት አንድም ስም ብቻ ተናገረ እንጂ ስለ መጽሐፉ ስም ከቶ የገለጠው ነገር እንደሌለ የታወቀ ነው ። የኋላ ሊቃውንት ግን «ንጽሕፍ መጽሐፈ ድጓ» እያሉ የመጽሐፉን ስም ድጓ በማለት ያመለክታሉ ፣ ግብሩንም ይገልጣሉ ። ይኸም አገላለጥ ቅሉ መቼ እንደተጀመረ ከቶ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም፤ ነገር ግን ጾመ ድጓ ሲል በጾም ጊዜ የሚዘመር የጾም ማመስገኛ መሆኑ ከታወቀ ፣ ድጓም ማለት ዝማሬ፤ መዝሙር፤ ምስጋና ማለት እንደሆነ ግምት ቢሰጠው ስሕተት ነው ሊባል አይቻልም ። እንዲያውም ዜማ ማለት ጩኸት ማለት ሳይሆን አይቀርም የማለት ግምት ይሰጣል ፤ ስለዚህም ድጓ ማለት ሙሾ ፣ ዜማ ማለት እንደሆነ በሌላ በኩል ይነገራል ። የሆነው ሆኖ ይኸ መጽሐፍ የታላቁ የቅዱስ ያሬድ ከፍተኛ ድርሰቱ እንደሆነና የቤተ ክርስቲያንንም የዓመቱን መዝሙር አጠቃሎ የያዘ እንደሆነ የታወቀ ነው ፤ ነገር ግን ሁሉም መቶ በመቶ የርሱ ነው ብሎ ለመቀበል በየድጓው መቅድም ላይ የሚጻፈው በጠቅላላው ድጓውን የቅዱስ ያሬድ ብቻ አድርጎ አያመለክትም፤ ምክንያቱም ግማሹ ከያሬድ ተያይዞ ዓረፍተ ዘመን ሳይገታው ሲወርድ ለብዙ ሊቃውንት ተዳርሷል፤ ከብዙ ሊቃውንትም ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ ሲሆን ግማሹ ግን በኋላ ዘመን በተነሡት ሊቃውንት በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ የተቀመረ እንደሆነ ያመለክታል ። እርሱም ሲገልጥ «እስመ ለዝንቱ መጽሐፍ መንፈቁ ተረክበ እመጻሕፍተ ካህናት ቀደምት ወመንፈቁ ተጽሕፈ በመዋዕለ ዘርዓ ያዕቆብ ንጉሥ» ይላል (መቅድመ ድጓን ተመልከት)። ምናልባት መንፈቁ የሚለው አልፎ አልፎ የገቡትን አዋልድ የተባሉትን ይሆን ? የሚል ግምት ይሰጣል ፤ ወይም በእርግጥ ግማሹ በኋላ ተጽፎ የገባ እንደሆነ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም ። በቃል የሚነገረው ግን በመላ የዜማ ድርሰት የተባለው

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉ ፤ በተለይም ድጓ የተባለው መጽሐፍ የቅዱስ ያሬድ ድርሰት እንደሆነ የታወቀ ነው ። የምልክቱ ዓይነትም በርሱ ጊዜ ፰ቱ ብቻ ነበሩ ይባላል ፤ ሌሎች ግን የተቀመሩት በቅዱስ ያሬድ ደቀ መዛሙርት በሐዊራ ፤ በሳዊራ ፤ በእስክንድራ ፤ በፖእስክንድራ ፤ በአቢድራ ነው ፤ የተቀሩትን ደግሞ የቀመሩ በአጼ ሠርጸ ድንግል ጊዜ የነበሩ አዛዥ ጌራና አዛዥ ራጉኤል የተባሉ ፣ የተድባበ ማርያም ሊቃውንት እንደሆኑ ይተረካል ፤ እነርሱም ምልክቱን በብዛት ሊያደርጉ የተገደዱበት ዋናው ምክንያት በግራኝ ወረራ ምክንያት ሊቃውንት አልቀው የዜማው ስልት ለመጥፋት ስለቀረበ ለደቀ መዝሙር እንዳያስቸግር በማለት ነው ።

ጥንታውያን የሆኑ አንድም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ነበሩ የሚባሉ የዜማ ምልክቶች ፰ ዓይነት የተባሉት እነዚህ ነበሩ ፤ ይዘት ፤ ደረት ፤ ድፋት ፤ ሂድ ፤ ቁርጥ ፤ ርክርክ ፤ ቅናት ፤ ጭረት ፤ ናቸው ። ይኸውም ቊጥር እንደ አውሮፓውያን የኖታ ምልክት ፰ ብቻ መሆናቸው ነው ።



ነገር ግን ከዚህም ሌላ በኋላ ጊዜ «ድርስና አንብር» የተባሉ ፪ ምልክቶች ተጨምረዋል ፤ ይኸም ሲደመር ፲ ይሆናል ፤ የ፲ሩ አውታረ በገና ምሳሌ ነው ። የኢትዮጵያ ሊቃውንት ግን ለዜማው ስልት በበለጠ ይሰጣል ብለው ከተጠቀሱት ምልክቶች ጋር ሌሎችም ብዙዎች ምልክቶች በየጊዜው ጨምረውባቸዋል ።

ሆኖም በዕዝልም በግዕዝም በዓራራይም ጊዜ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ሌሎችም እርስ በርሳቸው ቀለሞችን አዛምደው አንዱን ለአንዱ ምልክት አድርገው ወይም አንዱን ለአንዱ ሥረይ እያሉ ይሄዳሉ እንጅ በሕግ የታወቁት አሁንም ቢሆን እነዚሁ ናቸው ፤ በየጊዜው የተጨመሩ አንድም የተሻሻሉ ምልክቶች በብዛት ይገኛሉ ።

የድጓውም ዜማ ምንም ምልክት በየጊዜው ቢጨመርበት ከላይ እንደገለጥነው ግዕዝ ፤ ዕዝል ፤ ዓራራይ ፤ ብቻ ነው እንጅ ከዚህ የወጣ ዜማ ከቶ የለውም ምሳሌውም እንደሚከተለው ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ግዕዝ በአብ ፤ ዕዝል ፤ በወልድ ፤ ዓራራይ በመንፈስ ቅዱስ ፤ ይመሰላል ፤ ትርጕሙ ወይም ምሳሌው ግዕዝ ማለት ርቱዕ ማለት ነው ፤ አብን ርቱዕ ሎቱ ነአዙቶ ለማለት ፤ ዕዝል ጽኑዕ ነው ወልድ ጽኑዕ መከራን ተቀብሎ አዳምን ለማዳኑ ምሳሌ ፤ ዓራራይ ደግሞ ጥዑም ነው ፤ ሀብተ መንፈስ ቅዱስን መቀበላችንን ለማጠየቅ ነው ።

ግዕዝ በአብ፤ ዕዝል በወልድ ፥ ዓራራይ በመንፈስ ቅዱስ ይመሰላል ሦስቱም የዜማ ዓይነቶች በአንድ ላይ ሲገኙና በአብ በወልድ በመንፈስ ቅዱስ ሲመስሉ ሥርዓተ ቅዳሴውን ልንመለከት እንችላለን ፥ ማለት አሐዱ አብ ቅዱስ ብሎ በግዕዝ ፥ አሐዱ ወልድ ቅዱስ ብሎ በዕዝል ፥ አሐዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ብሎ በዓራራይ ጽፎ አመልክቶም ይገኛልና ። እንዲሁም ከግዕዝ ዜማ ዓራራይና ዕዝል ሊወጡ ይችላሉ ፤ ይኸውም ምሳሌ አለው ፤ ምሳሌውም ወልድ ከአብ የመወለዱ ፤ መንፈስ ቅዱስም የመሥረጹ ምሳሌ ነው ።

የዜማ ትምህርት በግዕዝ ፤ በዓራራይ ፤ በዕዝል ፤ ይወሰናል አልን እንጂ ፫ቱም ዓይነት ባ፩ ጊዜ ፪ቱም እየራሳቸው በአንድ ቀለም የሚገቡበት ጊዜ አለ ፤ ይኸውም የሚከተለው ነው ።

<u>፩ኛ/ በግዕዝ ፤ በዓራራይ ፤ በዕዝል ፤</u>

«ባሕረ ግርምት ፤ ገብረ ዓረፍተ ፤ ወበውስቴታ አርአየ ፍኖተ ፤ በእደ መልአኩ ዓቀቦሙ በገዳም ለሕዝቡ አርብዓ ዓመተ ፤ ወሴሰዮሙ መና ኅብስተ ፤ ኪነ ጥበቡ ዘአልቦ መስፈርተ» ይኸ ቀለሙ አንድ ሲሆን በግዕዝም ፤ በዕዝልም ፤ በዓራራይም ፤ የሚዜም ነው ፤ ይኸንም የመሰለ ብዙ ይገኛል ።

<u>፪ኛ/ በዕዝልና በግዕዝ የሆነ ፤</u>

«ኢትክል ተከብቶ ሀገር ፤ እንተ ተሐንፀት መልዕልተ ደብር ፤ ይእቲኬ ስብከታት ዘሐዋርያት ኢትክል ተከብቶ ሀገር» ይኸም ቀለሙ አንድ ሲሆን በዕዝልም በግዕዝም ሲባል ይታያል ይኸንም የመሰለ ብዙ ይገኛል ።

<u>፫ኛ/ ዓራራይና ዕዝል ።</u>

«ወአዘዘ ዱድያኖስ ንጉሥ አግበረ ሎቱ አሣዕነ ዘሐፂን ወአስተሰአንዎ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ተመትረ ሥርዉ ወተክዕወ ደሙ ለቅዱስ ጊዮርጊስ ፤ ተመትረ ሥርው ወተክዕወ ደሙ ፤ ወሶበ ስእነ ሠጊረ ድቡተ ሖረ ጸርሐ ጊዮርጊስ በዓቢይ ቃል ወይቤ እፎ ኢይሄሊ ከመ አምላኪየ ተሰቅለ ዲበ ዕፀ መስቀል» በዚህም መልክ ዓራራይና ዕዝል ሊባል ይችላል ቀለሙ ግን ይኸው ነው ፤

<u>፬ኛ/ ግዕዝና ዓራራይ በአንድ ላይ ሲገኙ ፤</u>

«ዘበዳዊት ተነበየ ወበዮሐንስ (እስከዚህ ግዕዝ ነው) ጥምቀተ ኀርየ በቃና ዘገሊላ ማየ ወይነ ረሰየ መዓዛ ቃልከ ይትወከፍ ጸሎትየ» ይኸ ደግሞ ዓራራይ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፭ኛ/ ግዕዝና ዕዝል በአንድ ላይ ሲገኙ ይኽ ዓይነት ነው ፤

ስምዐኒ እግዚኦ (ግዕዝ) ጸሎትየ ሃሌ ሉያ (ዕዝል) ወይብጻሕ ቅድሜከ (ግዕዝ) ገዓርየ ሃሌ ሉያ ወኢትሚጥ ገጸከ እምኔየ (ዕዝል) በዕለተ ምንዳቤየ አጽምእ እዝነከ (ግዕዝ) ኀቤየ ሃሌ ሉያ (ዕዝል) አመ ዕለተ እጼውአከ ፍጡነ (ግዕዝ) ስምዐኒ ሃሌ ሉያ ለዓለም ወለዓለመ ዓለም (ዕዝል) ወአመ ስዱስ ነሥአሙ (ግዕዝ) ኢየሱስ ለጴጥሮስ ወለያዕቆብ ወለዮሐንስ ወአዕረጎሙ ደብረ ነዋኃ (ዕዝል) እንተ ባሕቲቶሙ ወተወለጠ አርአያሁ በቅድሜሆሙ ።



ይኽም ድርሰት ዓመት እስከ ዓመት ሊዘመር የሚቻለውን ልዩ ዓይነት ፣ የመዝሙር ስልት ፤ በክፍለ ዘመናት በንዑስ ዘመናት በመክፈል በዓላትን አጽዋማትን በመከተል የተዘጋጀ ነው ።

ድጓ የተባለው ድርሰት የመጀመሪያው የቅዱስ ያሬድ ድርሰት ከመሆኑም በላይ የግጥም መልክ ያለው የተመጠነ አንድም የተለካ አሰካክ ያለው ድርሰት ስለሆነ እውነተኛ መዝሙር እንደሆነ ያስረዳል ።

እንኳን ድጓውን ቅኔውን ሳይቀር የደረሰው ቅዱስ ያሬድ ነው እየተባለ ይነገርለታል ፤ ይኽም የታመነ እውነት እንደሆነ ሊያረጋግጥለት የሚችለው የድጓውን ፤ የቃል ትምህርቱንም ሁሉ በጥንቃቄ የተመለከትን እንደሆነ ነው ፣ ለምሳሌ «ባሕረ ግርምት ገብረ ዓረፍት ፤ ወበውስቴታ አርአየ ፍኖተ ፤ በእደ መልአኩ ዓቀ

www.ethiopianorthodox.org

ቦሙ በገዳም ለሕዝቡ አርብዓ ዓመተ ወሴሰዮሙ መና ኅብስተ ኪነ ጥበቡ ዘአልቦ መሥፈርተ» የሚል ሲሆን ከቃል ትምህርት ውስጥ ደግሞ በግጥም መልክ ሲገኝ «አጥመቀ ወተጠመቀ ለሊከ ፤ ቃል ፈነወከ ነቢየ ልዑል ተሰመይከ» ይላል ፤ ሌላውም ብዙው በዚህ መልክ ይሄዳል ። ከዚህ ሌላ ደግሞ ግማሹን በ፩ ቤት አድርጎ ፪ኛውን ፫ኛውን በሌላ ቤት ይፈጽማል ፤ ግን የሚሔደው ግጥምነቱን ሳይለቅ ነው ፤ ለምሳሌ «ሃሌ ሉያ ለአብ ሚካኤል ብሂል ፤ ዕፁብ ነገር ፤ ሃሌ ሉያ ለወልድ ገብርኤል ብሂል ወልደ እግዚአብሔር» እስከዚህ በአንድ ቤት ነው ፤ «ሃሌ ሃሌ ሉያ ወለመንፈስ ቅዱስ ዓይኑ ዘርግብ ፤ ክነፊሁ ዘእሳት ፤ ወያሥተሰሪ ኃጢአተ ሕዝብ» ሲል ደግሞ በሌላ ቤት ይፈጽማል ። (ዓርያም ዘሐሙስ) ፤ ሌላውንም ሁሉ ጠንቅቀን ብንመለከት ፩ኛ/ እንደስድ ንባብ ሆኖ የቃሉ አሰካክ ግን የግጥም መልክ ያለው ሆኖ ይገኛል ፤ ፪ኛው እንደአውሮፓውያን ግጥም አንድ ቤት መቶ በመካከሉ ሌላ ቤት ያገባና በኋላ ቆይቶ ያነኑ ቤት ይመታል ፤ ይኸም የግጥም ዓይነት ነው ፤ ፫ኛው ደግሞ ፪ ፪ ቤት እየመታ በተለያየ ቤት ይዘልቃል ፤ ይኸንም ጠንቅቆ ቢከታተሉት ሁሉም ሊረዳው ይችላል ።

ይኸን ዜማ ቅዱስ ያሬድ ይድረሰው እንጅ እርሱ ለነማን እንዳስተማራቸው ወይም እንዳስተላለፈው ተከታዮቹስ እነማን እንደነበሩ ግልጥ ሆኖ አልታወቁም ፤ በአንዳንድ ታሪክ ብቻ መንክራ ፣ ሳዊራ ፣ ሐዊራ ፤ እስክንድራ ፣ ፓእስክንድራ ፤ አቢዳራ ተከተሉት ጻፉት አጠኑት ይባላል ። ገድሉ የሚለው ግን ስሜን ተራራ በስሙ በተሰየመው ገዳም ከዘጋበት ቦታ ድረስ ካህናት ስሜን ፤ እየሄዱ ይማሩ እንደነበረና ዜማው በመላ ኢትዮጵያ ደርሶ እንደነበረ ይነገራል ። (ገድሉን ተመመልከት) ።

በኋላ ግን በጉዲት ጥፋት ምክንያት ሊቃውንቱ ሁሉ አልቀው መጻሕፍቱም ተቆነጻጽለው ስለጠፉ በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ እንደገና ለመሰብሰብና ለመወሰን በቃ ይላል ።

በሌላ በኩል ደግሞ የቅዱስ ያሬድ ተከታዮች ለቅኔውም ለድጓውም ሐዊራና መንክራ የተባሉ ወሳኞች እንደነበሩ ይተረካል ፤ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርቱም ሥነ ሥርዓቱም ዜማው ከነሥልቱ የተወሰነው በዚያን ጊዜ ነው ።

## ፪ኛ የድጓ አስተጋባእያን ።

የድጓችን ዜማ እንደገና እስትጉቡእ ሆነ ማለት ተሰበሰበ ፤ ነገር ግን ከያሬድ በኋላ በጉዲት ወይም ብዙ ዘመን ቆይቶ ይሁን ግልጥ ሆኖ ባልታወቀ ምክንያት ጠፍቶ ሲኖር የሰበሰቡትና መልክ የሰጡት የወሰኑትም በአባ ጊዮርጊስ ሰብሳቢነት በአጼ ዘርዓ ያዕቆብ ተጠባባቂነት ነው ይባላል ።

ስለዚህም ብዙዎች ሰዎች የዜማን ስልት ከአባ ጊዮርጊስ እንደተማሩ ድጓውም እንደ ገና መልክ እንዳገኘ ግልጥ ሆኖ ይነገራል ፤ ይሁን እንጅ ይኸም

www.ethiopianorthodox.org

ቅምር በግራኝ ወረራ ምክንያት እንደገና የጠፋ የዜማውም ስልት እንደገና የተለወጠ ስለሆን ሊቃውንቱ ሲጨነቁ በቤተ ልሔም ገዳም አባ ልሳነ ዕፍረት የተባለ መነኵሴ አብነት የሆነውና እንደገና ቀማሪ የሆነው ድጓውን ይዞ ስለተገኘ የ፫ኛው ጊዜ ቀማሪ ተብሏል ። ይኸውም በመጀመሪያ ጊዜ በአክሱም ቅዱስ ያሬድ ደርሶ ቀምሮ ያስተማረው በጉዲት ምክንያት ጠፋ ፤ ፪ኛም አባ ጊዮርጊስ ዘጋስጫ ሰበሰበው አስተጋባው የሚለው ነው ። ፫ኛው ጊዜ ግን አባ ልሳነ ዕፍረት አብነት ሆኖ ተገኝቷል ፤ ቤተ ልሔምም የድጓ የምስክር ቦታ ለመሆን የቻለችውም በዚህ መልክ ነው እርሱም ልሳነ ዕፍረት መራሒ ዘቤተ ልሔም የተባለው ነው ። የአሁኑ ዜማ ግን ከርሱ የተገኘ እርሱ ያስተማረው ነው ፤ እርሱም አባ ዘቃለ አብን አስተምሮ በእግሩ እንዲተካ አድርጓል ።

ከዚያ በኋላ ግን ያለማቋረጥ ተያይዞ እስከኛ ዘመን ደርሷል ፤ የዘር አወራረዱም እንደሚከተለው ነው ።

አባ ዘቃለ አብም ቃለ ዓዋዲን አሠልጥኖ ተካ ፤ እርሱም የደብረ ሊባኖስ መምህር አንድም እጨጌ የሆነው ነው ። የቤተ ልሔም አስተዳዳሪዎች ሁሉ እጨጌዎች እየተባሉ የድጓ ምስክር እንደነበሩ ታሪክ ይነግረናል ፥ ለምሳሌ እጨጌ በትረ ጊዮርጊስን ሌሎችንም እንዲሁ እንመልከት ፤ ቃለ ዓዋዲ እንደገና ሕንፃ ሃይማኖትንና ተጠምቆ መድኅንን አስተማረ ፥ ሕንፃ ሃይማኖትም ወልደ መለኮትን አስተማረ ፤ ወልደ መለኮትም ሠርፀ ማርያምን አስተማረ ። ሠርፀ ማርያም ደግሞ ክንፈ ሚካኤልን አስተማረ ። በዚህን ጊዜ የቆማው ፤ የተጉለቴው ፤ የአሜብሬው ፤ የወንጨሬው ዜማ የተለየ ሆኖ ሲቀር በቀር በኢትዮጵያ ውስጥ በብዙ ቦታዎች የድጓ ትምህርት ተዳረሰ ለምሳሌ ቤጌምድርን አልፎ በትግሬ በደብረ ገሪማ ፤ በወሎ ፤ በደብረ ነጐድጓድ (ሐይቅ) በደብረ እግዚአብሔር እንዲሁም በአትሮንስ ማርያም ፤ በተድባበ ማርያም እንዲሁም በመካነ ሥላሴ ፤ በሸዋ ደግሞ በደብረ ሊባኖስ በሌላም ቦታ ተዳረሰ ቤጌምድር ግን ዳር እስከዳር የዜማ አብነት የድጓ ትምህርት ምንጭ ሆነች ።

ከዚህ በኋላ ግን በሁሉም ዘንድ ተበተነና የድጓ ዜማ ለሁሉም ተዳረሰ ። ክንፈ ሚካኤል የተባለው ሊቅ ደግሞ ለገብረ እግዚአብሔር (ለመሪጌታ ደርሶ) አስተማረ ፤ ገብረ እግዚአብሔርም ለገብረ መድኅን (ለአለቃ መርሻ) አስተማረ ። ገብረ መድኅንም ለስብሐተ ማርያም (ለአለቃ አምሳሉ) አስተማረ ። ከልሳነ ዕረፍት እስከ አለቃ አምሳሉ ድረስ ያሉ የቤተ ልሔም የድጓ ምስክሮች ፲ ብቻ ናቸው ፤ እነዚህም በቤተ ልሔም የድጓ ምስክሮች ሆነው የኖሩት ናቸው ።

ከትምህርታችን ውስጥ የዜማው ምስክር የታወቀው ቤተ ልሔም ስለሆነ የመምህራኑን ስምና ተራ በመጠኑ ለማወቅ ቅደም ተከተሉንም ለመዘርዘር በቃን ።

የአቋቋሙ የቅኔው የመጽሐፉ የሌላው ትምህርት ግን ትምህርቱ እንዲሁ

www.ethiopianorthodox.org

በየቦታው አስተምሮ መፍቀድ ብቻ ስለሆነ የመምህራኑ ተራ ሊጠበቅ ታሪኩም ሊታወቅ አልተቻለም ።

አንዳንድ ጊዜ የእገሌ ደቀ መዝሙር ነኝ ሲል ወይም የኔ አባት እገሌ ናቸው ሲል ተያይዞ ተከታትሎ ሲሔድ ብቻ ይታወቃል ፥ ይሁን እንጅ ደቀ መዝሙሩ ከ፩ እና ከ፪ት ከዚያም ከበለጠ ጉባኤ መግባቱ ስለማይቀር እነዚያን ሁሉ ሊያስጠራ አይችልም ፤ የድጓው ትምህርት ግን የትም ይማር እንጅ ምስክሩ አንድ ስለሆነ ፤ ለመቊጠር ተቻለ ፤ የምስክር ወረቀትም በትክክል የሚሰጥ በቤተ ልሔም ብቻ ነው ።

ምዕራፍ ፪ ።

# ክፍለ ድጓ ።

የድጓ መጽሐፍ በጥራዙ ብቻ ሳይሆን በኃይለ ቃሉ ታላቅ እንደመሆኑ ለዝማሬ ይመች ዘንድ በውስጡ ብዙ ክፍልን ይዞ ይገኛል ። ስለዚህም በ፬ ታላላቅ ክፍል ይከፈላል ፤ ይኸውም የ፬ቱ ወንጌላውያን ምሳሌ ነው ።

## ክፍሎቹም ።

### ፩ኛ/ ዮሐንስ የተባለው ክፍል ነው ፤

የመጀመሪያው ክፍል ዮሐንስ ይባላል ፤ ምክንያቱም ዮሐንስ የብሉይና የሐዲስ መሸጋገሪያ አንድም የሐዲስ መጀመሪያ ነበርና የዚህ ምሳሌ ነው ።

አንድም የድጓው መጀመሪያ ዮሐንስ ተባለ ስለዚህም ድጓው ብፁዕ አንተ ዮሐንስ ብሎ ይጀመራል ።

በዜማውም ውስጥ የዮሐንስን የሕይወት ታሪክ ይተርክና ወደ ሐዲስ ኪዳን ይሻገራል ። የዮሐንስም ፍጻሜ ስምዕ በዚሁ ዕለት ስለሆነ ዕለቱም ዘመኑም የድጓውም ክፍል ዮሐንስ ተብሏል ። በዜማው ከባድነት በቊጥሩ ብዛት ከሁሉም ዮሐንስ ይበልጣል ፥ በዮሐንስ ክፍል የሚዘመሩት ፲፻፭፻፷፯ ሲሆኑ የእርሱም ክፍል የሚባለው ከመስከረም ፩- ፳ ድረስ ነው ።

### ፪ኛ/ አስተምህሮ የተባለው ክፍል ነው ፤

አስተምህሮም ማለት የጌታን ትምህርት የሚገልጥ ነው ፤ ጌታም የአስተማረውን ይተርካል ፤ ይህንንም በመከተል ይዘመራል ። የአስተምህሮ ክፍል በ፩ ጊዜ የሚወሰን አይደለም በልዩ ልዩ ክፍለ ዘመናት ውስጥ ይገባል ፤ እየተመላለሰም ይዘመራል ። ይሁን እንጂ በአስተምህሮ ውስጥ የሚዘመረው ፲፻፬፻፷፬ ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ጾመ ድጓ የተባለው ክፍል ።

ከዚሁ ከአስተምህሮ የሚቈጠር ነው ይኸውም ክፍል የሚዘመረው በዓቢይ ጾም ጊዜ ብቻ ነው ፤ ክፍሉም አንዳንዶች መምህራን ከአስተምህሮ ውስጥ ነው ይላሉ እነዚህም የድጓውን ክፍል ፫ ብቻ የሚያደርጉ ናቸው ፤ ይሁን እንጅ በግድ ራሱን የቻለ ክፍል መሆን እንዳለበት የታመነ ነው ፤ የሆነው ሆኖ ራሱን የቻለ ክፍል ስላለው በገጽ ፹፫ ተመልከት ።

## ፫ኛ/ ፋሲካ የተባለው ክፍል ነው ፤

እርሱም ከትንሣኤ እስከ አባ ገሪማ የሚዘመረው ነው ። በውስጡም የሚይዘው ፫ሺ፩፻፷፱ ነው ። ይኸም ክፍል እንደገና በአርእስት ይከፈላል አርእስት የሚባሉትም ፷፪ ናቸው ። የ፷፪ቱ ሥነ ፍጥረት ምሳሌ ነው ፤ ይኸውም በገጽ ፸፪ የሚገኘው ነው ፤ ምስጋና ወይም ትምህርት ማለት ነው ።

## ፬ኛ/ የድጓው ዝርዝር ቍጥርና የዘመኑ አከፋፈል ።

| ተራ ቍ. | ዘዮሐንስ | ብዛት | ተራ ቍ. | ዘአስተ ምህሮ | ብዛት | ተራ ቍ. | ዘፋሲካ | ብዛት | ተራ ቍ. | ማጠቃለያ ስሙ | ጠ. ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ምስባክ | 19 | 1 | ምስማክ | 15 | 1 | ምስማክ | 22 | 1 | ምስማካት | 56 |
| 2 | ዋዜማ | 176 | 2 | ዋዜማ | 227 | 2 | ዋዜማ | 157 | 2 | ዋዜማዎች | |
| 3 | በአምስት | 51 | 3 | በአምስት | 43 | 3 | በአምስት | 56 | 3 | በአምስት | 150 |
| 4 | እግዚአብ ሔር ነግሠ | 43 | 4 | እግዚአብ ሔር ነግሠ | 24 | 4 | እግዚአብ ሔር ነግሠ | 52 | 4 | እግዚአብ ሔር ነግሠ | 119 |
| 5 | ይትባረክ | 62 | 5 | ይትባረክ | 46 | 5 | ይትባረክ | 58 | 5 | ይትባረክ | 166 |
| 6 | ሠለስት | 321 | 6 | ሠለስት | 320 | 6 | ሠለስት | 579 | 6 | ሠለስት | 1220 |
| 7 | ሰላም | 460 | 7 | ሰላም | 591 | 7 | ሰላም | 579 | 7 | ሰላም | 1630 |
| 8 | መዝሙር | 46 | 8 | መዝሙር | 53 | 8 | መዝሙር | 72 | 8 | መዝሙር | 171 |
| 9 | አርባዕት | 247 | 9 | አርባዕት | 216 | 9 | አርባዕት | 289 | 9 | አርባዕት | 752 |
| 10 | ዕዝል | 195 | 10 | ዕዝል | 176 | 10 | ዕዝል | 214 | 10 | ዕዝል | 585 |
| 11 | ማኅሌት | 82 | 11 | ማኅሌት | 59 | 11 | ማኅሌት | 54 | 11 | ማኅሌት | 195 |
| 12 | ስብሐተ ነግሀ | 39 | 12 | ስብሐተ ነግሀ | 58 | 12 | ስብሐተ ነግሀ | 88 | 12 | ስብሐተ ነግሀ | 18 |
| 13 | ዘይእዜ | 4 | 13 | ዘይእዜ | 15 | 13 | ዘይእዜ | 19 | 13 | ዘይእዜ | 38 |
| 14 | ዘአምላ ኪየ | 17 | 14 | ዘአምላ ኪየ | 17 | 14 | ዘአምላ ኪየ | 14 | 14 | ዘአምላ ኪየ | 48 |
| 15 | ዘናሁ | | 15 | ዘናሁ | | 15 | ዘናሁ | | 15 | ዘናሁ | |

www.ethiopianorthodox.org

## ፬ኛ የድጓው ዝርዝር ቊጥርና የዘመኑ አከፋፈል ።

| | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሠናይ | 12 | | ሠናይ | 4 | | ሠናይ | — | | ሠናይ | 16 |
| 16 | አርያም | 415 | 16 | አርያም | 252 | 16 | አርያም | | 16 | አርያም | 667 |
| 17 | እስመ | | 17 | እስመ | | 17 | እስመ | | 17 | እስመ | |
| | ለዓለም | 926 | | ለዓለም | 909 | | ለዓለም | 764 | | ለዓለም | 2599 |
| 18 | አቡን | 458 | 18 | አቡን | 437 | 18 | አቡን | 447 | 18 | አቡን | 1342 |
| 19 | ሀየንተ | | 19 | ሀየንተ | | 19 | ሀየንተ | | 19 | ሀየንተ | |
| | ቅኔዎች | 3 | | ቅኔዎች | | | ቅኔዎች | | | ቅኔዎች | 3 |
| 20 | ምዕዋድ | 1 | 20 | ምዕዋድ | 5 | 20 | ምዕዋድ | 1 | 20 | ምዕዋድ | 7 |
| | | | 21 | መወድስ | 3 | 21 | መወድስ | 1 | 21 | መወድስ | 4 |
| | | | 22 | ክብር | | | | | 22 | ክብር | |
| | | | | ይእቲ | 1 | | | | | ይእቲ | 1 |
| | | | 23 | ዝማሬ | 1 | | | | 23 | ዝማሬ | 1 |
| | | | 24 | ዕጣነ | | | | | 24 | ዕጣነ | |
| | | | | ሞገር | 1 | | | | | ሞገር | 1 |
| | | | 25 | ምቅናይ | 1 | | | | 25 | ምቅናይ | 1 |
| | | | | | | 22 | ሚበዝኁ | 1 | 26 | ሚበዝኁ | 1 |
| | | | | | | 23 | ብፁዕ | | 27 | ብፁዕ | |
| | | | | | | | ዘይሌቡ | 1 | | ዘይሌቡ | 1 |
| | | | | | | 24 | ኵልክሙ | 1 | 28 | ኵልክሙ | 1 |
| | ድምር | 3577 | | ድምር | 3474 | | ድምር | 3469 | | ድምር | 10.520 |

ዓመት እስከ ዓመት የሚዘመሩት እነዚህ ከዚህ በላይ የተዘረዘሩት ሲሆኑ ከነዚህም ውስጥ ብዙዎቹ ተራ የማይደርሳቸው በአንዳንድ አጋጣሚ ብቻ ተፈልገው ይባላሉ እንጅ በተወሰኑ በዓላት የሚዘመሩት የተወሰኑ በመሆናቸው የዓመት በዓላት ፤ የዓመት መዝሙር ፤ የዓመት አቡንና እስመ ለዓለም ተብለው ተለቅመው የወጡ የታወቁ ናቸው ።

እነዚህም ፰ቱ ጸዋትወ ዜማዎች በሚለው መጽሐፍ ታትመው ይገኛሉ፤ ይሁን እንጅ አንዳንድ ድጓ በጉንጩ የሚባሉት ከታወቁት መዝሙሮች ሌላ ከባሕሩ ድጓ ገብቶ የዋኘ ያልታወቀውንም እስመ ለዓለም አቡን መዝሙር ፈልፍሎ ወይም እንዱን ወደ አንዱ በመለወጥ ያቀረበ እንደሆን ነው ።

## ፭ኛ የድጓ ትምህርት በዘመናት ።

ማንኛውም ትምህርት በኢትዮጵያ እየተሻሻለ እየተለዋወጠ አዲስም ነገር እየገባበት ሲሄድ ድጓው ከዘመን ወደ ዘመን ሲሸጋገር ምንም ያሳየው ለውጥ የለም ፤ ለምሳሌ የቅኔ ለውጥ የቅኔ ስልት ያው ጥንታዊ ይሁን እንጅ ሊቃውንቱ በተቀኙ ቊጥር ሁልጊዜ አዲስ ቅኔ መሆን ስላለበት አዳዲስ ቅኔ ይቀኙ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ስለዚህም መልካም እንደተባለ እንደተደነቀ ይኖራል ፤ ይህም ሳይሆን እንደ ቅዳሴው ዘመናዊ ጥንታዊ እንደ ስለልኩላና ደብረ ዓባይ የተደረገ መሻሻል የለም ፤ ይኸን ሲመለከቱት የዜማ ትምህርት ባለበት ተቋርጦ የቀረ ጥበብ እንደሆነ ሳያስገምት አልቀረም ።

የቆሜው የአጫብሬው የተጉለቴው ሌላም ይኸን የመሳሰለው ልዩነት ቢኖረውም ቅሉ ከቤተልሔሙ የበለጠ የአረጀ እንጅ የተሻለ ነገር የለውም ፣ በዚያውም ላይ ከቆሜው በስተቀር ሌላውን ባለማወቅ በሚዜምበት ጊዜ እንደያዙት ቀረ ይባላል እንጅ ለጥንታዊነቱ ከቶ አስረጅ የለውም ፣ እንዲያውም አሁን ሁሉም የያዘውን እየተወ ወደ ቤተልሔም ሲጓዝ ይገኛል ።

የአቋቋም ትምህርት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ በአርባ አራቱ የጐንደር አድባራት ልክ ፵፬ ይትበሃል አንድም የአቋቋም ስልት ለመገኘት ቻለ ። ከዚያውም ውስጥ በቅርቡ ጊዜ የተክሌ አቋቋም ሲወጣ እየተፈለሰፈ እየታደሰ እንደሚሄድ ያስረዳል ፤ ድጓ ግን በዚያው ባለሕበት ሳይባል አልቀረም ።

ይሁን እንጅ እንደ መሪጌታው ተራቃቂነት በዲስኩር ወይም በግሥ መልክ አዲስ ዜማ አዲስ ድርሰት ደርሶ መስጠት ይችላል ።

በዚህም መልክ በድጓው መካከል አንዳንድ ዲቃላ (ዓዋልድ) እንዳለ ይነገራል ።



www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ሆኖ ዲቃላው የትኛው እንደሆነ ፤ ወይም መቼ እንዴት እንደገባ አልታወቀም ። ከዚህም ጋር የአንደኛው አስተያየት ለ፪ኛው እንግዳ ሳይሆንበት አልቀረም ፤ ባንዳንድ በኩል ደግሞ ምልክቱም ከቀን ወደ ቀን አዲስ እየገባበት እየተጨመረበት እየተሻሻለ እንደሄደ እናገኘዋለን ፤ ለምሳሌ አጥሩን ዘለሽ ግቢ ።

የጐንደር ኢያሱ
ወርቅ ይዟል በራሱ
አይሸሽ አይዋጋ ----

ይኸን የመሰለ ብዙ በጐንደር መንግሥት ጊዜ እየገባ እንደ አብነት የሆነ ምልክት እናገኛለን ። ይኸም አዲስ ገብ ነገር አብሮ በቀል መስሎ እንደሌሎች ምልክቶች ሆኖ ይገኛል ፤ በዓዋልድም መልክ የገባው የዳንኤል ድጓ የተባለው በፋርጣና በጋይንት ደጋ ለደጋ የሚገኙት ሊቃውንት የጨመሩት ብዙ አዋልድ ያለው ነው እየተባለ ይነገራል ።

የምስክሩ ድጓ ሳይቀር በቤተ ልሔም በ፫ ይከፈላል ፤ ይኸውም ፩ኛው የዳንኤል ፤ ፪ኛ/ ጌታዬ እንግዳ እየሁ ፤ ፫ኛ/ ብርሃነ ዓለም የሚባል ነው ፤ ልዩነቱ ሲጠየቅ በዚሁ በዓዋልድ ብዛትና ማነስ በምልክቱ ልዩነት እንደሆነ እንረዳዋለን ፤ ከዚህም በቀር ሰንበት አምኜ የሚባል ከድጓው የተውጣጣ እስትጉቡእ አለ ፤ እርሱም የመሻሻል ምልክት እንደነበር ያመለክታል ። ስሙ እንደሚያመለክተው ሁሉ በፍና ተሳልቆ የወጣለትና ሊቃውንቱ የማይስማሙበት ቁንጽል ነገር እንደሆነ የሚገመት ነው። ከዚህም ጋር ማን እንደ አስተጋባው መቼ እንደተሰበሰበ በአዋጅ ባለመታወቁ ተቀባይነትን ሳያገኝ ይኖራል ፤ ሆኖም የጐንደር አቋቋም ተማሪ በመጠኑ አጥንቶ ለመውጣት ተፈላጊ የሆኑትን የዓመት ቀለሞችን ስለያዘለት ያወጣው ሳይሆን አይቀርም ፤ የተወሰነውም በጐንደር መንግሥት ነው የሚሉ አሉ። ምክንያቱም የዓመት መዝሙሮችን እስመ ለዓለሞችን አቡኖችን ሰብስቦ ስለያዘ ነው ፤ አንዳንዶች ደግሞ የተሰበሰበው ወይም የተወሰነው በሸዋ ነው የሚሉ አሉ ፤ ምክንያቱም በብዛትም የሚጠቀሙበት እነርሱ ናቸውና ፤ ከነስሙም ሰንበት አምኜ ሳይሆን ትንሹ ድጓ ይሉታል ፤ ይኸንም ብቻ ያጠናሉ ይላሉ ። ይሁን እንጂ ሊሻሻል ከተፈለገ የሚያስቸግር አለመኖሩ አንዳንድ መምህራን ድርሰት ደርሰው ምልክት አመልክተው እንደቅኔ ለትልቅ ሰው ሰጥተው ዋጋ አግኝተውበት ይኖራሉ ፤ በመጠኑም ከዚህ የሚከተለውን እንመልከት ።



www.ethiopianorthodox.org

(መሪ ጌታ ጥበቡ መንግሥቱ) ። በዚህ መልክ ዘመናዊ ድርሰት ሊደርስ በዚህም መልክ ምልክት ሊያመለክት ይችላል ።

## ምዕራፍ ፫ ።

## ጾመ ድጓ ።

ጾመ ድጓ ከድጓው ፩ኛ ክፍል የሆነ ለጾም ጊዜ አገልግሎት የተቀመረ ነው ፤ መጀመሪያ በድጓው ክፍል በአስተምህሮ ውስጥ ይገኝ ነበር ፤ ነገር ግን በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ በደብረ ነጐድጓድና በደብረ እግዚአብሔር የነበሩ ሊቃውንት አባ ጊዮርጊስን ይዘው ከዚህ ክፍል አውጣጥተው ራሱን የቻለ ክፍል እንዳደረጉት ይነገርላቸዋል ። አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ዘመናትን በመክፈል ድጓውን የደረሰ ቅዱስ ያሬድ ስለሆነ ጾመ ድጓውንም ራሱን የቻለ ክፍል አድርጎ በዚያኑ ጊዜ ደረሰው የሚሉ አሉ ።

የጾመ ድጓውም ዝርዝር ሁናቴ እንደሚከተለው ነው ።

## ጾመ ድጓ ።

በመኃትው ከዋዜማው በፊት ዘወረደ ብሎ ይጀምራል ፥ ራሱ ዘወረደም መኃትው ነው ፤ መኃትውም ማለት ከዋዜማ በፊት የሚባል አንድም የዋዜማ መግቢያ ማለት ነው ።

«ቀጥሎም ኵኑ እንከ» በሚለው ዋዜማ ይጀምራል ፤ ከዚያም ቀጥሎ በአምስት ይባላል ። እንዲሁም እግዚአብሔር ነግሠ ይትባረክ ሠለስት ሰላም ይባላሉ ፤ እነዚህ ሁሉ በ፩ ዋዜማ የሚባሉ ናቸው ፤ ድምራቸውም ፰ ይሆናሉ ።

## ፩ኛ መዝሙር ዘሰንበት ።

በአንድ እሑድ የሚባለው ጾመ ድጓ ፳፩ ዓይነት ነው ፥ እርሱውም የሚከተለው ነው ።

፩— ተቀንዩ
፪— ዘአምላኪየ
፫— በአምስት
፬— አርባዕት
፭— በአምስት ፪
፮— አንድ እግዚአብሔር ነግሠ
፯— ዕዝል
፰— ማኅሌት
፱— ዘይእዜ
፲— ስብሐተ ነግህ
፲፩— አራት እስመ ለዓለም
፲፪— አንድ አቡን
፲፫— ሠለስት
፲፬— ሰላም

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ፩— | ሰላም | ፪፻፷ |
| ፪— | ዋዜማ የጾሙ | ፵፱ |
| ፫— | በአምስት | ፩፻፲፬ |
| ፬— | ይትባረክ | ፰ |
| ፭— | እግዚአብሔር ነግሠ | ፲፮ |
| ፮— | መዝሙር | ፰ |
| ፯— | ዘአምላኪየ | ፵፫ |
| ፲፩— | መወድስ | ፪ |
| ፲፪— | እስመ ለዓለም | ፲፱ |
| ፲፫— | ቅንዋት | ፩፻፰፩ |
| ፲፩— | አቡን | ፩፻፰፫ |
| ፲፫— | ዕዝል | ፶፪ |
| ፲፮— | ዘይእዜ | ፲፩ |
| ፲፯— | ማኅሌት | ፶ |
| ፲፰— | ስብሐተ ነግህ | ፶፱ |
| ፲፱— | ክብር ይእቲ | |
| ፳— | ዝማሬ | |

፳፩— ዕጣነ ሞገር በድምሩ ፲ ይሆናል ፤ የምዕዋድ አቡን ፫ ፡ የሰሙነ ሕማማት አቡን ፩ ፡ የስቅለት መዝሙር ፫ ፡ የወንጌል መርገፍ እለ ወጻቢሖ ፲፮ ፡ በዕዝል ፈንታ የገባ ህየንተ ዕዝል ፬ ፡ በገብር ኄር የገባ ህየንተ አቡን ፳ በኒቆዲሞስ አቡን ሆኖ የገባ ዋዜማ ቤት ፮ ፤ በዘአምላኪየ ቦታ የገባ አርባዕት ፬ ነው ፤ በሠለስት ቦታ የገባ ነግሥ ፩ ነው ፤ በጾም ውስጥ ያሉ የግዕዝ ዋዜማዎች ብቻ ፮ ናቸው ።

ስብሐተ ነግሁ ፡ ዋዜማው ፡ ዘአምላኪየው ፡ ማኅሌቱ ፡ ሠለስቱ እየተመላለሱ ይባላሉ እንጂ በዝርዝር ቊጥር ይህን ያህል አይገኝም ።

የምህላ ምስባክ ፫ ፡ መዝሙሩ ፫ ፡ ሰላሙ ፫ ፡ በጾም ውስጥ ፫ት ቀን ምህላ አለ ፤ በሆሣዕና ይባእን ፤ መኑ ውእቱን ፤ የስቅለት ለመስቀልከ ፡ አምንስቲቲ ግፍያሙ ፡ ክርስቶስ አምላክነ ፡ ንሴብሖ ፤ የቀዳም ሥዑር አመ ተንሥአ ፡ እመስቀሉ ክርስቶስ ፡ ይትነሣእ ፡ ተዐውቀ እነዚህ ሁሉ አይቆጠሩም ፤ ምክንያቱም የግብረ ሕማማት ሥራ ስለሆኑ ነው ።

ምዕራፍ ፩ ።

## የድጓ ይትበሃል ።

ይትበሃል ማለት በዚህን ጊዜ ይኸ ይባላል ፤ እንደ ማለት ነው ፡ ግን ሥነ ሥርዓትም ማለት ይሆናል ፡ ለምሳሌ የቤተ ክርስቲያን ይትበሃል ስንል የቤተ ክርስቲ

www.ethiopianorthodox.org

ያን ሥነ ሥርዓት አንድም በዚያን ጊዜ ይኽ ይባል ብላ የወሰነችው ሕግ እንደ ሆነ ይታወቃል ።

በጠቅላላው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ድጓውን ተከትሎ ስለሚሄድ የድጓውን ይትበሃል ጠንቅቀን ማወቅና መከተል ያስፈልገናል ፤ እርሱም እንዲህ ሲል ይጀምራል ወግ ወሥርዓት እምዮሐንስ እስከ ዮሐንስ ፤ ወእምዮሐንስ እስከ ዘካርያስ ፣ ዮሐንስ ይትበሃል ።

እምዮሐንስ እስከ ዘካርያስ ፯ቱ ዕለታት ዮሐንስ ይባላል ። በ፰ መስከረም ዘካርያስ ይትበሃል ፣ እምሳኒታ ዘካርያስ እስከ ሕንፀታ ፍሬ ይትበሃል ። አመ አሡሩ ወ፮ሱ ሕንፀት ይትበሃል ።

ከ፲፯ እስከ ጾዓተ ክረምት መስቀል ይትበሃል

ከ፳፮ እስከ አባ ዮሐኒ ጽጌ ይትበሃል

እምሳኒታ አባ ዮሐኒ እስከ ስብከት አስተምህሮ ርኁቀ መዓት መሐሪ ይትበሃል ።

<u>ስብከት</u> ፤ ለእመ ኮነ ኤልያስ በሠሉስ አመ ፲ ወ፫ ግበር ፤ በረቡዕ ለእመ ኮነ አመ ፲ ወሰኑዩ ግበር ፤ በሐሙስ ለእመ ኮነ አመ ፲ ወአሚሩ ግበር ፤

በዓርብ ለእመ ኮነ አመ ፲ሩ ግበር ።

በቀዳሚት ለእመ ኮነ አመ ተሱዑ ግበር ።

በእሑድ ለእመ ኮነ አመ ሰሙኑ ግበር ።

በሰኑይ ለእመ ኮነ አመ ሰቡዑ ግበር ።

ከስብከት እስከ ብርሃን ያለው ክፍለ ጊዜ ሁሉ በአንድ ስም ስብከት ይባላል ።

ከብርሃን እስከ ኖላዊ ያለውም እንዲሁ ብርሃን ይባላል ። ከኖላዊ እስከ ታኅሣሥ ፳፮ ያለው ጊዜ ኖላዊ ይባላል ። ፳፯ኛው ቀን ግን ተለይቶ መርዓዊ ይባላል ። ፳፰ኛው ቀን ደግሞ ጌና ወመርዓዊ ይባላል ። በዓለ መርዓዊን ከልደት አስቀድሞ ማድረግ ተገቢ ነው ፣ ይኸውም ፩ ቀን ነው ፤ በ፳፱ኛው ቀን ግን ልደትን ማድረግ ተገቢ ነው ፣ በአንድ ሳምንት ውስጥ ግን ልደት ይባላል ። ወበካልእ ሰንበት ዘውእቱ ናዝሬት ወሕፅነት ይትበሃል ። እምገሃድ እስከ ቀበላ ጾም ተወልደ ፣ አንሶሰወ ፣ አስተርአየ ይባላል ። ከጥምቀት በኋላ ከእሑድ እስከ መርዓዊ ያለው ጊዜ ጥምቀት ከብካብ አዊኖተ ወይን ይባላል ፣ እንደ ሰንበትም ይቈጠራል ።

ከቅበላ እስከ ሆሣዕና ያለው ጊዜ ደግሞ ጾም ይባላል ። ከሆሣዕና እስከ ፋሲካ ሐመ ይባላል ።

በዓርብ ተሰቅለ ሞተ ይባላል ። ከፋሲካ እስከ ዕርገት ፋሲካ ፤ ትንሣኤ ይባላል ፤ ሰንበት ነውና ። የፋሲካ ማግስት ሰኞ ጸአተ ሲኦል ማዕዶት ይባላል ። ማክሰኞ ደግሞ ቶማስ ይባላል ። ረቡዕ አልዓዛር ፣ ሐሙስ አዳም ፣ ዓርብ ቤተ ክርስቲያን ፣ ቀዳሚት አንስት ይባላል ፣ ከዕርገት እስከ አባ ገሪማ ዕርገት ይባላል ። ከአባ ገሪማ እስከ በዓተ ክረምት አስተምህሮ ይባላል ። አስተምህሮ በየቦታው ይገባል ፣ ያልነው ስለዚህ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ከበዓተ ክረምት እስከ ቁርቆስ ዘርእ ፤ ደመና ፤ ጊሜ ፤ ክረምት ይባላል ። ከቁርቆስ እስከ ማኅበር መብረቅ ፤ ባሕር አፍላግ ፤ ጠል ፤ ነጐድጓድ ይባላል ። ከማኅበር እስከ አብርሃም ደስያት ፤ ዕጕለ ቋዓት ፤ ዓይነ ዡሉ ይባላል ።

ከአብርሃም እስከ ዮሐንስ ፤ ጐኅ ጽባሕ ፤ ነግህ ፤ መዓልት ፤ ብርሃን ይባላል ። በጳጉሜን ምጽአት ይባላል ።

ምዕራፍ ፫ ።

# ክፍለ ዘመናት ።

## ፩ኛ ክረምት ።

የቤተ ክርስቲያናችን ይትበሃል ለዘመናት ክፍል ስለሠራ ድጓውም ያንኑ ተከትሎ በ፬ ክፍል ክፍሎ እንደሚከተለው ያመለክታል ፤ ዓመቱ በመላ ዓውደ ዓመት ይባላል ፤ ዓውደ ዓመትም ፫፻፷፭/፫፻፷፮ ይሆናል ።

በዘመነ ክረምትና በመፀው እንዲሁም በሐጋይና በፀደይ ዕለታት ጳጉሜን ትቶ በ፬ ዘመናት ቢከፍሉት ፺፩ ፺፩ ቀን ለአራቱ ይደርሳል፤ይኸንም ለማስረዳት እንዲህ ይላል።

ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ክፍለ ዘመኑ ለክረምት ትዌጥን አመ ፳ወ፮ ለሰኔ ወትፈጽም አመ ፳ ወሐሙሱ ለመስከረም ። ኍልቈ እሉ ዕለታት ተስዐ ውእቱ ፤ እምዝ ኢየሐፅፅ ወኢይትዌሰክ ወበውስቴቶሙ ሀለዉ ፫ቱ አዝማን ንኡሳን ዘመነ ዮሐንስ ፤ ወዘመነ ፍሬ ፤ ወዘመነ መስቀል ይላል ።

በዝርዝር ለማስረዳት ደግሞ እንዲህ ይላል ፤ ዘመነ ዮሐንስ ትዌጥን አመ አሚሩ ለመስከረም ወትፈጽም አመ ሰሙኑ ለመስከረም በዚህም ጊዜ «ንስሑ ወእመኑ እስመ ቀርበት ደእቲ መንግሥተ ሰማያት» እያለ አሕዛብን ስለአስተማረና ፍጻሜ ስምዑም በዚህ ስለሆነ ክፍለ ዘመኑ ዮሐንስ ተብሏል ። የነዚህም ዕለታት ቊጥራቸው ፳፫ ናቸው ።

ዘመነ ፍሬ ትዌጥን አመ ተሱዑ ወትፈጽም አመ ፲ ወ፮ ለመስከረም የእነዚህም ዕለታት ቊጥር ፳፫ ናቸው ፤ ምክንያቱም ጌታችን ትምህርቱን በፍሬ እየመሰለ ለሐዋርያት የማስተማሩ ምሳሌ ነው ።

ዘመነ መስቀል ትዌጥን አመ ፲ ወ፯ ለመስከረም ወትፌጽም አመ ፳ ወሐሙሱ ይላል ። የነዚህም ዕለታት ቊጥር ፱ ብቻ ናቸው ፤ ይኸንም ለማስረዳት «አካህን አእምር ጥንቁቀ እስመ ኢይውሕድ እምተሰዓቱ» ይላል ። ይኸውም ምሳሌ አለው ምሳሌውም ፪ ዕለታት እሌኒ ምህላ አድርጋ መስቀሉን የማግኘቷ ሁለቱ ዕለታት የአጼ ዳዊትና የአጼ ዘርዓ ያዕቆብ የአባትና የልጁ መስቀሉን ወደ ግሸን ያስገቡበት ምሳሌ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

አው አሐደ ይከውን ። አካህን ለቡ ዘንተ በተጠናቅቆ ከመ ኢይምሰልከ ዘመነ ኖላዊ ዘይትረከቡ ዠለሄ ፯ ዕለተ ። እሥራኤል ጠባቂ እንደሌለው መንጋ ተበታትነው ሲኖሩ ነቢያት ስለክርስቶስ መምጣት ተገልጦላቸው ጠባቂ መጣልን ፤ የእሥራኤል ጠባቂ አንተነህ ፤ ኖላዊሆሙ ለእሥራኤል አጽምዕ እያሉ ተናግረው ነበርና ያነን ለማ ስታወስ ኖላዊ አለ ። ኖላዊ የተባለው ስምንት ቀን ሲሆን ሁልጊዜ ልክ አይመ ጣም ፡ አንድ ጊዜ ከፍ አንድ ጊዜም ዝቅ ይላል ፡ ምሳሌም አለው ይኸውም ዝቅ ማለቱ በኖላዊ ስለተመሰለ ፤ ከፍ ማለቱ ደግሞ ሥልጣነ መለኮቱ ሳይለየው ከድን ግል የመወለዱ ምሳሌ ነው ።

በዚህ መልክ ዘመነ መፀው ይሔዳል ፤ በውስጡም ያሉ ንዑሳን ዘመናት ቢሆኑ በዚህ መልክ ይሄዳሉ ።

## ፫ኛ ሐጋይ ።

ሐጋይ ማለት ደረቅ ፤ ፀሐይ ማለት ነው ፤ እርሱም ከታኅሣሥ ፳፮ እስከ መጋ ቢት ፳፭ ድረስ ያለው ጊዜ ነው ። ስለዚህም የቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓት እንዲህ ይላል ፤ «ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ክፍለ ዘመኑ ለሐጋይ ፤ ትዌጥን አመ ፳ወ፮ ለታኅሣሥ ወትፌጽም አመ ፳ ወሐሙሱ ለመጋቢት ወኍልቈ እሉ ዕለታት ተሰዓ ውእቱ ፤ ወእምዝ ኢየሐፅፅ ወበውስቴቶሙ ሀለዉ ንዑሳን አዝማን ፬ቱ ዘው እቶሙ ዘመነ ልደት ፤ ዘመነ ናዝሬት ፤ ዘመነ ጥምቀት ወአስተርእዮ ፤ ወዘመነ ጾም ። ዘመነ ልደት ትዌጥን አመ ፳ ወተሱዑ ለታኅሣሥ ወትፌጽም እስከ አሐቲ ሰንበት ።

ዘመነ ናዝሬት ትዌጥን ድኅረ አሐቲ ሰንበት ፡ ወበሳኒታሁ ሰኑዩ ትዌጥን ወት ፌጽም አመ ፲ ለጥር ዘውእቱ ጥምቀተ ገሃድ ፤ ለእመ ኮነ ልደት በሰኑይ ፩ተ ዕለተ
በሠሉስ ለእመ ኮነ ፮ተ ዕለተ ።
በረቡዕ ለእመ ኮነ ፯ተ ዕለተ ።
በሐሙስ ለእመ ኮነ ፰ተ ዕለተ ።
በዓርብ ለእመ ኮነ ፱ተ ዕለተ ።
በቀዳሚት ለእመ ኮነ ፲ተ ዕለተ ።
በእሑድ ለእመ ኮነ ፲ተ ወ፩ደ ትረክብ ናዝሬት ። ለቡ ዘንተ በተጠናቅቆ ዘመነ ጥም ቀት ወአስተርእዮ ትዌጥን አመ ፲ወ፩ ለጥር ወትፌጽም አመ ፴ሁ ለጥር ፡ ወኍ ልቈ እሉ ዕለታት ፳ ውእቱ ዘይከውን በርደቱ ለጾም ወለእመ የዓርግ ጾም ኀበ ላዕላይ ቀመር ዘመነ አስተርእዮ ይበጽሕ እስከ አመ ሠሉሱ ለመጋቢት ፤ ወኍልቈ እሉ ዕለታት ፶ወ፫ ውእቱ እምዝ ኢየሐፅፅ ወኢይትዌሰከ ።

በዓለ መርዓዊ እምቅድመ ቀበላ ጾም ፯ተ ዕለተ ግበር ። ዘመነ ጾም ለእመ ትዌ ጥን አመ አሚሩ ለየካቲት ወትፌጽም አመ ፳ ወኀሙሱ ለመጋቢት ፤ ወኍልቈ እሉ ዕለታት ፶ወ፭ቱ ፤ ወለእመ ይበውእ ጾም አመ ሐሙሱ ለመጋቢት ይትፌጸም አመ ፳ ወተሱዑ ለሚያዝያ ፤ ወኍልቈ እሉ ዕለታት ፶ወ፭ ። ወእምዝ ኢየሐፅፅ ወኢይ

www.ethiopianorthodox.org

ውሕድ ። ወኢይትዌስክ ። አመ አሚሩ ለየካቲት እስከ ሐሙሱ ለመጋቢት የዓርግ ወይወርድ በዓተ ጾም ።

## ፩ኛ ፀደይ ።

ፀደይ ማለት ዘመነ ዘርእ ዘመነ በልግ ማለት ነው ፤ እርሱም ከመጋቢት ፳፮ እስከ ሰኔ ፳፭ ድረስ ነው ፤ እንደ ቤተ ክርስቲያናችን ሥርዓትም ስለ እርሱ እንዲህ ይላል ፤ ወለእመ ፈቀድከ ታእምር ክፍለ ዘመኑ ለፀደይ ትዌጥን አመ ፳ወ፮ ለመ ጋቢት ወትፌጽም አመ ፳ወ፭ ለሰኔ ፤ ወኍልቈ እሉ ዕለታት ተስዓ ውእቱ ። ወሀ ለዉ በውስቶቴሙ ፬ቱ አዝማን ንዑሳን ። ዘውእቶሙ ዘመነ ትንሣኤ ፤ ዘመነ ዕርገት ፤ ዘመነ ጰራቅሊጦስ ፣ ዘመነ አስተምህሮ ፣ ዘመነ ፋሲካ ።

ዕርገተ ጾም ይከውን አመ ፳ወ፯ ለመጋቢት እስከ ፴ሁ ለሚያዝያ እምዝ ኢየዓርግ ፣ ወኢይወርድ ። ወኍልቈ እሉ ዕለታት ፴ ወ፭ ውእቱ በዝየ የዓርግ ወይ ወርድ ወይተመያየጥ ።

ወለእመ ኮነ በዓለ ፋሲካ አመ ፴ሁ ለሚያዝያ ዘመነ ጰራቅሊጦስ ይትፌጸም አመ ፳ወ፯ ለሰኔ ወአሜሃ አልቦ ዘመነ አስተምህሮ ። ኢይትረከብ በላዕላይ ቀመሩ ለፋሲካ ፤ ባሕቱ እምክረምት አሐደ ዕለተ ታመጽእ ለዘመነ ጰራቅሊጦስ ። ወኍልቈ ዘሙኑ ለትንሣኤ ፴ወ፱ ውእቱ እምዝ ኢየዓርግ ዘመነ ዕርገት እም ፴ ዕለት ትዌ ጥን ወትፌጽም ፤ በ፲ቱ ዕለት እምዝ ኢየሐፅፅ ። ዘመነ ጰራቅሊጦስ ትይዌጥን በ፵ ዕለት ወትፌጽም ወትረ በእሑድ አመ ሰሙኑ ፤ ለእመ ረከብከ ዘመነ አስተምህሮ በዘመነ ዕርገት ጰራቅሊጦስ ፤ ምህላ ጰራቅሊጦስ ወአስተምህሮ ይገኛል ፤ በዚህም ጊዜ ወትብል ሠውር ፣ ወኍልቈ እሉሂ እምትንሣኤ እስከ ተፍጻሜተ ጰራቅሊጦስ ፶ወ፯ ውእቱ ።

ምዕራፍ ፮ ።

## የድጓ ቤቶች ።

የድጓ ቤቶች ስንል በዚህ ምዕራፍ ስለ ትምህርት ቤቶች መናገራችን አይ ደለም ። የድጓ ቤት ፤ የቅኔ ቤት ፤ የመጽሐፍ ቤት ሲል በእርግጥም ትምህርት ቤቱን ያመለክታል ፤ ከዚህ ላይ ግን የድጓ ቤቶች ስንል የድጓውን የዜማ ስልት አንድም ወገን ወገኑን የሚገልጥና የሚያስረዳውን መንገድ አንድ የሆነውን ነው ።

ይኸን የመሰለውን መንገድ በድጓ ትምህርት ቤት ይሉታል ። ዜማ ለመማርና የአንዱን ከሌላው ለመለየት መጀመሪያ ምልክቶችን ጠንቅቆ መለየትና ማወቅ ያስፈልጋል ፤ እንዲሁም በሁለተኛ ደረጃ ቤቶችን ለይቶ ማወቅ ተገቢ ነው ፤ እን ዲህ የሆነ እንደሆነ ደቀ መዝሙሩ ያለ ምንም ችግር የቀረበለትን ሁሉ ሊያዜም ይችላል ፣ መምህሩንም ብዙ ጊዜ አያስቸግርም ።

www.ethiopianorthodox.org

ድጓ እንዲሁ አገኝ አጣውን የተወሰነ ትምህርት አይደለም ፤ ነገር ግን ንባቡ የተመጠነ የተለካ ትምህርት ነው ፤ ስድ ንባብም ብቻ ሳይሆን የግጥም መልክ ያለው ከፍተኛ ድርሰት ነው ።

ይኸን ምጣኔ አንድም የመንገድ ዓይነት ለመለየት ቤቶችን ለይቶ ጠንቅቆ ማወቅ በግድ ያስፈልገዋል ። እያንዳንዱ ቤት በቃሉ አሰካክ በሃሌታው በንባቡ በዜማው ተመሳሳይ የሆነ መንገድ አለው ፤ እርሱንም ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

## ፩ኛ የግዕዝ አቡንና የመዝሙር ቤቶች ።

| ምሕፃረ ቃል | | ሙሉ ንባብ |
|---|---|---|
| ፌ | ሐ | ሐዳፌ ነፍስ |
| ጉሥ | ለ | ለንጉሥ |
| ማ | መ | ማይ ጥቀ |
| ኸ | መ | መኸሐት ሠርዓ ሰንበተ |
| ሰ | ሰ | ሰብሕ |
| በ | በ | በዝንቱ ማይ |
| ባ | | ባኡ |
| ብ | | ብርሃነ ሕይወት |
| ቀ | ቀ | ቀደሳ |
| ሥ | ነ | ነገሥት |
| ነ | | ነአምን በአብ |
| ታ | | ኑ ኑታ መሰለ ምሳሌ |
| ግድ | | ን ሰግድ |
| ቡ | አ | አ ቡነ |
| ኪ | | አምላኪየ አምላኪየ |
| ግ | | አድግ አልጸቀ ጾም |
| እ | | አርእየነ |
| ሁ | | አንተ ኬንያሁ |
| ሚ | | አግዳሚ |
| ሐ | | አመ መድቅሐ |
| ሩ | | አእምሩ |
| ድም | | አቀድም |
| ቆ | | አልጺቆ |
| ቱ | | አንተ ውእቱ |
| ዓቢ | | ዓቢይ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ኝ | | አዝፋኝ |
| እፎ | | እፎ ተወልደ |
| ራኒ | | ዕዝራኒ ርእያ |
| ሮ | | አፍቂሮ |
| ሮ | | ኢተዘኪሮ |
| ፊ | ክ | ክነፊ ርግብ |
| ዶ | ወ | ወልዶ መድኅኒ |
| ወብ | | ወብዙኃን |
| ዡ | | ወዡሉ ነገራ |
| ወበ | | ወበውእቱ መዋዕል |
| ያ | ዘ | ዘይቤ ሐዋርያ |
| የ | | ዘየእምን ብየ |
| ሮ | | ዘተናገሮ |
| ዘዮ | | ዘዮም መስቀል |
| ዕ | | ይስማዕ ሰማይ |
| ይ | | ይትፌሣሕ ሰማይ |
| ዎ | | ይሰጠዎ |
| ደ | ደ | ደምረነ |
| ዴ | | ዴግንዋ |
| ገሚ | ገ | ጊዜ ገሚድ |
| ግበ | | ግበሩ |
| ጸ | ጸ | ጸርሐት |

## ፲፯ኛ የአራራይ አቡንና የመዝሙር ቤቶች ።

| | | |
|---|---|---|
| ዝ | ሐ | ሐዋዝ |
| ገ | | ሐረገ ወይን |
| ሐጸ | | ሐጸበ እግረ አርዳኢሁ |
| ሀ | | ሀላዊ ዘአብ |
| ሐነ | | ሐነፀ |
| ድ | መ | መጽአ ወልድ |
| ጌል | ሰ | ሰባኬ ወንጌል |
| ያ | | ሰማያ አብርሃም |
| ቀዳ | ቀ | ቀዳሚ ዜማ |
| ሙ | በ | በእንተ ዕበዮሙ |
| ረ | | በቀዳሚ ገብረ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ነዩ | ተ | ተቀነዩ |
| ዊ | አ | አረጋዊ |
| ታ | ኑ | ኑኑታ መሰለ ምሳሌ |
| ር | | እንዘ ይነብር |
| ጣ | | ዕጣነ ሞገር |
| ና | | እስመ ናሁ |
| ኒ | | እስመ ጽልመትኒ |
| እጎ | | እጎትነ ይብልዋ |
| ኩ | ከ | ኩኑ እንከ |
| ዋ | ወ | ዋዜማ |
| ወረ | | ወረደ ቃል |
| ዘል | ዘ | ዘልፈ ነአኩቶ |
| ሴ | | ዘሙሴ |
| ቦ | | ዘይገለብቦ |
| ኬ | | ዝኬ ውእቱ |
| ጣሴ | | ዝስኩሰ ሚካኤል |
| ሃ | ይ | ይገብር ነግሃ |
| ቲ | | ይእቲ ማርያም |

## ፫ኛ የዕዝል ቤት ።

| | | |
|---|---|---|
| ስቡ | ሰ | ስቡሕ በውስተ ቅዱሳን |
| በአ | በአ | በአማን ቃልከ |
| ጢ | ተ | ተመየጢ |
| ግድ | ን | ንስግድ |
| ኑ | | ንዜኑ |
| ጣ | ዕ | ዕጣነ ሞገር ወደሞ ክቡረ |
| ጸቀ | | አልጸቀ ሳውል |
| ብፁዕ | | ወብፁዕሰ |
| ድየ | ወ | ወሪድየ |
| ኩ | ደ | ድኩሌ |
| ገ | ገ | ገብርኤል አብሠራ |

## ፬ኛ የግዕዝ እስመ ለዓለም ቤት ።

| | | |
|---|---|---|
| ዕ | ሰ | ስማዕ ሰማይ |
| ቁ | ቀ | ቁም በዘሀሎከ |

www.ethiopianorthodox.org

| | | |
|---|---|---|
| ቅል | | ቁም ዘኢያንቀለቅል |
| ቁሪ | | ቁም አንገርጋሪ |
| ልዎ | ተ | ተሰአልዎ |
| ጉ | | ትጉሀን |
| ሙ | ነ | ነገሮሙ በምሳሌ ። |
| ኑ | | ንዜኑ |
| ግድ | | ንስግድ |
| ነ | አ | አስተጋብዓተነ |
| ዮ | | አስተርእዮ |
| ሚ | | አግዳሚ |
| ቱ | | አንተ ውእቱ |
| ሪ | | አንገርጋሪ |
| ጺሪ | | አርዋዊ አንገርጋሪ |
| ዐቢ | | ዐቢይ |
| ዕፁ | | ዕፁብኒ |
| ኩ | ከ | ኵሉ ዘገብሩ |
| ኮነ | | ኮነ |
| ው | ወ | ውድቅ |
| ፅ | ዘ | ዘየሐፅብ |
| ል | | ዘያንቀለቅል |
| ሉ | ይ | ይቤሉ |
| ይ | | ይትፌሣሕ |
| ገ | ገ | ገብርኤል መልአክ |
| ጾ | ጾ | ጾመ ሙሴ |

## ፳ኛ የዓራራይ እስመ ለዓለም ቤት ።

| | | |
|---|---|---|
| ሀ | ሀ | ህላዌ ዘአብ |
| ቁራ | ቁ | ቁም ዓራራይ |
| ሮን | በ | በትረ አሮን |
| ነሥ | ነ | ነሥአ |
| ናሁ | | ናሁ |
| ብሐ | | ንሴብሖ |
| ጺራ | አ | አርዋዊ ዓራራይ |
| ቦ | ዘ | ዘይገለብቦ |
| ጥ | ጠ | ጥበብ |

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፯ ።

# የግዕዝና የዕዝል ዘየዓርግና ዘይወርድ ።

የኢትዮጵያ ዜማ በግዕዝና በዕዝል እንዲሁም በዓራራይ የተቀመረ ለመሆኑ ቀደም አድርገን አስረድተናል ፣ ይኸም ማለት ሦስት ዓይነት የዜማ ስልት አለው ማለት ነው። እነዚህም የዜማ ዓይነቶች እያንዳንዳቸው የሚባሉበት የተወሰኑ ጊዜያቶች አሏቸው ፤ እነርሱም አንዳንድ ጊዜ ክፍለ ዘመናቱን ይከተላሉ ፣ አንዳንድ ጊዜ ግን ልዩ ምክንያትን በመፈለግ በግዕዙ አንድም በዕዝሉ ሊዘመር ይቻላል ። ስለ ዓራራይ ግን የተለየ አንድም የተወሰነ ጊዜ የለውም በዕዝሉም በግዕዙም ጊዜ ራሱን በመቻል አንድም በጣልቃ ገብነት ሊነገር ይቻላል ።

ብዙ ጊዜ ይኸን ሥርዓት ሊያፋልሰው የሚችል ለእመ ኮነው ነው ። ስለማንኛውም አገልግሎት ይኸ የግዕዝና የዕዝል ስልት የሚጠበቅ ሲሆን ፣ ይበልጡኑ ይኸ ነገር የሚጠበቅ በቅዳሴ ጊዜ ብቻ ነው ። እንዲሁም አልፎ አልፎ በኪዳን ላይ ፣ እንዲሁም በዕጣነ ሞገር በጣም ይጠበቃል ። ይኸውም ሁሉ ሆኖ ሊቃውንቱ ጠንቅቀው ክፍለ ዘመናትን በመከተል የወሰኑት ዘየዓርግና ዘይወርድ ከዚህ እንደሚከተለው ነው ።

## ፩ኛ በልዩ ልዩ ጊዜያት ።

በሚያዝያ ፴ ቀን ትንሣኤ የዋለ እንደሆነ እስከ ሰኔ ፯ ቀን ድረስ ቅዳሴው ዕዝል ይሆናል ፤ ነገር ግን ከርሱ ቀደም ብሎ ያለው ጊዜ ማለት ከጾመ ቅበላ ጀምሮ እስከ ሆሣዕና ዋዜማ ባለው ጊዜ ቅዳሴው ግዕዝ ነው ፤ ዕጣነ ሞገሩም እርሱን ይከተላል።

ከሆሣዕና እስከ ትንሣኤ ፣ ከትንሣኤም እስከ አባ ገሪማ ድረስ ዕዝል ይሆናል። ከአባ ገሪማ ሳኒታ እስከ መስከረም ፳፭ ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ ግዕዝ ይሆናል ።

ከመስከረም ፳፮ እስከ ኅዳር ፮ ድረስ ያለው ጊዜ ደግሞ ዕዝል ይሆናል ። ከኅዳር ፮ ሳኒታ (አባ ዮሐኒ) ጀምሮ እስከ ስብከት ያለው ጊዜ ግዕዝን ይመለከታል ። ከስብከት ጀምሮ እስከ ጾመ ቅበላ ያለው ጊዜ ግን ዕዝል ይሆናል ። ከዚህም በቀር በግዕዝ ጊዜ ስቡሕ ከተባለ ምልጣንም ከተመለጠነ ዕዝል ይቀደሳል ።

## ፪ኛ ኪዳኑ ።

ኪዳን በሌሊት ፤ በነግህ ፤ በሰርክ ሊደርስ እንደሚገባ ሆኖ በ፫ ዓይነት የተዘጋጀ ነው ። እንዲሁም ኪዳን በግዕዝ በዕዝል በዓራራይ የሚደረስበት የተወሰነ ጊዜ አለው ፤ ይሁን እንጅ ብዙ ጊዜ የሚደርሰው በዕዝል ነው ። ፫ኛው ኪዳን ግን ሁል ጊዜም ዓራራይ ብቻ ነው ፤ ነገር ግን ከዓመቱ ውስጥ ፲፩ ጊዜያቶች ብቻ ኪዳን በግዕዝ ይደርሳል።

እነርሱም ፩/ ታኅሣሥ ፳፰ ቀን የአማኑኤል ዋዜማ ።

፪/ የገብር ኄር ሳምንት ከሰኞ እስከ ዓርብ በአሉት በአምስቱ ቀኖች

፫/ የሆሣዕና ዋዜማ

www.ethiopianorthodox.org

፬/ የዕርገት ዕለት
፭/ የደብረ ታቦር ዋዜማና ዕለት
፮/ ዮሐንስ
፯/ መስቀል
፰/ ኅዳር ሚካኤል ሰኔ ሚካኤል
፱/ ስብከት

በእነዚህ ዕለታት ኪዳኑ በግዕዝ ይደርሳል ። በዚህ ጊዜ ግን ህየንተ ዕዝሉ በግ ዕዝ ይገባል ።

## ፫ኛ የዋዜማ ግዕዝ ።

ዋዜማ የሚደረሰው ብዙ ጊዜ በዓራራይ ነው ፥ ነገር ግን በዓመቱ ውስጥ ፲፬ ቀኖች ብቻ በግዕዝ ይደረሳል ፤ እርሱም የቅዱስ ዮሐንስ ፤ የመስቀል ፤ የኅዳር ሚካ ኤል ፤ የስብከት ፤ የአማኑኤል ፤ የኒቆዲሞስ ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፤ ረቡዕ ፤ ሐሙስ ፤ ዓርብ ፤ ጰራቅሊጦስ የሆሣዕና ፣ የዕርገት የሰኔ ሚካኤል ነው ።

ምዕራፍ ፰ ።

## የድጓ አድራሽ ።

የድጓ ተማሪዎች በልዩ ልዩ ቦታ እየተዘዋወሩ ረኃቡን ጥሙን ታግሠው ከተ ማሩ ድጓውንም መላልሰው ከዘለቁት በኋላ አመሉንም ከለዩት በኋላ ራስን ችሎ ለማስተማር ይቻል ዘንድ ድጓውን ለማስመስከር ወደቤተ ልሔም ይወርዳሉ ። ቤተ ልሔም የተባለችው ቤተ መቅደስ በታሪኳ ጥንታዊት በሥራዋም አስደናቂ የሆነች በእርግጥም የሥነ ጥበብ ምንጭ የባህል ምስክር ልትሆን የምትችል በቤገ ምድር ውስጥ በጋይንት አውራጃ የምትገኝ ገዳም ናት ።

ከግራኝ ወረራ በኋላ የተነሡ የድጓ መምህራን ሁሉ በዚች በተቀደሰች ቦታ የምስክርነት አብነት ሁነው ስለሚያስተምሩ የድጓ አድራሾች ሁሉ በብዛት ወደ ርሷ ይጐርፋሉ ። ተማሪዎችም ቤተ ልሔም ከገቡ በኋላ የድጓ አድራሾች ይባላሉ እንጅ ተማሪዎች አይባሉም ።

በመጀመሪያ ጊዜ ተማሪው ድጓውን ለመማር ብዙ ዘመን ይፈጅበት በብዙ ቦታም ይዘዋወር ነበር ። ነገር ግን ገና ተማሪ ሳለ ድጓውን ራሱ ጽፎ አመልክቶ ወደ ቤተ ልሔም ስለሚወርድ ምንም ችግር አይገጥመውም ነበር ፤ ምክንያቱም የሚጠብቀው የወንበር ተራ እንጂ የመጽሐፍ ተራ አይደለምና አንዳንዶች ደግሞ ራሳቸው ድጓውን በመጻፍ ፈንታ የሀገራቸውን የቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ተው ሰው በዚያው ለማስመስከር ይወርዳሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

አንዳንዶቹ ግን ይኸ ሁሉ ዕድል ሳይገጥማቸው ይቀርና ባዶ እጃቸውን ወደ ቤተ ልሔም ወርደው የወንበርም የመጽሐፍ ተራ በመጠበቅ ብዙ ዘመን ያሳልፋሉ ። የታወቀው የድጓው ማድረሻ ጊዜ ፬ ዓመት ያህል ሲሆን ፤ አንዳንዶች ፈጣን ተማሪዎች ግን ከዚህ በፊት ፈጽመው ይሔዳሉ ፤ አንዳንዶች ደግሞ እስከ ፯ ዓመት ድረስ ይቆያሉ ፤ እነርሱም አንዳንድ ጊዜ ማድረስ ሳይችሉ በመቅረት ነው ፤ እንዲሁም ከአደረሱ በኋላ የሚቆዩ አሉ ። የሆነ ሁኖ የድጓ አድራሽ ወደ ቤተ ልሔም ሲወርድ ደግሞ እርሱ የሚያስቀጽላቸው ለምንውም የሚያበሉት ወጥተው ወርደው የሚረዱት እስከ ፻ ተማሪዎች ፩ አድራሽ ይይዛል ፤ የአድራሹንም ችሎታ የሚያውቁ የሚያስመሰግኑትም እነዚሁ ተማሪዎች ናቸው ። መምህሩ ከሚሰጡት የምስክር ወረቀት ይልቅ ዐዋቂነቱ የሚታወቀው ተማሪ ሲከተለው ሲከበው ዐዋቂነቱንም ሲመሰክርለት ነበር ።

ይሁን እንጅ ድጓውን በተራ ጠብቆ መዝለቅ ባህሉን ም ጠንቅቆ ማወቅ ስላለበት በዚህም መሠረት ሲፈጽም እንዲያስተምር የምስክር ወረቀት ይሰጠዋል ፤ ከድጓውም ላይ ስለ ትክክልነቱ ማኅተም ይታተምለታል ፤ ጽሑፍም ለተወለደበት ወይም ለሚቀጠርበት ደብር ይጻፍለታል ።

ከዚህም ሁሉ ይልቅ የምስክሩ መምህር የልብ ጸሎት ያደርጉለታል ፤ የልብም ምርቃን ይመርቁታል ፤ መሪጌታም ብለው ይሰይሙታል ፤ ይኸም ማለት የድጓ መምህር እንዲሆን እንዲያስተምርም ዲግሪ ተሰጠው ማለት ነው ። ድጓውን አስመሰከረ ከማለት ይልቅ አስመረቀ ይባላል ፤ ምክንያቱም ከምስክሩ ወረቀት ይልቅ መርቀው ጸሎት አድርገው ይሰዱታልና ። በፊት ተማሪ ተብሎ ተጠራ በኋላ ደግሞ አድራሽ ተብሎ ተሰየመ ፣ ከዚህ በኋላ ግን ስሙ ይለወጥና ከተመረቀ ወዲህ መሪጌታ ተብሎ ይሰየማል ። ወዲያው ተማሪ እንደ ንብ አውራ ይከበዋል ፤ ያጅበዋል ፤ ዕለቱንም ወጥቶ ከአደረበት ቦታ ያልታሰበ ተማሪ ይከበዋል ። እርሱም በተማረው መልክ እንዲያስተምር አደራ የተጣለበት የተመረቀበት በመሆኑ ልዋል ልደር ቤት ልሥራ ጐመን ልዝራ ሳይል ወዲያውኑ ማስተማር ይጀምራል ።

በጥንት ዘመን በቤተ ልሔም አድራሽ ተብለው የሚጠሩት እስከ መቶ ከዚያም በላይ ይገኙ ነበር ። የአንዳንዱ አድራሽ ረዳት ደግሞ ሲጨመሩ ቤተ ልሔምን ሁል ጊዜ አዲስ ከተማ አድርገዋት ይገኙ ነበር ።

አሁን ግን አድራሾች ምንም ቢበዙ እስከ ፴ ብቻ ይገኛሉ ፤ የነዚህም ረዳቶች እንደ ጥንቱ ብዙዎች አይደሉም ፣ ሆኖም አንዱ ሲወጣ አንዱ ሲገባ በመገኘቱ እስከ አሁን ጉባኤው ሳይፈታ በመቀጠል ላይ ይገኛል ። ይኸም ሥነ ሥርዓት የሚፈጸመው በዜማ ፤ በቅዳሴ ፤ በዝማሬ መዋሥዕት መምህራን ብቻ ነው ። እንደ ቅኔ እንደ መጽሐፍ እንደ አቋቋም ያሉት መምህራን ግን ሁሉም በየበኩላቸው እየመረቁ ደቀ መዝሙሩን ስለሚያወጡ ይኸ ሁሉ ወግ ማዕረግ ለመምህራኑ አይደርሳቸውም በአሁኑ ጊዜም ምስክር የሚሆን ችሎታቸውን የሚገልጥ የምስክር ወረቀት የላቸውም ፤ ቦታውም የዚህ ምስክር ተብሎ ዝናው አይነገርለትም ።

www.ethiopianorthodox.org

ሁኖም ለቅኔ ጐጃም ፤ ዋድላና ጐንደር እንዲሁም ለመጽሐፍና ለአቋቋም ጐንደር ምስክር ናቸው ፤ እየተባሉ መነገሩ አልቀረም ፤ ተማሪም በዚሁ መሠረት ወደነዚህ አገሮች መዝመቱን አላቋረጠም ፤ ይሁን እንጅ ቤተ ክርስቲያን በአዲሱ አቅድ ወስና የምስክሩን ወረቀት አዘጋጅታ ባለመስጠት ስንት ሊቃውንት በየዓመቱ እንደሚወጣ ልታውቅ አልቻለችም ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩—በጥንት ዘመን ድጓውን መማር ትልቅ ትግል ሲሆን ፤ የበለጠ ትግሉ ድጓውን መጻፍ ነበር ፤ ስለዚህም ብራናውን መሰብሰብ ብዙ ጊዜ አጥፍቶ ድጓውን መጻፍ ነበር ።

ተማሪዎችም ከወጡበት ጊዜ አንሥቶ አስመስክረው እስኪመለሱ ብዙ ጊዜ ያጠፉ የነበር በዚህ ምክንያት ነው ። ይኸም ሆኖ ሁሉም የመጻፍ ዕድል ስለሌላቸው እየተዋሱም ስለሚያስመሰክሩ የድጓ መጽሐፍ በየትም ቦታ አይገኝም ነበር ።

አሁን ግን በግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ መልካም ፈቃድ ከነምልክቱ ታትሞ በርካሽ ዋጋ ስለሚገኝ ፤ አስተማሪና ተማሪ ከተገኘ የመጽሐፉ ችግር ተወግዷል ለማለት ይቻላል ።

፪—የቤተ ክርስቲያን ሥነ ሥርዓት የበዓላት የአጽዋማት ዘየዓርግና ዘይወርድ የሚጠበቀው በድጓ ትምህርትና በድጓ መምህራን ዘንድ ነው ፤ እንዲያውም ቤተ ክርስቲያን የምትከፈተው በድጓ መምህራን ነው ለማለት ይቻላል ።

ብዙ ጊዜ እንደሚተቸው የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን በልዩ ልዩ ጥበብ ሳትራቀቅ የቀረችው በዜማ ተወስና ነው ፤ ዜማ ቤተ ክርስቲያንን ገደለ ይላሉ ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ ራሱ ዜማው አንድ ጥበብ ከመሆኑ ሌላ ለሌሎችም ጥናት በር ከፍቶ የሚሰጥ ይኸው ትምህርት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፫ ።

# ዝማሬና መዋሥዕት ።

## ምዕራፍ ፩ ።

## ዝማሬ ።

### ፩ኛ የዝማሬ ታሪክ ።

ዝማሬ ማለት ዘመረ አመሰገነ ካለው ከግዕዝ የወጣ ቃል ነው ፤ ትርጉሙም ምስጋና ማለት ነው ። ይኸ ቃል በግዕዝም በአማርኛም ምሥጢሩም ቃሉም የተያያዘ ነው ፤ ይኸውም ብቻ ሳይሆን ሴማውያን በሆኑ ቋንቋዎችም ሁሉ ቃሉም ትርጉሙም እንደዚሁ ያለመለወጥ ይገኛል ። በሌሎች ሴማውያን ቋንቋ ዝማሬ ለሌላም ጩኸት የሚሆን ቃል ነው ፤ የሆነው ሆኖ ዝማሬ ማለት ዛሬ እኛ በአዲስ ዘመን የምንዘምረውን ሁሉ መዝሙር ዝማሬ እንደምንለው በዚያን ዘመን ይዘመር የነበረውን መዝሙር ሁሉ ዝማሬ ብለውታል ።

ይሁን እንጂ ዝማሬ የተባለው ትምህርት በዚህ በያዝነው ክፍለ ትምህርት ውስጥ የተለየ ስምን ፤ የተለየም ክፍልን ይዞ ይገኛል ። ስለዚህ ዝማሬ የተባለው ማንኛውንም ምስጋና ሳይሆን በተለይ የታወቀውን የቅዱስ ያሬድ የሆነውን ፪ኛውን ድርሰት የሚያመለክት ስም ሆኖ ይገኛል ።

ብዙዎች ሊቃውንት እንደሚሉት ቅዱስ ያሬድ ይኸን ዝማሬ የተባለውን ድርሰት የደረሰው ዙር አንባ በተባለው ገዳም ተገኝቶ ነው ፤ እርሱም ከአፄ ገብረ መስቀልና ከአቡነ አረጋዊ ጋር በዚህ ቅዱስ ቦታ ተገኝቶ የደረሰውና ፫ ዓመት በዚሁ ቦታ የአስተማረው እንደሆነ ይናገራሉ ።

ስለ ድርሰቱም የሆነ እንደሆነ ምንም ጥርጥር የሌለበት የርሱ ልዩ ድርሰት እንደሆነ የታመነ ነው ፤ ይኸንም ለመረዳት ስንፈልግ ፤ ድርሳነ ዑራኤልንና ክብረ ነገሥቱን ልንመለከት ይገባናል ።

እርሱም «ወመሀረ ባቲ ፫ተ ዓመተ በዝማሬ ቃሎሙ ለመላእክት» ሲል እናገኘዋለን ። ይኸም ድርሰት ለአገልግሎት የሚውለው በቅዳሴ ጊዜ እንደ መልክአ ቍርባን ሆኖ ከክብር ይእቲ በኋላ ነው ።

### ፪ኛ የዝማሬ ክፍል ።

ዝማሬ ሁል ጊዜም ቢሆን በቤተ ክርስቲያን የሚደረሰው ስለ ቅዱስ ቍርባን ክብር እንደሆነ የታወቀ ሲሆን ፤ ክፍሉም ራሱን በቻለ ክፍል በአምስት

www.ethiopianorthodox.org

ይከፈላል ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ። ሀ/ ኅብስት ፤ ለ/ ጽዋዕ ፤ ሐ/ መንፈስ ፤ መ/ አኰቴት ፤ ሠ/ ምሥጢር ናቸው ።

ምሥጢርና አኰቴት የሚባሉትን ክፍሎች ገባሬ ሠናዩ ቄስ በአንብሮተ እድ ጊዜ በመቅደሱ እንዳለ ሆኖ የሚዘምረው መዝሙር ፤ የሚጸልየው ጸሎት ነው ፤ ለምሳሌ «ለዝ ኅብስት ምስሐ በዓል ፤ ወለዝ ጽዋዕ ደመ ነበልባል ፤ ሦዕዎ እሥራኤል በመልዕልተ ቅዱስ መስቀል » የሚለው ዓይነት ነው ። ሌሎቹ ሦስቱ ግን ከመቅደሱ ውጪ በመዘምራኑ ብቻ የሚዘመሩ ናቸው ።

አምስቱ ዓይነት ዝማሬዎች ሁሉ በ፩ ቀን ይባላሉ ፤ የአባባላቸውም ዓይነት ሀ/ አኰቴት የተባለው በቅዳሴው መካከል ላይ ሀበነ ሲል ይዘመራል ። ለ/ ኅብስት ፤ ጽዋዕ ፤ መንፈስ ፤ የተባሉት ደግሞ ከቍርባን ቀጥለው ይዘመራሉ ፤ ሐ/ ምሥጢር የተባለው ግን በዕጣነ ሞገር ጊዜ ይዘመራል ፤ በጥንት ዘመን አምስቱም ክፍል በ፩ ጊዜ እንዲባሉ ያዝ ስለነበር ፤ በዚሁ መሠረት ይፈጸም ነበር ግን አሁን አንድ ብቻ ይባላል ።

ሁሉም በአንድ ጊዜ ሊባሉ እንዲገባም ከዚህ የሚከተለው ቅኔ ያስረዳል «በምሥጢረ አምላክ ተክዕወ ደመ አኰቴቱ ለወልድ ፥ ጽዋዓ መንፈስ ይጸልል ወይምላዕ እንዘ ሆሣዕና ኅብስተ ነድ» ። በዚህ በዝማሬ ውስጥ እንደ ሌላው ዜማ ሁሉ ሦስት የዜማ ዓይነቶች ፤ ግዕዝ ፤ ዕዝል ፤ አራራይ ፤ የሚባሉት ሁሉ ይገኙበታል ። የዓመት በዓላት ፤ ክፍለ ዘመናት ሌሎችም ይኸን የመሳሰሉ ነክ የሆኑ ክፍሎችም ይገኙበታል ። እንዲሁም ቅዱሳንን የሚመለከት ልዩ ልዩ ምሥጢር ይገኝበታል ። የሆነ ሆኖ ጠቅላላው ከላይ የገለጥናቸው ፭ቱ ሲሆኑ በዝርዝር የሚከተሉት ናቸው ።

## ሀ- ኅብስት ፤

ኅብስት የሚባለው ዝማሬ ልዩ ምልክቱ ወይም ሲጀምር እስመ ለዓለም ምሕረቱ ብሎ ነው ።

የሚገልጠውም ብዙ ጊዜ ፤ ስለ ኅብስተ በረከት ነው ፤ በጠቅላላውም ስለ ምሥጢረ ቍርባን ነው ። የርሱም ነክ የሆኑ በግዕዝ ፪፻፲፱ ፤ በዕዝል ፩፻፴፪ ሲሆን ፤ ድምር ፫፻፶፩ ዝማሬ ይገኛል ።

## ለ- ጽዋዕ ፤

ጽዋዕ የሚባለው ዝማሬ ሲጀምር እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር በሚል ነው ። የሚገልጠውም ስለ ጽዋዓ አኰቴት ስለሆነ ብዙ ጊዜ የደሙን ነገር ይናገራል ። የርሱም ነክ የሆኑ በግዕዝ ፪፻፳፩ ፤ በዕዝል ፵፰ ሲሆኑ ፤ ድምሩ ፪፻፷፫ ዝማሬ ይገኝበታል ።

## ሐ- መንፈስ ፤

መንፈስ የሚባለው ሲጀምር ፤ «ሃሌ ሉያ» ብሎ ነው ። የሚገልጠውም ከላይ

www.ethiopianorthodox.org

እንደተናገርነው የሥጋውንና የደሙን ነገር ሲሆን ፤ የዚህ ነክ የሚሆኑ በቍጥር ፺፫ ይገኛሉ ።

### ሙ- ምሥጢር ፤

ምሥጢር የሚባለው በቀጥታ ቅዱስ ቍርባንን የሚመለክት ነው ። በጠቅላላው እርሱን የሚመለከቱ ቍጥራቸው ግዕዙ ፪፻፬ ሲሆን ፤ ዕዝሉ ፶፫ ጠቅላላ ድምራቸው ግን ፪፻፷፯ ይሆናሉ ።

### ሠ- አኰቴት ፤

አኰቴት የሚባለውም በቍጥር ፸፩ ሲሆን ፤ እንደ ክብር ይእቲና ዕጣነ ሞገር ያሉ ፯ ቍጥር ያላቸው አሉ ። አዋልድም የሆኑ ፪ ይገኛሉ ። በጠቅላላው ሁሉም በአንድ ሲደመር ፩ሺ፱ ይሆናል ። በዝማሬ ውስጥ የዓራራይ ዜማ ከኀብስት ፳፫ ፤ ከጽዋዕ ፲ ፤ ከመንፈስ ፲ የሚገኝ ሲሆን ፤ ከዝማሬ ውስጥ የሚገኘው የዓራራይ ዜማ ያላቸው ቍጥራቸው ፵፫ ብቻ ናቸው ።

ይኸንንም በጠቅላላው ለመማር በተለይም አስተማሪ ለመሆን የአንድ ዓመት ጊዜ ይፈጃል ። ይኸም ሊሆን የሚችለው በጾመ ድጓና በሌላ በልዩ ልዩ ዜማ የበሰለ እንደሆን ነው ፤ ምክንያቱም በምልክቱ ሊረዳው ይችላልና ። የሆነ ሆኖ ፤ ዝማሬ ራሱን የቻለ የዜማ ድምፅ ወዝና ስልት አለው ፤ ራሱንም የቻለ የምስክር ቦታ አለው ፤ ቦታውም ዙር አባ የተባለው ታላቁ ገዳም ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ።

## መዋሥዕት ።

## ፩ኛ የቃሉ ትርጉም ።

መዋሥዕት ማለት ቀጥተኛ ትርጒሙ አይታወቅም ፤ ሥራው ግን እንደሚያመለክተን የሆነ እንደሆነ ለሙታን የሚደረግ የፍትሐት ጸሎት መሆኑ የታወቀ ነው ።

ይኸም ጸሎት ወይም ዝማሬ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፤ ለበዓላት፤ለአጽዋማት ፤ ይኸንም ለመሳሰሉ አገልግሎቶች የሚውል አይደለም ። ይሁን እንጂ በዓመት አንድ ጊዜ ብቻ እንደ ቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ተቈጥሮ የሚዘመርበት ጊዜ አለ ፤ እርሱም የቅዳም ሥዑር ዕለት ነው ፤ በዚያን ጊዜም ቢሆን ቅሉ በፍትሐት መልክ ይደርሳል እንጂ እንደ ሌላ የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ይቈጠራል ተብሎ አይደለም ።

በዚያም ጊዜ ቢሆን የሚደርስበት ምክንያት የሙታን በኵር ሆኖ የተነሣው ክርስቶስ የቅዳም ሥዑር በከርሠ መቃብር እንደዋለ ስለሚታመን በሰው ልጅ መልክ ፍትሐት ለማድረግ የተሰጠ ውሳኔ ነው ።

እንዲሁም ይኸን የመሰለ አገልግሎት አለ ፤ ይኸውም በሕማማት ሳምንት ለሙታን ፍትሐት የማይደረግ ስለሆነ ፤ በዚህ ዕለት ለሙታንም ፤ ለሕያዋንም የፍትሐት ጸሎት ለማድረግ ሲባል የገባ ጸሎት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸ መዋሥዕት የተባለው ጸሎት የቅዱስ ያሬድ ድርሰት እንደሆነ የታመነ ሲሆን ፤ ከዝማሬ ድርሰቱ ጋር አብሮ እንደደረሰው ይነገርለታል ስለዚህም በትምህርት ጊዜ አብረው ያስተምሩታል ። በሞያም ቢሆን ቅሉ የዚሁ ሞያ ያላቸው ሊቃውንት መዋሥዕቱን የሚያስመሰክሩ ዙር አባ በተባለው ገዳም ነው ። በስምም ቢሆን ያለመለያየት ዋዜ እንኳን ሳይሻ ዝማሬ መዋሥዕት በማለት ይጠሩታል ። ለሙታን መታሰቢያ ጸሎት በተደረገ ጊዜ እንደግንዘቱ ጸሎት ለሁሉም የግድ አስፈላጊ ሆኖ ከርሱ ጋር ጐን ለጐን ይደርሳል ። ስለዚህም ለዕለት ፍትሐት ፣ ለሙት ዓመት መታሰቢያ በጠቅላላው ፍትሐት በተደረገ ጊዜ ሁሉ ይደርሳል ። መዋሥዕት የኀዘን ዜማ ያለው ስለሆነ ፤ በተለይ ድምፃዊ ካህን ተመርጦ በተመስጦ ይዘምረዋል ። ይኸም ሳይደርስ የቀረ እንደሆነ የሙቱ ወገኖች ቅር ይላቸዋል ።

የሚዘመረውም የዳዊትን መዝሙር እየተከተለ በዓሉንም ነክ የሆነ አንድም የሙቱን የሕይወት ታሪክ ተከትሎ ነው ። በዚህ መልክ ጥንቱን የተዘጋጀ ስለሆነ ፤ ምሥጢር የጠነቀቀ ደቀ መዝሙር ሲቃኘው ዕለት የደረሰው ድርሰት መስሎ ሲያስደንቅ ይታያል ።

## ፪ኛ የመዋሥዕት ቍጥር ።

መዋሥዕት ለጊዜው ለዘመኑ ተስማሚ ሆኖ የተሠራ ነው አንድም የሙቱን የሕይወት ታሪክ የተከተለ ሆኖ ተሠርቷል ። ብዙ ቍጥር የያዘውም ለሁሉ ነክ እንዲገኝለት በማለት ነው ። ቍጥሩም የሚከተለው ነው ፤ የመዋሥዕት ቍጥር ፱፻፸፬ ብቻ ነው ። ከዚህ ውስጥ ግዕዝ ፤ መዋሥዕት እናቱ ብቻ ፷፻፫ ሲሆን ፤ ምልጣኑ ፷፻፫ ይሆናል ።

ከዚህ ትርፍ ፺ ይገኛል ። ዕዝል መዋሥዕት ደግሞ እናቱ ፷ ሲሆን ፤ ምልጣኑ ፷ ብቻ ነው ።

ዓራራይ መዋሥዕት ደግሞ እናቱ ፩፻፬ ሲሆን ፤ ምልጣኑ እንደዚያው ፩፻፬ የዚህ ሁሉ ጠቅላላ ድምር ከላይ እንደ ገለጥነው ፱፻፸፬ ሲሆን ፤ ይኸኛውም እናት እናቱን ብቻ ቈጥረን ነው ። ሁሉም የሚጀምረው በዳዊት መዝሙር ነው ፤ አንዳንድ ጊዜ ግን መጀመሪያውም መጨረሻውም የዳዊት መዝሙር ይሆናል ፤ እንዲህ ያለው ከርሠ ዳዊት ይባላል ።

## ፫ኛ ደንበኛ ፍትሐት ለማድረስ ።

የመዋሥዕት ጸሎት ለማድረስ በመጀመሪያ ጸሎተ አኰቴት ይደረጋል ፤ ቀጥሎም የዳዊት መዝሙር ይጸለያል ፤ እንዲሁም ውዳሴ ማርያም ይደገማል ፤ ከዚያም በኋላ ዕዝል ይመራና ይዘመማል ፤ ይመረገዳል ፤ ይጸፋል ፤ ቀጥሎ እንዘ ነአኵቶ ይደርስና አቡን ይመራል ። ከዚያም በኋላ ፳ ግዕዝ መዋሥዕትና ፤ ፩

www.ethiopianorthodox.org

ዕዝል ፤ ደግሞም አንድ ዓራራይ ይደርሳል ። ግዕዝ መዋሥዕት የሚደርሰው ሁል ጊዜ ከዳዊት መዝሙር ብቻ ሲሆን ፤ ዓይራራይ ግን ከዳዊት መዝሙር ውስጥ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር እምሰማያት ፤ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር ስብሐተ ሐዲሰ ፤ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ ከሚባሉት ብቻ ይደርሳሉ ።

ከነቢያት ውስጥም ደግሞ ይባርክዎ ኵሉ ግብረ እግዚእ ለእግዚአብሔር የሚባለው ብቻ ይገባል ፤ በዕዝል መዋሥዕት ጊዜ ግን ነቢያት ሁሉ እየገቡ ይባ ላሉ ። ከዚህ ሁሉ በኋላ ግን አቡኑ እንደ ገና ይዘመምና ይመረገዳል ፤ ይጸፋል ፤ ከዚህም በኋላ እስመ ለዓለሞች ይቃኛሉ ። እነርሱም አንድ ሌጣ ፤ አንድ ቅንዋት ነክ የሆነ ሁለቱም ይጸፋሉ ። ከዚህ አያይዞ ደግሞ ሠለስት ፤ ቀጥሎም ሰላም ይደርስና የአንድ ሙሉ ፍትሐት ፍጻሜ ይሆናል ።

## ፬ኛ የጉዞ ፍትሐት ።

የጉዞ ፍትሐት የሆነ እንደሆነ አደራረሱ እንደ ደንበኛው ፍትሐት ከላይ እንደተናገርነው ሆኖ ልዩነቱ አንድ መዋሥዕት ተመርቶ በመካከሉ ዳዊትና ውዳሴ ማርያም ይደገማል ፤ ሌላው አባባል ግን እንደዚያው ነው ። ጉዞም የተባለ በት ምክንያት ሬሣው ከቤቱ ከወጣ በኋላ አንዳንድ ምዕራፍ እያረፈ በጟቱ መንገደ ሰማያት ምሳሌ ይፈታልና ። ደንበኛው ፍትሐት ለሁሉ ትክክል ሲሆን ፤ ስልፉ እንዲሞቅ ለቀሶው ወግ እንዲያገኝ ከእገሌ ይልቅ የኔ ይብለጥ እያሉ ስለሚፈቱ ጉዞ ተብሏል ።

አንዳንዶች ደግሞ የአድልዎ ሥራ እንደተደረገባቸው ለእገሌ እንዲህ አደ ረጉ ለኔ ግን እንዲህ አላደረጉልኝም እያሉ ያማርራሉ ፤ ይኸንም ለማለት የቻሉት ሁና ቴውን በመመልከት ብቻ ነው ።

ብዙ ጊዜ ፍትሐቱ ደምቆ የሚታየው ፤ ካህን በሞተ ጊዜ ነው ፤ ምክንያ ቱም ካህኑ የነርሱ የቅርብ ወንድም በመሆን ከልብ ያዝኑለታል ፤ ደንበኛም ጸሎት ያደርሱለታልና ፤ በዚያን ጊዜ አደራረስ ይደርሳል ፤ ቅኔውንም ያጕር ፉታል ፤ ለተመልካችም ምነው እኔን ካህን ባደረገኝ ያሰኛል ። በዚህም መልክ የተመለከተ ገጣሚ እንዲህ አለ ይባላል ። «ካህንና ዶሮ ሲሞት ነው ኵራቱ ፤ በቁመናውማ ጥሬ ነው ራቱ» ። ይኸም ማለት በሕይወቱ ያልነበረው ክብር ይሰ ጠዋል ፤ ለማንም ያልተገባ ፍትሐት ይደርስለታል ማለት ነው ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩—ዝማሬ ፤ ማኅሌት ካልተቆመ ፤ ደብተራም ከሌለ አይባልም ፤ ምክን ያቱም ቀሳውስቱ ስለማያውቁት ነው ፤ አንዳንድ ቀሳውስት በቃላቸው የያዙትን ከእንዘ ብዙኃኑ ጋር ይሉታል ።

www.ethiopianorthodox.org

፱—መዋሥዕት መሪ ጌታ በሌለበት ፍትሐት አይደርስም ፤ ግንዘቱን ደግመው ሥርዓተ ቅዳሴውን ብቻ አድርሰው ይተዉታል ።

እነዚህ ነገሮች በቤተ ክርስቲያን ቋሚ የጸሎት ቦታ አላቸው ከተባለ በአስፈላጊነታቸውም ከታመነበት እንደ ቅዳሴው ትምህርት አብሮ መሰጠት አለባቸው ፤ ያለዚያ ግን ጸሎቱ እንደ ታጐለ ያስገምታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፪ ።

# አቋቋም ።

ምዕራፍ ፩ ።

## የአቋቋም ሥነ ሥርዓት ።

### ፩ኛ የአቋቋም ታሪክ ።

አቋቋም ማለት የመቆም ሥነ ሥርዓት የአቋቋምን ልክ መልክ የሚናገር ትምህርት ማለት ነው ። ማኅሌቱ ተቁሞ በሚሠራበት ጊዜ የአገልግሎቱን ሥነ ሥርዓት የዜማውን ስልት የሚገልጥ አቅድ ማለት ነው ። ይኸውም አቅድ የተጀመረ ፤ ልክና መልክ የወጣለት ስሙም እንዲህ ሆኖ የታወቀው በጐንደር መንግሥት ጊዜ ነው ፤ በተለይም በአጼ አድያም ሰገድ ኢያሱ ጊዜ እንደሆነ ይነገራል ፤ እንዲሻሻል ያደረገው ሊቅ ግን ዕጨጌ ቃለ ዓዋዲ የተባለ የዜማ ሊቅ እንደሆነ የተመሰከረለት ነው ።

የማኅሌቱ ሥነ ሥርዓት ጥንታዊ ሲሆን የተጀመረውም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ ነው ይባላል ፤ ጀማሪውም እርሱ ራሱ ነው ። እርሱም በጸናጽልና በከበሮ ምስጋና ለእግዚአብሔር ያቀርብና ማኅሌትም ይቆም እንደነበር በታሪክም በሥዕልም ሁልጊዜ ይገለጣል ፤ ማለት አጼ ገብረ መስቀል በበትረ መንግሥታቸው ጫፍ እግሩን የወጉት በማኅሌት ተመስጠው እንደነበር ታሪክ ይነግረናል ።

ይኸ አዲስ ነገር እንዴት እንደተጀመረ በምንስ ምክንያት ተጀመረ ብለን ጠለቅ በማለት የመረመርን እንደሆነ ግን አጥጋቢ መልስ አናገኝም ፤ የሆነው ሆኖ እንደ ቆሜ እንደ አጫብሬ እንደ ወንጨሬ እንደ ተጉለቴ እንደ ዋድሌ ያሉት ሁሉ አሁንም የአቋቋም ሥርዓት ሳይኖራቸው ጥሬውን ዜማ ተከትለው እንደሚሔዱት ሁሉ የኛውም እንደዚሁ ሳይሆን አይቀርም ተብሎ ያስገምታል ። በጐንደር መንግሥት ግን የሁሉም ትምህርት አቅድ እንደ ወጣለት ሁሉ የማኅሌቱም ሥነ ሥርዓት መልክ ሊያገኝና በአሁኑ አቅድ ሊሠራ ቻለ ።

በሌላ መልክ ሲተረክ ደግሞ ለመጀመሪያ ጊዜ ተደረሰ የተባለበት ቦታ ሐመረ ኖኅ ሠለስቱ ምዕት ሲሆን ደራሲውም ባሕታዊ ኤስድሮስ የተባለ ሊቅ ነው ፤ እርሱም ከዕጨጌ ቃለ ዓዋዲ በፊት ወይም በኋላ እንደሆን ግልጥ የሆነ የዘመን ልዩነት የለውም ፤ እንዲሁ በአፍ ሲተረክ የመጣውን በመያዝ እንጂ እውነቱ ይኸ ነው በማለት የተወሳ ዓመተ ምሕረት ይዞ የሚሔድ ታሪክ የለም ። ቀጥሎም ወደ ደብረ ገነት አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል ተላለፈ ይባላል ፤ ከዚያ ቀጥሎ ግን ወደ ቅዱስ ሩፋኤል ደረሰ ።

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያም ቀጥሎ ፬ቱ እንስሳ ፤ ከዚያም በኋላ ወደ ደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ደረሰ ። ከዚያም አልፎ ወደ ደብረ ኃይል በዓታ ገባና ወንበር ተዘረ ጋለት በአዋጅም ታወቀ ይባላል ። ነገር ግን ይኸን የዛሬውን አቅድ ሊያገኝና በበ ለጠ ሊሻሻል የቻለው በአጼ ተክለ ሃይማኖት ዘመነ መንግሥት እንደሆነ ይነገራል ።

ይኸንም እንደ አቀናበሩ የሚገመቱት ሊቃውንት ደግሞ ብዙዎች ሲሆኑ ከላይ ከገለጥናቸው ከሁለቱ ሊቃውንት በቀር ስመ ጥር በመሆን የታወቁት አለቃ ሎዜ ገብሩ የሸዋ ተወላጅና አለቃ ሐሤት የተባሉ የስሜን ተወላጅ ናቸው ።

እንዲሁም ሖሜር እሸቱ የተባሉትም ጭምር ይገኙበታል ፤ ይሁን እንጂ በዘ መን ማን ቅድሚያ እንዳለው አይታወቅም ። እየዋለ እያደረ ግን ከአንድ ይትበ ሃል ይልቅ ወደ ብዙ እየተከፈለ ስለሔደ በ፵፬ቱ ጐንደር አድባራት ልክ ፵፬ት ይትበሃል ለመሆን ቻለ ።

በሌላ መልክ ደግሞ ከዚህ በሚቀጥለው ዓይነት ይተረካል ፤ የአቋቋም ትምህርት መልክ ያገኘው በአጼ በካፋ ዘመነ መንግሥት ነው ፥ ቀማሪውም አዛዥ ድሜጥሮስ የተባሉ ሊቅ ናቸው ፤ ቦታውም በቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስ ቲያን ጐንደር ነው ። መምህር ተስፋ ከዚያ ተምረው ደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ ላይ ወንበር ዘርግተው አስተምረዋል ። ከዚህም ሲወርድ ሲዋረድ ከሖ ሜር እሸቱ ደርሷል ፤ ሖሜር እሸቱ ግን ለመሪጌታ ገብረ ዮሐንስና ለመሪጌታ ላቀው አስተምረዋል ። ከዚህ በኋላ መሪጌታ ገብረ ዮሐንስ ለላይ ቤት አብነት ሲሆኑ ፤ መሪጌታ ላቀው ደግሞ ለታች ቤት አብነት ሁነዋል ።

እነዚህ ፪ቱ የአንድ ቤት ተማሪዎች ሲሆኑ ወዝ በመለወጥ አንዳንድም ይትበሃል በማሻሻል ስለተለያዩ የላይ ቤት የታች ቤት የሚለውን ስያሜና ለውጥ ሊያመጣ ችሏል ።

የታች ቤት የሚባለው ከጃን ተክል ዋርካ በታች ያሉት ሲሆኑ ፤ የላይ ቤት የሚባለው ደግሞ ከጃን ተክል ዋርካ በላይ የሚገኙት አብያተ ክርስቲያናት ናቸው ። የሆነው ሆኖ አሁን የሚታወቁት የአቋቋም ቤቶች ዋና ዋናዎች ፬ ብቻ ናቸው ። እነዚህም የላይ ቤት የታች ቤት (በዓታ) ፤ የሳንኳ ፤ የተክሌ ናቸው ።

ሳንኳ የተባለው ከጐጃም ጠቅላይ ግዛት ሳንኳ ጊዮርጊስ ከተባለው እየተ ነሡ የመጡ ሊቃውንት የሠፈሩበት ቦታ ነው ። ይኸ ዓይነት መዝሙር የሚዘ መረውም በቊስቋምና ይኸንም በመሳሰሉት አድባራት ነው ። በጥንት ዘመን ከሳንኳ የሚመጡት ሊቃውንት ቅባቶች ስለነበሩ ፤ የሚዘምረውም እምነታቸ ውን የመሰለ አንድም የተከተለ ነበር ፤ ስለዚህም ይትበሃሉን እንደ ሃይማኖት አድርገው አጥብቀው ይይዙት ነበር ፤ አሁን ግን ስሙ እንጅ ወንበር የለውም ።

ከነዚህም ውስጥ ፩ኛ/ ጥንታዊውን አንድም ምልክቱን ተከትሎ የሚሔ ደው አቋቋም ታች ቤት አንድም በዓታ ተብሎ የሚጠራው ነው ፤ አቅድ አግ ኝቶ መንገድ አውጥቶ በለቀቃ የሚሔደው ደግሞ የላይ ቤት የተባለው ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የሳንኳ የተባለው ደግሞ እንዲሁ በቁም የሚዘመር ልዩ አካል ገዝቶ ብዙ ደቀ መዝሙር አውጥቶ ይገኝ የነበረው ከላይ የገለጥነው ነው ።

ተክሌ የተባለው ግን ከዚህ ከላይ ቤት የወጣ በቅርቡ በኛ ዘመን አለቃ ገብረ ሐና ለልጃቸው ለአለቃ ተክሌ በሥውር አስተምረው ያወጡትና በርሱ ስም የሚጠራ ነው ። ተጀመረበት የሚባለውም ደብር ፤ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ላይ ነው ፤ የሆነ ሆኖ አሁን ከጐንደር አቋቋም ጋር ተክሌው የሚወዳደር ሆኖ ይገኛል ፤ በተለይም ለዝማሜ (ለዘንግ) ጊዜ ተክሌ ፣ ለጸናጽል ጊዜ ደግሞ ጐንደሬ የሚፈለግ እንደ ሆነ ደቀ መዛሙርቱ ተስማምተውበታል ፤ በዚህም መልክ ደቀ መዛሙርቱ ማጥናት ጀምረዋል ። የላይና የታች ቤት እየተባለ የሚጠራው ስም የመጻሕፍትን ትርጓሜ ስም ተከትሎ ነው እንጂ ለአቋቋሙ የወጣ አልነበረም አሁን ግን የአቋቋሙም ትምህርት ይኸንኑ ስም የግሉ አድርጎት ስለሚገኝ በብዛት ይጠራበታል ።

ከ፩ እስከ ፫ ዓይነት የሰጠነው አስተያየት በየቦታው በሚተረከው መልክ ስለሆነ ፤ የዚህኛው እውነት የዚያኛው ግን ሐሰት ነው ልል ባለመቻሌ ሁሉንም አመልክቻለሁ ፤ የተሻለውን መያዙ የደቀ መዝሙር ፈንታ ነው ። ግን ዋና ዋና የአቋቋም ቤቶች እየተባሉ ይጠሩ የነበሩት ባህሉንም በየበኩላቸው ይዘው ይጠሩበት የነበር ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

፩ ደብረ ብርሃን ሥላሴ
፪ ደብረ ገነት አጣጣሚ ቅዱስ ሚካኤል
፫ እልፍኝ ቅዱስ ጊዮርጊስ
፬ መንበረ መንግሥት መድኀኔ ዓለም
፭ ቀሃ ኢየሱስ
፮ ደብረ ፀሐይ ቊስቋም
፯ ፋሲለደስ
፰ ዮሐንስ መጥምቅ
፱ ዳራ ገንዳ ኤዎስጣቴዎስ
፲ ወልደ ነጐድጓድ ዮሐንስ
፲፩ ደብረ ምጥማቅ
፲፪ ፊት አቦ

## የላይ ቤት ።

፩ ግምጃ ቤት ማርያም
፪ ቅዱስ ገብርኤል
፫ ዐቢየ እግዚእ
፬ ፊት ሚካኤል

www.ethiopianorthodox.org

# የታች ቤት ።

በዓታ ፤

## ከላይ ቤት የተለዩ ።

፩ ሩፋኤል
፪ ፬ቱ እንስሳ
፫ ሠለስቱ ምዕት
፬ ደብረ መንክራት ቅዱስ ቂርቆስ
፭ ኤዎስጣቴዎስ ናቸው ።

ከዚህ በላይ የተከፈሉት የአቋቋም ትምህርት ቤቶች በዜማ ፣ በይትበሃል ትንሽ ለወጥ ያድርጉ እንጅ በትምህርት አሰጣጥ በኩል ያላቸው ስልት ፩ ዓይነት ነው ። ይኸውም እንደሚከተለው በ፭ ይከፈላል ።

ሀ/ የዓመት በዓል
ለ/ መዝሙር ፤
ሐ/ አርባዕትና ቅኔ
መ/ የወር በዓል
ሠ/ ጾመ ድጓ ፤ ( ቅንዋት ) ነው ።

እነዚህን ሁሉ አጠናቀው ለማወቅ የተለየም ጥናት ለመውሰድ መምህራን ሆነው ለማስተማር የሚችሉ ናቸው ። ለራሳቸው በመጠኑ ዕውቀትን የሚገበዩ ግን የወር በዓላትንና የዓመት በዓላቱን በመጠኑ ይቀጥላሉ እንጂ ይኸን ያህል ርቀው አያጠኑም ፤ የሆነ ሆኖ አንድ ጊዜ መንገዱን ከዐወቁት ሌላውን ሁሉ በዚሁ መንገድ ለመራመድ ይችላሉ ። የ፭ቱም ዓይነት የትምህርት ክፍል እንደ ሚከተለው ይዘረዘራሉ ።

### ሀ/ የዓመት በዓል ።

የዓመት በዓል የሚባሉት የእያንዳንዱ ቅዱሳን የጌታም የእመቤታችንም የመላእክትም በዓላት ናቸው ፤ በእነዚህ በታወቁት በዓላት የሚዘመሩት የዓመት በዓላት ቀለማት ይባላሉ ። የዓመት ቀለማት ተብለው በአቋቋም መልክ የሚታወቁት በዘመናት የተከፈሉት ክብረ ቅዱሳንን ነክ ያደረጉ ከፍ ባሉት በዓላት የሚዘመሩት ናቸው ።

የሚጠኑትም እነዚህና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው ። ስለዚህ በዓመት ውስጥ የሚገኙትን የቅዱሳን በዓል በመከተል ደቀ መዝሙሩ በዓመት ውስጥ ትምህርቱን ሊከታተል ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org

ለ/ መዝሙር ።

መዝሙር የተባለው ትምህርት ራሱን የቻለ ትምህርት ነው ፤ ይኸን ሁሉ አጠናቆ ስለሚያጠና እገሌ መዝሙር ቀጠለ ፤ ወይም ዐወቀ ተብሎ ይነገርለታል ።

ሐ/ አርባዕትና ቅኔ ።

አርባዕትና ቅኔ የተባለውም እንዲሁ ራሱን የቻለ ትምህርት ነው ፤ ይሁን እንጂ ይኸ ትምህርት በዳዊት መዝሙር መነሻነት የሚዘመረው የቅዱስ ያሬድ ድርሰት የሆነው ዜማ ሁሉ ነው ። ለጊዜው የተደረሰውን ዜማ ብቻ ሳይሆን በየጊዜው የሚደረሰውን ቅኔውን ሳይቀር ያጠናዋል ፤ በዚህም ጊዜ አርባዕትና ቅኔ የተባለውን ክፍል አጠናቆ ሊያውቅ ይችላል ።

መ/ የወር በዓል ።

የወር በዓል የተባለው ትምህርት ክብረ ቅዱሳንን ነክ የሆነ በየወሩ የሚዘመር ነው ፤ እርሱም በገጽ ፻፲፭ እንደሚገልጠው በየወሩ ማኅሌት በተቆመ ጊዜ የሚዘመረውን አጠናቆ ያውቃል ።

ሠ/ ጾመ ድጓ ፤ ወይም ቅንዋት ።

ጾመ ድጓ ወይም ቅንዋት የተባሉት በዓቢይ ጾም ጊዜ የሚዘመሩና የሚዘመሙ ናቸው ፤ በአሁኑ ጊዜ ቅንዋትን አጠናቀው ይዘው የሚያስትምሩ በጣም በቍጥር ያነሱ ናቸው ፤ ተማሪውም ብዙ አይከተለውም ስለጾመ ድጓ ግን በገጽ ፹፭—፹፱ እንደሚገልጠው ሁሉ በጾም ጊዜ የሚዘመረውን አጠናቆ የሚያስተምሩት ትምህርት ነው ።

ምዕራፍ ፪ ።

## የአቋቋም ትምህርት ስልት ።

በአቋቋም ትምህርት ውስጥ ብዙ ስልት አለው ፤ ይሁን እንጂ በበዓል ጊዜ ሊባሉ የሚያስፈልጉ ነገሮች አሉ ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ ዝማሜ (ዘንግ)

ዝማሜ ማለት ከመቋሚያው ጋር መዝመምና ቀና ማለት ነው ፤ መሪጌታው ዝማሜን በዘንግ እየቃኘ ከቀኝ ወደግራ ከላይ ወደታች ከወዘወዘው በኋላ ወደ መሬት እየመታ ይቃኘዋል ፤ ያዜመዋል ዝማሜም የተባለው ይኸ ዓይነቱ ሥራ ነው ። ሰውየውም ከዘንጉ ጋር ሰውነቱ ይወጣል ይወርዳል ቀኝ ግራም አብሮ ከዘንጉ ጋር ይወረወራል ያረገርጋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ዘንግ ቀድሞ ለመሪጌታው ብቻ እንዲመራበት የተፈቀደ ሌላው ግን አጃቢ እንደነበር እንጂ ሁሉ ዘንግ በመወርወር ሥነ ሥርዓቱን አያፋልስም ነበር ፤ ከመዋሉ ከማደሩ የተነሣ ግን ሁሉ አቋቋም በመማሩ ወይም በውድድር መልክ ከማን አንሼ በማለቱ ሁሉም ባለ ዘንግ እንደሆነ ይነገራል ። ነገሩም የሚመስል ነው ፤ ዛሬ ባለ ሙዚቃው ወይም የሙዚቃው መሪ ብቻ በዘንግ እንደሚጠቅሳቸውና እንደሚመራቸው ሁሉ በዚያም ጊዜ እንዲሁ እንደ ነበር የሚያመለክት ነው ።

## ለ/ ንዑስ መረግድ ።

ንዑስ መረግድ የሚባለው መዝሙርም ይሁን ምልጣን በዘንግ ዝማሜውን ከጨረሰ በኋላ በጸናጽልና በከበሮ ብቻ በንዑስ አመታት የሚዘመር ነው ። እርሱንም ከመጽፈያው ጀምሮ በአመላለስ ይዘምርና በኋላ ወደ ዓቢይ መረግድ ያገባዋል ። ንዑስ የተባለበትም በከበሮው አመታትም ሆነ በጸናጽሉ አወራረድ ብዙ መራቀቅ የሌለበት ሆኖ በቀላሉ ጥሬውን ዜማ አንድም ቁሙን መስሎ የሚዘመር ነው።

## ሐ/ ዓቢይ መረግድ ።

ዓቢይ መረግድ ማለት ቁሙን ዜማ ለቀቅ አድርጎ በልዩ ዜማ የሚዘመረው ነው ፤ ይኸ ዜማ በከበሮው አመታት በጸናጽሉም አወራረድ ቢሆን የተለየ መንገድ ያለው የአካልንም ንቅናቄ የሚጨምር መንገድ ነው ። የሁለቱም መንገድ በዜማው ስልት ትንሽ ለየት ይበል እንጂ በአወራረዱ ወይም በቃለ እግዚአብሔር አባባል ልክ እንደ ንዑስ መረግድ ነው ፣ ማለት ፣ ንዑሱ ፣ ከአነሣበት ላይ መረግዱም ይነሣል ፤ ንዑሱ ከአረፈበት ላይ መረግዱም ያርፋል ።

የዚህም የዓቢይ መረግድ ድርብ መረግድ የተባለ በወረብ ወይም በመልስ አመላለስ ጊዜ የሚመረገድ አለው ፣ ይኸውም ከቁም መረግድ ትንሽ ለየት ያለ መንገድ ነው ።

## መ/ ድርብ መረግድ ።

ይኸውም በበዓል ጊዜ የሚደረብ በተለይም በወረብ ወይም በመልስ ጊዜ የሚዘምሩት ነው ። በዓቢይ ሲያመረግድ ቆይቶ በድርብ ያስገባዋል ፣ ይኸም ምሳሌ አለው ፤ የጌታ ግርፋትን መደብደብን ያመለክታል ።

## ሠ/ ጽፋት ።

ጽፋት የተባለው ዜማ ደግሞ ከቁሙ ዜማና ከመረግዱ ለወጥ ያለ ፍጥነት ያለው ዜማ ነው ፤ ጽፋት የተባለበትም ምክንያት ክርስቶስን በጥፊ እየመላለሱ የመቱትን ምሳሌና ስም የያዘ ሁኖ ይገኛል ፤ በግዕዝ ቋንቋ ጽፋት ማለት በጥፊ መምታት አንድም መመታት ማለት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

የአካል ንቅናቄ የእጅም ፍጥነት በጸናጽሉ ላይ ከሌላው ጊዜ ይልቅ በዚህ በጽፋት ጊዜ ይታያል ፤ የጽፋትም ዜማ ከዘመኑ መዝሙር ያልራቀ ሆኖ ለሁሉም የሚገባ መስሎ ይታያል ።

ረ/ መልስ ።

መልስ ማለት ወዝ ባለው ድምፅ ከመጽፊያው ላይ መመለስ እየመላለሱም ማዜም ነው ፤ ለዘብ ባለ መልክ መጽፊያውን እየመላለሰ ያለዝበዋል ያዜመዋል ፤ ስለዚህም መልስ በማለት ፈንታ ለዘብ የሚሉ አሉ ፤ ለዘብ ባለ ድምፅ በሚያስደስት አኳኋን ይዘምሩታልና ።

ሰ/ ወረብ ።

ወረብ ማለት የተመረገደውን በመከተል ሌላም አረፍተ ነገር በመጨመር ወይም በመለወጥ መልስ የተባለውን በሚመስል ዜማ ይወርቡታል ፤ ጨርሰውም ለውጠው ይሉታል ፤ የእግሩን በራሱ የራሱን በእግር ያዛውሩታል ፤ እየመላለሱም ይዘምሩታል ። በዚህም በወረብና በመልስ ጊዜ መረግድም ጽፋትም ይገኝበታል ።

ምዕራፍ ፫ ።

## ማኅሌት ።

### ፩ኛ የቃሉ ትርጉም ።

ማኅሌት ማለት ኀለየ ዘፈነ ፤ ዘመረ ፤ አመሰገነ ካለው ከግዕዝ የወጣ ቃል ነው ። ሥራውም ስሙ እንደሚያመለክተው ምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሔር ማቅረብ ነው ፤ የሆነ ሆኖ ማኅሌት ሲባል የተለየ ስም ያለው ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ፩ኛው ክፍል ነው ።

እሑድ የሚቆመው መዝሙር አንድም መወድስ ሲባል ፤ በየወር በዓላት በየዓመት በዓላት የሚደረገው የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ደግሞ ማኅሌት ይባላል ፤ ስለመወድስ በገጽ ፷፰ የተገለጠውን ተመልከት ። መዝሙር ስለ ሚባለውም ይኸው መወድስ ሊያጠቃልል ይችላል ፤ ምክንያቱም ከመዝሙር ጋር የሚደረስ ነውና ፤ ሆኖም ከድጓው የሚወጣ በዓሉን ወይም ዕለቱን የሚነካው ተፈልጎ ይዘመራል ፤ ይኸም መዝሙር ይባላል ፤ ትርጕሙም እንደዚያው ምስጋና ዝማሬ ማለት ነው ።

ማኅሌት የተባለው ግን ስቡሕ ወውዱስ በማለት ይጀምርና በንዑስ መረግድ እንዲሁም በዓቢይ መረግድ እያመላለሰ ከአመሰገነ በኋላ ፤ ወደ፪ኛው ክፍል ይሔዳል ፤ ይኸውም ክፍል ነግሥ የተባለው ነው ። ነግሥም በዘወትር የሚደርስ ልዩ ድርሰት ወይም ግጥም ሲሆን እንደ መልክአ መልክ ሆኖ የቅዱሳንን የመላእክትን ፤ የጻድቃንን ፤ በበለጠም የሥላሴን ምስጋና የሚናገር ግጥም ነው ። በምን

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት ነግሥ እንደተባለ ግን አይታወቅም ፤ ይኸንንም የመሰለ መልክአ ጉባኤ የተባለ ሌላ ክፍል አለ ፤ የመልክአ መልክእ ስብስብ አንድም ጥርቅም ማለት ነው ፤ ከዚያም ውስጥ ቢሆን የዓመት በዓሉን ነክ የሆነው ብቻ ተፈልጎ ይመረገዳል ፤ ከዚያ በኋላ ግን ወደ ፫ኛው ክፍል ይራመዳል እርሱም መልክአ መልክ የተባለው ነው ። ዕለቱ ወይም በዓሉ የሚመለከተው ቅዱስ መልክ ከላይ በተገለጠው አኳኋን ይመረገዳል ። ነገር ግን በነግሥም በመልክአ መልክም እየገባ የሚመረገድ ሌላ ክፍል አለ ፤ እርሱም ዚቅ የተባለ ድርሰት ነው ፤ ትርጕሙም ከያሬድ ድርሰት ዝቅ ያለ ማለት እንደሆነ ይነገርለታል ፤ በእርግጥም ድርሰቱ የሌሎች ሊቃውንት ስለሆነ ይኸን ስም የሰጡት ይመስላል ።

እርሱም አንዳንዱ ስድ ንባብ አንዳንዱም የግጥም መልክ ያለው ሲሆን ደራሲው በትክክል ያልታወቀ ድርሰት ነው ፤ የሆነ ሆኖ ከሚዘመረው ከሚዜመው ነገር ሁሉ እየተውጣጣ የገባ ነው ለምሳሌ ከሰዓታት ከኪዳን ከመዋሥዕት ፤ ከዝማሬ ፤ ከድጓ ከሁሉም የተውጣጣና የተቀመረ ነገር ነው ። ዚቅ የተባለው በጠቅላላው ቍጥር ፩ሺ፱፻፲ ሲሆን ፍጹም እውነተኛ ዚቅ የሚባለውና ይኸንም ቍጥር የያዘው የአባ ጃሌው መዝገብ የተባለው አሁን ታትሞ የሚገኘው ነው ፤ ግን ያልተወሰነ የበዛም የአነሰም መዝገብ ሊኖር ይችላል ።

በጥሬ ዜማው ቀድሞ ግዕዝ አንድም ዓራራይ የተባለው ሁሉ ወደ ዕዝል እየተለወጠ ዚቅ ይሆናል ወደዚቅም ይገባል ፤ ለ፩ መልክ እስከ ፫ ዚቅ ይኖረዋል ፤ ግን ነኩ ብቻ እየታየ አንዱ ይገባል ። የላይ ቤት የታች ቤት ዚቅ እየተባለ ይጠራ እንጂ ሁሉም የሚያምንበት ዋና የሚባለው የአባ ጃሌው ነው ፥ ከዚያም ውስጥ ነክ ሆኖ የተገኘው ይመረገዳል ፥ እርሱንም አልፈው ከማኅሌተ ጽጌ ውስጥ ምሥጢር ያጋጠመውን አንድም ሁለትም አውጥተው ያመረግዳሉ ፤ እንዲሁም ስንክሣር ተነቦ ከተፈጸመ በኋላ አርኬው በዓሉን ነክ ሆኖ ሲገኝ ሊመረገድ ይቻላል ፤ ነገር ግን የዚህ አርኬ ዚቅ የለውም ፤ ስለዚህም ሁልጊዜም አይመረገድም ። ከዚህ በኋላ ወደ ሌላ ክፍል ይዛወራል ፤ ማለት ምልጣን የተባለውን ክፍል ይይዛል ፤ ይኸም ክፍል ፈጽሞ እስካሁን ከተገለጠው ክፍል የተለየ ነው ፤ ስለዚህ ያለፈውን አንድ ወገን አድርጎ ይኸን ፪ኛ ለማለት ይቻላል ፥ ምክንያቱም ከላይ የተገለጠው ሁሉ ጥሬውን ዜማ ተከትለው የድጓ መምህራን ሁሉ ሊያደርሱት ይችላሉ ፤ ይኸ ክፍል ግን ዝማሜ ያለበት የጸናጽልም አቋቋም የሚታይበት ክፍል ነው ።

ዕገሌ ስቡሕ ብሎ ይወጣል በቂ ችሎታም አለው የሚባለውም አቋቋም በመጠኑ ያወቀ ይትበሃሉንም የጠበቀ መሆኑን ያስረዳል ።

## ፪ኛ ምልጣን ።

ምልጣን የሚባለውም እስመ ለዓለም ተቃኝቶ አንገርጋሪው ተመርቶ የሚዜመው የሚጸነጸለው በጠቅላላው የሚዘመረው ነው ፤ በጠባብ አነጋገር ምልጣን የሚባል

www.ethiopianorthodox.org

አንገርጋሪው ብቻ ነው ፤ በሰፊው አነጋገር ግን እስመ ለዓለሙ ፤ አንገርጋሪው፤ ሰላሙ ፤ ይኸ ሁሉ በአንድ ላይ ምልጣን ይባላል።የመቋሚያው አነጣጠቅ የጸናጽሉ አወዳደቅ ፥ የቃለ እግዚአብሔሩ አደማመቅ የሚታየው በዚህ ምልጣን በተባለው ክፍል ነው ።

የአቋቋም ትምህርትም ዋጋ የሚሰጠው በዚህን ጊዜ ነው ፤ ማለት ዝማሜውም ጸናጽሉም በመፈራረቅ በቀኙና በግራ ይባላል ፤ ድርብ አደራረስ ይባላል ። የወር በዓል የሆነ እንደሆነ ግን ማኅሌቱ በዚህ ይፈጸማል ፤ ሰላሙን እንደጸፉ ማብቂያው ይሆናል ፤ አንድ አንድ ጊዜ በዓመት በዓለም ቢሆን ከዚህ ሳያልፉ ይቀራሉ ፤ ምክንያቱም በመልክአ መልኩና በዚቁ መረግድ እንዲሁም በወረቡ በምልጣኑ አመላለስ ጊዜውን ስለሚፈጁት ነው ።

አንዳንድ ጊዜ ግን አደራረስ የተባለውን ማኅሌት ለማድረስ ሲፈለግ መልክአ መልኩን እንዲሁ በቀላሉ ያልፉና ክሥተት አርያም አንድም ሙሉ አደራረስ ወደ ተባለው ይራመዳሉ ።

## ፫ኛ አደራረስ ።

አደራረስ የተባለው ክፍል ፈጽሞ ልዩ የሆነ ጥሬ ዜማን የሚጠይቅ ነው ፤ እርሱም በ፫ ይከፈላል ፤

፩ኛ ክሥተት አርያም አደራረስ የተባለው ማኅሌት ነው ፥ እርሱም በዓመት በዓል ይደረሳል ።

ክሥተት አርያም አደራረስ የሚባለው አጀማመሩ ልክ እስመ ለዓለም እንደተፈጸመ የውዳሴ ማርያም ዜማ ይደርሳል ፤ ቀጥሎም ይትፌሣሕ ልሳንየ ይልና ከዳዊት መዝሙር እየተውጣጣ ክሥተት ይደርሳል ፥ ይኸም በጠቅላላው ሲሆን የተለየ በዓሉን ብቻ የሚመለከት ምስባክ የተባለው ይደርሳል ፤ ይኸም ሲፈጸም የክሥተት ምቅናይ የተባለው እስመ ኪያከ ይመረገድና መንግሥቱ ይባላል ፤ ቀጥሎም ክሥተት አርያም ለማድረስ ተሣሃለኒ ብሎ መሪው ይጀምራል ።

የአርያም አደራረስ በጥንት ዘመን ከምልጣን በፊት ነበር ፥ ምክንያቱም በአርያሙ መካከል ምልጣን አለና ፤ ዛሬም ቢሆን አልፎ አልፎ በዚህ መልክ በቤተ ልሔም ይደርሳል ፥ ይኸም የሚሆንበት አብነቱ እንዳይጠፋ ነው ፤ በሌላው ቦታ ግን ጊዜውን በመከተሉ በመረግድና በወረብ ካሳለፉ በኋላ ክሥተት አርያም ይጀምራሉ ፥ እርሱም የሚሆንበት ምክንያት -ሀ- በዓሉ ደመቅ እንዲል ከበሮው እንዲንጋጋ ፤ -ለ- ከጥሬው ዜማ የገፋው በማነሱ ነው ፤ ምክንያቱም የአርያም አደራረስ ብዙውን ጊዜ ወደ ጥሬው ዜማ ያደላል ። አሁን እንደደንብ ሆኖ የተጠበቀው ከምልጣን በኋላ መድረሱ ነው ፤ ተጀምሮ ይቀራል እንጅ የሚዘልቀው እንኳን የለም ።

፪ኛው ስብሐተ ነግህ አደራረስ የተባለው ነው ፤ እርሱም በዘወትር ስብሐተ ነግህ ጊዜ በሚደርሱት በዳዊት መዝሙሮች ልክ ቅኔ እየደረሰ በዘንግ እየተዘመመ [illegible] ይ[illegible]ል።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸውም በሌላ ቃል አነጋገር ዓቢይ ስብሐተ ነግህ ወይም የዓመት በዓል ስብሐተ ነግህ የሚባለው ነው ።

፫ኛ የመዝሙር አደራረስ የተባለው ነው ፤ እርሱም በየሳምንቱ እሑድ ይደረሳል።

ምዕራፍ ፬ ።

## ሥርዓተ አደራረስ ።

አደራረስ ማለት የዜማው ልክ የአገልግሎት ሥርዓት መፈጸም መድረስ ማለት ነው ፤ በእርግጥም ለአንድ በዓል የተወሰነው የድጓ ዜማ ሁሉ በየዕለቱ እየገባ ይደርሳል ፤ የዜማው ስልት ይታያል ይኸም ቀርቶ ቅኔው ማለት በቁሙ ሌላም ዳዊቱን የመሰለ የቤተ ክርስቲያን ደንቦች ሁሉ ይደርሳሉና ።

ግን በመረግዱም ቢሆን የአቋቋሙ አደራረስ የተለየ ስለሆነ የርሱንም አደራረስ ይመረምራል ፤ እርሱም የሚከተለው ነው ።

## ፩ኛ የመልክ አደራረስ ድርብ መረግድ ።

ከቀኝም ከግራም ቢሆን መሪ ካለበት ወገን ይሥቅየኒ ብሎ አንድ ጊዜ ይዘልቃል።
አንሽ ፤ ይሥቅየኒ ለለጽባሑ ፪ ጊዜ ብሎ ከመ ይሠቅዮን ፩ ጊዜ ሲል ይዘልቃል ።
መሪ ፤ ከመይሠቅዮ ብሎ ፩ ጊዜ ይዘልቃል ።
አንሺ ፤ ከመይሠቅዮ ብሎ ፩ ጊዜ ይዘልቃል ።
መሪ ፤ በመረግድ ይሥቅየኒ ፪ ጊዜ ብሎ ከመ ይሠቅዮ ውኂዝ ከመ የሠቅዮ ውኂዝ ፪ ጊዜ ይልና ፤
ወደኋላ ተመልሶ ይሥቅየኒ ፪ ጊዜ ብሎ ፤ ከመ ይሠቅዮን ፩ ጊዜ ይዘልቃል ፤
አንሺ ፤ በመረግድ ይሥቅየኒ ፪ ጊዜ ብሎ ፤ ከመ ይሠቅዮ ውኂዝ ከመ ይሠቅዮ ውኂዝ ፪ ጊዜ ብሎ ፤
ወደኋላ ተመልሶ ይሥቅየኒን ፪ ጊዜ ብሎ ፤ ከመ ይሠቅዮን ፩ ጊዜ ይዘልቃል ።
መሪ ፤ በቁም ማርያም ድንግል ብሎ አንድ ጊዜ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል ።
አንሺ ፤ በመረግድ ማርያም ድንል ማርያም ድንግል ፪ ጊዜ ብሎ ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ፩ ጊዜ ሲል ።
መሪ ፤ አንድ ጊዜ ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ሲል ፤
አንሺ ፤ አንድ ጊዜ ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ይላል ።
መሪ ፤ ማርያም ድንግል ማርያም ድንግል ፪ ጊዜ ብሎ ፤ ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ፩ ጊዜ ሲል ፤
አንሺ ፤ ይሥቅየኒ ብሎ ፩ ጊዜ ይዘልቃል ።
መሪ ፤ ስላሞ ለዝክረ ስምኪ ብሎ እስከ መጨረሻ ው ይዘልቃል ።

www.ethiopianorthodox.org

አንሺ ፤ በመረግድ ሰላም ብሎ እስከ ቤት መምቻው ድረስ ፪ ጊዜ ይልና ፡ እምነ ከልበኔ ወቁስጥ ወእምነ ሰንበልት ምዑዝ ፩ ጊዜ ይላል ።
መሪ ፤ እምነ ከልበኔ እንደዚሁ ፩ ጊዜ ሲል ፡
አንሺ ፤ እምነ ከልበኔ እንደዚሁ ፩ ጊዜ ይላል ፡
መሪ ፤ ሰላም ሰላም ለዝክረ ስምኪ ብሎ ፪ ጊዜ ይልና እምነ ከልበኔ ወቁስጥን ብቻ ፩ ጊዜ ሲል ፡
አንሺ ፤ ወእምነ ሰንበልት ምዑዝ ብሎ ፩ ጊዜ ብቻ ይላል ።
መሪ ፤ ማርያም ድንግል ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ፩ ጊዜ ይላል ።
አንሺ ፤ ይሥቅየኒ ብሎ ፩ ጊዜ እስከ መጨረሻው ይዘልቃል ።

ይኸ ዓይነት አደራረስ የተጀመረው በጐንደር መንግሥት በተለይም በአጼ ኢያሱ አድያም ሰገድ ጊዜ ነው ፤ ምክንያቱም የጐንደር ካህናት ንጉሡ ለዑደት እስ ኪመጡ ለመጠበቅ መልኩን ሲመላለሱ ቆይተዋልና ።

## ፪ኛ የዚቅ አደራረስ ።

ይዌድስዋን ፡ መሪ በቁም ፩ ጊዜ ይዘልቃል ።

አንሺ ፤ በመረገድ ይዌድስዋ ፪ ጊዜ ብሎ ፡ ወይብልዋ በሐኪ ማርያም ሐዳስዩ ጣዕዋ ፩ ጊዜ ሲል ፡
መሪ ፤ ወይብልዋን ፩ ጊዜ ይላል ።
አንሺ ፤ ወይብልዋ ፩ ጊዜ ይላል ።
መሪ ፤ ይዌድስዋን ፪ ጊዜ እያለ ሒዶ ወይብልዋ ሲደርስ ፩ ጊዜ ብሎ ይጨርሳል ።
አንሺ ፤ በመረግድ ሰላም ብሎ እምነ ከልበኔ ወቁስጥ ወእምነ ሰንበልት ምዑዝ ፩ ጊዜ ብቻ ይልና ይዌድስዋን በመረግድ ፩ ጊዜ ብቻ ይዘልቃል ።
መሪ ፤ ማርያም ድንግል ለባሲተ ዓቢይ ትእዛዝ ፩ ጊዜ ይልና ይዌድስዋን በመ ረግድ ፩ ጊዜ እያለ ይዘልቃል ።
አንሺ ፤ ይሥቅየኒ ብሎ ፩ ጊዜ በቁም ዘልቆ ይጨርሳል ።

## ፫ኛ ሥርዓት አደራረስ ዘአንገርጋሪ ።

መሪ ፤ በቀኝም በግራም ቢሆን ይመራል ፡ አሁን በቀኝ በኩል እንደሆነ ነው ፡ በቁም መሪና ተመሪ ይዘልቃሉ ፩ ጊዜም በዚያው ወገን ይዘመዋል ።
በግራ ፤ በቁም ፩ ጊዜ ይዘልቅና ፤ ፩ ጊዜ በዝማሜ ይልዋል ። እንደገናም መሪ አመልጥኖና በቀኝ መንክር ስብሐተ ልደቱ ይላል ።
በግራ ፤ ያነሣና በዚያው አማን ብሎ ይዘልቃል ።
በቀኝ ፤ በኩል ፫ኛው አንሺ ያነሣል ፡ መንክር ብሎ ይጨርሳል ።

www.ethiopianorthodox.org

በግራ ፤ ደግሞ አማን ብሎ ይዘልቃል ።
በቀኝም ፤ አማን ብሎ ይዘልቃል ።
በግራ ፤ ደግሞ ፪ት ጊዜ አማን እያለ ይመላለሳል ።
ዳግመኛ መሪ አመልጥኖ መስቀሉ ይገባል ።
በቀኝ ፤ አማን በአማን ካለ በኋላ ፪ ጊዜ መንክር ፪ት ጊዜ አማን በአማን ይላል ።
እንደገናም ፭ ጊዜ ዘልቆ ይተዋል ።
በግራ ፤ እንደገና መንክር ይላል ።
በቀኝም ፤ መንክር ይላል ።
በግራ ፤ ደግሞ አማን በአማን ይላል ።
በ፬ኛው ጊዜ በቀኝ መንክር ብሎ ይጸፋል ።
በግራ ፤ መንክር ብሎ ይጸፋል ።

ከዚህ በኋላ ግን አማን በአማን ብለው በኀብረት ያሸበሽባሉ ። እስመ ለዓለሙ ንም እንዲሁ በቀኝና በግራ አዝማቹን በመክፈል ይዘምሩታል ይጸነጸላል ።

## ፬ኛ ሥርዓተ አደራረስ ዘአርያም ።

ከዚህ ክፍል ሲደርስ መጀመሪያ ፩፻፶ ዳዊትና ውዳሴ ማርያም ይደገማል ፤ የኪዳን ሰላም ይባላል ። ኪዳን ለከ እግዚኦ ፤ አምላከ ብርሃን ፥ ንሤልስ ለከ ፤ የተባሉት ብቻ ይባላሉ ።

ከዚህ ቀጥሎ ግን ይትፌሣሕ ልሳንየን መሪው ይመራል ፥ ይኸም ይዘመማል ፤ አንሺ ወገን በቁሙ እንደገና ይልና ይዘመዋል ፤ ከዚህ በኋላ ግን ክሥተቱ በማስ ተዛዘል በግራና በቀኝ ይባላል ፥ ምስባክም በዓሉን ተከትሎ ፫ ጊዜ ይባላል ።

ይኸውም እንደተፈጸመ እስመ ኪያከን ፪ ጊዜ እየመላለሰ ይለዋል ፤ ይኸውም ፭ ጊዜ በቁሙ ፭ ጊዜ በዝማሜ ነው ። በዝማሜ ከዘለቀ በኋላ ፤ መንግሥቱ ብሎ በጸናጽል ያነሣል ፤ እንደገናም ይኸንኑ አመርግዶ ይጸፋል ፥ ይኸም ሲፈጸም መን ግሥቱ የሚለውን ያለዝባል ።

ከዚህ በኋላ ተሣሃለኒን ይመራል ፥ ወዲያውም ሚበዝኅ ቅኔ ይደርሳል ። በሌላው በኩል ደግሞ ናሁ ይባርክዎን ይመራና መስተብቍዕ ይባላል ፤ ቀጥሎም ፫ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ በግዕዝ ይባላል ካህኑ ፥ ጸጋ ዘአብ ኂሩት ዘወልድ ብሎ ቡራኬ ይሰጣል ።

ከዚህም በማያያዝ የብቡን ይደግማል ፥ እንዲሁም ንሴብሖን ይላል ፤ በዚህ ጊዜ አንሺ የለም ፤ እስመ ተለዓለ ስሙ ይባላል ፤ እስመ በዛቲ ሰዓት የሚለውን በየበዓ ላቱ ይሉታል ። እንደገና መሪ አርያም ሃሌ ሉያ ለአብ ቀዳሚ ክርስቶስ በማለት ይመራል ፤ ቀጥሎም በእንተ ዕበዮሙ ይባላል ፥ ወይም የመላእክት በዓል የሆነ እን ደሆነ እስመ ተለዓለ ስሙ ፈራኅያነ እግዚአብሔር የሚለው ይባላል ።

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም ኵሎሙ ፤ ነደ እሳት እሙንቱ ይባላል ፣ አንድ ሰው ደግሞ አንተ በሰማይ የሚለውን ይላል ። አርያም ቀዳሚሁሰ ለዘየአምን የሚለው ይባላል ፤ አሁንም በ፪ አቀድም አእኵቶቶ ይባላል ፤ ይኸም ይመረገዳል ይጸፋልም ።

ከዚህ በኋላ ነቢያትን ለማድረስ ንሴብሖን ይመራና በቀኝ በግራ እያስተዛዘሉ ማይሰ ሎሙን በኅብረት ይሉታል ፤ ይኸንም ሲፈጽሙ ካህኑ ስብሐት ለአብ ፣ ስብሐት ለወልድ ፣ ስብሐት ለመንፈስ ቅዱስ ይላል ይሕ አሜን ።

ከዚህ በኋላ ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፣ አንሺ ደግሞ ቀዳሚ ዜማን ይመራና አቡን ዓራራይ ይባላል ፣ ይኸም ይመረገድና ይጸፋል ፤ ምዕዛል ደግሞ አጽምዕ ሰማይ የተባለውን ያስተዛዝላሉ ፣ ወአምዕአሙ ለሕዝብ በዘኢይሴብው የሚለውን በኅብረት ይዘምሩታል።

ካህኑ ስብሐት ለአብ----የሚለውን እንዳለፈው ይላል ፣ ሕዝቡም አሜን ይላሉ ። ፪ኛ- ሥላሴ ቅኔ ይቀኛሉ ፣ ከዚህ በኋላ ፪ኛው አንሺ ይገብሩ በዓለ የተባለውን አርያም ይመራል ፣ አቡንም በ፪ ግዕዝ ይባላል ። ወአምዕአሙ ለሕዝብ በዘኢይሴብው ብለው እስመ እሳትን ይስተዛዝላሉ ፤ ከዚህም በኋላ ስብሐት ለአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ የሚለውን በኅብረት ይላሉ ፣ በዚህን ጊዜ ግን ካህኑ ስብሐት ለአብ አይልም።

ሥላሴ ቅኔ ይቀኛሉ ፣ ከዚህ በኋላ ግን ቃለ ዓዋዲ የተባለው አርያም ይመራል ፣ አቡን ግዕዝ ይባላል ። በቀዳሚ ዜማ በ፩ ይባልና በይገብሩ በዓለ በ፪ ብርሃነ ሕይወት ይባላል ፤ በቃለ ዓዋዲ ከ፫-፮ ይባላል ፤ በ፫ም በ፬ም ፣ በ፭ በ፮ም ይባላል። በቀዳሚ ዜማ ከ፯-፲ ይባላል በ፯ም ፣ በ፰ም በ፱ም በ፲ም ፣ ከተባለ በኋላ በይገብሩ በዓለ እንበለ ብርሃነ ሕይወት ሌላ ደግሞ ይቤ እስጢፋኖስ ፣ ትቤሎ ብእሲት የሚለውን ወይም የሚመስለውን ቁም ቤት ይላሉ ። ኵሉ ዘገብራ ቤት ይባላል ። ከዚህ በኋላ ግን ስብሐት ብሎ ጸንዓ ልብየን ያስተዛዝላሉ ፤ በአእምሮ ወበለብዎ እግዚአብሔር የሚለው በኅብረት ይዘመራል ። ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል አርያም አክሊለ ሰማዕት ይባላል አቡን ኵሉ ዘገብራ ቤት በቁሙ ሃሌ ሉያ እየተባለ ይዘመራል ። በአእምሮ ወበለብዎ እግዚአብሔር ብሎ አንሰ ዕቤን ያስገባል ።

ግን በዚህን ጊዜ ማስተዛዘል የለም ፣ በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር ላይ ሲደርስ አስቀድሞ ፫ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ በዕዝል ፣ አያይዞም በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር ይላል ። ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፣ አርያም ተከሥተ አፉሁ ፤ አስተጋብአተነ ቤት አቡን ይባላል ። ተከሥተ አፉሁ የሚለው ባይገኝ ሌላም ሊባል ይቻላል ፣ በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር ይባላል ።

በቅድመ ቤተ እግዚአብሔር ብሎ እግዚኦ አኃዜ ኵሉ ዓለምን ያስተዛዝላሉ ፤ እስመ ኪያከ ይሴብሑ የሚለውን ይዘምራሉ ። ሥላሴ ቅኔ ይቀኛል ፣ አርያም ዮሐንስ ስሙ የሚለው ይባላል ፣ አቡን ተሰዓልዎ ንስግድ ቤት ይባላል ፣ እስመ ኪያከን ብሎ ፤ ጸራኀኩ በምንዳቤየን ያስገባል ፤ ትብጻሕን ዘኅብረት ይላል ። ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፣ አርያም አጥመቀሙን ይመራል ፣ አቡን ደግሞ አስተርእዮ ቤትና ዓቢይ ቤት ይባላል ።

ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፤ አርያም እስመ በትሕትና የሚለውን ይመራሉ ፤ አቡን እስመ ዋካ ቁም ቤት ይደርሳል ። ወይም ናስተበቍዕ ትሕትናከ የሚለው ይመራል ።

www.ethiopianorthodox.org

ወይም ይኸን የመሰለው ከመካከሉ ሃሌታ ያለው ይባላል ፤ በዚህን ጊዜ እስመ ለዓለሙ አቡን ነው ።

ኀላፊ ዘኢያንቀለቅል ወይም ባኡ ቤት ይባላል ፡ በካህን ስማዕ ሰማይን በል፤ በተሰፍሐ ትፍሥሕት ዓቢይ ቤት ዠሉ ዘገብሩ ቤት ፤ በከመ ቀስተ ደመና ዘኢያንቀለቅል በግነዩ በትጉሃን በዘልዐል ቁም ፡ ነገሮሙ ቤት ይትዓየን ውድቅ ቤት ነገሮሙ ቤት አስተርእዮ ቤት ይባላል ፡ ምዕዛል ይቀጥልና ፡ ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፡ አርያም ረኪቦሙ ሕፃነ ይባላል ።

አቡን አንገርጋሪ ቤት ይመራል ፤ በይቤ እስጢፋኖስ ፡ በተበሀሉ ትጉሃን ቤት ፡ ዓዲ በይቤ እስጢፋኖስ ትቤሎ ብእሲትን የመሰለ ይባላል ፤ ቁም ቤት በተበሀሉ ዠሉ ዘገብሩ ቤት ይባላል ። ለዘዓርገ ፡ ዘየሐጽብ አግዳሚ ቤት ፤ በአዋልድ በአኪሊሎሙ ፤ ዠሉ ዘገብሩ ፡ በፃዑ፡ ንዜኑ ፤ ዕጹብኒ ቤት ይባላል ፡ በወሰኑ ትጉሃን ፡ አስተጋብአተነ ይባላል ፤ በጽድቅ ውእቱ አርዋጺ አንገርጋሪ ይባላል ፡ በዕዝራኒ ርእያ ፡ እምነ በሐ ይኸንም የመሳሰሉት ይባላሉ ፤ ዠሉ ዘገብሩ ሲያልቅ ትብጻሕ ጸሎትየ ብሎ ጸሎተ ዳንኤልን ያስተዛዝላል ፡ ወበከመ ብዝኃ ምሕረትከ በኅብረት ይባላል ።

ሥላሴ ቅኔ ይደርሳል ፡ ከዚህም በኋላ ፳ ምዕዛሎች ይባላሉ ፤ ፀወንነ ይባላል ፡ መዝሙር ሀላዌ ቤት ይዘመራል ፡ ይትባረክ ይባላል ይኸም ሲፈጸም ፫ ጊዜ ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ ይባላል ።

ዋዜማ ቅኔ ይደርሳል ፡ አርያም ዓቢይ ዜማ ይባላል ፡ አቡን ጸርሐ ይባላል ፡ ወይም ዘይገለብቦ ይባላል ፡ ወይም የ፯ቱን ሃሌታ ዋዜማ በቁም ይሉታል ።

ይባርክዎ ይባላል ፤ እርሱም ግዕዝ ነው ፤ ማኅሌትም እየገባ ይደርሳል ። ፫ ጊዜ እግዚአ መሐረነ ክርስቶስ ይባላል ። ከዚህ በኋላ ክብር ይእቲ ይደርሳል ፤ ሰብሕዎ ለእግዚአብሔር በቅዱሳኑ እስከ ፍጻሜው ይገባል ።

ከዚህ በኋላ እንዘ ንብል ኢንትኃጕል ይባላል ፤ በበዓለ ማርያምና በበዓለ ወልድ እንዘ ንብል ኢንትኃጕል እምከብካበ ወልዳ ለድንግል ይባላል ።

አጭር ዋዜማ ይቀኛል ከክብር ይእቲ በፊት ሐዋርያቲሁ ከበበን የመሰለ ክብር ይእቲ መቀኘት እንዲገባ የሚናገሩ አሉ ፡ ከዚህ በኋላ አርያም ሕንጼሃ ይባላል ። በበዓለ ሐዋርያት በሕንጼሃ ፈንታ ሐረየ ፩ ወክልኤተ ይባላል ፡ አቡን ቅንዋት ቁራ ቤት ምዕዛል ወበከመ ብዝኃ ምሕረትከ ይባላል ፡ ከዚህም በኋላ እግዚአ ሰማዕኩን ያስተዛዝላሉ ፡ ሥላሴ ቅኔ ይቀኛሉ ፡ አርያም መስቀልከ ይባላል ፡ አቡን ናሁ ቤት ይባላል ። አርያም በመስቀሉ አተበነ ይባላል ፡ አቡንም ነሥአ ቤት ይባላል ፡ አርያም በመዳልው ደለወ ዓለመ ይባላል ፡ አቡን ጥበብ ቤት ይመራል ።

በካህናትና በባረከ ወኅይዝተ ወንጌል በኀረየና በሕንጼሃ ቁራ ቤት ፤ በአዳምና በሥላሴ ዋሕድ እምሰማይ ርደትከን የመሰለ ዕጣነ ሞገር ይባላል ። ምዕዛል ተዐብዮን ያስተዛዝላሉ ወፈነዎሙን በኅብረት ይሉታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሊቀ መላእክት ሲል ተቀባዮቹ አመ ዳግም ንፍሐተ ቀርን አመ ይትነሥኡ ሙታን ይላሉ ፤ መሪው እንደገና አመ ዳግም ንፍሐተ ቀርን አመ ይትነሥኡ ሙታን ሲል ተቀባዮች በፊት በዓራራይ ቀጥሎም በግዕዝ ፥ አንተ እስየነ የሚለውን እስከ መጨረሻው ይላሉ ።

ከዚህ በኋላ ካህኑ ቡራኬ ሲሰጥ እንዲህ ይላል ፥ «ዘዓይን ኢርእየ ወዕዝን ኢሰምዐ ውስተ ልበ ሰብእ ዘኢተሐለየ ዘአስተዳለወ እግዚአብሔር ለእለ ያፈቅርዎ ይእሰየኒ ይእስይክሙ እግዚአብሔር» በማለት ይሰጣል ፥ መዘምራኑም ፥ አሜን ይላሉ ። ከዚህ በኋላ ስንክሣር ይነበባል ፥ ውዳሴ ማርያም ይደርሳል ።

በዜማ ተፈሥሒ ማርያም በግዕዝ ይባላል ፤ ተአምር ይነበባል ፥ እንዲሁም ወንጌል ይነበባል ። ከዚህ በኋላ ግን ኪዳን በዓራራይ ዜማ ጸጋ ዘእግዚአብሔር የሃሉ ምስሌክሙ በማለት ፫ቱን የነግሁን ብቻ ያደርሳሉ ። በዚህን ጊዜ ሠለስት የለም ፤ ዕዝልና ሰላም ግን ይባላል ። እንዲሁም ፫ ጊዜ እግዚኦ መሐረነ ክርስቶስ ይባልና ክርስቶስ ፥ ጋዳ ቅዱስ እግዚኦ መሐረነ ፫ ጊዜ ይባላል ።

በመጨረሻም ስብሐት ለእግዚአብሔር ኪያነ ዘፈጠረ ከመ ናምልኮ፥ስብሐት ለማርያም እመ አምላክ እግዝእትነ ወመድኀኒትነ ፥ ስብሐት ለመስቀለ ክርስቶስ ዕፀ መድኃኒት ኃይልነ ወፀወንነ ፤ ጸሎተ ሃይማኖት ተደግሞ በማሳረጊያ ጸሎት ፍጻሜ ይሆናል ።

ምዕራፍ ፭ ።

## የማኅሌት መሣሪያዎች ።

በዚህ ዓለም የሰው ልጅ ደስታ መግለጫ መዝሙር ዘፈን ነው ፥ ለዚህም ማሣሪያ ልዩ ልዩ መሣሪያዎች አሉት ፤ የሰው ልጅ ግን በሥጋዊም ብቻ ሳይሆን በመንፈሳዊም ለስሜቱ ማርኪያ እንዲሆን መዝሙር መዘመር የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃዱ እንደሆነ ለማጠየቅ ልዩ ልዩ መዝሙር አዳዲስ መዝሙር መዘመር እንዲገባ በቅዱሳን ነቢያት አናግሯል ፤ በቅዱሳን መጻሕፍት አጽፏል ፤ ራሱም በምሴተ ኀሙስ ከሐዋርያት ጋር ዘምሯል ፤ አመስግኗል ፤ ንባብም አንብቧል (ማቴ.፳፯፡፴)። መሣሪያዎቹም የተለዩ እንደሆኑ በጽሑፍ ተገልጧል ፥ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

### ፩ኛ መቋሚያ ።

መቋሚያ ማለት መቆሚያ ፤ መደገፊያ ማለት ነው ፥ ምክንያቱም በጥንት ዘመን የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሥርዓት ሁሉ ረጅም ስለ ነበር ፤ በቤተ ክርስቲያን ውስጥም የማረፊያ ዘዴ እንደወንበር ያለ አንድም ሌላ መደገፊያ ስላልነበረ ሥርዓቱ ሁሉ እስኪፈጸም ምእመናን ቁመው መቆየት ግድ ስለነበረባቸው በዚህ በመቋሚያው ይደገፉ ነበር ፤ በደከሙ ጊዜ የሚጽናኑበት የሚደገፉት የሚቆሙበት ይኸ መሣሪያ በመሆኑ መቋሚያ ተብሏል ። ሲደገፉትም እንዲመች ስለታሰበ እንደ

www.ethiopianorthodox.org

ባላ ያለ የማይጐረብጥ ቅጽ ያለው ሁኖ ተሠርቷል ። ይኸን የመሰለ በምሥራቅ አብያተ ክርስቲያናትም እንዲሁ ወንበር ስለ ሌለ ደካማዎቹ የሚመረኰዙት የሚያርፉበት አስታሲዚያ የሚል ይገኛል ፤ ይኸም ቃል የሚያመለክተን አንደኛ እንደ ዓረፍት ያለ ከግንቡ ጋር አብሮ የተሠራ ያለዚያም በመቋሚያ ዓይነት የተሠራ እንደነበራቸው ነው ። ይኸም ዓይነት ነገር ጥንታውያን በሆኑ አብያተ ክርስቲያናት እሁን ድረስ ይገኛል ፤ በኛም ቤተ ክርስቲያን ቢሆን ፪ቱ ዓይነት ይገኛሉ ።

መቋሚያው የሚሠራው ከእንጨት ነው ፤ ይኸም ዘንጉም ላዩም እንጨት ሲሆን ነው ፤ እንዲሁም ከብር ከወርቅ ፤ ከናስ ፤ ከመዳብ ፤ ከብረት ፤ ይሠራል ፤ አሁን ድረስ በሁሉም ዓይነት ይገኛል ። አገልግሎቱ ግን ከላይ እንደተናገርነው ለመደገፊያው ብቻ ሳይሆን ፤ ለማኅሌቱ መምሪያ ፤ መቃኛም ይሆናል ። የማኅሌት መቆሚያ እንዲሁም የማኅሌቱ ሥነ ሥርዓት መምሪያ መቋሚያ ነው ፤ ማኅሌቱ ሲቆም የሚዘመረው ፤ ወይም ሲደክሙ የሚደገፉት የሚቆሙበት በመሆኑ መቋሚያ ተብሏል ። ይኸውም የዘመኑ የሙዚቃ መሪ እንደ መቋሚያ ያለ ዘንግ ይዞ ሙዚቃውን እንደሚቃኝ የኛም የዜማ መምህራን ሁሉ መሪዎች እንደመሆናቸው የሚይዙት ዘንግ ነው ።

መሪጌታው በዚህ በዘንጉ ስለሚቃኝና ስለሚመራ መሪጌታ ይሉታል ፤ የሚመራና የሚቃኝ ጌታ ማለት ነው ፤ እየዋለ እያደረ ግን ደብተራው ሁሉ በመምራትም በመመራትም ጊዜ ዘንግ እየያዘ ስለሚጠቀምበት መሪጌታው ለስሙ እንጂ በመቋሚያው ብቻውን የማይጠቀም ሁኗል ፤ ሁኖም ለሁሉም የውዝዋዜ መጥቀሻ መቋሚያ ወይም ዘንግ ይባላል ።

የመቋሚያና የዘንጉ አሠራር ግን ትንሽ ለወጥ ያለው ነው ፤ መቋሚያ የሚባለው የባላነት መልክ የመደገፊያነት አቅድ ሲኖረው ዘንግ የተባለው ፤ ግን የዘንግ ቅርጽ ሆኖ ራሱ ድቡልቡል የሆነ ነው ። ስለዚህ በአቋቋም ትምህርት መቋሚያ በማለት ፈንታ ዘንግ ይሉታል ። በዚህም መልክ የመቋሚያ ጥቅሙ ፩ኛ ለድካም መጽናኛ ነው ፤ ምክንያቱም በአሁኑ ካህናት ብቻ ሳይሆኑ የወንድ መኳንንት የሴት ወይዛዝርት ሁሉ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ጊዜ እንዳይደክሙ ይደገፉታል ። ፪ኛ ለዜማ መቃኛ ማስተካከያ መዝመሚያ ሆኖ ይገኛል ። ስለዚህ የአቋቋሙን ዓይነት ለመለየት ዘንጉ ተክሌ ጸናጽሉ ጐንደሬ እያሉ ይወስናሉ ፤ ይኸም የሚያመለክተው በማኅሌት ጊዜ መዝመም በተክሌ አቋቋም የበለጠ ይታይበታልና ።

በዘንግ አወራወር ወይም በዘንግ ዝማሜ ጊዜ የተክሌ አቋቋም በጣም ያምራል ፤ እርሱም አለቃ ገብረ ሐና የሸንበቆውን ዝማሜ ወይም ውዝዋዜ በነፋስ ኃይል የሚወዛወዘውን አይተው ከርሱው ወስደው ለልጃቸው ለአለቃ ተክሌ እንዳስተማሩት ይነገራል ። የሆነው ሆኖ ተክሌውም ጐንደሬውም አቋቋም የዘንግ ዝማሜ ወይም የዘንግ ዝማሬ ይገኝበታል ።

www.ethiopianorthodox.org

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በመቋሚያ ብቻ የሚፈጸመው በአጽዋማትና በኀዘን ጊዜ ነው ፣ በተለይም እንደ ዓቢይ ጾም ባለው ጊዜ ነው ። መቋሚያውን ከቀኝ ወደግራ ከወዘወዙ ወይም ከዘመሙ በኋላ ወደ ላይ አንስተው ወደታች ይወረውሩታል ፤ የዚህም ምሳሌ አለው ፤ እርሱውም አይሁድ ክርስቶስን ከሐና ወደቀያፋ ፤ ከቀያፋ ወደሐና ከአመላለሱት በኋላ በመስቀል ላይ እንደሰቀሉት ቀጥለውም ከመስቀል አውርደው እንደቀበሩት የሚገልጥ ትምህርት ነው ።

## ፬ኛ ጸናጽል ።

የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ሁሉ ምልጣኑ ፣ መዝሙሩ ፣ ይኸን የመሰለው ቃለ እግዚአብሔር ሁሉ በዘንግ ወይም በመቋሚያ ከተዘመረ በኋላ ሁልጊዜ ወደጸና ጽል ይገባል ። ጸናጽል የተባለው መሣሪያ ራሱ ያማረ ድምፅ ያለው ሁኖ መልኩም በልዩ ጌጥ የሚሠራ ነው ፤ ተጀመረም የሚባለው በዕብራውያን ነው ። እኛም ከዚ ያው ከዳዊት መዝሙር አግኝተን ከዕብራውያን ሥርዓት ጋር ተቀብለን ፣ እንዘምር በታለን ፣ እናመሰግንበታለን ፣ እርሱም እንዲህ ይላል «ሰብሕዎ በጸናጽል ዘሠናይ ቃሉ» ይኸም ማለት ድምፁ ያማረ በሆነ በጸናጽል መሣሪያ አመስግኑ ማለት ነው ። በዛሬውም ጊዜ ቢሆን ዘመናዊ የሆነ መሣሪያ በጸናጽል እግር የገባ አለ ምንም ቅርጹ ልዩ ይሁን እንጅ ድምፁ እንደ ጸናጽል የሚንሻሻ ነው ። ይኸውም በሥ ጋዊ ሙዚቃ የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው ። የጸናጽል አሠራር በቤተ ክርስቲ ያን አሁንም ሆነ ያው ዓይነት ሆኖ ከብር ፤ ከናስ ፤ ከብረት ይህንም ከመሳሰሉ መዓድኖች ነው ፤ ባለ ወግና ባለማዕረግ የሆነ ግን ከብርና ከወርቅ የተሠራ ጸናጽል ይይዛል ። የሁሉም ድምፅ ለምስጋና በተቃኘው መዝሙር የሚወጣና የሚወርድ ሲሆን ፤ የሚንሻሻ ድምፅ ያለው ነው ፣ የእርሱም አጣጣል ፩ኛ ንዑስ ፣ ፪ኛ ዓቢይ መረግድ ፫ኛ ለዘብ ፤ አንድም መልስ፤ወረብ በተባለው ጊዜ የሚገባ መሣሪያ ነው ። ጸናጽል ብዙውን ጊዜ የሚውለው ከከበሮ ጋር ነው እንጂ ብቻውን አይሆንም ።

## ፭ኛ ከበሮ ።

ከበሮ የሚባለው መሣሪያ በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውል ልዩ ድምፅ ያለው ውስጡ የተፈለፈለ እንጨት ሁኖ በቆዳ የተጠፈረ ነው ። እር ሱን የመሳሰሉ አታሞ ነጋሪት የተባሉ ለዘፈንና ለአዋጅ መንገሪያ ሁነው ይገኛሉ አሠራራቸውም ተመሣሣይ የሆኑ ናቸው ። ልዩነታቸው ግን ከበሮው ፪ት አፍ ያለው ሲሆን ፤ ነጋሪቱና አታሞው ደግሞ አንድ አፍ ብቻ ነው ፤ እንዲሁም አታሞው መጠኑ አነስ ያለ ሲሆን ፤ ነጋሪቱ ግን ሰፋ ተለቅም ያለ ነው ። ሆኖም ለዜማ ለዘፈን ለሙዚቃ መሣሪያነት ሁሉ ይውላል ። በሌላው አፍሪካ ሁሉ ይኸ ዓይነት መሣሪያ ይገኛል ጥቅሙ ግን በጣም የተለያየ ነው ። ይኸም መሣሪያ በሀገራችን በመዝሙር አገልግሎት እንዲውል የሆነው የእሥራኤል እምነት ወደ

www.ethiopianorthodox.org

ሀገራችን ከገባበት ጊዜ ጀምሮ ነው ለማለት ይቻላል ፤ ምክንያቱም በዳዊት መዝሙር ሰብሕዎ በከበሮ ወበትፍሥሕት የሚል አገላለጥ ስለሚገኝ ይህንኑ በመከተል ጥንታውያን አባቶች ሲጠቀሙበት እንደነበር የታወቀ ነው ። የከበሮው አመታት ጸናጽልን ተከትሎ የሚሔድ ነው ፤ እርሱም ብዙ ጊዜ ወደ ደስታ የሚያመራ ስለሆነ ፤ በታላላቅ አጽዋማትና በልዩ ኀዘን ጊዜ አይመታም ፤ ከዚህ በላይ የገለጥናቸው የምስጋና መሣሪያዎች ሁሉ ብዙ ጊዜ የምንጠቀምባቸው እኛ ኢትዮጵያውያን ብቻ ነን ፤ ሁኖም ዓይነቱ ለየት ይበል እንጅ ሌሎችም መሣሪያዎች አሏቸው ፤ በኛም ቤተ ክርስቲያንም ቢሆን እነዚህን መሣሪያዎች ለምስጋና ብቻ እንጅ ለቅዳሴ ተግባር እና ውላቸውም ፤ እንዲያውም በገዳም ጸናጽልና ከበሮ ለአገልግሎት ፈጽመው አይገቡም።

## ልዩ አስተያየት ።

፩- የአቋቋም የትመጣና መቼ ተጀመረ፡ የሚባለው አስተያየት ውሳኔ የሌለው ሐተታ ነው ። ሆኖም ከግራኝ ወረራ በኋላ መሆኑንና በጐንደር ዘመነ መንግሥት መሆኑን የሚገልጥ አስረጅ ይኸ ሞያ ተስፋፍቶ የሚገኝ በጐንደርና በአካባቢው ብቻ ነው ።

፪- ያቋቋም ሞያ ከምስጋናው ይልቅ የታይታ የጭፋሮ መልክ ይታይበታል በዚህም ሞያ የሠለጠኑት የኩራት መልክ ይታይባቸዋል ።

፫- ይኸ ዓይነት አገልግሎት በብዙ ገዳማት አይፈጸምም አይፈለግም ፤ ምክንያቱም ዓለማዊን ስሜት ስለሚያስከትል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፲ ።

# የቅዳሴ ትምህርት ።

## ምዕራፍ ፩ ።

## የቅዳሴ ዜማ ።

### ፩ኛ የቅዳሴ ታሪክ ።

የቅዳሴ መጻሕፍት በየጊዜው የተደረሱና ደራስያኑም ልዩ ልዩ ሊቃውንት ሲሆኑ ዜማውን ያቀናበረው አንድም የደረሰው ቅዱስ ያሬድ የተባለው የዜማ ሊቅ እንደሆነ በቤተ ክርስቲያናችን የታመነ ነው ።

በተለይም ቅዳሴ ማርያምን ንባቡን አባ ሕርያቆስ እየነገረው ዜማውን እርሱ ማይበሳ በምትባለው አገር ደረሰው ይባላል ። ስለዚህም ከሌሎች ቅዳሴዎች ይልቅ ሥረይ አንድም አንቀጽ በቅዳሴ ማርያም ይበዛል ። ስለ ቅዳሴ ትምህርት ከቅዱስ ያሬድ ጀምሮ በመከታተል በየጊዜው የተነሡ የመምህራን ታሪክ ግልጥ ሆኖ አይነገርላቸውም ፤ ሆኖም ግን በጥንት ዘመን ከዝማሬ መዋሥዕት ጋር በዙራንባ ገዳም ያስተምሩት ያስመሰክሩትም ነበር ፤ ስለዚህም የምስክርነቱ ቦታ በዚያ እንደነበር ይተረካል ። እየቆየ ግን የቅዳሴ ምስክር ቦታ ተብሎ ይነገርለት የነበረው በታሪክም ጉልቶ እስካሁን ድረስ የሚታወቀው ሰለልኩላ የተባለው ገዳም ነው ። የቅዳሴ ምስክር ቦታ በእርግጠኛው መቼ እንዴት ከዙራንባ ወደ ሰለልኩላ እንደተዛወረ አይታወቅም ፤ በአፈ ታሪክ እንደተገለጠው የሆነ እንደ ሆነ ግን በግራኝ ወረራ ምክንያት የቅዳሴ ዜማ ጠፍቶ ሲኖር መንግሥት እንደተቋቋመ ሰለልኩላ ምስክር ሁናለች ፤ ምክንያቱም መምህራኑ በዙራንባ ገዳም የተማሩ ከዙራንባ ገዳም ያስመሰከሩ ሁለት ደቀ መዛሙርት ቅዳሴውን አጠናቀው ዐውቀው ሰለልኩላ ገብተው ሲያስተምሩ ስለተገኙ እነርሱው ምስክር እንዲሆኑ ተደርገዋልና ።

ከጥቂት ዓመታትም በኋላ ደግሞ ምስክርነቱ ዙራንባ እንደገና ገብቶ ወንበር ተዘርግቶ ሲኖር እንደገና ባልታወቀ ምክንያት በሌለው ቦታ ጠፋና በሰለልኩላ ስለተገኘ ፤ ሰለልኩላ አሁንም የምስክር ቦታ እንድትሆን አፄ አድያም ሰገድ ኢያሱ ወሰኑ ይባላል ። ስለዚህም የቅዳሴ ዜማ ሰለል ብላ ገባች ሲሉ ቦታዋንም ሰለልኩላ ብለዋታል ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን እስካሁን ምስክር ሁና ትገኛለች ። ምንም የቅዳሴው የምስክር ቦታ የተለየ ይሁን እንጂ ፤ እስካሁን ድረስ ዝማሬና መዋሥዕት ተምሮ ተመርቆ ሲወጣ ቅዳሴም አብሮ ማስመስከር ግድ ስለነበረበት የዝማሬ መዋሥዕት መምህራን ሁሉ የቅዳሴ አዋቂዎችና ቅዳሴንም የሚያስተምሩ ነበሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

በቅርቡ በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግሥት ግን ከሰለልኩላ ወደደብረ ዓባይ የምስክርነቱ ቦታ ተዛወረ ። ይኸንም ስንል ሕዝቡ (ተማሪው) በራሱ ፈቃድ መረጠው እንጂ ሰለልኩላ አሁንም ቢሆን ምስክርነቱን አልተወችም ፤ ጉባኤውም አልተፈታም ። ሆኖም ከዚያ ተምረው የወጡትን መምህራን የሚቀበላቸው እምብዛም ነው ፤ ሁሉም ከደብረ ዓባይ የወጡትን ይፈልግ ጀመር ፤ ስለዚህም ተማሪው የደብረ ዓባይን ዜማ ይማር ጀመር ፤ በዚህም ምክንያት ደብረ ዓባይ በቅዳሴ ዜማ የታወቀች የመነኰሳትም መሰብሰቢያ ሆነች ።

በመጀመሪያ ደብረ ዓባይን የቅዳሴ ምስክር ቦታ ያስደረጉት መምህር ገብረ ኢየሱስ የተባሉ መምህር ናቸው ፤ እርሳቸውም ለመጀመሪያ ጊዜ ሰለልኩላ ተምረው ያስመረቁም በዚያው ነበር ፤ ነገር ግን በጣም ድምፃዊ ስለነበሩ ራሳቸው ወዝ እየሰጡ ዜማውን እያስረዘሙ በማዜማቸው ዜማቸው ተወዳጅ ሆነ ። መምህር ገብረ ኢየሱስም አዲሱን ዜማቸውን እንዳጠናቀቁ ለመጀመሪያ ጊዜ የገቡት አክሱም ገዳም ነበር ፤ ነገር ግን አክሱማውያን አናስገባም በማለት ስለከለከሏቸው ወደ ደብረ ዓባይ ገብተው ወንበር ዘረጉ ፤ ዜማቸው ተወዳጅ በመሆኑ መነኰሳቱ ሁሉ ከበቧቸው ፤ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ መምህር ገብረ ኢየሱስ የቅዳሴ ምስክር ደብረ ዓባይም የምስክር ቦታ ለመሆን በቁ ።

የሰለልኩላ ዜማ ግን እጥር ያለ የድጓውን ዜማ ተከትሎ የሚሔድ ሲሆን ድምፅ ላለው የሚወስነው በመሆኑ ሁሉም የደብረ ዓባይን ዜማ ይፈልግ ጀመር ። የደብረ ዓባይ ምስክርነት የተጀመረው በቅርብ ጊዜ ሲሆን ፤ ጀማሪውም መምህር ገብረ ኢየሱስ እንደሆኑ ከላይ ተናግረነዋል ፤ እርሳቸውንም የወረሱ ወይም በእግር የተተኩ አፈ መምህር ገብረ ኪዳን ሀብቱ የተባሉ ናቸው ፤ አፈ መምህር ገብረ ኪዳን ግን አሁንም ድረስ ያስተምራሉ ፤ ዕድሜያቸውም ፩፻፱ ዓመት ነው ።

ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ግን በዚያ የሚያስተምሩ ሁሉ ብዙ መምህራን ይገኛሉ ፤ ሁሉም በየበኩላቸው የምስክር ወረቀት ስለሚሰጡ አብነቱ እገሌ ነው ለማለት አይቻልም ፤ ይሁን እንጂ አሁንም ደብረ ዓባይ ላይ የታወቁ ፫ አስተማሪዎች እንዳሉ ይነገራል ።

## ፪ኛ ግብረ ዲቊና ።

ቅዳሴ ለመቀደስ መጀመሪያ ዲያቆን መሆን ስላስፈለገ ዲያቆኑ አስቀድሞ የዲያቆኑን ሥራ ጠንቅቆ ማወቅና መሥራት ስላለበት የመጀመሪያው ትምህርት ግብረ ዲቊና ተባለ ።

ብዙዎች ሰዎች ሙሉ ቅዳሴን መማር ሲያቅታቸው በአቋራጭ መንገድ ለመሔድ የዲያቆኑንና የሕዝቡን ድርሻ በአንቀጽ መልክ ያጠናሉ ። እንደዚህ ያለው ትምህርት ወንበር የማይዘረጋለት ብዙ ጊዜም ያልታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጂ በየገዳማቱና በየአድባራቱ ጥሩ ቀዳሽ ጥሩ ዲያቆን ወይም ቄስ የሚባሉት በመጠኑ በዚህ ዓይነት የተማሩ ናቸው ። ግብረ ዲቊና በሌላ ስም ደግሞ «ተሰ

www.ethiopianorthodox.org

የግል ቤተ መጻሕፍት



ጥዎ» ይባላል ፤ ይኸውም ቄሱ ሲዘምር ዲያቆኑ ወይም ሕዝቡ የሚመልሰው መልስ የሚያዜመው ዜማ ማለት ነው ።

በወንበርም ገብቶ ተምሮ ወይም ከድምፅ ሰምቶ ያጥናው እንጂ ይኸን ሳይማር ዲያቆኑም ቄሱም ሊቀድስ አይችልም ። በአሁኑ ጊዜ ግን ይበልጠውን መምህራኑም የሚያስተምሩት ልዑካኑም ራሳቸው የሚከታተሉት ይኸንኑ ተሰጥዎ የተባለውን ነው ፤ እንዲያውም አሁን ከዲያቆናትና ከቀሳውስት አልፎ የቅዳሴው መጽሐፍ «ይበል ሕዝብ» በሚለው መሠረት ሴቶችም ወንዶችም በጠቅላላው የጨዋ ልጅ ሁሉ ማጥናት ጀምሯል ።

ግብረ ዲቁና ወይም ተሰጥዎ የተባለውም ሕዝቡ በሚፈልገው መልክ ተዘጋጅቶ ወጥቶ ይገኛል ።

## ፫ኛ ሰዓታት ።

ሰዓታት በጐላ የታወቀው የሌሊት ጸሎት እንደሆነ ነው ፤ ነገር ግን ሰዓታት ራሱ በ፪ ይከፈላል ፤ ይኸውም የመዓልት ሰዓታትና የሌሊት ሰዓታት በመባል ነው ። የሰዓታትም ቀጥታ ትርጒም በየሰዓቱ የሚጸለይ ሰዓቶችንም ተመልክቶ የሚደርስ ጸሎት እንደነበር ክፍሉ ራሱ ያመለክታል ፤ ይኸም ዓይነት ጸሎት ከነስሙ በግሪክ ኦርቶዶክስ በካቶሊክ በአንግሊካን በሌሎችም እንዲሁ ይገኛል ፤ ስሙን «ኦሬስ ፤ አዎርስ» ይበሉት እንጂ ትርጒሙ ሰዓታት ማለት ነው ።

በእርግጥ ሰዓታት ስንል ሰዓት አይቶ ሰዓትም ለይቶ የሚደርስ እንጂ የመዓልት የሌሊት የሚል ውሳኔ የለውም ፤ ግን በሀገራችን በጠቅላላ የሚደረሰው በሌሊት ስለሆነ ሰዓታት በአልን ጊዜ የሌሊቱን ጸሎት እንደሆነ ሁሉ ሊረዳው ይችላል ። በብዙ ገዳማትና አድባራት በዓቢይ ጾምና በፍልሰታ የመዓልት ሰዓታት ይቆማል ፤ በጥቂቶቹ ገዳማትና አድባራት ግን ዓመት እስከ ዓመት የመዓልትም የሌሊትም ሰዓታት ሳይቋረጥ ስለሚቆም ፤ ሰዓታት ሲል የሚያሻማ ስም ስለሆነ የመዓልቱና የሌሊቱ ተለይቶ ካልተነገረ ሌላው ሊረዳው አይችልም ።

ሰዓታት በሀገራችን ተጀመረ የሚባለው ፤ በአባ ጊዮርጊስ ጊዜ በ፲፭ኛው መቶ ዘመን ግድም ነው ። በሌሎች ግን ጥንታዊ ጸሎት ሲሆን ፤ በኛ እስከ አባ ጊዮርጊስ ዘመን ቆየ ለማለት አይቻልም ፤ እንዲያውም ከሌሎች ዓለማት አስቀድሞ ገዳማት በሀገራችን ተስፋፍተው ሲቋቋሙ የሰዓታት ጸሎት ዘግይቶ እስከ ፲፭ኛው መቶ ዘመን ድረስ ቆየ ለማለት አስቸጋሪ ነው ። ነገሩን መልክ ለመስጠት ያህል ሐተታ ያደረግን እንደሆን ምናልባት አባ ጊዮርጊስ በማሳጠር በመጠቅለል ወይም በማስረዘም አሻሻሉት ፤ ወይም የጥንቱን ትተው ራሳቸው ደርሰው አቅርበው እንደሆን አልተለየም ፤ ገና ሰፊ ጥናት የሚጠይቅ ነገር ሆኖ ይገኛል ። የአረፍተ ነገሩ አሰካክ ትንሽ ይለያይ እንጂ ከላይ እንደገለጥኩት በሌሎች

www.ethiopianorthodox.org

አብያተ ክርስቲያናት ቀደም ብሎም ተጀምሮ ይሠራል ፤ እንግዲህ በሁሉ አንድ የሆነው ጸሎት በኛ ብቻ ተቋርጦ ቀየ ለማለት አይቻልም ። ይልቁንስ የጥንቱ ሰዓታት ሌላ ሁኖ ይኸ የአባ ጊዮርጊስ ይሆንን ? ወይስ ይኸ የጥንቱ ሁኖ የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ሌላ ይሆንን ? ይኸ ሁለቱ አጠራጣሪ ወይም አሻሚ ነገር ነው ፤ ይሁን እንጂ የአባ ጊዮርጊስ ሰዓታት ተብሎ በስማቸው ከተጠራው ከገዳማቸው የተገኘው ሰዓታት አሁን ከሚደረሰው ሰዓታት ብዙ ለየት ያለ ነው ፤ ምናልባት አባ ጊዮርጊስ የደረሰው ይኸ ሳይሆን አይቀርም የሚል ግምት አለ ፤ ይኸውም በመንበረ ጸባዖት ገዳም ይገኛል ።

## ፩ኛ የሰዓታቱ ክፍል ።

የሌሊት ሰዓታት ክፍል ፫ ነው ፤ ይኸውም «፩ኛ አአትብ ወእትነሣእ» የሚለው ፤ ፪ኛ «ሚካኤል ሊቀ መላእክት» ከሚለው ጀምሮ ያለው ፤ ፫ኛ/ «ለኖኅ ሐመሩ» ከሚለው ጀምሮ ያለው ነው ። ከዚህ ውስጥ ግን ተለይቶ የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት ይኸ ነው የቀረው ደግሞ የአባ እገሌ ነው ተብሎ እንኳን ባይታወቅም ብዙ አዳዲስ ነገር በመካከሉ እንደገባበት የታወቀ ነው ። ከዚህም ውስጥ በየምዕራፉ እየገባ የሚነገረው መስተብቍዕ የሐዋርያት መሆኑ የታወቀ ሲሆን ፡ ከሰዓታት ጋር በጣልቃ ገብነት ሁሉም ይጸለያል ። እንዲሁም ዘይነግሥ ዘቅዱስ ያሬድ በዚህ መልክ በጣልቃ እየገባ ይጸለያል ። ከዚህም ጋር ሰዓሉ ለነ - - - - እያለ ከሚሔደው ላይ በየጊዜው ተጨምሯል ፤ ይኸውም ይታወቅ ዘንድ በአንድ ቦታ የሚባለው ከሌላው የተለየ ሆኖ ይገኛል ። ግልጥ ሆኖ የተገኘው መረጃ ግን ኵሎሙ ሠራዊተ መላእክት የሚለው ጸሎት ነው ፤ ማለት ይኸ ጸሎት ቍጥሩ የበዛው በየጊዜው እየተደረሰ ከመጨመሩ የተነሣ እንደሆነ ይገመታል ፤ የአባ ጊዮርጊስ ኵሎሙ ግን ወባቲ የምትባለው ብቻ ናት ።

ዜማውም ግዕዝ ፡ ዕዝል ፡ አራራይ የተቀላቀለበት ይሁን እንጂ ይበልጠው ዓራራይ ነው ። በየክፍሉ ስለ እመቤታችንና ስለጌታችን በሰፊው ሲገልጽ ስለቅዱሳንም እንዲሁ አማላጅነታቸውን በመግለጥ ይናገራል ። በመላ ድርሰቱ የግጥም መንገድ ያለው ነው ፤ አንዳንዱ እስከ ፪ት ሌላው ግን ከዚህም በላይ ቤት ያለው ግጥም ነው ። ከሰዓታት ክፍሎች ውስጥ ከ፪ኛው ክፍል ሚካኤል ሊቀ መላእክት ከሚለው ጀምሮ የዘወትር ሰዓታት እንደሆነ ሊቃውንት ይናገራሉ ፤ እስከ ርሱም መጨረሻ ድረስ ያለው ብቻ የአባ ጊዮርጊስ ድርሰት እንደሆነ ሲነገር ፡ ለኖኅ ሐመሩ ከተባለው ጀምሮ ተፈሥሒ ማርያም እያለ የሚሔደውና መልክአ ሥዕል ፡ መልክአ ውዳሴ ይኸን የመሰለው ድርሰት በየጊዜው የተደረሰና የገባ እንጂ የአባ ጊዮርጊስ አለመሆኑ ግልጥ ነው ።

ሰብሐተ ፍቁር የተባለው በተለይም የእመቤታችን አፄ ልብነ ድንግል እንደደረሱት ይነገራል ፤ ግን ከአባ ጊዮርጊስ ሰዓታት ጋር ተደምሮ ሊደረስ ቻለ ።

www.ethiopianorthodox.org

ለኖኅ ሐመሩን ፣ ተፈሥሒ ማርያምን ፣ ለአዳም ፋሲካሁን ፣ አ ርጎርጎተ ሕሊናን አፄ ልብነ ድንግል ደርሰዋል ።

የቅዱሳን የመላእክት ስብሐተ ፍቁር ግን በየጊዜው እየተደረሰ የተጨመረ ነው ። ከዚያ በኋላ ግን ኪዳን ይደርሳል ፤ ኪዳኑም ጌታ የደረሰው ሲሆን ዜማውን ያቀናበረው ቅዱስ ያሬድ ነው ። የኪዳንም ዜማ አንቀጽ የበዛበት በጣም ከባድ የሆነ ነው ፤ በአንድ ቀን እስከዚህ ድረስ ይደርሳል ።

ሰዓታት በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ሁሉ ራሱን የቻለ አገልግሎት ስላለው ዲያቆናቱም ቀሳውስቱም እንደ ግብረ ዲቁናው አድርገው ይማሩታል ፤ ያጠኑታል ። ሰዓታት ብዙውን ጊዜ በየጠቅላይ ግዛቱ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት የሚደርሰው አንድ ዓይነት ሲሆን ፣ ከአንዳንድ ቦታዎች ላይ በሚገቡ ጸሎቶች ብቻ ይለያያሉ ። በአንዳንድ መጻሕፍት የብሉያት ንባብ በዛ ብለው ሲነበቡ ይገኛሉ ፤ ይኸም ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ሰዓታት ጋር ተመሳሳይ መሆኑን ይገልጣል ። አንዳንድ መጻሕፍት ደግሞ ብሉያትን ሳያበዛ ያገባና ምቅናይዎችን ያስገባል ፤ ይኸንን በደንብ ካልተማረው በድምፅ ሊያጠናው ከቶ አይቻልም በድምጫ ከአጠኑት ይልቅ ሰዓታት የተማሩት ሁሉንም ሲያስቀኑ ደንበኛም ዲያቆናትና ቀሳውስት ሲባሉ ከሌላውም የተለየ ግምት ሲሰጣቸው ይገኛሉ ።

ይሁን እንጂ ግብረ ዲቁናውንም ሰዓታቱንም በዲቁና ብቻ ለመወሰን የፈለገ ካልሆነ በቀር ሌላውን ጥሬውን ዜማ የቃል ትምህርቱንም ሳይማር ይኸን የተማረ እንደሆነ ይስቁበታል ፤ ሰሞነኛም ብለው ይሰድቡታል ፤ ይኸንም የሚያስረዳ ብዙው በደንብ ከመማር ይልቅ በድምጫ ሰምቶ መቀደስን እንደሚመርጥ የታወቀ ነው ፤ በዚህም ምክንያት ቀሳውስቱም ዲያቆናቱም የቅስናውንና የዲቁናውን ሞያ እንኳን በሚገባ ሳያጠናቅቁ ወደ ቅዳሴ አገልግሎት የሚገቡ ጥቂቶች አይደሉም ፤ ምንም ከፍተኛ ሞያ መማሩ ምንም ታላቅ ሊቅ ቢባል ዋናው ዓላማ ለመቀደስ ፣ ለመወደስ ፣ ለመስበክ ነበር ፤ ነገር ግን በዚህ አገልግሎት የሚውሉት ዝቅተኛ ዕውቀት ያላቸው ናቸው ፤ ከፍተኛ ዕውቀት አለን የሚሉ ግን በሕገ ወጥነት የሚታዩ ከዚህ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ውጪ ሁነው ይገኛሉ ፤ የሆነው ሆኖ ሰዓታትን ሁሉም አይሁኑ እንጂ በዚህ መልክ በሙሉ ይማራሉ ።

ምዕራፍ ፪ ።

## መዝገበ ቅዳሴ ።

መዝገበ ቅዳሴ የሚባለው ከሥርዓተ ቅዳሴው ጀምሮ ያለው በመላም ፲፬ቱ የቅዳሴ ዜማ ነው ፤ ከቅዳሴው ውስጥ በንባብ የሚባለው በጣም ጥቂት ከሆኑ ክፍሎች በቀር በሙሉ ይዜማል ። መዝገብም የተባለበት በዚያ የተመዘገቡ አንድም የተጻፉ ቃላት ሁሉ ስለሚዜሙ ከተመዘገበው ከተጻፈው አንድ ሳይቀር የሚ

www.ethiopianorthodox.org

ዜም ስለሆነ ነው ። የዚህም ቅዳሴ ዜማ ወዙ አንድም ለዛው ሌላ መልክ ይፍጠር እንጂ ምልክቱ እንደ ድጓው ነው ።

ቅዳሴ የሚማሩት ደቀ መዛሙርት ብዙ ጊዜ ምልክቱን የማያውቁ ብዙ ዜማም ያልተማሩ ሲሆኑ ፥ የቅዳሴው ዜማ ቁንጥ ያለው ስለሆነ ይቀናቸዋል ፤ ምልክቱንም በዚያው ያጠናሉ ። የዜማው ሁሉ ምልክቱ አንድ ዓይነት ሲሆን ፥ የድጓው መምህርና የቅዳሴው መምህር በአንድ ዓይነት ምልክት አዚሙ ቢሏቸው የቅዳሴው መምህር በቅዳሴው ወዝ በቅዳሴውም መንገድ ፥ የድጓውም መምህር በድጓው ወዝ በድጓውም ዜማ ያዜማሉ ፤ ማለት ምልክቱ ያው ሆኖ መንገዱ የተለያየ ነው ።

ቅዳሴ የሚቀድሱ ብዙ ጊዜ መነኰሳት በመሆናቸው የቅዳሴውንም ዜማ የሚማሩትና መምህራንም የሚሆኑ አብዛኛውን ጊዜ መነኰሳት ናቸው ።

ምዕራፍ ፫ ።

# አንቀጸ ቅዳሴ ።

ከዜማ ትምህርቶች ውስጥ አንቀጽ የሚበዛባቸው የቅዳሴ ትምህርት ፥ የዝማሬ የመዋሥዕት ነው ፤ ስለዚህ ምንም ደቀ መዝሙሩ በመዝገቡ ላይ ሁሉን ቢማር እንደገና አስተዋጽኦ የሆነ ስሙ አንቀጽ የተባለ ትምህርት አለ ፤ እርሱን መማር ብቻ ሳይሆን ለብቻው ጽፎ ይይዛል ። አንቀጽ የተባለው ስረይ የበዛበት ድርብ ዜማ ያለበት ፥ እርክርክ እንዲሁ የበዛበት ፥ ለተማሪው አስቸጋሪ መስሎ የታየው ከሥርዓተ ቅዳሴው ጀምሮ እስከ ኪዳኑ በአጭር ተውጣጥቶ የተጻፈው ነው ። እርሱን በመጨረሻ ጊዜ ያስተምሯቸዋል ፤ በዚህን ጊዜ ዕገሌ አንቀጸ ቅዳሴ ያውቃል ይባላል ፤ መምህርም ሁኖ ያስተምራል ፤ እርሱም የሚከተለው ነው ። ይኸም ለምሳሌ ያህል እንጂ በጠቅላላው አንቀጾችን ያሰፈርን አይደለም ።

## ፩ኛ አንቀጽ ዘኪዳን ።

ለከ እግዚኦ ለገባሬ ኵሉ ለዘኢ.ታስተርኢ አምላክ ፥ ለጥበበ ኵሉ ኃያል ፤ ንሴብሐከ ፤ ቃል ዘባሕቲቱ በቅዱሳኒሁ እሩፍ ፥ እምስብሐታት ዘኢያረምም ፥ ፈጣሬ ኅቡዓት ዘኢ.ታስተርኢ ፥ ጥበበ ኅቡዓት ቅድሳቲከ ፤ ኪያከ ንሴብሕ ዜናዊ በቋኤ ጸጋ መንፈስ ቅዱስ ፥ ኅበ ፃዔ ወቁንቁኔ ፥ ማዕበላተ ውሂዛተ መናፍስት ፥ ዘነቢያት ወሐዋርያት ፥ ወለትውልደ ትውልድ ዘኢየኃልቅ ፥ ዓለመ ሐታሚ ፥ እምቅድመ ሕሊና ኵሉ የአምር ወዘእንበለ ንስአሉ ፥ ንጉሥ ሠራዊተ ሰማያት ፥ ቃለ ዘኢያረምም ፥ ለሞት ዘለፎ ፥ ፀሐይ ዘኢየዐርብ ፥ ገባሬ መላእክት አበ ኵሉ ፥ ወበእን

www.ethiopianorthodox.org

ዝንቱ ፡ ሕሊናተ ርቱዓተ ፡ እለ ውስተ ሞቅሕ አድኅን ፡ እስመ ለከ እግዚኦ አም ላክነ መንግሥት ቡሩክ ።

ለከ ለአብ ዘኢይማስን ፡ ወመሠረተ ጥበባት ዓቃቤ አልባቢነ ፡ ዓለም እን በለ ይትገበር ፡ ምዕራፈ ስብሐተ ሃይማኖት ።

## ፪ኛ ዘሊጦን ።

እንዘ ነአኵቶ ፡ ስምከ ሕያው ዘኢይመውት ፡ ወረደ ላዕሌሆሙ ።

## ፫ኛ ዘመስተብቍዕ ።

ናስተበቍዕ ፡ ጸልዩ ፡ እግዚኦ ነጽር ላዕሌነ ፡ ወጥኢና ይረስየነ ፡ ለዱያን አኃው ፡ ዘአፍላግ ማያት ሀቦ አምላክ ፡ አዕርፍ እግዚኦ እለ አዕረፉ ውስተ ሕፃነ አብርሃም ፡ ውስተ ብሔር ሥዑር ፡ ወኢየዓርግ ።

## ፬ኛ ዘይነግሥ ።

ነአኵቶ ወንሴብሖ ፡ ሐዋፄሃ ለነፍስ ፡ አቡሁ ፡ ዘ፴ ወ፰ ክረምተ ፡ ወአል ዓዛርሃ ፤ ወለ፭ዱ ለእሙ ፤ ወለዘእንተ ደም ይውኅዛ ፡ ወፈኑ ፡ በዋሕድ ወልድከ ፡ ወለ ዓለመ ዓለም ፡ ከመ አንተ በእሉኒ ወከመ በኵሉ ይሰባሕ ፡ ለኵሉ እንስሳ ፡ ወባ ርከ ዓውደ ዓመት ፡ እስመ አንተ መሴስይ ፡ ለተድላ ወለዳኅና ፡ ወተናገር ውስተ ልቡ ፡ አንተ ዘእምሰማያት ዘእንበለ ሙስና ፡ መሴስየ ኵሉ ዘሥጋ ።

## ፭ኛ ዘጸዋትው ።

ሃሌ ሉያ ፡ ይሰደድ እምቤተ ክርስቲያን ፡ ፩ዱ አብ ቅዱስ ፩ዱ ወልድ ቅዱስ ፩ዱ ውእቱ መንፈስ ቅዱስ ፡ ጸልዩ በእንተ እለ ያበውኡ መባዓ ፡ ንስግድ ለአብ ወወልድ ፡ ዘእግዚአብሔር ቃል ፡ ወሰባኬ ወንጌለ መንግሥትከ ፡ መጠነ ትምህርትከ ፡ አአምላክ እግዚእነ ፡ ንሑር በፍናዊሆሙ ፡ ወዕቀባ ለቤተ ክርስቲ ያንከ ቅድስት ፡ ወባርከ ፡ ወእለተኰነነ አመ ይትፌደይ ኵሉ ፡ ዘኢይጸመም ቃል ዘኢ ያረምም ፡ ፀሐይ ዘኢየዓርብ ፡ ተዘከር ካዕበ ፡ ለእለ ቀደሙነ ነዊመ ፡ ወለከ ንፌኑ ፡ ቁሙ ወአጽምኡ ፡ ዜናሁ ፡ ወንጌል ቅዱስ ፡ ከበሮ ፡ ወርኢነ ስብሐቲሁ ፤ ወምስለ ኵሉ ፍጻሜ ማኅበሩ ፡ አግርር ወቀጥቅጥ ታሕተ ፡ ወንትመጦ ፡ ዘያስተርኢ ወዘኢያስተርኢ ።

## ፮ኛ ዘሐዋርያት ።

ወያዕቆብ ሐዋርያ ፡ ሱራፌል ወኪሩቤል ፡ ወማእሠረ ሰይጣን ይብትክ ፤ ወቦቱ ረሰይከ ለነ ለተድላ ፡ ይረስዮ ለምልዓተ መንፈስ ቅዱስ ፡ ወየውሀተ ልብ ፤ ነጽር ፡ ቅድሳት ለቅዱሳን ፡ እግዚኦ መሐረነ ፡ እንዘ ንሴብሕ ፡ ይደልወነ ከመ ንሳ ተፍ ፤ ምሥጢረ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፺፯ኛ ዘቅዳሴ እግዚእ ።

እመቦ ነውረ ሕሊና ፡ ዘቦ ድውየ ሕሊና ፡ ኢየሃሉ በመዓት ምስለ ካልኡ ፤
ንቅረብ ለመድኃኒተ ሕይወት ፡ ወኵሉ ሕዝብ ፡ ዓጸፍተ ብርሃናት ፡ እምድንግል
ተወሊዶ ፡ ፈቃደ አቡሁ ይፌጽም ፡ ወሕፃናተ ያልሕቅ ፡ ለዘባሕቲትከ ዘእምዓለም ፤
እምኵሉ ሕሊና ዘኢያሠምረከ ፡ ይደንግጽ ሞት ፡ ወኢአሚን ይርኃቅ ።

## ፺፰ኛ ዘዮሐንስ ።

ኀቤከ አንቃዕዶነ ፡ ነገረነ በእንቲአከ ፡ እንበይነ እሪናክሙ ፡ ዘኢይበሊ ፤
ልዑላን በበጾታሆሙ ኪሩቤል በግርማሆሙ ፡ ይጼውዑ ከመ ይቀድስዎ ፡ ወከ
ማሁ ንሴብሐከ ፡ ወተሐፅነ ከመ ሕፃን ጠብለልዎ በአጽርቅት ፡ አንሶሰወ ከመ
ሰብእ ፡ ወይግበር ከመ ሞተ በፈቃዱ ከመ ያሕይዎሙ ለምውታን ፡ ያስተጋብ
እሙ ለዝርዋን ፡ ፈልፈለ ረባሕ ወነቅዓ ትንቢት ፡ ልብስ ዘኢተአንመ ፡ ሐመር
ዘኢይሰበር ያረትእ ፡ እድ ይቡስ ፡ ያሰጥም ፡ መራእየ አኀርው ፡ በአጋንንተ ሌጌ
ዎን ፡ ወአኮ ዕንቍ ክቡር ፡ ለዘያድኅኖሙ ፡ ማዕከለ መንሱት ፡ በእንተ ኵሎሙ ሐዋ
ርያቲከ ፡ እለ ሐረስዋ በእንተ መርዔትከ ፡ በሀገርከ ፡ እንዘ ይደልወኒ ፡ ወበእንተ
ኵሎሙ እለ አበሱ ፡ አንተ ከመ እግዚአብሔር ፡ ወለእለሂ ኢነአምር ፡ ዘበዓይሂ
ኢይመውት ፡ ወከማሁ አስተጋብአነ ዘእንበለ ናፍቆ ለብርሃነ መንግሥተ ሰማ
ያት ፡ ወዓይኑ ሠናይ ዓይኑ አኰቴት ።

## ፺፱ኛ ዘአባ ሕርያቆስ ።

ጐሥዓ ልብየ ቃለ ሠናየ ፡ በቃለ ዝንጋዔ ፡ በአማን እሳት ፡ ከመ ዘበደመ
በግዕ ሐርጌ ፡ በእንተዝ ናፈቅረኪ ፡ ሊቃነ ጳጳሳት ፡ ቲቶ ፊልሞና ፡ ኦ መስተም
ህርት ፡ አንቲ በእንቲአሆሙ ፡ ኦ ምልዕተ ጸጋ ፤ ኦ ሙሐዘ ፍሥሐ ፡ ወፈነወ ኀቤኪ
ወልዶ ዘያፈቅር ፡ ኦ ድንግል ምልዕተ ውዳሴ ፡ ዘእምኔኪ ለብሰ አማኑኤል ፤ ልብ
ሰተ ሥጋ ዘኢይተረጐም ፡ ወሰዋስዊሁ ለያዕቆብ ፡ ጽላት ዘሙሴ ፡ ጸምር ዘጌዴ
ዎን ፡ እንበለ ሩካቤ ዘዳንኤል ፡ አኮ በፍትወተ ደነስ ፡ እምሰማየ ሰማያት ዘበሰለ ፡
እምሰማየ ሰማያት ዘተቀድሐ ፡ ተአቁረ ውስተ ማኅጸንኪ ፡ ወልድ ያጸሪ ፡ ፩ዱ
ገጸ እግዚአብሔር ፡ ዘበጸዳለ ብርሃኑ ፡ ወ፯ቱ መንጠላዕት ፡ እንዘ ንስቲት አባል
አንቲ ፡ እንዘ ንእስት መርዓት አንቲ ፡ ኦ ከዊነ እም ፡ ወያመዓብሎ መዋግደ ፡ ወየ
ዓይይ ፡ ለወድሶተ መጠነ ዕበዩ ፤ ግሩም ውእቱ ዘኢይደፈር ፡ ኦ እግዚኦ በከመ
አሜሃ ዘንተ ኅብስተ ባርክ ወፈትት ፡ ከመ ዮሴፍ ወኒቆዲሞስ እለ ገነዝዎ ፡ አብ
ጽሖ ካዕበ ኀበ ዘየዓቢ ፡ ሕሉና ሥላሴ ፡ ቃለ ቅዳሴሃ ፡ እስመ ወደሳ ፡ ወማኅበረ
ደናግል ወመነኰሳት ፡ ወምስለ ኵሉ ፍጻሜ ማኅበራ ፡ ታቦት ዘዶር ፡ እስመወደሳ
እግዚእነ እንዘ ይብል ማርያምሰ ኀርየት መክፈልተ ሠናየ ፡ ወይእዜኒ ንስአሎ

www.ethiopianorthodox.org

ለጸጋዌ ጸጋ ፡ አስተማወቅዎ እስትንፋሰ አድግ ወላህም ፡ ወኵሉ ዓጸባ ዘበጽሐኪ ምስሌሁ ።

## ፲ኛ ዘግሩም ።

ዘበጸጋሁ ተፈጥረ ለኵሉ ፡ ወእምቅድመ ግብረተ ሰማያት ፡ ወእምቅድመ ፍጥረተ መላእክት ፡ ወረከበ ፬ እንስሳ ፡ ዘጊዜ ወበዘከመዝ መዋዕል ፡ አኮ ከመ ብእሲ ዘደከመ ፡ ወአመ ወለደ ኢተባሕተወ ፡ አኮ ዘአንሶሰወ ከመ ያምጽእ አላ እመንበሩ ኢተሐውሰ ፡ አላ ጸገዎሙ ንስቲተ እምዘዚአሁ ብርሃን ፡ ወዘኢያስተ ርኢ ፡ ወእሳተ ሲኦል ፡ አስተዳለወ ፡ ወአትረፈ ሰማኒተ ነፍሰ ዘከመ እሮ ብሔሩ ወዘከመ እሮ ሀገሩ ፡ መንበሩ በእሳት ክሉል ወማኅደሩ በማይ ጥፉር ፡ ወዲበ ተድ ባበ ቤቱ ፡ ሕንባበ ማይ ዘኢይትከዓው ፡ ከመ ቀስተ ደመና ዘክረምት ፡ መብረቅ ዓውዱ ፡ ሀየ ሀለዉ አቤል ወሴት ወ ኄኖስ ፡ ያጸድቅ ለእመ ፈቀደ ፡ ወልብሰ ዘን ዝኅት በደም ፡ ሀየ ሀለዉ ጻድቃን ፡ ተዓቍረ ውስተ ማኅጸን ፡ አሜሃ ኢየሱስ ፡ ይቤ ገብረ ተአምራተ ፡ ፲ወ፪ ሐዋርያት ፡ ወሊቃነ ካህናት ነበሩ ዓውዶ ለኵን ኖቱ ፡ ኀበ መቃብረ እንግዳ ፡ ወቅንዋተ እደዊሁ ፡ ይረድ ወይምጻእ ፡ ሠራዕያነ ሕጋቲሃ ለአኃዜ ዓለም ፡ ዘውስተ ገጹ ለአዳም ።

## ፲፩ኛ ዘአትናቴዎስ ።

እለ ተጋባእክሙ ፡ ከመ ሰይፈ እሳት ፡ አ ለይብሰት ፡ ወለዓለመ ዓለም ። ዘእንበለ ዳዕሙ እንተ አቡነ አዳም ፡ በአምሳለ ዮርዳኖስ ፡ መሰንቆ ይእቲ ሃይማ ኖት ፡ እንተ ባቲ አኃዘ እግዚአብሔር ፤ ኢክረምት ወኢሐጋይ ፡ ወያወፊ አብ ለወ ልዱ ፡ ወኢተውላጠ ብእሲ ፡ እግዚኦ መኑ ይቀውም ቅድሜከ ፡ እመሰ ኃጢአተኑ ትትዓቀብ ፡ ወታንሰሐስሕ ኵሎሙ እለ የኃብሩ ፡ ወበል ኤልማስ ላማ ፡ በል አባ ወአቡየ ፡ እመልዕልተ መልዕልት ፡ ነዓኪ ወድሳሃ ለበኵረ በዓላት ።

## ፲፪ኛ ዘባስልዮስ ።

ገብረ ኵሎ ፡ እማይ ወእመንፈስ ቅዱስ ፡ ዘተእኅዝነ በምክንያቱ ፡ ዘመን ገለ አረፍቱ ፡ ለዓቂበ ትእዛዝ ፡ ወኵሎ እለ ውስተ ዝ ቅኔ ፡ ወጻድቅ አባ ቡላ ፡ እንድራኒቆስ ብንያሚ ያቃቱ ፡ ዮሐንስ ።

## ፲፫ኛ ዘጎርጎርዮስ ።

የማነ እዴሁ ፡ ወኢነሢኦ ገጽ ፡ ወያቄርብ ለአብ ዕጣነ ፡ አ አምላክ ዘለዓ ለም ፡ ይገብር በከመ ሐለየ ፡ ወማይ ጐየት ሶበ ርእየት ጊዜ ይበውእ ሊቀ ካህ ናት ፡ ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም ሆሣዕና በአርያም ፡ አቁመነ በየማንከ ሆሣዕና በአርያም ፫ ጊዜ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፲፬ኛ ዘኤጲፋንዮስ ።

አልቦ ሙስና ለመልክዑ ፥ ይትኃኰላ ሰማያት ፤ ወተከለ ፥ ከመ ወኢምንት ፥ ሐጸራ ለባሕር በአናቅጽ ወረሰየ ላቲ ደመና ልብሳ ወበጊሜ ፥ ወሜመ ውስቴታ ወየሐውር ፥ ወይሰጠዎ እንዘ ይብል ምንት ውእቱ ፀሐይ ዚአሁ ማይ ጠፈረ ጽርሑ ፥ ይገብር በከመ ሐለየ ፥ እስከ ደመ ዘካርያስ ወልደ በራክዩ ፥ ወያብእ ቅድሜሁ ወመኑ ዓርገ መልዕልተ ደመናት ፥ ይእቲ ትኄይስ ፥ ዲያብሎስ ወድቀ አርዌ ተከይደ ወከይሴ ተኃጕለ ፥ ተሰፋ ጸንዓ ወንጌል ተሰብከ ፥ ዘቦቱ ማሰነ ሙስና ።

## ፲፭ኛ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ።

ዘከመ እፎ ርደቱ ወዘከመ እፎ ልደቱ ፥ ተዓቍረ ውስተ ማኅጸነ ፥ ከለሜዳ ለተሣልቆ ፥ ለዘያለብሶሙ ፥ ዬ ዬ ዬ አውረድዎ እምዕፅ ፤ ወአምጽኡ አፈዋተ ከርቤ ፤ ኢይክል ሕሊና ልብ ፥ ኢዘቀዳሚ በልብሰተ ዝንቱ ሥጋ ፥ መንሱትኬ ውእቱ ንቅረብ ለመድኃኒትነ ።

## ፲፮ኛ ዘቄርሎስ ።

ወእግዚአ አጋእዝት ፥ ወዘባነ አብሕርት ዓለም በሕፍኑ ፥ ወታነሥአ ለእለ በልየ ሥጋሆሙ ፥ ወዮሐንስ መጥምቅ ወኵሎሙ ሐዋርያት ፥ በእንተ ኵሉ መልአከ ፥ እንተ ተለክአቶ በአምሳሊሁ ፥ በአኰቴቶሙ ለመላእክት ነጽሮ ፤ ኅር የቱ ፥ ንቡራን በኢ ቡዓዴ ።

## ፲፯ኛ ዘዲዮስቆሮስ

በኃይለ መለኮቱ፥ እግዚአብሔር በሥላሴሁ፥ ሞተ ከመ ያሕይዎሙ ለምውታን ።

## ፲፰ኛ ዘያዕቆብ ዘሥሩግ ።

እንዘ ትዜከሮሙ ፥ ወወሀብኮ ወአኰነንኮ ኵነኔ ሰማያት ፥ ወኵሉ ስም ፥ ሠራዊተ ሚካኤል በበነገዶሙ ፥ ንስቲት ወለት ወለቶሙ ፥ ገሊላዊት ሐቀፈተከ ፥ ሆሣዕና ዘምስለ አርዳኢከ ፥ ወበእንተ እሉ ፬ ወንጌላውያን አምሳለ መላእክት ይኩን ሚካኤል ፤ እግዚአ ዘተአምር አንተ ረሲ ይሰጠም በአምሳለ መላእክት ፤ ነዓኬ ሊቀ ካህናት ሌሊተ ፥ ተኖለዎሙ ከመ ማየ ክረምት ።

### <u>፪ኛ መንፈሳዊ አገልግሎትን ለመፈጸም የሚያስፈልገው ፤</u>

ቤተ ክርስቲያናችን የምትከፈትበት መንፈሳዊ አገልግሎታችንም የሚፈጸምበት ፤ ቅዳሴ ውዳሴ የሚደርስበት ፤ ይኸ የቅዳሴ ትምህርት ነበር ፤ ነገር ግን እን ደርሱ ሁኖ ደግሞ ዝቅተኛ ሞያ ተብሎ የሚቈጠር ነገር የለም ፤ ይኸም ይታወቅ

www.ethiopianorthodox.org

ዘንድ ሊቃውንቱ ሁሉ ሞያ ነው ብለው አይማሩትም ፤ ቢማሩትም አያገለግሉበትም ፤ ስለዚህም ሁሉም ከመቅደስ ውጭ ሁነው ይገኛሉ ። እንደእውነቱ ከሆነ ግን የመንፈሳዊው ትምህርት ወይም የቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መነሻውና መድረሻው ይኸው ቅዳሴው ስለሆነ ሁሉም አስቀድሞ ሊማረው በተገባው ነበር ።

በሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ግን የቅዳሴ ትምህርት ብለው የሚያስተምሩት ዜማውን ብቻ ሳይሆን ፤

፩/ ሥነ ሥርዓቱን ፥

፪/ ምልክቶችን ( ሲምቦሊክ )

፫/ የአሠራሩን አቅድ ነው ፤ በዚህ በኛ ግን የቅዳሴውን ትርጒም የሚያውቁ ሥራውን አንድም አቀዳደሱን አያውቁም፤ አንዳንድም ቢኖሩ በጣም ጥቂቶች ናቸው ።

ይኸ ትምህርት በሥራው የተለየ መልክ ነበረው ፤ ማለት አስተማሪዎች በትምህርት ገበታ ላይ ብቻ እንጂ በሥራ ተካፋይነት እምብዛም አይታይባቸውም ነበር ፤ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን ለቅዳሴው የትርጒሙም የዜማውም መምህራን ብዙዎች ቀዳሾች ሠራተኞች ሁነው በመገኘታቸው ለቤተ ክርስቲያን መልክ ሰጥተው ያረጀውን አድሰው ይገኛሉ ።

በዜማው ትምህርት ብዙ ሊቃውንት የሚገኙ ሲሆን ፤ ስለትርጒሙ በቅርብ ጊዜ ሞያ ብለው የደከሙበት ያስተማሩት በኋላም እንዲታተም ተርጒመው ያቀረቡት መምህር ክፍለ ገሪማ (አቡነ ሚካኤል ዘጐንደር) ናቸው ።

ምዕራፍ ፫ ።

## በኅብስቱና በወይኑ መለወጥ ጊዜ ።

በኅብስቱና በሥጋው መለወጥ ጊዜ የሚጸለዩት ጸሎቶች በተለያዩ ሰዎች በተለያዩም ጊዜያቶች የተደረሱ ይሁኑ እንጂ የ፲፬ቱ ቅዳሴያት የጸሎቱ ዓይነት የኃይለ ቃሉም ግንኙነት ከውላጤው ጸሎት ላይ ብዙዎች ቅዳሴዎች ወደ ሥነ ፍጥረት ሲያደሉ ፥ ብዙዎቹ ደግሞ ወደዶክተሪን ሲስቡ ለጸሎተ ቅዳሴው ተስማሚ ሁነው እማሬውን ድማሬውን ጠብቀው የሚሔዱ ጥቂቶች ናቸው ። ይሁን እንጂ በዚህ በውላጤው ጸሎት ላይ ሁሉም ይገናኛሉ ፤ እውነት ነው ፤ ከአንድ ላይ ሩቅ በአንዱ ላይ ቅርብ አድርጎ ቢያሳይም ቅሉ ምሥጢሩና ዓላማው አንድ ነው ። እንዲሁም ስለ ኅብስቱም ተናግሮ ስለ ወይኑ ሳይነገር ወከማሁ ብሎ ይተወዋል ፤ ለምሳሌም የሚከተለውን እንመልከት ።

## ፩ኛ ዘቅዳሴ ሐዋርያት ።

በይእቲ ዕለት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ነውር ። አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ ኀበ አቡሁ ፥

www.ethiopianorthodox.org

አእኰተ ፡ ባረከ ፡ ወፈተተ ፡ ወወሀቦሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ያንቅዖ ኵናት ለዘበእንቲአክሙ ይትፈተት ለኀድገተ ኃጢአት ወከማሁ ጽዋዕኒ አእኰቶ ባሪኮ ወቀዲሶ ወመጠዎሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ወለቤዛ ብዙኃን ።

## ፩ኛ ዘቅዳሴ እግዚእ ።

በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት ወንጹሐት እለ እንበለ ነውር ፡ አእኰተ ፡ ባረከ ፡ ወፈተተ ወመጠዎሙ ለአርዳኢሁ ነጊሮ እንዘ ይብል ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትፈተት ለኀድገተ ኃጢአት ፤ ወሶበ ዘንተ ትገብሩ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ ፤ ወከማሁ ጽዋዓ ወይን ቶሲሐከ አእኵተከ ባሪከከ ወቀዲሰከ ወወሀብኮሙ በአማን ደመከ ዝንቱ በአማን ዘተክዕወ በእንተ ኃጢአትነ ።

ከዚህ ላይ የሩቅና የቅርብ አስተያየት ይገኝበታል ፤ ምክንያቱም ሐዋርያት በምሴተ ኀሙስ እንዳዩት አእኰተ ፡ ባረከ ብለው እስከ ፍጻሜው በሩቅ ተናገሩ ፤ በመጽሐፈ ኪዳን ግን በኅብስቱ ላይ አእኰተ አለና በሩቅ ተናገሮ በጽዋዕ ላይ ግን አእኵተከ ብሎ በቅርብ ተናገረ ። ይኸም ቅሉ የቋንቋ ጉዳይ እንጂ ኃይለ ቃሉ በምንም ዓይነት አልተለያየም ፤ አንድ ነው ።

## ፫ኛ ዘቅዳሴ ማርያም ።

አሚሃ ኢየሱስ ክርስቶስ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት ወንጹሐት እለ እንበለ ርስሐት ፤ አንቃዕደወ ሰማየ ኀበ አቡሁ ወአስተምሐረ ወላዲሁ ወአማኅጸነ አርዳኢሁ ከመ ይዕቀቦሙ እምኵሉ እኩይ ። ባረከ እንዘ ቡሩክ ውእቱ ፈተተ እንዘ ቅዱስ ውእቱ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ለቤዛ ኵሉ ዓለም ። ወከማሁ ጽዋዓኒ እምድኅረ ተደሩ አንፀረ ወይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ያንቅዖ ኵናት ወለዝ ሶበ ትገብርዎ ተዝካረ ዚአየ ግበሩ ወተዝካረ ሞትየ ወተዝካረ ትንሣኤየ ትዜንዉ ።

አባ ሕርያቆስ ደግሞ ስለ ኅብስቱ ደኅና ይናገርና ወከማሁ ጽዋዓኒ ብሎ በጽዋው ላይ የሚሆነውን ቡራኬ ሳይናገር ይተወዋል ፤ ይኸም ማለት በኅብስት የተናገረውን መልሶ እንደተናገረ ስለሚቆጥረው ትቶታል ።

## ፬ኛ ዘዮሐንስ ወልደ ነጐድጓድ ።

ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት ሕፄሃ ለመርዓትከ ወሕዳጋቲሃ ለእንተ ኃደገ ምኵራባ ፤ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ

www.ethiopianorthodox.org

ወይቤሎሙ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ዘበልዐሂ ኢይመውት ወዘነሥአሂ ኢይማስን ንሥኡ ብልዑ እምኔሁ ኵልክሙ ፤ ወከማሁ ሰብሐ ዲበ ጽዋዕኒ ወይቤ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘሐዲስ ሥርዓት ንሥኡ ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ መንክር ተአምር ውእቱ ለኵልክሙ እለ ይሰግዱ ሎቱ ዓውደ ሰቃልያን ዘተጽሕፈ በደሙ ወተዓቅበ በመስቀሉ ወተኃትመ በስቅለቱ በእንተ ሕይወት ዘለዓለም በዘይትኀደግ ኃጢአቱ ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ ።

ከዚህ በላይ ወልደ ነጕድጓድ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ብሎ ሕፄሃ ለመርዓትከ ይላል ። ወደአብ ማሰማቱ ነው ፤ እንዲሁም ወከማሁ ዲበ ጽዋዕ ብሎ ቃሉን ይተዋል ፤ እንደ ቅዳሴ እግዚእ የኅብስቱን ለጽዋዕ አድርጎ መናገር ነው ።

## ፫ኛ ዘዮሐንስ አፈወርቅ ።

ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወንጹሐት ወብፁዓት እለ እንበለ ርስሐት ፤ አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ ኀበ አቡሁ እግዚአብሔር ወእግዚአ ኵሉ ወመልዕልተ ኵሉ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ዝ ውእቱ ሥጋየ መብልአ ጽድቅ ዘበአማን ። ዘበልአ እምኔሁ ለሕይወት ዘለዓለም ንሥኡ ብልዑ እምኔሁ ኵልክሙ ወከማሁ ጽዋዓኒ ቶስሐ ማየ ወወይነ አእኰተ ባረከ ወቀደሰ ወወሀቦሙ ወይቤሎሙ ዝውእቱ ደምየ ስቴ ሕይወት ዘበአማን ዘሰትየ እምኔሁ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ንሥኡ ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ ተአምር ውእቱ ለክሙ ለእለ እምድኅሬክሙ ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ ።

## ፬ኛ ዘጎርጎርዮስ ።

ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ዘተቀነወ ወበዘለሀኮ ለአዳም አቡነ ንጹሕ ውእቱ ዘእንበለ ርስሐት ወጽሩይ ውእቱ ዘእንበለ ተምያን አእኰቶ ባረኮ ወፈቴቶ ወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ለእሊአሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ መብልዐ ጽድቅ ዘበአማን ሥጋየ ውእቱ ዘይትወሀብ ለመድኃኒተ ኵሉ ዓለም ዘይበልዕሂ ወየሐዩ ለዓለመ ዓለም ። ወካዕበ አንጸረ ዲበ ጽዋዕ ማየ ሕይወት ምስለ ወይን አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወቀደሰ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ስቴ ሕይወት ዘበአማን ዘሰትየ እምኔሁ ቦ ሕይወት ዘለዓለም ንሥኡ ስትዩ ኵልክሙ እምኔሁ ይኩንክሙ ለሕይወት ወለመድኃኒት ።

## ፭ኛ ቅዳሴ ዘ ፫፻፲፰ ።

ወአንሶሰወ ምስሌሆሙ ወአርአዮሙ ሥርዓተ ምሥጢር ዘቍርባን ፤ ነሥአ ኅብስተ በቅድሜሆሙ ባረከ ወፈተተ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ዘበእንቲአክሙ ይትፈተት ለኅድገተ ኃጢአት ፤ ወከማሁ ጽዋዓኒ ባረከ ወይቤ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ለኅድገተ ኃጢአት ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፰ኛ ዘኤጲፋንዮስ ።

በይእቲ ሌሊት ምሴተ ኀሙስ ለጸቢሐ ዓርብ አመ ረፈቀ ውስተ ቤተ አልዓዛር ዓርኩ ነሥአ በእደዊሁ ኅብስተ ሥርናይ ናዕተ እምዘ አምጽኡ ሎቱ ለድ ራር ፤ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ዘይትፌተት በእንቲአክሙ ፤ ወካዕበ ቶስሐ ጽዋዓ ማይ ምስለ ወይን አእኰተ ባረከ ወቀደሰ ወመጠዎሙ ለሐዋርያቲሁ ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘይትከዓው በእንቲአክሙ ወዝንቱ ሥርዓት ይኩንክሙ ለተዝካረ ሞትየ ወትንሣኤየ ።

## ፱ኛ ዘዲዮስቆሮስ ።

በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱ ሳት ወብፁዓት እለ እንበለ ነውር ፤ አንቃዕደወ ሰማየ ኀበ አቡሁ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ንጹሐን ወለሐዋርያቲሁ ቅዱሳን ወይ ቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ለኅድገተ ኃጢአት ፤ ወከማሁ ጽዋዓኒ እምድኅረ ተደሩ ቶስሐ ማየ ምስለ ወይን አእ ኰተ ባረከ ወቀደሰ ወወሀቦሙ ለእሊአሁ ሐዋርያቲሁ ንጹሐን ወለአርዳኢሁ ቅዱ ሳን ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ለኅድገተ ኃጢአት ።

## ፲ኛ ዘያዕቆብ ዘሥሩግ ።

ነሣእከ ኅብስተ በእደዊከ ቅዱሳት ከመ ተሀቦሙ ለአርዳኢከ ንጹሐን ዘአ ሜሃ ባረከ ባርኮ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት ዘአሜሃ ፈተትከ ፈትቶ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት ፤ ወካዕበ ቶሲሐከ ጽዋዓ ወይን ምስለ ማይ ከመ ተሀቦሙ ለሐዋርያቲከ ንጹሐን ዘአሜሃ ቀደስከ ቀድሶ ይእዜኒ ለዝንቱ ጽዋዕ ዘአሜሃ መጠውከ መጥዎ ይእዜኒ ለዝንቱ ጽዋዕ ዘአሜሃ ደመርከ ደምሮ ይእዜኒ ለዝንቱ ኅብስት ምስለ ዝንቱ ጽዋዕ ይኩን ሥጋከ ወደመከ ።

## ፲፩ኛ ዘባስልዮስ ።

ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት እንበለ ርስሐት ወንጹ ሐት ወማኅየውያት አሜሃ ነጸረ ውስተ ሰማይ ኀቤከ ኀበ አቡሁ እግዚአብሔር ወእግዚአ ኵሉ ፍጥረት ። አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወወሀቦሙ ለአርዳኢሁ ቅዱሳን ወለሐዋርያቲሁ ንጹሐን ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ እምኔሁ ኵልክሙ ፤ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ለኅድገተ ኃጢአት ወከ መዝ ግበሩ ተዝካርየ ፤ ወከማሁ ካዕበ ጽዋዓኒ እምድኅረ ተደሩ ቶስሐ ማየ ምስለ

www.ethiopianorthodox.org

ወይን አእኰተ ባረከ ወቀደሰ ጥዕመ ወወሀቦሙ ለእሊአሁ አርዳኢሁ ቅዱሳን ወለሐዋርያቲሁ ንጹሓን ወይቤሎሙ ንሥኡ ስትዩ እምኔሁ ኵልክሙ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ለሥርየተ ኃጢአት ወከመዝ ግበሩ ተዝ ካርየ እስከ ሶበ እመጽእ ።

## ፲፪ኛ ዘአትናቴዎስ ።

ነሢእከ ኅብስተ በቅድሜሆሙ አእኰትከ ባረከ ወፈተትከ ወወሀብኮሙ እንዘ ትብል ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ዘአልቦ ተሌልዮ እምኔሁ ወከማሁ ጽዋዐኒ ቶሳሕከ ማየ ወወይነ አእኰትከ ባረከ ወቀደስከ ወወሀብኮሙ እንዘ ትብል ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘአልቦ ተፈልጦ እምኔሁ አምጣነ ትበልዕዎ ለዝንቱ ኅብስት ወትሰትይዎ ለዝንቱ ጽዋዕ ዜንዉ ሞትየ ወትንሣኤየ ወእመኑ ዕርገትየ ወዳግመ ምጽአትየ በስብሐት ።

## ፲፫ኛ ዘቄርሎስ ።

በይእቲ ሌሊት እንተ ባቲ አመ ያገብእዎ ነሥአ ኅብስተ በእደዊሁ ቅዱሳት ወብፁዓት ወንጹሐት እንበለ ነውር አንቃዕደወ ሰማየ ኀቤከ ኀበ አቡሁ ፤ አእኰተ ባረከ ወፈተተ ወይቤሎሙ ንሥኡ ብልዑ ዝውእቱ ሥጋየ ዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ወይትወሀብ ለቤዛ ኵሉ ዓለም በዘይትኃደግ ኃጢአት ፤ ወካዕበ እምድኅረ ተደሩ ነሥአ ጽዋዓ አእኰተ ባረከ ወቀደሰ ወይቤሎሙ ለአርዳኢሁ ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ዘሐዲስ ሥርዓት ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ለቤዛ ኵሉ ዓለም በዘይትኃደግ ኃጢአት ።

## ፲፬ኛ ዘጎርጎርዮስ ዘአርማንያ ።

ደምር እግዚኦ ትስብእተነ በመለኮትከ ዕበየከ በትሕትናነ ወትሕትናነ በዕበይከ ከመ ናቄርብ ለከ ዘንተ ቍርባነ ዘአንተ ወሀብከ ለአርዳኢከ እንዘ ትብል ንሥኡ ብልዑ ዝ ኅብስት ሥጋየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትፌተት ወይትወሀብ በዘይትኃደግ ኃጢአት ወበሕይወት ዘለዓለም ፤ ወከማሁ ዲበ ጽዋዕ ነገርኮሙ እንዘ ትብል ንሥኡ ስትዩ ዝ ጽዋዕ ደምየ ውእቱ ለዘበእንቲአክሙ ይትከዓው ወይትወሀብ በዘይትኃደግ ኃጢአት ወለሕይወት ዘለዓለም ፤ ወከመዝ ግበሩ ተዝካርየ ወትቤሎሙ አምጣነ ትበልዕዎ ለዝንቱ ኅብስት ወትሰትይዎ ለዝንቱ ጽዋዕ ሞተ ዚአየ ትዜንዉ ወበትንሣኤየ እንዘ ትትነሥኡ ወትትአመኑ ወግበሩ ተዝካርየ በስብሐት ወበውዳሴ በአኰቴት ወበዕበይ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፬ ።

# ቡራኬ ዘአፍአ ወውስጥ ።

በሥጋውና በደሙ ለውጥ ጊዜ አንድም በጠቅላላው በቅዳሴ ጊዜ ሊፈጸሙ የሚገባቸው ፵፪ ቡራኬዎች አሉ ። እነዚህም የውስጥና የውጭ ቡራኬዎች ይባላሉ ፤ ሀ/ የውስጥ ቡራኬዎች ፳፩/ ናቸው ፣ እነርሱም ቡሩክ እግዚአብሔር አብ አኃዜ ኵሉ ሲል እጁን በኅብስቱ ራስ ላይ ያመለክታል ። ወቡሩክ ወልድ ዋሕድ ሲል በእግሩ ላይ ይመለከታል ። ወቡሩክ መንፈስ ቅዱስ ሲል ከግራ ወደ ቀኝ ያመሳቅላል ፣ ይህ አንድ ቡራኬ ነው ።

በጽዋው ላይ ደግሞ ልክ እንደዚሁ ያደርጋል ፤ ደግሞም በአንድነት በኅብስቱና በጽዋው ላይ ልክ እንዳለፈው እያለና እያደረገ ይባርካል ፤ ሦስት ቡራኬ የተባሉት እነዚህ ናቸው ።

በጸሎተ እንፎራም ጊዜ እንደዚሁ ሦስት ጊዜ ይባርካል ፮ ይሆናል ። በጸሎተ ውላጤ ጊዜ አእኰተ ሲል አንድ ቡራኬ ፣ ባርክ ሲል አንድ ጊዜ ፤ ወፈትት ሲል ኦንድ ጊዜ ባርኮ በጣቱ የቀኖች ምልክት መውጋት ፣ ከራሱ ፣ ከእግሩ ፣ ከግራና ከቀኝ ፤ ፫ኛም ከጐድኑ ላይ ይወጋዋል ። ቡራኬ ፫ት ይሆናል ። በጽዋው ላይ ደግሞ እንደዚሁ ሦስት ጊዜ ፤ ይባርካል ፮ ይሆናል ። የቀድሞው ፮ ያሁኑ ፮ ሲደመሩ ፲፪ ይሆናሉ ፤ ይረስዮ ሲል ደግሞ አንድ ከኅብስት አንድ ከጽዋዕ ፤ ሦስተኛውን ግን ከሁለቱ ላይ በአንድነት ይባርካል ፣ ይህ ፫ ቡራኬ ይሆናል ።

እአምን እአምን እአምን ወእትአምን ሲል ይኀትም ሥጋ በደም አንድ በኅብስት ይላል ፣ በሥጋ ላይ ሦስት በደም ላይ ሦስት ይባርካል፤ይህ ፮ ይሆናል ፤ ይረስዮ ሦስቱና ፮ቱ ሲደመሩ ፱ ይሆናሉ ። የቀድሞው ፲፪ አለ ፤ ከዚህ ፱ ሲደመር ፳፩ ይሆናል ፤ የውስጥ ቡራኬ ማለት በኅብስትና በጽዋ ላይ የሚሆን ይህ ነው ።

፳፩ ጊዜ ቡራኬ የሆነበትም ምክንያት አለው ፤ ምሳሌም አለው ፤ እርሱም ኀሙስ ማታ ጌታን ሦስት ሰዓት አሳልፈው ይዘውታል ፣ በ፱ኛው ሰዓት ሌሊት መከራ ተቀብሎበታል ፤ በመዓልት ቅድስት ነፍሱ ከቅዱስ ሥጋው እስክትለይ ፱ ሰዓት መከራን ተቀብሏል ። ነፍሱ ከተለየች በኋላም በመስቀል ሁለት ሰዓት ቆይቷል ። አውርደው እስከ ቀበሩበት ጊዜ ፤ አንድ ሰዓት ይሆናል ። ይህ ሲደመር ፳፩ ሰዓት ይሆናል ። በ፳፩ዱ ሰዓት በተቀበለው መከራ ካሣ እንደ ተፈጸመ ዓለምም እንደዳነችና እንደ ተባረከች እንደ ተቀደሰች ለማጠየቅ ነው ።

ለ/ የአፍኣ ቡራኬ የሚባሉትም እንደዚሁ ፳፩ ናቸው ፤ እነርሱም አርኅቅ ሲል ፫ ጊዜ ፤ በፍትሐት ዘወልድ ጊዜ አግብርቲከ እለ ተልእኩ ሲል ፫ ጊዜ ቡራኬ ፤ ወዕቀባ ሲል ፫ ጊዜ ፤ ሁሉም ሲደመር ዘጠኝ ይሆናል ፤ በወንጌል ላይ ቃል ብቻ ነው ወንጌል መባረክ አይገባም ይላሉና ፤ ከወንጌል በኋላ ግን ሁለት ጸዋትው አሉ ፤ በዚያን ጊዜ አንዳንድ ቡራኬ አላቸው ሁለት ቡራኬ ይሆናሉ ፤ በጠቅላላው

www.ethiopianorthodox.org

ደብረ ሪታና ቤተ ስብ
የግል ቤተ መጻሕፍት



እስከዚህ ፲፩ ይሆናሉ ፤ በጸሎተ ቡራኬ ጊዜ ሦስት በጸሎተ ንስሐ ጊዜ ሦስት አለው ፤ ፯ ይሆናሉ ፥ እለ ጸዋዕከ ሲል ፩ አድኅን ሕዝበከ ሲል ፩ ሁሉም ሲደመሩ ፲ ይሆናሉ ፤ ነገር ግን እለ ጸዋዕከን የቆጠሩ እንደሆነ እግዚአብሔር የሃሉ የሚለው ከቍጥር ውጭ ይሆናል ። እግዚአብሔር የሃሉ የተቈጠረ እንደሆነ እለ ጸዋዕከ ከቍጥር አይገባም ይላሉ ፤ ይህ ዓይነት ቡራኬ ግን በሕዝብ ላይ የሚሆን ነው ፤ ይኸ ሁሉ ሲደመር ፵፪ ይሆናል ።

## ፩ኛ ፍታቴ ።

የፍታቴውም መንገድ መጀመሪያ ከላይ ወደታች ይወርዳል ፤ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራም ወደቀኝ ያልፋል ፤ እንዲሁም ዙሪያውን ይከባል ፤ በመጨረሻ ግን ወደላይ ይወጣል ። መጀመሪያ ከ፪ት ያነቃዋል ፤ ይኸውም የሥጋና የቃል ምሳሌ ነው ።

ዘባኑንም አይለየውም ፤ ይኸም የተዋሕዶ ምሳሌ ነው ። እንዲሁም የነፍስና የሥጋ ምሳሌ ይሆናል ፤ ዘባኑ ግን የመለኮት ምሳሌ ነው ፤ ከሁለቱም አልተለየምና ክፍዮችን የላዩን ወደታች የታቹን ወደላይ ያደርገዋል ፥ አምላክ ሰው ፤ ሰው አምላክ እንደሆነ ለማጠየቅ የቀኙን ወደ ግራ የግራውን ወደቀኝ ያዘዋውረዋል ፥ ኃያሉ ድኩም ፥ ድኩሙ ኃያል የመሆኑ ምሳሌ ነው ፤ እንደገና ሁሉንም እየቦታ ይመልሰዋል ፥ ይኸም የተዓቅቦ ምሳሌ ነው ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩- የቅዳሴ ሞያ እንደቀላል ተቈጥሮ የሚማሩት ደካሞች የሆኑ መነኮሳት ናቸው ፥ እነርሱም ዜማውን ብቻ እንጂ ምሥጢሩን አያውቁትም ፤ ስለዚህ በየቤተ ክርስቲያኑ የሚታየው የአገልግሎት መዘበራረቅ ከዚሁ የተነሣ ነው።

፪- ከቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ዝቅተኛ ሞያ መስሎ የሚታየው ቅዳሴው ነው ፥ ምክንያቱም ደብተራው ሁሉ ማኅሌቱን ከማታው ጀምሮ ሲያቀልጠው እያደረ ሲነጋ ቅዳሴ ሲገቡ ጥሎት ወጥቶ ይሔዳል ። አንድ ቄስ መቀሰሱ ካልቀረ ዜማውን ፤ ንባቡን ፤ ትርጕሙን ፤ ሥነ ሥርዓቱን አብሮ ጠንቅቆ ማወቅ ያስፈልገዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፫ ።

# የግዕዝ ትምህርት ።

ምዕራፍ ፩ ።

## የግሥ ትርጉም ።

ግሥ ማለት ቀለም አገሥጋሽ ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ማንኛውም አረፍተ ነገር ያለ ግሥ የማይነገር የማይገሠግሥም ነውና ፤ ዕርባታው ሁሉ ሲወርድ ግሥ ወረደ ይባላል ።

የግዕዝ ትምህርት መጀመሪያው ግሥ ይባላል ፤ ቅኔ ከመቍጠሩ በፊት ግሥ መግሠሥ ማውረድ ነው ፤ ስለዚህ የግዕዝ ትምህርት ሁሉ ግሥ ለማለት ግዕዝ ተብሏል ። ብዙዎች ሊቃውንት እንደሚሉት የሆነ እንደሆነ ግን ግሥ ማለት ግዕዝ ካለው ቃል የተወረሰ እንደሆነ ይናገራሉ ።

ግዕዝም ማለት ፊደሉ በግዕዝ ፊደል ብቻ የሚጀመር ስለሆነ ቋንቋውም ግዕዝ ተባለ ፤ ስለዚህም የርሱ ቃላት ሁሉ ግሥ ተባለ የሚሉ አሉ ። በቂ አስረጅ አለው በማለት ግን ጕላ አድርገው የሚናገሩት አገሬ ብሔረ አግዓዚት (ነፃ የወጣች አገር) ቋንቋውም ግዕዝ ተባለ ፤ ግዕዝም ነፃ ራሱን የቻለ ቋንቋ ሆነ ፤ ሰዎችም አግዓዝያን ነፃ የወጡ አንድም ነፃ የሚያወጡ እግዓዝያን እንደተባሉ ይናገራሉ ፤ ስለዚህም በግዕዝ ግሥ ተባለ ሲሉ ያስረዳሉ ። ግዕዝ የተባለው ቋንቋ ግን ለኢትዮጵያ ሕያው ቋንቋ ሆኖ ብዙ መጻሕፍት ተተርጕመውበት ብዙ ድርሰቶችም ተደርሰውበት ብዙም ሕጋዊ ሥራም ተሠርቶበት የቈየ ቋንቋ ነው ከ፲፪ኛው መቶ ዘመን ወዲህ ግን በርሱ ቦታ አማርኛ ስለገባበት ግዕዝ የቤተ ክርስቲያን ቋንቋ ብቻ ሆኖ እስካሁን ሳይጠፋ ሲሠራበት ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በቤተ ክርስቲያንም ቢሆን በንባብና በዜማ ካህናት ብቻ ይጠቀሙበታል እንጅ ከንግግር አደባባይ ከወጣ ብዙ ጊዜው ነው ።

የቀረው ቀርቶ በካህናቱም ዘንድ የተነበበው ምን ማለት እንደሆነ የሚያውቁት ጥቂቶች ናቸው ፤ እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ ከቤተ ክርስቲያን ውስጥም ሳይወጣ አልቀረም ፤ ምክንያቱም ብዙውን ጊዜ በከተማ ውስጥ ባሉት አብያተ ክርስቲያናት የሚጸለየው በአማርኛ ስለሆነ ነው ።

ለሀገርና ለቤተ ክርስቲያን ግንኙነትና አንድነት ግዕዝ ብዙ ረድቶ ነበር ፤ ምክንያቱም ማንኛውም ጕሳ ክርስቲያን ከሆነ ለንግግር የየራሱ ቋንቋ ይኑረው እንጂ በቤተ ክርስቲያን በኩል ግን ግዕዙን የወል ቋንቋ አድርጎ ሲጠቀምበት ቆይቷል ፤ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን አንድ የሚያስደስት ነገር አለ ፤ እርሱም ግዕዝ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ከፈተና ውስጥ ማለፊያ አንዱ በመሆኑ ወጣቶች እንደሚማሩት ሁኗልና ።

www.ethiopianorthodox.org

ግዕዝ እንድም ግሥ የተባለው ትምህርት እንደዚህ ብሎ ይውጣ እንጂ ግሥ በሚለው ቃል ዛሬ በብዙ መልክ ይጠቀሙበታል ፤

ሀ/ የአረፍተ ነገር ማሠሪያ አንቀጽ ፥ በአማርኛ ቋንቋ ሳይቀር ግሥ የሚለው ቃል የአረፍተ ነገር ማሠሪያ አንቀጽ እንደሆነ ከግዕዙ ተወርሶ ይገኛል ።

ለ/ አንድ ትልቅ ሰው በመጣ ጊዜ ካህናት ሲቀበሉት ግሥ ገሠው ግጥም ገጥመው ፥ ጥቅስ ጠቅሰው ነው ፤ ይኸም ግሥ ይባላል ፤ ይኸም ከመጻሕፍት የተያያዙ ቃላት ሲገኙበት ነው ። ስለዚህም እነ እገሌ እገሌን እንዲህ ያለ ግሥ ገሠው ተቀበሉት ይባላል ።

ሐ/ መጽሐፍን ተንተርሶ ወይም ተመርኩዞ የሚቀኙት ቅኔ ግሥ ቅኔ ይባላል ፤ ይኸም ማለት ግጥሙ ቅኔ ምሥጢሩ መጽሐፍ የሆነ ቅኔ ማለት ነው ። ግሥ በዚህ መልክ የተለያየ ስም ስላለው ለማወቅ ያህል ዘረዘርነው እንጂ ግሥ በማለት በዚህ ክፍል የምንናገረው ከግዕዝ ትምህርት ውስጥ ፩ኛውን ክፍል ነው ።

ግዕዝ ጠቅላላ ስም ቢሆን ፤ የቃላቱን ዝርዝር ግሥና ነባር በማለት ይናገረዋል ፤ ነባር የተባለው የማይወርድ ፣ የማይረባ ፤ የማይበዛም ቃል ሲሆን ግሥ የተባለው ግን በብዙ መልክ የሚወርድ የሚረባ ከአንድ ቃል ብዙ መልክ ያላቸው ቃላት ሊገኙበት የሚችሉበት ነው ። ለመጀመሪያም ጊዜ ተማሪ ወደ ቅኔ ቤት ሲገባ ሊያጠናው የሚገባው ቃላትን ስለሆነ ቃላቱ ሁሉ ግሦች ወይም ግሥ ይባላሉ ፤ እርሱንም ደረጃ በደረጃ የፊደልን ተራ በመጠበቅ ያጠናዋል ። የግሥ አጠናንም ዘዴ በ፪ ዓይነት ይከፈላል ፤ እርሱውም ሀ/ ነጠላ ግሥ ፤ ለ/ ድርብ ግሥ በማለት ነው ። የያንዳንዳቸውንም አካሄድ ከዚህ እንደሚከተለው ተመልከት ።

## ሀ/ ፩ የነጠላ ግሥ አወራረድ ፤

ተማሪው የግዕዝን ስልት በሚገባ ለማወቅ ቃላት ማጥናት ስላለበት ነጠላውን ግሥና ኀብር ቃላትን ደረጃ በደረጃ እንዲሁም የፊደሎችን ተራ በመጠበቅ ያጠናል ። የእርሱም መንገድ እንደሚከተለው ያለ ው ።

### ሀ/ የነጠላ ግሥ መንገድ ፤

| | |
|---|---|
| ሎሀ | ጻፈ |
| ለሀሀ | ቀዳ |
| ላሀልሀ | ራሰ |
| ለምሀ | ለማ |
| ለስሐ | አልጫ ሆነ |
| ለቅሐ | አበደረ |
| ለብሐ | ሠራ |
| ለትሐ | ተጐነጨ |
| ለጥሐ | ገበረ |



www.ethiopianorthodox.org

ነጠላው ግሥ በዚህ መልክ ከሀ — ፈ ድረስ ይሔዳል ፤ ለዚህም ዓይነት አወራረድ ደግሞ ነባር አለው ፤ እርሱውም እንደሚከተለው ነው ።

ለ/ የነባር መንገድ ፤

| | |
|---|---|
| ሮሐ | የአገር ስም |
| በሀ | እንዴት ዋልህ |
| ከሐ | ወዲያ ከዚያ ወዲያ |
| ለሊሁ | እርሱ ቅሉ |
| ምስሌሁ | ከርሱ ጋር |
| ስማዚያሁ | ስሚዛ |

እንዲህ እያለ በዝርዝር የነጠላውን ግሥና ተራ ቅደም ተከተል ከነባሩ ጋር ተማሪው ጠንቅቆ ያጠናል ። ይኸንም ዓይነት ጥናት ከሀ — ፈ ድረስ ይሔደዋል ። ተማሪው ግሡን ከነነባሩ በዚህ መልክ ከአጠናው በኋላ ቃላትን ለማያያዝ አረፍተ ነገርን ለመሥራት ይጀምራል ። ግዕዙን ከነመልኩ ለማጥናት ሲፈለግ ግን ዕርባ ግሥ ወይም ድርብ አወራረድ የተባለውን ያጠናል ፤

## ፪ኛ አጭር አረፍተ ነገር መሥራት ።

ተማሪው ቃላት ብቻ ማጥናት ጠቃሚው ስላይደለ ያጠናቸውን ቃላት በአጭር አረፍተ ነገር እንዲያውላቸው ይገደዳል ። ለምሳሌ «በልዓ ኀብስተ» እን ጀራን በላ ፤ «ሰትየ ማየ» ውኃን ጠጣ ፤ «ተንሥአ እምንዋሙ» ከእንቅልፉ ተነሣ የሚልና በዚህ መልክ የሚሔድ ነው ። ይኸንም በሚማሩበት ጊዜ ሊጠነቀቁ የሚ ገባቸው ነገሮች እንድም ሊርቋቸው የሚገባቸው ጸያፎች ይገኛሉ ። እነርሱም የሚ ከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ አንድና ብዙ
፪ኛ/ ገቢርና ተገብሮ
፫ኛ/ ሩቅና ቅርብ
፬ኛ/ ወንድና ሴት
፭ኛ/ ነባቢና ኢነባቢ
፮ኛ/ ቦታና ባለቤት
፯ኛ/ ስምና ግብር
፰ኛ/ ከአንቀጽ ወዲያ ቅጽል
፱ኛ/ ፍርቅ
፲ኛ/ ዝርው
፲፩ኛ/ ሳቢና ተሳቢ
፲፪ኛ/ የደቂቅ ድፋት

www.ethiopianorthodox.org

፲፫ኛ/ ያለ ወገኑ ተናባቢ

፲፬ኛ/ ሳድስ የሚያናግረውን ግዕዝ ፤ ግዕዝ የሚያናግረውን ሳድስ ማናገር

፲፭ኛ/ ክፋና ደግ

፲፮ኛ/ ልጅና የልጅ ልጅ

ይኸንም የመሳሰሉ ብዙዎች ይገኛሉ ፤ ይሁን እንጂ ምንም ጀማሪ ተማሪም ቢሆን ከነዚህ ጸያፎች ብዙዎችን ጠንቅቆና ለይቶ ማወቅ ግዴታው ነበር ።

## ፫ኛ የአረፍተ ነገሮች ሞያ ።

ከላይ የገለጥናቸው አረፍተ ነገሮች በስልት በስልታቸው ለመግባት ምልክት ይሆን ዘንድ እያንዳንዱ ቃል መተንተንና ሞያ መስጠት በግድ ያስፈልጋል፤ እንደዚህም ያለው ጥናት ሞያ መስጠት ይባላል ። በአንድ አረፍተ ነገር ውስጥ ሞያ ሲሰጥ መላው እንኳን ባይሆን ከሞላ ጐደል ከዚህ በታች የሚከተሉት ሞያዎች መገኘት አለባቸው ።

፩ኛ/ ባለቤት

፪ኛ/ አንቀጽ (ማሠሪያ)

፫ኛ/ ሳቢ

፬ኛ/ ሰሚ ባለቤት

፭ኛ/ ቅጽል

፮ኛ/ ዘርፍ

፯ኛ/ ዘርፍ ደፊ

፰ኛ/ ቃለ አጋኖ

፱ኛ/ አንቀጽ አጐላማሽ

፲ኛ/ በቁም ቀሪ የተባሉትና እነዚህን የመሳሰሉ ናቸው ።

## ፬ኛ ድርብ ግሥ ።

ድርብ ግሥ የሚባለው በዝርዝር የሚረባው ግሥ ነው ፤ ይሁን እንጂ ግሥ በመሠረቱ በ፱ ሠራዊት ተዘርዝሮ በ፰ አርእስት ተከፍሎ በ፯ አዕማድ ተጠቃሎ በዐቢይ አንቀጽ ፥ በንዑስ አንቀጽ ፥ በደቂቅ ፥ በባዕድ ቅጽል ፥ በመራሕያን ፥ በዝርዝር ቅጽል እየገባ በምልዓት የሚገሠሥ ዕርባታ አለው ፤ በዚህ መልክ የሚሔድ ይኸንም የመሰለ ግሥን የሚመለከተው ትምህርት ዕርባታ ግሥ ይባላል ። ዕርባ ግሥ የተባሉት ደግሞ በጠቅላላው በ፬ ክፍል ይከፈላሉ ፤ እነርሱም ስምንቱ አርእስት ከሠራዊቶቻቸው ጋር ፩ ወገን በመሆን ፩ ይባላሉ ። ፪ኛ/ አዕማድ የተባሉት አንድ ወገን ፩ ይባላሉ ። ፫ኛ/ የአእመረ ጓዝና የይቤ ዕርባታ አንድ ወገን ፬ኛ/ ተናባቢ ግሥና ምሳሌ ግሥ የተባሉት አንድ ወገን ሁነው ይቆጠራሉ ፤ እነ

www.ethiopianorthodox.org

ዚህም ሲደመሩ ፬ ይሆናሉ ። እንደ ገና እነዚህም ፬ቱ በ፲፫ ታላላቅ ክፍል ይከ ፈላሉ ፤ እነርሱም ፤

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ/ | ቀተለ | ፰ኛ/ | ቆመ |
| ፪ኛ/ | ቀደሰ | ፱ኛ/ | አዕማድ |
| ፫ኛ/ | ገብረ | ፲ኛ/ | የአእመረ ዕርባታ ጓዝ |
| ፬ኛ/ | አእመረ | ፲፩ኛ/ | የይቤ ዕርባታ |
| ፭ኛ/ | ባረከ | ፲፪ኛ/ | ተናባቢ ግሥ |
| ፮ኛ/ | ሤመ | ፲፫ኛ/ | ምሳሌ ግሥ ናቸው ። |
| ፯ኛ/ | ብህለ | | |

ምንም ብዙ ሕገ ወጥ ዕርባታዎች በግዕዛችን ቢገኙም ደንበኞቹ ግሦች እነዚህን ተከትለው የሚሔዱ ስለሆነ የጠበቀም የጠበቀውን መንገድ ፥ የላላውም የላላውን ግሥ እየተከተሉ ይረባሉ ፤ እነዚህንም ይመስላሉ ። ለነዚህም መነሻና መድረሻ የተወሰነ ልክና መልክ አላቸው ፤ መነሻቸውንና መድረሻቸውን የሚያ መለክተው አንቀጽ « መራሁት » ተብሎ ይጠራል ፤ ትርጒሙም መፍቻ እንድም መክፈቻ ማለት ነው ። መራሁት የሚባሉ አንቀጾችም ፥ ግሦች የሚነሱባቸው ፭ አናቅጽ ናቸው ፤ እነርሱም ግዕዝ ፥ ራብዕ ፥ ሐምስ ፥ ሳድስ ሳብዕ ናቸው ። የሁሉም መድረሻ ግን አንድ ብቻ ነው ፤ እርሱውም ግዕዝ ነው ። በጠቅላላም መራሁት የተባሉበት የግሥ መነሻ በር ከፋቾችም ስለሆኑ ነው ። እንግዲህ በመላ የግዕዝ ግሦች በየቦታቸው በብዙ መልክ ይረባሉ ፥ ይወርዳሉ ፤ አንዱ እስከ ፬፻ ዘር ፡ ን ድም ዘርፍ ያገኛል ፤ ለምሳሌ አእመረን ተመልከት ። ይኸንም የሚከተለው የግ ዕዝ መንገድ ሁሉ ዕርባታ ወይም አወራረድ ይባላል ። ይኸም ዓይነት የአገባብ መንገድ በየቅኔ ቤቱ ፈጽሞ የተለያየ ነው ፤ ሆኖም አማካዩን መንገድ ተከትሎ የተዘጋጀ ነው ።

ምንም የአገባቡ ስልት በዚህ መልክ ቢሆን በትምህርት ቤት የሚገኙት ተማሪዎች ሁሉ በልዩ ልዩ ክፍል የመማር ዕድል የሌላቸው ነበሩ ፤ ማለት ቅኔም ቢዘረፍ ግሥም ቢወርድ በአንድ ላይ ስለሚያጠኑ ጥሬና ብስል ይሆንባቸው ነበር፤ ይሁን እንጂ ጀማሪው ተማሪም የግሡን አወራረድ በዚህ መልክ ማጥናት ስለአ ለበት ከሀ — ፈ ያለውን የግሥ አወራረድ ፤ የዘር አወጣጥ ፤ የአረፍተ ነገር ጥናት ተስፋ ሳይቆርጥ በዚህ መልክ ለማጥናት ይቀጥላል ፤ ስለዚህ ተማሪው በዚህ ደረጃ ድርብ ግሥ የተባለውን በደንብ ያጠናል ። ይኸም ሲሆን ግሡ በዓመት ውስጥ ከ፭ እስከ ፯ ጊዜ ያህል ስለሚወርድለት ተማሪው ተቀኝቶ ከመውጣቱ በፊት የየዕ ለቱን እየተከታተለ በደንብ ስለሚያጠና ቃላት ጠግቦ ግዕዝ ዐውቆ ይወጣልና ። የግሡም አወራረድ እንደቤቱ ይሁን እንጂ የግሥ ቤቶች ፯ ናቸው ፤ ሌላ ሕገ ወጥ ግሥም ቢኖር በነርሱ አወራረድ ይሄዳል ። ለምሳሌም ያህል ይኸን አወ ራረድ እንመልከት ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፳ኛ የአእመረ አወራረድ ።

| | |
|---|---|
| አእመረ | አወቀ |
| የአምር | ያውቃል |
| ያእምር | ያውቅ ዘንድ |
| ያእምር | ይወቅ |
| አእምሮ | ማወቅ |
| አእምሮት | » |
| አእማሪ | ያወቀ |
| አእማርያን | ያወቁ |
| አእማሪት | ያወቀች |
| አእማርያት | ያወቁ |
| እሙር | የታወቀ |
| አእማሪ | የሚያውቅ አዋቂ |
| ማእምር | አዋቂ |
| አእምሮ | እውቀት |

በዚህ መልክ እያንዳንዱን ግሥ ያወርዳል ፣ ወይም ያጠናል ፤ ይሁን እንጂ ከዚህም በበለጠ ዝርዝር ዕርባ ግሥ የተባለውን እንደሚከተለው ያወርዳል ፤ አን ድም ያጠናል ።

<u>፩ኛ/ የራቀው ወንድ ሲያውቅ ፤</u>

| | |
|---|---|
| አእመረ | አወቀ |
| የአምር | ያውቃል |
| ያእምር | ያውቅ ዘንድ |
| ያእምር | ይወቅ |

<u>፪ኛ/ የቅርብ ወንድ ሲያውቅ ፤</u>

| | |
|---|---|
| አእመርከ | አወቅህ |
| ተአምር | ታውቃለህ |
| ታእምር | ታውቅ ዘንድ |
| አእምር | እወቅ |

<u>፫ኛ/ የሩቆች ወንዶች ሲያውቁ ፤</u>

| | |
|---|---|
| አእመሩ | አወቁ |
| የአምሩ | ያውቃሉ |
| ያእምሩ | ያውቁ ዘንድ |
| ያእምሩ | ይወቁ |

www.ethiopianorthodox.org

## ፬ኛ/ የቅርቦች ወንዶች ሲያውቁ ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክሙ | አወቃችሁ |
| ተአምሩ | ታውቃላችሁ |
| ታእምሩ | ታውቁ ዘንድ |
| አእምሩ | እወቁ |

## ፭ኛ/ የሩቅ ሴት ስታውቅ ፤

| | |
|---|---|
| አእመረት | አወቀች |
| ተአምር | ታውቃለች |
| ታእምር | ታውቅ ዘንድ |
| ታእምር | ትወቅ |

## ፮ኛ/ የቅርቢቱ ሴት ስታውቅ ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኪ | አወቅሽ |
| ተአምሪ | ታውቂያለሽ |
| ታእምሪ | ታውቂ ዘንድ |
| አእምሪ | እወቂ |

## ፯ኛ/ የሩቆች ሴቶች ሲያውቁ ፤

| | |
|---|---|
| አእመራ | አወቁ |
| የአምራ | ያውቃሉ |
| ያእምራ | ያውቁ ዘንድ |
| ያእምራ | ይወቁ |

## ፰ኛ/ የቅርቦች ሴቶች ሲያውቁ ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክን | አወቃችሁ |
| ተአምራ | ታውቃላችሁ |
| ታእምራ | ታውቁ ዘንድ |
| አእመራ | እወቁ |

## ፱ኛ/ እኔ ያለው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኩ | አወቅሁ |
| አአምር | አውቃለሁ |
| አእምር | አውቅ ዘንድ |
| አእምር | ልወቅ |

www.ethiopianorthodox.org

፲ኛ/ ንሕነ ያለው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርነ | አወቅነ |
| ነአምር | እናውቃለን |
| ናእምር | እናውቅ ዘንድ |
| ናእምር | እንወቅ |

## ንዑስ አንቀጽ ።

ናእምር ሲል ዘንድ፥ እንጅ፥ ል ፥ ሊ ፥ ሊያ ፥ ይሆናል።ይኸም እንደሚከተለው ይሆናል።

| | |
|---|---|
| እንዲያውቅ | እንዲያውቁ |
| እንድታውቅ | እንድታውቁ |
| ሊያውቅ | ሊያውቁ |
| ልታውቅ | ልታውቁ እንዲህ እያለ ይረባል ። |

እስከዚህ መደብ ይባላል ። ከዚህ ወዲህ ያለው ግን ዝርዝር ነው ፤ ስሙም «የዋህት» ዕርባታ ይሉታል ።

## የአንቀጽ ዝርዝር ።

| | |
|---|---|
| ሳብዕ | የሩቅ ወንድ ዝርዝር |
| ራብዕ | የሩቅ ሴት |
| ነ | አነ ያለው ነው ። |

ሀ/ ፩/ የሩቅ ወንድ

የሩቁን ወንድ በዝርዝር ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሮ | አወቀው አወቀለት አወቀበት ሁሉም በዚህ መልክ ይሔዳል እንዲህም እያለ ይረባል ። |
| የአምሮ | ያውቀዋል |
| ያእምሮ | ያውቀው ዘንድ |
| ያእምሮ | ይወቀው |

፪ኛ/ ቅርቡን ወንድ ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረከ | አወቀህ |
| የአምረከ | ያውቅኻል |
| ያእምርከ | ያውቅህ ዘንድ |
| ያእምርከ | ይወቅህ |

፫ኛ/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሮሙ | አወቃቸው |

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| የአምሮሙ | ያውቃቸዋል |
| ያእምሮሙ | ያውቃቸው ዘንድ |
| ያእምሮሙ | ይወቃቸው |

፬ኛ/ ቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረክሙ | አወቃችሁ |
| የአምረክሙ | ያውቃችኋል |
| ያእምርክሙ | ያውቃችሁ ዘንድ |
| ያእምርክሙ | ይወቃችሁ |

፭ኛ/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራ | አወቃት |
| የአምራ | ያውቃታል |
| ያእምራ | ያውቃት ዘንድ |
| ያእምራ | ይወቃት |

፮ኛ/ ቅርቢቱን ሴት ሲያውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመረኪ | አወቀሽ |
| የአምረኪ | ያውቅሻል |
| ያእምርኪ | ያውቅሽ ዘንድ |
| ያእምርኪ | ይወቅሽ |

፯ኛ/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሮን | አወቃቸው |
| የአምሮን | ያውቃቸዋል |
| ያእምሮን | ያውቃቸው ዘንድ |
| ያእምሮን | ይወቃቸው |

፰ኛ/ የቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረክን | አወቃችሁ |
| የአምረክን | ያውቃችኋል |
| ያእምርክን | ያውቃችሁ ዘንድ |
| ያእምርክን | ይወቃችሁ |

፱ኛ/ እኔ የሚለውን ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረኒ | አወቀኝ |
| የአምረኒ | ያውቀኛል |

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| ያእምረኒ | ያውቀኝ ዘንድ |
| ያእምረኒ | ይወቀኝ |

፲ኛ/ ንሕነ የሚሉትን ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረነ | አወቀን |
| የአምረነ | ያውቀናል |
| ያእምረነ | ያውቀን ዘንድ |
| ያእምረነ | ይወቀን |

ለ/ ፩/ ቅርቡ ወንድ ሩቁን ወንድ ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኮ | አወቅኸው |
| ተአምሮ | ታውቀዋለህ |
| ታእምሮ | ታውቀው ዘንድ |
| አእምሮ | እወቀው |

፪ኛ/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኮሙ | አወቅኻቸው |
| ተአምሮሙ | ታውቃቸዋለህ |
| ታእምሮሙ | ታውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮሙ | እወቃቸው |

፫ኛ/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርካ | አወቅኻት |
| ተአምራ | ታውቃታለህ |
| ታእምራ | ታውቃት ዘንድ |
| አእምራ | እወቃት |

፬ኛ/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኮን | አወቅኻቸው |
| ተአምሮን | ታውቃቸዋለህ |
| ታእምሮን | ታውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮን | እወቃቸው |

፭ኛ/ አነ የሚለውን ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርከኒ | አወቅኸኝ |
| ተአምረኒ | ታውቀኛለህ |
| ታእምረኒ | ታውቀኝ ዘንድ |
| አእምረኒ | እወቀኝ |

www.ethiopianorthodox.org

ንሕነ የሚሉትን ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርከነ | አወቅኸን |
| ተአምረነ | ታውቀናለህ |
| ታእምረነ | ታውቀን ዘንድ |
| አእምረነ | እወቀን |

ሐ/ ፩/ ብዙዎች ሩቆች ወንዶች ሩቁን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርዎ | አወቁት |
| የአምርዎ | ያውቁታል ፤ |
| ያእምርዎ | ያውቁት ዘንድ |
| ያእምርዎ | ይወቁት |

፪/ ቅርቡን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩከ | አወቁህ |
| የአምሩከ | ያውቁኻል |
| ያእምሩከ | ያውቁህ ዘንድ |
| ያእምሩከ | ይወቁህ |

፫/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርዎሙ | አወቋቸው |
| የአምርዎሙ | ያውቋቸዋል |
| ያእምርዎሙ | ያውቋቸው ዘንድ |
| ያእምርዎሙ | ይወቋቸው |

፬/ ቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩክሙ | አወቋችሁ |
| የአምሩክሙ | ያውቋችኋል |
| ያእምሩክሙ | ያውቋችሁ ዘንድ |
| ያእምሩክሙ | ይወቋችሁ |

፭/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርዋ | አወቋት |
| የአምርዋ | ያውቋታል |
| ያእምርዋ | ያውቋት ዘንድ |
| ያእምርዋ | ይወቋት |

www.ethiopianorthodox.org

፮/ ቅርቢቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩኪ | አወቁሽ |
| የአምሩኪ | ያውቁሻል |
| ያእምሩኪ | ያውቁሽ ዘንድ |
| ያእምሩኪ | ይወቁሽ |

፯/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርዎን | አወቋቸው |
| የአምርዎን | ያውቋቸዋል |
| ያእምርዎን | ያውቋቸው ዘንድ |
| ያእምርዎን | ይወቋቸው |

፰/ ቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩክን | አወቋችሁ |
| የአምሩክን | ያውቋችኋል |
| ያእምሩክን | ያውቋችሁ ዘንድ |
| ያእምሩክን | ይወቋችሁ |

፱/ አነ ያለውን ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩኒ | አወቁኝ |
| የአምሩኒ | ያውቁኛል |
| ያእምሩኒ | ያውቁኝ ዘንድ |
| ያእምሩኒ | ይወቁኝ |

ንሕነ ያሉትን ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመሩነ | አወቁነ |
| የአምሩነ | ያውቁናል |
| ያእምሩነ | ያውቁን ዘንድ |
| ያእምሩነ | ይወቁን |

መ/ ፩/ ቅርቦች ወንዶች ሩቁን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክምዎ | አወቃችሁት |
| ተአምርዎ | ታውቁታላችሁ |
| ታእምርዎ | ታውቁት ዘንድ |
| አእምርዎ | እወቁት |

www.ethiopianorthodox.org

፪/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክምዎሙ | አወቃችኋቸው |
| ተአምርዎሙ | ታውቋቸዋላችሁ |
| ታእምርዎሙ | ታውቋቸው ዘንድ |
| አእምርዎሙ | እወቋቸው |

፫/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክምዋ | አወቃችኋት |
| ተአምርዋ | ታውቋታላችሁ |
| ታእምርዋ | ታውቋት ዘንድ |
| አእምርዋ | እወቋት |

፬/ ሩቆችን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክመዎን | አወቃችኋቸው |
| ተአምርዎን | ታውቋቸዋላችሁ |
| ታእምርዎን | ታውቋቸው ዘንድ |
| አእምርዎን | እወቋቸው |

እኔ የሚለውን ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክሙኒ | አወቃችሁኝ |
| ተአምሩኒ | ታውቁኛላችሁ |
| ታእምሩኒ | ታውቁኝ ዘንድ |
| አእምሩኒ | እወቁኝ |

ንሕነ የሚሉትን ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክሙነ | አወቃችሁን |
| ተአምሩነ | ታውቁናላችሁ |
| ታእምሩነ | ታውቁን ዘንድ |
| አእምሩነ | እወቁን |

ሠ/ ፩/ ሩቂቱ ሴት ሩቁን ወንድ ስታውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረቶ | አወቀችው |
| ተአምሮ | ታውቀዋለት |
| ታእምሮ | ታውቀው ዘንድ |
| ታእምሮ | ትወቀው |

www.ethiopianorthodox.org

## ፪/ ቅርቡን ወንድ ስታውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተከ | አወቀችህ |
| ተአምረከ | ታውቅህ አለች |
| ታእምርከ | ታውቅህ ዘንድ |
| ታእምርከ | ትወቅህ |

## ፫/ ሩቆቹን ወንዶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረቶሙ | አወቀቻቸው |
| ተአምሮሙ | ታውቃቸዋለች |
| ታእምሮሙ | ታውቃቸው ዘንድ |
| ታእምሮሙ | ትወቃቸው |

## ፬/ ቅርቦቹን ወንዶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተክሙ | አወቀቻችሁ |
| ተአምረክሙ | ታውቃችኋለች |
| ታእምርክሙ | ታውቃችሁ ዘንድ |
| ታእምርክሙ | ትወቃችሁ |

## ፭/ ሩቂቱን ሴት ስታውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመረታ | አወቀቻት |
| ተአምራ | ታውቃታለች |
| ታእምራ | ታውቃት ዘንድ |
| ታእምራ | ትወቃት |

## ፮/ ቅርቢቱን ሴት ስታውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተኪ | አወቀችሽ |
| ተአምረኪ | ታውቅሻለች |
| ታእምርኪ | ታውቅሽ ዘንድ |
| ታእምርኪ | ትወቅሽ |

## ፯/ ሩቆቹን ሴቶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረቶን | አወቀቻቸው |
| ተአምሮን | ታውቃቸዋለች |
| ታእምሮን | ታውቃቸው ዘንድ |
| ታእምሮን | ትወቃቸው |

www.ethiopianorthodox.org

፰/ ቅርቦቹን ሴቶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተክን | አወቀቻችሁ |
| ተአምረክን | ታውቃችኋለች |
| ታእምርክን | ታውቃችሁ ዘንድ |
| ታእምርክን | ትወቃችሁ |

አነ የሚለውን ስታውቅ ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተኒ | አወቀችኝ |
| ተአምረኒ | ታውቀኛለች |
| ታእምረኒ | ታውቀኝ ዘንድ |
| ታእምረኒ | ትወቀኝ |

ንሕነ የሚሉትን ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመረተነ | አወቀችነ |
| ተአምረነ | ታውቀናለች |
| ታእምረነ | ታውቀን ዘንድ |
| ታእምረነ | ትወቀነ |

ረ/ ፩/ ቅርቢቱ ሴት ሩቁን ወንድ ስታውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮ | አወቅሽው |
| ተአምሪዮ | ታውቂዋለሽ |
| ታእምሪዮ | ታውቂው ዘንድ |
| አእምሪዮ | እወቂው |

፪/ ሩቆቹን ወንዶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮሙ | አወቅሻቸው |
| ተአምሪዮሙ | ታውቂያቸዋለሽ |
| ታእምሪዮሙ | ታውቂያቸው ዘንድ |
| አእምሪዮሙ | እወቂያቸው |

፫/ ሩቂቱን ሴት ስታውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኪያ | አወቅሻት |
| ተአምሪያ | ታውቂያታለሽ |
| ታእምሪያ | ታውቂያት ዘንድ |
| አእምሪያ | እወቂያት ። |

www.ethiopianorthodox.org

፬/ ሩቆቹን ሴቶች ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኪዮን | አወቅኻቸው |
| ተአምሪዮን | ታውቂያቸዋለሽ |
| ታእምሪዮን | ታውቂያቸው ዘንድ |
| አእምሪዮን | እወቂያቸው |

፭/ አነ የሚለውን ስታውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክኒ | አወቅሺኝ |
| ተአምርኒ | ታውቂኛለሽ |
| ታእምርኒ | ታውቂኝ ዘንድ |
| አእምርኒ | እወቂኝ |

ንሕነ የሚሉትን ስታውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክነ | አወቅሽን |
| ተአምርነ | ታውቂናለሽ |
| ታእምርነ | ታውቂን ዘንድ |
| አእምርነ | እወቂን |

ሰ/ ፩/ ሩቆች ሴቶች ሩቁን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራሁ | አወቁት |
| የአምራሁ | ያውቁታል |
| ያእምራሁ | ያውቁት ዘንድ |
| ያእምራሁ | ይወቁት |

፪/ ቅርቡን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራከ | አወቁህ |
| የአምራከ | ያውቁኻል |
| ያእምራከ | ያውቁህ ዘንድ |
| ያእምራከ | ይወቁህ |

፫/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመራሆሙ | አወቋቸው |
| የአምራሆሙ | ያውቋቸዋል |
| ያእምራሆሙ | ያውቋቸው ዘንድ |
| ያእምራሆሙ | ይወቋቸው |

www.ethiopianorthodox.org

፬/ ቅርቦችን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመራክሙ | አወቋችሁ |
| የአምራክሙ | ያውቋችኋል |
| ያእምራክሙ | ያውቋችሁ ዘንድ |
| ያእምራክሙ | ይወቋችሁ |

፭/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራሃ | አወቋት |
| የአምራሃ | ያውቋታል |
| ያእምራሃ | ያውቋት ዘንድ |
| ያእምራሃ | ይወቋት |

፮/ ቅርቢቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራኪ | አወቁሽ |
| የአምራኪ | ያውቁሻል |
| ያእምራኪ | ያውቁሽ ዘንድ |
| ያእምራኪ | ይወቁሽ |

፯/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመራሆን | አወቋቸው |
| የአምራሆን | ያውቋቸዋል |
| ያእምራሆን | ያውቋቸው ዘንድ |
| ያእምራሆን | ይወቋቸው |

፰/ ቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመራክን | አወቋችሁ |
| የአምራክን | ያውቋችኋል |
| ያእምራክን | ያውቋችሁ ዘንድ |
| ያእምራክን | ይወቋችሁ |

እኔ የሚለውን ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመራኒ | አወቁኝ |
| የአምራኒ | ያውቁኛል |
| ያእምራኒ | ያውቁኝ ዘንድ |
| ያእምራኒ | ይወቁኝ |

www.ethiopianorthodox.org

ንሕነ የሚሉትን ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመራነ | አወቁን |
| የአምራነ | ያውቁናል |
| ያእምራነ | ያውቁን ዘንድ |
| ያእምራነ | ይወቁን |

፩/ ቅርቦች ሴቶች ሩቁን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርካሁ | አወቃችሁት |
| ተአምራሁ | ታውቁታላችሁ |
| ታእምራሁ | ታውቁት ዘንድ |
| አእምራሁ | እወቁት |

፪/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክናሆሙ | አወቃችኋቸው |
| ተአምራሆሙ | ታውቋቸዋላችሁ |
| ታእምራሆሙ | ታውቋቸው ዘንድ |
| አእምራሆሙ | እወቋቸው |

፫/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክናሃ | አወቃችኋት |
| ተአምራሃ | ታውቋታላችሁ |
| ታእምራሃ | ታውቋት ዘንድ |
| አእምራሃ | እወቋት |

፬/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክናሆን | አወቃችኋቸው |
| ተአምራሆን | ታውቋቸዋላችሁ |
| ታእምራሆን | ታውቋቸው ዘንድ |
| አእምራሆን | እወቋቸው |

አነ የሚሉትን ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክናኒ | አወቃችሁኝ |
| ተአምራኒ | ታውቁኛላችሁ |
| ታእምራኒ | ታውቁኝ ዘንድ |
| አእምራኒ | እወቁኝ |

www.ethiopianorthodox.org

ንሕነ የሚሉትን ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርከናነ | አወቃችሁን |
| ተአምራነ | ታውቁናላችሁ |
| ታእምራነ | ታውቁን ዘንድ |
| አእምራነ | እወቁን |

በ/ ፩/ አነ የሚለው የሩቁን ወንድ ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርከዎ | አወቅሁት |
| አአምሮ | አውቀዋለሁ |
| አእምሮ | አውቀው ዘንድ |
| አእምሮ | ልወቀው |

፪/ ቅርቡን ወንድ ሲያውቀው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኩከ | አወቅሁህ |
| አአምረከ | አውቅሃለሁ |
| አእምርከ | አውቅህ ዘንድ |
| አእምርከ | ልወቅህ |

፫/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርከዎሙ | አወቅኋቸው |
| አአምሮሙ | አውቃቸዋለሁ |
| አእምሮሙ | አውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮሙ | ልወቃቸው |

፬/ ቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኩክሙ | አወቅኋችሁ |
| አአምረክሙ | አውቃችኋለሁ |
| አእምርክሙ | አውቃችሁ ዘንድ |
| አእምርክሙ | ልወቃችሁ |

፭/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክዋ | አወቅኋት |
| አአምራ | አውቃታለሁ |
| አእምራ | አውቃት ዘንድ |
| አእምራ | ልወቃት |

www.ethiopianorthodox.org

### ፮/ ቅርቢቱን ሴት ሲያውቃት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኩኪ | አወቅሁሽ |
| አአምረኪ | አውቅሻለሁ |
| አእምርኪ | አውቅሽ ዘንድ |
| አእምርኪ | ልወቅሽ |

### ፯/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርክዎን | አወቅኋቸው |
| አአምሮን | አውቃቸዋለሁ |
| አእምሮን | አውቃቸው ዘንድ |
| አእምሮን | ልወቃቸው |

### ፰/ ቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቃቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርኩክን | አወቅኋችሁ |
| አእምረክን | አውቃችኋለሁ |
| አእመርክን | አውቃችሁ ዘንድ |
| አእመርክን | ልወቃችሁ |

### ተ/ ፩/ ንሕነ የሚሉት ሩቁን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናሁ | አወቅነው |
| ነአምሮ | እናውቀዋለን |
| ናእምሮ | እናውቀው ዘንድ |
| ናእምሮ | እንወቀው |

### ፪/ ቅርቡን ወንድ ሲያውቁት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናከ | አወቅንህ |
| ነአምረከ | እናውቅሃለን |
| ናእምርከ | እናውቅህ ዘንድ |
| ናእምርከ | እንወቅህ |

### ፫/ ሩቆቹን ወንዶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናሆሙ | አወቅናቸው |
| ነአምሮሙ | እናውቃቸዋለን |
| ናእምሮሙ | እናውቃቸው ዘንድ |
| ናእምሮሙ | እንወቃቸው |

www.ethiopianorthodox.org

፩/ ቅርቦቹን ወንዶች ሲያውቋቸው

| | |
|---|---|
| አእመርናክሙ | አወቅናችሁ |
| ነአምረክሙ | እናውቃችኋለን |
| ናእምርክሙ | እናውቃችሁ ዘንድ |
| ናእምርክሙ | እንወቃችሁ |

፪/ ሩቂቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናሃ | አወቅናት |
| ነአምራ | እናውቃታለን |
| ናእምራ | እናውቃት ዘንድ |
| ናእምራ | እንወቃት |

፫/ ቅርቢቱን ሴት ሲያውቋት ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናኪ | አወቅነሽ |
| ነአምረኪ | እናውቅሻለን |
| ናእምርኪ | እናውቅሽ ዘንድ |
| ናእምርኪ | እንወቅሽ |

፬/ ሩቆቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናሆን | አወቅናቸው |
| ነአምሮን | እናውቃቸዋለን |
| ናእምሮን | እናውቃቸው ዘንድ |
| ናእምሮን | እንወቃቸው |

፭/ ቅርቦቹን ሴቶች ሲያውቋቸው ፤

| | |
|---|---|
| አእመርናክን | አወቅናችሁ |
| ነአምረክን | እናውቃችኋለን |
| ናእምርክን | እናውቃችሁ ዘንድ |
| ናእምርክን | እንወቃችሁ |

ከመጀመሪያ ጀምሮ እስከዚህ ድረስ በሰማንያ ሠራዊት ይዘረዘራል ።

| | |
|---|---|
| አእምሮ አእምሮት | ማወቅ |
| አእምሮቱ | ማወቁ |
| አእምሮትከ | ማወቅህ |
| አእምሮቶሙ | ማወቃቸው |

www.ethiopianorthodox.org

| | |
|---|---|
| አእምሮትክሙ | ማወቃችሁ |
| አእምሮታ | ማወቋ |
| አእምሮትኪ | ማወቅሽ |
| አእምሮቶን | ማወቃቸው |
| አእምሮትክን | ማወቃችሁ |
| አእምሮትየ | ማወቄ |
| አእምሮትነ | ማወቃችን |

## ቦ ዝ ።

| | |
|---|---|
| አእሚሮ | አውቆ |
| አእሚረከ | አውቀህ |
| አእሚሮሙ | አውቀው |
| አእሚረክሙ | አውቃችሁ |
| አእሚራ | አውቃ |
| አእሚረኪ | አውቀሽ |
| አእሚሮን | አውቀው |
| አእሚረክን | አውቃችሁ |
| አእሚርየ | አውቄ |
| አእሚረነ | አውቀን |

## ቅጽል ።

አእማሪ — ያወቀ ፣ የሚያውቅ ፣ ያወቅህ ፣ የምታውቅ
ያወቅሁ ፣ የማውቅ ።

አእማርያን — ያወቁ ፣ የሚያውቁ ፣ ያወቃችሁ ፣ የምታውቁ ።

አእማሪት — ያወቀች ፣ የምታውቅ ፣ ያወቅሽ ፣ የምታውቂ ።

**የብዙ ሴቶች**

አእማርያት — ያወቁ ፣ የሚያውቁ ፣ ያወቃችሁ ፣ የምታውቁ ።

**ሳድስ ቅጽል**

እሙር — የታወቀ ፣ የሚታወቅ ፣ የታወቅህ ፣ የምትታወቅ ፣ የታወ
ቅሁ ፣ የምታውቅ ።

እሙራን — የታወቁ ፣ የሚታወቁ ፣ የታወቃችሁ ፣ የምትታወቁ ።

እምርት — የታወቀች ፣ የምታውቅ ፣ የታወቅሽ ፣ የምትታወቂ ።

www.ethiopianorthodox.org

<u>የብዙ ሴቶች</u>

| | |
|---|---|
| እሙራት | የታወቁ ፥ የሚታወቁ ፥ የታወቃችሁ ፥ የምትታወቁ ፤ |

<u>መስም ቅጽል</u>

| | |
|---|---|
| ምእማር | ማወቂያ ፥ ማሳወቂያ ፤ |
| ምስትእማር | መተዋወቂያ |

<u>ሳቢ ዘር</u>

| | |
|---|---|
| እምረት | ማወቅ |

የአእመረ ደንበኛ ዕርባታ በዚህ ዓይነት ሲሔድ ከ፬፻—፭፻ አረባብ አለው ፤ አንዳንድ መምህራን ግን ከዚህ በበለጠ ያረቡታል ፤ እያንዳንዱም ግሥ በየቤቱ በየሠራዊቱ በዚህ መልክ ይወርዳል ። የማንኛውም መምህር ዕርባታ ማስተማሪያ ሕግን ተከትሎ የሚሔድና ቀላል መንገድ ሆኖ አንድም መስሎ የተገኘው አእመረ ስለሆነ ጀማሪም ቢሆን ይህንን ለማጥናት መሞከሩ አይቀርም ፤ ተማሪም እርስ በርሱ ሲሰዳደብ ይኸ «አእመረን እንኳን ያላረባ» ይለዋል ፤ ፍቹም ግዕዝ የማያውቅ ማለት ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ።

# የግዕዝ ቃላት ቊጥር ።

የግዕዝ ቋንቋ ጥንታዊና ራሱን የቻለ ነው ፤ አንድ ቋንቋ ራሱን ለመቻል በብዙ ሺህ የሚቈጠሩ ቃላቶች የግድ ያስፈልገዋል ። ስለዚህ ግዕዝም የአንድ ሕዝብ ቋንቋ ብዙ ሥራ የተሠራበት ፥ መጻሕፍት የተጻፉበት ስለሆነ ፤ ብዙ ቃላት አሉት ፤ የቃላቱንም መጠን ለማወቅ የያንዳንዱን ቃላት በዚህ መልክ እናሳያለን። እነዚህም ቃላት ከአንድ ግሥ የሚወጡትን ዘርፎችና ቅጽሎች ሳይጨምር ራሱን ግሡንና ነባሩን ብቻ በመቊጠር ነው ። የነዚህም ቃላት አቈጣጠር ተራቸው እንደሚከተለው ነው ።

| | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|
| ሀ | የሀ | ነጠላ | ግሥ | ፭፻፹ | |
| | | | ነባር | ፫፻፷፱ | ፱፻፱ |
| ለ | የለ | ነጠላ | ግሥ | ፭፻፲፫ | |
| | | | ነባር | ፫፻፷፯ | ፰፻፹ |
| መ | የመን | ነጠላ | ግሥ | ፭፻፳፫ | |
| | | | ነባር | ፫፻፹፰ | ፱፻፲፩ |
| ሠ | የሠ | ነጠላ | ግሥ | ፭፻፸፯ | |
| | | | ነባር | ፬፻፸፱ | ፲፻፶፮ |

www.ethiopianorthodox.org

ይኸንም አንቀጹን ከነነባሩ ሲፈቱ ግሡን ሲያወርዱ በዓመት እንደ መም ህሩ ነው እንጂ ከ፭ — ፮ ጊዜ የሚያወርዱ አሉ ። አንዳንዶች በዚሁ ልክ አንዳን ዶች ከዚህ ዝቅ አድርገው በዓመት ያወርዳሉ ።

የግዕዝ ቋንቋችን ሕያውና ብዙ የተሠራበት ስለሆነ ፤ ይኸን ያህል ቃላት ይዞ ይገኛል ። ይኸም ቍጥር አንዳንድ መምህራን እንደሚስማሙበት ነው እንጂ እንደ ጥቂቶቹ ግን ከዚህም ሊበዛ ወይም ሊያንስ ይችላል ፤ ምክንያቱም ቃሉ ግዕዝ ከሆነ ነገሩ ሁሉ ግሥ አለው በማለት ነገሩን ሁሉ ግሥ እንዳለው እየቆ ጠሩ ያወርዱታል ፤ ለምሳሌ ተአበነ ድንጋይ ሆነ ፣ አሶተ እሳት ሆነ በማለት ዕብን እሳት ያለውን የነባር ቃል ሁሉ ግሥ ያወጡለታል ። በዚህም ሁሉ ዘር ሲወጣ በጣም ብዙ የሆነ ቍጥር ይኖረዋልና ። እንዲሁም የሌላውን ሕዝብ ቋንቋ በመቀ ላቀል ወደ ግዕዝ አግብተው ቍጥሩን ያበዙታል ፤ እንዲያውም ነባር ናቸው የሚባ ሉት ከውጪ የተወረሱ ቃላት ናቸው ።

በዚህም የቃላት አወጣጥ ውስጥ ሁለትና ፫ ተመሳሳይ የሆኑ ፊደሎች አልገቡም ፤ ለምሳሌ የሀ ፊደል ፫ ዓይነት ያለው ሲሆን የሚወርደው በመጀመሪ ያው ብቻ እንጂ ሌላው በዚያው እየገባ ይነገራል ፤ ስለዚህ እንዲህም ሲሆን ቍጥሩ በዛ ያለ ነው ።

ግሡን እንዲህ አድርጎ እስኪያጠናው ድረስ ተማሪው ቅኔ መቍጠር ቀርቶ እስከ መዝረፍም ሊደርስ ይችላል ፤ ማለት ሁሉ ግልጥ ሆኖለት አንዱ በአለ ቅኔ የሚሔድበት መንገድ ወለል ብሎ ስለሚታየው ሁለተኛው ሊነጥቀው ይችላል ፤ ለምሳሌ በአማርኛ ቋንቋ አንዱ ግጥም በመግጠም ላይ ሳለ ሌላው የሚሔድበትን ለማወቅ እንደሚችል ሁሉ በግዕዝም የበሰለ ሁሉ እንዲሁ ነው ።

## ምዕራፍ ፫ ።

## ጉ ት ።

ጉት የሚባለው ሥውር ነገር የምሥጢር መፍቻና የአእምሮ መገመቻ ነው ፤ ይሁን እንጅ ጉት የሚባል ስም ከየት እንዴት እንደመጣ አይታወቅም ፤ በሥራ ሲገለጥ ግን ከተራ አረፍተ ነገር የተለየ ሆኖ በጣም ኀብርነት ያለው አስ ተያየትን የያዘ ወይም ሥውር ምሥጢርን ያዘለ አረፍተ ነገር ሁኖ እናገኘዋለን። ግዕዝና አማርኛው ሁለት ዓይነት ፍቺ ያለው የቃል ብቻ ሳይሆን የምሥጢር ኀብርነት ፤ በምሥጢር ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ደግሞ የቃል አስተያየት ያለበት ስለሆነ፤ አንዳንዱን ጉት ተማሪው ቀርቶ መምህራንም የማያውቁትና የማያገኙት ይሆናል። ስለዚህ ቀላል ቀላሉን ጉት ብቻ በመጠኑ ተማሪው ሊረዳው የሚቻለውን ያህል መምህራን ያስተምራሉ ። ጉትም በግጥም ወይም በስድ ንባብ ዓይነት ሊሆን ይች ላል ፤ እንዲሁም አንድ አረፍተ ነገር ወይም ሁለት ቤት ሊሆንም ይችላል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ ጉት በስድ ንባብ ።

ጉት የተባለው የቅኔ መንገድ አንድ ቤት ወይም በልዩ ንባብ ሲገኝ እንደ ሚከተለው ይሆናል ።

፩/ «አዕዱግ ፍኖቶሙ» አህዮች ጐዳ ናቸው ። መንገዳቸው ያለ አስመስሎ ቀንድ የላቸውም ጐዳ ናቸው ማለቱ ነው ።

፪/ « ሀገሮሙ ለሕፃናት » የሕፃናት ሀገራቸው ሲል አገርን ያለ መስሎ ሁ-የምትባለው ፊደል ለሕፃናት ገራቸው ቀናቸው ናት በተሎ ያጠኗታል ማለቱ ነው ።

፫/ «ሀለፈ ሰማዩ» ሰማዩ አለፈ ያለ አስመስሎ ሀ-ፊ ፤ ለተባለው ፊደል ሰማዩ ነው ፤ ሩቅ ነው አለ ።

፬/ «አኮ ዘተምህረ ይከውን መምህረ » እከክ አኮ የተማረ መምህር ይሆናል ። መከራውን የታገሠ ትልቅ ይሆናል ማለቱ ነው ።

፭/ «ሶበ ተሰቅል አምላክ ፒሪልዩ» አምላክ በተሰቀለ ጊዜ ቀን ጠፋ ፤ ፒሪልዩ የተባለው ስም ቀን ጠፋ የተባለ ዛፍ ነው ፤ አምላክ በተሰቀለ ጊዜ ቀን ጠፋ ማለትም ፀሐይ ጨለመ ማለት ነው ።

፮/ «ሰብእ ይድኅን ዕብነ በተራክቦ » ሰው ድንጋይን በማገናኘት ይድናል ፤ ያለ አስመስሎ በተራ ክቦ ድንጋይን ደርድሮ ምሽግ አድርጎ ይድናል አለ ።

፯/ «በክረምት አእደውናሃ» በክረምት አሻገር—ናት ። አሻ መሬት በክረምት ገርናት አለ ።

፰/ « ስመ እፅ ታፈርሆ ለነጋዴ» ነጋዴን የእንጨት ስም ታስፈራዋለች ማለት ቀረጥ ታስፈራዋለች ማለት ነው ።

፱/ «ዘማ ቀነተት ሐቋሃ» ዘማዊት ሴት ወገቧን ታጠቀች ያለ አስመስሎ ዘ-እማ ወገቧን ታጠቀች ቅጥሏ ከወገቧ ላይ ሆነ ማለት ነው ።

፲/ « አዛብ ትበልእ ደርሆ » ዶሮ ጭራ ትበላለች ፤ ማለት ዶሮ አዝመራ የላትም ጭራ ቆፍራ ትበላለች ማለት ነው ።

፲፩/ «ሕፃናት ኖሙ ከመ ደብተራ » ሕፃናት እንደ ደብተራ ተኙ ያለ አስመ ስሎ ከመደቡ ላይ ተራ በተራ ተኙ ማለት ነው ።

፲፪/ «ካህን የኀድር በመቃብር» ካህን ጽሮ ደጉሶ በመቃ ብዕሩ ያድራል ያለ አስመስሎ በመቃብር ይኖራል ምውት ነው ማለት ነው ።

፲፫/ «ቂርቆስ ኮነ ሐጋየ» ቂርቆስ በጋን ሆነ ፤ ማለት ቂርቆስ በጋን ተቀቀለ ማለት ነው ።

፲፬/ «ባሕረ ኢያሪኮ ማይ በኤዎስጣቴዎስ» የኢያሪኮ ባሕር በኤዎስጣቴዎስ ውኃ ያለ መስሎ የኢያሪኮ ባሕር በኤዎስጣቴዎስ ማይ አለ ፤ ማለት መሐላ ማይ ተገዛች ማለቱ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፭/ « ሐወጸ ሰማይ ወምድር እሙንቱ » ጉበኙ ሰማይና ምድር ናቸው ፤ ያለ አስመስሎ ሐ- ወ ጸ እነዚህ እያንዳንዳቸው ሩቅና ሩቅ ናቸው ርቀታቸውም ሰማ ይና ምድር ናቸው ።

፲፮/ «ካህናት በጽድቆሙ» ካህናት በጽድ ስር ቆሙ ማለቱ ነው ።

፲፯/ «ብእሲት መርድእ ፈትለ ወጸብሐ» ሴት ተማሪ ፈትሉንና ወጥን ሲል ስም አስመስሎ ተናገረ እንጅ ተማሪ ብሎ ግሥ አድርጎ መናገሩ ነው ።

፲፰/ «ማዕረረ ኀራሲ በቆለ ጠፍአ» የአራሺ አዝመራ በቅሎ ጠፋ ፤ አዝመራው ከበቀለ በኋላ ጠፋ ወይም የአዝመራው ባለቤት በቅሎ ጠፋ ማለት ነው ።

፲፱/ «ሰሎሜ ወዮሴፍ እምኔሁ በግብፅ» ሰሎሜና ዮሴፍ በግብፅ ከሱ ክርሱ ጋር ነበሩ ፤ ያለ አስመስሎ የሚበሉት የሚጠጡት ስላጡ በግብፅ ከሱ ጠቆሩ አለ ።

፳/ «በቅል ይበልእ ስመ ርእሱ» በቅሎ የራሱን ስም ይበላል ማለት በቅሎው ሲነዳ መጭ ይባላል ፤ መጭ ማለት የርሱ መነጃ ስሙ ነውና ። ምግቡም መጭ የተ ባለ ቅጠል ነውና ።

፳፩/ «እስማኤል ሀብተ ሥጋ ዘተወልደ እምአጋር» የሥጋ ሀብት እስማኤል ከአጋር የተወለደ፤ማለቱ ብዙ ጊዜ ሀብት የሚገኘው በአጋር በወገን ነው ማለት ነው ።

፳፪/ «ብእሲት ነሥአት ሊባኖስ» ሴት ደጋንያዘች ሴት ደጋውን ነፋሻውን መንገድ ያዘች ሔደች ፤ ያለ አስመስሎ መፍተያውን መንደፊያውን ደጋኑን ያዘች አለ ።

፳፫/ «ስመ አፍ ያወርድ ሲኦል» ማማት ወደ ሲኦል ያወርዳል ማማት የተ ባለ ወፍ አለና ።

፳፬/ «ሕፃን ቀሊል አንሥአ ሣእረ» ሕፃኑ ፈደሉን ቀን ለማለት ሣርን አነሣ ።

፳፭/ «አጽነነት ወልድ በመልዕልተ መስቀል ሰሌዳ» ወልድ ት በመስቀል ሰሌዳ ላይ ራሱን አዘነበለ ።

በሌላ መልክ ደግሞ ጉት ሲቀርብ የንባቡ አሰካክ እንደ ጉባኤ ቃና ሆኖ ስልቱ ግን ወይም መንገዱ ጉት ሆኖ ኅብርነት ያለው እንደሁለተኛ ደረጃ ይገኛል ።

## ፪ኛ ጉት በግጥም ።

፩/ ትቤላ በእግር ተከለ ሃይማኖት እጉየ ። ዳዕሙ በክንፍ የዐብየኒ ኪያየ ። ላ ፡ ተከለ ሃይማኖት ወንድሜ ነው አለች ፤ እግሩ ማጠሩን ነው ፤ ነገር ግን በክንፍ ይበል ጠኛል ማለት ላ ሌላ ቅጠል የላትምና ።

፪/ ስተይ አጽንኖተ ክሳድ ወርእስ ። እስመ በላዕሌኬ ተጽሕፈ ስመ ኢየሱስ ክርስቶስ ። ስ ፡ ራስሽን ማዘንበል ተይ ፤ ቀጥተኛ ሁኝ ፤ በአንች ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ስም ተጽፏልና ።

፫/ ይቤሎ ለንጊኖስ ሐራ ሮምያ እጉየ ።
በዓይኑ ዋሕድ እስመ ይመስል ኪያየ ።
ሎ ፡ ለንጊኖስን ወንድሜ ነህ አለው ፤ አንድ ዓይና በመሆኑ እኔን ይመስላልና ።
ለንጊኖስ አንድ ዓይና ነው ፤ ሎም እንዲሁ ፩ ዓይና ነውና ።

www.ethiopianorthodox.org

፬/ ኦ ሕፃን ጸረ ዚአከ ሐንካስ ።
አምጣነ ዓይኖ አውጻእከ በሣእረ ገዳም ንዑስ ።
ሕፃን ሆይ ጠላትህን ሐን ካሳ ካስ ፤ ዓይኑን በሣር አውጥተኸዋልና ማለት ጠንቁለኸዋልና ፤

፭/ ወልድ እንከ ምጽንጋእ ዘወሀበተከ እም ። ሥጋ ወአጽመ እስመ ተፈጸመ ጾም ።

ልጅ ! ሆይ እናትህ የሰጠችህን ሥጋና አጥንት ጋጥ የከብት በረት ጾሙ አልቋልና ።

፮/ ቅድስተ ቅዱሳን ዘኮነት ቤተ ክርስቲያን ቅድስተ ።
ካህናት ሳሙኤል አምጣነ ያፈቅር ዘንተ ።

፯/ ሥጋ ለሞቱ ሕሙመ ፍቅረ ሰብእ እግዚእ ።
ይሁዳ ደዌከ እስመ ውእቱ ጽኑእ ።

የሰው ፍቅር ያሳመመሕ ጌታ ሆይ ሞትን ሥጋ (ፍራ) ደዌህ ይሁዳ ጽኑእ ነውና ። አማርኛ በሠለጠነበት ጊዜ ግን የአማርኛ ጉት ደግሞ ተፈጠረ ፤ ነገር ግን ብዙው ጸያፍን የተከተለ ስለሆነ ለመጥቀስ ስላላስፈለገ ትቼዋለሁ ። ከግዕዝም ቢሆን እንዲሁም በቀልድ መልክ የተዘጋጀው ብዙው ነው ። እርሱንም ማወቁ መልካም ሲሆን የያዝነውን ሥራ ጸያፍነቱ እንዳያቀለው በማለት አልፈነዋል ። ከአማርኛ ውም ውስጥ በመጠኑ እንደሚከተለው እንገልጣለን ።

፩/ ራምኖን በክረምት ምን መሰላ ከረመች ፤ ዶግ በክረምት ምን መሰለች በማለት ጥያቄን ያቀረበ መስሎ ዶግ በክረምት ስለተመቸው እንደ ም ፡ ጉን ጠፍ ዘርጋ ብላ ከረመች ይላል ።

፪/ አንዲት እንጨት አለች ስሟ ቊጥር ምንጣፍ ፤ እርሷን የተረገመ ከሊ ቃውንት ይጣፍ ።

ይኸ ማለት አንድ እንጨት ስሙ ቊጥርም ምንጣፍም የሆነች ሽንት የተባለች እንጨት ነበረች ፤ ምንጣፍ ያለው ነት ነው (ጥ) ሺህ ያለው ደግሞ ቊጥር ነው ።

፫/ በቀን ዓይታ ጆሮ አማራት ፤ ይኸም ማለት በ ፡ የተባለችው ፊደል ቀን ዓይታ እንደርሱ ለመሆን ጆሮ አማራት ማለት ነው ።

በዚህ ጉት በተባለው መንገድ ብዙዎች መምህራን አይጠቀሙበትም ፤ እንዲያውም ተማሪዎች በቀልድ መልክ የሚያጠኑት ሆኖ ይገኛል ። አንዳንዶች ደግሞ ተማሪዎች ዘይቤ ከለዩ ምሥጢር ከአደላደሉ በኋላ የሚያጠኑት እንደሆን ይገመታል ፤ አንዳንዶች ግን ከዚህ እንደጻፍነው ሁሉ ይህንኑ ደረጃ ጠብቀው የቅኔ መንገድ መልመጃ የአፍ መፍቻ አድርገው ያስተምራሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፩ ።

# ቅ ኔ ።

## ፩ኛ የቅኔ ትርጉም ።

የቅኔን ትርጉም ሊቃውንት ሁሉ እንደመሰላቸው የቃሉን መስልነት እየተከተሉ አንድም እየፈለጉ የሆነውንም ያልሆነውንም ትርጉም ሰጥተውት ይገኛሉ ። እንደመሰላቸውም ይተረጉማሉ ለተባለው አስረጅ የሚከተለውን እንመልከት ፤ ቅኔ ማለት «ቈነቈነ» ነቀዘ ፤ ቁንቁን በላው ማለት ነው ብለው ቁንቁን እንጨትን እንደሚ ባለው ቅኔም የሰውን አእምሮ ይበላል በማለት ፈጽሞ ንባቡ ከትርጕሙ ያልተስተካከለ አስተያየት ይሰጣሉ ። ሌሎች ደግሞ የተሻለ ትርጕም ሰጠን መስሏቸው «ተቀንየ» ተገዛ ከአለው ከግዕዙ የወጣ አገዛዝ ማለት እንደሆነ የሚተረጕሙ አሉ ።

እውነተኛ ትርጕም ግን ቅኔ ማለት ግጥም አንድም የምስጋና ግጥም ማለት ነው ። የጥንት ሕዝቦች በተለይም ዕብራውያን ግጥም እየገጠሙ ማለት ቅኔ እየተቀኙ አምላካቸውን አመስግነዋል ፤ ከነዚያም ውስጥ በተለይ ነቢዩ ዳዊት ራሱ ግጥም ገጥሞ ፈጣሪውን ከማመስገኑ በላይ ሌላው ሰው ቅኔ እንዲቀኝ ምስጋናም እንዲያቀርብ ሲያዝ «ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት » ሲል ዘምሮዋል ፤ ሌላውንም አዟል ፤ በኋላም የኢትዮጵያ ሊቅ የዜማና የቅኔ ደራሲ ቅዱስ ያሬድ የተባለው « ተቀነዩ ለእግዚአብሔር በፍርሃት » ሲል ዘምሯል ። ሌላውም እንዲቀኝ አዟል ስለዚህ ቅኔ ማለት ምስጋና አንድም የግጥም ምስጋና ማለት ነው ።

## ፪ኛ የቅኔ ደራሲ ።

የቅኔው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ እንደሆነ ሊቃውንቱ በብዛት ይስማማሉ ፤ ነገር ግን ከያሬድ ቀጥሎ እገሌ ተብሎ የተማረና የታወቀ የቅኔ ደራሲ ባለመኖሩ አንድም ባለመጠቀሱ ከብዙ ዘመን በኋላ እየተነሡ ልዩ ልዩ ሊቃውንት ራሳቸው እንደ ደረሱ የሚገመቱ አሉ ።

ይሁን እንጂ በአንዳንድ ታሪክ እንደሚገለጠው ሁሉ ከቅዱስ ያሬድ ቀጥለው የተነሡና የቅኔን ሞያ ዐውቀው የተከተሉት ሐዊራ ፤ መንክራ ፤ እስክንድራ ፤ ፖእስክንድራ ፤ አቢዲራ ፤ የተባሉ ሊቃውንት እንደሆኑ ይጽፋሉ ይናገራሉም ፤ እንዲያውም በቅኔ ግጥም ሳይቀር «ወጠፈረ እሉ አብያት እስከነ ይእዜ ኢተነሥተ ፤ ሐዊራስ ወመንክራ ዘተጋብዑ ድርገተ» ፤ ሲል ተቀኝቷል ። —ይሁን እንጂ እነዚህም በአጼ እስክንድር ዘመን የነበሩ ሊቃውንት እንደነበሩ የሚናገሩ አሉ ፤ በዚህም ሁሉ ምክንያት ሁሉም የተስማሙበት እውነተኛውም አስተያየት ይህ ነው ተብሎ የሚገመተው የመጀመሪያው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ መሆኑ ነው ፤ ለዚህም አስረጅ የሚሆነው በመላ ድጓው በቅኔ መልክ የተደረሰ እንደሆነ ርሱም የራሱ

www.ethiopianorthodox.org

ድርሰት እንደሆነ መገመቱ ነው ፤ ስለቤቱ አገጣጠም ግን በዚያን ጊዜ ብዙ ጥንቃቄ ያልነበረበት እንደ ጉት ያለ እንደነበረ ይታመናል ፤ የቅኔ ቤቱ የተወሰነው በአጼ እስክንድር ጊዜ እንደሆነ ሊቃውንት ይስማሙበታል ። ዋድሎች ግን እንደሚሉት ቅኔ ጥንታዊ ፍልስፍና ነው ብለው ያምናሉ ፤ ይኸንም ለማስረዳት ሲሉ ደራሲው ዮሐንስ ፍልሱፍ እንደሆነ ይናገራሉ ፤ ይኸንም የመሰለ አስተያየት ደግሞ ጐንደሮች በበኩላቸው ሲሰጡ የቅኔ ደራሲ ተዋነይ የተባለው ሊቅ እንደሆነ ይናገራሉ ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ደቀ እስጢፋ የተባለ ሊቅ እንደ ደረሰው ይናገራሉ ፤ እርሱም ጽርዕ ድረስ ሔዶ ብዙ ጥበባትን ከቀሰመ በኋላ ሰባት ዓይነት የሚያስደንቁ ነገሮችን ይዞ ወደ አገሩ እንደ ተመለሰ ይናገራሉ ። ይሁን እንጂ ስድስቱ ጥበባት የጥንቆላ ሥራዎች ስለሆኑ ፤ በአገሩ ላይ ተጠልተዋል ፤ ተቀባይነትም አላገኙም ፤ ግን እስከ አሁንም ይሠራል ፤ በሥውር ከአንዱ ወደ አንዱ መተላለፉ አልቀረም ።

ቅኔ ግን በግጥሙ በምሥጢሩ በቃል አሰካኩ ተወዳጅነትን ስለአገኘ ሁሉም በግልጥ ይማረው ያስተምረው ጀመረ ። ደቀ እስጢፋም ቅኔውን ከሌሎች ደቀመዛሙርት ጋር ለአጼ እስክንድር አስተምሯል ። የቅኔ ሥርዓት በዚያን ጊዜ የታወቀ የተወደደም ይሁን እንጂ ቤቱ ፤ ሐረጉ ፤ እንደዛሬው የተመጠነና የተለካ አልነበረም ። አንዳንድ ጊዜ ግን ቤት ሲኖረው ፤ አንዳንድ ጊዜም እንዲሁ ያለ ቤት በጉት መልክ ሲቀኙት ኑረዋል ። እርሱም እንደሚከተለው ያለ ነው ፤ ጉት ቅኔ ፤ « እእግዚእየ ክርስቶስ ለአርእስተ ኃጣውዕ ሠለስቱ ፤ በሐቅለ ቆሮንቶስ ኢሞዕኮሙኑ አኮኑ ተአሥሩ ነገሥት ወርቀ መዝገብ የኀቡ ፤ መፍትሔ ሥራይሰ ለወርቅ ተአሥሮ በፈትለ ክርስቶስ ጥቀ ፤ አፍቅሮ ንዋይ ያጤይቅ ወርቀ ኤዶም በኀል ተወክፈ እምነ ነገሥተ ሰገል » ይላል ።

አንዳንድ ጊዜ ግን ደንበኛ ቤት ያለው ሁኖ እናገኘዋለን ፤ ይሁን እንጂ ቤትም ቢኖረው ቅሉ ምን ቅኔ እንደሆነ ስም አልነበረውም የተመጠነና የተለካ መንገድም አልነበረውም ፤ እንዲሁ ግጥሙን መግጠም ብቻ ነበር ፤ ይኸውም የሚከተለው ዓይነት ግጥም ነበር ።

« አይቴ ኀለፈ ወልድ እጉኪ ንጉሥ ልብነ ድንግል ፤
ንኅሥሦ ምስሌኪ እመ ንረክቦ በኀቅል ።
ሶበ ደቂቃ ይብልዋ በንባበ ሐዋዝ ቃል ።
መካነ ሥላሴ ትጸርኀ ወትብል ።
ወሪዶ ይርአይ አኮኑ ገነተ ጊዮርጊስ ዓፀደ ኮል ።
ትረክብዎ በህየ በዘከመዝ አምሳል ።
ቀይሕ ገጹ ወርእሱ ድሉል » የሚል ነበር ።

ደቀ እስጢፋም ከንጉሡ ጋር ወዳጅነት ከፍ ፤ ያለም ባለሟልነት ነበረው ፤ ነገር ግን በራሱ መጥፎ ሥራ የነበረውን ተወዳጅነት አጣ ፤ ጥፋቱም የንጉሡን

www.ethiopianorthodox.org

ሚስት ያወሰልት ስለነበር ነው ። በዚህም ሳይመለስ ጽርዕ ከተማረው በ፩ኛው ጥበቡ እንደመሠወር አድርጐ ይዞ ጠፋ ፤ ሁሉም በነገሩ ሲጨነቁ ሲያዝኑም ሳለ ከሊቃውንቱ አንዱ ነገሩ ተገልጦለት የንጉሡ ሚስት እጅዋን ተሰብራ ከማሕሉ ፤ ደቅ አለች አሉ ብሎ ተቀኘ ። በዚህ ጊዜ ንጉሡ እስክንድር ቅኔ ዐዋቂ ስለነበር ነገሩ ገባውና ደቅ ውስጥ መገኘቷን አረጋገጠ ፤ ወዲያውም ጉዞውን ጀመረና ሲገሠግሥ ደቅ ደረሰ ። ደቀ እስጢፋም ከንግሥቲቱ ጋር በሰላም ተቀምጦ ሳለ ንጉሡ በድንገት ስለደረሰበት ደነገጠና እየተርበተበተ ይኽንን ተቀኘ ።

«ይቤ አጋግ ከመዝኑ ሞት መሪር ።
በጊዜ ረገዘ ሳሙኤል መምህር ።
ወሰራቄ ንግሥት አነ ደቀ እስጢፋ ኀሡር ።
አንበሳ እስክንድር ፤ ዕጓለ አንበሳ እንዘ ትጥህር ።
እምእርአይከ ተኀጠኒ ምድር » አለ ።
ንጉሥ እስክንድርም ለቅኔው አጸፋውን እንዲህ ሲል መለሰ ።
«ምንት አገበረከ ቍንጽለ ገዳም አንተ ቤተ አንበሳ በዊአ ፤
ኢትሰምዕኑ ጥኀረቶ በአፍአ ።
እስመ እምኔየሰ ተጋንዮትከ ጠፍአ ።
አንበሳ በኃይሉ እምድኀረ ሞዓ ።
ኀድግሰ ዘለከ ብጽአ ።
ጽንሖ ለእሳት ከዊነከ ብርአ »። ብሎ

ከተቀመጠበት ቤት እሳት ለቀቀበት ይባላል ።

ይኽ ዓይነት ግጥም ቅኔ ሲባል ወይም ሲሆን መንገዱ የጉት ዓይነት እንጂ የአሁኑን መንገድ አልተከተለም ።

ይሁን እንጂ ደቀ እስጢፋም በዕፀ መሠውር ከጢሱ ጋር ንግሥቲቱን ይዞ ሳይቃጠል ጠፋ ይባላል ። እስከ አሁንም አለ አልሞተም ተሠውሯል እየተባለ እርሱም የአገሩ ሰዎችም ሳይቀሩ በተሠወረው ደሴት ውስጥ ይኖራሉ እየተባለ በተረት መልክ ይተረካል ። ይሁን እንጂ ከደቀ እስጢፋ ከተማሩት ብዙዎች ሊቃውንት ፩ኛው ተዋነይ ስለሆነ እርሱም የቅኔ ደራሲ ተብሎ በመገመት ይነገርለታል ።

ሌላው አስተያየት ዳግም ቅኔን የደረሰው ዮሐንስ ገብላዊ የተባለው ሊቅ እንደሆነ ይነገርለታል ፤ እርሱም እንደሌሎች በፍልስፍና መንገድ ሳይሆን ግብር ገብቶ ምሥጢር አቃንቶ እንደወጣና እንዳስተማረ ነው ። የነበረበትም አገር በወሎ ጠቅላይ ግዛት በምትገኝ አማራ ሳይንት በተባለችው በዚያን ጊዜ ከተማዋ ደብረ ታቦር በተባለች ቦታ ነው ። እርሱም ለብዙ ሰዎች አስተምሯል ። ግን አብነት አድርጐ ያወጣው ወይም በእግሩ የተካው አባ ወልደ ገብርኤል የተባለውን መነኵሴ ነው ። አባ ወልደ ገብርኤልም ለሠምረ ክርስቶስ አስተምሯል ፤ ሠምረ አብም ይለዋል ። ሠምረ አብም ጉባኤ አስፍቶ ደቀ መዝሙር

www.ethiopianorthodox.org

አብዝቶ ያስተምር ነበር ፤ የቀረው ቀርቶ ለንጉሡ ለአፄ በዕደ ማርያም አስተም ሯል ፤ ንጉሡ አፄ በዕደ ማርያም ቅኔ በማወቃቸው እንዲህ ሲሉ ተቀኙ ይባላል ።

« ድኅረ ተሰብረ አጽንአ ለሰብእናን ልሕኩት
ለብሐዊ ክርስቶስ በማየ ሐዲስ ጥምቀት » ።

ይኸም ሠምረ አብ ለልሂብና ለኤልያብ አስተምሯል ። ኤልያብም ለተዋ ነይና ለድድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ ። ተዋነይ የጐንጅ መንገድ አባት ሆነ ፤ ድድቅ ወልደ ማርያም ደግሞ ለዋድላ መንገድ አብነት ሆነ ። የቅኔ ቤት ወይም የመንገድ ልዩነት በዚህን ጊዜ ተጀመረ ፤ ማለት ጊዜው የጦርነት ጊዜ ስለነበረ የግራኝ ወረራ ሆነና በመካከል ብዙ መገናኘት መወያየት ጠፋ ፤ ስለዚህ የተዋ ነይ ደቀ መዛሙርት ቅኔውን ከባድ አገባቡን እጥር አድርገው ይዘው ተገኙ። ድድቅ ወልደ ማርያም ግን ጉባኤ ሳይፈታ አብነቱንም ሳያጠፋ ይዞ ስለተገኘ የቅኔ መንገድ የአገባብ ሥነ ሥርዓት ከነጠባዩ ከነይትበሃሉ ለመጠበቅ ቻለ ። እርሱም በዚህ ስም የታወቀ በመሆኑ የእርሱን ሞያ የያዙ ሁሉ ድድቅ እየተ ባሉ ወንበሩን ይዘው ሲያስተምሩ ኖረዋል ፤ በዚህም ምክንያት የዋድላ ቅኔ ወይም አገባብ እየተባለ ሲመሰገን አገሩ ሳይቀር በነርሱ ሲጠራ ኖሯል ። በዚህም መልክ በዋድላ መንገድ ሲያስተምሩ የነበሩ ፯ ድድቅ እንደነበሩ ታሪክ ይናገራል ።

ሆኖም የመጨረሻው ድድቅ ለድድቅ ወልደ ማርያም አስተማረ ድድቅ ወልደ ማርያም ደግሞ ለማዕበል ወልደ ሕይወት ሜጫ አስተማረ ፤ ማዕበል ወልደ ሕይወትም ለአለቃ ጌታሁን ጌቴ ገሞራ ሚካኤል ደብር አስተማሩ ።

ከዚህ በኋላ ግን አንዱ መምህር የዋድላውን የጐንጂን የዋሸራውን አገ ባብ ሁሉ በመቀላቀል ሁሉም አይቅረኝ በማለት እየቀዳ እየተቃዳ ተያይዞ የሚ ሔድ ሆኗል ። ነገሩን እርቀን ስንመለከት ጠለቅም ብለን ስንመረምር የቅኔ ደራሽ በእርግጥ ቅዱስ ያሬድ መሆኑ አይጠረጠርም ፤ ነገር ግን በመካከለኛው ዘመን ጠፍቶ ኖሮ በየቦታው አንዳንድ ሊቃውንት ተነሥተው ስለአስፋፉት እነርሱ እንደደረሱት ይተረክላቸዋል ፤ ለምሳሌ በድጓው በኩል ብንመለከት ይኸን የመሰለ ነገር ያጋጥመናል ፤ ማለት የድጓው ደራሲ ቅዱስ ያሬድ ሲሆን ቤተ ልሔም ፤ ቆሜ ፤ ወንጨሬ ፤ አጫብሬ ፤ ዋድሌ ፤ ተጉለቴ ፤ እየተባለ ሲነገር ይኖራል ፤ ይኸን ሁሉ ሊያመጣ የቻለው የዘመን ብዛት በመካከሉም የተፈጠረ ጦርነት እንጂ ምልክቱ የድጓው ዘር አንድ ስለሆነ ፤ ደራሲውም ፩ እንደሆነ ያመለክታል ፤ ይኸውም ቅዱስ ያሬድ መሆኑ ነው ።

የሆነው ሁኖ ቅኔ ከሌላው ሞያ ይልቅ በኢትዮጵያችን ብልጫ ያለው ዕውቀት ሆኖ ሲነገር ይኖራል ፤ የቅኔውም ስምና ሞያ የቤቱ ልክና የሚባልበትም ጊዜ ፤ የያንዳንዱም ቅኔ ትርጕምና አስተያየት እንደሚከተለው ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

# ፫ኛ የቅኔው ዓይነት ።

## ፩/ ጉባኤ ቃና ቅኔ ፤

ሀ/ ዕዝል ጉባኤ ቃና ፤
ለ/ ግዕዝ ጉባኤ ቃና ፤
ሐ/ አጭር ጉባኤ ቃና ፤

መ/ ረጅም ጉባኤ ቃና የሚባሉ አሉ ፤ ሁሉም ሁለት ሁለት ቤት ነው ። ይኸ ረጅምና አጭር ጉባኤ ቃና የተባለው ሐረጉ ይረዝማል ወይም ያጥራል እንጂ ቤቱ ያው አንድ ዓይነት ነው ፤ ማለት ሁለት ቤት ነው ። ሁለት ቤትም የሆነበት ምክንያት የትስብእትና የመለኮት ምሳሌ ነው ፤ በግዕዙም በዕዝሉም ጉባኤ ቃና ረጅምም አጭርም ይገኛል ።

ይኸም ቅኔ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ የሚባለው መወድስ በሚደረስ በትም ጊዜ አምላኪየ አምላኪየ እገይስ ኀቤከ ተብሎ ከሌሎች ቅኔዎች በፊት ነው ፤ ይኸውም ስብሐተ ነግህ በተቆመ ጊዜ ረቡና ዓርብ ሲሆን ነው ፤ በዚያም ጊዜ ዕዝል ይሆናል ፤ በዓቢይ ጾም ግን ግዕዝ ብቻ ይሆናል ። እንዲሁም በታላላቅ በዓላት ስብሐተ ነግህ በደረሰ ጊዜ መጀመሪያ የሚደርስ ቅኔ ነው ፤ በተለይም ስብሐተ ነግህ በተቆመ ጊዜ ረቡዕ ዓርብ ሲሆን ይደርሳል ፤ ምክንያቱም ነገረ መስ ቀልን ይመለከታልና ። ይኸ ቅኔ በትምህርትም ጊዜ የአፍ መፍቻ የስልት መል መጃ ነው ፤ ምክንያቱም ቤቱ ሁለት ብቻ በመሆኑ ለጀማሪዎች በቀላሉ ለመግ ጠም ይረዳቸዋል ።

ጉባኤ ቃና የተባለበት ምክንያት ግን በትክክል አይታወቅም ፤ በአን ዳንድ አፈ ታሪክ እንደሚነገረው ።

ሀ/ የቅኔ ቤት የቅኔም ትምህርት ተለካ ተዋጣለት ጉባኤው ተቃና ተጀ መረ እንደማለት ነው ብለው ይገምታሉ ፤ ይኸውም በቅዱስ ያሬድ ጊዜ እንደ ሆነና ቅኔንም የጀመረ እርሱው እንደሆነ ይናገራሉ ።

ለ/ በሸዋ ጠቅላይ ግዛት ቃና በሚባል ሀገር የተደረገ ጉባኤ የተደረሰም ግጥም እንደሆነ ይናገራሉ ። የሆነው ሆኖ ጉባኤ ቀና በሚለው ብንሔድ ለቅኔው ሁሉ መግቢያ መቃኛ ሆኖ እናገኘዋለን ።

## ፪/ ዘአምላኪየ ቅኔ ።

ዘአምላኪየ የተባለው ቅኔ ፤ ቤቱ ፫ት ነው ፤ ይኸውም የሥላሴ ምሳሌ ነው ፤ መካከለኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል ፤ ዜማው ግን ሁልጊዜ ዕዝል ብቻ ነው ። በቤተ ክርስቲያንም የሚደርሰው በዓቢይ ጾም መወድስ ሲቆምና በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ በተለይም ሰኞ ፤ ማክሰኞ ፤ ሐሙስ በሆነ ጊዜ ነው ። ስሙም ዘአምላኪየ የተባለበት ምክንያት የቅኔው መጀመሪያ አምላኪየ አምላኪየ እገ

www.ethiopianorthodox.org

ይሥ ኀቤከ የሚለው የዳዊት መዝሙር እየተዘመረ ስለሚደርስ ነው ። የጉባኤ ቃና እንዲሁም የዘአምላኪየ መነሻቸው ይኸውም አምላኪየ አምላኪየ እገይሥ ኀቤከ የሚለው መዝሙር ነው ። የሚደረሱትም በመፈራረቅ ስለሆነ መነሻው አንድ ነው ።

## ፫· ሚበዝኁ ቅኔ ፤

ሚበዝኁ ቅኔ ፫ ቤት ነው ይኸውም የሥላሴ ምሳሌ ነው ፤ እንደዘአምላኪየው ፪ኛው ቤት መንደርደሪያ ይባላል ። ከዚህ በላይ ያለው ቅኔ ሁሉም ወይም ከጉባኤ ቃና በቀር መንደርደሪያ ያለው ነው ። ዜማው ግን ሁል ጊዜ ግዕዝ ነው ። ስሙ ሚበዝኁ የተባለበት እግዚአ ሚበዝኁ በተባለው የዳዊት መዝሙር የሚነሣ ስለሆነ ነው ። እርሱም በቤተ ክርስቲያን የሚደርስበት ።

ሀ/ ሁልጊዜ እሑድ በዓቢይ ጾምና በሌላው መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ነው ።

ለ/ አደራረስ በሚደረስበት ጊዜ ከዘአምላኪየ ጋር በአደራረስ የሚፈራረቅ ቅኔ ነው ።

## ፬· ዋዜማ ቅኔ ፤

ሀ/ ረጅም ዋዜማ የርሱም ቤት ፬ ነው ፤ ይኸውም የ፬ቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው ፤ ዜማው ግን ዓራራይ ነው ።

ለ/ አጭር ዋዜማ ፤ ቤቱም ፱ ነው ፤ የትስብእትና የመለኮት ምሳሌ ነው ። ዋዜማ ማለት ብዙ ጊዜ በበዓሉ ዋዜማ የሚደርስ ቅኔ ስለሆነ በዚያው ስም ተጠርቷል ። ረጅሙ ዋዜማ ሁልጊዜ በየታላላቁ በዓላት በዋዜማው ጊዜ የሚቀኙት ቅኔ የሚገጥሙትም ግጥም የሚያቀርቡትም ምስጋና ነው ።

ስለዚህም ዋዜማ ተብሏል ፤ ረጅሙ ዋዜማ በዋዜማ ጊዜ ፫ ቅኔዎችን ይቀኛሉ ። አጭሩ ዋዜማ ግን በቅኔው መንገድ ቦታውን ስለያዘ ብቻ ዋዜማ አሉት እንጂ የሚደረሰው በመወድስ ጊዜ ነው ፤ ከርሱም በፊት የሚዘመረው የዳዊት መዝሙር « ለእግዚአብሔር ምድር በምልዓ ፤ እግዚአብሔር ነግሠ » የሚል ነው ። ይኸም ማለት እንደሌሎቹ ቅኔዎች የዳዊትን መዝሙር ወይም መነሻ አልተከተለም ስሙንም አልያዘም ። ዋዜማ በአርያም አደራረስ ጊዜ ሁለት ይባላል ፤ ይትባረኩ ማረፊያ የሆን እንደሆነ ዋዜማ ይደረጋል ፤ እርሱም እንደነዋ በግዑያለ ነው ።

## ፭· ሥላሴ ቅኔ ።

የሥላሴ ቅኔ ቤቱ ፮ ነው ፤ ምሳሌውም የ፮ቱ ቃላተ ወንጌል ነው ዜማው ግን ሁልጊዜ ዕዝል ነው ፤ ይኸንም ቅኔ የሚቀኙት ፤ ፩ኛ/ በታላቅ በዓላት ዋዜማ ጊዜ ፩ ሥላሴ ሁልጊዜ አለ ፤ ፪ኛ/ በክሥተት አርያም ጊዜ ነው ። ይሁን እንጂ የሽማግሌዎች ወይም የአዋቂዎች ቅኔ ነው እየተባለ ስለሚገመት የሚሰጠው በዕውቀት ለበሰሉ ሰዎች ብቻ ነው ። ሥላሴም የተባለበት ምክ


www.ethiopianorthodox.org

ንያት ይትባረክ እግዚአብሔር አምላከ አበዊነ በሚለው በጸሎተ ፫ቱ ደቂቅ ድር ሰት እየገባ የሚነገር ስለሆነ ፤ አምላከ አብርሃም አምላከ ይስሐቅ አምላከ ያዕቆብ እያለ ፫ ትንትን የሚገልጠውን እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው ።

## ፮. ዘይእዜ ቅኔ ።

ዘይእዜ ማለት «ይእዜ ትስእሮ ለገብርከ» በማለት የሚጀመር ስለሆነ ነው ፤ ዘይእዜ የተባለው ቅኔ አጭርም ረጅም አለው ። የረጅሙ ዘይእዜ ቤት ፭ ነው ፤ ያ፭ቱ አዕማደ ምሥጢር ምሳሌ ነው ። ዜማው ግን ግዕዝ ነው ፤ አጭሩ ዘይ እዜ ቤት ፫ ብቻ ነው ። ስሙም ሣህልከ ይባላል ፤ ቅኔውም እንደሚከተለው ነው ።

«ፍትሐ ሞተ ኀርቃል ንጉሥ ዘተካፈሉ ።
ወፍትሐ ኢንጉሥ ዮናታን ዘተካፈሉ በቃሉ ።
ኢሀለዉኑ በኢትዮጵያ ሞተ ምኒልክ ከመ ያስስሉ » ።

ዜማውም ዓራራይ ነው ፤ ስሙንም ሣህልከ እያሉ የሚጠሩት ተሣሃለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ የሚለውን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው ። ይኸ ውም ቅኔ ረጅምም አጭርም ቢሆን ብዙ ጊዜ የሚቀኙት ስለ ንጉሥ ክብር ነው ። ስለዚህም የሚቀኘው ሰው በዕውቀት በዕድሜው ከፍ ያለ ምሥጢር ያደላደለ ታሪክ ያወቀ መሆን አለበት ።

ዘይእዜ የተባለበት ምክንያት ይእዜ ትሥዕሮ ለገብርከ የሚለውን የነቢዩን መዝሙር እየዘመሩ ስለሚጀምሩት ነው ። ረጅሙ ዘይእዜ የሚደረሰው በታላላቅ በዓላት ዋዜማ ጊዜ ነው ። እንዲሁም በስብሐተ ነግህ አደራረስ ጊዜ ይቀኙ ታል ፤ ሣህልከ የተባለው ግን መወድስ በሚደረስበት ጊዜ ብቻ ነው ።

## ፯. መወድስ ቅኔ ።

መወድስ ቅኔ የተባለው ረጅም ቅኔ ደግሞ ፪ ዓይነት ነው ፤ እርሱም ሀ/ ፍታሕ ሊተ የተባለው ሲሆን ፤ ቤቱም ፰ ነው ፤ የ፰ ብሔረ ኦሪት ምሳሌ ነው ፤ ዜማው ደግሞ ዓራራይ ነው ።

ለ/ ዠልክሙ የተባለው ሲሆን ፤ ቤቱም ፱ ነው ፤ የ፱ኙ ሐፁረ መስቀል ምሳሌ ነው ። እንዲሁም አጭር መወድስ ወይም አጭር ዠልክሙ የሚባሉ አሉ ፤ ቤታቸውም ሁለት ነው ። ሁለቱም ወገን መወድስ የተባሉበት ምክንያት እልታ ወቀም ፤ የሚሰጠው ሐተታ ግን መወድስ የተባለው የቃል ትምህርት በደረሰ ጊዜ የሚቀኙት ቅኔ ስለሆነ ፤ ነው ፤ ወይም ራሱ ቅኔ ማለት ምስጋና ማለት እንደሆነ ወደሰ አመሰገነ ብሎ መወድስ ምስጋና በመሆኑ ነው ሲሉ የሚናገሩ አሉ ። ፍታሕ ሊተ የተባለው በዳዊት መዝሙር በሚጀመርበት ስለተጠራ ነው ፤ ዠልክሙ የተባለውም ደግሞ ዠልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ የተባለው መዝሙር እየተዘመረ ስለሚጀመር ነው ። ሁለቱም መወድሶች በተለይም ዠል

www.ethiopianorthodox.org

ክሙ ለሽማግሌ ሰው ተመርጦ የሚሰጥ ቅኔ ነው ፤ እንዲያውም አንዳንድ ጊዜ ፤ ወይም በተለይ በታወቀ በዓል ለቤተ ክርስቲያኑ አስተዳዳሪ (አለቃ) የ ሚሰጥ ቅኔ ነው ።

## ፰· ክብር ይእቲ ቅኔ ።

ክብር ይእቲ ቅኔ ሁልጊዜ ነገረ መስቀልን የያዘ ስለሆነ ፤ እንደ መርዶ ይቆጠራል ፤ ሲቀኙም በጣም በለሆሳስ መሆኑ ስለዚህ ነው ይባላል ። ክብር ይእቲ የሚባለው ቅኔም ፪ ዓይነት ነው ፤ ይህም ፥

ሀ/ ግዕዝ ክብር ይእቲ ፬ ቤት ብቻ ነው ።

ለ/ ዕዝል ክብር ይእቲ ፬ ቤት ብቻ ነው ።

ይኸም ቅኔ ሁልጊዜ የሚመለከተው ነገረ መስቀልን ብቻ ነው ። ስለዚህ ማንም ቢቀኝ ከዚህ አይወጣም ፤ ስሙ ክብር ይእቲ የተባለበትም «ክብር ይእቲ ዛቲ ለኵሉ ጻድቃኑ» የተባለው መዝሙረ ዳዊት ስለሚዘመር ነው ። በእርሱ እግር የሚገቡ ቅዱስ ያሬድ የደረሳቸው በተለይ በዓቢይ ጾም መጨረሻ የሚባሉ እንደ ሐዋርያቲሁ ከበበ ፤ እንደ ሕንፂሃ ይኸንም የመሰሉ ሌሎች ክብር ይእቲዎች አሉ ፤ እነርሱም ሳይለወጡ ራሳቸው ይባላሉ ፤ ወይም በነርሱ ልክ ግጥም (ቅኔ) ይቀኛሉ ።

## ፱· ዕጣነ ሞገር ቅኔ ።

ዕጣነ ሞገር የተባለው የቅኔ ዓይነት ፪ ነው ። እርሱም ፤

ሀ/ ግዕዝ ዕጣነ ሞገር ፯ ቤት ፤

ለ/ ዕዝል ዕጣነ ሞገር ፲፩ ቤት ነው ።

ሁለቱም ዓይነት ዕጣነ ሞገር ትልልቅ የሆነ ፪ ክፍል አላቸው ፤ ይኸውም እስከ መንደርደሪያው ያለው የሁለቱም ቅኔዎች ግጥም በዓሉን ወይም ዕለቱን የሚመለከት ሲሆን ፤ ከመንደርደሪያው ጀምሮ ያለው ግን ስሙም አሠረ ንጉሥ ይባላል ፤ የሚሰጠውም ለንጉሥ ክብር ብቻ ነው ።

ይኸውም ማለት ምስጋና ታሪክ ሌላም ሁናቴ ቢሆን የንጉሥንና የታላላቅ ሰዎችን ሁናቴ የሚገልጥ ክፍል ነው ። ይኸም ሲሆን ግዕዙ ዕጣነ ሞገር ፬ ቤት በዓሉን ወይም ዕለቱን ሲመለከት ፤ ፫ ቤት ግን አሠረ ንጉሥ ስለሆነ ፤ ለሰው ማመስገኛ የሚሰጥ ነው ። ዕዝሉ ዕጣነ ሞገር ደግሞ ፯ ቤት ዕለቱን ወይም በዓሉን ሲመለከት ፤ ፬ ቤት ግን አሠረ ንጉሥ ስለሆነ ለሰው ልጅ ማመስገኛ ሆኗል ፤ እንዲያውም በዚሁ ክፍል ሰውን ይሰድቡበታል ፤ ወይም ይመርቁበታል ። እንዲሁም ይረግሙበታል ፤ የቅኔውን መልኩን አሳጥተውታል ። በጥንት ዘመን ግን ለንጉሥ ብቻ የሚሰጥ የክብሩ መግለጫ የቤተ ክርስቲያን አባልነት መብት መታወቂያ ነበር ፤ ስለዚህም አሠረ ንጉሥ ይሉታል ።

ዕጣነ ሞገር የተባለበትም ምክንያት የጸሎት ፤ የማዕጠንት ማሳረጊያ ፤ መደምደሚያ ስለሆነ ነው ፤ በእርግጥም ከዚያ በኋላ በቤተ ክርስቲያን የሚደረግ

www.ethiopianorthodox.org

ሌላ አገልግሎት ሌላም መዝሙር የለም ፤ ማሰናበቻው እርሱ ነውና ። በግዕዙ ዕጣነ ሞገር ጊዜ በተወሰኑት ዓመታት ዕለታት ከሌላው ቅኔ ተለይቶ ቤቱን ሳይ ጠብቅ በግዕዝ ጀምሮ በሳብእ ይጨርሳል ። ለምሳሌ ለ ሉ ሊ ላ ሌ ል ሎ ፤ እያለ ሊሔድ ይችላል ። ይኸም ሊሆን የሚችለው በተወሰኑት ዕለታት ብቻ ነው ።

## ፩ የቅኔ ቤት ።

የቅኔ ትምህርት ቤት የቅኔ ቤት ይባላል ፤ የቅኔ ቤት እንደ ማለት ነው ። ከዚህ ግን የቅኔ ቤት ስንል የቅኔው ግጥም በመጨረሻ የሚገናኙትን ፤ ወይም የመሳሰሉትን ፊደሎች ማለታችን ነው ። የቅኔው መልክ የሚታወቀው በአንድ ፊደል የጨረሰ አንድ ቤት ያለው እንደሆን ነው ።

በመጨረሻ የሚገጥመው ፊደል ቤት ይባላል ፤ ማለት ተመሳሳይ ቃል መጨረሻው አንድ ዓይነት የሆነ ማለት ነው ። እንኳን ለቅኔው ለሌላው መዝ ሙር ግጥም ወይም ዘፈን ይኸንንም ለመሰለው ሁሉ ቤት አለው ቤትም ይመታል ፤ ቤት ይገጥማል ይባላል ። ይኸንም ለማስረዳት የቅኔውን ሁሉ ቤት ለቅመው ፤ ደምረው ፸፫ እንደሆነ ይናገራሉ ፤ እርሱም እንደሚከተለው ነው ።—

### የቅኔ ቤቶች ።

| | |
|---|---|
| ጉባኤ ቃና . . . . . . . . | ፪ |
| ዘአምላኪየ . . . . . . . . | ፫ |
| ሚበዝኁ . . . . . . . . . | ፫ |
| ዋዜማ . . . . . . . . . | ፭ |
| አጭር ዋዜማ . . . . . . . | ፪ |
| ሥላሴ . . . . . . . . . | ፯ |
| ዘይእዜ . . . . . . . . . | ፭ |
| አጭር ዘይእዜ . . . . . . . | ፪ |
| ሣህልከ . . . . . . . . . | ፫ |
| የፍታሕ ሊተ . . . . . . . | ፰ |
| የኰልክሙ . . . . . . . . | ፱ |
| ሕንፂሃ . . . . . . . . . | ፪ |
| ሐዋርያቲሁ ከበበ . . . . . . | ፪ |
| ግዕዝ ክብር ይእቲ . . . . . . | ፩ |
| ዕዝል ክብር ይእቲ . . . . . . | ፩ |
| ግዕዝ ዕጣነ ሞገር . . . . . . | ፯ |
| ዕዝል ዕጣነ ሞገር . . . . . . . | ፲፩ ድምር ፸፫ ይሆናል ፤ |

የዚህንም ድምር እርግጠኛነት ለማስረዳት ከዚህ የሚከተለውን ተቀኝተዋል።

«ደቀ እስጢፋ ጻድቅ ከመ እስክንድር

በመንፈስ ቅዱስ ነበበ ሐሳባተ ነቢይ ቅኔያተ ።

www.ethiopianorthodox.org

እምቅኔያቲሁ ለያሬድ ዘእንበለ ያትርፍ ምንተ ።
ወከመ ኢይኅድሩ ውስተ አፍአ ለቅኔያቲሁ ሐነፀ ዓብያተ ፸ ወሰማኒተ ።
ወጠፈረ እሉ አብያት እስከነ ይእዜ ኢተነስተ ።
ሐዊራስ ወመንከራ ዘተጋብኡ ድርገተ ።
ዘምስለ ብዑል እስክንድር አስተጋብኡ ምሥጢራተ ።
መንከራተሂ መተሩ ወተመሰሉ መጥባሕተ ።
ለመጥባሕት እስመ ልማዱ ከፈሎተ ዋሕድ አርባዕተ» ።

አንዳንድ ሊቃውንት እንደሚሉት ጥንቱን ለቅኔ ቤት አልነበረውም ፤ በልዩ ልዩ ዓይነት ወይም ዘዴ ይሄድ ነበር እንጂ ፤ እንዲሁ ተመሳሳይ ጠባይ ያለው ፊደል ማለት ራብዕና ራብዕ ፤ ሳድስና ሳድስ ፤ እንደዚሁም ሁሉ ሌላው መግጠሙ ብቻ እንጂ ተመሣሣይ ፊደል መኖር አስፈላጊ አለመሆኑን ይናገራሉ ። ይኸም ሁናቴ በሌላው አገር ሁሉ ይደረግ እንደነበር የታመነ ነው ።

ቅዱስ ያሬድ ቅኔን ሲደርስ ቤት አለመሥራቱን ወይም ለቅኔ ቤት አለመኖሩን ለማስረዳት አንድ ሊቅ ይኸንን ቅኔ እንደተቀኘ ይጠቅሳሉ ።

«ተትሕተ ያሬድ ዘኢተትሕተ ፤
ለቅኔያቲሁ ደቂቅ እስመ ኢሐነፀ ቤተ» ።

ፍቺውም ያልተዋረደ ያሬድ ተዋረደ ። ለቅኔዎች ልጆች ቤትን አልሠራምና ማለት ነው ፤ ይኸም ቅኔ አጭር ዘይእዜ ይባላል ፤ አሁን ድረስ ይቀኙታል ። የሚባለውም በአማኑኤልና እርሱን በመሳሰሉት በዓላት ይትባረኩና ዘይእዜው ግዕዝ በሆነ ጊዜ በፊት ረጅሙን በኋላ አጭሩን ይሉታል ። ይበልጠውን በቅኔ መልክ ይደረስ እንደነበር ባለፉት ምዕራፎች አስረድተናል ። አሁንም ቢሆን ቤት የሚመቱ በየዓመቱ ሳይለወጡ እንደ ክብር ይእቲና እንደ ዕጣነ ሞገር ያሉ ቅኔዎች አሉ እነርሱም ፤

ሀ/ « ሕንፂሃ ወሱራሬሃ አዳም ፤
እምአስካለ ወይን ጉርዔሃ ጥዑም » ።
ለ/ « ሐዋርያቲሁ ከበበ ፤
እግረ አርዳኢሁ ሐጸበ ፤
ኮኖሙ አበ ወእመ ወመሐርሙ ጥበበ » ፤ የሚል ነው ።

ይኸንም የመሰለ የማይለወጥ ከጾመ ድጓው ውስጥ አለ ፤ ግን ቅኔም ቢሆን ብዙ ዓይነት ይገኛል ፤ ለምሳሌ በሕንፂሃ ዐይነት ፤ «እንከሰ ቀራንዮ ኢየሐውር እግዚእነ ፤ እስመ ቀራንዮ ምድረ ደም ኮነ ፣ » እንዳለው ያለ ነው ፤ ከነርሱም ውስጥ ብዙዎች ቤት ያላቸው ናቸው ። የሚበልጡት ግን ያለ ቤት የቀሩ ናቸው ። በቤቱ አመታት ግን ብዙ የተለያየ የሊቃውንት አስተያየት አለበት ፤ ይኸውም ፤ አንዳንዶች ሀ/ ቤት መሆኑን እንጂ ሃሌታው ፤ ሐመሩ ወይም ብዙኃኑ ሃ/ መሆኑን አይጠብቁም ። በተለይም የዚህ ተመሳሳይ የሆነውን ፊደል

www.ethiopianorthodox.org

ራብዑን ከግዕዝ ሳይለዩ በድምፅ ሐ/ከሆነ ብለው የሚቀኙ አሉ። አንዳንዶች ግን ይኸን ሁናቴ ይቃወማሉ ፤ ማለት ፪ ወይም ፫ ፊደል የሚገባበት ከሆነ ፤ ምንም ድምፁ አንድ ቢሆን ፊደሉ መልኩን ተራውን ከለወጠ ቤቱ እንደፈረሰ ይቆጥሩታል ። እንዲያውም በመጀመሪያው ክፍል እንደተናገርነው የያንዳንዱ ፊደል የተለየ ድምፅ የተለየም ቍጥር የተለየም ትርጒም ያለው መሆኑ የታወቀ ስለሆነ ፤ በቅኔ ቀርቶ በሌላም ጊዜ ሊለወጥ እንደማይገባ ይናገራሉ ።

## ፫ በቅኔ ውስጥ የሚገኙ ክፍሎች ።

ከዚህ ቀደም በክፍል በክፍሉ እንደተናገርነው ሁሉ በዚህም ውስጥ ቅኔ ተብሎ ለያንዳንዱም ስም ቢኖረው ቅሉ በአንዱ ቅኔ ውስጥ ምን ክፍል እንዳለው እንናገራለን።

፩/ ሐረግ የሚባል አለ ፤ ይኸውም ከአንዱ ቤት እስከ ሁለተኛው ያለው አረፍተ ነገር ነው ።

፪/ መንደርደሪያ ይባላል ፤ ይኸውም የዘአምላኪየ ሁለተኛው ቤት ፤ የዋ ዜማም ሁለተኛው ቤት ፤ የሥላሴም ሁለተኛው ቤት ፤ የዘይእዜም ሁለተኛው ቤት የመወድስ ግን ሦስተኛው ቤት ፤ እንዲሁም የግዕዝ ዕጣነ ሞገር ፤ አራተኛው ቤት ሲሆን ፤ የዕዝል ዕጣነ ሞገር ግን ስድስተኛው ቤት ነው ፤ የቀሩት ቅኔዎች ደግሞ መንደርደሪያ የላቸውም ። ለምሳሌ እንደ ጉባኤ ቃና ፤ እንደ ክብር ይእቲ ፤

፫/ ቧኄ ይባላል ፤ ይኸውም የመወድስ አራተኛው ቤት ነው ፤ ለመወ ድስ ብቻ እንጂ በሌሎቹ ቅኔዎች ቧኄ የላቸውም ።

፬/ ለዓለም ፤ ይኸውም የመወድስ ስድስተኛው ቤት ነው ፤ የሚገኘውም በመወድስ ብቻ ነው ።

፭/ መጽፊያ ፤ ይኸውም የዋዜማ አራተኛው ቤት የሥላሴም አራተኛው ቤት የዘይእዜም አራተኛው ቤት ሲሆን ፤ የመወድስ ግን ዘጠነኛው ቤት ነው የግዕዝ ዕጣነ ሞገር ደግሞ ሰባተኛው ቤት ሲሆን ፤ የዕዝል ዕጣነ ሞገር ግን ዘጠነኛው ቤት ነው ። የቀሩት ቅኔዎች ደግሞ መጽፊያ የላቸውም ፤ ከላይ እንደገለጥነው ነው ፤

፮/ ሆኛ ፤ ይኸም ማለት ቤት ከመምታቱ በፊት የሚገኝ ቤት ወይም ሐረግ ነው ። ይኸ ሐረግ በስድ ንባብ መሔድ ሲገባው ፤ ቤት የሚመቱ አሉ ። ይኸ ሆኛ ጸያፍ ይባላል ።

ምዕራፍ ፭ ።

## የቅኔ መንገድ ።

የቅኔዎች ዓይነትና ብዛት ከዚህ በፊት በምዕራፍ ፫ የተገለጡት ሲሆኑ ፤ መንገዳቸው ግን ብዙና ልዩ ልዩ ዓይነት ነው ። ብዙዎች መንገዶች በሁሉ ዘንድ የታወቁ ሲሆኑ ፤ ጥቂቶች ግን እንዲሁ በቃል ብቻ ይኸን ያህል ቍጥር ማለት እንጂ አስረጂ አልተገኘም ፤ አንዳንዱ ደግሞ የመምህራኑ ቅኔ ለአስረጂ ያህል ቢገኝ ከአ

www.ethiopianorthodox.org

ንድ ላይ ብቻ ነክ ቢኖረው ነው እንጂ ቅኔውን በመላ ጉባኤ ቃናም መወድስም ቢሆን አይዘልቀውም ። የሆነ ሆኖ ለጊዜው የተገኙትን የቅኔ መንገዶች ብዛት ከነቅኔያቸው ከዚህ በሚከተለው መንገድ እጽፋለሁ ።

፩· ሰምና ወርቅ ጉባኤ ቃና ።

ኢትኅዘኒ እንከ ጉባኤ ቃና ድንግል ፤
አምባነ የአምር ለኪ ዘፈጠረኪ አስካል ። ( ከመሪጌታ አስካል )

፪· ሰም ገፊ መንገድ ( ዋዜማ ) ከሊቀ ኅሩያን ዘገየ ።

ኢየሱስ ገሊላዊ ኀበ ገሊላዊ ዮሐንስ
ወኀበ ዮርዳኖስ ሖረ ።
ውእቱ እንዘ በተጠምቆ ኢየኃሥሥ ክብረ ።
ጊዮርጊስኒ ኢይኅስስ ዮሐንስሃ ወባሕረ ።
ዮሐንስሃ ረሰየ ርእሶ ምቱረ ፤
ወክሳዶ ዮርዳኖሰ ገብረ ።

፫· ተመኩሳይ መንገድ ( መወድስ ቅኔ ፤ የማዕበል ደሴ ) ፤

ኅቡዓ ቊረ ቃዴስ ባሕር ፍጽመ አቤግያ
ከዓዌ ኅብረ ወርቅ ዘሜዶን በዘዳንኤል ኅሠሣ ።
እስመ በግበ ኅቅል ሰቈላቅ ውዋዔ ጌዶር አንበሳ ።
ወኅልቀተ ወርቅ ይውህጥ ፤ ነዊሃ አጽባእተ ሰሎሜ ዘሰሎሞን ዓሣ ።
ወዕዋለ ዕድግት ዘኤፍራታ ፤ በተኃይሎ ትጸውር ብዕለ ሳምናዊ አቢሳ ።
አእዳውሂ ዘሰሎሜ ዘሥጋ ኤልያስ ለብሳ ።
በዘርአ አልህምት ዘአብርሃም አራዊተ ሶምሶን ይጸንሳ ፤
ወአመ ፈድፈደት ግፍዕ ጥበበ ኦርዮ እምንእሳ ።
ዓይነ አንበሳ ኀበ ዕድግት ወዓይነ ዕድግት ኀበ አንበሳ ።

፬· ውስጠ ወይራ መንገድ (ዋዜማ ፤ ዘዕቡይ ካሣ)

ኖትያ ባሕረ ብርት ቴዎድሮስ ፤ እስኩ ተጸአን አሕማረ ኬልቄዶን ኵሎ ።
ከመ ትዕዱ ምልዓተ ዘርእየ ኢሳይያስ አውሎ ።
ኢትግበርሰ እምእሉ እንበለ ትግበር ተከፍሎ ።
ጌራ ነገሥተ ፋርስ ወሜዶን ተቀጽሎ ።
ጌራ ወርቅ በርእስከ ሀሎ ።

፭· አገናኝ መንገድ ፤ (የመወድስ ለዓለም)

ጸላእኩ ሰብአ እምነ ርእስየ ፤ ዘትርጓሜሁ በቀል ወዘንባቡ ሐሰት ።
እስመ እምልሳኑ ለሰብእ ዘይበልእ መሬት ፤

www.ethiopianorthodox.org

ለፊ ትሕትና ወለፊ ትዕቢት ፤
ይወጽኡ በስብከት ፤ እንዘ በላዕሌሁ ይሄሉ እንተ ኢይተርፍ ሞት ።
(ከመ.ጋቢ ወልደ ማርያም)

፮· አታላይ መንገድ (ጉባኤ ቃና)

ተለዐለት ጴጥሮስ እንተ በመስቀል ፍኖቱ ።
አዕዋዴ ሥቃይ ጽኑዕ ለገላውዴዎስ ፍቅርቱ ።

፯· ድርድር ውስጠዘ መንገድ ጉባኤ ቃና (ከሊቀ ኅሩያን ዘገየ) ።

ሰማዕት ሶምሶን ቀታሊ ቀታሌ ቀታሊ ኃይላተ
አክያ ኢዮአብ አንበሳ መልአከ ሐሰት ሞተ ።

፰· ጽድቅ መንገድ ፤

እኩያን አይሁድ ለእግዚአሙ ሰቀሉ ።
ንባበ አሪት ቅድስተ እስመ አጥፍአ በቃሉ ።

፱· አንፃር መንገድ ጉባኤ ቃና ።

ጊዮርጊስ ሰማዕት ኢሳይያስሃ መሰለ
በዘኢሳይያስ ግብር እስመ ጊዮርጊስ ወዓለ ።

፲· ሙሻዘር መንገድ (ጉባኤ ቃና ከአስታአ በረከት ጌጡ)

ላዕለ ሳሌም ግፍዕ ሀገረ ዳዊት ንጉሥ
ሰሎሞን ወይን ንጉሠ ዳዊት በለስ ።

፲፩· የምሥጢር ምርምር መንገድ (መወድስ) ።

ምክረ ንጉሠ ቤቴል ሐልቀ በሕሊና ኬፋ ፤ እንበለ መሳክው ትትገበር
ስፍሐ መቃብር ንድቅ ፤
እስመ ይቤለነ ሄኖክ መቃብረ ድንግል ዕሙቅ ።
ምዕራብ አይቴ ወአይቴ ምሥራቅ ።
ወበደብረ ሲና ኢትወድቅ ፤ ልሳነ ዕፄ ወንጌል እንተ ነጸራ መልከ ጼዴቅ
ካዕበሂ አመ ተአሥረ በጽዋዓ ወርቅ ፤

. . . . . . . . . . . . . . . . . . .

ወአመ ተፈነወ ነግሃ ላእከ ዘጊዮርጊስ ጽድቅ ፤
ሥጋ ማርያም አዛርያስ በሕማመ ኦዝያን ይስሕቅ ።

፲፪· ንጽጽር መንገድ (ሥላሴ ቅኔ) ።

ዓለም እስከ ጊዜሃ
በኀብለ ዝንጋዔ ትስሕበነ ፤ ወታወርደነ ካዕበ ኀበ ዘቀዳሚ መርገም ።

www.ethiopianorthodox.org

ለዘተወለደነ በሥጋ ወደም ፤
ዘእእመራሰ ጠቢብ ለባዊ ለኀልፈተ ዛቲ ዓለም ።
ፍዳ ወይን ይስተይ ማየ ዝናም ፤
ወሀየንተ ልብስ ይትከደን ቈጽለ አዕዋም ።
እስመ ዛቲ ጽላሎት ወሕልም ፤— (ከራስ ወልደ ገብርኤል )

ተሰጧ የግል ቤተ መጻሕፍት

፲፫· ኅብር መንገድ (ጉባኤ ቃና ፤ ከመ. ጌራ ፤)

ሰሎሜ ስመኪ ኢታኅስሚ ወኢትግሥሢ መሶበ
እንበለ ፩ዱ ኅብስት አምጣነ አልቦ ዘቀርበ ።

፲፬· ፀፀት መንገድ (ሚበዝኁ) ፤

በዘወልደ ስምዖን ወርኀ ለእመ ሀሎ ሰሎሞን እምኢሴጠ በዙረ ዙሉ ፤
በወርቀ ይሁዳ ወሳሌም ይሁዳ ብእሴ ላዕሉ ።
አምጣነ ረሰየ ወርቀ አቤዝ ሰሎሞን ከመ ዕፀወ ሐቅል ዙሉ ።

፲፭· ፈጠራ መንገድ (ዋዜማ) ፤

ስመ ኢተኃቡኒ ወኢትበሉኒ በልዓ ሥጋ ዮሐንስ አዳም ።
ይብለነ አፈ ጉባዔሃ ለዓባይ ገዳም ።
እስመ ሥጋ ዮሐንስ ሐልቀ በዘእለ ዳንኤል ጾም ።

፲፮· ምጸት መንገድ (ሚበዝኁ) ፤

ለምእዛረ ፀሐይ ሕዝቅያስ ዘውስተ ሕይወት ወሞት መሳክወ ንጉሥ ቤተ
ሰላም ።
አኀዞ በእድ ሕፃነ አእምሮ ሰናክሬም ።

፲፯· ዝምዝም ወርቅ መን ( ከዓስትዓ በረከት )

ኃይለ ሥላሴ ፀሐይ ብርሃነ ዓለም
ኃይለ ሥላሴ ኮከብ ዘሠረቀ በጽባሕ ፤
ኃይለ ሥላሴ ናርዶስ ጽጌ ደንጐላት ቀይሀ ።
በትረ ሃይማኖት ኃይለ ሥላሴ ዘታጸንእ መንግሥተ ነጋሢ ሰሎሞን መካሀ ።
አፈወ መንግሥት ኃይለ ሥላሴ ፤ ኃይለ ሥላሴ ቀንሞስ ኃይለ ሥላሴ ሐረገ
ንጽሕ ።
ዕንቈ ክብርሂ ኃይለ ሥላሴ አምሳለ ፀሐይ ወወርኅ ።
ባሕረ ጥበባት ኃይለ ሥላሴ ኃይለ ሥላሴ ሐመረ ኖኅ ።
ኃይለ ሥላሴ ፈለግ ምቅድኁ ምሥጢር ብዙኅ ።
ልደትከ ጣዕመ ወይን በማኅፀነ ጥበብ ለይትቀዳሀ ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፰· የወርቅ ተነጻጻሪ (መወድስ ከአለቃ ይኩ· ኦም)

አርአያ ሰአሊ ይትዐወቅ በአርአያ ሥዕሉ፤ ሰአሌ ፍጥረታት
ሰአለ በአርአያሁ ጥበብ ።
እመኒ መንክር አምሳለ መልክዑ ረኪብ ።
አኮ መንክር በዘሐታቲ ዕፅብተ ፍካሬ ንባብ ወብዙኅ ንባብ ።
እስመ ኢያሥመረት ለልዑል፤ዕበየ ቆሙ ለሳኦል ወግርማ ርእየቱ ለኤልያብ።
ለረኪብሰ አምሳሊሁ ለእግዚአብሔር ቅሩብ ።
ንኩን ቅዱሳን ዘከመ ቅዱስ ባሕርየ አብ ።
ወእምከመ ሀሎ ኀቤነ አፍቅሮተ ሰብእ ማኅየብ ።
ዘእንበለ ክልዓት ንቅዳህ አምሳለ ጠፈር ማየ ናጌብ ።

፲፱· የወፍ እግር መንገድ (ዕዝል ዕጣነ ሞገር)

እግዚአብሔር ተወልደ እምነ ማርያም ወይን ።
ዘአዕጹቂሃ ሰማዕት ወጻድቃን ።
ወእግዚአብሔር ሠረገላ ቀሊለ ሩጸት ሥልጣን ።
አቀሞሙ በየማን ።
ለአእጋሪሁ ኤልያስ ወሙሴ ጽጌያተ አሪት ሮማን ።

፳· ስም ጥቅል መን (የመወድስ ለዓለም) ።

ለዳዊትሂ ዘወረደ ዕመቀ መደንግፅ ሥልጣን ።
ደብረ ተዋርዶ በቅድመ ገጹ የዓርጉ ኃያላን ።
እስመ ከመ ዐውሎ ረዊፅ መዓዛ ፈረሱ ሥሂን ።
ወኩናተ መብረቅ በጊዜ ጸብእ አስካለ መጥባሕት ሐረገ ወይን ።

፳፩· የኃዳሪና የማኅደር መን (የመወድስ ለዓለም) ።

ቅድመሰ ለእሥራኤል እንዘ ሰላማዊ ዘመን ።
ዓለመ ተድላ ዘእሥራኤል ይትፌሥሑ ነዳያን ።
እስመ ሐረገ ወይን ጥሉል ወአስካለ ጥሉል ወይን ።
ኬብሮን በዳዊት ወዳዊት በኬብሮን ።

፳፪· ሠረዝ መንገድ (ዘአምላኪየ)

ደመና ዘቆመ ቅድመ ገጸ ሙሴ በሲና ።
ወበታቦር ቅድመ ገጸ ወልድ ዘቆመ ደመና
ምውቅ አኮ ጸዋሬ ምውቅ መና ።

፳፫· ድርብ ሠረዝ መን (ሥላሴ ቅኔ)

አስተብጽኡ ነፋሳት ዓሣ ኢየሱስ ወጴጥሮስ ወሩፋኤል ባሕረ ጥብርያ
ዶስ አኮኑ አመ ኢየሱስ ወፈረ ።

www.ethiopianorthodox.org

በሕዳጥ ዓሣ አጽገበ ማኅበረ ።
ወእምከርሠ ዓሣ አውጽአ ጸባሕተ ቄሣር ዲናረ ።
መሠግር ጴጥሮስ አመ አሥገረ ።
ሩፋኤልኒ ሥራየ በዘአእመረ ።
በዓሣሁ አኅየወ ዕውረ ።

፩፬· እጹብ ፍና መን ፤ ( ከመሪ ጌታ ዓምደ ብርሃን )

ምሥጢረ ሥላሴ ማዕድ ለእመ ተሠርዐ
ዓምደ ብርሃናት ዳንኤል ጠቢብ ወመፈክር ፤
ዘዘእደ ቶማስ ቶማስ ዘዘደማስቆ መንበር ።
ዘዕዝነ ባስልዮስ ባስልዮስ ለኪሶን ገሞራ ሶርያ ጠፈር ።
ዘልቡና ቄርሎስ ቄርሎስ ዘዘኢሳይያስ ኄር ።
ዘቴዎጐሎስ ሰማርያ ዘኃይለ አዴር ማኅደር ።
ተጸንሰ ኢተጸንሰ ነጸረ ይኔጽር ።
ኀብረ ቀመ ኢየኀብር ።
ገሠሠ ኢገሠሠ ኢያእመረ የአምር ።

፩፭· ጉት መንገድ ( ከሰይፈ ሥላሴ ዮሐንስ )

በዘእምዘ ኮነ ብሂለ ብሂል ኃይለ ሥላሴ አብርሃም ደብረ ዘምድረ
ከነዓን ሐዳስ ።
ነሥአ ኢነሥአ ለይስሐቅ ሞገስ ።
ኃይለ ሥላሴ አብርሃም መንበረ ንግሡ መቅደስ ።
ጽርሐ ቤተ ንጉሥ ኢዮስያስ ።
ሀሎ ግእዛን ካህነ መንፈስ ።
ኢሀለው ግብርናት መብእስ ።

፩፮· ፍና ተሳልቆ መንገድ ፤ ( ጉባኤ ቃና )

ለዋሕድ ወልድ እንተ አልቦቱ ዘቦቱ ፤
እመ ባሕርየ አብ አብ ግዘፈ ሥጋ አልቦቱ ። ( ከሊቀ ኅሩያን ዘገየ )

፩፯· አገባብ ድርድር ፤ ( ጉባኤ ቃና)

ጠየቀ ጴጥሮስ እምነ እግዚኡ ዋሕድ ።
ከመ ከመ ፀሐይ ወንጌል ወከመ ከመ ቅብዕ ካህድ ። ( ከሊቀ ኅ/ ዘገየ)

፩፰· እርካብ መንገድ ፤ ( ጉባኤ ቃና )

ኢያሱ ኃይልከ ዘተጋድሎ ሱላሜ ።
ቅጽረ ኑፋቄ ነሠተ ወልደ ኢየሉጣ ዘሮሜ። ( ከሊቀ ኅ/ ዘገየ )

www.ethiopianorthodox.org

፳፱. <u>እርከን መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ኪሮስ እግር ዘተጋድሎ ኢያሱ
ዘወንጌል ከነዓን በጽንፈ ቀኖና ያንሶሱ ። (ከሊ. ኅ. ዘገየ)

፴. <u>አበላላጭ መንገድ ።</u>

ምስያጠ ዓመፃ ዓለም ሕጽጽተ አእምሮ፡ኢረከብነ ብኪ ረብሐ ሥጋ ወነፍስ።
አምጣነ ኅዳጥ ሴጥኪ ወመድሎትኪ ንዑስ ።
ዓዲ በላዕለ ዝንቱ ጥዒናኪ ደዌ ወፍቅርኪ ባዕስ ።
እምዝኒ ዘይብዕስ ፤ ዘረከበኪ ይጼአር ወዘኢረከበኪ ይጼነስ ።
ንሕነሂ ኢንጸወን በደብረ ጽዮን ሐዳስ ፤
ጽዮን ለርእሳ ጸወነ ተጋሥሥ ።
ወበውስተ ሰማይ ኢንግበር ማኅደረ ሥጋ ወነፍስ ።
ሰማይ ለርእሱ ምስለ ምድር ይደመሰስ ። (ዘመምህር ጽጌ)

፴፩. <u>ዘሎ ገባ መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ጸግበ ወልድ ከርሠ ማርያም ረኃብ ።
ነጸሬ ተሰቅሎ መዓረ ጣዕመ ባሕርዩ ለአብ ። (ከሊ. ኅ. ዘገየ)

፴፪. <u>ጭፍን መንገድ ።</u>

ጨሜዎስ ሐንካሰ አዕይንት ክልኤቱ
እምነ ሐዊር ብርሃን በግበ ኢሐዊር የአቱ ።

፴፫. <u>ቅጽል አወዳደቅ መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ልሂቅ ጴጥሮስ ማእምረ ነሣኢ አዛበ
ገብረ አብ ረድእ ንሥሐ ልቡና ጥበበ ።

፴፬. <u>አመጸኛ ዳኛ መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ማርያም ወይን ስኩራነ ነገሥት ሥላሴ ፤
ህልወ ፍቅረ ሰብእ ጣዕም ጥዕምተ ልሳነ ውዳሴ (ከሊቀ. ኅ. ዘገየ)

፴፭. <u>መደንግፅ ሥራና መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ሐና ድንግል ዘእምዘ ተረከበት ሐና
ሥላሴ ቅድስት እምነ ቅዱስ ሕልቃና ።

፴፮. <u>ባዕድ መንገድ ።</u> (ጉባኤ ቃና)

ረኃብ ኪራም ዘገብሮ ለቴዎድሮስ ሕንባበ
አእመሮ ለዮሴፍ ኬንያ ማርያምሃ ጥበበ ።

www.ethiopianorthodox.org

፵፯. ጉበኛ መን ። (ጉባኤ ቃና)

አመ ርእየ ሰይፈ እንተ ይከውን እራቀ
ኢክዱነ እስናን ቶማስ ከመ ሕፃናት ሰሐቀ ።

፵፰. የዘመድና ባዕድ ዝርዝር መንገድ ። (አጭር ዋዜማ)

በዕፀ ገዳም ቀራንዮ እንተ ሐነፀ ማኅደረ
መለኮት አሐዱ ፈጠሮ ፍጡረ ።

፵፱. ሥራና መንገድ ። ( ዘአምላኪየ)

እግዚአብሔር እግዚእ ለእግዚአብሔር ኬፋ
ስብሐተ ማኅጼ ወሀቦ ለተስፋ
አምጣነ ወሀቦ ስብሐተ ማዕዶ ዘመልአከ ሐሰት ገደፋ ። (ከሊ. ኅ. ዘገየ)

፶. ቅጽል ከምሳሌ መንገድ ።

ምናነ ማልኮስ ሰይፈ ተስፋ ሕፃናት ፤ ኢትኅድጉ ሕዝብ ዕዝራ ወኤልያስ
አኮኑ መጥባሕት ተስፋ ዮሐንስ ፤ ትበቁዕ ለሥጋ ወዓዲ ለነፍስ ።
ወይኤምኀዋ በጽባሕ ሊቃውንት ዘደም አዕጋር ሕዝበ ቶማስ ።
ትትረአይሂ እምርኁቅ ከመ ማኅቶት ሐዲስ ።
ጳውሎስ ዘሠአላ ተመትሮ ቤተ መቅደስ ።
ወተሳለምዋ ይስሐቅ ወገላውዴዎስ ።
በበዓለ ዮሐንስ ተጋድሎ ወበዓለ ዓቢይ ፋሲለደስ ።
(ከመሪጌታ ዓምደ ብርሃን)

፶፩. ግሥግሥ መንገድ ። ( ዘአምላኪየ)

ለዘ ለዘ — ለሞት ሰሎሞን ፤ ወልደ ቤርሳቤሕ አንግሦ ።
ዳዊት ይሁዳ መአብስ ሄሶ ።
ናታን እድ ተግሣፀ ልቡና ሐንከሶ ።

፶፪. የዘመድ ዳኛ መንገድ ።

በቀለ ኬፋ ወሳውል አሠረ ኑፋቄ ደምሰስከ
አማኑኤል ሙሴ ዘጽድቀ ነሣእከ
አኮኑ ግፉዓ ሃይማኖተከ ገሠፅከ ።

፶፫. ገስጋሽ መንገድ ። ( ዘአምላኪየ)

አመ እንዘ ይሬኢ ሰይፈ አርዌ አመፃ ኃይሎ
ጳውሎስ ፈራሀ ልቡና ለገጹ ከለሎ
አንሥአ ጴጥሮስ ካልዑ በትረ ሃይማኖት ተሰቅሎ ።

www.ethiopianorthodox.org

፺፬. <u>አትሮንስ መንገድ</u> ። (ሚበዝኍ)

ንጸሬ ዓይነ ጴጥሮስ ንስር ወንጻሬ ልዮን ቋዕ ነጸረ ኢነጸረ
ተዋሕዶ ሥጋ ወቃል ወኩነተ ቋዕ ኅሡረ
አኮኑ ይጸልእ ክልኤ ግብራተ ወኩነተ ንስጥሮስ ሠምረ ።

፺፭. <u>ሑረተ ንህብ መንገድ</u> ። (ሚበዝኍ)

ዓይነ ዘዘሖረ ነግህ ጸራቅሊጦስ ሄኖክ ዘእምዘ ሱቱኤል ንጽሕ ።
ሀሎ ተንሥአ ኬፋ ገነተ በርህ ፤
አስተርአየ ሳውል ዕብራዊ ነጸሬ መልክአ ገጹ ለኖኅ (ከሊ.ኀ. ዘገየ)

፺፮. <u>ዙር ተዛወር መንገድ</u> (ሚበዝኍ)

ርኅወ ሰማይ ጸላዕተ ጽርሐ ተጋድሎ ዳዊት እንተ ኢሐመ ዘሐመ ።
አቤሴሎም ኪሮስ በዘተኀትመ ኀተመ ።
አቤሴሎም ኪሮስ ዘበዘሀሎ ጸላዕት ቤተ መንግሥቱ ኢኖመ ።

፺፯. <u>ግጭት መንገድ</u> ። (ሚበዝኍ)

ዘመነ ዘመኑ ለናየስ ዳዊት ሰሎሞን ዘመነ ሰሎሞን ተክለ አልፋ ።
ነጸሬ ሳሙኤል እምላክ ሳሙኤል ዘመሴፋ ።
ዘእምወልደ ይስሐቅ ይስሐቅ ያዕቆብ ያንሥእ ተረፈ ፊንሐስ ሐገፋ ።

፺፰. <u>መከታ መንገድ</u> ። (ሚበዝኍ)

ገብረ መርዓዊ ዳዊት ኀዳጌ ጳውሊ ኢዮአብ ብእሲተ ምግብናሁ ።
ወሐዳጌ ባዕድ ብንያም ፍትወተ ምልክናሁ ።
ጳውሊ ኢዮአብ ፍቁረ ዮናታን ወልድ እንተ አፍቀሮሙ ናሁ ።

፺፱. <u>ወርቅ ፍስ መንገድ ፤ (መወድስ ቅኔ ከሰ. ሥላሴ ዮሐንስ)</u>

ኵላ ብእሲት ከመ ብእሲት ፤ እስከነ እንግዳ ይመጽእ ወየኀድር ውስተ
ቤት ።
ወኵሉ ማኅፈድ እስከ ይመጽእ ክረምት ።
እንግዳሰ ሶበ ተአንገደ ተኃፍር ብእሲት ።
ዘአኮ ከመ ብእሲት ወሶበ ክረምት ይደምፅ ነውረ ማኅፈድ ይትከሠት
ዘንተሂ ናስተሐይጽ እምትውልደ ዓለም እሉት ።
ኵሉ እስመ ጻድቅ ወኵሉ ዘሃይማኖት ።
እስከ ከመ ነግድ ይመጽእ ለአሥምሮ ጽድቅ መሥዋዕት ።
ወርቀ ሃይማኖት ዘይፈትን ክርስቶስ ነደ እሳት ።

www.ethiopianorthodox.org

### ፺. አረሳሽ መንገድ ።　(ሚበዝኍ)

ኀልወ ኤሊ ኤልያስ ቢጸ ቢጸ ሮሳ ለራሄል መርኬዛ ገብረ መርዓዊ ።
ሐና ሜልኮል ሳሙኤል አረጋዊ
እስመ ነሥአ ራሄል ወሐና ዘነሥአ ፍዳ ሕይወቶን ማኅየዊ ። (ከሊ. ኅ. ዘገየ)

### ፺፩. እግር ብረት አታላይ መንገድ ።

ባህለ ዘዘሐማ ኢዩኤል ጸዋሬ ጸወርት አስዋከ ሐፃውንተ እለ ብርት
ፆታ አጋግ ባኦስ ወኤሊ መስቀለ ሞት
አልጸቀ በጽሐ አማኑኤል ናታን ጸዋሬ ፍትሐ ሞት ዳዊት ። (ከሊ.ኅ.)

### ፺፪. አጭር ግጭት መንገድ ።　(ሚበዝኍ)

መሐፔለ ፈርዖን ማይ ፤ ጋይደ ጋይዱ ለቂርቆስ መልአከ መላእክት ሐራ
ዘመደ ዘመዱ ለሮቤል ሰዶም ወገሞራ ።
ዮሴፍ ሎጥ መልአከ ማያት ዮናስ በምሕፃበ ደቂቅ ነከራ ።

### ፺፫. ሰምና ወርቅ መጽሔት መንገድ ።

በሃሌ ብሂል እግዚእ አደወ ሞተ ቤተ ትእማን መሬታዌ
መቃብረ ዮሴፍ ዮሴፍ ዘወጽአ እምህላዌ
ወርቀ ፍሥሐ ተረክበ ጊጋር ሰብእ በነጽሮ ኃይል ነነዌ ።

### ፺፬. አሳሳፊ መንገድ ። (ሚበዝኍ)

ንግሠ ህላዌሁ ለኪሮስ ንግሠ ቃል ሰሎሞን ሰሎሞን አስተዳለወ
ዳዊት ጳውሎስ ዘዘይጸልዓ ፊተወ ።
እስመ በእግሩ ለይስሐቅ ወላዴ አብርሃም ወልድ ወልደ ተባርኮ ሀለወ ።

### ፺፭. ወጭ ወራጅ መንገድ ።　(ሚበዝኍ)

ተክለ ዕፀ ገነት ኤልያስ መዓዛ ወይኑ ለሴሬቅ ኤፍሬም አስካለ ኬፋ ።
ፍና ኢያሪኮ ሐውልት ዕንባቆም ተክለ አልፋ ።
ዘእምነጽሮ ዓይን ወልብ ነጽሮተ እግሩ ይቀውም በፍኖተ ኤልያስ ተስፋ።

### ፺፮. የብሂል አደናገር መንገድ ።　(ሚበዝኍ)

በሃሌ ኩነቱ ለሰብእ ብሂል ገብርኤል እሳተ ኩነት ላዕላዌ ።
መጽአ መጽአ ገብርኤል ላእከ ነነዌ ።
ምሁረ ኢምሁር ዮሴፍ ብእሲ መዓተ ነገረ ብዙኀ ምንሳዌ ።

www.ethiopianorthodox.org

፶፯. ዘር ተመለስ መንገድ ። (ሚበዝኁ)

ሰይፈ መዓቱ ለአብ ነደ ዘዘሔራን ኢዮአብ ወሐማ ደቂቀ ነዌ ።
መገብተ ጸዋሪ መስቀለ እሳት ጸረ ነነዌ ።
መርዶክዮስ ዮናስ ተአዘዙ ገብሩ ደቂቀ ቤቱ ለአርዌ ።

፶፰. ጠፊና አጥፊ መንገድ ። (ዋዜማ)

ዜናከ ጼና ማይ፤እስመ እንዘ ርእሰከ ዳታን ቅኑተ ቅናት ፍቅር ።
ልብሰከ ቆሬ ነደ ነድ ባሕር ።
እስመ ንብረትከ ቅብዕ ፀሐየ ፀሐይ ቁር ።
እምንብረተ ቤቱ ለኢዮብ ምቱረ እእጋር ።
አይሁዳዊ መሰግል ዘምድር ። (ከሊቀ. ኅ. ዘገየ)

፶፱. ሠረገላ መንገድ ። (ዋዜማ)

ለብሰ ወኢለብሰ፤አርከ ልበ ቶማስ ቶማስ ሐዋርያሁ ለሙሴ
ኤፍሬም ካልኡ ለኤፍሬም ምናሴ
እንተ ኢየሐልቅ ጥቀ ትምህርተ ሕይወቱ ለአውሴ
ወዘኢየሐልቅ ጸምረ ልብሰ ቅዳሴ ።
ተአሚኖ በኄራን ሥላሴ ።

፷. ተመላላሽ መንገድ ። (ዋዜማ)

ፍቅርተ ላእከ ሞት ዘተጋድሎ፤ዘዘቴዎድሮስ ኃይል እንተ ወልደ አዴር ሐማ።
ፈጸመ ፈጽሞ ፈጽሞ ፈጸማ ።
ኢዮርብአም ባዕድ አምልኮተ ባዕድ ዘማ ።
ኢያእመረ ሄኖክ መልአከ ራማ ።
በየማኑ ልቡና ያቅማ ።

፷፩. ተቀባባይ መንገድ ። (ዋዜማ)

ተመይጠ በዘተመይጠ፤ፍዳ ቤተ አርዌ ሶርሶር ክፍለ ስልሞናስር አርዌ
ለኪሶን ይሁዳ ፍዳ ዓቤል ደዌ ።
ሕፀፀ ሕፁፃን ዘልዮን ቤተ መራእዩ ለነዌ ።
ሥጋ ወቃል ሕዝበ ምንታዌ ።
እስመ ቆመ በዋሕድ ህላዌ ።

፷፪. እግር በራስ መንገድ (ሚበዝኁ ቅኔ ከሰይፈ ሥላሴ)

እግረ ዘዮናስ ጴጥሮስ ግዱፈ ግዱፋን መስቀለ ማዕበለ ባሕር ቀራን ንዮስ ።

www.ethiopianorthodox.org

ነገደ ጳውሎስ ፍቅር ወተሰፋ መስቀል ርእስ ።
ተገድፈ ወድቀ ዮናታን ይስሐቅ እሡረ ፍቅረ ቢጽ ነፋስ ።

## ፷፫. የብሂል ሠረገላ መንገድ ፤

ብሂል ኢያእመረ ለትጹን ነቢይ ግብረ ሠናየ ዝክር ይሁዳ ።
ወብሂል አእጹቀ ወይን ጽቡረ ኤዳ ።
ብሂለ ኢይለብስ ባሕር ክለሜዳ ።
ኀበ ጸንዓ ማዕበል ፍዳ ።

## ፷፬. የውስጠዘ አደናግር መንገድ ። (ዋዜማ)

ከሃሌ ኢክሂል አክርጾታ ፤ ለርስሐተ ሥጋ ጸሊም መሐፒለ ዕድ ሕንጻጼ
በዘእምዘ አልቦ ያዝያን ሐራጼ ።
ዓይነ መርኬዛ ዘሮጌል አንቀጸ ቴዳ ኢዮጼ ።
መሳክወ ቤቱ ለኢዮብ ከመ ሰራጼ ።
ድኅረ ሄጸ መርዓዌ አክራጼ ።

## ፷፭. ጭፍን መንገድ ። (ዋዜማ)

ቶማስ እውረ እግር ፤ እምረዊጽ መጥባሕት በዘባነ አእዱግ ወድቀ ።
ወበልዮን ቢጹ ሐፊሮ ሰሐቀ ።
ፍዳ ዘርእየ ንስጥሮስ እንተ ለርእሱ ኢያቀ ።
ወበመሪሆቱ አዕዱግ እምትረት አልጸቀ ።
በትንሣኤ ከመ ይኅሥሥ እርቀ ።

## ፷፮. የዘ መከታ መንገድ ። (ዋዜማ)

በዘእምዘ ቶማስ ኢያቡስቴ ፤
ዘበዘከርካዕ ያዕቆብ ምዑዘ ሞዑዛን እምርሂ ።
በለስ ዕዝራ ወአውልእ ዮዳሂ ።
ሠወራ ሠወረ ኑፋቄ ማኒ ሳቡሄ ።
አልጸቀ በጽሐ ዘበ ዮፍታሔ ።
አስተርአየ ጽጌ ወይን ሰባሔ ።

## ፷፯. አጥፌ ለሚ አልሚ መንገድ ። (ዋዜማ)

ኮከበ አሕዛብ እሳተ ማይ ፤ እንዘ ቂርቆስ ነድ ነፋሰ ነፋስ ጢስ ።
እሳት ዓይነ ዓይን ጢሰ ጢሰ ጢስ ነፋስ ።
ወለእመ ቂርቆስ ወርቅ እሳተ እሳት ክርስቶስ ።
ሃይማኖት ማይ ተክለ ተክል ሐዲስ ።
ከመ ሙሴ ዕብነ ዕብን ሐንካስ ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፰. ሥርጽ መንገድ ።     ( ዋዜማ )

ግሩማን መላእክት ፤ ባሕርየ ነፋስ ወነድ እስመ እንዘ ፍሉጥ ገዳሙ ።
ለኪሩቤል ባሕርየ ሥላሴ ተፈልጦ አልቦሙ ።
ድኅረ በዕዝራ ወሄኖክ ብሔረ ሕያዋን ተስይሙ ።
ወጠቢብ ሰሎሞን በዞረ ዚአሆሙ ።
ኢያእመረ ኅዳጠ ግብሮሙ ።

፳፱. ገስጋሽ ኅቡእ መንገድ ።

ገይበ ዘጳውሊ ፤ መቃርዮስ ኮነ ዘእንጦንዮስ ባሕታዊ ።
ገረመ ዘሙሴ ዮሐንስ ዜናዊ ።
እስከ ከመ ኖኅ ተክፍለ ዘኢሳይያስ ሌዋዊ ።
እምኅበ ሕይወት ወሞት ተፈናዊ ።
ለጠይቆ ገጸ ሰብእ ሥጋዊ ።

፴. አንቀጽ ድርድር መንገድ ።

ተሰብአ ተዋረደ ፤ ዘዘኢያስተርአየ ነግሀ ኢያስተርአየ አግዘፈ ።
መለኮት እስመ በዕድሜሁ ተዐውቀ ተጽሕፈ ።
እመ ከማሁ ለሄኖክ ኢተዘከረ ኀለፈ ።
ወለእመ ተንሥአ ወድቀ ተሰብሐ ተርፈ ።
ድኅረ ጸረ ተረከበ ተገድፈ ።

፴፩. ግጭት አታላይ መንገድ ።

ለጌርሳም ተላዊሁ ፤ ፍና ፍና ጌርሳም ጌርሳም ፍና ኅቅለ ጌርሳም ነፍሱ ።
ለዘጌርሳም ዕፀ አስተፍሥሐ እርከ ዕፅ ያንሶሱ ።
ሥርወ ሥርወ ግያዝ ግያዝ ሥርወ ተዋርዶ ሞገሱ ።
በዘኅቅለ ጋቤር ጋቤር ማኅደረ ንግሡ ።
ኢገፍአቶ ገፍአቶ ኢያሱ ።

፴፪. ሰም ወራሽ መን. ( ሥላሴ መጽፈያ )

ኀበ ገብረ ኢዮብ ከብካብ ደዌ ።
ዘአፍአ ይከውን ውሳጣዌ ።
ወዘውስጥ ይከውን አፍአዌ ። ( ከሊቀ ኀሩያን ዘገየ )

፴፫. ስንሰለት መንገድ ። ( ሥላሴ ቅኔ )

በዘኮነ ቀራንዮ ፤ ማዕከለ ትርብዕት ስቅለተ ሐማ ስቁለ
መርዶክዮስ አስቴር ወስቅለተ ስቀለት ዘሙሴ ።

www.ethiopianorthodox.org

አርዌ ብርት አርዌ ዓምደ ብረት ምናሴ ።
አቀብተ አቀብቱ ለኖኅ ሐመረ ተርሴስ ብናሴ ፤
እንዘቦ በአይኅ ዕብነ ቅዳሴ ።
ፀሐየ ምልክና ባቢሎን ገጸ ሥላሴ ።
እመ ኮነ በመስቀል ድምሳሴ ። ( ከሊ· ኀ· ዘገየ )

፸፬· <u>ተያያዥ አታላይ መን·</u> ( ሥላሴ ቅኔ )

ተረክበ ቃለ ብሂል ፤ ይብል ዮሐንስ ልሳነ ወርቅ ይብል ልዮን ነባቢ
ጽእለተ ዲዮስቆሮስ ባዕድ ።
ይብል ማኒ ዘአልቦ ዘመድ ።
ይብል መርቅያን ሰማዒ ቃለ መቅዶንዮስ አብድ ።
ይብል ንስጥሮስ መምህረ ካሀድ ።
ይብል ዮሐንስ መምህረ ውሉድ ።
ኢተረክበ በድንግል ልማድ ።

፸፭· <u>ጉቶ መንገድ ።</u> ( ሥላሴ ቅኔ )

በዘእምዘ ሀሎ ብሂል ብሂለ ብሂል ቴዎድሮስ አቤሴሎም ገጽ ዘቴዎድ
ሮስ ዳዊት ።
ርእየ ኢርእዮ ለሰዶም ቀኖት ።
ቴዎድሮስ ሎጥ ቴልጌል ቴልፌልሶር ሞት ።
ላእከ ሦርያ ነደ እሳት ።
ተረክበ ራእሶን መልእከ ሐሰት ።
ኢተረክበ ሕዝቅያስ ሰማዕት ።

፸፮· <u>ዛንጀር መንገድ ።</u> ( ሥላሴ ቅኔ )

ኮነ አሜከላ ፤ ነገሩ ለስምዖን መስግላዊ ዘይመስል ያፍ ጸዓዳ ዘውሳጤሁ
ጽልመት ።
ወጸሊመ ዓሣ ዘውስጡ ሞሠርት ።
እመ ከማሁ ለሰዶም ዘዘለያቲሁ እሳት
ልሳኑ በሊህ እንተ መጥባሕት ፣
አምጣነ ልቡ ጽኑዕ ዘአልቦ ፍርሃት
ኢያእመራ ለናእስ ኂሩት ።

፸፯· <u>ክፋይ ግጭት መን</u> ( ሥላሴ ቅኔ )

መአንስሰ መአንስሰ ፤ ኢመአንሰሰ መአንስስ መእንሰስ ሞተ ኅብረ
አቤል በለስ ።
ሥርወ ደም ኢዮርጌ ደመና ነፋስ ።

www.ethiopianorthodox.org

ኬፕሮ ኬፕሮ ጋውሎስ ያቀ ኬፕሮ ጋውሎስ ክርስቶስ ።
ኬፕሮ ኬፕሮ ጋውሎስ ጋውሎስ ።
ጋውሎስ ያቀ በኤዶምያስ ።
ኢመዋቲ ኤዶምያስ መርስ ።

፸፰· ዘማች መንገድ ። ( ዘይእዜ ቅኔ )

ጌጸሁ ለአውናን ጌጸ አውናን ፤ ጌጸ አውናን አውናን ጌጸ ጌጸ አውናን ጌጸ ።
ጌጸ ጋዜር ጌጸ ኖኅ ጌጸ ጌጸሆሙ ለዘቦ ምጉንጸ ።
ምጉንጸ ጌጸ ጋይራስ ምጉንጸ ጋይራስ ቀለጸ ።
ኀቅለ ቀለዮጸ በጋዜር ኀበ ኤርጸጸ ።
አንስቲያ ታቦር ቃል ኀበ አክርጸት አግሪጸ ።

፸፱· ጅብ ሲወጉ በአህያ ይጠጉ ፤ መንገድ (የመወድስ ለዓለም)

እመኒ አስተርእየ ጽጌ መቅደንዮስ ባእስ ።
ምሉዓ ምልዕት ተደንግሎ ማርያም መንፈስ ቅዱስ ።
እንዘቦ ኢርእየ ገጸ ቄርሎስ ንጉሥ ።
ምኑነ እንተ ፍቅር ሰሐበቶ አምላክነ ንስጥሮስ (ከሊ· ጎ· ዘገየ)

፹· እባብ ያየ በልጥ ይሸሻል መንገድ ፤

አንተሰ ወልደ ዮና አጽቀ አቤሜሌክ ወይን ።
እስመ እምሐዊር ፍና ነጽሮ ሰማየ ሰማያት ፍኖተ ዓይን ።
ወእምነ ሐዊር መስቀል ፍኖተ አማኑኤል ዕብን ።
ዕውራን አእጋሪክ ወአዕይንቲክ ሐንካሳን ።

፹፩· ልብሰ ወርቅ መን (የመወድስ ለዓለም)

እወል ድሂ በድምፅ እንዘ ኢይዘርእ ዘርዐ ።
እልፈ አራዊተ ወእልፈ አባግዐ ።

፹፪· ጉብኛ መንገድ ።

ዘርአ ወራዙት ንባበ እመ ኢያጽምዓ ዕዝና ።
እሳት ዘተአርቀ ለብሰ እምክዳና ።

፹፫· ርቀት ልብሰ ወርቅ መን (የመወድስ ለዓለም)

በዝኃሂ ወፈድፈደ ንዴተ ወልዳ ስሉጥ ።
ስብአ ወአግማለ እስመ በዘሠምረ ይዌልጥ ።
ወእምነ ምስያጥ ኃይል ኢይትፈለጥ ።
ያበውእ እንተ አፍአ ወያወጽእ እንተ ውስጥ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፹፩. ሰም ረገፍ መን. (የመወድስ ለዓለም)

አብርሃምሂ ብዝኃ አርምሞ እንተ ነበረ ምስሌሁ ።
ወጽአ እምሀገሩ ወፍሉጥ እም አዝማዲሁ ።
ሆሳዕና ዳዊት ይስሐቅ እንተ ፈድፈደ ጺጋሁ ።
በያዕቆብ ዕብነ ደብር አምጣነ አኅደረ ቡራኬሁ ።

## ፹፪. ሰላጢን መንገድ ።

በአስተዳልዎ ጥበበ ማዕደ ሥላሴ ፤ ሊቀ ኀባዝያን አብርሃም ጠቢብ
ወማእምር ፤
እንተ እንተ ፈቀደ ገብረ እግዚአብሔር ።
እግዚአብሔር እንዘ ይብል ፤ ትጥዕም እምዙሉ አእምሮ መዓር ።
ጣዕማ ጣዕመ ሀሊብ ወልደ ነጐድጓድ ዳንኤል አልቦ በፍና ግብር ።
ጥበብ ሕልመ ነጋሤ ኢየሐውር በእግር ።
ከመ ናአስ ተክለ አልፋ ሐዊረ ኢሐዊር ኢየሐውር ።
ባሕረ ጥበባት ዮሴፍ እንዘ ፍሉጠ ባሕር ባሕር ።
ወከመ ከመ ዕብን ኢለባዊ ሰሚዓ ኢሰሚዕ ኢይትናገር (ከሊኅ ዘገየ)

## ፹፫. ፍና እቅፍት መንገድ ።

ባሕርየ ዘዘቦ ዘቦሙ እንተ ሀለወት ፤ ዘቦ ዘቦሙ ድንጋሌ ድንግል
ምልክና ።
አጋእዝተ ኪሩብ ኪሩቤል ንጽሐ መላእክት ሐና ።
እምኤልሳዕ ካልዑ ኤልያስ ሕልቃና
እሥራኤል ሕዝበ ዮና ፤ ኤሊ ንጉሥ ገዓረ ቃለ ሙሴና ።
ሳሙኤል ቃለ ዓዋዲ እንተ ለሥጋሁ መነና ።
ኃደገ ግብረ ሥጋ ወኃለፈ እምወሰና ።
አምጣነ ገሠሥ መልአክ በሩጸተ አክናፍ ደመና ።
ኢይንበር ምስለ ኤሊ ኤልያስ ዘውገ ዮና ።

## ፹፬. እግር ብረት መንገድ ።

ጸዋሬ ጽንሰ ባዕድ ቶማስ ጽንሰ ደመ ሰይፍ ፤ ማኅፀነ ካህን ወርኅ ኮነ
ወኢኮነ ።
ጽንሰ መወልድ መዓልተ ዘዘ አጽመ ሮቤል ኮነ
ፀሐይ ጸዳለ መስቀል ዘኢኮነ ኮነ ።
ጽንሰ ከዊነ ቃል ማሕምም ወጸረ ፍትሐ ሞት ስምዖን ዘፍቁረ ኪራም ኮነ።
ወዮሐንስ አረጋዊ እንተ ከመ ኤርምያስ ኮነ
ንባበ መወልድ አስቆሮታዊ ጸሎተ ዕንባቆም እመ ኮነ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወጸሎተ ዕንባቆም ግፍዕ አመ ቀራንዮስ ኮነ ።
ፍዳ እንተ ቀድሐ ማየ ቃና ማየ ዕለተ ዓርብ እስመ ኮነ ። (ከሊቀ· ኅ· ዘገየ)

## ፻፰· ድርብ አሰናካይ መንገድ ።

እደ ቤተ ሦርሶር ስምዖን መሐፒለ ዘቦ ፤ አድራ — ማሌቅ ባኦስ ማኒ
ዘእምዘ ሀሎ ።
ወ . . . . . ት ሜልኮስ መሐፒለ ሐዊን እብሎ ።
ለኪሶን አክርጳተ ኤሊ ወፊንሐስ ጴተሎ ።
ኢዮራም ኢዮርብአም ሮቤል ሄኖክ መሐፒለ ዮሐንስ እብሎ
ሙሴ አምላከ ሙሴ መሐፒለ ቅብዕ ተከሎ ።
ሎምና ፀሐየ ሎምና ፈለገ ኢያቤስ ዘተኃጕሎ ።
እምተንከተመ አሴር አቤል አንጽሖተ አሴር ዘሎ ።
ለተንከተመ ኖኅ ኢያቡስቴ ሠረገላ ኤልያስ ይመስሎ ።

## ፻፱· ባዕድ አካሄድ መንገድ ።

ከብርተ ማርያም ሥዕል ፈጣሬ ሥላሴ ፤ እንስሳ ወስብእ ግብረ አብ
ዓፀደ ወይን ።
ዘእምነባቤ አፍ ጴጥሮስ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ዕዝን ።
ጳውሎስ ልሳኑ ለዮሐንስ ዓይን ።
ነጻሬ ኅቡዓት ይኔጽሮ ለበልዓም ሄኖክ ሚጠተ ጴዋዌ እግረ ብርሃን ።
ያከብሩ ማርያምሃ መካነ ጻድቃን ።
እስመ ቃለ ወልድ አጽምአታ ጽምምተ ዝናማት ልበ ዕብን ።
ወኢኮነታ ድንግለ እጼተ ማኅጸን ።
እስመ እመወሊድ ተክለ አልፋ ዘማዊተ ዓይን ትከውን ።

## ፲· ቅጽል ድርድር መንገድ ።

ፀዳለ ብርሃኑ ለበርሀ እንተ በርሀ በርሀ ፤ እንተ ዓይነ ዓይኑ ለክብር
እንተ ክብረ ክብሩ ለመአብስ ።
እንተ መርሀ መርሁ ለኤናግ ቄርሎስ ።
አብርሃም መቃሪ መቃርዮስ ርእስ ።
ሄኖክ እንጦንዮስ ኬፋ ዳንኤል ልብድዮስ ኢዮስያስ ።
ሶፎር ኢያቡስቴ ሞተ እስጢፋኖስ ባእስ ።
ምናሴ ሐረገ ወይን ይሁዳ አጽቀ በለስ ።
ዕንባቆም ኤልሳዕ ወልደ ዘካርያስ መርስ ።
ኤልያስ ተክለ አልፋ ተክለ ሃይማኖት ኢሳይያስ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፻፮· የልጅ ልጅ መንገድ ።

ገባሬ ግቡር ሰማይ ጽርሐ ኢየሉጣ ፤ እመ እመ ቂርቆስ ሲራክ ጥበብ
ሠርጐ አሚን ።
ዕዝነ ዕዝነ ሙሴ ባስልዮስ ወለተ አሜን ።
ዕዝነ ዕዝነ እዝኑ ለስምዖን ሐጺን ።
ሰሚዓ ኢሰሚዕ ቃለ ወለት ጸጋመ ሕልመ ኖኅ ዮሴፍ ድንግል እደ የማን ።
ገብርኤል እግረ እግሩ ለሩጸተ ጤሜዎስ ዓይን ።
ብርሃን ገጸ ፍና ሐንካሰ ሐንካስ ዕብነ ዕብን ።
ነጻሬ ኢሐዊር ውርዙተ መሳክወ ኢዮብ ዕዝን ።
ድምፀ ቃለ መብረቅ ወአንበሳ ኢሳይያስ ቃለ ቀርን ። ( ከሊቀ· ኅ· ዘገየ )

## ፻፯· ተከታታይ መንገድ ።

ሙሴ ወፈርዖን ከመ ተበአሱ ፤ እመ ጸብአ ልብ አንሥአ በቤተ ሥላሴ
መቅዶንዮስ ።
ተክለ ሃይማኖት ወክህ እንዘ ይለብስ ።
ልብሰ ጸብዕ ቅዳሴ እስከ እግር እምርእስ ።
ወለተራድአ መርቆሬዎስ ፤ ፈረሰ ዚአሁ ጸአነ ኀቤሁ ከመ ይጊሥ ።
ይርዓይሂ ከመ ተዘርወ ቀትለ መቅዶንዮስ ባእስ ።
ቆመ እምአንክሮ መልዕልተ አዕባን መንፈስ ቅዱስ ።
እስመ እንዘ ይረውጽ ወድቀ ላዕለ አርዮስ ንዑስ ።
ነፍሶ ዘኢያእመረ መቅዶንዮስ መአብስ ። ( ከሊቀ· ኅሩ· ዘገየ )

## ፻፰· ውስጠዘ ተራ ቅጽል መንገድ ።

ሥርወ አጽቀ ዘግባ አብርሃም ወላዴ ውሉድ ፤ ወላዴ መወልድ ውሉደ
ገብርኤልሃ ዜናዌ ።
ዕንባቆምሃ ሰማዕተ ተፈናዌ ።
ዳዊት ለባዊ ሙሴሃ ለባዌ ።
ይስሐቅ በዙረ ነዌ ያዕቆብ ኮል አማኑኤል ዕፀ ዘዌ ።
ዘበዘ መስቀል ጽላሎቱ ዘዓይነ አይሁድ አርዌ ።
ደንገፀ ኢደንገፀ ምሳሌ አርዌ ብርት ሥነ ሥጋዌ ።
አስተርአየ መጽአ በእግረ ያዝያን ደዌ ።
ዘበዘ ኢሳይያስ ተናገረ አልጸቀ አዜባዌ ።

## ፻፱· የአደናግር ሰረዝ መንገድ ።

አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ ፤ አዳም ወአቤል ወምሳሌ ሔዋን እም ።
እስመ እምወልዱ ለአብ ወልደ እንበረም ።

www.ethiopianorthodox.org

አብ ወወልድ አሐዱ አቡሁ ለሴም ።
ወመንፈስ ቅዱስ ወላዴ ካም ።
እንዘ ጥበቡ ሐመር ምዕላደ አርዌ ወላህም ።
ይትርፍስ ከመ ተነግረ ምሳሌ ዚአሃ ለቅድም ።
እምኤፍሬም ለምናሴ ማርያም ለማርያም ።
መሰለታ ትኩን ፍሥሐ ዙሉ ዓለም ።
እመኒ ኢይመስሎ ለአብርሃም አብርሃም ። (ከሊቀ ኅሩያን ዘገየ)

፻፳፫. ራስ ከብዶ መንገድ ። (አጭር ዙልክሙ)

እግረ ጴጥሮስ ሮጸ አንበለ ዋሕድ ፈረስ ።
በሩጸተ እግሩ ለሄኖክ ነፋስ ፤ (ኪሊ. ኅ. ዘገየ)

፻፳፬. ዘመድ መንገድ ። (ሕንፄሃ)

በንጹሕ ድንግል ለእንተ ወለደታ ወልደ ።
ማርያም አሐቲ — አፍቀረታ ባዕደ ።

፻፳፭. ዓይነ ወኃ መንገድ ።

ማርያም ከርካእ እንተ አሕመልመት ቈጽለ ።
ጸገየት ድንጋሌ ወፈረየት ቃለ ።

፻፳፮. የጋን መብራት መንገድ (ዕዝል ክብር ይእቲ)

ወልደ ዘዘጴጥሮስ ዮናስ ነጻሪ መገብተ መስቀል ምናሴ ።
አዕይንተ ፀሐይ ያዝያን ወአዛርያስ ብናሴ ።
ተዐደወ ገብረ እግዚአብሔር ሙሴ ።
ቆመ ገብረ እራቆ በጽንፈ ሀገር ሥላሴ ።

፻፳፯. የንዑስ አንቀጽ ሰረዝ መንገድ ። (ክብር ይእቲ)

ቀዲሖተ እሳት ማየ እንተ ዘለፋ ወጸዋሬ ዕፅ እሳተ ።
ለባዊ ዮሐንስ ነጻሬ ነጽሮ ክልኤተ ።
ከዊኖተ ምድር ሰማየ ወለቢሰ ብርሃን ጽልመተ ።
ተሴስዮ ጠሊ ወአድግ አንበሳ ወቀኒተ በግዕመ ጥባሕተ ። (ኪሊ. ኅ. ዘገየ)

፻. የብሂል እግርበራስ መንገድ ፤ (ክብር ይእቲ)

ብሂለ ብሂል ፀሐይ ሐዋርያ መዘምራነ ሰብእ ሥላሴ ።
ኢይሰምዕ ስመ ፍትሐ ግፉዓን ውዳሴ ።
ኢሳይያስ ወርኀ ዘፍኖተ ኮከብ ድምሳሴ ።
ኢየሐውር ሖረ በፍኖቱ ለመስተሣልቅ ምናሴ ።

www.ethiopianorthodox.org

### ፻፩. <u>ድርብ ወጭ ወራጅ መንገድ</u> ። ( ክብር ይእቲ ግዕዝ )

ትርጓሜ ሕልመ ፈርዖን ፈርዖን ዘውገ ቤተ አብርሃም አብርሃም ።
ላእከ ቤተ ይስሐቅ ይስሐቅ እደ ቤተ ዖዝያን ሴም ።
ፀሐየ ፀሐይ ዳንኤል ዘእምዘ ኤርምያስ ካም ።
ወርኃ ወርኃ ሮቤል ሕዝቅያስ ሮብዓም ።

### ፻፪. <u>ምንዝግዝግ መንገድ</u> ( ሕንዜሃ )

ኬፋ ላዕለ አይሁድ እሳተ ረዋጺ ነፋስ ።
ወአይሁድ በኬፋ አዕይንት ዘጢስ ።

### ፻፫. <u>አኀዝ አካሔድ</u> መንገድ ።

ምሑረ ምሑራን ሰማኒቱ ፤ አሥሩ ቃላት በወስኮ ሐምስ ሐምሳ ።
ምዕተ እሥራ ወምዕተ ሠላሳ ።
መምህረ ምሁራን ክብርት ዘትርጓሜ ሠላስ ስሳ ።
ለዘአዕይንታ አሥር ፍና ኃሠሣ ።
እምአእምሮ ሰሎሞን ኢሂሣ ።

### ፻፬. <u>የማስጠበቅ መንገድ</u> ። ( ሕንዜሃ )

እንከሰ ቀራንዮ ኢየሐውር እግዚእነ ።
እስመ ቀራንዮ ምድረ ደም ኮነ ።

### ፻፭. <u>ግሥ መንገድ</u> ( ዋዜማ ዘንቡረ ዕድ አበበ )

እምነ መጥቅዖሙ ለሠለስቱ ፤ ይሁዳ ወፋርስ አመ ቃለ ገብርኤል ዖደ
እሳት ዘመጠነ ደብር ውስተ ባሕር ወረደ
ወጢሰ መዓቱ ዘዓርገ እምነ ቀላይ አሐደ ።
ለፀሐይ ባቢሎን ከደና ገሃደ ።
ወአትለወ ድኅሬሁ በረደ ።

### ፻፮. <u>ኩሸት መን</u> ( የመወድስ ለዓለም )

ዕፁብሂ ለሰማዒሁ በቢታንያ ዘኮነ ።
ንጉሠ ዓለም ሆሣዕና በዲበ ዕዋል እስመ ተጽዕነ ።

### ፻፯. <u>ስሚ መንገድ (ቍልክሙ ።)</u>

ኒቆዲሞስ ሊቅ ወንጌለ መንግሥት ፤ እመንፈሳዊት ተዓቢ እም አሪት
እመ ሥጋከ ።
ሕማመ ሙሴ አሪት ለእመ ሐመምከ ። በሌሊት አኮኑ ትገይሥ ኀቤከ ።

www.ethiopianorthodox.org

ወንጌል እመ ነፍስከ ለእመ ተሐውር ድኅረ አሪት ወላዲትከ ።
ገነዝዋሂ ወቀበርዋ ለአሪተ ሙሴ እምከ
በሐዲስ ልብሰ ጸጋ ሐዋርያተ ወልድ አጻብኢከ ።
ባሕቱ ኀዘን በከመ ጳውሎስ ለከ ።
ለከልኤ እስመ ተከፍለ ኢሳይያስ ልቡናከ ።
ዘመነ ምናሴ ነቢይ አፍቅሮተ ልብ አምለከ ።
ለ፪ኤ እስመ ተከፍለ ኢሳይያስ ልቡናከ ። (ከመ. ጌታ ላዕከ ማር)

፻፳. ሙሉ ጎብር አማርኛ (መወድስ ።)

ረድኤት የራቀው ረኀብ የነዌ ተማሪ ፤ የሚቆጣው ሰው ባይኖር የተ
ማረውን መልክ አጠፉ ።
ጠላት ነውና ለእህል አርሶ እንዳገባ ሲደፉ ።
ደግሞም ተሐንፀት በመዝገብ እጅ ፤ ዓምደ ወርቅ ቅኔ የካህን ደገፉ ።
ደግሞ ያመጣል ጥቁር እንግዳ የተማሪ ልሳን እሳት ከአዳራሽ ሆኖ ሲያናፋ ።
መዝገብሂ የዳዊት ሎሌ ከጐጃም ጦርነት ሲጋፋ ።
ጉባኤ ቃና ሀብትሽ ይመር ተማርካ መጣች በዘረፋ ።
ወጥመድ ናትና ለሰው ምንም ከዲያብሎስ ባትከፋ ።
ፃእረ ሞት ጉባኤ ቃና በሥጋ የምታለፋ ። (ከመሪ ጌታ መዝገቡ)

፻፱. እጥፍ ድርብ ጎብር ።

የዘላን እመቤት ሥጋዬ ባልን የማታፍሪ ፤ ጻድቃን ያበሉትን ያህል
ዳዋውን ጠራርገሽ አንቺ አስወቃሽ ።
አሁን ምን ዳኛ አለ ይሆን ይኸን ጉድጓድ መላሽ ።
ደግሞም ባል ስትሺሪ አረሜን አይተሽ ።
በተራ ወጥሽ ምነው ለእንግዳ ፤ አሁን ዝግን ሁኖ ሊቀርብ አዳራሽ
ተሠርቶልሽ ።
ነፍስየሂ የቤት ወይዘሮ የምትሄጅው በሻሽ ።
ያሳስብሻል የማታ ራት መንገደኛውን ዓለማምነሽ ።
ወመሬታዊ ሥጋየ ይኸንን ለም አገር ትተሽ ።
እንዴት ይሄዳል ከተማሰው ካባ ጌጥ ብለሽ እንደኮራሽ ።
(ከመሪጌታ መርዓዊ)

፻፲. የፍየል ዓይን ወደ ቅጠል ፤ የነብር ዓይን ወደፍየል መንገድ ።

መወድስ ቅኔ ።

ሕዝብየ አሮን ልሙደ በዊዕ ፤ ቅድመ ናቡቴ ግፋዕ ግፍዓ ናቡቴ ደብተራ ።
አስቆቅዎትከ ምንት ሰቆቃወ ነቢይ ዕዝራ ።

www.ethiopianorthodox.org

በእለ ይፈቅዱ መከራከ ወይፈቅዶሙ ለእሉ መከራ ።
እምቅድመ ዝኒ እምብሔራ ፤ሰበ ወጽአ ሎጥ ዘመደ ናኮር ወ/ ታራ ።
አኮኑ ለነነዌ ኅበ ኢተሳተፈ ግብራ ።
ፈቃደ ገሞራ ኅበ ዝሙት ወፈቃደ እሳት ኅበ ገሞራ ።
እመኒ ኅሬ ኅለፈ እንዘ ይዴግንዎ ሐራ ።
ልበ ግብፅ መንገለ ኅሬ ወመንገለ ግብፅ ልበ ኤርትራ ።

አለቃ ኢሳይያስ( ጥንት የጐንደር ቅኔ ። )

## ፪፻፩· አፍራሽ መን· (መወድስ ።)

መድሎተ ፍጡራን መዓልት እንዘ ያጸንን ፤ሥእርት ይትበቀል ወኢ
ይከውን በቀለ ።
በእንተ አኃው ያውርድ ፍሬ ዕፀ ገዳም ቀትለ ።
አቤሴሎም በሥእርተ ርእሱ አኮኑ ተሰቅለ ።
ወኮነ ቀታሌሁ ለቀታሌ ነፍስ ሶምሶን ዘየዓቅብ መዋዕለ ።
ይተኃጐልሂ ምሳሌ ዝንቱ በከመ ተኃጕለ ።
በሥርዓተ ዕንባቆም መወድስ ዕንባቆም ተለዓለ ።
ዕንባቆምሃ ይፈኑ አምጣነ ወኃበ ቃለ ።
ሊቀ መላእክት ሀብተ ድንግል ዘይከይድ ነበልባለ ።( ከአለቃ ዕንባቆም)

## ፪፻፪· ትንቢታዊ መንገድ ፤ ( መወድስ እስከ ማንደርደሪያው )

ኃይለ ሥላሴ ኢታንክር እመ እቤለከ ፤ ርኢኩከ አንሰ ታሕተ ዕፀ
ሐረር ዓባይ ።
ሀለወከ ትዕርግ መንበረ ምኒልክ ሰማይ ።
ወብከ ዘተሐቱ በዕንቍ መንግሥተ አቡከ ሰሎሞን ባሕርይ ።

( አለቃ አርአያ ወረታ )

## ፪፻፫· የዘመድ ጭውውት መንገድ ።

ትቤ ልብየ ብእሲተ ቴቍሔ ፤እግዚአ ኃያላን ፍቁር እግዚእየ አድኅነኒ
እስመ ኅበ ቄድሮስ ሀብተ ቢጽ ፤ ለአከት ምሳሌ ሀብትየ አቃኒ ።
እምዙሉሰ ዘየዓቢ ተፈልጦተ አኃው አርድእት በበጊዜሁ የኀዝነኒ
እስርርሂ ወእእርፍ እምረኀበ ሥጋ ማሳኒ ።
ከንፈ ከመ ርግብ መኑ ዘይሁበኒ ።
ሀላዌ ሥጋ ጳውሎስ እስመ ይቤለኒ ።
እለ እስክንድሮስ ተሐምሞ ብዙኃ ሣቅየኒ ።(የአቡነ አብርሃም መወድስ)

www.ethiopianorthodox.org

## ፪፻፩. አጥላቂ መንገድ ።

ሥነ ጽጌ ረዳ ዓለም አንተ ትትነገሬ ፤ ወተኃልፌ ቅጽበተ አርአያ
ጽላሎት ወሕልም ።
እምነ አሐዱ አፉኪ አምጣነ ይወጽአ ዮም ።
ለፌ ቡራኬ ወለፌ መርገም ።
ወምንተ ይኤድም
ዘመነነኪ ሖረ መንገለ አስቄጥስ ገዳም ።
አነሂ አረማዊ እንዘ ክርስቲያናዊ በስም ።
ለለ ጽባሁ በኃጢአት እንዘ ጽንዓ ኃይልየ አደክም ።
ዘመንየ ኵሎ ፈጸምኩ እንበለ ጸሎት ወጾም ።
መዓልተ በመብልዕ ወሌሊተ በንዋም ። (የራስ ወልደ ገብርኤል)

## ፪፻፪. ምሳሌ መንገድ መወድስ ።

ጉልቄ ሕማማት እስፍንተ እዜንወክሙ ኦ አኃው ዘትነብሩ ምስሌየ ።
እስመ ከመ ርግብ እነብብ እመ እገብር ሥቃየ ።
ወሥእነ ነጽሮተ ገጹ ለፀሐይ ዓይንየ ።
ወእንዘ ኢይትቀነይ ለአምላኪየ
ዘመንየ ኃለቀ ከመ ዕፀ ከንቱ ላዕሌየ ።
ዮምሂ እመ ኃልቀ ዕፀ መከራ ሥጋየ ።
በመንፈቀ ሌሊት ያውእዩኒ አሳታውያን ሕማማትየ ።
ወእንዘ ኢየሐውር አንሰ ፍኖተ ወንጌል እምየ ።
ወሪደ መቃብር ወሞተ ሥጋ ይቀድሙ ለዕድሜየ ። (ራስ ወ/ ገብርኤል)

## ፪፻፫. ትችት መንገድ ።

ኦ መሬት ዘመደ ሥጋየ እም እመ ተፈጠርኩ አንሰ በይነ ዘኮንክኒ ምስማከ።
ወሀየንተ በላዕኩ እክለ እንተ በቆለ ዲቤከ ።
ዕዳ ሞት ፍዳ ኢይተርፍ ብከ ።
ባሕቱ ኢትጕጕዕ እስመ ጊዜ ጽኑዕ ሞትየ ሲሳየ ዕለት እከውነከ ።
ኅዳጠሂ ተዓገሠኒ እስከነ እመጽእ ለከ ።
እስመ አንተ ዘዚአየ ወአነ ዘዚአከ ።
ወበግብረ ብዙኅ ሥላቅ እመ ሀሎኩ ላዕሌከ ።
ቀዳሚ በይነ ያርከኒ ደኅሪ እፀውረከ ። (የመምህር ወሰኑ)

## ፪፻፬. ጉራማይሌ መንገድ ።

ንዒ ንዒ ጉባዔ ቃና ድመት
አምጣነ ተክዕወ ለኪ ልበ ተማሪ ወተት ። (ዘመሪጌታ አስካል)

www.ethiopianorthodox.org

ከዚህም ሌላ የቅኔ መንገድ በብዙ መልክ ይገኛል ፤ ለምሳሌም ያለ ቅኔው በጕት መልክ ብቻ የተገለጡትን ሰሞች እንደሚከተለው እገልጣለሁ ።

፩/ ተከታታይ ሠረዝ መንገድ ፤
፪/ ውስጠ » »
፫/ የቅጽል መንታ ሠረዝ መንገድ ፤
፬/ ሌባ ሠረዝ መንገድ
፭/ የማኅበር ሳቢ ሠረዝ መንገድ ።
፮/ የከመ ሠረዝ መንገድ ፤
፯/ ነጣቂ ነባር ሠረዝ መንገድ ፤
፰/ የቦታ ደርዝ መንገድ ፤
፱/ የስም » »
፲/ የግብር ስም ደርዝ መንገድ ፤
፲፩/ አጥፌ ደርዝ መንገድ ፤
፲፪/ ነጣቂ ደርዝ መንገድ ፤
፲፫/ የሠርፅ ደርዝ መንገድ ፤
፲፬/ ጠቃሽ ደርዝ መንገድ ፤
፲፭/ ፍና ድርሰት መንገድ ፤
፲፮/ ፍና ሐዲስ መንገድ ፤
፲፯/ ፍኖተ ሰርቅ መንገድ ፤
፲፰/ ፍኖተ መንበር መንገድ ፤
፲፱/ ነጠላ ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳/ እጽፍ ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳፩/ ያንድና የብዙ ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳፪/ የስም ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳፫/ የቅጽል ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳፬/ የጾታ ቅጽል ውስጠ ወይራ መንገድ ።
፳፭/ የአኃዝ ቅጽል ውስጠ ወይራ መንገድ
፳፮/ የወርቅ ውስጠ ወይራ መንገድ ፤
፳፯/ የራሱ የሆነ አጥፌ መንገድ ፤
፳፰/ ተመላሽ የሆነ አጥፌ መንገድ ፤
፳፱/ ነጠላ እግር ብረት መንገድ ፤
፴/ ድርብ እግር ብረት መንገድ ፤
፴፩/ አፍዛዥ እጥፍ መንገድ ፤
፴፪/ ዘማች መንገድ ፤

የቅዱስ ሩፋኤል ቤተ ክርስቲያን የግል ቤተ መጻሕፍት

www.ethiopianorthodox.org

፷፫/ ድርብ መንገድ ፤
፷፬/ ሥሉጥ መንገድ ፤
፷፭/ እግረ ፀሐይ »
፷፮/ ተመሳሳይ መንገድ ፤
፷፯/ ሠርፅ ሂያጅ መንገድ ፤
፷፰/ የወ ሠርፅ ተከታይ መንገድ ፤
፷፱/ መንታ ዘርፍ መንገድ ፤
፸/ የዘርፍ ዘርፍ መንገድ ፤
፸፩/ ምፀት ቅጽል መንገድ ፤
፸፪/ የስም ቅጽል ዘላይ መንገድ ፤
፸፫/ የስም አነጻጸር መንገድ ፤
፸፬/ ነጠላ ስም ቅጽል መንገድ ፤
፸፭/ የስም ቅጽል መንገድ ፤
፸፮/ የወርቅ ተራ ፍላፃ መንገድ ፤
፸፯/ የስም ነጠላ መንገድ ፤
፸፰/ የወርቅ ነጠላ መንገድ ፤
፸፱/ የትርጓሜ የዘር ግጭት መንገድ ፤
፹/ የዘ. አታላይ መንገድ ፤
፹፩/ ወራሽ መንገድ ፤
፹፪/ አረሳሽ መንገድ ፤
፹፫/ የዘ . ገፊ መንገድ ፤
፹፬/ ከጅ ልብሰ ወርቅ መንገድ ፤
፹፭/ የልብሰ ወርቅ ራስ ክብዶ መንገድ ፤
፹፮/ የአጸፋ ልብሰ ወርቅ መንገድ ፤
፹፯/ ነጠላ ጠቃሽ መንገድ ፤
፹፰/ የከመ መከታ መንገድ ፤
፹፱/ አፍዛዥ ጠቃሽ መንገድ ፤
፺/ የወ. መከታ መንገድ ፤
፺፩/ የዘ. እርከን መንገድ ፤
፺፪/ የአኩኑ እርከን መንገድ ፤
፺፫/ የዘ . እርካብ መንገድ ፤
፺፬/ የስም አነሣሽ መንገድ ፤
፺፭/ አሳዛኝ መንገድ ፤
፺፮/ ንባብ ለጋሽ መንገድ ፤
፺፯/ ቱማታ መንገድ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፷፰/ ምሥጢር አሳላፊ መንገድ ፤
፷፱/ ተደራቢ መንገድ ፤
፸/ የገቢር ሥራና መንገድ ፤
፸፩/ የተገብሮ ሥራና መንገድ ፤
፸፪/ አሳይቶ ሂያጅ መንገድ ፤
፸፫/ ተመላላሽ መንገድ ፤
፸፬/ አሰናካይ መንገድ ፤
፸፭/ አሰናካይ ማሠሪያ መንገድ ፤
፸፮/ አሰደንጋጭ መንገድ ፤
፸፯/ የወርቅ ዘርፍ መንገድ ።
፸፰/ ረጅም ዙር ተከተል መንገድ ፤
፸፱/ የስም ዘርፍ መንገድ ፤
፹/ ረጅም ወጭ ወራጅ መንገድ ፤
፹፩/ ተላላፊ መንገድ ፤
፹፪/ የስም ፍላፃ መንገድ ፤
፹፫/ እንሣሽ መንገድ ፤
፹፬/ አለምላሚ መንገድ ፤
፹፭/ የቅጽል ሥውር መንገድ ፤
፹፮/ መንታ ሠረዝ መንገድ ፤
፹፯/ የዘርፍ ወራሽ መንገድ ፤
፹፰/ የስም ዘርፍ መንገድ ፤
፹፱/ ጋራጅ መንገድ ፤
፺/ ተዐጋሚ መንገድ ፤
፺፩/ ድርብ ነፍስ መንገድ ፤
፺፪/ ድርብ ቅናት መንገድ ፤
፺፫/ ሥራና ሠረዝ መንገድ ፤
፺፬/ የውስጠ ዘ ሠንጠረዥ መንገድ ።

ምዕራፍ ፮ ።

## ልዩ ማስረጃ ።

የቅኔ መንገዶች ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ሲሆኑ ሌላም ይኸን የመሰለ ብዙ ዓይነት ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ ለጊዜው ለአስረጅ ያህል ይኸን ብቻ ጽፈ ናል ። በቅኔ ቤት ሆነ ብለው መምህራኑ የሚያስተምሩት በተለይም ለጀማሪ የአፍ መፍቻ ለለዩት መቀኛ የሚያደርጉት ሰምና ወርቅ የተባለውንና እርሱን የመሳሰሉ ቀላል ዓይነቶች መንገዶች ናቸው ። ተማሪው እንኳን ቅኔ ለመለየት ሲጀምር

www.ethiopianorthodox.org

እገሌ ሰምና ወርቅ መትከል ጀምሯል ይባላል ፤ በጣም ሲለይ ደግሞ ከርሱ ከፍ ያለ ጒዳና የተባለውን ቅኔ ይቀኛል ።

እነዚህ የቅኔዎች መንገዶች ሁለቱም በጣም ተወዳጅ የሆኑ ይበልም የሚያሰኙ ናቸው ።

በሌላው ረገድ ጒዳና ቅኔ በውስጠ ዘ ይሂድ እንጅ አፈታቱ ከሰምና ወርቅ ፤ ምሳሌ አሰጣጡም ከዚያው አያልፍም ፤ አንዳንድ ጊዜ ሰሙ ደክሞ ወርቁ ብቻ ደምቆ ሲገኝ ወርቃወርቅ ቅኔ ይባላል ። አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ኅብር ነው በማለት ወርቅንም ሰምንም የሚጠቀለልበት ጊዜ አለ ፤ እንዲሁም ሰሙ ሳይለይ ሲቀር ሰም ረገፍ ይባላል ፤ አንዳንድ ጊዜም ጽድቅ መስሎ ኅብርነት ያለው ወርቃ ወርቅ መስሎ ሰምነት ያለው መንገድ አለ ፤ ለምሳሌ « ዕፁብሂ ለሰማዒሁ በቢታንያ ዘኮነ ። ንጉሠ ዓለም ሆሣዕና በዲበ ዕዋል እስመ ተጽእነ » ይላል ። ይኽ ዓይነቱ መንገድ ግን ኅብርነት አለው ፤ ደግሞም ጽድቅ ነው ፤ ደግሞ ሰም ረገፍ መስሎ ይታያል ፤ ጥንታዊ የቅኔ መልክ ይኽን የመሰለ ነበር ፤ ማለት ጽድቅነቱን ሳይለቅ ኩሸቱ ሳይበዛ ፤ ምስጋናነት ያለው ነበር ። ኅብር ነት ያለው ቅኔ አንዳንድ ጊዜ ከግሥ ከመጽሐፍ ጥቅስ ጋር ይገኛል ፤ አዋቂም የሚያሰኘው እንደዚህ አድርጎ አስተባብሮ መቅኘት እንጂ ምሥጢሩን ሰውሮ ቤቱን ብቻ መግጠም እንደ ኀቡእ ሰም መድገም ይመስላል ። እንደዚህ ያለውን መንገድ ለይቶ ቤት ሞልቶ ሲገኝ እገሌ ተቀኘ ይባላል ፤ ግን እነዚህን መን ገዶች ማወቅ ብቻ ሳይሆን በነዚህ ቅኔዎች ሁልጊዜ ሲቀኝ የነዚህንም አባባል ለይቶ ሲያውቅና መዝረፍ ሲጀምር እገሌ ቅኔ አዋቂ ነው ይባላል ።

ያ ቅኔ አዋቂ ነው የተባለው ሰው በመጠኑ ጒዳና የተባለውን ፪ኛውን ክፍል ማጥናት አለበት ፤ በተለየም አታላይ መንገድ ፤ ዝምዝም ወርቅ ፤ እግር ብረት የተባሉትንና እነርሱንም የመሰሉትን ይቀጥል ነበር ፤ በነዚህም የቅኔ መን ገዶችም አንዳንድ ጊዜ ሰዎችን ያስቸግሩበት ዕውቀታቸውንም ያስገምቱበት ነበር ። በዚህ መልክ የሔድን እንደሆነ የቅኔ መንገድ ዋናው ፪ ክፍል ነው ለማ ለት ይቻላል ፤ ይኸውም ፩ኛው ሰምና ወርቅ የተባለው መንገድ ነው ። በርሱም ውስጥ ።

ሀ/ ሰምና ወርቅ
ለ/ ኅብር
ሐ/ ወርቃ ወርቅ ፤
መ/ ሰም ረገፍ ፤
ሠ/ ሰም ገፊ ፤
ረ/ ጽድቅ ፤
ሰ/ ግሥ ፤ ይኽንንም የመሰሳሉት ክፍሎች የሚገኙበት ክፍል ነው።

www.ethiopianorthodox.org

፪ኛ/ የተባለው መንገድ ደግሞ ጕዳና ነው፤ በርሱም ውስጥ ፤

ሀ/ ውስጠ ዘ
ለ/ አታላይ ፤
ሐ/ እግር ብረት ፤
መ/ ውስጠ ወይራ ፤
ሠ/ አሰናካይ ፤
ረ/ እግር በራስ ፤

ሌሎችም ይኸን የመሳሰሉት ናቸው ።

ግዕዝም አማርኛም ቅኔ ቢሆን በነዚህ ጕዳናዎች ሊሔዱ ይችላሉ ፤ ስለዚህም የአማርኛ የግዕዝ ቅኔ ተብሎ በሁለት ሊከፈል ይገባው የነበረውን የቋንቋ መለያየት እንጂ መንገዱ ከዚህ ስለማይወጣ መክፈሉን ያስቀርልናል ።

እርግጥ ነው በአሁኑ ጊዜ ብዙ ሊቃውንት ለታላላቅ ሰዎች ቅኔ ሲሰጡ ከግዕዙ ይልቅ ወደ አማርኛው አመዝነዋል ፤ አንዳንዶች ደግሞ እኩል በኩል ግዕዝና አማርኛ እያደራረቡ ይሰጣሉ ፤ ጉራማይሌ አንድም ፍሩንድስ መንገድ ይባላል ፤ ይሁን እንጂ ይኸም ግዕዝ የመድከሙን አማርኛ የመንገሡን የቋንቋችን የመሸጋገሪያ ጊዜ መሆኑን በቀጥታ ያመለክታል እንጂ መንገዱ ፈጽሞ አልተለወጠም ። በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ላይ ግን አሁንም ቢሆን ቅኔ የግዕዝን ቦታ እንደያዘ ነው ፤ እንዲሁም ቅኔ የታወቀና የተመጠነ ሕግ ወግና ሥርዓት ያለው መሆኑን ስንናገር ጥቂቶቹ መንገዱን ሳይጠብቁ የሚሔዱ እንዳሉ ልናውቅ ይገባናል ፤ እንዲህም ከሆነ በሕገኛ መንገድ በመሔድና በሕገ ወጥነት በ፪ ዓይነት ሊከፈል ይቻላል ማለት ነው ። ሕገኛ/ ቅኔ የተባለው ከጉባኤ ቃና እስከ ዕጣነ ሞገር ያለው ሁልጊዜ የሚቀኙት ነው ፤ ሕገ ወጥ የተባለው ግን በዓመት ሁለት ጊዜና ከዚያም ትንሽ በለጥ ባሉ ጊዜ የሚቀኙት ነው ፤ እነዚህም እንደ ሐዋርያቲሁ ከበበ፤ እንደ ሕንፄሃ ያሉ አጭር ዋዜማ፤ ሠልከሙ፤ ዘይእዜ ሌላም የመሳሰሉት ቅኔዎች ናቸው ። እንደ ሐዋርያቲሁ ከበበና እንደ ሕንፄሃ ያሉት በክብር ይእቲ ፈንታ ይገባሉ ፤ ሐዋርያቲሁ ከበበ በክብር ይእቲ ፈንታ እየገባ ሲሆን ቤቱም ፩ ነው ። እነርሱም ሊገቡላቸው የሚያስፈልጉ የታወቁ ዕለታት የኒቆዲሞስ ሰሞን ሰኞና ማክሰኞ ነው ።

በነዚህ ዕለታት ጾመ ድጓው ዓራራይ ሲሆን ቅኔውም በዚሁ እንዲሔድ በማለት መንገዱ ተለውጧል ፤ እንዲሁም ቅኔዎች በተለይም ዕጣነ ሞገሮች ቦታቸውን እየለዋወጡ የሚሔዱበት ጊዜ አለ፤ ይኸውም የመጋቢት መስቀል ፤ የመጋቢት መድኀኔ ዓለም ፤ የመጋቢት በዓለ እግዚአብሔር ሲሆን በዋዜማቸው ዕጣነ ሞገሩ ግዕዝ በሚሆንበት ጊዜ ነው ። ቤቱንም ሲለውጥ በመ ፤ ጀምሮ እንደሆነ በሞ ፤ ይፈጽማል ። ወይም በመ ፤ በሰ ፤ በቀ ፤ በለ ፤ ጀምሮ እንደሆነ በነርሱ ሳብእ ይፈጽማል ። ይሁን እንጅ መስቀል በሚለው ፊደል ብቻ ይሔዳል እንጂ

www.ethiopianorthodox.org

ከዚያ አይወጣም ። በወግ በታሪክ በትምህርት መልክ ቅኔን እንዲህ አድርጎ ከነባህሉ ከነየትመጣው ተማሪው ያጠናል በየደረሰበትም በዚህ መልክ ይቀኛል ።

ምዕራፍ ፺ ።

## ጠቅላላ አገባብ ።

አገባብ ማለት የነገር አሰካክ አንድም አገባብ ማለት ነው ። ይኸም ለግዕዝ ቋንቋ ንግግር ስልት አንድም ሞያ መስጠት ማለት ነው ። በአሁኑ ዘመን አነጋገር ሰዋስው እንደማለት ( ግራመር ) ነው ። ምንክያቱም ግዕዝ ቋንቋ ራሱን የቻለ ከሴማውያን ቋንቋዎች ፩ኛው ስለሆነ ለነገሩ አንድም ለንግግሩ ደንበኛ አሰካክ ደንበኛም አገባብ አለው ። የዚህንም ቃል አሰካክ ወይም አገባብ በዚህ መልክ ቀምረው ያስተምሩታል ፤ ስሙንም አገባብ ብለውታል ፤ ይኸም ሊቃውንት ጠንቅቀው ደንቡንም ጠብቀው ይናገሩበት ያስተምሩበትም እንደ ነበር የሚያመለክት ነው ።

ነገር ግን እየዋለና እያደረ የግዕዝ ቋንቋ ለንግግር አስቸጋሪ በመሆኑ ለቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ አገልግሎት ብቻ እንዲውል ሆኗል ፤ ይሁን እንጂ በግዕዝ ትምህርት ውስጥ ከፍተኛው ክፍል የዚህ እርባ ቅምርና የጠቅላላ አገባብ ትምህርት ነው ፤ ምክንያቱም አሁንም በቋንቋ መልክ እንነጋገርበት ቢባል ለንግግር ስልት የሚሰጠው ሞያውን አሰካኩን አገባቡን የሚገልጥ ይኸው አገባብ የተባለው ትምህርት ነው ። አገባብም የተባሉት ከግሥ በቀር በጠቅላላ የአረፍተ ነገርን አቀማመጥ የቃላቱንም አቀራረጽ መስጠት ሲሆን ሁሉም በጠቅላላው በ፫ ይከፈላሉ ፤ እነርሱም ዓቢይ አገባብ ፤ ደቂቅ አገባብ ፤ ንዑስ አገባብ የሚባሉ ናቸው ።

### ፩ ዓቢይ አገባብ ።

ይኸም አገባብ በነባር አንቀጽ ፤ በዘማች አንቀጽ፤ በቀዳማይ ፤ በካልዓይ ፤ በሣልሳይ እየገባ ይሠራል ፤ አንቀጽም ያፈርሳል ፤ ስለዚህ ዓቢይ ተብሏል ፤ ለዚህም አስረጅ የሚሆን « ወርቀ አምጽኡ ሎቱ እስመ ንጉሥ ውእቱ ፤ እንዘባ ውስተ ማኅፀና እመንፈስ ቅዱስ ይላል » በነባር አንቀጽ ሲገባ ። « ክርስቶስ ሞተ እስመ ለብሰ ሥጋ » ይላል ፤ በቀዳማይ ሲገባ ። « አመ ይመጽእ ወልድ በስብሐቲሁ » ይላል በካልዓይ ሲገባ ። « እስመ ሣህልኪ ይኩን ላዕለ ኵልነ » ይላል ፤ በሣልሳይ ሲገባ ። ሌላም ይኸን የመሰለውን ሁሉ ያሳያል እንዲሁም በአገባብ በአንቀጽ በባለቤት ላይ እየወደቀ ነጇም ተነጇም ይሆናል ። ለምሳሌም « እስመ ጴጥሮስ ይሜህር በወንጌል ሕገ ፤ » እስመ በወንጌል ይሜህር ሕገ ጴጥሮስ » ማለቱን ያሳያል።

### ፪ ደቂቅ አገባብ ።

ይኸም አገባብ እንደ ዓበይት አገባብ በዓበይት አናቅጽ እየወደቀ አንቀጽ ስላላስቀረ ደቂቅ ይባላል ፤ ነገር ግን ዓበይት አገባብ ከአንቀጽ ላይ እን

www.ethiopianorthodox.org

ደወደቁ እርሱም በሰዋስው ላይ እየወደቀ ማድረጊያ ፤ መነሻ ፤ ተቀባይ ፤ ተሳቢ ስለ ሆነ አገባብ ይባላል ። ለምሳሌም « ዲበ መንበረ ሙሴ ነበሩ ጸሐፍት » ይላል ፤ ማድረጊያ ሲሆን ፤ « ተውህቦ ሕግ ለሙሴ » ይላል አቀባይ ሲሆን ፤ « አብርሃም ወለዶ ለይስሐቅ » ይላል ፤ ተሳቢ ፤ ሲሆን ሌላም ይኸን የመሰለ ነው ።

## ፫ ንዑስ አገባብ ።

ንዑስ የተባለበትም ቅጽል እየሆነ በመግባቱ ነው ፤ ለምሳሌም «ዓይ ፤» « ምንት » ፤ የሚለውና ሌላም ይኸን የመሰለ ነው ። ይኸውም በሞያ ሲውል ቅጽል ይሆናል ፤ ቅጽልም ሲሆን አንድም በቅጽል ቦታ ሲገኝ « ዓይ ልሳን » « ምንት ነገር » ይላል ። ይኸንም በመሰለ መንገድ ይሄዳል ፤ በቂ ሲሆንም « አይ ወረደ » ፤ « ምንት መጽአ ፤ ይላል ። አገባብም የተባለበት እንደ ዓበይት አገ ባብ ከአንቀጽ በኋላ እየወደቀ አንቀጽ ስለሚያስቀርና እንደ ደቂቅ አገባብም ከሰ ዋስው ላይ ስለሚወድቅ ነው ፤ ለምሳሌ « ይትርፍስ ፍቅረ ባዕድ » ይላል ። አንቀጽ ሲያፈርስ ደግሞ « ዘመድኒ ኢይትአመን » ይላል ፤ እንደዚያው ነው ። በሰዋስው ላይ ሲወድቅ ደግሞ « ይሙት አብድ እምይሙት ጠቢብ » ይላል ። በመጻሕፍት ውስጥ ያሉትን ሕገ ወጥ አረፍተ ነገሮች በመዘርዘር ወይም ሕግ ያላቸውን እንደ አብነት አድርጐ በመጥቀስ ሁሉንም በቃላቸው ይዘው ያስተምሩ ነበር ። ተማሪውም በሙሉ እንኳን ባይሆን በመጠኑ እነዚህን መንገዶች ካልተ መለከታቸው ግዕዙ በቀላሉ አያስኬደውም ነበር ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩— ግዕዝ ቋንቋነቱ ከቀረ ጀምሮ ብዙ ቃላት ሳይጠፉበት አልቀረም ፤ ምክንያቱም ለአንዳንድ ነገር ቃል ሲፈለግ ግዕዝ ጠባብ አማርኛ ግን ሰፊ መስሎ ይታያል ፤ ይኸም የሚያመለክተው የግዕዙን መድከም የቃሉን ማጠር ነው ።

፪— የቅኔ መንገድ ብዙ ሲሆን በአሁኑ ጊዜ ከዚህ ከጻፍናቸው ያነሰ እንጂ የበ ለጠ የሚያውቅ ሊቅ አልተገኘም ። በቃል እንደሚናገሩት የሆነ እንደሆነ እስከ ፩ሺህ ከዚያም በላይ እንደሆነ ይነገራል ። ግን ይዞ የተገኘ የለም ።

ከዚህም ከጻፍነው ውስጥ አብዛኛው የሊቀ ኅሩያን ዘገየ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፱ ።

# የመጻሕፍት ትርጓሜ ።

## ምዕራፍ ፩

## የትርጓሜ ስልት

### ፩ኛ የትርጓሜ ታሪክ ።

የመጻሕፍት የአንድም ትርጓሜ ስልት በሀገራችን መቼ እንደተጀመረ እስካሁን ግልጥ ሆኖ አይታወቅም ፤ ከዚህም ጋር ማን እንደጀመረው ፤ የትስ ሀገር እንደተጀመረ በሁሉ ዘንድ ግልጥ አይደለም ። በግምት የሄድን እንደ ሆነ ግን መጻሕፍተ አሪት ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ሲተረጐሙ የርሱም ጥንታዊ የአንድም ትርጕም አብሮ እንደገባ ይታመናል ፤ ከዚህም ሌላ ከሕገ አሪት ጋር ሊቃውንተ አሪት በንግሥተ ሳባ ጊዜ ከቀዳማዊ ምኒልክ ጋር አብረው ወደ ኢትዮጵያ ስለመጡ እነርሱ ሲተረጕሙት ሲያስተምሩት ኑረዋል የማለት ግምት ይሰጣል ። በእርግጥም አሪት በጥንት ዘመን ተተርጕማ በአገራችን ቋንቋ ይሠራባት ነበር የሚለው ታሪክ እውነተኛ ሁኖ ተቀባይነት ከአገኘ ፡ ሊቃውንተ አሪትም ወደ ሀገራችን መግባታቸው እርግጥ መሆኑን እምነን ከተቀበልን መጻሕፍትም ሲተረጐሙ መኖራቸው ከቶ የሚያጠራጥረን ሊሆን አይችልም ። ይኸም ከሆነ አሪታውያን መጻሕፍት ቀደም ብለው ሲነበቡ በአንድም ትርጕም ስልት ሲተረጐሙ ኑረዋል ፤ በኋላም በዚያው መልክ ቀጥለዋል ፤ በክርስትና ጊዜ ደግሞ እንደገና መጻሕፍተ ብሉያትና መጻሕፍተ ሐዲሳት ከጽርእ ወደ ግዕዝ በቀጥታ በተተረጐሙ ጊዜ የአንድም ትርጓሜ ስልት አብሮ ወደ አገራችን እንደገባ ፤ እንድም የትርጓሜውንም መጽሐፍ እንደ አብነት አድርገው አብረው እንደ አስገቡት ይገመታል ። ከዚያም አያይዞ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ ብዙ መጻሕፍተ ሊቃውንት ፤ ሲተረጐሙ የትርጓሜ ስልት የሆኑ መጻሕፍት ሁሉ ሳይተረጐሙ አልቀሩም የሚል አስተያየት ይሰጣል ፤ ይኸንም ለመረዳት ስንፈልግ ቅዱስ ያሬድ ጥበባት ሁሉ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ከተገለጡለት ወዲህ የመጻሕፍትን ትርጓሜ ሁሉ ዐወቀ ይባላል ፤ ይኸም ማለት ፤ እንደሌላው ድርሰቱ ሁሉ አዲስ ድርሰት ደረሰ ማለት ሳይሆን የጥንቱን መጽሐፍ በጥንቱ ትርጓሜ ስልት አጠና ፤ ዐወቀ ፤ መረመረም ማለት ነው ( ገድሉን ተመልከት ) ። ቅዱሳት መጻሕፍት ወደ ቋንቋችን የተተረጐሙበት ጊዜ አይታወቅም አልን እንጂ የዮሐንስ አፈወርቅ ፡ የቅዱስ ባስልዮስ ፡ የቅዱስ ኤፍሬም ፡ የአቡ ፈረጅ እንዲሁም የሌሎች ሊቃውንት ትርጓሜዎች ወደ አገራችን ተተርጕመው እንደገቡ እስከ አሁንም እንደሚገኙ የታወቀ ነው ፤ ዛሬም በየገዳማቱ በየአድባራቱ ግዕዙን በግዕዝ በአንድም ትርጓሜ ስልት የሚገልጡ ብዙ ዓይነት መጻሕፍት በልዩ ልዩም ደራስያን የተደረሱ አንድም በልዩ ልዩ ጊዜ የተተረጐሙ እንዳሉ የታወቀ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኽ ዓይነት ግምት የወል በመሆኑ እንደ እውነት ይቆጠራል እንጂ በትርጓሜውም መጻሕፍት ቃል በቃል አጥንቶ ፤ ወይም ከሰው አግኝቶ ፤ ወይም ራሱ ተጣጥሮ እገሌ ደረሰው ጀመረው ስለማይባል ፤ ታሪኩም ከታሪክ ጋር ተያይዞ ስለአልመጣ ልብን አኩርቶ አፍን መልቶ እንዲናገሩ አያደርግም ፤ ለምርምርም ክፍት በር አይገኝም ፤ ስለዚህም እንደዚሁ ማለፍ ግድ ይሆንብናል ። የሆነው ሆኖ እውነቱን የተመረኰዘ አስተያየት ለመያዝ የፈለግን እንደሆነ ስለ ዘመኑ በአክሱም ዘመነ መንግሥት ተጀመረ ማለት ግድ ይሆንብናል ፤ ሆኖም ይኽ በቋ ሳይሆን በየክፍለ ዘመናቱ ሁሉ ሳያቋርጥ ሲወርድ ሲዋረድ ከቆየ በኋላ አካል ገዝቶ መልክ አግኝቶ ለመታወቅ የቻለው በጐንደር ዘመነ መንግሥት ነው ።

## ፪ኛ የትርጓሜ ስልት በጐንደር ።

በጐንደር ዘመነ መንግሥት ጊዜ ጥበባት ሁሉ መልክ እንዳገኙ ፤ እንደተወሰኑ ሁሉ የመጻሕፍትም ትርጓሜ መልክ አግኝቶ አደባባይ ወጥቶ ፤ ብዙ ደቀ መዛሙርትም አግኝቶ ፤ ይኸን የአሁኑን ፍለጋ ይዞ ለመስፋፋት ችሏል ፤ ከዚያም ጀምሮ እስከ አሁን ለመተላለፍ በቅቷል ፤ ብዙ መምራህንም ተነሥተዋል ፤ ብዙም ደቀ መዛሙርት አውጥተዋል ። መምህራኑም ኢትዮጵያውያን ብቻ ሳይሆኑ ብዙ የውጭ ሊቃውንትም ይገኙበት እንደነበር የታወቀ ነው ። ከነርሱም ውስጥ የታወቁት እነ ሙአልም ጴጥሮስ ( የጀርመን ተወላጅ ) እነ ጳውሎስ ዝክሪን የዓረብ ተወላጅ የተባሉና ሌሎችም ነበሩ ።

በዚህም መልክ ሲተረክ ምንም ቀደም ያሉ ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት ቢኖሩ ለአስረጂ ያህል ከቅርቡ ለመጀመር እንዲህ ሲሉ ይተርካሉ ፤ ጳውሎስ ዝክሪን አባ ጳውሊን አስተማረ ። አባ ጳውሊም ፡ ሠርፄ ክርስቶስን አስተምሮ በእግሩ ተካ ። ሠርፄ ክርስቶስም ጽጌ ድንግልን አስተምሮ ተካ ። ጽጌ ድንግልም አባ ያዕቆብን አባ ያዕቆብም በትረ ክርስቶስን ፤ በትረ ክርስቶስም አለቃ ጓንጕልን አለቃ ጓንጕልም መምህር ኤስድሮስን በእግሩ ተካ ። መምህር ኤስድሮስ ግን እንደገና ብዙ መጻሕፍትን በማንበብ የቀድሞውን ትርጓሜ አድሰዋል ፤ ሰውየው ዓይነ ሥውር ሲሆኑ ፫፻ መጻሕፍት እንዳነበቡ ይተረከላቸዋል ፤ ብዙ ትርጓሜንም አቃንተዋል ፤ ስለዚህም እስከ ዛሬ ድረስ የመምህር ኤስድሮስ ትርጓሜ እየተባለ የጠመመው የቀናበት የጐደለው የሞላበት የርሳቸው ትርጓሜ ነው ።

ሰውየው ከላይ እንደገለጥነው ሁሉ ዓይነ ሥውር ሲሆኑ በዕውቀታቸው ጥልቀት በምርምራቸው ብዛት አራት ዓይና ተብለው ይጠሩ ነበር ። የሊቅነትም ምስክር መማር ብቻ ሳይሆን መመርመርም ነው ፤ ለመመርመርም ማንበብ ያስፈልጋል ፤ ስለዚህም ይኽን ያህል መጻሕፍት ለማንበብ በመንፈሳቸው ተገደዱ ፤ እንዲያውም ቀደም ብለው ያወጧቸው ብዙ ደቀ መዛሙርት ነበሩ ፤ እነርሱም በየሀገሩ ተበትነው ሲያስተምሩ ሳለ እርሳቸው መጻሕፍትን ለማንበብ ወደ ጣና

www.ethiopianorthodox.org

ደሴት ገቡና ከላይ የገለጥናቸውን ብዙ መጻሕፍትን አንብበው ምሥጢር በበለጠ አደላድለው ከተመለሱ በኋላ ደቀ መዛሙርቶቻቸውን የቀረን ነገር አለና ኑ እን ደገና እንመርምር ፤ እንማር ብለው ቢጠሯቸው ብዙዎች የመምህራቸውን ቃል አክብረው ሲመጡ ጥቂቶቹ ግን « ንሕነሰ ኢተወለድነ እምዝሙት » እኛስ አንተ ኢባታችን ሳትሰስን ( አዲስ ትርጕም ሳታመጣ ) የተወለድን ነን ፤ እንደ ገና ወደ ት/ ቤት አንገባም ሲሉ መለሱላቸው ። ስለዚህ ብዙዎች በአዲሱ አቅድ ሲያጠኑ ጥቂቶቹ ግን በዚያው ጸኑ ፤ ስለዚህም ሁለት ዓይነት ትርጓሜ ቤት ሊፈጠር ቻለ ፤ ይኸውም የላይ ቤትና የታች ቤት የተባለው ነው ። የላይ ቤት የተባለው ትርጓሜ መምህራቸው ቢጠሯቸው አንመጣም ብለው ትርጓሜው ንም አናሻሽልም እንደገናም አናጠናም ፤ ያሉት መምህራን ትርጕም ነው ፡ ይኸ ውም አብዛኛው የጐጃም ትርጕም የተባለው ባለብዙ ሐተታ ነው ።

የታች ቤት ትርጕም የተባለው ደግሞ እንደገና ከመምህራቸው ጋር በመ ወያየት ትርጕም ያሻሻሉ ምሥጢር ያደላደሉ ሰዎች ትርጕም ነው ፤ እርሱም የጐ ንደር ትርጕም የሚባለው ፤ ነው ዛሬም ጉባኤው ሰፍቶ የሚገኘው እርሱው ነው ፤

መምህር ኤስድሮስ በዚህ መልክ አስተምረው ሥነ ክርስቶስ የተባለ ደቀ መዝሙር አወጡ ። ሥነ ክርስቶስም አለቃ ወልደ ኢብን አስተማሩ ። አለቃ ወልደ አብ የተባሉት መምህር የሸዋ ተወላጅ የሆኑ በዕውቀታቸው እንዲሁ የትርጕም አባት ወይም ፈጣሪ የተባሉ ናቸው ፤ ምክንያቱም የትርጓሜው ስልት ከርሳቸው ሲደርስ እንደገና መልክ አግኝቶ ስለተነሣ ነው ፤ እርሳቸውም ከመምህራቸው ከአ ገኙት ዕውቀት ጋር ፷፻ መጻሕፍት አንብበው የትርጕሙን ስልት አሻሽለው ለደቀ መዝሙር እንዲመች አድርገው በማቅረባቸው እስከ አሁን ሲደነቁ ይኖራሉ ።

እኒህም ሊቅ ከዚህ ደረጃ ሊደርሱ የቻሉት በአገራቸው ሳሉ ከመበለት ጋር በማጫፈር ወደ መክፈልት ስለ ተጠሩ እንዴት የዓቃቢት ተጫፋሪ እሆና ለሁ በማለት ተናደው ለትምህርት ወደ ጐንደር እንደሄዱ ይነገራል ፤ ከዚያም እንደደ ረሱ ጊዜ ሳይወስኑ በትጋት ከመማራቸው የተነሣ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህር ሆነው ይኸን ስም ሊያገኙ ቻሉ ። አለቃ ወልደ አብም ለራሳቸው ብቻ ሊቅ ሳይሆኑ አለቃ ወልደ ሚካኤልን አለቃ ገብረ ኢየሱስ የተባሉትን ደቀ መዛሙርት አስተማሩ ።

አለቃ ወልደ ሚካኤል የተባሉት መምህራቸውን አክለው መስለው ስለ ተገኙ ሊቃውንት ሁሉ እንደ ወንድማማች አድርገው ወልደ አብ ወልደ ሚካ ኤል እያሉ አሁን ድረስ ይጠሯቸዋል ። የርሳቸውም ሀገር ስሜን ሲሆን ብዙ መጻ ሕፍትን በማንበብ በትርጕምም ስልት በመስጠት የታወቁ ሊቅ ነበሩ ፤ ስለዕውቀ ታቸውም ፩ ዓይና እየተባሉ ይጠሩ ነበር ። አለቃ ወልደ ሚካኤልም ጉባኤ አስ ፍተው በማስተማራቸው ደረስጌ ገብረ ማርያምንና መምህር ወልደ ሩፋኤልን አለቃ መንክር ዘአክሱምን መምህር ተክለ ማርያምን ፣ አለቃ ኀሩይንና አለቃ ወልደ አማኑኤልን ፤ መምህር ወልደ ጊዮርጊስን መምህር ወልደ ሚካኤልን

www.ethiopianorthodox.org

የዜና ማርቆሱን አስተማሩ ከዚህ በኋላ ግን የመጻሕፍት መምህራን በብዙ ሐረግ የሚቆጠር ስምን አግኝቷል ፤ እንዲሁም የትርጓሜው ስልት እየተለያየ በመገኘት እስካሁን በዚሁ መልክ ይቀጥላል ፤ እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር መምህሩን የመምህሩንም አባትና አያት ፤ ቅድመ አያት ወደ ላይ ሲቆጠር ከዚህ ከቆጠርነው ሐረግ ይደርሳል ፤ ከዚያም በላይ ሊወጣ ይችላል ። የኛን ቤት በተለይም እኔን የሚመለከተውን በዚህ መልክ እቀጥራለሁ ፤ መምህር ወልደ ሚካኤል የዜና ማርቆሱ አቡነ አብርሃምን ተክተዋል ። አቡነ አብርሃም ጉባኤ አስፍተው ደቀ መዝሙር አብዝተው በማስተማራቸው መምህር ሰይፈ ሥላሴን አቡነ ዮሐንስን ፤ አቡነ ሚካኤልን ፤ መምህር ፈንታን ፤ አለቃ አምኃን ፤ መምህር ጥዑመ ልሳንን ፤ ተክተዋል ። መምህር ሰይፈ ሥላሴ ደግሞ ጉባኤ አስፍተው በማስተማራቸው ከዚህ በታች ስማቸው የተጠቀሱትን ደቀ መዛሙርት አውጥተዋል ። መምህር ቀጸላ ሰይፉን ፤ አባ ምክረ ማርያም ሰይፉን ፤ ንቡረ እድ አበበ ሻውልን ፤ መምህር ዘወንጌልን ፤ አለቃ ሀብተ ወልድን ፤ መምህር ገብረ ሕይወትን ፤ መምህር ገብረ ማርያም ወርቄን ፤ መምህር አፈ ወርቅን አለቃ ሲራክን ፤ ሊቀ ሥልጣናት ሀብተ ማርያምን ፤ እንዲሁም በሞት የተለዩት አለቃ መዘምር ፤ አለቃ ወልደ ዳዊት ፤ አባ ተክለ ሐዲስ ፤ አባ ገብረ ማርያም ናቸው ። የሐዲስ ኪዳን በዚህ መልክ ሲሄድ የመጽሐፈ ሊቃውንት ትርጉም መምህራን ደግሞ እንደሚከተለው ነው ። ከዚያም ውስጥ የፍትሐ ነገሥትን የትርጉም መምህራንን እንመልከት ።

ጴጥሮስ ወልደ አብድል ሰይድ ከዓረብ ወደ ግዕዝ መልሶ ለሐዋርያነ ክርስቶስ አስተምሮታል ፤ ሐዋርያነ ክርስቶስም ለሊቀ ካህናት ወልደዮና አስተምሯል ፤ ከሊቀ ካህናት ወልደ ዮናም ሲያያዝ ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ደርሷል ፤ ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ፤ ከዐቃቤ ሰዓት ከብቴ አለቃ ወልደ አብ ፤ ከአለቃ ወልደ አብ አዛዥ ለሚህ ፤ ከአዛዥ ለሚህ ሙሉጌታ ኪዳነ ማርያም ፤ ከሙሉጌታ ኪዳነ ማርያም በዛብህ ፤ ከበዛብህ እርቅ ይሁን ፤ ከእርቅ ይሁን አለቃ ዮሐንስ ፤ በአንድ ወገን ከእጨጌ በትረ ጊዮርጊስ ሲያያዝ ጐሹ ሀብቱ ፤ ከጐሹ ሀብቱ አለቃ ውሂብ ፤ ከአለቃ ውሂብ አለቃ የተመኙ ፤ ከአለቃ የተመኙ ሙሉጌታ ኪዳነ ማርያም ፤ ከዚህ በኋላ ግን እንደቀደመው ይሄዳል ። በብሉይ ኪዳን በሊቃውንት በመጻሕፍተ መነኮሳት በቍጥር መጻሕፍት የተለየ አቈጣጠር አለው ።

እንደ ኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ትምህርት በመጻሕፍት ትርጓሜ ውስጥ ፬ ዓይነት ክፍል አለው ፤ እነዚህንም ሞያዎች አጠናቀው የሚያውቁት ሊቃውንት ፬ ዓይና እየተባሉ ሲጠሩ ይኖሩ ነበር ፤ ፬ የተባሉትም የጉባኤ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው ።

## ፩ኛ መጻሕፍተ ብሉያት ።

መጻሕፍተ ብሉያት በመላ እንደ አንድ ጉባኤ ተቈጥረው ይጠራሉ ፤ ይኸንም አጠናቆ ያወቀ የብሉይ መምህር ወይም መጋቤ ብሉይ እየተባለ ይጠራል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ መጻሕፍተ ሐዲሳት ።

መጻሕፍተ ሐዲሳት በመላ አንድ ጉባኤ ተብለው ይጠራሉ በጉባኤው መልክ ግን በ፫ ይከፈላሉ ፤ እነርሱም ወንጌል ፬ ፤ የጳውሎስ መልእክት ፪ ፤ ሌሎች በመላ ፫ኛ ክፍል ይሆናሉ ። እነዚህም እያንዳንዳቸው በዓመት ፪ ጊዜ ይዘለቃሉ ከሐዲስ ኪዳን ውስጥ አንድም ትርጉም ላይ ብዙ ጊዜ የሚወርደው እስከ ፲፮ ጊዜ ብቻ ነው ። ይኸውም በዮሐንስ ራእይ ላይ የሚገኘው «ፈረስ ፀዓዳ» የሚለው ታላቅ አወራረድ ነው ፤ እርሱንም ያወቀ ደቀ መዝሙር የሐዲስ መምህር ወይም መጋቢ ሐዲስ እየተባለ ይጠራል ።

## ፫ኛ መጻሕፍተ ሊቃውንት ።

መጻሕፍተ ሊቃውንትም የሚባሉት እንደፍትሐ ነገሥት ቄርሎስ ፤ ዮሐንስ አፈ ወርቅ ፤ ሃይማኖተ አበው ፤ መጻሕፍተ ቅዳሴያት ሌላም ይኸን የመሳሰሉ ናቸው ። እነርሱም በመላ አንድ ጉባኤ ተብለው ይጠራሉ ፤ ይኸውም ፫ኛ ጉባኤ ይሆናል ማለት ነው ።

## ፬ኛ መጻሕፍተ መነኮሳት ።

መጻሕፍተ መነኮሳት ለብቻው አንድ ጉባኤ ተብሎ ይጠራል ፤ እርሱ ሲደመር ፬ ይሆናል ። ስለዚህም የ፬ ጉባኤ መምህር እገሌ ወይም ፬ ዓይናው እየተባሉ ሊቃውንቱ ይጠራሉ ። አንድ ጊዜ ግን የቀኍጥር ትምህርት ፭ኛ ጉባኤ እንደነበር ይነገራል ፤ አንዳንዶች ሊቃውንት ደግሞ ከሊቃውንት ጉባኤ ጋር በመጨመር ፬ ብቻ እንደሆነ ያጸናሉ ። አንዳንዶች ግን እንዲያውም የቀኍጥርን ትምህርት ከዓይን መጻሕፍት ጋር ጨምረው ከቀኍጥር ውጭ ያደርጉታል ። ስለዚህ በጉባኤ የታወቁት ከላይ የቈጠርናቸው ፬ቱ ክፍሎች ብቻ ናቸው ። አራትን በመላ ንባቡ ከነትርጕሙ ከነምሥጢሩ ይዞ እያስተማረ የሚኖር መጋቤ ብሉይ ተብሎ ከፍ ያለ ደረጃ ይዞ እንደነበር የታመነ ነው ። እንዲሁም መጻሕፍተ ሐዲሳቱን በመላ ንባቡን ከነትርጕሙ ከነምሥጢሩ ይዞ መጋቤ ሐዲስ እየተባለ ተከብሮ ያስተምር እንደነበር ፤ ብዙ ደቀ መዛሙርትን እንዳስገኘ የታወቀ ነው ። መጻሕፍተ ሊቃውንትም እንዲሁ ንባቡን ከነትርጕሙ ከነምሥጢሩ አስፋፍቶ ስለሚያውቅ ከፍ ያለ ክብር አግኝቶ ይኖር እንደነበር የታመነ ነው ።

እንዲሁም መጻሕፍተ መነኰሳትን በዚሁ መልክ ይዞ ሲያስተምር ይከበር ነበር ፤ በተለይ ፬ቱን ሁሉ አንድ አድርጎ ስለያዘ በማድነቅ ብቻ ፬ ዓይና ይባል ነበር ።

በዚህም ስም ይጠሩ የነበሩ ብዙዎች ናቸው ፤ ለምሳሌ ከላይ ከቆጠርናቸው ሌላ እነ ዐቃቤ ሰዓት ከብቴ ፤ አራት ዓይና ጐሹ ፤ አራት ዓይና ሙተሬ ገብረ ማርያም እነርሱንም የመሰሉ ሌሎች ነበሩ ዛሬም በኛ ጊዜ ፬ ዓይና የሚባሉ

www.ethiopianorthodox.org

ሁሉንም የሚያውቁ አለቃ አየለ ዓለሙ በጐንደር ይገኛሉ ። እርሳቸውም የመጀመሪያውን የካህን ዲግሪ የክብር ዶክተርነት በ፲፱፻፷ ዓ. ም. ከቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዩኒቬርስቲ ያገኙ ናቸው ።

በጥንት ጊዜ የነበሩ መምህራን ግን ሁሉም ፬ ዓይና እንደ ነበሩ እንረዳለን ፤ ምክንያቱም ሊቃውንቱ ጥበብ በቃን የማይሉ ከትምህርት ቤት ወደ ሀገራቸው ለመመለስ የማይቸኩሉ ነበሩና ። በአሁኑ ጊዜ ግን እንደዚህ አይደለም ፤ ምክንያቱም ፩ኛ/ ትምህርቱ በአጭር እንዲወሰን በማለት ደቀ መዝሙሩ የ፪ ሙያ ባለ ቤት ይሆን ዘንድ መምህራኑ አይፈቅዱለትም ፤ እርሱም ዕውቀትን በቶሎ አይሸምትም ፤ ፪ኛ/ አማርኛውን ብቻ በመጠበቅ የትርጓሜውን አመል ለይቶ ለማወቅ ሲል ደቀ መዝሙሩም በ፩ ሞያ ብቻ መወሰን ግድ ይሆንበታል ።

ምዕራፍ ፪ ።

## የትርጓሜ ዓይነት ።

የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን ራሱን የቻለ ቋንቋ ስላላት ራሱን የቻለ የትርጓሜ ስልት አላት ። በነዚህም የትርጓሜ ትምህርት ከመምህራን ፩ኛው ከሌላው የበለጠ አስተያየት አለው እየተባለ ሲገመትበት ዕውቀቱም ሲመዘገብለት ኖሯል ። ልዩ ልዩ የትርጓሜ ዓይነቶች ወይም ስልቶች ሲኖሩን እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

### ፩ኛ የአንድም ትርጓሜ ።

የአንድም ትርጓሜ የሚባለው አንድ ጊዜ ከተተረጐመ በኋላ እንደገና አንድም እያለ እስከ አሥርና እስከ ፲፫ ጊዜ ድረስ የሚያወርዱት አወራረድ የሚሰጡትም ሐተታ ነው ። ስለአንድም ትርጉም በግዕዝ ቋንቋ አንድም በማለት ፈንታ አው ፡ ቦ ፡ ይላል ። የዚህም ፍች ሌላም ይህን የመሰለ ትርጉም አለው እንደማለት እንደማማረጥም ነው ። በአማርኛ ግን ፪ኛ ወይም ፫ኛ አይልም እንጂ አንድም እያለ እስከ ፲፮ ጊዜ ይወርዳል ፤ ሆኖም ግን ፪ኛ ወይም ፫ኛ እንደማለት የሚያስቈጥር ነው ። ይኸም አንድም ትርጉም አንድ ጊዜ የተወሰነ ስለሆነ ሊሻሻል ሊለወጥ ወይም ሊጨመርበት የማይቻል ሆኖ እስከ አሁን የቆየ ስለሆነ ደቀ መዝሙሩ ምንም መርማሪና አስተዋይ ቢሆን በዚሁ ብቻ መወሰን ግድ ይሆንበታል ፤ በአንዳንድ ቦታ ላይ እንኳን ትንሽ ለውጥ ያደረገ እንደሆን የቀረው ቀርቶ አማርኛውን እንኳን ያሻሻለ እንደሆን የኔታ እገሌማ ትርጓሜውን ዘንግተውታል አማርኛውን ረስተውታል እየተባለ ብዙ ይነገርበታል ። እንዲያውም ዋና ደቀ መዝሙር የሚባለው መምህሩ ከሚተነፍሱበት የተነፈሰ ፤ ከሚያርፉበት ያረፈ በቀጥታ ያለምንም ለውጥ ወይም አስተያየት ያንኑ ይዞ የተገኘ እንደሆነ ነው ። እን

www.ethiopianorthodox.org

ደዚህ ያለው ብቻ ለአብነትነት ሲፈለግ እንደ ትልቅም ሁኖ ሲቈጠር በመምህሩም እግር ሲተካ ቆይቷል ። አንድም ብሎ ትርጕም የተረጐመ ብዙ ሐተታ አትቶ በቂ እስረጅ ያመጣ የተደበቀውን ያወጣ እንደሆነ መናፍቅ ይሉታል ያልሆነም ስም ያወጡለታል ፤ ስለ ሊቅነቱም በማመስገን ፈንታ «ከመናፍቅ ትርጓሜ ከትንባሆ ልምላሜ» አይጠፋም በማለት ስሙን ያጠፉት ነበር ። እንዲሁም «የጠጣን ልጅ በዛፍ የመናፍቅን ልጅ በአፍ» ማን ይችላል ይሏቸዋል ። ይኸን በመፍራት ደግሞ የተፈጥሮ ዕውቀት ያለው ታላቁ ሊቅ በትምህርት ሊራቀቅ ሲችል ወደ ኋላ ይስበው ይጐትተው ነበር ፤ ቢመረመርም ለራሱ ወይም ለግል ለሚወዳቸው ደቀ መዛሙርት ለብቻ ይነግር ነበር እንጂ በአደባባይ ሊያስረዳ አይቻልም ነበር ።

ይኸም ሁኖ አንዳንድ ሊቃውንት ከሌላው ተለያይተው ከፍተኛ ግምት ይሰጣቸው ዝናቸውም ይነገርላቸው የነበር እንደዚህ ያለውን የልማድ መሣሪያ እየበጠሱ ስለሚገኙ ነው ። የአንድም ትርጓሜ አገባብን በመጠበቅ ወይም እርሱን ሳይሻ ዘይቤን ብቻ በመጠበቅ ወይም ምሥጢሩን በመከተል ይተረጐሙታል ፤ ይኸም ከሆነ ልዩ ልዩ መንገድ አለው ማለት ነው ፤ እንዲሁም አገባብን በማውጣት ሲተረጕሙ እስመንና ከመን ለማውጣት ሲሉ በልዩ መንገድ ይተረጕማሉ ። ዘይቤውን ሳይከተል ደግሞ ምሥጢሩን ብቻ በመከተል ሲተረጕሙ ይገኛሉ ። ከዚህም ጋር ታሪክ በመተረክ ምሳሌ በመመሰል ሐተታ በማተት ይተረጕማሉ ። እያንዳንዱ ኃይለ ቃል ለምን እንደተነገረም ምክንያቱን ይሰጣሉ ፤ ለዚያም አስረጅ ጥቅስ ይጠቅሳሉ ፤ በጠቅላላው አንዱን ከአንዱ ጋር አፋጭተው ለሁሉም ሞያ ሰጥተው ሥውሩን ገልጠው ምሳሌውን ፈትተው ያስረዳሉ የአንድም ትርጓሜ ዓይነት ይኸን የመሰለ ነው ።

## ፪ኛ ነጠላ ትርጓሜ ።

ነጠላ ትርጓሜ የሚባለው ዘይቤውን ብቻ በቀጥታ የሚተረጕም ምንም ሐተታ የማያደርግ ፪ኛው የትርጕም ዓይነት ነው ። በዚህም ዓይት ትርጕም ጥንታውያን የሆኑትን መጻሕፍት በተለይም ለዕለት አገልግሎት በጣም አስፈላጊ የሆኑትን ከውጭ ቋንቋ ወደ ግዕዝ ተርጕመዋል ፡ ከግዕዝም ወደ አማርኛ ሲተረጐሙ ቆይተዋል ፤ አሁንም በመቀጠል ላይ ይገኛሉ ። ይሁን እንጂ ይኸ የአማርኛ ትርጕም ሊቃውንቱ አዲስ ሳይሆንባቸው አልቀረም ፤ ምክንያቱም በመራቀቅ በአንድም ትርጕም ስለኖሩ ነው ። በዚህም ምክንያት የጥንቱ ሊቃውንት መጽሐፍ ቅዱስን ሳይቀር አንቀበልም ይሉ የነበረበት አስረጅ የሌለው ነጠላ ትርጕም ነው በማለት ነው ። የአንድም ትርጕም በፈለጉት መንገድ ለመውሰድ ንባቡን ለማቅናት ምሥጢሩን ለማሸራሸት ይመች ነበረ ፤ ይኸ ግን ያልተቃናው ንባብ እንደዚያው እንዳለ ሳይቃና ሲተረጐም ምሥጢሩን አያስረዳም ወይም ወደ ክህደት ያደርሳል የሚል ፍርሃትም ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

በዚህም በነጠላ ትርጕም ውስጥ ፪ ዓይነት መንገድ ይገኝበታል ፤ ይኸውም ሀ) ቀጥታ ዘይቤ ፤ ይኸም ማለት ከላይ እንዳተትነው ሁሉ የተነበበውን በቀጥታ መተርጐም ነው ፤ «ለምሳሌ በልዋ ለዛቲ ቊንጽል» ያችን ቀበሮ በሏት «አንተ ኰዘሕ» አንተ ድንጋይ ነህ የሚል ነው ። እውነተኛውና ቀጥተኛውም ትርጕም ይኸ ዓይነት ነው ፤ ምክንያቱም የአንድም ትርጕም በሆነ ጊዜ እንደትምህርቱ ሊቁ ሊዋኝበት ይችላል ሰፋ ያለ አስተያየት ይሰጣል ትርጕሙን ይለውጣል በሌላም መንገድ ሊሄድ ይችላል ፡ ይኸን በመሰለ መንገድ በሄደ ጊዜም የመጽሐፉ ጠቅላላ ሃሳብ ሊጠፋ ይችላል ። ቅዱሳት መጻሕፍት በዓለም ላይ አንድ ሆነው የተገኙት እንዲሁ በቀጥተኛው ዘይቤ ብቻ በመተርጐማቸው ነው ።

## ፫ኛ የምሥጢር ትርጓሜ ።

ይኸም ንባቡን ሳይሻ አገባቡን ሳይጠብቅ ምሥጢሩን ብቻ በመጠበቅ የሚተረጐሙት ዓይነት ነው ፤ ለምሳሌም «በልዋ ለዛቲ ቊንጽል» ሲል ሄሮድስን እንዲህ በሏት «አንተ ኰዘሐ» ሲል አንተ መሠረት ነህ የሚል ነው ። በዕድሜ ሸማግሌ በሐሳብም እንደዚያው የሆኑ ሁሉ የምሥጢሩን ትርጓሜ ብቻ ይወዳሉ ፤ ምክንያቱም ምሥጢሩን በአንድም ትርጕም ቀደም ብለው ስለሚያውቁት ያ መሆኑን ስለሚረዱት ነው ። ሌላ ቋንቋ ያጠኑ የሌላውን የትርጕም ስልት የተከታተሉ ግን የቀጥተኛውን ዘይቤ ትርጕም ይመርጣሉ ፤ ምክንያቱም ነጠላ ቀጥተኛ ትርጕም ከሆነ ያኑ የተነበበውን መተርጐም ስለአለባቸው ነው ።

### ምዕራፍ ፫ ።

## የመጻሕፍት ትርጕም በአሁኑ ጊዜ ።

በዚህ በያዝነው በ፳ኛው መቶ ዘመን ጥበባት እየሰፉ ዕውቀትም እየተሻሻለ ሲሄድ እኛም ከዓለም ጋር ለመራመድ እንችል ዘንድ መጻሕፍቶቻችን ሁሉ ከላይ በተናገርናቸው የትርጕም ዓይነቶች ተተርጕመዋል ፤ መተርጐም ብቻ ሳይሆን እየታተሙም በየሰው እጅ እንዲገቡ ሁነዋል ፤ የሊቃውንቱንም ድካም በጣም አቃለዋል ። ይኸን ከፍተኛ ዕድል ለሀገራችን በጠቅላላው ፤ በተለይም ለቤተ ክርስቲያናችን የሰጡ ታላቁ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ናቸው ፤ እርሳቸውም ከሊቃውንቱ ጋር የኖሩ የጉባኤን ጣዕም ያወቁ በመሆናቸው ቤተ ክርስቲያን ብዙ ምሥጢር እንዳላት ሊቃውንቱም የተደበቀ ብዙ ዕውቀት እንዳላቸው በመረዳት ይኸው ተጠብቆ የኖረ የዕውቀት ቅርስ በቀላሉ ለዓለም እንዲደርስ በሀገራችንም በብዛት እንዲታወቅ በማለት ።

ሀ) ሊቃውንቱን ከያሉበት ሰብስበው ልብስ ጉርስ በመስጠት ከችግር እንዲድኑ አድርገዋቸዋል ፤ ወዲያውም የማይተዋወቁት እንዲተዋወቁ ዕውቀት

www.ethiopianorthodox.org

ለዕውቀት እንዲለዋወጡ ዕድል ሰጥተዋቸዋል ፤ ምክንያቱም ሊቃውንቱ ተለያ ይተው የተማሩ ስለሆኑ የተለያየ ሐሳብ ነበራቸው ፤ ስለዚህም ፩ኛው ሁለተኛውን በባለጋራነት ዓይን ይመለከተው ነበር ። ስለዚህም የመጀመሪያው እርምጃ ሊቃ ውንቱ ኅብረት እንዲኖራቸው ሞያቸው መሥመር እንዲይዝ ረድተዋቸዋል ። በዚ ህም መሠረት በጠቅላላ መጻሕፍቶቻችን ግማሹ በአንድም ትርጓሜ እንዲተረ ጐሙ ግማሾቹም በነጠላ ትርጉም እንዲተረጐሙ አድርገዋል ።

ለ) በገንዘባቸው የማኅተም መኪና ከአውሮፓ አስመጥተው የተተረጐ ሙትን መጻሕፍት በቅደም ተከተል አሳትመዋል ፤ ታትመውም ለገዳማት ለአድባ ራት ታድለዋል ።

ሀ) በአንድም ትርጉም ተተርጉመው የታተሙ ፤

፩/ ፬ቱ ወንጌላውያን
፪/ መጻሕፍተ መነኰሳት
፫/ ፲፬ቱ ቅዳሴዎች በመላው
፬/ የዮሐንስ አፈወርቅ መጽሐፍ ፪ ክፍል
፭/ ውዳሴ ማርያምና ቅዳሴ ማርያም
፮/ የፍትሐ ነገሥት መጽሐፍ ።
፯/ ሲራክና ሰሎሞን ፤

ለ) በነጠላ ተተርጉመው የታተሙ ፤

፩ኛ/ መጽሐፍ ቅዱስ በመላ ።
፪ኛ ፲፬ መጻሕፍተ ቅዳሴያት ።
፫ኛ/ የጸሎት መጻሕፍት ።
፬ኛ/ ዳዊት ።
፭ኛ/ ፍትሐ ነገሥት ።
፮ኛ/ ተአምረ ማርያም ።

ሌላም ይኸን የመሰለው ሁሉ ተተርጉሟል ለሕዝብ ለአብያተ ክርስቲያናትም በለጋሥነት ታድሏል።ሌሎች ብዙ ደግሞ ተተርጉመው ለማሳተም ዕድል ያልደረሳቸው መጻሕፍት አሉ፤ እነርሱም ጊዜያቸውን ይጠብቃሉ፤ ከነርሱ ፩ዱ ፍትሐ ነገሥት ነው፤ በዚያን ጊዜ የታተመውን ጠላት ቢያቃጥለው ዕድል አግኝቶ ለመታተም በቅቷል ።

ሐ- የትርጉሙ ሊቃውንት ፤

በትርጉም ሥራ የግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ሐሳብ ደጋፊ በመሆን ቅን አገ ልግሎታቸውን ያበረከቱ የኢትዮጵያ ሊቃውንት ብዙ ናቸው ። የአሠራራቸውም አቅድ በዋሉበት ሞያ በተሠማሩበትም መሥመር ስለሆነ ብዙ ግዳጅን ፈጽመ ዋል ። አንዳንድ ሊቃውንት ግን ፪ ወይም ፫ ዓይና በመሆናቸው በየችሎታቸው

www.ethiopianorthodox.org

እየገቡ ሠርተዋል ። እነዚህም ሊቃውንት ብዙዎች ሲሆኑ ስማቸው በሞያቸውና በሥራቸው የታወቁት የሚከተሉት ናቸው ።

መ. የአንድም ትርጒም ሥራ መምህራን ፤

## ፩ኛ አርባዕቱ ወንጌልን ተርጒመው ያቀረቡ ።

፩ኛ/ መምህር ወልደ ሩፋኤልና አለቃ ገብረ መድኅን ናቸው ።

፪ኛ/ የቅዳሴ መጻሕፍትን መምህር ገሪማ (ብፁዕ አቡነ ሚካኤል) ፤

፫ኛ/ የዮሐንስ አፈወርቅን ድርሳኑንና ተግሣፁን ሊቁ ገብረ ክርስቶስ ፤

፬ኛ/ መጽሐፈ መነኮሳትን ኑረጋዊ መንፈሳዊን መምህር ደስታ(ብፁዕ አቡነ አብርሃም) ማር ይስሐቅን አለቃ ደስታ እሼቴ፤ፊልክስዩስን አባ ገብረ ክርስቶስ (አባ ወግሪስ)

፭ኛ/ መጽሐፈ ሲራክን ደቂቀ ነቢያትን አለቃ ኃይለ ሥላሴና መርስዔ ኀዘን ወልደ ቂርቆስ ፤ (ክቡር ብላታ)

፮ኛ መጽሐፈ ሰሎሞንን አምስቱን ክፍል መልአከ ገነት ክፍሌ ፤

፯ኛ/ አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መጽሐፈ ሕዝቅኤልን ፤

፰ኛ/ መምህር ወልደ ጊዮርጊስ ዘራጉኤል ቅዳሴ ማርያምን ፤

፱ኛ/ መምህር ገሪማ በቅዳሴው ትርጒም የወጣ ቅዳሴ ማርያምን ፤

፲ኛ/ የተአምረ ማርያምን ነጠላ ትርጒም አባ ተስፋ ጊዮርጊስ ፤

፲፩ኛ/ አባ ተስፋ ጊዮርጊስ መዝሙረ ዳዊትን በነጠላ ትርጒም ፤

፲፪ኛ/ ኪዳንንና ትምህርተ ኅቡአትን አባ ኪዳነ ማርያም ።

፲፫ኛ/ ፬ቱ ወንጌልንና ግብረ ሐዋርያትን በነጠላ ትርጒም ብላቴን ጌታ ኅሩይ ወ/ ሥላሴ ናቸው ።

ሠ- ተተርጒመው ሳይታተሙ የቀሩ ፤

፩ኛ/ ቄርሎስን አለቃ በዛብህ ፤

፪ኛ/ ሃይማኖተ አበውን ጌታ አለቃ ገብረ መድኅን ፤

፫ኛ/ ፍትሐ ነገሥትን መንፈሳዊውን አለቃ ገብረ አብ ፤ ሥጋዊውን አለቃ ጠብቄና ግራ ጌታ ወልደየስ ተርጒመዋል እርሱ ግን በኋላ ታትሟል ።

ረ. የመጽሐፍ ቅዱስን ነጠላ ትርጒም የተረጐሙ ።

## ፩ኛ ብሉይ ኪዳንን የተረጐሙ ።

፩ኛ/ መልአከ ገነት ክፍሌ ፤

፪ኛ/ መልአከ ብርሃን ጽጌ ፤

፫ኛ/ መምህር ተክሌ ዘመናገሻ ፤

፬ኛ/ አለቃ ብሉይ ተክሌ ዘጐንደር ፤

፭ኛ/ አለቃ ታመነ ዘአማራ ሳይንት ፤

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ. ሐዲስ ኪዳንን የተረጐሙ ።

፩ኛ/ ንቡረ እድ ተክሌ (ሐዲስ ተክሌ)
፪ኛ/ አለቃ ኅሩይ ዘጐንደር ፤
፫ኛ/ አለቃ ለማ ዘመካነ ሥላሴ ፤
፬ኛ/ አለቃ ቀጸላ ዘእንጠጦ ማርያም ፤

እነዚህ ሊቃውንት እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሁነው በየክፍላቸው በቅንነት ሠርተው ያበረከቱ ናቸው ። ሥራቸውም ቀዋሚና ዘላቂ ሁኖ የነርሱንና የንጉሠ ነገሥቱን ሥራ ሲያስታውስ ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፩ ።

# የሕግ ትምህርት ።

ምዕራፍ ፩ ።

## ሕግጋት በኢትዮጵያ ።

### ፩ኛ የሕግ ትርጉም ።

ሕግ ማለት ሐገገ ሕግ ሠራ ከሚለው ከግዕዙ የወጣ ቃል ነው፤ ቀጥተኛ ትርጉሙም መወሰን፤ መግታት ማለት ነው ፤ ምክንያቱም ሕግ የሰው ልጅ የኑሮው መመጠኛ የመብቱ መወሰኛ የማኅበራዊም ኑሮው መገኛ ነውና ።

ይኸም ማለት አንድ ሰው እንደፈለገው ከሆነ እብድ ወይም ዘመናይ ተብሎ ከማኅበራዊ ኑሮ ውጭ ይሆናል እንጂ በዐዋቂ ሰው ደረጃ የሚገምተው የለም ፤ ይኸም ከሆነ እርሱ የሰውን መብት የደፈረውን ያህል ሌሎችም እርሱን ይደፍሩታል ፤ ስለዚህ ሕግን ይወስናል አጥፊውን ይከላከላል ፤ ከሕግ ውጭ ለሚሆን ሰው ለኑሮውም ልክ መልክ ሊኖረው አይችልም ማለት ነው ። ሕግ በሚለው አንጻር ቀኖና የሚል ቃል ይገኛል ፤ ጥንታዊ የትመጣው ግን የጽርእ ነው ፤ በዚያውም ቋንቋ ሲተረጐም ማሥመሪያ መምሪያ ልክ ማግቢያ ማለት ነው ፤ በአንድ ወረቀት ላይ በትክክል ለመሥራት መሥመር ያስፈልጋል ፤ ለማሥመር ማሥመሪያ ያስፈልጋል ፤ እንዲሁም በዚህ ዓለም ለመኖር ለማኅበራዊ ኑሮም ሥርዓት ለሰው ልጅ ሁሉ ሕግ በግድ ያስፈልጋል ፤ ሕግም በትክክለኛ መንገድ መሥመር ሆኖ ማንኛውንም ሰው ከተፈለገው ግብ ያደርሳል ። በዚህም መሠረት ኢትዮጵያ በሕግ ጸንታ ስትማር ስታስተምር ትኖራለች ፤ ከሕግ ውጭ የሆነችበት ጊዜ ከቶ የለም ፤ እንዲያውም ከጊዜ ወደጊዜ ሕገጋትን እያሻሻለች የሕግ ባለቤት ሁና እንደኖረች የታወቀ ነው ።

### ፪ኛ የሕግጋት መጻሕፍት ቍጥር

ዘመናት አልፈው ዘመናት ሲተኩ ለሰው ልጅ ጊዜውን የመሰለ ሕግ ሊኖረው ያስፈልጋል፤ ስለዚህ ኢትዮጵያ በየጊዜው ያሻሻለቻቸው የሕግጋት መጻሕፍት አሏት። ተሻሽለው ከጊዜ ወደ ጊዜ የተወሰኑት ሕግጋትም ከዚህ የሚከተሉት ናቸው ።

### ሀ. ኦሪታዊ ሕግ ።

ሀገራችን በመጀመሪያው ጊዜ ሕገ ኦሪትን እንደተቀበለች በሙሴ ሕግ ትመራ እንደነበረች የታወቀ ነው ፤ እንዲያውም ከክርስትና በኋላም እስከ አሁን በፍትሐ ነገሥት ውስጥ ሳይቀር ይበልጠው ክፍል ያው ኦሪታዊው ሕግ እንደነበር ጥርጥር የለበትም ፤ ለምሳሌም «ዓይን ቤዛ ዓይን ፤ ሰን ቤዛ ሰን » እየተባለ ሲፈረድ

www.ethiopianorthodox.org

የቆየው በዚሁ መሠረት ነው ። አሠርቱ ቃላት ኦሪታዊ ሕግ ሁኖ እንዲጸና በዚያውም እንዲሠራ ቤተ ክርስቲያናችን ስታስተምር ኖራለች ፤ ግን እንደ አሁኑ የሕግ መጽሐፍ የተለየ አንቀጽ ወጥቶለት የታወቀ አልነበረም ፤ ግን በሃይማኖት መልክ ሲማረውና ሲያስተምረው በዚያውም መሠረት ሲጠብቀው የኖረ ነው ። ይህንም ሕግ ሰው በተላለፈ ጊዜ መንግሥት ሲፈርድበት ቤተ ክርስቲያንም ስት ደግፈው ኑራለች ፤ ይኸም ሕግ ከጥንት ከሕገ ኦሪት የመጣ እንደመሆኑ ኢትዮጵያ ሕገ ኦሪትን ስትቀበል አብራ የተቀበለችው እንደሆነ ይታመናል ።

## ለ· ዲዲስቅልያ ።

ከዚህ ከኦሪታዊ ሕግ በኋላ ደግሞ ዲዲስቅልያ የተባለ የሕግ መጽሐፍ በሀገራችን እንደነበረ ሕዝቡም አክብሮ ተቀብሎ ሲማረውና ሲያስተምረው እንደኖረ የታወቀ ነው ። ዲዲስቅልያም ማለት ቃሉ የጽርእ ቃል ሲሆን ትር ጉሙ ትምህርት ማለት ነው ። ቅዱሳን ሐዋርያት ከሐዲስ ኪዳን ለትምህርት ያውጣጡት ነው ፤ አሁንም ቢሆን በሌሎች ቤተ ክርስቲያን ስሙ እንደሚያመለክ ተው ለትምህርት ተዘጋጅቶ ይገኛል ፤ እንዲያውም ለትምህርተ ሕፃናት ጠቃሚ ሆኖ በመገኘቱ እስከ አሁን እንደሚጠቀሙበት የታወቀ ነው ። በኛ ቤተ ክርስ ቲያን የሚገኘው ዲዲስቅልያ የተባለው መጽሐፍ ግን የተዘጋጀው ከትምህርቱ ይልቅ በሕግ መልክ ነው ፤ ይኸም ማለት ወደ ሐዲስ ሕግ ስንዛወር የክርስቲ ያን ወገኖች ሁሉ ይማሩት እንደነበር የታመነ ነው ። ችግሩ ግን ከመቼ ጀምሮ እስከ መቼ ተሠራበት የሚል ጥያቄን የሚያስከትል ሆኖ ይገኛል ፤ የሆነው ሁኖ ለሞራል ሕግ ጠቃሚ በመሆኑ አባቶች በሥርዓተ ትምህርት ውሳኔ ውስጥ እንዳ ስገቡትና ሁሉም እንዲማሩት እንዳደረጉት «መቅድመ መሐርዎሙ ለውሉድ ክሙ መጽሐፈ ሲራክ ወሰሎሞን ወመዝሙረ ዳዊት ወዲዲስቅልያ» ሲል እናገኘ ዋለን ፤ እስከ ቅርብ ጊዜም በዚሁ መሠረት ይጠቀሙበት እንደነበር የታወቀ ነው ፤ ይኸም መጽሐፍ ፵፫ አንቀጽ ያለው ሁኖ ይገኛል ።

## ሐ· ቀሌምንጦስ ።

ቀሌምንጦስ የተባለው እንደሰብአ አርድእት የሚቆጠር ፣ የቅዱስ ጴጥሮስ ደቀ መዝሙር የሆነ በኋላም ጊዜ በሮም ኤጲስ ቆጶስ የተሾመ ሰው ነው ። እርሱም በስሙ የሚጠሩ ፰ መጻሕፍት ጽፏል ፣ ከነርሱም ውስጥ ፫ ብቻ እንደ ሕግ መጽሐፍ ተቈጥረው በሕግ መጽሐፍ ይጠቀሳሉ፤ሌላው ግን ታሪክነቱን የያዘ ይመስላል፤ይሁን እንጂ ሁሉም በቋንቋችን ተተርጉመው ከሕግ መጻሕፍት ውስጥ ገብተው ይገኛሉ ፤ የመጀመሪያው ቀሌምንጦስ ፸፩ ቀኖናዎችን ይዞ ይገኛል ፤ የርሱም መሪ ምልክቱ ረስጣ ይላል ።

ሁለተኛው ቀሌምንጦስ ፶፯ ቀኖናዎች ይዞ ይገኛል ፤ መሪ ምልክቱም ረስጠብ ይላል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሦስተኛው ቀሌምንጦስም ፹፪ ቀኖና ብቻ አሉት ፤ የርሱም መሪ ምልክቱ ረስጠጅ የሚል ነው ።

እነዚህም ክፍሎች በአንድ ስም ሲጠሩ ቀሌምንጦስ ይባላሉ ፤ በመሪ ምልክቶች ሲገኙ ግን ከላይ እንደገለጥነው ነው ። በቤተ ክርስቲያናችን ሌላ ተጨማሪ ስም አላቸው ፤ ይኸውም ትእዛዝ ፤ ግጽው ፤ አብጠሊስ የሚል ነው ። ፫ኛው መጽሐፍ ግን በግብፃውያን ዲዲስቅልያ በማለት የታወቀ ነው ፤ እንዲሁም ትእዛዝን ግጽውን አብጠሊስን ፫ቱን አንድ አድርጎ ፫ኛው ቀሌምንጦስ አለው እንጂ ሁሉም አንድ ነው የሚሉ አሉ ።

## መ. ሲኖዶስ ።

ሲኖዶስ ማለት ጉባኤ የቤተ ክርስቲያኖች አንድነት ስብሰባ ማለት ሲሆን ውሳኔውም እንዲሁ ሲኖዶስ ይባላል ፤ ከዚህ ላይ ግን ሲኖዶስ በማለት የሚነገረው ቃል የሲኖዶሶችን ውሳኔዎች ነው ፤ ይኸም ከሐዋርያት ጀምሮ እስከ መካከለኛው መቶ ዘመን የተደረጉት የሲኖዶስ ውሳኔዎችን ይዞ የሚገኝ መጽሐፍ በመሆኑ ይኸን ስም ወስዷል ። ከውጭ የተተረጐመ ብቻ አይመስልም ከኛም በየጊዜው ሳይጨመርበት አልቀረም ለምሳሌ ፫ኛው ክፍል ላይ በ፲፰ኛው መቶ ዘመን የተወሰነውን ፈውስ መንፈሳዊን በከፊል አስገብቶት ይገኛል ።

መጽሐፉም ፫ ክፍል ሲኖረው ማን እንደሰበሰበው ፤ መቼ እንደተሰበሰበ ግልጥ የሆነ ማስረጃ የለውም ፤ ይሁን እንጂ የዘመኑን ቅደም ተከተል ጠብቆ የተሰበሰበና በ፫ትም ክፍል የተከፈለ ስለሆነ ፩ኛውን በ፫ኛውና በ፬ኛው መቶ ዘመን የነበሩ አባቶች ሰብስበው በ፩ ክፍል ያቆዩት ይመስላል ። ፪ኛውን ክፍል ደግሞ ጉባኤዎቹ ከተፈጸሙ በኋላ በ፮ኛውና በ፯ኛው መቶ ዘመን ሰብሰበው ከጥንቱ ጋር ያገናኙት ይመስላል ። ፫ኛው ግን በጣም ቀረብ ያለ ዘመን ያለው ሲመስል ውሳኔውም ኢትዮጵያዊ ይመስላል ፤ ምክንያቱም ቴዎድሮስ የተባለ የ፩ ገዳም መምህር ከጻፈው የተውጣጣና ከፈውስ መንፈሳዊ ውስጥ ብዙ የገባ ስላለበት ነው ። ይሁን እንጂ ይኸ ሲኖዶስ የተባለው መጽሐፍ የዓለም ቤተ ክርስቲያናት ጉባኤዎችንና የብሔራዊ ቤተ ክርስቲያን ውሳኔዎችን ጠንቅቆ የያዘ እትስጉቡዕ ስለሆነ ለሕግ መጽሐፍ ምንጭነት ከፍ ያለ ጥቅም አለው ። ማንኛውም የሕግ መጽሐፍ ቅጅ ሲሆን እርሱ ግን የሕግ ምንጭ የሕግጋት እናት መሆኑ ነው ። እርሱም በ፫ት ክፍል ይከፈላል ስንል በአንዳንዱ ክፍል ምን ዓይነት ሕግ እንደሚገኝና ቍጥሩስ ስንት እንደሆነ በሚከተለው እንገልጣለን ።

በክፍል ፩ ውስጥ ፲፫ ምዕራፎች ይገኛሉ ፤ ይኸውም የሐዋርያ ቀኖና የተባለው ነው ። ከ፩ኛው ክፍል ፸፩ አንቀጽ ይገኝበታል ፤ በ፪ኛው ክፍል ፶፮ አንቀጽ ይገኝበታል ። በ፫ኛው ክፍል ፹፫ አንቀጽ ይገኝበታል ፤ በ፬ኛው ክፍል ፹፩ ትእዛዛት ይገኙበታል ። ይኸውም ክፍል የሐዋርያት ቀኖናዎች ትርጉም


www.ethiopianorthodox.org

## ረ· ፈውስ መንፈሳዊ ።

ይኸ መጽሐፍ ደግሞ ማን እንደደረሰው ፣ መቼ እንደተደረሰ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም ። በኛ ቤተ ክርስቲያን እንደሚነገረው የሆነ እንደሆነ ፣ ፍትሐ ነገሥት ከመተርጐሙ በፊት በአፄ ዘርዓ ያዕቆብ ጊዜ የተቀመረ እንደሆን ነው ፤ ይኸውም እርሳቸው ሊቃውንቱን አዘው የተዘጋጀ ነው ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ይሠራበት የነበረ ሕግ እንደሆነ ይነገርለታል ፤ የውጪ ሊቃውንት እንደሚያስረዱት ደግሞ ፣ አፄ ዘርዓ ያዕቆብ ብሔራዊ የቤተ ክርስቲያንን ሥርዓት ለጊዜያቸው ተስማሚ በሆነ መንገድ ለመሥራት ተነሣሥተው በወሰኑ ጊዜ ፣ እንደ ዓላማቸው ለመምራት ይችሉ ዘንድ የወሰኑት ፣ ያጻፉት ሕግ እንደሆነ ይነገራል ። የተውጣጣውም ከዚህ በላይ ከተነገሩት መድበሎች እንደሆነ ብዙው አንቀጽ ያስረዳናል ። ይኸም ከሆነ በ፲፭ኛው መቶ ዘመን የተወሰነ ሕግ እንደሆነ ይታወቃል ፤ ነገር ግን አሁንም ቢሆን መነሻው ይታወቅ እንጂ ፣ መድረሻው እስከ መቼ እንደሆን እስከ መቼስ እንደሠራ ግልጥ ሆኖ አይታወቅም ። ከዚህ በላይ የዘረዘርናቸው ሕግጋት ሁሉ ብዙውን ጊዜ የሚመለከቱት የቤተ ክርስቲያንን ሥነ ሥርዓት ነው እንጂ ፣ ስለሥጋዊ ሕይወት ሰፋ ያለ አስተያየት የላቸውም ፤ ምክንያቱም ንጉሡ የሃይማኖትም ፣ የፖለቲክም መሪ እንደነበር ሕዝቡም በአንድ ሕግ ይተዳደር እንደ ነበር የሚያመለክተን ነው ። ስለዚህ ሕግጋት አዋቂዎች ፣ ፈራጆች ይኸን ሁሉ ጠንቅቀው ማወቅና መፍረድ ለደቀ መዛሙርቱም ማስተማር ግድ ነበረባቸው ይኸም መጽሐፍ ፶፩ አንቀጽ ያለው ነበር ።

ከነዚህ ሕግጋት ውስጥ ምንም ትርጕሙ ባይቃና ስለሥጋዊም ስለመንፈሳዊም አስተዳደር ሰፋ ያለ አስተያየትን ይዞ ሕዝብ ሲተዳደር የኖረው የፍትሐ ነገሥቱ ነው ።

### ምዕራፍ ፪ ።

## ፍትሐ ነገሥት ።

ፍትሐ ነገሥት ስሙ እንደሚያመለክተው የነገሥታት መጽሐፍ ወይም መፍረጃ ማለት ነው ። ግን ሥጋዊ ሕግ ብቻ ወይም የነገሥታት ብቻ መፍረጃ አልነበረም ፤ ነገር ግን መንፈሳዊና ሥጋዊ ክፍል ያለው ትልቅ መጽሐፍ ነው ። ፍትሐ ነገሥት በሚለው መጽሐፍ በሃይማኖትም በሥጋዊም የመጨረሻውን ፍርድ ይሰጡ ነበር ። ፍትሐ ነገሥት መንፈሳዊ ክፍል ይኑረው እንጂ ፣ በመንፈሳዊውም ቢሆን ቅሉ የመጨረሻውን ፍርድ ይሰጥ ይሠራ ይቀጣ የነበረው ንጉሡ ነውና ያን በመመልከት ፍትሐ ነገሥት ይለዋል ፤ እንዲያውም መንፈሳዊ ያለው ቤተ ክርስቲያንን ወይም ሃይማኖትን ሲመለከት ነው እንጂ ፣ ሥጋዊ ክፍል ያለውና ብዙውንም የሥጋዊ ዳኝነት ይመለከታል ። ፍትሐ ነገሥት በጠቅላላው በመ

www.ethiopianorthodox.org

ንፈሳዊና በሥጋዊ ክፍል ይከፈል እንጂ ፡ አንቀጽ ከአንቀጽ በማያያዝ ያለማቋረጥ ሲቈጠር ፶፩ አንቀጽ እንዳለው የታወቀ ነው ።

## ፩ኛ መንፈሳዊ ።

መንፈሳዊ ክፍል የሚባለው ፳፪ አንቀጽ አለው ፤ እርሱም ፍጹም የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ሕግጋትን ስለያዘ መንፈሳዊ ክፍል ተብሏል ።

፩ኛ አንቀጽ ስለቤተ ክርስቲያን መሠረት ይናገራል ፤ የማንኛውም መንፈሳዊን አገልግሎት መሠረቱ ቤተ ክርስቲያን ነውና ፤ በዚሁም አንቀጽ ቤተ ክርስቲያን ወይም ለቤተ ክርስቲያን የሚያስፈልጉትን ነገሮች በዝርዝር ያስረዳል ።

፪ኛ አንቀጽ ስለመጻሕፍት አምላካውያት ይነገራል፤ ይኸም ክፍል በመጀመሪያ ቅዱሳት መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር መሆናቸውን በመንፈስ እግዚአብሔር መጻፋቸውን ያስረዳል ። ስማቸውንም መጻሕፍት ውኩፋት ፥ ወይም መጻሕፍት አምላካውያት ይላቸዋል ፤ ከዚያም ቀጥሎ ቍጥራቸውንና ስማቸውን ይዘረዝራል ።

፫ኛ አንቀጽ ፥ ስለ ጥምቀተ ክርስትና ይናገራል ፤ ይኸም ክፍል በመጀመሪያ ጥምቀት ለትንሽም ለትልቅም ፥ ለወንድም ለሴትም በጠቅላላ ለሰው ልጅ የተሠራ መሆኑን ያብራራል ። ቀጥሎም የጥምቀቱን ሥነ ሥርዓት ይደነግጋል ።

፬ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ሊቃነ ጳጳሳት ሹመት ፥ ስለ ሥራቸው ፥ ስለ ኑሯቸው በቅዱሳት መጻሕፍት የተገለጠውን በመጥቀስ ዘርዝሮ ያስረዳል ። በ፪ ደረጃ በአስተያየት የተወሰነውን ሊሠሩት የሚገባቸውንም ይናገራል ።

፭ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ኤጲስ ቆጶሳት አመራረጥ ፥ ስለ አኗኗራቸው ይናገራል ፤ ማለት በምርጫው ጊዜ ተገቢነቱን ወይም የማይገባ መሆኑን ልዩ ማስረጃ ያለው መሆኑን በሰፊው ዘርዝሮ ያስረዳል ።

፮ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ቀሳውስት ይናገራል ፤ እርሱም መጀመሪያ የመመረጫቸውን ፥ ቀጥሎም የችሎታቸውን ፥ መጨረሻም የሥራቸውን ነገር ይናገራል ፤

፯ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ዲያቆናት ይናገራል ፤ እርሱም በጠቅላላ አሳቡ እንደ ቀሳውስት ነው ።

፰ኛ/ ስለ ንዑሳን መዓርጋት ይናገራል ፤ እነርሱም ንፍቀ ዲያቆን ፥ አናጉንስጢስ (አንባቢ) መዘምር ፥ አፃዌ ኆኅት ናቸው ፥ እንዲሁም ስለ ደናግልና እነርሱን ስለ መሳሰሉት ምርጫቸውን ይናገራል ።

፱ኛ/ ካህናት ሊሠሩት የሚገባውን ይገልጣል ።

፲ኛ/ ስለ መነኮሳት ይናገራል ፤ እርሱም ወደ ምንኵስና ዓለም የገባ እንደ ሆነ የመነኮሳት ሥራ እንዴት እንደሆነ በዝርዝር የሚያስረዳ ነው ።

፲፩ኛ/ ሕዝባውያን ወይም ምእመናን ሊሠሩትና ሊፈጽሙት የሚገባቸውን ይናገራል ።

www.ethiopianorthodox.org

፲፪ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ቅዳሴ ይናገራል ፤ ማለት የቅዳሴውን ሥነ ሥርዓት የመቀደሻውን ንዋያት ይናገራል ።

፲፫ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ቍርባን ይናገራል ፤ ማለት የቍርባኑን ዓይነት ይናገራል

፲፬ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ጸሎት ይናገራል ፤ ማለት የጸሎቱን ሥነ ሥርዓት ፣ የጸሎቱን ሰዓታትና ዓይነት ይናገራል ።

፲፭ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ አጽዋማት ይናገራል ፤ ማለት የአጽዋማትን ቍጥር የጊዜያቸውን ሁናቴ ፣ የሚከለከሉትን ነገሮች ሁሉ በሰፊው ያስረዳል ።

፲፮ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ምጽዋት ይናገራል ፤ የምጽዋትን ትርጉም ፣ የምጽዋትን ዓይነት ፣ የምጽዋትን ጥቅም ይናገራል ።

፲፯ኛ/ አንቀጽ ፣ በንዋየ ቅድሳት ላይ ስለሚሾሙ ምእመናን ይናገራል ማለት የሹመቱን ዓይነት ፣ የሥራውን ዝርዝር ያመለክታል ።

፲፰ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ አሥራት ፣ በኵራት ይናገራል ፤ ማለት ምእመናን ሁሉ ከገቢያቸው ፤ መጀመሪያም የደረሰውን ፤ ከሀብቱም ከ፲ አንዱን እንዲሰጡ ያዛል ።

፲፱ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ በዓላት አከባበርና ስለ በዓላትም ይናገራል ።

፳ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ሰማዕታት ይናገራል ፤ ማንም ሰው ምስክርነቱን መስጠትና ምስክርም ሁኖ መቅረብ እንደሚገባው ይናገራል ።

፳፩ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ድውያን ይናገራል ፤ ማለት በሽተኞች በጸሎት ሊፈወሱ እንደሚችሉ ይናገራል ።

፳፪ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ሙታን ይናገራል ፤ ማለት ስለ ፍትሐቱ ፣ ስለ ልቅሶው ይናገራል ።

## ፪ኛ ሥጋዊ ።

ሥጋዊ ክፍል የሚባለው ፳፱ አንቀጽ አለው፤ በመንፈሳዊ ክፍል ስለ መንፈሳዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንደሚያስረዳ ፣ በዚህም በሥጋዊው ክፍል ስለ ሥጋዊው የአስተዳደር ሥርዓት ይናገራል ። የአንቀጹ አቈጣጠር ግን ከመንፈሳዊው ጋር ይያያዛል ።

፳፫ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ መብል ፣ ስለ ልብስ ፣ ስለ ቤትና ስለ ተግባረ እድ ፤ እንዲሁም ክርስቲያን የሆነ ሁሉ ሊያደርገው ስለሚገባ ይናገራል ፤ ማለት እንዲህ ያለውን መብል ብሉ (አትብሉ) ፣ እንዲህ ያለውን ልብስ ልበሱ (አትልበሱ) ፣ እንዲህ ያለውን ቤት ሥሩ (አትሥሩ) እያለ ያስረዳል ።

፳፬ኛ/ አንቀጽ ፣ ስለ ማጨት ፣ ስለ መታጨት ፣ ስለ ማግባት ይናገራል ፤ ማለት ወንድ ለሴት ማጫ መስጠትና ወንድ በስንት ዓመቱ ፣ ሴትም በስንት ዓመቷ ማግባት እንደሚገባ ያስረዳል ። በመንፈሳዊና በሥጋዊ ተዘምዶ መካከል በስንተኛው ቤት መጋባት እንደሚቻል ፣ ቀጥሎም ጋብቻ በምን ዓይነት ነውር መፍረስ እንደሚቻል ይገልጣል ፤ ደግሞም የተቻለው ሰው ጋብቻን ሊተው እንደሚገባም ሲል ያብራራል ።

www.ethiopianorthodox.org

፳፭ኛ/ አንቀጽ ፡ ዕቁባት ማስቀመጥ እንደማይገባ ይናገራል ፤ ማለት ያገባም ሆነ ያላገባም በሕገ ወጥነት ዝሙት መሥራት ከሰማንያ ውጪ ዕቁባት ማበጀት በሕግ የተከለከለ መሆኑን ይገልጻል ።

፳፮ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ስጦታ ፡ ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል በተወሰነ ጊዜ ስጦታ ማድረግና በተወሰነው ጊዜ ያለአጠፌታ መቀበል እንደሚገባና ስለ ሰጪው ፡ ስለ ሚሰጠው ሰውና ስለሚሰጠው ገንዘብ ያብራራል ።

፳፯ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ብድር ፡ ስለ መያዣ ፡ ስለ ዋስትና ፡ ስለ ምግብና ይናገራል ማለት ያለ አራጣ ማበደር የእግዚአብሔር ትእዛዝና ከምጽዋትም የሚቈጠር እንደሆነ ፡ ተበዳሪም ለመክፈል ማሰብ እንደሚገባው ይናገራል ። ቀጥሎም ተበዳሪ መያዣ መስጠት ፡ ዋስ መጥራት እንደሚገባው ይገልጻል ።

፳፰ኛ/ አንቀጽ ስለ ትውስት ይናገራል ፤ ማለት የተውሶን ገንዘብ ወይም እንስሳ እስከ ተወሰነ ጊዜና እስከ ተወሰነ ቦታ ያለመያዣ በኪራይ ማዋስ እንደሚገባ ያስረዳል ።

፳፱ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ አደራ ይናገራል ፤ ማለት አደራ አስቀማጭ የሚያስቀምጠውን ነገር ለይቶ ማስቀመጥና አደራ ተቀባዩም ተግቶ መጠበቅ ፡ ከተቀበለ በኋላም በአደራው ዕቃ መጠቀምና ለሌላ አሳልፎ መስጠት እንደማይገባ ይናገራል ።

፴ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ምግብና (ሹመት) ይናገራል ፤ ማለት አንድ ሰው በገንዘብ ላይ ታማኝ ሁኖ መሾም እንዲገባው ያብራራል ።

፴፩ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ነፃነት ፡ ስለ ባርነትና ስለ ነፃ አውጪዎች ይናገራል ፤ ይህ ክፍል አገልጋይ ምን ዓይነት ሥራ ለጌታው ቢሠራ ነፃ መውጣት እንደሚገባውም በንዑሳን ክፍሎች ይገልጻል ። ቀጥሎም አንዱ ለአንዱ መገዛት በምን ምክንያት እንደመጣና ሁሉም በተፈጥሮ እኩል መሆኑን ያስረዳል ።

፴፪ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ምግብና ይናገራል ፤ ማለት አካለ መጠን ባላደረሱ ልጆችና አእምሮአቸውን ባጡ ሰዎች ላይ ፡ ደግሞም ወላጆች ባረጁ ጊዜ በነርሱ ላይ ልጆች እንደ ሞግዚት እንዲሆኑ ያብራራል ።

፴፫ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ መሸጥና መግዛት ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል ሻጭና ገዥ እርግጠኛ በገንዘባቸው ላይ ባለመብቶች ካልሆኑ መሸጥ ወይም መግዛት እንደማይችሉ ፡ ቀጥሎም መሸጥ የማይገባው እንዳይሸጥ ፡ መሸጥና መግዛት የማይፈቀድባቸውንና የሚፈቀድባቸውን ዕለታት ለይቶ በ፯ ንዑሳን ክፍሎች ያስረዳል ።

፴፬ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ሽርክና ይናገራል ፤ ማለት ፪ና ፫ ሰዎች ወይም ከዚህ በላይ ሁነው ገንዘብ በማዋጣት ፡ ገንዘብ የሌለውም በጉልበት ከባለገንዘቦች ጋር በመሻረክ መነገድና ማትረፍ እንደሚችል ያብራራል ።

፴፭ኛ/ አንቀጽ ፡ ስለ ማስገደድና ስለ መቀማት ይናገራል ፤ ማለት አንዱ ሌላውን ስለ ሃይማኖት ቢያስገድደው መታገሥና መከራ መቀበል እንደሚገባው ቀጥሎም የማይገባውንና የተከለከለውን እንዲያደርግ ማስገደድ እንዳይገባ

www.ethiopianorthodox.org

እንዲሁም አንዱ የራሱ ያይደለውን ቢቀማና ለራሱ ገንዘብ ቢያደርግ ስለማይገባ ያብራራል ።

፴፯ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ ኪራይ ፤ ስለ አከራይና ተከራይ ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል አንድን ነገር በሙሉ ወይም በከፊል ስለማከራየት ፤ ይገልጣል ። ቀጥሎም መከራየት (ማከራየት) ስለሚፈርስበት ፤ ሠራተኛን ስለ መቅጠርና ስለ መቀጠር ያስረዳል ።

፴፰ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ መንገዶች ፤ ስለ ሜዳዎች ፤ ስለ አካባቢ ሕንፃና ፤ ስለ ማደስ ፤ ስለ ውሀ ቦዮች ይናገራል ፤ ማለት በቤትና በቤት ፤ በአትክልትና በአትክልት መካከል ምን ያህል ስፋት መኖር እንደሚገባ ፤ ሕንፃን በማደስ ጊዜ በአንዱና በሌላው መካከል ስላለው ስምምነት በ፯ ንዑሳን ክፍሎች ይገልጻል ።

፴፱ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ ብድር ትርፍ የጋራ ይናገራል ፤ ማለት ሁለት ሦስት ከዚህ በላይም ሁነው ቢሆንም ገንዘብ ተበድረው በትርፍ መጋራት እንደሚገባ ፤ የሚበደሩትም ገንዘብ በሚዛን ፤ በቍጥር ተለይቶ የታወቀ ካልሆነ ስምምነቱ እንደማይጸና ያብራራል ።

፵፩ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ መታመን ይናገራል ፤ ማለት አካለ መጠን ያደረሰ አእምሮው ልክ የሚሠራ ፤ በሌላ ሰው ሥር ያይደለ ፤ ኃጢአትን ስለ መናገርም ሆነ ስለ ገንዘብ ቢናገር ቃሉ ሊታመን እንዲገባ ያስረዳል ፤ ቀጥሎም ከላይ ከተጠቀሱት ውጪ የሆነ ቢናገር ቃሉ ታማኝ እንደማይሆን ይገልጻል ።

፵ኛ/ አንቀጽ ፤ ከጠፉ በኋላ ስለሚገኝ ነገር ይናገራል ፤ ማለት አንድ ዕቃ ወድቆ ቢገኝ ወይም ልጅ እንስሳ ሲኮበልል ቢገኝ ባለቤቱ (ጌታው) እስከሚፈልገው ድረስ በጥንቃቄ ማስቀመጥና መጠበቅ እንዲገባ በሰፊው ያብራራል ።

፵፩ኛ/ አንቀጽ ፤ በገንዘቡ ማዘዝ ስለሚገባው ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል አንድ ሰው ገንዘቡን በጽሑፍ ወይም ያለ ጽሑፍ ለሌላ ማዘዝ እንደሚችል ፤ በሚሞትበትም ጊዜ ለወደደው ሊሰጥ እንደሚችል ይገልጻል ። ቀጥሎም ምንም ባለገንዘብ ቢሆን በሌላ ሥር ያለ አካለ መጠን ያላደረሰ ፤ አእምሮው ልክ የማይሠራ በሽተኛ በገንዘቡ ማዘዝ እንደማይችል ያብራራል ።

፵፪ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ ርስት ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል ውርስ የሚገባቸውም በአባት በኩል እስከዚህ ፤ በእናት በኩል እስከዚህ ትውልድ ድረስ ያሉ ይውረሱ ፤ ከዚያም ወንድ ይሁን ያህል ፤ ሴት ይሁን ያህል ትውረስ እያለ ስለ ውርስ በሰፊው ይገልጻል ።

፵፫ኛ/ አንቀጽ ፤ ስለ ዳኛ ፤ ስለ ምስክሮች ይናገራል ፤ ማለት ዳኛ በግድ አስፈላጊ እንደሆነ ፤ ዳኛ መሆን የሚገባው ምን ዓይነት ሰው እንደሆንና ስለ ሹመቱ ስለ አመራረጡ በሰፊው ይገልጻል ። ቀጥሎም ማንኛውም ሰው ስለሚያውቀው ስለ ሰማው ፤ ስለ አየው ምስክር መሆን እንደሚችል ምስክር ለመሆን የሚችል ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ ያብራራል ።

www.ethiopianorthodox.org

፵፬ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ነገሥታት ይናገራል ፤ ይኸ ክፍል የሚነግሠው ንጉሥ ከምን ወገን ስለሚመረጥ ፥ ስለሚያደርገው ነገር ፥ ማድረግም ስለማይገባው ነገር በሰፊው ይገልጻል ።

፵፭ኛ/ አንቀጽ ፥ ከብሉይና ከሐዲስ ተውጣጥቶ መነገር ስለሚገባው ይናገራል ፤ ማለት እግዚአብሔር በአሪት ለሙሴ የሰጠውን አሥሩን ትእዛዛትና ሌሎችንም ኋላ በሐዲስ ራሱ ጌታችን ክርስቶስ በተራራው ስብከቱ ላይ የተናገራቸውን ስድስቱን ትእዛዛትና ሌሎችንም በሰፊው ያብራራል ። ቀጥሎም ከተከታዮቹ የተነገሩትን የምክር ቃላት ያስረዳል ።

፵፮ኛ/ አንቀጽ ፥ አምላክን ስለሚክዱ ሰዎች ቅጣት ይናገራል ፤ ማለት አምላክን ቢክዱ ምን ዓይነት ቅጣት እንደሚፈጸምባቸውና ለመካድ የሚያደርስ ልዩ ልዩ የባዕድ አምልኮት ፥ ዘርፍ የሆነውን መሥራት እንዳይገባ በሰፊው ያስረዳል ።

፵፯ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ መግደልና ስለ ቅጣቱ ይናገራል ፤ ማለት መግደል በሕግም ሆነ በፍትሕ ጠባይአዊ ክልክል መሆኑንና የድርጊቱን ሁናቴ ማለት በስሕተት ወይም በቂም ፥ በዛቻ ፥ በድፍረት ቢፈጸም ቀጥሎም ስለገዳይና ባለደም እርቅ ፥ ስለ ገዳይ መጸጸት ያስረዳል ።

፵፰ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ዝሙት ፥ በመንፈሳዊና በሥጋዊ በኩል ስለሚደረገው ቅጣትም ይናገራል ። ይህ ክፍል ሚስት ያገቡ በሚስት ላይ ፤ ያላገቡም በማግባት ፈንታ በሕገ ወጥነት ስለሚፈጽሙት የዝሙት ሥራ ቅጣቱን ደረጃ በደረጃ ይሰጣል ።

፵፱ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ሌቦች ሥጋዊና መንፈሳዊ ቅጣት ይናገራል ፤ ማለት ከቤተ ክርስቲያንና ከሌላ ቦታ ከሰረቀ በቀን ከሰረቀና በሌሊት ከሰረቀ ሰው ቅጣት ፥ ከሕዝባዊ ሌላና ከካህን ሌባ ቅጣት ደረጃ እየሰጠ ያብራራል ።

፶ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ስካር ፥ ስለ አራጣ ፥ ስለ ዓመፀኛ ልጅ ፥ ስለ ነገር ሰብቅ ፥ በጠቅላላ ስለ ልዩ ልዩ ኃጢአተኞች ይናገራል ። ይህ ክፍል ኃጢአት ሁኖ ሊያስቀጣና ከማኅበራዊ ኑሮ ውጪ ሊያደርግ የሚችለውን ነገር ከመፈጸም መከልከል እንደሚገባ ይገልጻል ።

፶፩ኛ/ አንቀጽ ፥ ስለ ጸጉር ማሳደግ ፥ ስለ ግዝረት ፥ ስለ መታመን ፥ ደግሞም የጊዜው ሹም (አለቃ) እንደጊዜው እንደዘመኑ በተወሰነው ላይ መጨመር ፥ ከተወሰነው ላይ መቀነስ እንደሚገባው ይናገራል ፤ ማለት ጸጉርን ማሳደግ ፥ ጸጉርን መላጨት መገዘርና አለመገዘር ፥ በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ እንዴት እንደሆነ በሰፊው ያብራራል ።

በመጨረሻም ከ፵፪ኛው አንቀጽ ጋር የሚመሳሰል ፥ በአንዳንድ የትውልድ ሐረግ የሚለይ በ፬፻፵፬ ዓ. ም. የእስክንድርያው ሊቀ ጳጳስ ቄርሎስ የጻፈው የመወራረስ አንቀጽ አለ ። ይኸ ክፍል ወደላይና ወደታች ፥ ወደጐንና ወደጐን ትውልድን ሰፋ አድርጎ በመቍጠር ያወራረስን ነገር በሰፊው ያስረዳል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ምዕራፍ ፫ ።

# የፍትሐ ነገሥት እውነተኛነት

ፍትሐ ነገሥት የሚባለው መጽሐፍ የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ እንደሆነ በማመን
በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንና መንግሥት ታላቅ ክብር ያለውና ቅዱስነትም የሚሰጠው
ሕግ ነው።ከክብሩም ብዛት የተነሣ ማንም እየተነሣ አባላ እንዳይመታው፤ለተለዩ ሰዎች
በትምህርት መልክ ብቻ ሲሰጥ ቆይቷል፤ጉባኤውም የሚኬደው በሰገነት ነበር፤
የሕግ ዐዋቂውም ሰው ይከበርና ሊቁ የመባልም ማዕረግ ይሰጠው ነበር። ብዙ የም
ርምር ሰዎች ግን ፍትሐ ነገሥቱ በሰገነት ይኬድ የነበረበት ምክንያት ከክብሩ
ይልቅ ሁሉም የሕግ ሊቅ እንዳይሆን በምቀኝነት እንዲሠወር የተደረገ ዘዴ መሆ
ኑን ይናገራሉ። ሌሎች ደግሞ ሁሉ ጥራዝ ነጠቅ እንዳይሆን ትምህርቱ ለሚከተት
ላቸው ደቀ መዛሙርት ብቻ ይሰጥ ስለነበር በሰገነት መኬድ ግድ ሆነበት ይላሉ።
በዚያም ሆነ በዚህ ምክንያት በሰገነት መኬዱ ግልጥ መሆኑንና ሕግ ለሁሉም አለ
መዳረሱን ማመን ሲኖርብን ፍትሐ ነገሥቱ ግን ከፍ ያለ ክብርና ተፈላጊነትም እንደ
ነበረው የታመነ ነው። መጽሐፉ በብዙ ሊቃውንት እጅ ባለመዋሉ ደግሞ ብዙ አቃ
ቂር ሳይደረግበት ዕውነቱና ሐሰቱ ሳይገለጥበት ይኖራል፤ማለት ሁሉም የ፫፻፲፰
ሊቃውንት ውሳኔ ሳይሆን በየጊዜው የተደረጉ የዓለም ቤተ ክርስቲያንና የብሔ
ራዊ ቤተ ክርስቲያን ሲኖዶሶች ተገናኝተው የተቀመሩ መሆናቸውን የሚያውቁ
በመጠኑ ናቸው። እንዲሁም ከጽርዕ የተተረጐመ እንደመሆኑ አብርሃም ቀሲስ ወደ
ዓረብኛ ሲተረጉም ከራሱ ስሜት እያወጣ የጨመረበት ብዙ ይገኛል፤ በዚህ
አንፃርም ከቀድሞው ውሳኔ ያስቀረው ሊኖር ይችል ይሆናል። ፍትሐ ነገሥት
የሚል ስም የተሰጠውም ወደ ግዕዝ ሲተረጐም ሳይሆን አይቀርም፤ ውሳኔው ሥጋ
ዊና መንፈሳዊ ሲሆን የነገሥት ፍትሕ መሆኑን ሲያመለክት የቤተ ክርስቲያን
ድርሻ የሆነውን ፍትሕ የረሳ ይመስላል፤ ነገር ግን ነገሥታቱ የሃይማኖትም የአ
ስተዳደርም ኃላፊነት እንደነበራቸው ለማስታውስ ያህል ነው በማለት ፍትሐ ነገ
ሥት ብለውታል። እንዲያውም ሊቃውንቱ እንደሚያትቱት ፍትሐ ነገሥቱ ሊተረ
ጐም የቻለው አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በተመኙት መሠረት መሆኑ እርግጥ ነው፤ ይኸውም
አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በመጀመሪያ መናኝ የነበሩ ፍጹም መንፈሳዊ ንጉሠ ነገሥት ነበሩ፤
ከርሳቸው በፊት ያልነበረ ለጊዜው ተመሳሳይ ከሕዝብ ጋር የሚያስተሣስር ሕግ ለሀገ
ራቸው እንዲታወጅ ያስደረጉትም ከእውነተኛነታቸው የተነሣ መሆኑ ግልጥ ነው፤
እንዲያውም ዘርዓ ያዕቆብ ከሚለው ስያሜ ሌላ ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ የሚለው
የማዕርግ ስያሜ የተሰጣቸው በዚሁ ሕግ ቀማሪነታቸው ነው፤ ምክንያቱም ቆስጠ
ንጢኖስ ፫፻፲፰ቱን ሊቃውንት ሰብስቦ ለዘመኑ ተስማሚ የሆነ ሕግ እንዲሠሩለትና
እንዲሰጡት እንደጠየቃቸው ሁሉ አጼ ዘርዓ ያዕቆብም ያገሩን ሊቃውንት ሰብ
ስበው በዘመነ ወንጌል እየኖርኩ በሕገ ኦሪት እፈርዳለሁ፤ስለዚህ ብሔራዊ ሕግ

www.ethiopianorthodox.org

ሊሆን የሚገባውን ሕግ ወስናችሁ ስጡኝ አሏቸው ፤ እነርሱም የንጉሡን ቀና አስተያየት የሃይማኖቱን ፍጹምነት የሐሳቡን ቅዱስነት ተመልክተው ወዲያውኑ ተሰብስበው አሁን ፈውስ መንፈሳዊ እየተባለ የሚጠራውን ሕግ ወስነው አቀረቡለት ይባላል ። ይኸም ሕግ ፍጹም መንፈሳዊ አመራርን ብቻ በተለይም ድርቅናን ያዘለ ሕግ እንጅ አህጉራዊ ፍትሕን የማይመለከት በመሆኑ ምኞቱ ያልተፈጸመለት መሆኑን በየጊዜው ይገልጥ እንደነበር ከኢትዮጵያውያን አልፎ ለግብፃዊው ጴጥሮስ አብደል ሰይድ እንደገለጠለት እንረዳለን ። እርሱም ይህ ፍትሐ ነገሥት የተባለው መጽሐፍ በዓረብኛ እንደሚገኝና ቢተረጐም ጠቃሚ መሆኑን ምኞቱም እንደሚፈጸምለት ገልጠ ነገረው ፤ እንግዲያውስ ከማንኛውም ሰው ይልቅ አንተው ፪ቱንም ዓይነት ቋንቋዎች ታውቃለህና ፈጽምልኝ ብሎ ስለጠየቀው ከዓረብ ወደ ግዕዝ ፍትሐ ነገሥትን ተርጕሞ እንደሰጠው በመቅድሙ ሊቃውንቶቻችን ያብራራሉ ። እንግዲህ አጼ ዘርዓ ያዕቆብ በመጀመሪያ ሊቃውንቱን እንደ ፫፻፲፰ ሊቃውንት ብሔራዊ ሕግ እንዲሠሩለት ስለጠየቀ ፤ ቀጥሎም የ፫፻፲፰ ሊቃውንት ውሳኔ በሀገሩ ቋንቋ ተተርጕሞ እንዲሠራበትና መንፈሳዊ አስተዳደር እንዲኖረው በመጣሩ የሕግ ሰው መሆኑን በግልጥ ለማስታወቅ ዘርዓ ያዕቆብን ቆስጠንጢኖስ ብለው ሰይመውታል ፤ ስለዚህም ዘተሰምየ ቆስጠንጢኖስ ተብሏል ።

በፍትሐ ነገሥቱ ላይ ከአበው ውሳኔ ጋር ግብፃውያን በተለይ ያስቀመጡት ዕዝል ቅጥል « ወሰብአ ኢትዮጵያሰ ኢይሢሙ መምህራኒሆሙ » የሚል ይገኛል ፤ ይኸም ከግል ፍላጐታቸው የተነሣ የደቀሉት ነው ። እርሱም ሥርዋጽ በሚለው ትእምርተ ጥቅስ እንጅ በተለመደው አጠቃቀስ በአንቀጽ ውስጥ የገባ አይደለም ። በዚህም መልክ ሥርዋፅ እያለ በየአንቀጹ መካከል የሚገባ ብዙ አለ ፤ እርሱንም በጥብቅ ሲመረምሩት አብርሃም ቀሲስ በራሱ ፈቃድ ያስገባው ይመስላል ፤ ትርጕሙም ሥርዋጽ ማለት « የጠመመ ማቅኛ የጐደለ መሙሊያ » ነው ይላሉ ፤ ስለዚህም ያልተቃና ሐሳብ ባለበት ሁሉ የራሱን ፍላጐት ለማሟላት ሲል በየቦታው አስገብቶበታል ለማለት ይቻላል ። ይኸም ዕንቅፋት የሆነ አንቀጽና ሌላም ይኸን የመሰለ አስቸጋሪ አንቀጽ እያለ በኢትዮጵያ ፍትሐ ነገሥት ቅዱስ ሕግ ፤ እየተባለ ሲከበር ይኖራል ። በቤተ ክርስቲያናችን አሁንም ቢሆን ሌላ ሕግ የለም ገናም አልወጣም ሆነም ቀረ የሚጠቀሰው ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ፤ ይኸም ማለት ክፉውንም ደጉንም እንዳዘለ ይዞ ይገኛል ማለት ነው ። በመንግሥት በኩል ግን ፍትሐ ነገሥቱ የምንጭነት ሥልጣን ሳይነፈገው በሕግ በኩል ራሱን የቻለ ሌላ ሕግ ሠርቶ እርሱን በመድበልነቱ ብቻ ይጠቀምበታል ። ፍትሐ ነገሥት በታሪክ በኩል ይኸን የመሰለ ዋጋ ሲኖረው ከላይ እንደገለጥኩት በቤተ ክርስቲያን አሁንም ገና የሕግነት ቦታውን እንደያዘ ይገኛል ፤ ይሁን እንጂ በታሪክነቱም በሕግነቱም ቢሆን ብዙ ፈላጊ አለው ፤ ስለዚህም በአንድምታ ትርጓሜ ፤ በነጠላ ትርጓሜ በእንግሊዝኛ ታትሞ ይገኛል ። ወደፊት ግን ጊዜ ቢገኝ ግዕዙን አስተካክሎ

www.ethiopianorthodox.org

መተርጐም ሳያስፈልግ አይቀርም ። ፍትሐ ነገሥቱ በሕግነት መልክ ባይሠራበትም ቅሉ ሁሉም ፍትሐ ነገሥት እንዲህ ይላል የሚለውን ጥቅስ ለመስማት ይጓጓል ፤ ስለዚህ መጽሐፉን ለማንበብ ታሪኩን ለመስማት ምሥጢሩን ለመረዳት የሚፈልገው ብዙ ነው ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩/ በኢትዮጵያ የሕግ መጻሕፍት ብዙ መሆናቸውን ለመግለጥ ያህል ስማቸውን ሁኔታቸውን በመግለጥ ጻፍን እንጂ ።—
 ሀ/ አደባባይ ወጥቶ የሚታወቀው ፤
 ለ/ በጉባኤ የሚኬደው (የሚተረጐም) ፍትሐ ነገሥቱ ብቻ ነው ።

፪/ ሌሎች የሕግ መጻሕፍት የሕግ መጻሕፍትነታቸው በፍትሐ ነገሥቱ ስለተገለጠ የኛ ቤተ ክርስቲያን ቀርታ ሌሎች አብያተ ክርስቲያናት በሕግ መጽሐፍ ሊስት ላይ ያስቀምጧቸዋል ፤ በኛ ግን የዓይን አንድም የንባብ መጽሐፍ ዋጋ የሚሰጣቸው ይመስላል ።

፫/ ሁሉም ታትመው አንድም ተባዝተው በየእጁ ለሁሉ ስላልተዳረሱ የብዙዎች መጻሕፍት ስማቸው እንጂ ዝርዝር ነገራቸው ሙሉ አንቀጻቸው አይደለም ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፲፩ ።

# የቍጥር ትምህርት ።

### ምዕራፍ ፩ ።

## የዘመን አቈጣጠር ስልት ።

ኢትዮጵያ ራሳቸውን የቻሉ ብዙ ዓይነቶች ባህሎች እንዳሏት መላልሰን ተናግረናል ፤ ከባህሎቿም ውስጥ ፩ኛውና በጣም ሁሉን የሚያስደንቀው ራሱን የቻለ የዘመን አቈጣጠር ስልት ፣ ልዩም ስፍረ ሰዓት መኖሩ ነው ። ማንኛውም ሕዝብ እምነ ት ያለው ሆኖ ከተገኘ እንደ ሕጉ ለማምለክ የተለየ የዘመን አቈጣጠር ስልት እንዳለው የታወቀ ነው ። የኢትዮጵያ ግን ከዚያ ሁሉ የተለየ አኳኋን አለው ፤ ማለት በእምነት አንድ ከሆኑት ፣ አንድም ጥንት የዚህ ዓይነት አቈጣጠር ነበራቸው ከተባሉት አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ ሳይቀር ተለይታ አቅዱ ሳይ ጠፋ ፣ ስልቱ ሳይለወጥ ሊቃውንቱም ታላቅ ዕውቀት አድርገው ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲያስተላልፉና ፣ ሲሠሩበት መገኘቱ ነው ። ይኸም ሁናቴ ሊቃውንቱን ከፍተኛ ግምት የሚያሰጣቸው ሆኖ ተገኝቷል ።

## ፩ኛ የመጻሕፍቱ ቍጥር ።

ስለ ዘመን አቈጣጠር ልዩ ልዩ መጻሕፍት በልዩ ልዩም ዘመናት ተጽፈ ዋል ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

ሀ/ አቡሻህር ፣ ይኸ መጽሐፍ በደራሲው ስም የሚጠራ ነው ፣ መጽሐፉም ትርጉም ሳይሆን አልቀረም ፤ ምክንያቱም ስሙ እንደሚያመለክተው ከግብፅ ወይም ከምሥራቅ ዓለም የተወረሰ ይመስላል ። መጽሐፉም በመጠኑ ከፍ ያለ ስለ ዘመናትም አቈጣጠር ራሱን የቻለ መንገድ ያለው ነው ።

ለ/ መርሐ ዕውር ፣ ይኸ ድርሰት ግን ኢትዮጵያውያን ሊቃውንት በአስተ ዋጽኦ የቀመሩት ይመስላል ፤ ስሙ እንደሚያመለክተው ከዚያም ከዚህም አውጥ ተው ሊቃውንት ቀመሩት ፤ ዕውሩ አንድም ደንቆሮው ማለት ያልተማረው ሳይ ቀር የሚሠራበት የቍጥሩን ስልት የሚያመለክት ስለሆነ ፣ መርሐ ዕውር ተብሏል ።

ሐ/ ባሕረ ሐሳብ ፣ ይኸም ድርሰት ኢትዮጵያዊ ቅምር ይመስላል ፤ ቃሉም ሥራውም ያመለክታል ። የቃሉ ፍቺ የአሳብ ባሕር በማለት ሲነገር ብዙ መመራ መር ፣ ብዙም መራቀቅ እንዳለበት የሚያጠይቅ ነው ፤ በእርግጥም በመደመር በመቀነስ ፣ እንዲሁም በማብዛት ፣ በማካፈል ብቻ መድከም ሳይሆን ፣ ብተቱን ስፍረ ሰዓቱን ፣ አዕዋዳቱን ፣ ቀመሩን ፣ ሕፀፁን ይኸንም የመሳሰሉትን አንቀጾች ቦታ ሰጥቶ ሞያውን ለይቶ ማስቀመጥ በባሕረ አሳብ መዋኘት ነውና ። ሥራውም

www.ethiopianorthodox.org

ባሕረ ሐሳብ የሚባለው ከሌሎች መጻሕፍት ተውጣጥቶ በየዓመቱ በአጭር የሚታወጅበት አጽዋማት ፥ በዓላት የሚታወቁበት ሁሉ የሚያውቀው ትምህርት ነው ፤ ይኸንም ደረሰው የሚባለው ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው ። መጻሕፍቱ ይኸን የመሰሉ ሲሆኑ ሌሎችም በደራሲዎች የሚጠሩ አሉ ፤ እነርሱም ሰይድ ወልደ መጥሪቅ ፥ መሐሎብ ፥ በብነጋዊ ፥ ሰይዳውያን አይሁድ ፥ ድሜጥሮስ ፥ ዮሐንስ አፈወርቅ ቄርሎስ ፥ ኤጲፋንዮስ ፥ ዮሐንስ ዘደማስቆ ፥ ማርቆስ ወልደ ቀንበር ፥ ጊዮርጊስ ወልደ አሚድ ፥ አቡሻህር ወልደ አቢል ሀረብ የተባሉና ሌሎችም ናቸው ።

## ፪ኛ የትርጕም ስልት ።

እነዚህንም መጻሕፍት እንደሌሎች መጻሕፍት ሁሉ የጉባኤ መጻሕፍት አድርገው ሊቃውንት ይተረጕሟቸው ፥ ያስተምሯቸውም ነበር ። ቍጥራቸውን ግን አንዳንድ ሊቃውንት ራሳቸውን አስችለው ፩ኛ የቍጥር ትምህርት ብለው ሲሰይሙ ፥ አንዳንድ ሊቃውንት ደግሞ ከሊቃውንት መጻሕፍት ጋር አግብተው ይቈጥሩታል ፤ የሆነ ሆኖ ትምህርቱ ጠቃሚ መሆኑ ታውቆ ራሱን የቻለ ጉባኤ ተሰጥቶት ሲፈተት ፥ ሲተረጐም እንደኖረ የታወቀ ነው ። ወደአሁኑ ጊዜ ግን መጻሕፍቱ መተርጐማቸው ቀርቶ ወይም ራሱን የቻለ ጉባኤ መሆኑ ቀርቶ እገሌ አቡሻህር ዐዋቂ ነው ፤ ወይም የቍጥርን መጻሕፍት ያውቃል ብቻ ይባል ነበር ። በአሁኑ ዘመን ግን እንዲያውም ፈጽሞ ጠፍቷል ፤ የሆነው ሆኖ ስለዚህ ትምህርት በረጅሙም በአጭሩም ብዙ መጻሕፍት ተጽፈዋል ፤ ሐተታም ተሰጥቷል ፤ ይኸም ሁሉ ታትሞ ይገኛል ። ስለዚህም ማንኛውም ካህን በቀላሉ ሊያውቀውና አንዱን ከአንዱ አጋጭቶና አፋጭቶ ዘመናትን ፥ አጽዋማትን ፥ በዓላትን ፥ ስፍረ ሰዓትን ሊያገኝ ችሏል ።

ስለዚህም በየዓመቱ በዘመን መለወጫ ጊዜ በየቤተ ክርስቲያኑ ይነገራል ይታወጃል ፤ ሕዝቡም ይኸንን ለመስማት ወደቤተ ክርስቲያን በብዛት ይጐርፋል ፤ ዛሬ ግን በየከተማው ስለዓመቱ የባሕረ ሐሳብ መንገድ እየታተመ ስለሚወጣ ብዙ መኳንቱና ለመስማት ወደቤተ ክርስቲያን መጕረፉን ቀንሶታል ።

## ፫ኛ የቍጥር ትምህርት ደረጃ ።

የቍጥር ትምህርት በጥንት ዘመን እንደ አስትሮኖሚ ስለሚቈጠር ትልቅም ዕውቀት እንዳለው ስለሚገመት ለትምህርቱ ከፍተኛ ደረጃ ይሰጠው ነበር ፤ ሊቃውንቱም እንደ አስትሮኖሚስት በጣም ይከበሩ ነበር ። በእርግጥም እንደ አስትሮኖሚስቶች እየሆኑ ምሕዋረ ፀሐይን ፥ ክፍለ ዘመናትን ፥ የልዩ ልዩ ፕላኔቶችን አቀማመጥ ለይቶ ያለ ቴሌስኮፕ በልማድ ብቻ ዐውቀው ኤክሊፕስ የሚሆንበትን ጊዜ ለይተው ይናገሩ ፤ እንደ ሜትሮሊጂስቶችም የድርቁን ፥ የዝናቡን ጊዜ ለይተው ያውቁ ነበር ፤ ይኸንም ለመመርመር ልዩ አቅድ ነበራቸው ። አሁን ግን የነ

www.ethiopianorthodox.org

ርሱን ጥናት ሲመለከቱት የትምህርታቸውም ዘዴ በጣም ከባድ እንደነበር ይታመናል ። የጽሕፈቱንም አቀማመጥ ሲመለከቱት ሌላ ግምት የሚሰጠው ማለት እንደጠልሰም ያለ ነገር እንጂ ቁም ነገር መስሎ አይታይም ። ብዙ ጥበባቸው ጥላ ጥሎበት ሲታይና ሳይታወቅ ይኖራል ። የማንኛውም ነገር መፍቻው ቁልፍ ይኸው የቍጥር ትምህርት ነበር ፤ ማለት ሱባኤው የሚገደፍ ፥ ምሕዋረ ፀሐይ ፥ መሳክወ ፀሐይ ፥ ምዕዛረ ፀሐይ የሚለካው የሚታወቀው በዚሁ ትምህርት ነበር ። የዓመት ዓለምና የዓመት ምሕረት መሥፈሪያና መለኪያ ፤ የዘመኑ ቍጥር የሚታወቀው በዚሁ በቍጥር ትምህርት ነው ፤ ስለዚህ ትምህርቱም ከፍተኛ ፥ ሊቃውንቱም ከፍ ያሉ እንደነበሩ ይገመታል ። ሊቃውንቱም በመራቀቅ አንዱ ከአንዱ የተለየ መንገድ ነበራቸው ፤ አሁንም ቅሉ የተለያየ አስተያየትን የያዙ መጻሕፍት ለመገኘት የቻሉት በዚሁ ምክንያት ነው ። የፊደሎቻችን ሞያና ቍጥር የሚታወቀው ፥ በዚሁ በቍጥር ትምህርት ስልት ነው ፤ የቀረው ቀርቶ ነገረ ደብተራው ፥ ሐሳበ ደብተራው የሚሠራበት ኮከብ የሚቈጠርበት ፥ ዓውደ ነገሥት የሚገለጥበት ሁሉ በዚሁ ስልት ነበር ።

ቄስ አፄ ገብረ መድኅን የተባሉ ሊቅ እንደአስትሮኖሚስት የሚገመቱ ነበሩ ። ምክንያቱም በዚሁ በቍጥር ትምህርት የበሰለ ዕውቀት ስለነበራቸው ነው ፤ ግን በዚሁ አንጻር ደግሞ ዓውደ ነገሥት ዐዋቂ ነበሩ የጥንቈልናም ሥራ ይሠሩ ነበር ፤ ስለዚህም ከፍተኛ ግምት ተጥሎባቸው ነበር ። ትምህርቱን ሊያዋርደው የቻለው ግን ፥ የቍጥር ስልት ለሌላ ተግባር ማለት ለጥንቆላ በመዋሉ ነገረ ደብተራንም በመከተሉ ነው ።

ምዕራፍ ፪ ።

## ባሕረ ሐሳብ ።

ባሕረ ሐሳብ የተባለው የቍጥር ትምህርት ከፍ ያለ የምርምር ዘዴ ፥ የሃሳብ ጥልቀት ስላለው የማይዋኝ በመሆኑ ባሕር ይባላል ፤ እርሱንም ቀደም ስንል ገልጠነዋል ። እንዲሁም ሰውየውን መርቶ ከአሰበው ግብ የሚያደርስ በትክክል እንዲመረምር መንገዱን ጥርጊያ አድርጎ የሚያሳይ መንገድ በመሆኑ መርሐ ዕውር ተብሎ ይጠራል ፤ ይኸንም እንዲሁ በሰፊው ገልጠናል ፤ በዚህም መሠረት ትምህርቱ መርሐ ዕውር ተብሎ ይጠራል ። በዚህም መሠረት ሊቃውንቱ መርሐ ዕውር ሲባል የተለየ መጽሐፍ ያለው ልዩ ጉባኤ የሚደረግለት እንደሆነ አድርገው ሲገምቱ ፥ ባሕረ ሐሳብን ግን ቀላል ትምህርት ሁሉም የሚያውቀው አድርገው የሚገምቱ አሉ ፤ በአንድ በኩል እውነት ነው ማለት በየዓመቱ የሚታወጀው በቀላሉ የዓመቱን ፥ የዕለቱን ፥ የአጽዋማቱን ፥ የበዓላቱን ቀመር የሚያወጡበት መንገድ ባሕረ ሐሳብ ይባላል ፤ ነገር ግን እያንዳንዱ ዝርዝር ነገር የሚያስረዱ የቃላት መፍቻ ፥ የብተቱ ማግኛ ፥ የአቈጣጠሩን ስልት የሚናገረው መርሐ

www.ethiopianorthodox.org

ዕውር ይባላል ። የሆነው ሆኖ ይኸ ትምህርት የአውራኅን ብተት ፣ የቀናትን መቁጠሪያ ፣ የበዓላትን ማክበሪያ ፣ የአጽዋማትን መቀበያና መግደፊያ ለይቶ የሚናገር የዕውቀት ዘዴ ነው ። በውስጡ የሚይዘውን በመጠኑ ስንዘረዝር ቀመሮች እንዴት እንደሚገኙ ፣ ዓመታት እንዴት እንደሚመላለሱ የሰንበታት ክፍልና ሱባዔ ሰንበታት እንዴት እንደሚቈጠሩ ፣ ኢዮቤልዩ ማለት ምን ማለት እንደሆነና እንዴት እንደሚቈጠር አቅዱን ፣ እንዲክትዮንና ጳጉሜን እንዴት እንደሚዘዋወሩ ሐሳበ ሰማይና ሐሳበ ምድር እንዴት እንደሚገኙ ፣ ሐሳበ ፀሐይና ሐሳበ ወርኅ ፣ አበቅቴ ፀሐይና አበቅቴ ወርኅ ፣ ዕለተ መጥቅዕ እንዴት እንደሚገኝ መነሻቸውንና መድረሻቸውን የሚያስረዳ ትምህርት ነው ።

## ፩ኛ የቃላት ትርጒም ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሞያዎች በምንመረምርበት ጊዜ ፣ የቃላቶቹ ፍቺ ፣ የአቀማመጣቸውም ስልት እንዳያስቸግሩን አስቀድመን የቃላቱን ትርጒም እናስቀምጣለን ።

| | |
|---|---|
| ሀ/ ቀመር | አቈጣጠር |
| ለ/ ሐሳብ | » |
| ሐ/ ዓውድ ፡ አዕዋድ | መሣፍርት |
| መ/ አበቅቴ | የሌሊት ሐሳብ ማውጫ |
| ሠ/ መጥቅዕ | ደወል |
| ረ/ ተውሳክ | የጾም ማውጫ |
| ሰ/ ሕፀፅ | ጉድለት |
| ሸ/ እንዲክቲዮን | የጳጉሜ ፩ኛው ቀን |
| ቀ/ ጥንተዮን | የፀሐይ መገኛ |
| በ/ ሱባዔ | ሰባት (ሰባተኛ) |
| ተ/ ኬክሮስ | ስፍረ ሰዓት |
| ቸ/ ክንተሮስ | ንዑስ ስፍረ ሰዓት |

እነዚህ ቃላት ይበልጠቹ ግዕዝ ፣ አንድም ጥንታዊ አማርኛ እንደሆኑ ይገመታሉ ፤ ስለዚህ ግዕዝ ለሚያውቁ ቀላል ሁነው ሲታወቁ ፣ ለአንድ አንድ ሰው ግን እንደ ዕንቈቅልሽ ሆኖባቸው ባዕድ ነገር አድርገው ይመለከቱታል ። ስለዚህ በመጠኑ መተርጐም በግድ አስፈለገ ። አንድ አንድ ቃላት ግን የውጪ ቃላት እንደሆኑ የሚገመቱ አሉ ፤ ለምሳሌ ዮን እንዲክቲዮን ፣ ኬክሮስ ፣ ክንትሮስ ፣ ሌሎችም እነዚህን የመሰሉ ናቸው ። ብዙዎች ቃላት የኛው ሁነው በትክክል ሊቃውንቶቻችን ሲፈትቱት ሲታዩ ፣ ኢትዮጵያዊው ሥልጣኔ ቀደም ብሎ የገባ እንጂ ምንም የውጪ እጅ የገባበት ጥበብ አይመስልም ፤ ከዚህም ጋር በዚህ ዓይነት ስልት የሚቈጥር ሀገር አሁን የለም ። የውጪውን ቃላት ስንመለከት ደግሞ ጥበቡ

www.ethiopianorthodox.org

የውጪ ሁኖ ወደኛ የተተረጐመ ትምህርት እንደሆነ ያጠይቃል ፤ የሆነው ሁኖ በሀገራችን እንኳን ከገባ ብዙ ዘመናት አልፈውበታል ። ስለዚህ ኢትዮጵያዊ ዕው ቀት ሆነ ለማለት የዘመኑ ረጅምነት ሊያስደፍረን ይችላል ።

ከእንግዲህ ወዲህ እነዚህ ቃላት እየተመላለሱ የሚገጥሙን ስለሆነ ፥ እያ ንዳንዳቸውን የቃሎች ፍቺ ጠንቅቆ ማወቅ ይገባል ።

## ፪ኛ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ።

ባሕረ ሐሳብ ፥ አንድም መርሐ ዕውር የተባለው የዘመን አወጣጥ ስልት ቀደም ብሎ በኦሪት የነበረ ፥ በኋላም በሐዲስ ዘመን ፥ ከዚያም ያለማቋረጥ እስከ አሁን ድረስ ይኑር እንጂ ፥ ሊቃውንት እንደሚያትቱት ባሕረ ሐሳብን የደረሰ ቅዱስ ድሜጥሮስ ነው ይላሉ ። እርሱም በማርቆስ ወንበር ላይ የተቀመጠ በ፲፪ኛው መቶ ዘመን የነበረ ሊቀ ጳጳስ እንደሆነ ይናገራሉ ፤ እርሱም ያገባ ፥ ግን ድንግል የሆነ ሰው እንደነበር የሕይወት ታሪኩን አስፋፍተው ይነግሩለታል ። ስለ ሰው የው ታሪክ በሊቃነ ጳጳሳት ስም ተራ ይገኝ እንጂ ፥ ያገባ ወይም ድንግል እንደ ሆነ ፥ እንዲሁም ባሕረ ሐሳብን የደረሰ እንደሆነ አይነገርለትም ። እንዲያውም እኛ የያዝነው የዘመን አቈጣጠር እስክንድርያዊ እንደሆነ ሲነገርለት ፥ ድርሰቱ ጥንታዊ ፥ አንድም ኦሪታዊ እንደሆነ ይነገራል ፤ ለምሳሌ ዘመን በመስከረም መለ ወጫችን ጥንታዊ ሕግ ዓለም የተስማማበት ነበር ። ምንም እንኳን ምሥራቁ ዓለም ፤ ምዕራቡም ሳይቀር እንዲክቲዮን ብለው መስከረም ፭ ቀን የባጀት ዓመት አን ድም መለዋወጫ ዓመት አድርገው ያከብሩት ነበር ። እንዲሁም ጳጉሜንን ከወ ራቱ ትርፍ የሆኑትን ዕለታት ሰብስቦ አምጥቶ በዓመቱ መጨረሻ ላይ እንዲቈ ጠሩ የሆነው በዚሁ መሠረት ነው ። በእስክንድርያ ላይ በጥሌሞሶች በነበሩበት ጊዜ የነበረ የዘመን አቈጣጠር ስልት ይኸን በመሰለ መልክ ነበር ፤ ራሱ ቃሉ ጳጉሜን የሚለው ጽርዐዊ እንደሆነ ኤፓጉሜን ማለት እንደሆነ የታወቀ ነው ።

የሆነው ሆኖ ይኸ ቅዱስ ድሜጥሮስ የቀመረው ነው ብለን በየዓመቱ መጀመሪያ ላይ የምንናገረው ሐሳበ ድሜጥሮስ እንደሆነ የታወቀ ነው ።

## ምዕራፍ ፫ ።

## ሐሳበ ኦሪት ።

ስለ ዘመን አቈጣጠር በኦሪት ዘመን የተጀመረው ውጤት ሰጥቶ ነገሩ ተከብሮ ሲሠራበት እንደቆየ የታወቀ ነው ። ዋናው ዓላማ ግን ሀ/ በዓላትን አጽዋማ ትን በቀላሉ ለማውጣት ፥ ለ/ የክርስቶስን መምጣት የሥጋዌን እርግጠኛነቱን ለማወቅ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ ኦሪታውያን አጽዋማትና በዓላት ።

በኦሪቱ ጊዜ አንዳንድ ታላላቅ ሥራ የተሠሩባቸውን አጋጣሚዎች እየጠበቁ በዓላቱን ሁሉ ያከብሩ ፣ አጽዋማቱን ይጾሙ ነበሩ ፤ እነርሱም የሚከተሉት ናቸው ።

፩ኛ/ በዓለ መጥቅዕ የተባለው በዓል ነበር ፤ ይኸውም የዘመን መለወጫ ሲሆን ፣ ከጳጉሜ እስከ መስከረም አጋማሽ የሚውል የነበረው በዓል ነው ።

፪ኛ/ ጾመ አይሁድ

፫ኛ/ መጸለት የተባለ በዓል ነበር ይኸውም የቂጣ በዓል ማለት ነው ።

፬ኛ/ ፍሥሕ ይኸውም ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበት ዕለት ነው ።

፭ኛ/ ልበ ምድር የኤርትራን ባሕር የተሻገሩበት

፮ኛ/ በዓለ ሠዊት አዝመራው እሸት የሚሰጥበት

፯ኛ/ ጾመ አስቴር ራሷ የጾመችው ነው ።

፰ኛ/ ጾመ ዮዲት ራሷ የጾመችው ነው ።

እነዚህ ስምንቱ በጥንቱ ጊዜ ይኑሩ እንጂ ፣ አሁንም ሳይቀር የተከበሩ ናቸው ። እነዚህም እንዴት እንደተጀመሩ ለማወቅ ስንፈልግ ፤ መጥቅዕ የተባለው በኖኅ ጊዜ ተጀመረ ይባላል ፤ ምክንያቱም ኖኅ እንስሳት ፣ አራዊት ወደ መርከብ እንዲገቡለት መጥቅዕ ጠቃ ፤ ማለት ደወል ደወለ ፤ በዚያን ጊዜ ተሰበሰቡለት ፤ ስለዚህ የሰው ልጅ እንስሳት ፣ አራዊት የዳነበት ጊዜ የዘመን መቍጠሪያ መጀመሪያ ነው ብለው ያከብሩ ነበር ። ይኸን ተአምር የተደረገበትን የመጥቅዕ ዕለት ክብር ሰጥተው ሲያከብሩት ይኖራሉ « ክብሩሰ ለዕለተ መጥቅዕ ቀዳሚ በኖኅ » ይላልና ።

በዓለ መጸለት የቂጣ በዓል ማለት ነው ፤ ይኸም ማለት ያልቦካ ቂጣ የሚበሉበት ጊዜ ነው ፤ ፍሥሕ ከግብፅ ባርነት ነፃ የወጡበት መታሰቢያ ዕለት ነው ፤ ፍሥሕም ማለት ፋሲካም ማለት ነው።ሌሎቹ ግን በአብርሃም ጊዜ ተጀመሩ ይባላል፤ናእት በሚበሉበት ጊዜ የሚረጨው ደም (ንዝኀተ ደም) በግዓ ፍሥሕም በሙሴ ተጀመረ ይባላል ። አጽዋማትም ጾመ ነነዌ ፣ በነነዌ ጾመ አስቴር በአስቴር (በሐማ ጊዜ) ተጀመረ፤ ጾመ ዮዲት በዮዲት ጊዜ ተጀመረ። የሆሎሆርኒስን አንገት ባስቈረጠችው ጊዜ፤እነዚህንና እነዚህን የመሳሰሉት ሁሉ በኦሪት ተጀምረው ኦሪታዊ መልክ ይዘው ሲኖሩ፣ ወደ ኢትዮጵያ በጥንት ዘመን የገቡና አንዳንዶቹም እስከ አሁን ሳይለወጡ እንዳሉ፣አንዳንዶቹም በእግራቸው ሌላ እየተተካባቸው መልካቸውን ለውጠው የሚገኙ ናቸው። በዚህም ሆነ በዚያ የዘመን አቈጣጠራችን ስልት ጥንታዊ የሆነ ከኦሪት ጋር የተያያዘ ነው።

### ምዕራፍ ፬ ።

## ሐሳበ ነቢያት ።

ነቢያት ሁሉ ከአዳም ጀምሮ በየጊዜው እየተነሡ ትንቢት ሲናገሩ፣ ሱባዔ ሲቈጥሩ ፣ የክርስቶስን ሰው መሆን ፣ እንዲሁም ፪ኛ መምጣቱን ደጅ ሲጠኑ ኑረ

www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ/ መጥቅዕን ለማግኘት ለመጥቅዕ ፲፱ ፲፱ ዕለት ይሰጧል ፤ ፲ ፲ሩ መቶ ፴፥ ፱ ፱ኙ መቶ ፲፯ ይሆናል ፤ ፪፻፵፯ ይሆናል ። በ፰ ፴ ሲገደፍ ፯ ይተርፋል ፤ ይኸ መጥቅዕ ይሆናል ።

አበቅቴና መጥቅዕ አንድ ሁነው ቢቈጠሩ ፴ ይሆናሉ ፤ ከ፴ አይወጡም ፤ ከ፴ አይወርዱም ፤ ወትረ ይከውኑ ፴ ኢየዓርጉ እም፴ ወኢይወርዱ እም፴ እንዲል ።

ትርጓሜያቸውም አበቅቴ ማለት ተረፈ ዘመን ነው ፤ አበቅቴ ብሂል ተረፈ ዓመት » እንዲል ። መጥቅዕ ማለት በቁሙ መጥቅዕ ነጋሪት ማለት ነው ። እን ዲህ ከሆነ ስለምን ዕለቱ መጥቅዕ ተባለ ቢሉ ፥ መጥቅዕና ነጋሪት በተመታ ጊዜ ሰው ሁሉ እንዲሰበሰብ ፥ ይኸም አጽዋማትን ፥ በዓላትን ይሰበስባልና ፤ ስለዚህ ዕለቱ መጥቅዕ ተባለ ። «ወብሂለ መጥቅዕሂ አስተጋባኢ ብሂል ፤ እስመ ከመ መጥ ቅዕ ዘዕብን ወዘዕፅ ዘብርት ወዘሐፂን ያስተጋብዕ ኵሎ ሰብአ ውእቱኒ ከማሁ ያስተጋብዕ ኵሎ አጽዋማተ ወበዓላተ » እንዲል ። አበቅቴ ከሕፀፀ ከሠርቀ ዕለት ጋር የሌሊት ማውጫ ነው ። መጥቅዕ ከዕለታት ተውሳክ ጋራ የአጽዋማት ፥ የበዓ ላት ማውጫ ነው ።

## ፫ኛ የዕለታት ተውሳክ ማውጫ ።

የዕለታት ተውሳክ በቅዳሜ ይጀመራል ።

| | | |
|---|---|---|
| የቅዳሜ ተውሳክ | | ፰ ነው |
| የእሑድ | » | ፯ » |
| የሰኞ | » | ፮ » |
| የማክሰኞ | » | ፭ » |
| የረቡዕ | » | ፬ » |
| የኀሙስ | » | ፫ » |
| የዓርብ | » | ፪ » |

የአጽዋማትና የበዓላት ተውሳክ ደግሞ ከዚህ የሚቀጥለው ነው ። ለነነዌ ተውሳክ የለውም ፤ ምክንያቱም መሠረቱ መጥቅዕ ስለሆነ ነው ።

| | | |
|---|---|---|
| የበዓተ ጾም ተውሳክ | | ፲፬ ነው |
| የደብረ ዘይት | » | ፲፩ » |
| የሆሣዕና | » | ፪ » |
| የስቅለት | » | ፯ » |
| የትንሣኤ | » | ፱ » |
| የረክበ ካህናት | » | ፫ » |
| የዕርገት | » | ፲፰ » |
| የጰራቅሊጦስ | » | ፳፰ » |

www.ethiopianorthodox.org

፫/ መጸለት
፬/ ፍሥሐ
፭/ ልበ ምድር
፮/ በዓለ ሠዊት
፯/ ጾመ አስቴር
፰/ ጾመ ዮዲት ናቸው ።

ለመጥቅዕ ተውሳክ የለውም ።

| | | |
|---|---|---|
| የጾመ አይሁድ ተውሳክ | | ፱ ነው |
| የመጸለት | » | ፲፬ ነው |
| የፍሥሐ | » | ፲ ነው |
| የልበ ምድር | » | ፫ » |
| የበዓለ ሠዊት | » | ፴ » |
| የጾመ አስቴር | » | ፳፩ » |
| የጾመ ዮዲት | » | ፳፰ » |

ከፍሥሐ ግን ቢጀምሩት የልበ ምድር ተውሳክ ፳፫ ነው ።

| | | |
|---|---|---|
| የበዓለ ሠዊት ተውሳክ | | ፳ ነው |
| የጾመ አስቴር | » | ፲፩ » |
| የጾመ ዮዲት | » | ፲፰ » |
| ሌሊታቸውም የመጥቅዕ | | ፩ » |
| የጾመ አይሁድ ሌሊት | | ፲ » |
| የመጸለት ሌሊት | | ፲፭ » |
| የፍሥሐ ሌሊት | | ፲፬ » |

የልበ ምድር ሌሊት በሚያዝያ የሆነ እንደሆነ ፯ ነው ፤ በግንቦት የሆነ እንደሆነ ፰ ነው ።

| | |
|---|---|
| የበዓለ ሠዊት ሌሊት | ፭ » |
| የጾመ አስቴር ሌሊት | ፳፯ » |
| የጾመ ዮዲት በነሐሴ የሆነ እንደሆነ | ፬ » |
| በመስከረም የሆነ እንደሆነ | ፳፱ » |

ከዚህም መጥቅዕ ጾመ አይሁድ ፣ መጸለት ተለይተው በጥቅምትና በመስከረም ይውላሉ ። ፍሥሐ በሚያዝያና በመጋቢት ይውላል ። ልበ ምድር በግንቦትና በሚያዝያ ይውላል ። በዓለ ሠዊት በሰኔና በግንቦት ይውላል ። ጾመ አስቴርና ጾመ ዮዲት በጳጉሜንና በነሐሴ ይውላል ። በ፳፫ ፤ በ፲ ፣ በ፲፪ ፣ በ፲፫ መጥቅዕ ጊዜ ጾመ ዮዲት ተለይቶ በመስከረም ይውላል ፤ ግን ከ፲፩ አይወጣም ።

www.ethiopianorthodox.org

የአይሁድን ጾማቸውን አንጾመውም ፥ በዓላቸውንም አናከብረውም ፤ ነገር ግን ኦሪት ለወንጌል አምሳል መርገፍ እንደሆነች ሁሉ ፥ በዘመነ ብሉይ የተሠሩ አጽዋማት ፥ በዓላትም በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩ አጽዋማትና በዓላት አምሳል መርገፍ ስለሆኑ እንቈጥራቸዋለን ፤ እርሱም እንደሚከተለው ነው ።

በመጥቅዕ ዕለት ዮሐንስ ገብቶበታል ።
በጾመ አይሁድ ጾመ ንስሐ ገብቶበታል ።
በመጸለት ጥምቀት ገብቶበታል ።
በፍሥሕ ፋሲካ ገብቶበታል ።
በልበ ምድር ማዕዶት ገብቶበታል ።
በበዓለ ሠዊት ጰራቅሊጦስ ገብቶበታል ።
በጾመ አስቴርና በጾመ ዮዲት ዓርብና ረቡዕ ገብተውባቸዋል ።

## ፳ኛ የቀመር አወጣጥ ።

የቀመር ሁሉ መጀመሪያ አልቦ ነው ፤ ፍጻሜው ግን በ፲፰ አበቅቴ ነው ። ለአበቅቴ ፲፩ መንሣታችን ስለምን ነው ? ያልን እንደሆነ ዓውደ ዓመት ፫፻፷፭ ዕለት ነው ፤ ከዚህ ጨረቃ ፫፻፶፬ ዕለት ስታነሣለት ፲፩ ይተርፋል ፤ ለአበቅቴ ፲፩ መንሣታችን ስለዚህ ነው ።

ልደተ አበቅቴን ኋላ እናመጣዋለን ፤ አዋጁ ግን እንዳይቀር ከነሐሴ ከ፰ በታች አይወርድም ፤ ከጳጉሜን ከ፭ በላይ አይወጣም ። ፮ኛው ጳጉሜን ከአበቅቴ ገብቶ አለመቈጠሩ ስለምን ነው ? ያልን እንደሆነ ፥ ፬ቱ ወንጌላውያን በሰዓት በኬክሮስ ከአራት አድርገው ይካፈሉታል እንጂ እንደ አምስቱ ጳጉሜን ለአንዱም ለአንዱም አይደርስምና ፤ ከአበቅቴ ገብቶ አለመቈጠሩ ስለዚህ ነው ።

በአልቦ ጊዜ የጨረቃ ዓውደ ዓመት በመስከረም መባቻ ይጀመራል ፤ ይኸውም በነሐሴ በ፳፬ በመፈጸሙ ይታወቃል። ከመስከረም እስከ ሐምሌ ፫፻፴ ፤ ይሆናል ፤ ፶፬ ለማድረግ ከነሐሴ ፳፬ ያመጧል ፤ የጨረቃ ዓውደ ዓመት የተባለ ይኸ ነው ። ያን ጊዜ ልደተ አበቅቴ በነሐሴ ፳፭ ይሆናል ። ከነሐሴ ፯ ከጳጉሜን ፭ ፲፩ ይሆናል ፤ ጥንተ አበቅቴ የተባለው ይኸ ነው ። ከመስከረም እስከ ሐምሌ ፫፻፴ ይሆናል ፤ ፫፻፴ና ፲፩ ሲደምሩት ፫፻፵፩ ይሆናል ፤ ፶፬ ለማድረግ ግን ከነሐሴ ፲፫ ማምጣት ያስፈልጋል ፤ የጨረቃ ዓውደ ዓመት የተባለ ይኸ ነው ። ያን ጊዜ ልደተ አበቅቴ በነሐሴ ፲፬ ይሆናል ። ከነሐሴ ፲፯ ከጳጉሜን ፭ ፥ ፳፪ ይሆናል ፤ የ፪ኛ ዓመት አበቅቴ የተባለው ይኸ ነው ።

ከመስከረም እስከ ሐምሌ ፫፻፴ ይሆናል ። ፫፻፴ና ፳፪ ሲደምሩት ፫፻፶፪ ይሆናል ፤ ፶፬ ለማድረግ ግን ከጳጉሜ ፪ ያመጧል ፤ የጨረቃ ዓውደ ዓመት የተባለ ይኸ ነው ፤ ያን ጊዜ ልደተ አበቅቴ በጳጉሜን በ፫ ይሆናል ። ከጳጉሜን ፫ ይተርፋል ፤ ፫ኛው ዓመት አበቅቴ ይኸ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይሆናል፤ ይኸ ሕፁፅ ነው ይገደፋል አይቈጠርም፤ ፳፱ አበቅቴ ፩ መጥቅዕ የለም ያን ጊዜ ሌሊት በሕፀፅና አልቦ በሆነ በሠርቀ ዕለት ብቻ ይወጣል ።

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በዓመቱ | | ፲፩ | አበቅቴ | ይገኛል ። |
| በ፪ኛው | ዓመት | ፳፪ | አበቅቴ | ይገኛል ። |
| በ፫ኛው | ዓመት | ፫ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፬ኛው | ዓመት | ፲፬ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፭ኛው | ዓመት | ፳፭ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፮ኛው | ዓመት | ፮ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፯ኛው | ዓመት | ፲፯ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፰ኛው | ዓመት | ፳፰ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፱ኛው | ዓመት | ፱ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲ኛው | ዓመት | ፳ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፩ኛው | ዓመት | ፩ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፪ኛው | ዓመት | ፲፪ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፫ኛው | ዓመት | ፳፫ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፬ኛው | ዓመት | ፬ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፭ኛው | ዓመት | ፲፭ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፮ኛው | ዓመት | ፳፮ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፯ኛው | ዓመት | ፯ | አበቅቴ | ይገኛል |
| በ፲፰ኛው | ዓመት | ፲፰ | አበቅቴ | ይገኛል |

ባለው አበቅቴ ላይ ፲፩ ቢጨምሩ የሚመጣው፤ ፲፱ ቢጨምሩ ያለፈው ይታወቃል ። ፳፪ ቢጨምሩ የሚመጣው የሁለተኛው ዓመት፤ ፰ ቢጨምሩ ያለፈው የሁለተኛው ዓመት ይታወቃል ።

## ፯ኛ የአበቅቴና የፍሥሐ አወጣጥ ።

አበቅቴና ፍሥሐ ፩ ሁነው ቢቈጠሩ ቢያንሱ ፲ ቢበዙ ፴ ይሆናሉ « አበቅቴ ወፍሥሐ እመ ይውኅዱ ፲ተ ወእመ ይበዝኁ ፴ዓ ይከውኑ » እንዲል ።
በአልቦ ጊዜ ፍሥሐ በሚያዝያ በ፲ ይሆናል ።
እመ ይውኅዱ ፲ተ ያለው ስለዚህ ነው ።
በ፲፩ አበቅቴ ጊዜ ፍሥሐ በመጋቢት በ፳፱ ይሆናል
እመ ይበዝኁ ፴ ይከውኑ ያለው ይኸ ነው ።
በ፳፪ አበቅቴ ጊዜ ፍሥሐ በሚያዝያ በ፲፰ ይሆናል ።
በ፫ አበቅቴ ጊዜ ፍሥሐ በሚያዝያ ፯ ይሆናል
እመ ይውኅዱ ፲ተ ይከውኑ ያለው ይኸ ነው ።
በ፲፬ አበቅቴ ጊዜ ፍሥሐ በመጋቢት በ፳፮ ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

ረው ዕለቱን መሠረት አድርገን አጽዋማትን ፡ በዓላትን እናወጣበታለን ፤ አንድም ለአበቅቴ ፲፩ ነሥቶ ለመጥቅዕ ፲፱ ካልነው አጽዋማት ፡ በዓላት ባልተገኙም ነበርና ለመጥቅዕ ፲፱ መንሣታችን ስለዚህ ነው ። ዳግመኛም ካለፈው መጥቅዕ ሳኒታ ጀምሮ እስከሚመጣው መጥቅዕ ድረስ ቢያንስ ፲፱ ፣ ቢበዛ ፵፱ ዕለት ይገኛል ። ፲፱ ቢገኝ ያለውን ይይዟል ፤ ፵፱ ቢገኝ ፴ውን ገድፎ ፲፱ኙን ይይዟል « ማዕከለ መጥቅዕ ዘኀለፈ ወማዕከለ መጥቅዕ ዘይመጽእ ቦ ጊዜ በበ፲ቱ ወ፱ቱ ወቦ ጊዜ በበ፵ ወ፱ቱ ዕለት ይትረከብ » እንዲል ።

ማዕከል የተባለ ተረፈ መጥቅዕ ነው ፤ ተረፈ መጥቅዕ ከ፲፱ በታች የሆነ እንደሆነ ፲፱ ለማድረግ ከሚመጣው ዓመት ዕለታትን ያመጧል ፤ ከ፲፱ በላይ የሆነ እንደሆነ ፵፱ ለማድረግ ከሚመጣው ወር ዕለት እያመጡ ይቈጥሯል ።

በ፲፩ አበቅቴ ጊዜ መጥቅዕ በመስከረም በ፲፱ ይሆናል ፤ ከወሩ ፲፱ ሲያነሡለት ፲፩ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ።

ይኸን ፲፱ ለማድረግ ከጥቅምት ፰ ያመጧል ፤ ከወሩ ፰ ሲያነሡለት ፳፪ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ። ይኸን ፵፱ ለማድረግ ከመስከረም ፳፯ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፵ ወ፱ቱ ዕለት ይትረከብ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፳፯ ሲያነሡለት ፫ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፲፱ ለማድረግ ከመስከረም ፲፮ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በ፲ቱ ወ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፲፮ ሲያነሡለት ፲፬ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸንን ፲፱ ለማድረግ ከጥቅምት ፭ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፲ቱ ወ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፭ ሲያነሡለት ፳፭ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፵፱ ለማድረግ ከመስከረም ፳፬ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፵ ወ፱ቱ ዕለት ይትረከብ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፳፬ ሲያነሡለት ፮ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፲፱ ለማድረግ ከጥቅምት ፲፫ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፲ቱ ወ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፲፫ ሲያነሡለት ፲፯ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፲፱ ለማድረግ ከጥቅምት ፪ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፲ቱ ወተ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፪ ሲያነሡለት ፳፰ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፵፱ ለማድረግ ከመስከረም ፳፩ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፵ ወተ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

ከወሩ ፳፩ ሲያነሡለት ፱ ይተርፋል ፤ ተረፈ መጥቅዕ የተባለ ይኸ ነው ፤ ይኸን ፲፱ ለማድረግ ከጥቅምት ፲ ያመጧል ፤ ቦ ጊዜ በበ፲ቱ ወ፱ቱ ያለው ይኸ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| በ፯ኛው | » | ፳፬ | » | » |
| በ፯ኛው | » | ፲፫ | » | » |
| በ፰ኛው | » | ፪ | » | » |
| በ፱ኛው | » | ፳፩ | » | » |
| በ፲ኛው | » | ፲ | » | » |
| በ፲፩ኛው | » | ፳፱ | » | » |
| በ፲፪ኛው | » | ፲፰ | » | » |
| በ፲፫ኛው | » | ፯ | » | » |
| በ፲፬ኛው | » | ፳፮ | » | » |
| በ፲፭ኛው | » | ፲፭ | » | » |
| በ፲፮ኛው | » | ፬ | » | » |
| በ፲፯ኛው | » | ፳፫ | » | » |
| በ፲፰ኛው | » | ፲፪ | » | » |

መጥቅዕ የተባለ ፯ኛው ጨረቃ ፯ኛው ሠርቀ ወርኀ ነው ፤ እንዲህ ከሆነ ስለምን ነው ዕለቱ መጥቅዕ የተባለ ቢሉ ፡ ቀድሞ ሌዋውያን ዓመተ ኅድገትን ለመንገር ነጋሪት ይመቱበት ነበረና ስለዚህ ዕለቱ መጥቅዕ ተባለ ፤ ይኸውም ከመስከረም ፲፭ በታች አይወርድም ፤ ከጥቅምት ፲፫ አይወጣም ፤ መመላለሻው ፳፱ ይሆናል ፤ በዚህ ሲመላለስ ይኖራል ። እንዲህ ስለሆነ ግን መጥቅዕ የሚውልበት ዕለቱ ፲፱ ነው ፤ ፲፩ዱ በመስከረም ነው ፤ ፰ቱ በጥቅምት ነው ።

ከመስከረም ከ፲፭ በላይ በ፲፯ ፡ በ፳ ፡ በ፳፪ ፡ በ፳፭ ፡ በ፳፰ በሊህ በ፭ ዕለታት አይውልባቸውም ፤ ከ፲፮ቱ ፭ ሲነሣለት ፲፩ ይተርፋል ፤ ፲፩ዱ በመስከረም መሆኑ በዚህ ይታወቃል ። ከጥቅምት ከ፲፫ በታች በ፲፩ ፡ በ፱ ፡ በ፯ ፡ በ፫ ፡ በ፩ በሊህ በ፭ቱ ዕለታት አይውልባቸውም ። ከ፲፫ቱ ፭ ሲነሣለት ፰ ይተርፋል ፤ ፰ቱ በጥቅምት መሆኑ በዚህ ይታወቃል ።

ባለው መጥቅዕ ላይ ፲፱ ቢጨምሩ የሚመጣው ፤ ፲፩ ቢጨምሩ ያለፈው ይታወቃል ። ፰ ቢጨምሩ የሚመጣው የ፪ኛው ዓመት ይታወቃል ፤ ፳፪ ቢጨምሩ ያለፈው የሁለተኛው ዓመት መጥቅዕ ይታወቃል ።

በዘመነ ብሉይ በተሠሩ አጽዋማትና በዓላት ላይ ፲፱ ቢጨምሩ የሚመጣው ይታወቃል ፤ ፲፩ ቢጨምሩ ያለፈው ይታወቃል ። ፰ ቢጨምሩ የሚመጣው የ፪ኛው ዓመት ይታወቃል ፤ ፳፪ ቢጨምሩ ያለፈው የ፪ኛው ዓመት ይታወቃል ።

## ፱ኛ የዕለታት ተውሳክ የትመጣ ።

ነነዌን ለማግኘትና የዕለታት ተውሳክ የመጣበትን ለማወቅ ዕለተ መጥቅዕ በቀዳም የሆነ እንደሆነ ከሳኒታ መጥቅዕ ጀምሮ እስከ ነነዌ ድረስ ፩፻፳፰ ዕለት ይገኛል ። እሑድ የሆነ እንደሆነ ፩፻፳፯ ዕለት ይገኛል ።


www.ethiopianorthodox.org

ሰኞ የሆነ እንደሆነ ፩፻፷፮ ይገኛል ።
ማክሰኞ » ፩፻፷፭ »
ረቡዕ » ፩፻፷፬ »
ኀሙስ » ፩፻፷፫ »
ዓርብ » ፩፻፷፪ »

ሁሉንም በ፴ በ፴ ገድፎ የተረፈው የዕለታት ተውሳክ ይሆናሉ ።

ምዕራፍ ፮ ።

# በዓላትና አጽዋማት ።

## ፩ኛ የዘመነ ሐዲስ አጽዋማትና በዓላት ።

በዘመነ ሐዲስ ለተሠሩት አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው ነነዌ ነው ። ከነነዌ ሳኒታ ጀምሮ እስከ በአተ ጾም ፲፬ ዕለት ይገኛል ።

» ደብረ ዘይት ፵፩ ይገኛል ።
» ሆሣዕና ፷፪ »
» ስቅለት ፷፯ »
» ትንሣኤ ፷፱ »
» ረክበ ካህናት ፺፫ »
» ዕርገት ፻፰ »
» ጰራቅሊጦስ ፻፲፰ »
» ጾመ ሐዋርያት ፻፲፱ »
» ጾመ ድኅነት ፻፳፩ »

ሁሉንም በ፴ ፤ በ፴ ፤ ገድፎ የተረፈውን የአጽዋማት የበዓላት ተውሳክ ያደርጓል ።

## ፪ኛ ዘመነ ብሉይ ።

በዘመነ ብሉይ ለተሠሩ አጽዋማትና በዓላት መሠረታቸው መጥቅዕ ነው ። ከመጥቅዕ ሳኒታ ጀምሮ እስከ ጾመ አይሁድ ፱ ዕለት ይገኛል ።

» መጸለት ፲፬ »
» ፍሥሕ ፩፻፭ »
» ልበ ምድር ፪፻ ዕለት
» በዓለ ሠዊት ፪፻፴ »
» ጾመ አስቴር ፫፻፷፩ »
» ጾመ ዮዲት ፫፻፷፰ »

www.ethiopianorthodox.org

የጾመ ዮዲት ተውሳክ ፳፰ ነው ፤ ፳፰ና ፲፭ ፵፫ ይሆናል ። ፴ውን ገድፎ ፲፫ ይተርፋል ፤ ያን ጊዜ ጾመ ዮዲት በነሐሴ በ፲፫ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወርድም ።

## ፯ኛ የጾመ አይሁድ ኢየዓርግ ።

የጾመ አይሁድ ኢየዓርግ እንደሚከተለው ነው ፤ የጾመ አይሁድ ተውሳክ ፱ነው ፤ መጥቅዕ ፲፫ ይሆናል ፤ ሲደመር ፳፪ ይሆናል ፤ ያን ጊዜ ጾመ አይሁድ በጥቅምት በ፳፪ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወጣም ። የመጸለት ተውሳክ ፲፬ ነው ፤ ፲፬ና ፲፫ ፳፯ ይሆናል ፤ ያን ጊዜ መጸለት በጥቅምት በ፳፯ ይሆናል ከዚህ አይወጣም ።

የፍሥሐ ተውሳክ ፲ ነው ፤ ፲ና ፲፫ ፳፫ ይሆናል ፤ ያን ጊዜ ፍሥሐ በሚያዝያ በ፳፫ ይሆናል ከዚህ አይወጣም ።

የልበ ምድር ተውሳክ ፤ ፫ ነው ፤ ፫ና ፲፫ ፲፮ ይሆናል ፤ ያን ጊዜ ልበ ምድር በግንቦት በ፲፮ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወጣም ።

የበዓለ ሠዊት ተውሳክ ፴ ነው ፤ ፴ና ፲፫ ፵፫ ይሆናል ፤ ፴ውን ገድፎ ፲፫ ይተርፋል ፤ ያን ጊዜ በዓለ ሠዊት በሰኔ በ፲፫ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወጣም ።

የጾመ አስቴር ተውሳክ ፳፩ ነው ፤ ፳፩ና ፲፫ ፴፬ ይሆናል ፤ ፴ውን ገድፎ ፬ ይተርፋል ፤ ያን ጊዜ ጾመ አስቴር በጳጉሜ በ፬ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወጣም ።

የጾመ ዮዲት ተውሳክ ፳፰ ነው ፤ ፳፰ና ፲፫ ፵፩ ይሆናል ፤ ፴ውን ገድፎ ፲፩ ይተርፋል ፤ ያን ጊዜ ጾመ ዮዲት በመስከረም በ፲፩ ይሆናል ፤ ከዚህ አይወጣም ።

## ፰ኛ የወንጌላውያን አወጣጥ ።

ዓመተ ወንጌላውያንን ለማወቅ ዓመተ ዓለምን ከአራት መክፈል ያስፈልጋል ።

አንድ ዘመን ቢተርፍ ማቴዎስ ይባላል ።
ሁለት ዘመን ቢተርፍ ማርቆስ ይባላል
ሦስት ዘመን ቢተርፍ ሉቃስ ይባላል ።
ቢተካከል (አራት) ቢሆን ዮሐንስ ይባላል ።

## ፱ኛ የጥንተ ዮን አወጣጥ ።

ጥንተ ዮንን ለማወቅ ዓመተ ዓለምን ከአራት ይከፍሏል ፤ በዚያ ላይ መጠነ ራብዕትን ይጨምሯል ፤ ሁሉንም በ፯ ፤ በ፯ ፤ ገድፎ ከተረፈው አንዱን አትቶ የቀረው ጥንተ ዮን ይባላል ። ጥንተ ዮንም ማለት ጥንተ ፀሐይ ማለት ነው ። ጥንተ ዮን በረቡዕ ይጀመራል ።

የረቡዕ ጥንተ ዮን ፩ ነው ።
የኀሙስ ጥንተ ዮን ፪ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

| | | | |
|---|---|---|---|
| የዓርብ | ጥንተ ዖን | ፫ | ነው ። |
| የቀዳም | » | ፬ | ነው ። |
| የእሑድ | » | ፭ | » |
| የሰኞ | » | ፮ | » |
| የማክሰኞ | » | ፯ | » |

## ፱ኛ የዕለተ ዮሐንስ አወጣጥ ።

ዕለተ ዮሐንስን ለማወቅ በጥንተ ዖን በወጣው ላይ ሁለቱን ዕለተ ጠቢባን ይጨምሯል ፤ ሁሉንም በ፯ ፤ በ፯ ገድፎ ሳያትቱ የተረፈው ዕለተ ዮሐንስ ይሆናል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቢተርፍ ዕለተ ዮሐንስ | እሑድ | ይሆናል ። |
| ፪ | » | ሰኞ | » |
| ፫ | » | ማክሰኞ | » |
| ፬ | » | ረቡዕ | » |
| ፭ | » | ኀሙስ | » |
| ፮ | » | ዓርብ | » |
| ፯ | » | ቀዳም | » |

## ፲ኛ የሰንበተ ክርስቲያን ዕለት አወጣጥ ።

የሰንበተ ክርስቲያንን ዕለተ በዓላትን ለማወቅ በያመቱ የሚገኘውን ጥንተ ዖን በየወርኁ የሚገኘውን አጽፌ አውራኅ አንድ አድርጎ ቆጥሮ ሁሉንም በ፯ ፤ በ፯ ፤ ገድፎ ሳያትቱ የተረፈው ሰንበተ ክርስቲያን ዕለተ በዓላት ይባላል ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ፩ | ቢተርፍ | አሚር አሚሩ | ይባላል ። |
| ፪ | » | ሠኑዩ | » |
| ፫ | » | ሠሉሱ | » |
| ፬ | » | ረቡዑ | » |
| ፭ | » | ኀሙሱ | » |
| ፮ | » | ሰዱሱ | » |
| ፯ | » | ሰቡዑ | » |

## ፲፩ኛ የታሕታይ ቀመር አወጣጥ ።

ታሕታይ ቀመር በአንድ ዓቢይ ቀመር ፬ ጊዜ ይመላለሳል ።
፩ኛው ቀመር በተጀመረ በ፶፬ ዘመን ይሆናል ።
፪ኛው በተጀመረ በ፩፻፷፱ ዘመን ይሆናል ።
፫ኛው በተጀመረ በ፪፻፷፬ ዘመን ይሆናል ።

www.ethiopianorthodox.org

፩ኛው በተጀመረ በ፩፻፴፩ ዘመን ይሆናል ።
ይኸውም በአበቅቴ በጥንተ ዖን ይታወቃል ።

## ፲፪ኛ የላዕላይ ቀመር አወጣጥ ።

ላዕላይ ቀመር በአንድ ዓቢይ ቀመር ፬ ጊዜ ይመላለሳል ።
፩ኛ ቀመር በተጀመረ በ፴፯ ዘመን ይሆናል ።
፪ኛ ቀመር በተጀመረ በ፩፻፴፪ ዘመን ይሆናል ።
፫ኛ ቀመር በተጀመረ በ፪፻፲፯ ዘመን ይሆናል ።
፬ኛ ቀመር በተጀመረ በ፫፻፴፩ ዘመን ይሆናል ።
ይኸውም በአበቅቴ በጥንተ ዖን ይታወቃል ።

## ፲፫ኛ ሱባዔ ወንጌላውያን ።

፬ቱ ወንጌላውያን አንዱን ዓቢይ ቀመር ፤ ከ፬ አድርገው ቢካፈሉት በዘመን ፩፻፴፫ ፡ ፩፻፴፫ ፤ በሱባዔ ፲፱ ፡ ፲፱ ይደርሳቸዋል ። ይኸውም ሰንበተ ማቴዎስ ፤ ሰንበተ ማርቆስ ፤ ሰንበተ ሉቃስ ፤ ሰንበተ ዮሐንስ ይባላል ።

ሰንበት ማለት ሱባዔ ማለት ነው ።
አልቦን የሚቀበል ወንጌላዊ አራት አራተኛው ነው ።
ከማቴዎስ ዮሐንስ ፤
ከዮሐንስ ሉቃስ ።
ከሉቃስ ማርቆስ ፤
ከማርቆስ ማቴዎስ ይቀበላል ።
ከወደፊቱ ግን ሠገር አለና ከርሱ የሚቀበል ወንጌላዊ በ፬ኛው ቀን ይቀበላል ።
ሉቃስና ማርቆስ አርእስተ አናቅጽ የሆኑ እንደሆን ቀመራቸውን በ፫ኛው ቀን ይፈጽማሉ ። ከርሳቸው የሚቀበል ወንጌላዊ በ፬ኛው ቀን ይቀበላል ።
ዮሐንስ ቀመሩን በሳኒታ ይፈጽማል ። ከርሱ የሚቀበል ወንጌላዊ በ፫ኛው ቀን ይቀበላል ።
ጥንተ ቀመር ማክሰኞ ነው ፤ ማክሰኞ ማቴዎስ ፩
ማቴዎስ ፭
ዓርብ ማቴዎስ ፱
ረቡዕ ማቴዎስ ፲፫
ሰኞ ማቴዎስ ፲፯
ማክሰኞ ማርቆስ ፲፰
ረቡዕ ሉቃስ ፲፱ ፩ ንዑስ ቀመር ተፈጸመ ።
ኀሙስ ሠግር ነው
ዓርብ ዮሐንስ ፩

www.ethiopianorthodox.org

ረቡዕ ዮሐንስ ፭
ሰኞ ዮሐንስ ፱
ቀዳም ዮሐንስ ፲፫
ኀሙስ ዮሐንስ ፲፯
ዓርብ ማቴዎስ ፲፰
ቀዳም ማርቆስ ፲፱ ዓመት ፪ ንዑስ ቀመር ተፈጸመ ።
እሑድ ሉቃስ ፩
ዓርብ ሉቃስ ፭
ረቡዕ ሉቃስ ፱
ሰኞ ሉቃስ ፲፫
ቀዳም ሉቃስ ፲፯
እሑድ ሠግር ነው ።
ሰኞ ዮሐንስ ፲፰
ማቴዎስ ማክሰኞ ፲፱ ዓመት ፫ ንዑስ ቀመር ተፈጸመ ።
ረቡዕ ማርቆስ ፩
ሰኞ ማርቆስ ፭
ቀዳም ማርቆስ ፱
ኀሙስ ማርቆስ ፲፫
ማክሰኞ ማርቆስ ፲፯
ረቡዕ ሉቃስ ፲፰
ኀሙስ ሠግር ነው ።
ዓርብ ዮሐንስ ፲፱ ዓመት ፬ ንዑስ ቀመር ተፈጸመ ።

ንዑስ ቀመር ፬ ሲሞላ አንድ ማዕከላዊ ቀመር ይሆናል ፤ ማዕከላዊ ቀመር ፯ ሲሞላ ፩ ዓቢይ ቀመር ይሆናል ፤ ጥንታት ፬ ናቸው ። ምንና ምን ቢሉ ፤ ጥንተ ዓለም ፤ ጥንተ ቀመር ፤ ጥንተ ፀሐይ ፤ ጥንተ ጨረቃ ናቸው ።

ጥንተ ዓለም እሑድ ነው ።
ጥንተ ቀመር ማክሰኞ ነው ።
ጥንተ ፀሐይ ረቡዕ ነው ።
ጥንተ ጨረቃ ኀሙስ ነው ።

## ልዩ አስተያየት ።

፩—የቍጥር ትምህርት የተባለው ማንኛውንም እውነት በቍጥር ሚዛንነት ለማግኘት የተደረገ ሙከራ ነው ። ስለዚህ የዘመኑ ቍጥር ፤ የኮከቡ ቍጥር ሐሳበ ፊደሉ ፤ ሐሳበ ዳዊቱ ክፋውም ደጉም በዚሁ ይሠራ ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

፪—የዘመኑ አቈጣጠር ኢትዮጵያዊ መልክ ይኑረው እንጂ በጥንት ዘመን ዓለም የተስማማበት በተለይም ምሥራቃዊው ዓለም የተስማማበት ነበር ፤ አሁን ግን ኢትዮጵያዊ ባህል ሆኖ በጣም እንግዳ ነገር የሆነ የቍጥር ስልት አለው ።

፫—በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያ ብዙና ልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያን ይኑሩ እንጂ ይኸ ጥበብ የተጠበቀውም ጥንቱንም የተያዘው በኦርቶዶክሱ ክፍል ብቻ ነው ።

፬—ስለዚህ ጥበብ አስረጂነት ያላቸው የኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ካህናት ብቻ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፲፪ ።

# ኪነ ጥበባት ።

## ምዕራፍ ፩ ።

## ሥነ ጽሑፍ ።

### ፩ኛ የቁም ጽሕፈት ትምህርት ።

ሥነ ጽሑፍ በኢትዮጵያ ከፍ ያለ ግምት የተሰጠበት ፤ ቋንቋው የተሻሻለበት ፤ የፊደል አጣጣልና የቁም ጽሕፈት አቃቂር በብዛት የታየበት ጥበብ ነው ።

ነገር ግን ይኸ ሁሉ ሁኔታ የተስፋፋበት ጊዜ ከመቼ ጀምሮ እንደሆነ እንኳን እርግጠኛው ዘመን ባይታወቅም ከ፲፪ኛው መቶ ዘመናት ጀምሮ በየዘመናቱ አቅድን በመለወጥ ከ፩ኛው ዘመን የሚለይበት ልዩ ምልክትን በመተው እያስፋፉ ሲጽፉ እንደመጡ መጻሕፍት ይመሰክራሉ ። ከሳቢያቲክ ፊደል እንኳን ወደግዕዝ አንድም አሁን ወዳለው የጽሕፈት ጠባይ ለመድረስ የተቻለው የቁም ጽሕፈት ሥራ በጣም የተስፋፋ በመሆኑ ነው ። ምንም በአገራችን ብዙ ምርምር ተደርጎ ይኸ ዓይነት ጽሑፍ የዚህኛው መቶ ዘመን አቅድ ነው ፤ ያኛው ግን የዚያኛው መቶ ዘመን ሥነ ጽሑፍ ስልት ነው ተብሎ ልክ መልክ ባይሰጠውም የኛም ሆኑ የውጭ መርማሪዎች ስለጥንትነቱ መታወቂያ ብቻ የሰጡት ማስረጃ ስላለ በልዩ ልዩ ዐረፍተ ዘመን እየተነሡ በልዩ ልዩ ስልት እንደተጻፉ የሚያስረዳ ትልቅ ምስክር ሆኖ ተገኝቷል ይኸም ቁም ጽሕፈት የተባለው የፊደልን ጠባይ የሥነ ጽሑፍን ስልት ጠብቆና ጠንቅቆ የሚሔድ የነጥቦችን አቀማመጥ ፤ የአረፍተ ነገርን አመራረጥ ፤ በጠቅላላም ቁም ነገር ያለው መጽሐፍ ሆኖ እንዲገኝ በጥንቃቄ መሠራቱ ነው ።

#### ሀ. በቁም ጽሕፈት የሚጻፉ መጻሕፍት ።

በዚህ በቁም ጽሕፈት የሚጻፉ መጻሕፍት በመጀመሪያው ደረጃ ቅዱሳት መጻሕፍት ሲሆኑ ፤ በ፪ኛው ደረጃ ደግሞ ልዩ ልዩ ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት የሚውሉ መጻሕፍት እንደ ገድለ ቅዱስን ፤ ድርሳናት ፤ ተግሣጻት ፤ ዳዊት ናቸው ። እንዲሁም በ፫ኛ ደረጃ የፍልስፍና የታሪክ መጻሕፍትና እነዚህንም የመሳሰሉት ናቸው ፤ እነዚህም መጻሕፍት መዝገቡ ፩ ሲሆን ፤ ከአንዱ የተገኘውን ለሌላው ለማዳረስ ሲፈልጉ የግድ በቁም ጽሕፈት ቀድተው መስጠት ስለነበረባቸው ጸሐፊዎች ሁሉ ጊዜያቸውን ለዚህ ለተቀደሰ ተግባር ያውሉት ነበር ። ሲጽፉ ዓመት የሚፈጅ መጽሐፍ ይገኛል ፤ ነገር ግን በመጻፍና ብራናም በማውጣት ቀለም በመበጥበጥ ሌላውንም ሥራ ሁሉ በመሥራት ሳይሰለቹ ይሠሩ ነበር ፤ በዚህም

www.ethiopianorthodox.org

ምክንያት ገዳማት ፤ አድባራትና ልዩ ልዩ ቦታዎች ሁሉ የታሪክ መደብር ፤ የሥነ ጽሑፍ ምንጭ ሁነው ተገኝተዋል።በኛ በሀገራችን ቀርቶ ዛሬ በውጭ አገር ያሉ ዩኒቨር ስቲዎችንና ቤተ መጻሕፍትን መልተው የሚገኙ እንደዚህ ብለው የተጻፉት ናቸው ።

## ለ. የሚያጽፏቸው ።

እነዚህን መጻሕፍት ጠቃሚነታቸውን በመረዳት የሚያጽፉት ፤

ሀ—በልዩ ልዩ ዘመን የተነሡ ነገሥታት ነበሩ ፤ በማንኛውም ገዳምና ደብር ስንሔድ የምናገኛቸው መጻሕፍት ብዙዎቹ በየዘመኑ የተነሡትን ነገሥታት የሚያወሱ ናቸው ማለት «ተጽሕፈ በትእዛዙ ለንጉሥነ ዕገሌ አንድም ዘአጥረዮ በንዋዩ ፤ አንድም ዘአጽሐፎ» የሚል እናገኝበታለን ።

ነገሥታቱ በዚህ መልክ ሲያጽፉ ለጊዜው መጻሕፍቱ በብዛት እንዲገኙና ለአገልግሎት እንዲውሉ ረድተዋል ፤ ለአሁኑ ጊዜ ግን ለታሪክ ምቹ ምዕራፍን ሰጥተው ይገኛሉ ።

ለ/ መኳንንትና የሴት ወይዛዝርት ፤ እነርሱም ቢሆኑ በነገሥታቱ መልክ ለጐለቱትና ለአስገደሙት አንድም ለተሣሉበት ታቦት በዚሁ መልክ እያጻፉ ይሰጡ ነበር ።

ሐ/ መነኮሳትና ባሕታውያን ፤ እነርሱም እንዲሁ ለአገልግሎት እንዲውሉ ቅዱስ ተግባር አድርገው ሕይወታቸውን ሁሉ ለዚህ አውለው ይጽፉት ነበር ፤ ፩ኛም ሥራ እንዳይፈቱ በዚህ ተወስነው ይኸንም ሲሠሩ ይኖሩ ነበር ።

## ፩ኛ የጥቁር ቀለም አወጣጥ ።

በኢትዮጵያ ብዙ ጥበባት ቀደም ብለው የተፈለሰፉ ይገኛሉ ፤ ከነዚህም ውስጥ ልዩ ልዩ መልክ ያላቸው ቀለማትን ማውጣትና በልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉትን መሣሪያዎች ራሳቸው ሠርተው ማውጣት ነበር ፤ ይኸም ቅሉ ሊሆን የቻለው ፍላጐቱ ከማስገደዱ የተነሣ ነው ፤ ለምሳሌ ጥቁር ቀለምን ለማ ውጣት ከዚህ በታች በተዘረዘረው መሠረት ይሠራል ።

### ሀ. ጥላሸትና ከሰል ።

በመጀመሪያ ከልዩ ልዩ ዕቃዎች ጥላሸት ይሰበሰባል ፤ እርሱም የምጣድ ፤ የድስትና የሌላም የማናቸውንም ይኸን የመሳሰሉ ከእሳት የሚደርሱትን ዕቃዎች ጥላት ነው ።

፩ኛ/ የክትክታን ቅጠል አቃጥሎ ደቁሶ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ።
፪ኛ/ የቀረጥን ቅጠል አቃጥሎ ከሰሉን ደቁሶ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ።
፫ኛ/ የቅርቅሐን ሽልፋፎት ( ልባስ ) አክስሎ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ።
፬ኛ/ የቀንጠፋን ቅጠል አክስሎ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

፮ኛ/ የበጉን ቀንድ አቃጥሎ አሳርሮ ደቁሶ ከጥላሸቱ ጋር ይቀላቅለዋል ።

፯ኛ/ የኑጉን ፍሬ አሳርሮ ቆልቶ በኋላም አንፈቅፍቆ አፍልቶ የላቦቱን ውኃ አጠራቅሞ እየጨመሩ ማሸት ፤

፰ኛ/ ማዋሐጃ የሚሆን የግራር ሙጫ ተጠራቅሞ ይጨመራል ።

፱ኛ/ ይኸ ሁሉ ተጠራቅሞ ንጹሕ ቦታ ይዞ የተጠቀሱትን መቃስማት ሁሉ አልሞና አለስልሶ በአንድ ላይ ቀላቅሎ አንፈቅፍቆ በጠንካራ ዕቃ አድርጎ በየጊዜው እያሹ ማቆየት ፤ በመቆየቱና በመታሸቱ ሲደርቅ ሐሩሩን እየጨመሩ ጠም ዘዝ ባለ ጊዜ እንደገና ጠንክሮ ማሸት ነው ።

## ለ. የሐሩሩ ዓይነት ።

ሐሩር የሚባለው ለቀለሙ ወዝ የሚሰጥ የእኽል ቅርጣን ነው ፤ እርሱም ገብስም ፤ ስንዴም ፤ እንክርዳድም ቢሆን እንደተገኘ ይሆናል ፤ ግን ከተገኘ የዳጉሳ ሐሩር የበለጠ ይሆናል ። እርሱንም ቆልቶ መቀቀል ነው ፤ ከዚህም በኋላ የዚህ ውኃ በጣም ሳይቀጥን እየተዘፈዘፈ እየቆየ በየጊዜው ይጨመራል ፤ ደኅና አድርጎ እንዲቦካም ሙቀት ያለው ቦታ ያስፈልጋል ።

## ሐ. ቀለሙ ተፈላጊ ሆኖ የሚደርስበት ጊዜ ።

ቀለሙ በዚህ ዓይነት ሲቦካ ቆይቶ በተፈላጊው መንገድ እንዲሠራበት ሲፈለግ የሚፈጀው ጊዜ እንዳስተሻሸቱ ይሁን እንጂ ቢቸኩል ፫ ወር ድረስ መቡካት አለበት ፤ ያለዚያ ግን ፮ ወር ታሽቶ የወጣ እንደሆን ጥፉ ቢሉት የማይጠፋ መሠረት ያለው ቀለም ይሆናል ። ከዚያ በኋላ ልጥልጥ አድርጎ ለብዙ ዘመን ሊያገለግል እንደሚችል በብዛት ከፍሎ ከፍሎ ያስቀምጠዋል ። አንዳንዶች ይኸን ሥራዩ ብለው እያወጡ ይሸጣሉ ፤ ግን አስተማሪዎችና ተማሪዎች ከመግዛት ይልቅ ራሳቸው ቢያወጡ የቀለለ ስለሚሆንላቸው በየጊዜው ራሳቸው ይሠራሉ ። ቀዩንና አረንጓዴውን ከአፈርና ከልዩ ልዩ ቅጠል በዚሁ መልክ ይቀምሙታል ፤ ሌላውን ግን እነዚህን ሁለቱን በማገናኘት እየበጠበጡ ሲሠሩበት ልዩ ልዩ ኅብር ያላቸውን ቀለማት ይሰጣል ። በዚህ ሱሳን ወርድ ያወርዳሉ ፤ ሐረግ ይጥላሉ ፤ ሥዕል ይሥላሉ ። እንደዚህ ብሎ የወጣው ቀለም ብራናው ፈጽሞ ካላረጀና ካላለቀ አያረጅ አያፈጅ ወይም ብራናውን አይጎዳ አያበላሽ ተስማምቶ ይኖራል ፤ አሁን የሚሠራበት የውጪ አገር ቀለም ግን ብዙ ዘይት ስላለበት ብራናውን ያበላሻል ።

## መ. ተበጥብጦ የሚጻፍበት ጊዜ ።

ልጥልጥ አንድም እንክብል የነበረው ቀለም ሊጻፍበት ሲያስፈልግ በቀለም ቀንድ ይበጠበጣል ፤ እርሱም ደኅና አድርጎ እንዲቦካ ፪ ቀን ያህል መዋል በግድ ያስፈልገዋል ። የቀለም ቀንድ የተባለውም ከከብት ቀንድ የሚሠራ የቀዩና የጥቁሩ ቀለም ተለይቶ ተሠርቶ ቅርጹ አምሮ ለዚሁ ተግባር ብቻ ተዘጋጅቶ የሚገኝ ዕቃ ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ሠ. የሚጻፍበት ብዕር ።

የሚጻፍበትም ነገር ደግሞ በጥንት ጊዜ የዶሮ አንድም የአሞራ ላባ ነበር ፤ አሁን ግን ሸንበቆ ፤ የሴት ቀስት ፤ ይኸንንም የመሳሰሉት ዕፀዋት የሚገኝ ነው ። ለዚሁም ምሳሌ ጠቀስ ንግግር ሲያደርጉ ፤ « ወካህን የጎድር በመቃብር » ይላሉ ። ትርጉሙም ካህን የሚያድረው በመቃ ብዕር ነው ማለት ነው ።

## ፫ኛ የብራና አወጣጥና የማውጫው መሣሪያዎች ።

ብራና ለማውጣት ብዙ ድካም ያለበት ብዙ ጊዜም የሚፈጅ ሥራ ነው ፤ ሆኖም መምህራኑ አንድም ጸሐፊዎቹ ሁሉ ሳይሰለቹ በየጊዜው ሲያወጡና በዚያም ሲሠሩ ይኖራሉ ፤ አወጣጡም እንደሚከተለው ነው ።

፩ኛ/ ቆዳው ከውኃ ይነከራል ፤ እስኪበሰብስም ይቆያል ፤ ይኸም ቆዳ ተፈላጊ ጽዳት ያለው ነው ተብሎ የሚገመት የፍየል ቆዳ የሆነ እንደሆነ ነው ፤ ነገር ግን የበግም ቆዳ ይሆናል ። እንዲሁም የልዩ ልዩ እንስሳት ሳይቀር ሊሆን ይችላል ፤ እንዲያውም በቀድሞ ጊዜ የፈረስና የአህያ ቆዳ ሳይቀር ብራና ይሆን ነበር እያሉ እንደተረት የሚያወሩ አሉ ፤ ግን ነገሩ እውነት አይመስልም ፤ ምክንያቱም እነዚህ እንስሳት ራሳቸው ርኩሳን ናቸው እየተባሉ ሲጠሩ ቆይተው ሲሞቱ በቆዳቸው ቅዱስ መጽሐፍ ሊጻፍበት አይችልምና ነው ።

፪ኛ/ ቆዳው ከላይ በተጠቀሰው መልክ ርሶ ሲወጣ እንደ አልጋ በተሠራ እንጨት ይወጠራል ።

ሀ. ሥጋው ይፋቃል ፤ ይታጠባል ፤ ይራመማል ፤

ለ. ሲደርቅ ጠጉሩ ይፋቃል ፤ በሻፎ ድንጋይ ማለት ዓይን ዓይን ባለው ድንጋይም ይራመማል ። በውስጡም ፤ በውጪውም ይራመማል ፤ ይታጠባል ፤ ይጠራልም ።

ሐ/ ከጠራና ከነፃ በኋላ ሲደርቅ እንደ ቅጹ ዓይነት እየተቆረጠ እየተሠመረ ይጻፍበታል ፤ ለዚህም የሚያስፈልጉ የተለዩ መሣሪያዎች አሉት ።

## ሀ· የብራና ማውጫ መሣሪያዎች ።

ብራና ለማውጣት ሲፈለግ ከዚህ የሚከተሉት መሣሪያዎች መኖር አለባቸው ። እነዚህም ፤—

፩ኛ/ ማፈፊያ (ካራ) የብረቱ ዓይነት ሞረድ የሚመስል ይሆንና የሥራው ዓይነት ስለቱ ዙሮ የገጠመ ሥጋውን የሚያስለቅቅበት መሣሪያ ነው ።

፪ኛ/ መላጫ( መጥረቢያ) የተባለ ነው ፤ ይኸውም የብረቱ ዓይነት እንደዚሁ ሲሆን ፤ ሥራውም እንደዚሁ ጠጉሩን የሚላጭበት ነው ።

፫ኛ/ መዋጠሪያ ይባላል ፤ እርሱውም አራት መዓዘን ያለው እንጨት ብራናውን ቆዳውን የሚወጥርበት ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

፬ኛ/ መሠቆሪያ የተባለው ለበቅ (ዘንግ) ነው ፤ ይኸውም በቆዳው እየገባ ከግንዱ ጋር የሚያገናኝ ነው ።

፭ኛ/ መራመሚያ ድንጋይ ፤ ይኸውም ዓይን ዓይን ያለው ሻሮ ድንጋይ ነው ፤ እርሱም ጠጉሩን ከቆዳው ሥጋውንም የሚያስለቅቅ ለብራናውም ጥራትን የሚሰጥ ዕቃ ነው ።

፮ኛ/ ገመድ አንድም መወጠሪያ ነው ።

፯ኛ/ ማስመሪያ መሳፍቻ (ወስፌ) ነው ፤ ይኸውም መሥመሩን የሚያሠምሩበት መሣሪያ ነው ።

፰ኛ/ መቁረጫት (መቀስ) እርሱም ብራናውን በቅጽ በቅጹ መቁረጫ ነው ።

፱ኛ/ መድመፅ እርሱ ደግሞ ለብራናው ለኸት የሚሰጥ ቀለም እንዲቀበል የሚያደርግ መሣሪያ ሲሆን ፤ ፪ ዓይነት ነው ።

ሀ/ የደቅ ሥራ ሸክላ እርሱም ደግሞ ሥጋውን የሚዳምጹበት ነው ።

ለ/ ነጭ ሸክላ ነው ፤ ርሱም ደግሞ በጠጉር በኩል ያለውን ችግር የሚያቃልል መሣሪያ ነው ።

## ምዕራፍ ፪ ።

# ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥዕል ።

## ፩ኛ የሥዕል ታሪክ ።

የኢትዮጵያ የሥዕል ታሪክ መነሻ በጣም የራቀ ነው ፤ የሥዕልና የቅርጽ ባህል መዲና ከሆነችው ከአፍሪካ ውስጥ ከቅርጽ ጋር ያልተቋረጠ ዝምድና የሥዕልም ባህል ያላት ኢትዮጵያ ናት ።

ከልደተ ክርስቶስ በፊት ግብፅ የሥልጣኔ ብርሃን በወጣበት ጊዜ ፤ ኢትዮጵያም በኪነ ጥበብ መራመዷን የሚገልጽ በታሪክ ዓምድ ላይ ጉልህ የሆነ ማስረጃ በንግድ ስምምነት መሠረት ኢትዮጵያ የሥዕል ቀለማትን ለግብፅ ትልክላት እንደነበር የሚተረከው የማያጠራጥር ነው ።

ከልደት በኋላ የኢትዮጵያ ሥዕል ከመካከለኛው ምሥራቅ የክርስትና ዓሣሣልና ከቤዛንቲን ሥዕሎች ጋር በመደባለቅ ምሥራቃዊ ቢመስልም ፤ የጥንቱን የዓሣሣሉን መሠረት ሳይለቅ እስካለንበት ዘመን በመድረሱ ፤ ኢትዮጵያ ራሱን የቻለ የሥዕል ባህል ባለቤት ለመባል ረድቷታል ። የዓሣሣሉም መልክና የቦታ አቀማመጥ የሐሳቡ አገላለጥ ከማንም ቅጅ ያልሆነ ብሔራዊ ጥናት ብቻ እንደሆነ ታምኖበታል ። እየዋለ እያደረ ግን የኛው ሥዕል መልክ ወደሌላው የሔደውን ያህል የኛም ከሌላ እያዩ እንደደባለቁበት ይታመናል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ የሥዕል መሣሪያዎች ።

ለሥዕል የሚያስፈልጉ ብዙ ነገሮች አሉን ፥ እነዚህም ሁሉ ብሔራውያን በመሆናቸው ምንም ችግር ሳይፈጥሩ ሲሠራባቸው ቆይቷል ፤ ለምሳሌ የሥዕል መሣሪያዎች ቀለማት በያይነታቸው እንዲሁም እንደ ብሩሽ ፤ በለሴ ጨርቅ ፤ ከሰል ያሉት እንዲሁም ማጣበቂያዎች የሚሆኑት የስንዴ አንድም የቀይ ጤፍ ሙቅ ነበር ፤ እንዲሁም ዕብነ በረድ ፤ ሙጫ ፤ የቁርበት ማሸጊያ ፤ ዕንቍላልና ዕንቧይ ይኸንም የመሳሰሉ ሌሎችም ቢሆኑ በቅርብ የሚገኙና በሁሉም ዘንድ የታወቁ ነበሩ ፤ ስለዚህም ያለ ችግር ይሠራባቸው ነበር ።

<u>ሀ. ቀለማት ፤</u> ልዩ ልዩ ዓይነት ቀለማት የሚያስፈልጉት ለሥዕል መልክ መስጫ ሲሆኑ ኅብራቸው ብዙ የሆኑ እንደ ቦታው አስፈላጊነት ይሰጡት ነበር ፤ እነዚህ ቀለማት በሀገረ ሰብእ ተሠርተው ስለሚቀርቡ ከቶ ችግር አልነበረም ።

<u>ለ. ብሩሽ ፤</u> ይኸም ቀለማቱን ለመቀቢያ በነርሱው ሠሪነት የተሠራ ነበር ፤

<u>ሐ. በለሴ ጨርቅ ፤</u> ይኸም መሣሪያ ለሥዕል ሙቁ ከአጣበቀው በኋላ ነጭ ቀለም ይቀባ የነበረው ጨርቅ ነው ።

<u>መ. ከሰል ፤</u> ለሥዕሎች መንደፊያ የሚሆን ቀለምነት ያላቸው እንጨቶች ቀምበጣቸው እየተቆረጠ ይከስልና በዚያ ይነደፍ ነበር ።

<u>ሠ. የስንዴ ፤</u> ወይም የቀይ ጤፍ ሙቅ ፤ ይኸም ጨርቁን ከግድግዳው ላይ ለመለጠፊያ የሚረዳ ነበር ።

<u>ረ. ዕብነ በረድ ፤</u> ጨርቁ ከተለጠፈ በኋላ ከንድፉ በፊት ለማለስለሻና በጣም እንዲነጣ የሚቀባ ነጭ ቀለም ነበር ።

<u>ሰ. ሙጫ ፤</u> ይኸም ለብራና ሥዕል አንድም ለሐረግ ቀለማት መበጥበጫና ወዝ መስጫ ነው ።

<u>ሸ. የቁርበት ማሸጊያ ፤</u> ይኸም ከዕንቍላል ጋር ተደባልቆ ለቀለማት መበጥበጫና ማድረቂያ የሚሆን ነበር ።

<u>ቀ. ዕንቍላል ፤</u> ለቀለማት መበጥበጫና ወዝ ለመስጫ ከማሸጊያ ጋር ሳያድር ለዕለት አገልግሎት የሚውል ነበር ።

<u>በ. የዕንቧይ ውኃ ፤</u> ይኸም ደግሞ ዝንቦችና ሌሎችም ተባዮች ቀለማትን እንዳይበሏቸው ከቀለማት ጋር ተደባልቆ ለመከላከያ ያገለግል የነበረው ነው ።

## ፫ኛ ዕቃዎች እንዴት እንደሚገኙ ።

<u>ሀ. የቀለማት አወጣጥ ፤</u> ቀለማት እንዴት እንደሚወጡ በገጽ ፪፻፰፰ ተመልከት።

<u>ለ. ቡሩሽ ፤</u> ብሩሽ ሲሠራ በመጀመሪያ እንጨት ይሾልና ያህያ ጋማ በክርታሥሮ በሰም አንድም በቁልቋል ደም ይጣበቃል ከዚያም በኋላ ይሣልበታል ።

www.ethiopianorthodox.org

ሐ. በለሴ ጨርቅ ፤ ጥጡ በቤት እመቤት ይፈተላል ፤ ከዚያ በኋላ በታወቀ ሸማኔ ይሠራል ።

መ. የስንዴ ፤ አንድም የቀይ ጤፍ ሙቅ ፤ የስንዴ አንድም የጤፍ ሙቅ የተባለው ፤ ቀጠን ብሎ ይበጠበጥና ይፈላል ፤ በረድ እንዳለም ለማጣበቂያ ግድግዳ ውና ጨርቁ ይቀባል ይጣበቃልም ።

ሠ. ከሰል ፤ ይኸም የክትክታና የወይራ ጭራሮች ተሰብስበው ፤ ጉድጓድ ተቆ ፍሮ ይከሰላል ነዲዱ ካለቀለት በኋላ ጢሱ እንዳይወጣ አክንባሎ መሰል ደንጋይ ይደፋበታል ፤ ተበረደ በኋላ አውጥቶ ይሠራበታል ፤ ንድፍ ይነደፍበታል ።

ረ. ዕብነ በረድ ፤ ዕብነ በረድም በእሳት አርሮ ይፈጭና በወንፊት ተነፍቶ በማሸጊያ ውኃ ተበጥብጦ ለጨርቅ መደብ መቀቢያ ይሆናል ።

ሰ. ሙጫ ፤ የግራር ሙጫ ከውኃ ደባልቆ በፀሐይ አንድም በእሳት ቀልጦ ለብራና ሥዕል ከቀለማት ጋራ ይቀላቀላል ።

ቀ. የቁርበት ማሸጊያ ፤ ማሸጊያ የተባለው የከብት ቆዳ በደንብ ይታጠብና ተተልትሎ በጋን ይቀቀላል ፤ ሲበስልና ቆዳው ጨርሶ ሲነፍር በማጣሪያ ይጣራል ፤ የተጣ ራው ውኃ በየቃው በቀዝቃዛ ቦታ ይቀመጣል ፤ ከረጋ በኋላ በቢላዋ ይከፋፈልና ማንቃ ላይ ተደርጎ ይደርቃል ፤ ከዚያም በኋላ ለሥራ በተፈለገ ጊዜ በሚያስፈልገው መጠን እየተበጠበጠ ይሠራበታል ፤ ማሸጊያው ሊውል የሚችለው ፤

፩ኛ ለሥዕል ጨርቅ ግድግዳ ላይ ለመለጠፊያ ከስንዴ ሙቅ ጋር ተደባ ልቆ መጣበቅ ይሆናል ።

፪ኛ ለቀለም መሥሪያ ያገለግላል ።

በ. ዕንቊላል ፤ የዕንቊላል አስኳል ከማሸጊያ ጋር ለቀለማት መበጥበጫ ከሰማያዊና ከነጭ ቀለም በስተቀር ይገባል በሁለቱ ቀለማት የማይገባው እንዳያ ጠቊራቸው ነው ።

## ፩ኛ ባህላዊ ዓሣሣል ።

የኢትዮጵያ ሥዕል ግቡ ታሪክን መተረክ ትምህርትን መስጠት ስለሆነ ፤ የቅርበትንና የርቀትን መጠን በጥንቃቄ ሳይከታተል ትምህርት ጠቀስ ታሪካዊ መልኩን ሳይለውጥ አንድም ሳያስቀር በዝርዝር ይገልጻል ። ትምህርታዊ መልኩንና የታሪኩን መልእክት ፍጹም ለማድረግ በማለት በሥዕሎቹ ብቻ ሳይወሰን በተጨ ማሪም የሥዕሎቹ መግለጫ ይጻፍበታል ። የሥዕሎቹንም ጉላት ለማሳየት ማንኛ ውንም ዝርዝር ሥዕሎች በጥቁርና በከባድ ቀለማት ይነቀሳል ፤ በኢትዮጵያ ባህል ዓሣሣል ዋነኛው ሥራ መንፈሳዊ ሥዕሎች ስለሆኑ ፤ እነኙሁም ሥዕሎች እየተደጋ ገሙ በብዛት ከመሣላቸው የተነሣ የተወሰነ የማይለወጥ ባህላዊ ልማዶችና ደምቦች ወጥተውላቸዋል ። ከነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

ሀ. ጌታችንን ኢየሱስን የሰቀሉት አይሁድ ፤ አረማውያንና ዲያብሎስ ፤ እንዲሁም ሰይጣናት የሚባሉት በአንድ አቅጣጫ ፤ በአንድ መልክ ፤ በአንድ ዓይን ብቻ ይሣላሉ ፤ ቅዱሳን መላእክት ሌላም ሰው ቢሆን በሙሉ መልክ ከሁለት ዓይን ጋር ይሣላል ። ለማንም አመልካች ሁሉ ባንድ ጐን አንድም አቅጣጫ ባንድ ዓይን የተሳለ ሁሉ የክፉ የኃጢአተኛም ምልክት ነው ። በሙሉ መልክና ከነሁለት ዓይኑ የተሣለ ግን ቅዱስ መሆኑን በማየት ባጭሩ ይረዳዋል ።

ለ. በሥዕለ ስቅለት ላይ ሁልጊዜ ጌታችን ራሱን ወደቀኝ እንዳዘነበለ ይሣላል ።

ሐ. ምስለ ፍቁር ወልዳም ሁልጊዜ ጌታ ከግራ ወደቀኝ ሁኖ ፤ እመቤታችንም ራሷን ወደግራ አዘንብላ ትሣላለች ።

መ. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን በቅኔ ማኅሌት ፤ በመቅደስና ፤ በቅድስት የተከፈለ ሲሆን ፤ ሁልጊዜ ሥዕሎቹ የሚሳሉት በመቅደሱ አራት ገጾች ላይ ነው ፤ የማይለወጠውም ባህላዊ አቀማመጣቸው እንደሚቀጥለው ይሆናል ።

፩. በምሥራቅ ገጽ ፤ ነገደ ኢየሱስ ተብሎ የጌታችን የተአምራት ታሪኮች የሐዋርያት ሥራና ተጋድሎ ፤ የኤፍሬም እመቤት የተባለችው ይሳሉበታል ።

፪. በምዕራብ ገጽ ፤ ነገደ ስቅለትና የልደት ፤ የጥምቀት ፤ ሕማማተ መስቀል ፤ ትንሣኤ ፤ ምስለ ፍቁር ወልዳና የቅዱስ ጊዮርጊስ ሥዕሎች ይሳሉበታል ።

፫. በሰሜን ገጽ ፤ ነገደ ሰማዕታት ተብሎ የሰማዕታት ታሪክና እሞሙ ለሰማዕታት የተባለች የመቤታችን ሥዕሎች ይሳሉበታል ።

፬. በደቡብ ገጽ ነገደ ማርያም ፤ ተብሎ ከልደቷ እስከ ተንሣኤዋ ድረስ ያለው የእመቤታችን ታሪክና የምጽአት ታሪክ ይሣላሉ ።

፭. ከምኋሩ በላይ በምሥራቅ ዕርገት ፤ በምዕራብ ቅድስት ሥላሴ ፤ በሰሜን ደብረ ታቦር ፤ በደቡብ ደብረ ምጥማቅ ይሳሉበታል ።

፮. በመቅደስ በሮች ፤ በምዕራብ የመቅደሱ መዝጊያዎች ላይ ቅዱስ ሚካኤል ፈርዖንን ከነሠራዊቱ እንዳሰጠመና ቅዱስ ሩፋኤል ዓሣንበሪውን እንደወጋ ይሣሉበታል ።

፯/ በአራቱም ገጾች ደግሞ ፤ ልዩ ልዩ የሆነ የመላእክት ቅድስናን የሚገልጡ ሥዕሎችና ሐረግ ይጣልበታል ።

፰/ የቤተ ክርስቲያን ሥዕሎች ፤ የሚያሥሉ ምዕመናን ተማኅጸንኩ እንዳሉ በሚዘከሩት ቅዱስ ሥር እንደ ወደቁ ይሣላሉ ። በማንኛውም ቤተ ክርስቲያን ቢሆን ፤ ሥዕል የተሣለ ከሆነ የሚገኘው ይኸው ዓይነት አቀማመጥ ነው ።

## ፭ኛ የሠዓሊው ሁኔታ ።

ሠዓሊው በኢትዮጵያ ኅብረተ ሰብ ውስጥ ምሁር በመሆኑና በሊቅነት ደረጃ ስለሚቈጠር ሁልጊዜ የሚጠራበት የማዕርግ ስም አለቃ የሚል ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

### ሀ. የሠዓሊ ዋጋ ።

የጥንት ሠዓሊ የተከበረ በመሆኑ በመንግሥት ታዞ ቢስልም ቅሉ ሥራውን ሠርቶ እስከ አስረከበበት ድረስ በየወሩ ሙክት ፥ ከ፫ እስከ ፭ ዳውላ እኽል ፥ ከ፩ እስከ ፪ ጉንዶ ቅቤ ፤ ከ፩ እስከ ፪ ጉንዶ ማር ፤ የወር ወጪ ከ፲ እስከ ፳ ብር ይቀበል ነበር ። በተጨማሪም በሚሥለው ደብር አጥቢያ ተዝካር የተደረገ እንደሆነ እንደደብሩ አለቃ ወግ ነበረው ፤ ይኸውም አንድ ሽንጥ ሥጋ ፥ ገንቦ ጠላና አሥር እንጀራ ይሔድለት ነበረ ፤ ባለተዝካሩ ሰው እስቦ ያላከ እንደሆነ ፲ ብር ዳፋን ይቀጣ ነበር ።

ሠዓሊው ሥራውን ሲጨርስ የሥራው ዋጋ ከ፩ሺህ ብር በላይ ገንዘብ ተሰጥቶት ቀሚስና ድርብ ይሸለም መልከኚኘነትም ያገኝ ነበር ።

### ለ. የሥዕል ቃላት ።

የኢትዮጵያ የሥዕል ባህል የብዙ ዘመናት ታሪክና የረቀቀ በመሆኑ ራሱን የቻለ አንቀጽ አለው ማለት ራሱን የቻለ ትርጒም ይገኝበታል ።

ከነዚሁም ቃላቶችና ትርጓሜያቸው በከፊል ከዚህ በታች ተዘርዝረዋል ።

ናዞርድ ፤ የቀለም ስም ሰማያዊ መልክ ማለት ነው ።

ለሂ ፤ ውበት መስጠት ማለት ነው ።

ነጠብጣብ ፤ ይኸም ማለት ጌጣጌጥ መስጠት ማለት ነው ።

ማዋዛት ፤ አክላትን ጨርሶ መሳል ማለት ነው ።

መንፈስ ያለው ፤ ስሜት የሚሰጥ ሥዕል ማለት ነው ።

ሐረግ መጣል ፤ ሐረግ መጣል መሥራት ወይም መሣል ማለት ነው ።

ብሩህና ጥላ ፤ የብርሃንን አቅጣጫ ተከትሎ የሥዕሎችን ክብነት የሚያሣይ ሥዕልነው

መደብ ፤ ማለት ሥዕል ያላረፈበት ትርፍ ሰሌዳ ነው ።

የቁመት ፤ ማንኛውንም ነገር በሙሉ አካል የሚያሣይ ሥዕል ።

አይር ፤ ድብልቅልቅ ማለት ነው ፤ ይኸም የቀለምን ዓይነት የሚያሣይ ማለት ነው ።

ለምሳሌ ሰማያዊና ብጫ ሲታይ (ሲደባለቅ) አረንጓዴ ጥቁር ቀለም ይሆናል ።

ጉርድ ፤ የአንድን አካል ወገብ ወይም ከአንገት በላይ የሚያሣይ ሥዕል ማለት ነው ።

ምዕራፍ ፫ ።

## የድጉሥ ሥራ ።

### ፩ኛ የድጉሥ ጌጥ ።

እንደሌላው ረቂቅ ጥበባችን ሁሉ የድጉሥ ሥራም በኢትዮጵያችን በጣም የተስፋፋ ነበር ። የድጉሥ ሥራ ማለትም በቆዳ ላይ የሚደረግ ጌጣጌጥና ሐረግ ነው ፤

www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ጌጥ ብዙ ጊዜ የሚታየው በመጻሕፍት ገበታና በመጻሕፍት ማኅደር ላይ ነው ፤ ይሁን እንጂ በአንዳንድ ልብም ዕቃዎች ላይም መዋሉ አልቀረም ፤ ለምሳሌ በጐራዴና በሰይፍ ሰገባ (ማኅደር) በበቅሎና በፈረስ ዕቃ ፤ እንዲሁም በልዩ ልዩ የቤት ዕቃ ላይም እንዲሁ ይውል ነበር ፤ የባሕር ዓረብ የለበሰው ዕቃ ሁሉ ጌጥ ይወጣለት ድጕሥ ይጣልበት ነበር ።

የድጕሡም ዓይነት እንደዕቃው ሁናቴ የጌጡም አገባብ ቦታ ነበረው እንጂ እንደ አገኘ አይጣልም ነበር ፤ ማለት ለማንኛውም ጌጥ ስምና ቍጥር አለው ፤ ከእገሌ ቀጥሎ እገሌ የገባ እንደሆነ ጌጡ ጐልቶ ጥልፉ ተለይቶ ታይቶ ያስደስታል ፤ ከእገሌ በፊት እገሌ የገባ እንደሆነ ግን ሥራው ረቂቅ ይሆናል ጥልፉም የጠበቀ ይሆናል በማለት ተራ እየጠበቁ ይደጕሡ ነበር ። የመድጐሡም መሣሪያ ብዙ ዓይነት ሲሆን በአንድ ሥራ ላይ ሁሉንም የሚያስገቡ አዋቂዎች ነበሩ ፤ አሁን ግን ግማሹ እንኳን ቢገባ ነው እንጂ ሁሉም አይገቡም ፤ ስለዚህም ለዓይን ሞቅ ደመቅ አይልም ። የሆነው ሁኖ ጥበቡ ሳይጠፋ እስካሁን ድረስ በመሠራት ላይ የሚገኝ በመሆኑ ያስደስታል ። የመሣሪያውም ዓይነት ፲፪ ሲሆን ስሙም እንደሚከተለው ልዩ ልዩ ነው ።

## ፪ኛ የመድጐሥ ዓይነት ስምና ቍጥር ።

፩ኛ/ ርእሰ መድጐሥ
፪ኛ/ መርገጫ
፫ኛ/ መሳቢያ
፬ኛ/ ዓይነ ርግብ
፭ኛ/ የውኃ እናት
፮ኛ/ ቀርነ በግዕ
፯ኛ/ ባለዘንባባ
፰ኛ/ ባለገመድ
፱ኛ/ ፍየል ፈለግ
፲ኛ/ ትፍትፍ
፲፩ኛ/ ጥምዝ
፲፪ኛ/ — የዚህ ቍጥር ስሙ ጠፍቷል ከሥራም ውጪ ሁኗል።

ከላይ እንደተናገርነው ለአንድ ሥራ ሁሉም በአንድ ጊዜ ስለሚያስፈልጉ በጣም አስፈላጊና አድማቂ የሆኑትን መሣሪያዎች ብቻ በመከተል አንድ በአንድ እየተረሳ እንዳይሄድ ያሰጋል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፲፫ ።

# የመምህራን ሕይወት ።

### ምዕራፍ ፩ ።

## የመምህራን ታሪክ ።

ጥንታውያን የኢትዮጵያ መምህራን ክብር የሚገባቸው ቀዋሚ ታሪክ ያላቸው ናቸው ፤ ስለዚህ ለእሉት ሽልማት ለሞቱትም የመታሰቢያ ሐውልት ሊቆምላቸው ፤ የበዓል ቀን ተለይቶ መታሰቢያቸው ሊከበርላቸው የሚገቡ ናቸው ። አርቆ በሚያሳይ መነጽር የተመለከትን እንደሆን እነዚህ ሊቃውንት ሁሉ ለሀገራችን ታላላቅ ሥራን የሠሩ ፤ ዕውቀትን በነፃ ያካፈሉ ፤ በሀገራችን ታላቅ ዝናን ያተረፉ ናቸው ። ይኸን ሁሉ ሞያና የሀገር ባህል የጠበቁና ያስተላለፉ ፤ ሕዝባችን ሥልጣኔን ይዞ እንዲቆይ በቀላሉም ለመጪው ትውልድ ለማስተላለፍ የቻሉ እነርሱ በአስተማሩት ትምህርት ነው ። ሕዝቡን ሕዝብ አድርገው ፤ ሐሞተ ቈራጥና ደፋር አድርገው ፤ ለነፃነትና ለሃይማኖት ተጋዳይ እንዲሆን የሠሩና የአስተማሩ እነርሱ ናቸው ። ሀገሩን አፍቃሪ ንጉሡን አክባሪ በጠቅላላም የያዘውን ሁሉ ጥቅሙንና ጉዳቱን ዐውቆ እንዲኖር ያደረጉና መምሪያ የሚሰጡ እነርሱ ነበሩ ። ይኸን ሁሉ ለማድረግ የቻሉት ግን የኢትዮጵያ መምህራን መከራ የማያቸንፋቸው ፤ ማግኘትና ማጣት ቢፈራረቃቸው ግምት የማይሰጡት ፤ በረኃብ የማይፈቱ ፤ ማዕርጋቸውን እንጂ ሆዳቸውን የማይወዱ አባቶች ስለነበሩ ነው ። አባቶቻችን ትልቅ ዕውቀት የነበራቸው ናቸው ፤ ስለዚህም ባሕረ ሐሳብን በቀላሉ የሚዋኙ ለጥበብ በቃኝ የማይሉ ነበሩ ፤ እነዚህ መምህራን ሞያችንና ሥልጣኔያችን እንዳይጠፉ በማለት ተርበው ከመማራቸው ይልቅ ተርበው ማስተማራቸው በሰፊው ይነገርላቸዋል ። ግማሾቹ ደግሞ ራሳቸው እያረሱና እየቆፈሩ የሚያስተምሩ ነበሩ ፤ እንዲያውም አንዱን ተማሪ ከምሥራቅ አንዱን ከደቡብ አንዱንና ሁለቱን ከርሻው መካከል እያደረጉ ሲያርሱ በተመላለሱ ቊጥር ያስተምሩ ነበር ። ግማሾቹ ደግሞ እንደ ዕድል ሆኖላቸው በንጉሥ ፤ በመኳንንት ፤ በሴት ወይዛዝርትም እየተደገፉ የሚኖሩና የሚያስተምሩ ነበሩ ። ይኸም ሆነ ወይም ያ መምህራን በማግኘታቸው ወይም በማጣታቸው ቸል ሳይሉ ሲያስተምሩ የቆዩና ሀገራቸውን ከአፍሪካ ለይተው የዕውቀት ምንጭ ፤ የነፃነት መዝገብ አድርገው መቆየታቸው የታወቀ ነው ። ይሁን እንጂ ዛሬ ጠለቅ ብሎ ጥንታዊ ባህላችንን የሚመረምር ባለመኖሩ የሊቃውንቱን የዕውቀታቸውን መጠን የባህላችንን ሁኔታ ያወቀና ለመምህርነታቸውም ግምት ሊሰጣቸው የቻለ የለም ። ዕውቀታችንም ከቀን ወደቀን እያደረ ወደታች ሲሔድ ሲዋረድ ይገኛል ፤ በጥንት ዘመን የሆነ እንደሆነ ግን መምህራኑ በአንድ ዓይነት ዕውቀት ሳይወሰኑ የጠፋውን በመፈለግ የደከመውን በማጽናት ከዕውቀት ወደ ዕውቀት ይራመዱ ነበር ። እንዲያውም

www.ethiopianorthodox.org

አንድ መምህር ከሁለትና ከሦስት ዓይነት ዕውቀት በላይ ስለአለው ያን ሁሉ በሕይወቱ ሳለ ለማካፈል ሲል ለሕይወቱ ሳያስብ ለተማሪ በሚመቸው ሀገር እየዞረ እየተንከራተተ ያስተምር ነበር ፤ ተማሪው ለልመና በጠቅላላም ለሕይወቱ ከተመቸው መምህሩ በቦታ አይወሰንም እንዲሁ እንደዞረ ይኖር ነበር ። ለማስተማር አሁን ፥ በኋላ ፥ ነገ በማለት ጊዜ ሳይወሰን በቀን በሌሊት እያለ ያስተምር ነበር ። የቀረው ቀርቶ በትዳር ያለው አስተማሪ እንኳን ከቤቱ በሌሊት ወጥቶ ሲያስተምር ከቶ ቅር አይለውም ነበር ፤ ቀንም እንዲሁ ሲያስተምር ይውላል ። ይኸም ሆኖ አይደክመውም ነበር ፤ ቤትም ቢኖረው ቅሉ ከተማሪው የሚለየው ነገር ከቶ አልነበረውም ፤ ለዚህም ሁሉ ድካሙ ዋጋ ሆኖ የሚከፍለው ነገር አልነበረውም ። ሕዝብም ቢቀጥረው ቅሉ እርሻ ያርስለት አንድም ከአዝመራ ጥቂት ይሰጠው እንደሆን እንጂ ለኑሮው በቂ የሚሆን ፥ ትዳሩን የሚያቸንፍበት ከፍ ያለ ነገር አይሰጠውም ነበር ። ግን መምህሩ ሁሉንም ሳያስታውሰው በማስተማሩ ብቻ ተደስቶ መንፈሱ ጸንቶ ችግሩን አቸንፎ ይኖራል ፤ የቀረው ቀርቶ በቤቱ ውስጥ እንኳን ልዩ ልዩ ፈተና ቢደርስበት ከቁም ነገር አይቆጥረውም ነበር ። ስለዚህም አስረጂ አንድ ትዳር የያዘ መምህር ሁልጊዜ ለትዳሩ ሳያስብ ሲያስተምር በመዋሉና ሲያስተምር ፤ በማደሩ ሚስቱ ተናዳ ማታ ለራት ሲቀርብ በመሶብ ከድና ድንውን አቀረበችለት ይባላል ፥ ይኸም የሚያመለክት ሥራህ ማስተማር ከሆነ ራትህም እርሱው ይሁን ማለት ነው ። ለመምህራን ከቤት ሳይቀር እስከዚህ የሚደርስ ፈተና ነበረባቸው ፤ የችግራቸውም ዓይነት ብዛት ይኸ ነው አይባልም ነበር ። ብዙ መምህራን በተማሪነት ሳሉ ከተጐዱት ይልቅ በመምህርነታቸው የተጐዱት ይበልጣል ስለዚህም ሕይወታቸው በበሽታ የተሰነካከለ ሆኖ የዕድሜ ልክ በሽታ የያዛቸው ፥ ሲሠቃዩም የኖሩ ብዙ ነበሩ ፤ ከነዚህም ውስጥ ወዲያውም ተቀስፈው የሞቱ ብዙ ናቸው ። በዚህም ሁሉ ምክንያት ብዙ ጥናት ያደረጉ መምህራን በየሀገሩ አይገኙም ፤ በቍጥር ያነሱም ቢገኙ በጣም በተራራቀ ቦታ ነበር ፤ የመምህራን ጠቅላላ ሕይወታቸውን ለማወቅ ስንፈልግ ግን የየአንዳንዱን ትምህርት መምህር ታሪክ መናገር በግድ ያስፈልጋል።

## ፩ኛ የዜማ መምህር ።

የድጓው ትምህርት በገጽ ፸፬—፺፯ እንደተናገርነው ሲሆን በመጠኑም ከዚህ እንደሚከተለው እንገልጣለን ።

### ሀ/ የድጓ መምህር ፤

አንድ ሰው የድጓውን ትምህርት በጀመረ በ፯ ዓመቱ ድጓውን ሊያስመሰክር ይችላል ። ከዚያም ጊዜ ጀምሮ ዕድሜውን በሙሉ ያለምንም ቸልተኝነት ማስተማር አለበት ። እርሱም ሲያስተምር የፊደልን ቅርጽ የጽሕፈትን ዘዴ የቤተ ክርስቲያንን አገልግሎትና ሥርዓት ከዜማው ጋር ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸም ማለት ድጓውን ሲያስተምር ከፊደልና ከንባብ አስጀምሮ ድጓውን እስኪዘልቁ ድረስ እንጂ በድጓ ብቻ አይወሰንም ነበር ። እርሱም ትምህርቱን ወይም ግጼታውን እንዲወጣ ማስተማር ሲጀምር እገሌ ወንበር ዘረጋ ይባላል ። ሲሞት ወይም ሲታመም ወይም በልዩ ልዩ ምክንያት ማስተማሩ ሲቀር ደግሞ የእገሌ ወንበር ታጠፈ ይባላል ። ይኸም የሆነበት ምክንያት ምናልባት በጥንት ዘመን መምህሩ በሚዘረጋና በሚታጠፍ ወንበር ይቀመጥ ኑሮ እንደሆን ፤ ወይም የድጓው መዘርጊያ አትሮንሱ ስለሚታጠፍና ስለሚዘረጋ እንደሆነ አይታወቅም ።

የድጓው መምህር ግብረ ገብነት ፤ ያለው ለብዙ ነገር አብነት የሚሆን ፤ ብዙ ነገር የሚወሰድበት ነበር ። ብዙ ጊዜም ሥልጣነ ክህነትን የሚቀበል ፤ ውዳሴ ማርያም ደጋሚ ፤ የትሩፋት ሁሉ ምሳሌ ስለሆነ ፤ ተማሪዎች ይኸን ሁሉ በመመልከት ይከተሉት ነበር ። የድጓ መምህራን ጉባኤ አድርገው ስብከት አይሰበኩ እንጂ ቤተ ክርስቲያን በማገልገል በማስተማር ሥራቸውን ያከበሩና እነርሱም የተከበሩ ነበሩ ። ድጓን ያህል ከባድ ነገር ዘሩን ከነምልክቱ በቃል ይዘው ሲያስተምሩ መኖር በጣም አስደናቂ ነገር ነው ። ከዚህም በላይ ድጓን ያህል ነገር ከማስተማር ሥራው ጋር በየጊዜው ይጽፋል ፤ ያመለክታል ፥ ግን በሥራው ብዛት በጫጫታው ምክንያት ከቶ አይሳሳትም ፤ ከጻፍኩ ሥራም ከያዝኩ ብሎ ከማስተማሩ ቸል አይልም ወይም ጩኸቱን አይሰለቸውም ነበር ፤ እንዲህም ብሎ ሲሠራ ሲደርቅ ይኖራል ። ከማንኛውም አስተማሪ ይልቅ ድርቀት የሥራም ብዛት በዜማ አስተማሪ ይበልጣል ፥ ግን በየቤተ ክርስቲያኑ በዝተው የሚገኙት በዝተውም የሚያስተምሩት ደግሞ የድጓ መምህራን አንድም የዜማ መምህራን ናቸው ። ከማነኛውም ሞያ መምህር ይልቅ ሥራዓተ ቤተ ክርስቲያንን እንዲሁም የራሳቸውን ሞያ ከነ ይትበሃሉ ጠንቅቀው የሚያውቁና የሚያስተምሩ የዜማ መምህራን ናቸው ።

## ለ/ ጾመ ድጓ ፤

ስለጾመ ድጓ በገጽ ፲፭—፲፯ የተሰጠውን ተመልከት ፤ ሆኖም ጾመ ድጓ ሞያ ሆኖ ለብቻው ወንበር የለውም ፤ ግን አንዳንድ ጾመ ድጓንና ምዕራፍን እናስተምራለን እያሉ ጀማሮችን ከፊደል አንሥተው የሚረዱ አሉ ፤ የማስተማር አቅዳቸው ግን ከላይ እንደገለጥነው እንደሌላው የዜማ መምህር ያለ ነው ።

## ሐ/ ዝማሬና መዋሥዕት ፤

ስለዝማሬ መዋሥዕት በገጽ ፪፪—፪፯ የተገለጠውን ተመልከት እነዚህም ትምህርቶች ትምህርታቸው ወይም ሞያቸው ራሳቸውን የቻሉ የተለየ የምስክር ቤት ያላቸው ሲሆኑ እነዚህን ብቻ ሞያ አድርጎ ለመውጣት ፪ ዓመት ያህል ይወስዳሉ ፤ ብዙ ጊዜም ቅዳሴን አብረው ያስተምሩ ስለነበር እንደዚሁ ቅዳሴ ማስመስከር ነበረባቸው ። እርሱም የሚፈጀው ጊዜ አንድ ዓመት ነው ፤ ስለሆነ በጠቅላላው ፫ ዓመት ያህል መማርና ማስመስከር ነበረባቸው ። እነዚህም መምህራን በቀላሉ በት

www.ethiopianorthodox.org

ንሽ ጊዜ ሊያከናውኑ የሚችሉት ሌላውን ዜማ አጥንተው ምልክት ለይተው የገቡ እንደሆነ ነው ። እነዚህም መምህራን ሞያቸውን ከማስተማራቸው ሌላ ጀማሮችን ሳይቀር ይረዱ ያስተምሩ ነበር ፤ በአሁኑ ጊዜ ግን ቅዳሴን ለይተው መነኮሳቱ በብዛት ስለወሰዱት ትምህርቱም ተለያይቶ የሚሰጥ ሁኗል ። ቅዳሴ የሚያስተምሩ መነኮሳት ያኑ ቅዳሴውን ብቻ ስለሚያውቁ ሌላ ሳይጨምሩ ያስተምራሉ ።

እስከዚህ የተናገርናቸው የዜማ መምህራን የተባሉት ሁሉ ፤ መንፈሳውያን ፥ ግብረ ገብነት ያላቸው ፤ ሕሊናቸው የተሰበረ ፥ በእርግጥም ካህናተ እግዚአብሔር ሊባሉ የሚገባቸው ናቸው ።

## መ/ አቋቋም ፤

ስለ አቋቋም ትምህርት በገጽ ፺፰—፺፰፺ ተመልከት ሁኖም የአቋቋም መምህር ለመሆን ፬ ዓመት ያህል ይጠይቃል ። ብዙ ጊዜ መምህራን የሚገኙት በከተማ በተለይም እንደ ጐንደር ባሉትና በሌሎችም ከተማዎች ስለሆነ የኩራት መንፈስ የሚታይባቸው ሁሉን እናውቃለን የሚመስላቸው ናቸው ፤ እንዲያውም ማኅሌቱ የሚታወከው ደብተራው የሚሸበረው እነርሱ የገቡ እንደሆነ ነው ፤ ስለዚህም ተመልካች ባለቅኔ ከዚህ የሚከተለውን በኀዘን መልክ ተቀኝቷል ።

«አሌ ለክሙ ካህናተ ዜማ ፤ ዘትገብሩ ማኅሌተ በከበሮ ወጸናጽል ።
እስመ ዘኵሉ ዕለት አስበ ማኅሌትክሙ ኮል ።
ለጽድቅ አኮ ዳዕሙ ለኃጕል ።
ወኢኮነ ለበዓል ፤ ዳዕሙ ውእቱ ለአርዮ ሐዳስ ድንግል ።
እመሰ ኢገደፍክሙ አርዑተ ዝንቱ አምሳል ።
ትከውኑ ግዱፋነ ውስተ ታሕቲት ግበ ሲኦል
ወትከውኑ ዳግመ አምሳለ ፈረስ ወበቅል ።
እለ ይትመየጡ ድኅሬሆሙ በልጓም ወበኀሣል » ።

ሆኖም ማኅሌቱ ደግሞ ወገንና ሥርዓት ሊኖረው የሚችለው አቋቋም የሚያውቁ ግብረ ገብነት ያላቸው መምህራን የተገኙ እንደሆነ ነው ።

የአቋቋም መምህራን ብዙ ጊዜ ዜማ ያለዩትን ጀማሪዎችን አያስተምሩም ፤ በገጠር የሚገኙ የአቋቋም መምህራን ግን ጀማሪዎችን ያስተምራሉ ። የዜማ መምህራን ሁሉ ትዕግሥተኞች ሥልጣነ ክህነት ያላቸው ፥ ዓይነ አፋሮች ሲሆኑ ፤ የአቋቋም መምህራን ግን ትዕቢተኞች ፤ ቅሬዎች ፥ የአመንዝርነትም መልክ የሚታይባቸው ናቸው ፤ እንደገናም ከኛ በቀር ማንም አዋቂ የለም ባዮች ነበሩ ፥ ለዚህም አስረጅ የተክሌ አቋቋም ጀማሪ የሆነው አለቃ ተክሌ የተባለው የአለቃ ገብረ ሐና ልጅና ተማሪ ፥ ደብረ ታቦር ኢየሱስ ወጥቶ ማኅሌት እንደተቆመ ከመካከል ገብቶ መበጥበጡ ብቻ ሳይበቃው ፥ የድጓ መምህራኑን ከቁም ነገር ሳይቆጥራቸው ፤ እንዲያውም ሲሰድባቸው «ለድፍን ፋርጣ እኔ ነኝ አክሊሉ» አለ ይባላል ፤ ለድፍን ሲል ለመላው ያለ አስ

www.ethiopianorthodox.org

መስሎ ደንቆሮ ብሎ ሲሰድብ ነው።የአቋቋም መምህራን ብዙዎች ዘንግ መወርወርን፤ጸና ጽል መጸንጸልን ብቻ እንጂ ከጥሬው ዜማ ላይ እምብዛም ናቸው፣ አንዳንዶች ግን ጥሬውንም ዜማ ቢሆን ደኅና አድርገው ከማወቃቸው ጋር ይትበሃሉን ሁሉ ጠንቅቀው ያውቃሉ፤ እንዲያውም የአቋቋም ቍጥሩ ከዜማ ትምህርት ስለሆነ ዋና ባለሞያ ለመሆን አስቀድሞ ከጥሬው ዜማ በኋላ በዘንጉ ቀጥሎም በጸናጽል ያጠናዋል ።

## ፪ኛ የቅኔ መምህራን ።

ስለቅኔ ሞያና ትምህርት በገጽ ፻፵፬—፪፻፲፩ የተገለጠውን ተመልከት፤ መምህራኑና የትምህርት አሰጣጣቸው ግን እንደሚከተለው ነበር ። የቅኔ መምህራን በኢትዮጵያ ላይ በብዛት ይገኙ ነበር ፣ ከእገሌም እገሌ ይበልጣል እየተባለ ይነገርላቸው የነበሩ ብዙ ናቸው ። ትምህርቱም የዕውቀት በር መክፈቻ የአእምሮ መገመቻ የጥበባት ሁሉ መግለጫ ምንጭ የግዕዝ ትምህርት እንደሆነ በማመን ተማሪው በብዛት ወደነርሱ ይጐርፍ ነበር ። ሆኖም ተማሪው እንደፈለገ ትምህርት እንዳይሰጠው መምህራኑ ዕውቀታቸውን የመሸንገል ዘዴ ነበራቸው ፤ ይሁን እንጂ የኑሮ ደረጃቸው ዝቅተኛ ሕይወታቸውም ልክ እንደሌላው መምህራን ነው ፤ ማለት ግማሹ ቤት ንብረት ይዞ እያሳረሰ ሲኖር፣ ግማሹ እንዲሁ በልመና እንጀራ እየኖሩ ያስተማሩ ብዙ ናቸው ። በጠባይ ግን ከዜማው መምህራን የተለየ ጉድለት ይታይባቸው ነበር ፤ ስለዚህም ከትሕትና ይልቅ ኩራት ይታይባቸው የነበር በቅኔ መምህራን ላይ ነው ። እንኳን እነርሱ ተማሪያቸው ሳይቀር ምሥጢር ከለየ ቅኔ ከቆጠረ በኋላ ሰው ለማነጋገር ይቸግረው እንደነበር የታወቀ ነው ፤ ደበሎውን አዙሮ ወደኋላ ይለብስ፤ ራቁቱንም ያሳይ የነበር ደበሎውን ወደፊቱ ከአፍንጫው ላይ ለማድረግ እንዲመቸው ነበር ። መምህራን ለመምህራንም እኔ እበልጥ እኔ እበልጥ በማለት በውድድር መልክ ቅኔ ሲዛረፉ እንዲህ ተባባሉ ይባላል « ማዕበል ቅኔከ ለእመ ገፍዓኒ ። ተንተንኩ ለወዲቅ ወእግዚአብሔር አንሥአኒ » ሲል ለአለቃ ካሣ በመመስከር አለቃ ዱሪ ተቀኙ ይባላል ። አለቃ ካሣም «ዱሪ ዱሪ የቅኔ ፈጣሪ» ብለዋቸዋል ።

እንዲሁም ደግሞ አገባብ ሲጠያየቁ ፈተና ሲፈታተኑ ይኖሩ ነበር ፤ የተለዩ እማኞች ዳኞች እያወጡ ጥያቄ ይጠያየቁ ሊቅነታቸውንም ያጸድቁ ነበር ፤ ለዚህም አስረጂ ፪ የቅኔ መምህራን እኔ እበልጣለሁ እኔ እበልጣለሁ በማለት ባልተማሩ ሰዎች ዳኝነት ቆሙ ፤ አንዱ ጮሌነት የበዛበት ስለነበር፤ አሁን እኔ ስጠይቀው እንደ ዐመሉ ትርጕሙን በመንገር ፈንታ እንጃ ይለኛል እንጂ አይመልስልኝም ልብ አድርጋችሁ ስሙልኝ አላቸው ። ፪ኛውም የባላንጣውን አስረጂ ከሰማ በኋላ እንዴት እኔ መልሱን በትክክል እመልሳለሁ እንጂ እንጃ እላለሁ ብሎ ጥያቄውን ሲጠብቅ ሳለ ጮሌው መምህር ትርጕሙ እንጃ የሚያሰኘውን ግዕዝ « እንዳኢ» ማለት ምን ማለት ነው ሲል ጥያቄውን አቀረበለት ፤ ተጠያቂውም በመቸኮል እንጃ ሲል መለሰለት ፤ ዳኞች ግን የሰጠው መልስ ትርጕም መሆኑን ሳያ

www.ethiopianorthodox.org

ውቁ ለምን እንጃ ትላለህ መልስልን እንጂ ሲሉ አላዋቂነቱን በአደባባይ መሰከሩበ ትና ፈረዱበት ይባላል ። እንኳን የቅኔ መምህራን ተማሪዎች ሳይቀሩ ከየኔታ እገሌ ይልቅ የኔታ እገሌ ይበልጣሉ እያሉ ሲያጣሉ ፤ ሲያወዳድሩ ፤ ሲያፎካክሩ ይኖሩ ነበር ።

የቅኔ መምህራንም ምንም በዕድሜ ሽማግሌዎች እንኳን ቢሆኑ የጠ ባይ ልጅነት ነበረባቸው ፤ ስለዚህ ጠብን በመፈለግ ራሳቸው ሌሎች የቅኔ መምህራን ወደአሉበት እየዞሩ አንዳንድ ጊዜ ተማሪ መስሎ በመቅረብ ፤ አንዳንድ ጊዜም ግልጥ በግልጥ ከመምህሩ ጋር ዘረፋ በመግጠም እንደ በግ አውራ ሲዋጉ ይታዩ ነበር ። የቅኔ መምህራን በዘረፋም ጊዜ ሆነ ወይም በቤተ ክርስቲያን በተ ቀኙ ጊዜ ከምስጋናው ይልቅ የምጸቱን የጐዳናውን መንገድ በመፈለግ እንዳይ መረመር እንዳይገኝ አድርጎ ሰድቦ መቀኘትን ይመርጡ ነበር ። በብዛት ያለውን ተናገርን እንጂ እንዲሁም ደግሞ ብዙ ቅዱሳን መምህራን እንደነበሩ ፤ ዕድሜ ልካ ቸውን በተባሕትዎ እንዳሳለፉ የታወቀ ነው ። የቅኔ ትምህርት መልኩ እንደ ቋንቋ ትምህርት ሲሆን መምህራኑ ግን ቅዱሳን ከመሆናቸው የተነሣ መንፈሳዊ ትምህርት ነው ብለው እንደ መንፈሳዊ ትምህርትም ቈጥረው ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋ እናገኝበታለን በነፍሳችን እንጠቀምበታለን ብለው ተግተው ነቅተው በማስተማራቸው ዕውቀትን እስከ አሁን ለማቆየት ቻሉ ። እንዲሁም ለደቀመዛ ሙርቱ ምሥጢሩን ገልጠው መንገዱን መርተው የሚያሳድጉ እነዚሁ መምህ ራን ነበሩ ። በእርግጥም መጻሕፍት ሁሉ የሚነበቡና የሚተረጐሙም ፤ የምስጋናውና የጸሎቱ ፤ የአገልግሎቱ ሁሉ ስልት የሚታወቀው ቅኔ በመቀኘት ግዕዝን በመማር እንደሆነ የታወቀ ነው ። ምንም ጥሬ ዜማ ቢያውቅ ፤ ምንም አቋቋም ከነባህሉ ቢያጠ ናቅቅ ቅኔ ካልተቀኘ ሰውየው እንደፈራ እንደቀለለ ይኖር ነበር እንጂ በቂ ዕውቀት አለኝ ብሎ በያዘው ትምህርት አይኮራም ነበር ። የቅኔ መምህራን ግን ይኸን ሁሉ በማወቅ ለኢትዮጵያችን ብርሃን ለመስጠት ሕይወታቸውን ሁሉ መሥዋዕት አድር ገው ቆርጠው የተነሡና የሠሩ በመሆናቸው ኢትዮጵያን ለማብራት ችለዋል ።

## ፫ኛ የትርጓሜ መምህራን ።

የትርጓሜ መጻሕፍት መምህራን በቍጥር በጣም ያነሱ የሚገኙባቸውም ቦታዎች የተወሰኑ ስለነበር ደቀ መዛሙርትም በብዛት አይገኙም ነበር ። የትር ጓሜ ትምህርት አድካሚ ስለሆነ ፤ በዕድሜው የበሰለ ምሥጢር ያደላደለ ፥ ትሕት ናንም ገንዘብ ያደረገ ፥ የመናኝነት መልክ የሚታይበት ፥ ልታወቅ ልታይ የማይል ሽማግሌ ሰው ብቻ ቆርጦ ተነሥቶ ይማር ነበር ፤ የመጽሐፍ ተማሪም የሚተረጐ መው መጽሐፍ ራሱ በየጊዜው ስለሚወቅሰው የመጽሐፍ መምህር እንኳን እርሱ ተማሪው ሳይቀር ትዕግሥተኛ ሁሉን አመዛዛኝ ነበር ። ጥበባት ሁሉ ከዚያ ስለሚገኙ ደግሞ አስተዋይም ነበር ፤ የዜማው መምህራን የዜማ ምልክት ስለአላ ቸው የቅኔውም ትምህርት በመጀመሪያ አገባብ ሲማሩ እንጂ በኋላ ችግር አያጋ

www.ethiopianorthodox.org

ጥማቸውም ጽፈው ደጉሰው ይይዙት ነበር ። የመጽሐፍ መምህራን ግን ከዚህ በፊት የተጻፈ የትርጓሜን ስልት የሚያሳይ ስለሌለ በፊት ሲማሩ በኋላም ሲያስተምሩ ትልቅ ችግር ነበረባቸው ፤ ስለዚህም ሁልጊዜ ዓይናቸው መጽሐፍ ከመመልከት ፤ አእምሯቸው ምሥጢር ከማሸራሸት ተለይቶ አያውቅም ነበር ። የትርጓሜ ትምህርት ምልክት ቢኖረው ቅሉ ራሳቸው በመጠኑ ያመልክቱ እንጂ ሙሉ ትርጒም ስላይደለ አማርኛው እንዳይለወጥ ምሥጢሩ እንዳይፋለስ ከፍ ያለ ጥንቃቄ ነበረባቸው ፤ ከእነዚህ መምህራን ውስጥ አብዛኞዎች መጽሐፉ ከሚናገረው ይልቅ አብዝተን እንሠራለን ትሩፋት እናሳያለን በማለት በጥብቅ ስለሚሠሩ ሕይወታቸውን በትምህርት ያሳልፉት ነበር ። ከሁሉ የላቀ ክብር ይሰጣቸው ነበር ፤ ከሁሉም የላቀ አስተያየት ያላቸው በመሆናቸው ሁሉ ያከብራቸው ነበር ። ሌሎችም ሊቃውንት ሁሉ ምንም ሁሉን ቢያውቁት ትንሽም ትልቅም ክርክር በመካከላቸው የተነሣ እንደሆነ ከመጽሐፍ መምህር እንሂድ በማለት የነገሩ ማለቂያ የክርክሩ መብረጃ የሚሆነው የመጽሐፉ መምህር ነበር ። የመጽሐፍ መምህራን ፤ እንኳን እነርሱ ተማሪዎቻቸው ሳይቀሩ የተለየ ክብር ነበራቸው ፤ ስለዚህም ልመና እንኳ እንዳይለምኑ ልዩ ልዩ አስተያየት ይደረግላቸው ፤ መንደር ተለይቶ ይሰጣቸው ፤ ድርጐ ይታዘዝላቸው ነበር ፣ በዚህም መልክ አጥንት የሚሰብረውን ትምህርት ጊዜ ሳይወስኑ እንሾምበታለን ፤ ቀለብም እናገኝበታለን ፤ ሳይሉ ለራሳቸው ዕውቀትና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት እናውለዋለን በማለት ቆርጠው ይማሩት ነበር ። መምህራኑም ከጡዋት እስከ ማታ ጉባኤ ዘርግተው ደቀ መዛሙርት አብዝተው ያስተምሩ ነበር ። የትርጓሜ ትምህርት መቼ እንዴት ወደ ሀገራችን እንደመጣ አይታወቅ እንጂ ሞያው ተከብሮ ከመምህር ወደ መምህር እየተላለፈ ሳያቋርጥ እስከ አሁን ድረስ ይገኛል ። የመጽሐፍ ትምህርትም የተወሰነ የመጨረሻ ጊዜ ነበረው ማለት ጉባኤው የሚዘለቅበት ደቀ መዝሙሩ የሚያጠናቅቅበት ፤ ይሁን እንጂ ምሥጢር አልተከተተልኝም ትርጓሜው አልተሸራሸልኝም በማለት ዕድሜ ልካቸውን በጉባኤ የሚያሳልፉ ነበሩ ።

ምዕራፍ ፱ ።

## የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ።

መምህራን በውድ ያለ ቀለብ በግድም በቀለብ ያስተምሩ እንጂ ሁለቱም ዓይነት የትምህርት አሰጣጣቸው ዘዴ የትምህርቱም ጊዜ አንድ ዓይነት ነበር ፤ ቀለብ ያለውም ተቈጣጣሪ ሳይኖረው ፤ ቀለብ የሌለውም ምን አለብኝ ሳይል በፈቃድ ሰዓቱን አክብሮ ያስተምር ነበር ፤ ዋጋውን ከተማሪው እቀበላለሁ እንዳይል ተማሪው ሲማር ኖሮ ሲሔድ እንኳን ደህና ሁን ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ ሔድኩኝ የሚል ድምፅ ሳያሰማ ጥሎ ይሔድ ነበር ። ከሕዝቡ ዋጋ አገኛለሁ እንዳይል ሕዝቡ ስንት ልጅ አወጣህ ስንት ቀን አስተማርህ የሚል መቈጣጠሪያ ዘዴ

www.ethiopianorthodox.org

አልነበረውም ሆኖም መምህሩ እግዚአብሔርን ታዛቢ አድርጎ የራሱንም ችግር ተመልክቶ ተግቶ ነቅቶ ያስተምር ነበር ። ይኸ አስተያየት ለልዩ ልዩ ትምህርት መምህራን ሲሆን የያንዳንዱን የትምህርት ዓይነት መምህራን የትምህርት ዓይነት አሰጣጥ እንደሚከተለው እንመልከት ።

## ፩ኛ. የዜማ ትምህርት አሰጣጥ ዘዴ ።

የዜማው ትምህርት በሁለት ዓይነት ይከፈላል ፤ ይኸውም ፤

### ሀ) የቃል ትምህርት ፤

ይኸ ትምህርት ስሙ እንደሚያመለክተው ንባቡን ወይም የዳዊቱን መዝሙር ተማሪዎች በቃላቸው ከያዙ በኋላ በማታና በሌሊት ይማሩታል ፤ ለምሳሌ ማታ ከ፩ እስከ ፫ ሰዓት ሲማሩ ያመሻሉ ፤ ሌሊትም እንዲሁ ከንጋቱ ፲ ሰዓት ጀምረው እስከ ፲፪ ሰዓት ከንጋቱ ድረስ መምህራኑ ደከመን ሰለቸን ሳይሉ ያስተምራሉ ፤ አንድ አንድ ጊዜ ተማሪውን እየቀሰቀሱ ያስተምሩ ነበር ።

### ለ) ድጓ ጾመ ድጓ ዝማሬ መዋሥዕት ፤

ቅዳሴ ሌላም ይኸን የመሳሰለውን ሁሉ ወንበር አዘርግተው አንዱን በቀኝ አንዱን በግራ አንዱን በፊት አንዱን በጀርባ አድርገው መምህራኑ አንድ ጊዜ ወደ አንዱ አንድ ጊዜ ወደ ሌላው ፊታቸውን በመመለስ ሲያዳምጡ ሲመልሱ ሲነጋገሩ አንድ ጊዜ እንኳን ሳያርፉ ከጧቱ ፫ ሰዓት የጀመሩ እስከ ፯ ተኩል ይቆያሉ ። ከዚያም ከ፰ ሰዓት ጀምረው እስከ ፲፩ ሰዓት ሲያስተምሩ ይውላሉ ።

### ሐ) አቋቋም ፤

የአቋቋምም ትምህርት በዚሁ መልክ ይሰጣል ፤ ብዙ ጊዜ ጥሬውን ዜማ የሚከተል ስለሆነ ፤ የድጓውን ጊዜ ያመለክታል ፤ መቋሚያውና ጸናጽሉ ግን የቃል ስለሆነ የቃሉን ትምህርት ይከተላል ። የአቋቋም መምህር ጀማሪዎችን የፊደልና የንባብ ተማሪዎችን ሳይቀር እንዲሁ በዙሪያቸው አድርገው ተወራጅ አስተማሪ ለየአንዳንዱ በማድረግ ያስተምራሉ ። የዜማው ተማሪ በዕለቱ ሲማር የዋለው ባለወንበር ይባላል ፤ ሌሎች ተራ ያልደረሳቸው ወይም እርሱን ሲመለከቱ ይውላሉ ወይም የተዋረድ ሲያስተምሩ ይውላሉ ፤ እንደዚህ እያለ ለሁሉ ይዳረሳል ። ተማሪ በብዛት የሚገኝበት በአስተማሪዎችም ችግር የሚፈጥርባቸው በዜማ መምህር ላይ ነበር ። ይሁን እንጂ መምህሩ ደግሞ ተማሪ ስለበዛለት ጉባኤ ስለሰፋለት ደስ ብሎት ያስተምራል እንጂ አይሳቀቅም አይመረርም ነበር ።

## ፪ኛ የቅኔ ትምህርት ።

የቅኔ ትምህርት የሚሰጠው ብዙ ጊዜ ቀንና ማታ ብቻ ነው ፤ አንዳንድ መምህራን ብቻ ሌሊትም የሚያስተምሩ አሉ ፤ ያውም ማታ ግሥ ማውረድ ፤ ቅኔ መዝረፍ ፤ ሞያውን መንገር ሲሆን ሌሊት ተማሪው የሚያጠናበት ትምህር

www.ethiopianorthodox.org

ቱን የሚያሸራሽበት ጊዜ ነው ፤ ቀን ግን ራሱ ቅኔ ሲቆጥር ፤ ራሱን ሲመረምር የሚውልበትና በተወሰነ ሰዓት በግምት ከአምስት ሰዓት ጀምሮ ግን ሲቆጥር የዋለውን የሚነግርበት የነገረውን አሳርሞ የሚያጠናበት ጊዜ ነው ። ይኸንም ሁሉ ሲሠራ መምህሩ ከተማሪው ጋር የሚደክም እንጂ የተለየ ዕረፍት የሚያገኝበት ጊዜ የለውም ። ከዕለታት አንድ ቀን ዘመድ ለመጠየቅ አንድም በልዩ ምክንያት ወንበር ሳይዘረጋ የቀረ እንደሆነ ፤ ከተማሪው ውስጥ ግማሹ ከድቶ ፤ ከትምህርት ቤት ወጥቶ ያገኘዋል ፤ እርሱም ቢበላም ባይበላም ሳይርበው ፤ ክብር አንድም ሀብት ብሎ የያዘው ተማሪን ስለሆነ እንዳይበተንበት ዕረፍት ሳይሻ ፤ ፀጥታ ሳያገኝ እንዲሁ ሕይወቱን ያሳልፋል ። በቅኔ ትምህርት ጀማሪም ቢመጣ አብሮ መድከም አለበት እንጂ የተለየ ርዳታ ለጀማሪው አይሰጠውም ፤ እርግጥ በተዋረድ ዘራፊ እንዳለ አንድም የተለየ ተማሪ እንዲረዳው እንዲያስቀጽለው ይሰጠዋል ።

## ፫ኛ የመጽሐፍ ትምህርት ።

የመጽሐፍ ትምህርት እንደዩንቨርስቲ ትምህርት በንግግር በዲስኩር መልክ አንድ ጊዜ ብቻ ተሰምቶ የሚያዝ እንጂ ቃል በቃል ከላይ እንደቆጠርናቸው ትምህርቶች በልዩ መልክ የሚነገር ትምህርት አይደለም ፤ የጉባኤውም ዓይነት በመጽሐፉ ክፍል ብቻ ሳይሆን በሰዎች ልክ ይወሰናል ። ሁልጊዜ በጧት የማይታጐሉ ጉባኤዎች አሉ ፤ እነዚህም አንዳንድ ጊዜ ደቀ መዛሙርቶች በትምህርት መልክ ይከታተሏቸዋል ። ፪—፫ ጊዜ ስለሚመላለሱ በቶሎ ያስቀሯቸዋል ፤ እንዲህም እያለ በተዘለቀና በተከለሰ ቊጥር ተከታትለው ሊያጠኑ ትርጕሙን ሊያስቀሩ ይችላሉ ። አንዳንዶች ግን በትምህርቱ መልክ የያዙትን ብቻ እየተከታተሉ በቀን እስከ ፫ ጊዜ ከዚያም በላይ እየተሔደላቸው በቀን በቀን አንዳንድ ጉባኤ አጥንተው ለመዋል ይችላሉ ፤ ከዚያም በላይ ሊኬድላቸው ይችላል ፤ እነርሱም ከዚህ በላይ አጥንተው ሊውሉ ይችላሉ ። እንደ ጉባኤው ስፋት መምህሩ ጊዜውን ሊወስን ይችላል ፤ ይኸ ሁሉ የሚሆነው ከ፲፪ ሰዓት ከንጋቱ ጀምሮ እስከ ፯ ሰዓት ከቀኑ ከዚያም ከ፱ ጀምሮ እስከ ፲፩ ሰዓት ከቀኑ ጉባኤውን ዘርግቶ ይውላል ፤ ትምህርቱ ለመምህሩም ለተማሪውም አንድ በመሆኑ በቀን ብቻ ይማራሉ ያስተምራሉ እንጂ በሌሊት ጉባኤ የለም ። ለተማሪዎች የሚኬደው ጉባኤ በጀሮ አንድ ጊዜ ሰምቶ ማስቀረት ከባድ ስለሆነ ፤ በየሰዓቱ ጆሮውን ቀቅሮ ዓይነ ልቡናውን ሰብስቦ መዋል ግድ ይሆንበታል ፤ ለመምህሩ የሚከብደው ለያንዳንዱ ተማሪ እንደጮኸ ለዚያም ሁሉ አማርኛው እንዳይለወጥ ምሥጢሩ እንዳይፋለስ እንደአገኘ እንዳይናገር ከፍ ያለ ጥንቃቄ ማድረጉ ነው ፤ በዚህ መልክ የብሉያትን የሐዲሳትን የሊቃውንትን የመጽሐፈ መነኮሳትን ትርጉም ሲማሩና ሲያስተምሩ ኑረዋል ። ተማሪዎችም በዚህም መልክ ተምረው ምሥጢር አሸራሽተው አብነት ሁነው ወጥተው የሚያስተምሩ ነበሩ ፤ የመጽሐፍ ትምህርትም በዚህ መልክ ሲተላለፍ እስከ አሁን ድረስ ቆይቷል ፤ ግን አንዳንድ ደቀ መዛሙርት ከአ

www.ethiopianorthodox.org

ንድ መምህር ዘንድ በዚህ መልክ ሲቀጽሉ ኑረው ወደሌላው ተዛውረው ያስፋፋሉ አንዳንድ ግን በዚያው በተማሩት ተመርቀው ማስተማር ይጀምራሉ ።

## ምዕራፍ ፫ ።

# መምህራን ይገኙበት የነበረው ቦታ ።

የመጻሕፍት መምህራን በትምህርት ዓይነት የተለያዩ እንደመሆናቸው የሚገኙበት ቦታም እንዲሁ የተለያየ ነበር ፤ ማለት የዜማ መምህራን በተፈለገው ልክ በማንኛውም ቦታ የሚገኙ ሲሆኑ ፤ ከዚያውም ውስጥ የአቋቋም የቅዳሴ የዝ ማሬ መዋሥዕት መምህራን የተፈለገውን ያህል በየቦታው አይገኙም ፤ እነዚህ መምህራን በመጠኑ እየተመረቁ ስለወጡ ይሆን ? ወይም ሞያው ዝቅተኛ ሆኖ ብዙ ተማሪዎች ሳይከታተሉት ቀርተው ይሆን አይታወቅም ፥ እንደተፈለገው የሚገኝ ፤ ብዙውን ጊዜም ተማሪ ሰፍሮባቸው ቤተ ክርስቲያን ከብራባቸው የሚገኙ የድጓና የቅኔ መምህራን ብቻ ነበሩ ፤ ምክንያቱም ተማሪው ሁሉ በመጠኑ ዜማ ማወቅ ስለነበረበት ፤ ወደ ድጓው መምህራንም በብዛት ስለሚጐርፍ ፤ መምህራንም በብዛት ተመርቀው ይወጡና በየደብሩ ቀርቶ በየገጠሩ ስለሚቀጠሩ ፥ በድጓ መም ህራን በኩል ከቶ ችግር አልነበረም ፤ ስለዚህ ለተማሪውም ችግር ሳይፈጥርበት ትምህርቱን በቀላሉ ማከናወን ስለነበረበት ፤ ራሱም የድጓ መምህር ለመሆን ይጣጣር ነበር ። የቅኔም መምህራን እንዲሁ በብዛት በየቦታው ስለሚገኙ ተማሪው ባይበዛም እንኳን በመጠኑ ለራሱ ቅኔ መቀኘት ፤ ግዕዝም ማወቅ ስለነበረበት ፤ መምህራንም በብዛት ተመርቀው ይወጡና በደብሩ ቀርቶ በገጠሩ በብዛት ስለ ሚገኙ ተማሪውም እንዲሁ በየትኛውም ቦታ በብዛት ይገኝ ነበር ። ተማሪውም መምህራኑን እንደልቡ አግኝቶ ከመማሩ የተነሣ ትምህርቱን አከናውኖ ለአስተ ማሪነት በቶሎ ይመረቅ ነበር ፤ በዚህም መልክ የሚመረቁ እንዲሁ በቍጥር ብዙ ነበሩ ። የመጻሕፍት መምህራን ግን ምናልባት ጥንትም በአክሱም በኋላም በላሊ በላ ፤ ቀጥሎም በጐንደር አሁንም በአዲስ አበባና በየጠቅላይ ግዛቱ ከተማዎችና በታላላቅ አድባራት ገዳማት ስመ ጥሩ በሆኑት ቦታዎች እንጂ እንዲሁ በማን ኛውም ቦታ የማይገኙ ነበሩ ። ከዚያውም ውስጥ የብሉያት ትርጓሜ መምህራን እየተቀነሱ ከመሔዳቸው የተነሣ ከነዚህም ከተማዎች በመጠኑ እንጂ በሁሉም የማይ ገኙ ነበሩ ። የሊቃውንትም መምህራን እንዲሁ እያነሱ ከመሔዳቸው የተነሣ በቦታ መወሰኑ ቀርቶ በሰው ብቻ እገሌ አለ እየተባለ ይቈጠሩ ነበር ፤ የመጻሕ ፍተ መነኮሳትም መምህራን እንዲሁ ነበሩ ፤ ማለት በሰው እንጂ በቦታ የማይወ ሰኑ ነበሩ ። የሐዲስ ኪዳን መምህራን ግን አሁንም ቢሆን በየትኛው ቦታ በብዛት የሚገኙ ናቸው ። አሁንም ቢሆን ለማንኛውም ጉባኤ መምህራን አሉበት ተብሎ የሚገመቱ ቦታዎች ፤

www.ethiopianorthodox.org

፩/ በአዲስ አበባ ከተማ

፪/ በሸዋ

ሀ) ደብረ ሊባኖስ
ለ) ዝቋላ
ሐ) አንኮበር
መ) አዲስ ዓለም
ሠ) ሌሎች ልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት

፫/ በወሎ

ሀ) ደሴ
ለ) ላሊበላ
ሐ) ተድባበ ማርያምና
መ) ሌሎች ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት

፬/ ትግሬ

ሀ) አክሱም
ለ) ደብረ ዳሞ
ሐ) መቀሌ
መ) ጭሕ
ሠ) ሌሎች ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት

፭/ ኤርትራ

ሀ) አሥመራ
ለ) ደብረ ቢዘን
ሐ) ደብረ መርቆሬ
መ) ሌሎች ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት

፮/ ቤገምድር

ሀ) ጐንደር
ለ) ደብረ ታቦር
ሐ) መካነ ኢየሱስ
መ) ደረስጌ
ሠ) ዙራንባ
ረ) ሌሎች ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት

www.ethiopianorthodox.org

፯/ <u>ጐጃም</u>

ሀ) ደብረ ማርቆስ
ለ) ሞጣ
ሐ) ድማኅ
መ) መርጡለ ማርያም
ሠ) ኤልያስ
ረ) ልዩ ልዩ አድባራትና ገዳማት

፰/ <u>ሐረር</u>

ሀ) ሐረርጌ
ለ) ሌሎች ልዩ ልዩ ገዳማትና አድባራት

፱/ ሌሎች ጠቅላይ ግዛቶችም እንዲሁ በየዋና ከተማዎችና በየአንዳንድ ገዳማት ሊገኝ ይቻላል ። ይኸውም በአሁኑ ዘመን መምህራኑ የዕለት ፍላጎታቸውን ለማርካት ሲሉ ስለተበተኑ ብቻ ነው ፤ በዚህም ምክንያት አሁን ግን የተፈለገው መምህር ሊገኝ የሚችለው ሆነም ቀረም በአዲስ አበባ ከተማችን ብቻ ነው ። ምክንያቱም ።

፩/ ቀለብ እንደልብ ስለሚገኝ
፪/ በደጅ ጥናት እንደ መጡ በዚሁ ስለሚቀሩ
፫/ በልዩ ትእዛዝ መምህራኑ ስለሚጠሩ ነው ።

ጥንት ግን በነዚህ በዘረዘርናቸው ቦታዎችና ይኸንም በመሰለ ቦታዎች ሁነው ጉባኤያቸውን አስፍተው ደቀ መዛሙርት አብዝተው ያላቸውን ዕውቀት ሲያካፍሉ ይገኙ የነበሩ መምህራን በቍጥር በርከት ያሉ ነበሩ ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፲፩ ።

# የተማሪዎች ሕይወት ።

ምዕራፍ ፩ ።

## የተማሪዎች ታሪክ ።

በሀገራችን ስለትምህርት አሰጣጥና ስለተማሪዎች ሕይወት ጥንታዊ የሆነ ወግና ሥርዓት ነበረው ማለት ትምህርቱም መልክና ልክ የነበረው፤ የሚጀመርበትም ጊዜ የተወሰነ ሲሆን ፤ ትምህርቱንም የሚፈጽምበት ጊዜ እንዲሁ የተወሰነ ጊዜ ነበረው ፤ ይኸም ብቻ ሳይሆን የትምህርቱም ዓይነት የተወሰነ ነበር ፤ ነገር ግን ከዋለ ካደረ ዘንድ ሁሉም ቀለሙን እየለቀቀ መልኩን እየለወጠ በመሔዱ ብዙ ጊዜ ነበር እንጂ ነው የሚባለው እያነሰ ሔዷል ። ትምህርታችንም ልክ መልክ የሌለው መስሎ በመታየቱ ለጠያቂዎች መልስ ለመስጠት ችግር ሆኗል፤ ስለዚህ የተማሪውን የሕይወት ታሪክ ተራ በተራ በነበር መልክ እንደሚከተለው ስንገልጥ ጥንታዊ ባህል የትምህርት ሥነ ሥርዓት የነበረን ሕዝቦች ሆነን በመገኘታችን ኩራት ሊሰማን ይገባል ።

### ፩ኛ ትምህርት የሚጀመርበት ጊዜ ።

ወላጆች ልጅ በወለዱ በ፯ ዓመት ከ፯ ወር ከ፯ ቀን ትምህርት እንዲጀምር ያደርጉ ነበር ፤ ይኸም ሁናቴ በአንድ በኩል ትምህርት እንዲገባው የተደረገው የአምልኮት ነገርን የያዘ ይመስላል ፤ በ፪ኛው በኩል ግን ሕዝባችን ከዛሬ ይልቅ የትምህርት ፍላጎት በይበልጥ በጥንት ጊዜ እንደነበረው ያጠይቃል ። በዚህም ሆነ ወይም በዚያ ትምህርት የሚጀምረው በዚያን ጊዜ በዚህ ዕድሜ በዚህም መልክ ሲሆን ፤ ወጣቱ በ፳ ዓመቱ ትምህርቱን ይፈጽም ነበር ፤ ማለት ዳዊት ደግሞ ሽልማት ማግኘት ነበረበት ። የታወቁ የትምህርት መነሻና መድረሻ የውል ውሳኔ ሁነው የኖሩት እነዚህ ነበሩ ፡ ወጣቱም በተወሰነለት ጊዜ የተወሰነውንም ትምህርት አጠናቆ በመገኘቱ ፩ኛ/ ከወላጅ አባቱና ከእናቱ ፤ ፪ኛ/ ከክርስትና አባቱ ፤ ፫ኛ/ ከአጎቱና ከአክስቱ ዘንድ ልዩ ልዩ ሽልማት ያገኝ ነበር ። ከሽልማቱም በላይ እገሌ ዳዊት ደገመ እየተባለ ቃለ አጋኖ ይደረግለት ምስጋናም ይቀርብለት ነበር ፤ በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ ወደ ከፍተኛ ትምህርት ለመጓዝ መንገዳቸውን ያቀኑ ፤ መንፈሳቸውን ያጸኑ ነበር ። ይኸውም ትምህርት በቤታቸው ሳሉ በአካባቢው በሚገኘው መምህር ፤ ወይም ከቤት ተቀጥሮላቸው ለሚማሩ ወጣቶች ነበር እንጂ ለሁሉ ይኸ ዓይነት ዕድል አይሰጠውም ነበር ። በዚህም ምክንያት ብዙዎች ተማሪዎች አገራቸውን ለቀው ቤታቸውን ጥለው ሩቅ አገር ድረስ ሔደው ስለሚማሩ ይኸ ዕድሜ አይገጥማቸውም ፤ ይኸም ዓይነት ማዕርግ ወይም ሽልማት አይጠብቃቸውም ነበር ። እንዲያውም ብዙ

www.ethiopianorthodox.org

ጊዜ ሊቅም ሁነው የሚገቡት እንዲሁ ቤታቸውን ለቀው ከዘመድ ርቀው የሚማሩት ተማሪዎች ነበሩ ። አንዳንድ ቤተሰብ ይኸን በመመልከት ለልጃቸው ስንቅ እየሰጡ እርቆ ሔዶ እንዲማርላቸው ያደርጉ ነበር ፤ ግን ቀስ በቀስ ተማሪው ከነርሱ ጠፍቶ ያለበትን ቦታ ሰውሮ ጥበብን ሲሸምት አገር ለአገር ሲንከራተት ይኖር ነበር ።

## ፪ኛ የተማሪው ምግብ ።

ተማሪው የላመ የጣመ ነገር ከቶ አያገኝም ነበር ፤ እንዲሁ ውጥንቅጥ የተባለ በቆሎ የሔድን እንደሆነ ጥሬና ብስል ፤ በእንጀራ በኩል የሔድን እንደሆነ ለምለምና የነካካ ፣ ጠቅላላውን የተመለከትን እንደሆን ግን ልዩ ልዩ ነገር ተደባልቆ ይሰጠው የነበረውን ያመለክታል ። የሚለምነውም ቤት ተለይቶ ስለሚሰጠው ባዕዶች ዘመዶች ሆነው እንደ ግብር አድርገው ማታ ማታ ሁልጊዜ ድርሻውን አዘጋጅተው ይሰጡ እንጂ ለሰውነቱ ለጤንነቱ አስበው ተጠንቅቀው የሚያቀዩት ነገር አልነበረም ፣ አንድም ተማሪውን የሚረዳ ሌላ ድርጅት ከቶ አልነበረም ። በተማሪውና በባላገሩ ለማኝ መካከል ደግሞ ከፍ ያለ ልዩነት ነበረው ፣ ማለት የባላገሩን ለማኝ ሕዝቡ ስሙን ለማኝ ይለው ነበር ፤ መለመንም የውርደት ሥራ ሆኖ እገሌ ለማኝ ሆነ የተባለ እንደሆነ ከፍ ያለ ውርደት ይደርስበት ከወገንም መለየት ነበረበት ። ስለዚህ ማንም ሰው ሲለምን ከማይታወቅበት አገር ሔዶ ይለምን ነበር ፤ ስሙ ግን አሁንም ለማኝ ነው ። ተማሪ ግን ተማሪ ቈሚል ተማሪ ይለምናል ይባላል እንጅ ለማኝ አይባልም ነበር ፤ ምክንያቱም ጥበብ ለማፍራት ዕውቀት ለመገብየት የፈቃድ ስደተኛ እንጂ አጥቶ ነጥቶ የተሰደደ አይደለምና ። ተማሪውም ምንም ሩቅ አገር ቢሔድ መንገደኛም ቢሆን ወደማታ ጊዜ እንጂ ቀን አይለምንም ፤ ሲማር ወይም ሲዞር ውሎ እንደሆነ የሚለምነው ማታ ነበር ፤ መንገድም ሔዶ እንደሆነ ከሚያድርበት ቤት ክርስቲያን አካባቢ ይለምን ነበር ፣ በቀን ሲለምን ቢታይ ግን አሁንም እንግዳ እንደሆነና አዲስ ከአገሩ የወጣ እንደሆነ ይታወቃል ሕዝቡም በጣም ያዝንለታል ።

## ፫ኛ ልብሱ ።

ተማሪው ምንም የባለጸጋ ልጅ ቢሆን ወደ ትምህርት ቤት የሚሔደው አገር ጥሎ ኰብሎ ስለሆነ ፤ ልብሱ ደበሎ ነው ፤ አንዳንድ ጋቢ ለብሰው የሚማሩ ይገኛሉ ፣ ግን በጣም ያነሱ ናቸው ፤ እነርሱንም ሕዝቡ ገና አዲስ ጋጠወጥ (አዲስ መጥ) እንደሆኑ ይገምታቸዋል ። እንዲያውም በበለጠ ለማኝ እንጂ ተማሪ አይላቸውም ፤ ስለዚህም ደንበኛውን የተማሪውን ድርሻ ቍራሽ አይሰጣቸውም ፤ በዚህም ምክንያት ተማሪዎች ከሀገራቸው እንደወጡ በቶሎ ደበሎ ማስፋት ግድ ይሆንባቸዋል ። አንዳንድ ከፍተኛ ዕውቀት ያላቸው ተማሪዎች ግን በሞያቸው የታወቁ በዚያው አገር ብዙ ጊዜ የኖሩ እንደሆነ በርኖስ ይለብሳሉ ፣

www.ethiopianorthodox.org

ሰውም የተለያየ አስተያየት ያደርግላቸዋል ፡ ከተማሪዎችም የተለየ ግምት ሰጥቶ ያከብራቸዋል፡ ያለዚያ ግን አሁንም በርኖስ ለብሶ ልመና ወደማይታወቅበት መንደር ቢሔድ ለማኝ ተብሎ ይሰደባል እንጅ ተማሪ የሚለው የለም ። በጥንት ዘመን መማር ክብር ነበር ፤ ልብሱም ደበሎው ጌጥ ነበር ስለዚህ «የርሱ ዳባ ለኔ ይመስለኛል ካባ» ይሉት ነበር ። ተማሪው ከደበሎው ጋር ቀጭን ሱሪ ይታጠቅ ስለነበር ስሙን አሻል ይሉት ነበር ፤ ስለጌጥነቱም ሲመሰክሩ «ለተማሪ ቀጭን ሱሪ» እያሉ ግጥም ይገጥሙለት ነበር ። የተማሪው መለዮ ምልክት ደበሎው ሲሆን ሊቅ ከሆነ በኋላ ግን በርኖስ ፤ ካባ ይደርብ ነበር ፤ ግን እንደዚህም ከሆነ በኋላ ራሱ የሚያስቀጽላቸው ተማሪዎች እየለመኑ ይመግቡት ነበር እንጂ እርሱ ወደ ልመና አይወጣም ነበር ። መለመኛውም እንጀራ መያዣው ኮፊዳ የተባለው ከሰሌን የተሠራ እንጂ ከረጢት ወይም አቁማዳ አይሆንም ነበር ። ለማኞች ግን በማንኛውም መቋጠሪያ ዕቃ ስለሚይዙ ለማኝነታቸውም ሲታወቅ ፤ የተማሪው መታወቂያ ይኸው ነበር ። ተማሪው እንደዚህ ተብሎ የተወሰኑትን ትምህርቶች በዚያው ማጠናቀቅ ስለነበረበት እያንዳንዱን ትምህርት በሚከተሉት ጊዜያቶች አጠናቆ ማወቅ ነበረበት ።

ከፊደል እስከ ዳዊት መድገም በ፩ ዓመቱ የጀመረ እንደሆነ በ፯ ዓመቱ ይፈጸማል ፡ በ፯ ዓመቱ የጀመረ እንደሆነ በ፲ ዓመቱ ይፈጽማል ።

## ፩ኛ የዜማ ትምህርት ።

ከውዳሴ ማርያም እስከ መወድስ ፪ ዓመት ይፈጅበታል ፤ ይኸውም ትጉህ የሆነ እንደሆነ ነው ፤ የምዕራፍ ትምህርት ፪ ዓመት ፤ የጾም ምዕራፍ ትምህርት ፭ ዓመት ይወስድበት ነበር ። የጾመ ድጓ ትምህርት በ፭ ዓመት ውስጥ ደኅና አድርጎ ለማወቅ ይችላል ።

የድጓ ትምህርት በ፫ ዓመት ይዘለቃል ፤ ይኸውም ደኅና አድርጎ ለማወቅ ነው ። ለማስተማር ይቻል ዘንድ ግን አንድም ለማስመስከር ሲፈልግ እንደገና ፩ ዓመት ይጠይቅበታል ፤ ይኸውም ቀደም ብሎ ድጓውን የጻፈ እንደሆን ነው ። ዝማሬና መዋሥዕት ለማወቅ ፪ ዓመት ይጠይቃል ፤ ለማስመስከር ግን ፭ ዓመት ይጠይቅበታል ፤ በድምሩ ፫ ዓመት ይፈጃል ። የቅዳሴ ዜማ ትምህርት ፭ ዓመት ይፈጃል ፤ ደኅና አድርጎ ለማወቅና ለማስተማር ግን እንደገና ዓመት ይጠይቃል በድምሩ ፪ ዓመት ይፈጃል ።

የአቋቋም ትምህርት ፡ ፭ ዓመት ይፈጃል መምህር ለመሆን ሲፈለግ እንደገና ፫ ዓመት ይጠይቃል ፡ ስለዚህ በጠቅላላው ፩ ዓመት ይፈጅበታል ማለት ነው ።

## ፫ኛ የቅኔ ትምህርት ።

ቅኔ ለመቀኘት ፭ ዓመት ይጠይቃል ፤ ደኅና አድርጎ ለማወቅ ግን ፪ ዓመት ይፈጃል ፡ ዘራፊ ለመሆን ደግሞ ፫ ዓመት ይፈጃል ፤ ሙሉ አስተማሪ ለመሆን ከዚህ በላይ ከተጠቀሱት ዓመታት ሌላ ፫ ዓመት ይፈጃል ።

www.ethiopianorthodox.org

ይኸን ግምት የወሰድነው ማንኛውም ተማሪ ችግር ሳያገኘው ዙረትም ሳያበዛ ጠንክሮ የተማረ እንደሆንና ልዩም ስጦታ ያለውን ብቻ በመመልከት እንጂ ከዚህ በላይ ብዙ ዘመን የሚፈጅባቸው፤ሕይወታቸውንም በዚሁ የሚያሳልፉ እንደነበሩ የታወቀ ነው ። እነዚህን ሁሉ በመጠኑ ለማወቅና ራሱን ለመቻል የሚፈጅበት ጠቅላላው ዘመን ፲፬ ዓመት ነው ። ይኸውም በዜማ ትምህርት ራሱን ከቻለና ምልክት ከለየ በኋላ ያለማቋረጥ የተማረ እንደሆን ነው ። ይኸን ዕውቀት በመጠኑ በዚህ መልክ ሸምተው በቶሎ ወደ አገራቸው የሚመለሱ ብዙዎች ነበሩ ፤ ሌሎች ግን የአንድ ትምህርት መምህር ብቻ ሳይሆን የ፪ና የ፫ ዓይነት ትምህርት አስተማሪ ለመሆን ረዘም ያለ እንዲያውም ያልተወሰነ ጊዜ ይወስዳሉ ፣ በዚህም መልክ የተማሪነት መልካቸውን ለውጠው እስኪያረጁ ድረስ እየተማሩ በጣም ከሸመገሉ በኋላ በመምህርነት መልክ ይገለጣሉ ።

ምዕራፍ ፪ ።

## የተማሪዎች ችግር ።

ትምህርት በኢትዮጵያ ይወደድ ፤ ሕዝቡም ትምህርት ቤት በኅብረት ይሠራ ፤ አስተማሪም ይቀጠር እንጂ በተማሪዎች ላይ ስሙና ዓይነቱ ብዙ የሆነ ችግር ነበረባቸው ፣ ለምሳሌ ያህልም እንደሚከተለው በመጠኑ እንገልጣለን ።

### ፩ኛ ከወላጆች ዘንድ የሚደርሰው ችግር ።

ይኸውም ወላዶች የልጃቸውን መማር በጣም ሲወዱ በዚያን ጊዜ የነበረው የትምህርት ቤት ሁሉ ሩቅ ስለሆነ ፤ ልጃችን ይጠፋብናል ፤ እንደወጣም ይቀርብናል በማለት በመፍራት ልጃቸውን እንዳይማር የሚከለክሉ ጥቂቶች አልነበሩም ። በእርግጥም ልጃቸው ሊማር እንደወጣ ሙቶ አንድም መንኖ የሚቀርባቸው ብዙዎች ናቸው ። ተማሪውም በሞተ ጊዜ ዘመዶች ሳያውቁት ከቀብሩም ሳይደርሱ ምን እንደ ሆነ ሳያውቁ ከነገ ዛሬ ተምሮ ይመጣል እያሉ በተስፋ ይጠብቁ ነበር ፤ በዚህም ዓይነት ወላጆቹ አልቀው ወንድሞቹና እኅቶቹ እስኪያረጁ ወሬው ተረስቶ የሚቀር አለ ፤ ፈጽሞም እስከ ልጅ ልጅ ድረስ ወሬው ጠፍቶ የሚቀር አለ ። ለዚህም አስረጅ የሚሆን ተማሪ በሞተ ጊዜ ግጥም ሲገጥም ። « ተማሪ በሞተ በ፺ ዓመቱ ተምሮ ይመጣል ትላለች እናቱ » ተብሏል ። ስለዚህም ይኸን በመፍራት ወላጆች ልጆቻቸው እንዳይማሩ ያደርጉ ነበር ፤ የቀረው ቀርቶ ደጅም እንዲወጡባቸው ፈጽሞ አይፈቅዱም ነበር ። ልጅ ደግሞ እንደምንም ብሎ ጠፍቶ ወይም አምልጦ ሔዶ መማር ግድ ስለነበረበት በዚያን ጊዜ የነበረው የተማሪው የመንፈስ ውጊያ ቀላል አልነበረም ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ ወላጆች ለራሳቸው ጥቅም ሲሉ ።

ወላጆች ልጆቻቸውን ትምህርት ይከለክሉ ነበር ፤ ወላጆች ልጃቸውን ከብት ይጠብቁልናል አዝመራ ይከባከቡልናል በማለት የትምህርቱን ጥቅም እያወቁ ለዕድላቸው አርቀው ያልተመለከቱ እንዲሁ ልጆቻቸውን ከትምህርት ይከለክሉ ነበር ። ስለዚህም ተማሪዎች በበኩላቸው አምልጠ ለመሔድ የነበራቸው ችግር ከባድ ነበር ፤ ወይም አምልጠው ከሔዱ በኋላም ይመጡና ይወስዱናል የሚል ችግር ነበረባቸው ።

## ፫ኛ ፈሪ ይሆንብናል በማለት ።

ወላጆች ልጃቸው ወኔ ያጣብናል ፈሪ ይሆንብናል እያሉ ትምህርት የሚከለክሉ ነበሩ ፣ በእርግጥም ተማሪ ይፈራል ይባላል ፣ ምክንያቱም ሲጠየቅ ተማሪው የሚፈራው ሞተ ነፍሱን ስለዐወቀ ነው ተብሏል ። ስለፍርሃቱም ግጥም ሲገጠም ፡-

«የተማሪ ወዳጅ ቢቀር ምናባቱ ፤ ጐራዴ ሲመዙ ይላል በአዛኙቱ» ይባላል ። ኢትዮጵያውያን የኀበዝ ወኔ ስለነበራቸው ፈሪ ሰው አይወዱም ነበር ፤ በዚህም ምክንያት የተማረውን ሰው እንደፈሪ ይቆጥሩት ነበር ፤ ስለዚህ ልጆቻቸው እንዲማሩ አይፈቅዱም ነበር ። ተማሪውም በዚህ መልክ እንዳይማር ከቤቱም እንዳይወጣ ሲታሠርና ቤት ለቤት እንዲኖር ያደረጉት ነበር ፤ ነገር ግን እንደማንም ብሎ ከቤቱ ወጥቶ አምልጦ ጠፍቶ ወደ ትምህርት ቤት መሔድ ግድ ስለነበረበት በዚያን ጊዜ ታላቅ የመንፈስ ውጊያ ፤ ችግርም ነበረበት ። ዘመዶችም እርሱን ለመፈለግ ሲሔዱ እንዳያገኙት ከዚህ አገር ገቡ ሲሉት ወደሌላው አገር በመሔድ ፤ ሲዘዋወር ይኖራል ። አንዳንድ ተማሪዎችም በዚሁ ምክንያት እንዲሁ እንደዞሩ እግረ ተማሪ ብቻ ሁነው የሚቀሩ ነበሩ ። ተማሪውም ስሙን እንኳን በየጊዜው ሲለዋውጥ የሚኖረው በዚህ ፍራቻ ማንነቱ እንዳይታወቅ ማድረጉ የታመነ እውነት ነው ።

## ፬ኛ ተማሪዎችን የሚያሰቅቅ ነገር ስለነበር ።

ወላጆች ልጆቻቸው እንዲማሩላቸው ሲጥሩ ልጆች ደግሞ የማይፈቅዱ ነበሩ ፤ በግድም ወደ ትምህርት ቤት ወላጆች ሲያስገቡአቸው ቀለብም ሲጭኑላቸው እንዲሁ ዕድሜያቸውን በከንቱ ሳይማሩ የሚፈጁ ነበሩ ፣ ምክንያቱም ከትምህርት ወደኋላ የሚያስቀሯቸውና ካህን እንዳይሆኑ የሚያሳፍሩ ነገሮች ፩ኛ/ ከላይ የጠቀስናቸው ሲሆኑ ፤ ፪ኛው ደግሞ ተማሪውን ወይም ካህኑን ዕጣን ጠባሽ እያሉ በዚያን ጊዜ ይሰድቡት ስለነበር ልጁ ይህን ስም ሁልጊዜ በመስማቱ እንዳይሰደብ ሊማር አይፈቅድም ።

## ፭ኛ የረኃቡና የጥሙ ብዛት ።

ደኃም ባለጸጋም ብትሆን እናት ለልጅዋ የምትሰጠው ክቶ አታጣም ፤ ልጅም በቤተ ዘመዱ ዘንድ የተከበረ ሲሆን ወደ ትምህርት ቤት ከሔደ ጀምሮ ግን እየለመነ መብላት ግድ ስለሚሆንበት ደረቁ እንጀራ ያንቀዋል ፣ ዘመድ ይናፍቀዋል ፤

www.ethiopianorthodox.org

ብዙም ቅር ይለዋል ። ስለዚህ ተማሪው በጣም ይቸገር ነበር ፤ በተለይም ሁልጊዜ ከውሻ ጋር መታገል ስለነበረበት ውሻው ግቢውን ለማስከበር እንግዳ ሰው እንዳ ይዞር በግድ መጮኽ መናከስም ነበረበት ፤ ተማሪው ደግሞ ቍራሽ እንጀራን በመ ፈለግ ቤት ለቤት መዞር መለመን ግድ ነበረበት ፤ ስለዚህ በተማሪውና በውሻው መካከል የነበረው ጥል በጣም የከረረና አሠቃቂም ነበር ። ውሻው ከመናከሱና ከች ግሩ ብዛት የተነሣ ተማሪው በእንጕርጕሮ መልክ ሲገጥም « እናቴ ባየሽ እኅቴ ባየሽ ፤ በቍራሽ እንጀራ ሲያባርረኝ ውሻ » ሲል ገጥሟል ። ተማሪው እንደዚህም ዞሮ ለምኖ ገና ሳይቃናለት ችግሩም ሳይወገድለት ይኖር ነበር ፤ ተማሪው ስለችግሩ ብዛት ቅኔ ሲቀኝ ፤ «ረኃብሂ ገጸ ወጨፎ በገባ ጊዜ ከአንጀቴ ፤ ንዑ ከዳናትየ እናቴ ወአባቴ » ብሏል ፤ ጸዋትወ መከራው ብዙ ፤ ዓይነቱ የተለያየ ሁኖ ስለሚጨነቅ በፈ ቃዱ አባቱንና እናቱን በጠቅላላም ዘመዶቹን ሁሉ ጥሎ ከሔደ በኋላ በልዩ ልዩ አጋ ጣሚ ማንሣት ችግሩንም መግለጥ ግድ ይሆንበታል ። ከችግሩ ብዛት የተነሣ ተማሪ ውን ዳፍንት የተባለ የዓይን በሽታ ይይዘው ነበር ፤ ይኸም በሽታ የታወቀው የተ ማሪ በሽታ በመባል ነበር ፤ ሕመሙ የሚነሣው ከችግር ብዛት ከሰውነት ጕዳት ፤ የላ መና የጣመ ካለመቅመስ የተነሣ እንደሆነ ይታወቃል ። ተማሪውን ይኸ በሽታ ከያ ዘው በኋላ ጀንበር ከገባች ጊዜ ጀምሮ በመሪ እንደሆነ እንጂ በእግሩ ሊራመድ ከቶ አይችልም ፤ ስለዚህ በሔደበት ማደር ግድ ነበረበት ፤ እንደዚህም እየሆነ አንድ ቀን ጠሙን ሲያድር አንድ ቀንም ሲቀምስ ተስፋ ሳይቆርጥ ይማር ነበር ። ግን ትምህርቱን አያቋርጥ እንጂ የኀዘን ድምፅን ማሰማቱ አይቀርም ፤ በተለይም ልመና ሔዶ ባዶውን ኮፋዳ ይዞ ሲመለስ እንዲህ ይል ነበር « ከአባቴም ከናቴም ከእኅቶ ቼም መርዶ ፤ እጅግ ያሳዝናል የኮፋዳ ባዶ »

## ፮ኛ እርስ በርስ በመጣላት ።

ተማሪ ለተማሪ ሲገናኝ መደባደብ በጨቤም መዋጋት ነበረበት ። ዋናው የጥሉ ምክንያት ግን ይኸው የቁራሽ እንጀራ እንደነበር የታወቀ ነው ፤ ማለት አንዱ የአ ንዱን ድርሻ ወይም ሰበካ ሲለምን የአገኘው እንደሆን በከፍተኛ ደረጃ ጥልን ያበ ቅሉ ነበር ። እንዲሁም በትምህርት ምክንያት በመናናቅ የኔ መምህር ይበልጣል የኔ ይበልጣል በማለት ተማሪ ለተማሪ ይጣላ ነበር ። ይኸውም «ይብራና ይብራ ተጣሉ በሰው ሽንብራ » ፤ እንደተባለው በማያገባቸው ጉዳይ በሰው ቤት እንጀራ እየገቡ መጣለት ነው ። በዚህም ምክንያት የሞቱ አካላቸውንም ያጡ ብዙዎች ናቸው ፤ ይኸም የተማሪ አንደኛው ችግር ነበር ።

## ፯ኛ የትምህርቱ አሰጣጥ ።

ተማሪው አገሩን ዘመዶቹን ጥሎ የዕውቀትም ስደተኛ ሆኖ ሲኖር ትም ህርት ግን እንደ ልቡ አያገኝም ነበር ፤ ይኸውም የሚሆንበት ወንበር ይበ

www.ethiopianorthodox.org

ዛና ተራ በመጠበቅ ብዙ ጊዜ ያጠፉ ነበር ። ምክንያቱም ዝነኛ የሆኑትን አስ ተማሪዎች ተማሪ በብዛት ስለሚከባቸው ወንበር ለመዘርጋት ተራ ለማግኘት በቶሎ አይችልም ነበርና ። ስለዚህ ያሰበውን ያህል ትምህርቱን በጊዜው ሊያ ጠናቅቀው አይችልም ፤ ብዙ ጊዜ መፍጀትም ዘመን መቍጠርም በግድ ነበረ በት ፤ በዚህም ምክንያት ከእገሌ እገሌ ይሻል ይሆን በማለት ተማሪው ከሀገር ወደሀገር በመዘዋወር ይኖር ነበር ፤ እግረ ተማሪም ሆኖ እንዲቀር ከሚያደር ጉት ምክንያቶች አንደኛው ይኸ ነበር ። ወይም ከመዞሩ የተነሣ በሽታ ሰርቆ ይሞታል ፤ ወይም ዕድሜውን ልክ በሽተኛ ሆኖ ይቀራል ። ከዚህም በስተቀር አስተማሪው ትምህርት በመሸለጉ ፤ አንዳንድ አስተማሪዎች ለተማሪ ጥበብ በመሠ ወር ፣ ትምህርት ባለማስተማር ተማሪውን ያጉላሉት ያስቸግሩትም ነበር ፣ እንዲያ ውም ጥያቄ ሲያቀርብላቸው ምሥጢር እንዳያደላድል በዕውቀትም እንዳይበስል እየተመቀኙ ስትደርስበት ታገኘዋለህ የሚል መልስ ይሰጡት ነበር ፤ እንጂ ቀጥ ተኛ መልስ አይመልሱላቸውም ነበር ። አንዳንዶች መምህራንም አፍ አውጥተው እኛ ስንት ዘመን የደከምንበትን በአንድ ቀን ነጥቀህ ልትሄድ ነው እያሉ በቁጣ ቃል ይናገሩ ተማሪውንም ያጉላሉትና ያስቸግሩት ነበር ፤ ስለዚህም ለተማሪው ችግር ተጨማሪ ይሆኑበት ነበር ማለት ነው ።

በተማሪው ላይ ይኸንንና ይኸን የመሳሰሉ ሌሎችም ችግሮች ነበሩበት ፤ ግን ግማሹ ይኸን ሁሉ ችግር አመለጥኩ መስሎት አገር ለአገር ሲዞር ሲንከራተ ትም ከላይ እንደገለጥነው እግረ ተማሪ ሆኖ የቀረ ብዙ ነው ። አንዳንዱ ግን ጥራዝ ነጠቅ እየሆነ ጥልቅ ዕውቀት ሳይኖረው ከዚያም ከዚህም ነጥቆና ጀሮ ጠገብ በመ ሆን ብቻ እንዲሁ አፈ ተማሪ ሆኖ የቀረ አለ ። አንዳንዱ ግን ይኸን ሁሉ ችግር በትዕግሥት አቸንፎ ልበ ተማሪ ሆኖ ከፍ ያለ ሞያ ይዞ ከፍ ያለ ማዕረግ ያገኘ አለ ። ከዚህ የበለጠው ግን እንዲሁ በከንቱ ሕይወቱን ያጣው አካሉ የጐደለው ጨርሶም ሞቶ የቀረው ብዙ ነው ።

ይኸ ከዚህ በላይ ከተዘረዘረው መከራ ግማሹ በሌሎች ሲደርስባቸው ያየ ሁት ሲሆን ግማሹ ግን በኔ በራሴም ላይ የደረሰ ያየሁትም ዕውነት ነገር ነው ፤ ሆኖም ሞያ ለመያዝ እንደዚህ ሆኖ መማር ግዴታ ነበር ። ሊቃውንት የሚባሉ ትም ይኸን ሁሉ ጸዋትወ መከራ በትዕግሥት አሳልፈው ዕውቀትን በየዓይነቱ ገብ ይተው በመገኘታቸው ነው ፤ ጥንታውያን ተማሪዎች እንዲህ ብለው ሲማሩ ፤ መከ ራም ሲገጥማቸው በችግር ሳይፈቱ ፤ ለጥናታቸው ዘመን ሳይወሰኑ ዕድሜ ልካቸ ውን ለመማር ስለቆረጡ ዕውቀታቸው በጣም ጥልቅ የሆነ ነበር እንዲያውም ከእ ገሌ ይልቅ እገሌ ያውቃል እገሌም ይበልጣል ። እያለ ሕዝቡ ያወዳድር ስለነበር በሕዝብ ዘንድም ታላቅ ሚዛን የዕውቀት መገመቻ ስለነበር ሊቃውንቱ ዝናን ለማ ትረፍ ከፍ ያለ ውድድር ያሳዩ ነበር ፤ ችግሩን ቅሉ ያስረሳቸው የነበር ይኸ ዓይ ነቱ ውድድር ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፫ ።

# የተማሪዎች ዘዴኛነት

በጥንት ዘመን ይማሩ የነበሩት ሰዎች ጥቂቶች በመሆናቸው እነርሱ ብቻ ዐዋቂዎች ፤ እነርሱም ብቻ ዘዴኛዎች እየተባሉ ይነገርላቸው ይከበሩም ነበር ፤ ግን አሁንም ቢሆን ዘዴኛ የሚሆኑ የነገሩን መውጫውንና መግቢያውን የሚያውቁ የተማሩ ብቻ እንደሆኑ የታወቀ ነው ። በቀድሞ ጊዜ ግን በእውር ዘንድ አንድ ዓይና ብርቅ ነው እንደተባለው ሁሉ ባልተማረው ሕዝብ መካከል ብርቅና ድንቅ ሆኖ የሚታየው የሚነገረውም የተማሪዎች ጮሌነትና ዘዴኛነት ብቻ ነበር ።

የዕረፍት ጊዜ ማሳለፊያ የተማሪዎች ቀልድ ነበር ፤ ተረቱም ምሳሌውም የሚነገረው ስለተማሪዎች ብቻ ነበር ፤ አንዳንዱን ራሱ ሕዝቡ የፈጠረው ሳይሆን አይቀርም ፤ አንዳንዱ ግን በእርግጥም የሆነና የተሠራ ነው ፤ ምክንያቱም ተማሪው ብዙ ነገር ስለሚማር ሁሉን ነገር እንደ ቀላል አድርጐ ይመለከተውና በሕዝ ቡም ላይ ይቀልድ ስለነበር ነው ።

## ሀ/ በዐዋቂነቱ ፤

ተማሪዎች በጥንት ዘመን ዐዋቂዎች ተብለው ይገመቱ ስለነበር ዓውደ ነገሥት ይገልጡልናል ፤ ዕድላችንን ይነግሩናል በማለት እንዲጠነቁሉላቸው ሰዎች ወደነርሱ በብዛት ይጐርፉ ነበር ። ተማሪዎችን ግን አለማወቃቸውን እያወቁ ለእ ንጀራ ማግኛ ብቻ ዘዴ ብለውም የያዙት ስለሆነ የጠየቋቸውን ሁሉ ያወቁ መስ ለው ይነግሩ ይሠሩም ነበር ።

## ለ/ በመድኃኒት በኩል ፤

ተማሪዎች ዕፀዋትን ስማቸውን ከነተግባራቸው ያውቃሉና ያበጠውን አፍርጠው ፤ የጐረበውን ልጠው ፤ ሥር ምሰው ፤ ቅጠል በጥሰው ያድኑናል በማለት የሚጠብቁ ነበሩ ። ተማሪዎችም ከዕፀዋቱ ቅመም በላይ ቀይ ወረቀት ነጭ ወረ ቀት በማለት የሐሰት ድግምት እየሰጡ ሕዝቡን ይገዙት ነበር ፤ እንዲያውም የሰው ልጅ ሁሉ በሕይወቱ ሳለ ብቻ ሳይሆን በጊዜ ሞቱም አብሮት የሚቀ በር ልፋፈ ጽድቅ የሚባል ጽሑፍ በአንገትህ እሠር ትድናለህ እያሉ እየጻፉ ይሸጡ ስለነበር ሕዝቡ በውድም በግድም ያንኑ ገዝቶ ያሥር ነበር ፤ በዚ ህም ሁሉ ምክንያት ተማሪዎች ብዙ ገቢ ያስገቡ ነበር ። በጠቅላላ በዚህ መን ገድ የሆነውን ያልሆነውን እየሠሩ ለሌላውም ተማሪ እያስተማሩ በመስደዳቸው አንዳንዱ ትምህርቱን ትቶ በምትሐቱ አምኖበት ጊዜውን በጥንቆላና ሥር በመ ማስ ቅጠልም በመበጠስ ያሳልፈው ነበር ። በዚህም መልክ የሐሰቱ ወይም የምት ሐቱ ሥራ እየተስፋፋ እስካሁን ድረስ ይገኛል ግን «የማያድን ጠንቋይ መድኃኒቱ

www.ethiopianorthodox.org

ለዋይ» እንደተባለው ሁሉ ድግምቱ እንኳን ሌላውን ሊያድን ራሱንም ሳያድን ኑሮው ሳይሻሻል እንዲኖር ያደርገዋል ።

## ሐ/ በቀልድ በኩል ፤

ተማሪ ከጮሌነቱ የተነሣ ታላላቅ ቁም ነገር ይነገርለታል ፤ በእርግጥ አድራጐት ይሆናል ፤ ወይም ፈጥሮ አውርቶ ይሆናል ፤ ወይም ሕዝቡ እየፈጠረ ጮሌነቱን ስላወቀ የተናገረው ይሆናል ፤ በተማሪ ላይ አንዳንዱም ብዙ ጸያፍ የሆነ አንዳንዱም ተረት ለበስ ቁም ነገር ይነገርለታል ፤ ሕዝቡ ግን ለጊዜ ማሳ ለፊያ ለማለት ሁሉንም ዓይነት ጸያፉንም ሳይጠብቅ ያወራል ፤ ከዚህ ላይ ግን ለምሳሌ ያህል በቀልድ መልክ የሚወራለትን የተማሪውን ጮሌነት አስረጅ የሚ ሆን እገልጣለሁ ። ከዕለታት በአንደኛው ቀን ተማሪው ራቅ ወደአለ ቦታ አገር ሔዶ እንደልማዱ ቊራሽ ሲለምን ሴትዮዋ ቊራሹን ልትሰጥ ይዛ ወጣች ተማሪው የተንከላተመ በመሆኑ አሳዝኗት ቆም ብላ ተሜ አገርህ ወዴት ነው ? አለችው ። እርሱም በተለምዶ ጮሌነቱ ትክክለኛውን ነገር ሳይናገር ከእንማይ አላት እርሷም ቸኩላ ከሰማይ አለችው ። አዎ እሜቴ ሲል መለሰላት እርሷም ገርነት ያጠቃት ስለነበረች አባባና እማማ ደኅና ናቸውን አለችው ። እርሱም ከውሉ እንደገባችለት አየና ነገሩን በማጤን እውነተኛ መስሎ እንዲህ ሲል ይመልስለታል ፤ አባትዎና እናትዎ በጤና በኩል በጣም ደኅና ናቸው ፤ ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ የሚለብሱት ልብሳቸው ስለአለቀባቸው ተቸግረዋል ፤ አንዳንድ ጊዜም በዚሁ ምክንያት ከቤተ ክርስቲያን ይቀራሉ አላት ። በዚያን ጊዜ ወይም ዛሬ ቢሆን በባ ላገሩ ጥሩ ልማድ አለ ፤ ይኸውም የቤተ ክርስቲያን መሳምያ የወንዱም የሴቱም የተለየ የማዕርግ ልብስ እንዳለው ነው ። ዛሬ ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲገባ ፎጣተጠ ምጥሞ ብርድ ልብስ ተለብሶ በድፍረት ይገባል ። ሴትዮዋ በዚህ ጊዜ ደነገጠችና አሁን ልብሱን ብሰጥህ ታደርስልኛለህ አለችው ፤ እርሱም ሳያስበው ሙሉ ልብስ ሊያገኝ መሆኑን ተረድቶ በደንብ ነዋ እሜቴ አላት ፤ እንግዲያውስ አሥሬ እስካመጣልህ ድረስ ከዚህ ቆየኝ ብላ ወደ ጓዳዋ ገባችና ለአባቷ የባሏን ሙሉ ልብስ ለእናቷም የርሷን ሙሉ ልብስ አሥራ አደራህን አድርስልኝ ሰላምታም ንገርልኝ ብላ ሰጠ ችው ። እርሱም እጅ ነሥቶ ተቀብሎ ትንሽ እልፍ እንዳለ የሴትዮዋ ባል ከሥራ ውሎ ገባ ፤ ሴትዋም ለባሏ እኽል ውኃ ላቅርብለት ሳትል የምሥራች የአባባንና የእ ማማን ወሬ አገኘሁ በጣም ደኅና ናቸው ። ነገር ግን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሲሔዱ የሚለብሱት አልቆባቸው ተቸግረዋል ስለአሉኝ የአንተን ሙሉ ልብስ ለአባባ የኔን ሙሉ ልብስ ለእማማ ሰጥቼ ሰደድኩት በጣም ደስ ብሎኛል ስትል የርሷን ደስታ ፤ የባሏን ግን መርዶ አቆየችው ። ባልየውም እውነት ነው ሰው ከፈረሰ ከበ ሰበሰ በኋላ ቤተ ክርስቲያን ይሄዳል ፤ ልብስ ያልቅበታል ትይኛለሽ ቤቴን አስዘር ፈሽኛል ልብሴን ገፈሽኛል በማለት እየተበሳጨ ደግሞስ ምን ጊዜ ነው መጥቶ የወሰደው አላት ፤ አንተ ልትመጣ ትንሽ ሲቀር ነው ፤ እንዲያውም የሔደው በዚህ

www.ethiopianorthodox.org

መንገድ ነው ብላ አመለከተችው ፤ እርሱም ተናዷልና በእግሬ ብሄድ አልደርስበትም በማለት ፈረሱን ጭኖ ሩጫውን ቀጠለ ። ጮሌው ተማሪ ግን የልብሱን ባለቤት በፈረስ መከተሉን አርቆ ተመለከተና ደበሎውን ገልብጦ ለብሶ የያዘውን ልብስ ከቁጥቋጦ ደብቆ ከአንድ ቁልቁለት አፋፍ ላይ ወደታች መሄዱን ትቶ ወደ አቀበቱ ሲወጣ ከባለቤቱ ጋር ተገናኙ ፣ ባለቤቱም ቸኩለና አንተ ተማሪ እንደምን አለህ አንድ ልብስ የተሸከመ ሰው በዚህ ሲሄድ አላየኸም አለው ፤ እርሱም አሁን ለትንሽ ይኸችን ቁልቁለት ወረደ አለው ፣ አሁን እደርስበት ይመስልኻል አለው እርሱም ኧረ ቅርብ ነው ፤ ነገር ግን ገደሉና ቁልቁለቱ ለፈረስ አይመችምና እስኪያዘግሙ እንዳይቸገሩ እንጅ በእግርዎ ቢሆን ይደርሱበት ነበር አለው ። እንግዲያውስ ወረታህን ስመለስ እከፍላለሁና ይኽን ፈረስ ይዘኽ ቆየኝ አለው ! እርሱም የዕቃው መጫኛ የሚሆን ፈረስ ስለአገኘ ደስ ብሎት እሺ ጌታዬ ይዤ እቆያለሁ አለው ፤ ስምህ ማን ይባላል ሲል ባለቤቱ ስሙን ጠየቀው ፤ ተማሪውም የአሁኑ ይባስ እባላለሁ አለው ። በል እንካ ያዝልኝ እንዳገኘሁት በቶሎ እመለሳለሁ ሲል ፈረሱን ሰጥቶ በእግሩ መንገዱን ቀጠለ ፣ ተማሪው ደግሞ ልብሱን ከአስቀመጠበት ቁጥቋጦ ያወጣና ፈረሱን ጋልቦ መንገዱን ለውጦ አመለጠ ። ባለቤቱ የተባለውን ሰውየ አጣና ፈረሱን ወደያዘለት ሰው ቢሄድ እርሱንም አጣው ። የአሁኑ ይባስ እያለም ቢጣራ የውኃ ሽታ ሆነ ፤ ተማሪው ግን ሁለቱንም ሰዎች ማለት ገሩንም ጮሌውንም አታሎ አገሩን ገባ ይባላል ። ያ ሰው ግን እያዘነ እየተከዘ ወደቤቱ ተመለሰ ፤ ነገር ግን ሚስቱ እንድታውቅበት ስለአልፈለገ ከደጅ ሲደርስ አሳቡን ለውጦ ሰማሽ ወይ እኅቴ ያ የአልሽው ነገር እውነት ሆኖ አገኘሁትና ለዕቃ መጫኛ እንዲሆናቸው ፈረሱን ሰጥቼ መጣሁኝ አላት ።

ይኽን የመሰሉ ተረቶች ስለ ተማሪው ይነገራሉ ፤ ይኸም ሁሉ የሚተረክለት ተማሪው ጮሌነት ያበዛ ዘዴኛነትን ገንዘቡ ያደረገ ስለነበር ነው ።

## ምዕራፍ ፬ ።

# የተማሪና የሕዝብ ግንኙነት ።

## ፩ኛ ተማሪ ።

ተማሪው ቤተ ሰቡንና ወገኑን ጥሎ ፤ ቆዳውን ጠቅልሎ ፤ ቅሉን አንጠልጥሎ ወደባዕድ ሀገር ይሰደድ እንጂ በሚኖርበት አገር ሁሉ እንግዳ ሳይሆን ፤ ማኅበራዊ ኑሮን መሥርቶ ፤ አዲስ እቅድ አውጥቶ ለሕዝቡ ሁሉ በተለይም በግል ለሚያውቃቸው ሕዝቦች ሲያገለግል ይገኛል ፤ ይኸውም ልብስ ያጥብ ፤ ጥላ ይሠራና ያበረክት ፤ ጭራ ቆንኖ ይሰጥ ይኽንም የመሳሰሉ ዝምድናን አንድም ወዳጅነትን የሚፈጥሩ ነገሮችን በመፍጠር በራሱ ፈቃድ ይሠራ ነበር ። እን

www.ethiopianorthodox.org

ዲሁም ተማሪዎች የሚበሉት የሚለብሱት ሳይኖራቸው ማኅበራዊ ኑሮን በመ ደገፍ የደብረ ታቦርን በዓል ብዙ ድግስ በመደገስ ሕዝቡን ይጋብዙና ያበሉ ያጠጡ ነበር ፤ ማኅበርም በመግባት የተለዩ በዓላትን በመያዝ ከሕዝቡ ጋር ይገናኙ ነበር ። ተስኢነነ በማለት በሰበሰቡት ገንዘብ የጽጌን በዓል እየደገሱ ሕዝቡን ያበሉ ያጠጡም ማኅበራዊ ኑሮን ይገልጡ ነበር ። ከዚህም ጋር በጸ ሎት ሕዝቡን ያስቡት ይዘክሩት ነበር ፤ ይኸም ማለት ተማሪ ምግብ ሳይኖ ረው ቀርቶ ምንም ቢራብ ቢጠማ ማታ ጸሎታ ለማርያም ሳይል አያድርም ነበር ፤ በዚህም አጋጣሚ ያለበትን ደብርና ሕዝቡን ያስብ ነበር ፡ በጠቅላላም ይኸን በመሳሰለው የአንድነት መግለጫ ይጠቀሙ ነበር ።

## ፪ኛ ሕዝብ ።

ሕዝብ ደግሞ በበኩሉ ለጊዜው ተማሪው በጸሎቱ በትሩፋቱ ይጠቅመኛል በማለት ፪ኛም በትምህርቱ ለሀገር ይጠቅማል በማለት አርቆ በማሰብ ተማ ሪው ተምሮ እስኪወጣ አንድም ያለበትን ደብር ለቆ እስኪሄድ ድረስ እን ጀራ በመዘከር በበዓላት ጊዜ እየጠሩ በመጋበዝ ፤ በክረምት ጊዜ በቤታቸው ሰብስቦ በመያዝ ባዕድነት ጠፍቶ ዝምድና እንዲፈጠር ያደርጉ ይከባከቡ ነበር ይኸንም ተግባር ግዴታ በማድረግ ፡—

### ሀ/ ተማሪዎች በታመሙ ጊዜ ፤

ተማሪዎች ሲታመሙ እህል ውኃ በማቅረብ ፤ አንድም በቤታቸው ወስ ደው በማስታመም ይረዱ ነበር ።

### ለ/ በድግስ ጊዜ ፤

እንደ ቦታውና እንደ ደብሩ ታላቅነት ወይም ታናሽነት ነው እንጂ ትልቅ ድግስ ሲደገስ ለደብሩ ካህናት ብቻ ሳይሆን ለተማሪም ለብቻው የሚታሰብበት ቦታ ወይም ጊዜ ነበር ፤ ይኸም ፩ኛ ተማሪው ከመብዛቱ የተነሣ ልዩ ድግስ የሚያሳስብ በመሆኑ ለብቻው መጠራቱን ያመለክታል ፤ ፪ኛ ተማሪ በቅል ውጥ ብቻ እንዳይመጣ ራሱን የቻለ ጥሪ ተደርጐለት ተከብሮ ቦታውን እን ዲይዝ ማለት ነው ። ብዙ ጊዜ ግን ይኸ ዓይነት ግብዣ የሚደረገው ታላ ላቅ አድባራት ተማሪ በማይለይበት ክብሩም በሚታወቅበት ነው ። ይሁን እንጂ በአንዳንዱ ቦታ ደግሞ ተማሪ ለድግስ አይጠራም ነበር ፤ ምክንያቱም የተጠራ እንደሆነ እየኮራ ይቀራል ። የተረሳ እንደሆን ግን ሊቀላውጥ ይሄ ዳል በማለት ነው ፤ ይኸም አስተያየት የተፈተነ እውነት ነው ።

### ሐ/ ተማሪ በሞተ ጊዜ ፤

ምንም የእግዚአብሔር ጸጋ ከተማሪዎቹ ባይለይና ብዙ ጊዜ ሞት ባያጠ ቃቸው አልፎ አልፎ አንድ ተማሪ የሞተ እንደሆነ ሕዝቡ በመላ የኀዘኑን

www.ethiopianorthodox.org

ዕለት አክብሮ ይውላል ፤ ሙሾ ይወጣል ፤ መዋሥዕቱ ይመራል ፤ ቅኔው ይጐርፋል ። ይኸም የሚያመለክተው ከተራው ሕዝብ እስከ ካህናቱ ያለውን የኀዘን ተካፋይነት ነው ።

<u>እንዲህም ሲሉ ይገጥሙለት ነበር</u> ፦

በተማረው ድጓ በጸፈው ግንዘት ፤
ውረድ ውረድ አሉት ግባተ መሬት ።
   ተማሪ በሞተ በሰባት ዓመቱ ፤
   ተምሮ ይመጣል ትላለች እናቱ ።
ካህን ሞተ ብሎ አይነግሩም አዋጅ ፤
እንዲያው በየደብሩ መላክ ነበር እንጅ ።
   እንዴት ካህን ይሙት ካህን ይቀበር ፤
   ጸናጽሉ የወርቅ መቋሚያው የብር ።
እንግዲህ መቃብር ቶሎ ቶሎ ተማር ፤
ድጓ ተሸክሞ መጣልህ መምህር ።
   አብ እሳት ወልድ እሳት መንፈስ ቅዱስ እሳት ፤
   እንዴት ካህን ይሙት ጕሣን የቀደሳት ።

ይኸንም የመሳሰሉ ሌሎች ግጥሞች የኀዘን እንጕርጕሮዎች ያቀርቡለት ነበር ።

www.ethiopianorthodox.org

ክፍል ፲፫ ።

# የኢትዮጵያ ካህናት የማዕርግ ስም ።

ምዕራፍ ፩ ።

## የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መዓርጋት ።

የኢትዮጵያ ካህናት ሁሉ ከላይ በዘረዘርነው መልክ ብዙ ጊዜ በትምህርት ከደከሙና ልዩ ልዩ ሞያ ገብይተው እንደመገኘታቸው መጠን ከፍተኛም ዝቅተኛም ዕውቀት ይኑራቸው እንጂ እንደ አቅማቸው የተወሰነ አገልግሎት በቤተ ክርስቲያን እንዲያበረክቱ ይሰጠቸዋል ። ስለዚህም ደግሞ አገልግሎታቸውን የመሰሉ አንድም የተከተሉ የማዕርግ ስሞች ይሰጣቸዋል ። ይኸውም እንደሚከተለው ያለ ነው ።

## ፩ኛ በገጠር ቤተ ክርስቲያን ።

ሀ- በልዑካን ።

ገጠር በሆነው በማነኛውም ቤተ ክርስቲያን ሊገኝ የሚችል መዓርግ ።

፩ኛ/ ንፍቅ ዲያቆን-የዲያቆን ተወራጅ ።
፪ኛ/ ዲያቆን -ሙሉ ዲያቆን ።
፫ኛ/ ቄስ ።

እነዚህ ዓይነት አገልጋዮች ከሌሉት ቤተ ክርስቲያን እንዳለ አይቆጠርም። ቅዳሴም አይቀደስም ።

ለ- በመዘምራን ።

፩ኛ/ ደብተራ -ሙሉ ችሎታ የሌለው ዘማሪ

፪ኛ/ መሪጌታ - ሙሉ ችሎታ ያለው አስተማሪ የዜማ ፣ የቅኔ ፣ የአቋቋም መምህር ሲሆን መሪጌታ ነው የሚባለው ፤

፫ኛ/ ገበዝ - የቤተ ክርስቲያንን ውስጣዊ አገልግሎትና የቅዳሴ ሥርዓትን የሚጠብቅ ፣ ንዋየ ቅድሳትን ሌሎችንም ንብረቶች የቤተ ክርስቲያን ሀብት የሆኑትን ሁሉ የሚቆጣጠር ነው ። በማንኛውም የገጠር ቤተ ክርስቲያን ከመሪጌታው በቀር ሁሉም ይገኛሉ ፤ በግድም መገኘት አለባቸው ። በአንዳንድ ገጠር ቤተ ክርስቲያን ግን በእርግጥ መሪጌታም ቢሆን ሊገኝ አስፈላጊ ስለሆነ ሕዝቡ በበጐ ፈቃድ መሪጌታውን ለመቅጠር ልዩ ልዩ የገንዘብ መዋጮ ያደርጋል ፤ የተፈለገውን የትምህርት ዓይነት መምህር ይቀጥራል ፣ ስለዚህም በገጠር ቤተ ክርስቲያን መሪጌታ ሳይቀር በግድ ይገኛል ። ከዚህ በላይ እንደተገለጠው ከመሪጌታው በቀር ሁሉም ጥልቅ ዕውቀት አይኑራቸው እንጂ በመጠኑ የ፩ኛ ወይም የ፪ኛ ደረጃ ዕውቀት ይኖራቸዋል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፪ኛ በደብር ቤተ ክርስቲያን ።

፩ኛ/ መጨኔ - የአገፋሪ ተወራጅ ።
፪ኛ/ አጋፋሪ የካህናት አስተናባሪ ።
፫ኛ/ ግራ ጌታ በግራ የሚቆምና በግራ በኩል የሚደረገውን የዜማውን ስልትና የማኅሌቱን ሥርዓት የሚጠብቅ ነው ።
፬ኛ/ ቀኝ ጌታ - በቀኝ የሚቆምና በቀኝ በኩል የሚደረገውን፣ የዜማውን ስልትና የማኅሌቱን ሥርዓት የሚጠብቅ ።
፭ኛ/ ርእሰ ደብር- የደብሩ ራስ ከመሪጌታው ቀጥሎ የሚያስተናብር ።
፮ኛ/ ጸወነ ደብር (በቆማ ፋሲለደስ) ብቻ የሚገኝ ስም ።
፯ኛ/ ሊቀ ጠበብት }
፰ኛ/ ሊቀ መዘምራን } እነዚህ ሁለቱ ትክክል የሆኑ ማዕርጎች ናቸው ።

ስለዚህ ፩ኛው ባለበት ፪ኛው አይኖርም ።

፱ነኛ/ አፈ ሊቅ በታዕካ ነገሥት ብቻ የሚገኝ ።
፲ኛ/ መሪጌታ - በመላ ይትበሃልን ጠብቆ የመዝሙርን ዓይነት የማኅሌቱን ሥነ ሥርዓት የሚያስከብር ነው ።
፲፩ኛ/ አለቃ - የደብር አስተዳዳሪ ።
፲፪ኛ/ መምህር - የገዳም አስተዳዳሪ ።

ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩቱ ማዕርጎች ብዙዎች በነገሥታቱ በመሳፍንቱ የሚሾሙ ከፍ ያሉ ማዕርጎች ናቸው ። የደቀ መዝሙሩ የትምህርቱና የድካሙ ውጤት የሚታወቀው በዚህን ጊዜ ነበር ፤ ማለት እንደ ሞያው መጠን የክብር ስም ሲሰጠው ፤ ሲሾም ሲሸለም ፤ አንዳንዱ ግን በዚያው በደብሩ ማኅበር ፈቃድ ይሾሙት ነበር ። ይሁን እንጂ በዚያም ደጅ ጠንቶ ብዙ አገልግሎ የሥራ ችሎታቸውን አሳይቶ መሾም ስለነበር ይኽ ሹመት ሲገኝ እንደ ቀላል ነገር አይቆጥሩትም ነበር ። እየዋለ እያደረ ግን በከፍተኛ ሥልጣን ላይ የሚገኙት ያልተማሩ በመሆናቸው ምክትል የሚሆናቸውና የሚሾሟቸው ሁሉ የነርሱ ተወራጆች እንዲሆኑ ያልተማሩ መሆን በግድ አስፈለገ ። «ልጅህ ተምሯል ቢለው እንዳይሾም» አለው ይባላል ። ስለዚህም ባለሙያዎቹ ቦታ አጡ ፤ እነርሱ በመጐሰቆላቸው ሞያውም ተጐሳቆለ ተከታይም እስከ መጥፋት ደረሰ ።

## ፫ኛ ገዳም ።

፩ኛ/ አርድእት - ረዳቶች ወይም አገልጋዮች ማለት ነው ።
፪ኛ/ ሊቀ አርድእት- የአገልጋዮች አለቃ
፫ኛ/ እጓል መጋቢ-ምክትል መጋቢ ማለት ነው ።
፬ኛ/ መጋቢ- የገዳሙ የንብረት ሹም

www.ethiopianorthodox.org

፭ኛ/ ጸሐፊ
፮ኛ/ ገበዝ
፯ኛ/ አፈ መምህር- የመምህሩ ወኪል ነው ።
፰ኛ/ የዕቃ ቤት- ንብረቱን የሚጠብቅ የዕቃ ግምጃ ቤት ሹም ።
፱ነኛ/ መምህር- አስተዳዳሪ ነው ።

እነዚህ የገዳሙ ቀዋምያን ስሞች ናቸው ፤ ነገር ግን በአንዳንዱ ገዳም ጥቂቶቹ ስሞች የተለያዩ ይሁኑ እንጂ ብዙው ተመሳሳይ ነው ። እነዚህም ዓይነት ሰዎች ከሌሉት ገዳሙ ይፈርሳል አንድነቱ ይጠፋል ።

በዚህም መልክ ባለመሠራቱ የአንዳንዱ ገዳም አስተዳደር ከአንዱ ሰው እጅ ብቻ በመግባቱ ገዳሙ ሊደክም ሀብቱ ሊባክን ቻለ ።

ምዕራፍ ፪ ።

## የካህናት የማዕርግ ስም

፩ኛ/ ዐፃዊ ኆኅት - የመቅደሱን በሩን ወይም መጋረጃውን የሚዘጋና የሚከፍት ።
፪ኛ/ አናጕንስጢስ - በቅዳሴ ጊዜ ንባብ የሚያነብ ።
፫ኛ/ መዘምር - በቅዳሴ ጊዜ ተሰጠዎ የሚቀበል ።
፬ኛ/ ንፍቅ ዲያቆን ።
፭ኛ/ ዲያቆን - ሙሉ ዲያቆን ።
፮ኛ/ ሊቀ ዲያቆን ።
፯ኛ/ ቄስ ።
፰ኛ/ አቡነ ቀሲስ - የአቡን ጸሐፊ ወይም ጉዳይ ፈጻሚ ።
፱ነኛ/ ሊቀ ካህናት - የካህናት አለቃ (የአቡን ገጸ በረከት ሰብሳቢ) ።
፲ኛ/ ቆሞስ - የቁምስና ማዕርግ ያለው መነኵሴ ቄስ ።
፲፩ኛ/ ኤጲስ ቆጶስ - ጳጳስ ።
፲፪ኛ/ ጳጳስ - ጳጳስ ።
፲፫ኛ/ ሊቀ ጳጳስ - የጳጳስ አለቃ ።
፲፬ኛ/ ሚትሮፖሊስ - የከተማ እናት ማለት ሲሆን በታላቅ ከተማ ለሚሾም ሊቀ ጳጳስ የሚሰጥ መዓርግ ነው ።
፲፭ኛ/ ፓትሪያርክ - ርእሰ አበው ማለት ነው ።

ምንም ከቆሞስ በላይ የነበረው ማዕርግ በተወላጆቻችን ባይሰጣቸውና ቀደም ብሎም ባይታወቅ ስምነቱ የቤተ ክርስቲያን ማዕርግ መሆኑን ለማስረዳት ያህል ጽፈናል ። ፓትሪያርክ የተባለው ማዕርግ ግን በተለይ በመጨረሻ እስኪሰጠን

www.ethiopianorthodox.org

ድረስ ቀድሞ አልነበረንም ። ቢኖርም የአንድ ደብር አለቃ ስም ብቻ ሁኖ ነው የኖረው ፤ ይኸውም የተድባበ ማርያም ደብር አለቃ ነው ።

## የደብርና የገዳም አስተዳዳሪዎች የክብር ስም ።

፩ኛ/ ንቡረ እድ - የአክሱም ጽዮንና የአዲስ ዓለም ማርያም አስተዳዳሪ በአንብሮተ እድ የተሾመ ሥልጣነ ክህነት ያለው ።
፪ኛ/ እጨጌ - የደብረ ሊባኖስ ገዳም አስተዳዳሪ በመላም በኢትዮጵያ ገዳማት አስተዳዳሪ ሆኖ የኖረ ።
፫ኛ/ ጸባቴ - የደብረ ሊባኖስ ምክትል አስተዳዳሪ
፬ኛ/ ፓትሪያርክ - የተደባበ ማርያም መምህር
፭ኛ/ አለቃ - የብዙ አድባራት አስተዳዳሪ ስም
፮ኛ/ ርዑሰ ርዑሳን-የመርጡለ ማርያም አስተዳዳሪ ስም
፯ኛ/ መክብብ- የአትሮንሰ ማርያም አስተዳዳሪ ስም ።
፰ኛ/ ሊቀ ሊቃውንት- የታዕካ ነገሥት በዓታ ማርያም አስተዳዳሪ ስም
፱ነኛ/ ሊቀ ሥልጣናት- የመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል አስተዳዳሪ ስም ።
፲ኛ/ መልአከ መልአክ- የቀራንዮ ።

ከዚህ ጀምሮ ወደታች ያለው ግን በጐንደሮች ጊዜ ወጥቶ አሁን ግን በብዙ ከተማዎች ያሉ አድባራት የሚጠቀሙበት የማዕርግ ስም ነው ።

፲፩ኛ/ መልአከ ምሕረት ።
፲፪ኛ/ መልአከ ሣህል
፲፫ኛ/ መልአከ ፀሐይ
፲፬ኛ/ » ገነት
፲፭ኛ/ » ኃይል
፲፮ኛ » ብርሃን
፲፯ኛ/ ሊቀ ማእምራን
፲፰ኛ/ መልአከ ጽዮን
፲፱ኛ/ » ሕይወት
፳ኛ/ » ጽጌ
፳፩ኛ/ » አርያም
፳፪ኛ/ ሊቀ ኅሩያን
፳፫ኛ/ ቄስ አጼ
፳፬ኛ/ አፈ መምህር
፳፭ኛ/ አበ ምኔት የገዳም አስተዳዳሪ
፳፮ኛ/ እመ ምኔት የገዳም እናት (አስተዳዳሪ)

www.ethiopianorthodox.org

ምዕራፍ ፫ ።

# የአድባራትና የገዳማት የማዕርግ ስም ።

እያንዳንዱ ደብር እንደ ሰው ልጅ የክርስትና ስም አለው፤ጸሎትም ሲደርስ ከቤተ ክህነትም ሲጻፍ የሚነሣው በዚህ ስሙ እንጂ ሕዝቡ በሚያውቀው በመጠሪያ ስሙ አይደለም ። እንዲያውም ለአስተዳዳሪዎች የሚሰጠው የማዕርግ ስም ከዚሁ ጋር የተያያዘ ነው ። ለምሳሌ ደብሩ ደብረ ሣህል ተብሎ እንደሆነ አስተዳዳሪው መልአከ ሣህል ይባላል፤ ደብሩ ደብረ ገነት ተብሎ እንደሆነ አስተዳዳሪው መልአከ ገነት ይባላል፤ሌላውም እንዲሁ ነው ። ለምሳሌም ያህል ከዚህ እንደሚከተለው እንመልከት ።

፩ኛ/ ደብረ ጽዮን
፪ኛ/ መንበረ ጸባዖት
፫ኛ/ ታዕካ ነገሥት
፬ኛ/ መንበረ መንግሥት
፭ኛ/ ደብረ ፀሐይ
፮ኛ/ ደብረ ሣህል
፯ኛ/ ደብረ ኃይል
፰ኛ/ ደብረ ገነት
፱ነኛ/ ሐመረ ኖኅ
፲ኛ/ መንበረ ልዑል
፲፩ኛ/ ማኅደረ ስብሐት
፲፪ኛ/ ቀራንዮ
፲፫ኛ/ ደብረ አሚን
፲፬ኛ/ ደብረ ሃይማኖት
፲፭ኛ/ ደብረ ልዑል
፲፮ኛ/ ማኅደረ ማርያም
፲፯ኛ/ ደብረ ድማኅ
፲፰ኛ/ መካነ ኢየሱስ
፲፱ነኛ/ ቅድስተ ቅዱሳን
፳ኛ/ ደብረ ጽጌ
፳፩ኛ/ ምስካየ ኅዙናን
፳፪ኛ/ መካነ ሥላሴ
፳፫ኛ/ ደብረ መንክራት
፳፬ኛ/ ደብረ ምጽላል
፳፭ኛ/ ጽርሐ አርያም

www.ethiopianorthodox.org

፹፮ኛ/ መርጡለ ማርያም
፹፯ኛ/ ተደባበ ማርያም
፹፰ኛ/ አትሮንስ ማርያም
፹፱ነኛ/ ምስካበ ቅዱሳን
፺ኛ/ ደብረ ኖኅ
፺፩ኛ/ ደብረ ታቦር
፺፪ኛ/ መንበረ ብርሃን
፺፫ኛ/ ደብረ ሲና
፺፬ኛ/ ምጽላለ ማርያም
፺፭ኛ/ ቤተ ማርያም
፺፮ኛ/ ገነተ ማርያም
፺፯ኛ/ ደብረ ወርቅ
፺፰ኛ/ ደብረ ዕንቍ
፺፱ነኛ/ ደብረ ነጐድጓድ
፻ኛ/ መካነ ሰማዕት
፻፩ኛ/ ደብረ ዓባይ
፻፪/ ደብረ ምጥማቅ


www.ethiopianorthodox.org

# ማጠቃለያ ።

ኢትዮጵያ ጥንታዊት ሀገር የሆነችውን ያህል ብዙ ጥንታውያን ነገሮችም እንዳሏት በልዩ ልዩ ክፍልና ምዕራፎች የገለጥናቸው ጥበባት ምስክር ናቸው ። ይሁን እንጂ በየአረፍተ ዘመናቱ ተቀናቃኞችና ጠላቶች በርሷ ላይ በመነሣታቸው ጥንታውያን የሆኑ ነገሮችን ሁሉ እያደኑ እንዳጠፉ ጥርጥር ሳይሆን እውነት ነው። በታሪክ እንኳን ግልጥ ሁኖ የታወቀውን ፲ኛውን የጥፋት ጊዜ ብናነሣ በቂ ምሳሌ ይሆነናል ፤ ይኸውም የጉዲት ወረራ ነው ። የርሷም ጥላቻ በቤተ ክርስቲያንና በመንፈሳውያን ነገሮች ላይ በመሆኑ ተከታትላም ታጠፋውም የነበረ ይኸንና ይኸን የመሰለውን ነው ። ደግሞም በዚያን ጊዜ ጥበባት ሁሉ ሊመነጩ ይችሉ የነበር በቤተ ክርስቲያን ነበር ፤ ቁም ነገርነት ያላቸው የጥንት ቅርሶችም ይጠበቁ የነበር በቤተ ክርስቲያን ነበር ። እንግዲህ በዚያን ጊዜ ያልጠፋ ምን ነገር ይገኛል ? ሊቃውንቱ ታድነው ተገድለዋል ፤ መጻሕፍቱ ተቆነጻጽለዋል ፤ አብያተ ክርስቲያናትም ተቃጥለዋል ፤ በጠቅላላም በአክሱም ጊዜ ተፈጥሮና ተፈልስፎ የነበረውን ሁሉ በዚያን ጊዜ አጥፍታዋለች ። ለልዩ ልዩ ጥናት መነሻና መድረሻ ይሆኑ የነበሩ ጥበባት ሁሉ አብረው እንደጠፉ ዓይነ ልቡና ያለው አይስተውም ፤ ታዲያስ ጥበባችንን ትምህርታችንን በጠቅላላም ባህላችንን መልሶ ማን ገነባው ? እንዴትስ ተገነባ ? ይኸ ደግሞ ራሱን የቻለ ከፍ ያለ ጥናትን ይጠይቃል ፤ መልሱም ቀላል አይደለም ፤ ሁሉም ነገር ተቋርጦ ጠፍቶ ኑሮ መጀመሩ የታወቀ ነው ፤ ይሁን እንጂ የተገኘውን አሁን ያለውን ያህል ከመሬት በታች ሳይውልና ሳይጠፋ አልቀረም ለማለት እንችላለን ። እንዲያውም የተገኘው ሳይቀር ከነመልኩ ከጥንታዊ ባሕርዩ ጋር መሆኑን ቅሉ ያጠራጥራል ፤ ምክንያቱም «ሥጋ ከመሬት ወድቆ አፈር ሳይዝ አይነሣም » ይባላል ፤ ይኸ እርግጥ ሳይሆን አይቀርም ፤ እንዲህም ከሆነ ብዙ ጥበባት ፈጽመው ወድመውብን የተገኙትም ብዙ ለውጥ አግኝቷቸው ይሆናል ።

የብዙ ጥናቶች መግቢያቸው በሩ እየጠፋ የሚያስቸግረው ፤ የትመጣውም እየጠፋ መነሻው ያልታወቀ እየሆነ የሚያስቸግረውና ጥያቄው ሁሉ ያለመልስ እንዲሁ ተንጠልጥሎ የሚገኘው ስለዚህ እንደሆነ የታመነ ነው ። ይሁን እንጂ የጠፋው መንግሥት እንደገና ሲቋቋም ፤ ቤተ ክርስቲያኗም አገልግሎቷን ስትቀጥል ክርስቲያናዊ ጥበባችን ከሞላ ጐደል ወዲያውን ቀጥሎ በዚህ መልክ ለመገኘትችሏል።

ብዙ ነገር የተፈጠረበት ከዓለም ጋር ግንኙነት የነበረበት ጊዜ የአክሱም ዘመነ መንግሥት ነው ፤ ብዙ ጥፋትም የደረሰው በርሱ መንግሥት መጨረሻ ላይ ነው ፤ ለምሳሌ በሥነ ጽሑፋችን ረገድ የተስፋፋ ድርጅት እንደነበር ሲታወቅ እርግጠኛውን ሁኔታ የሚያስረዳ በብራና ወይም በፓፒሩስ ወይም በሌላ ነገር ላይ ተጽፎ የተገኘ ነገር የለም ፤ ምናልባት ፈጽሞ ወድሟል ፤ ወይም ከመሬት በታች ውሏል ፤ ወይስ - - - - - - ያልተብራራ ነገር አለ ። እንደአጋጣሚ ሁኖ በደንጊያውና

www.ethiopianorthodox.org

በሐውልቱ ላይ የተጻፉትና የተቀረጹት ባይኖሩ እንዴት እንጽፍ እንደነበር ፤ ሥውር ሁኖ በቀረ ነበር ፡ የቅርጸ ቅርጹም የፊደሉም ድምፅ የቋንቋውም ነገር በዚህ መልክ ሳይጠፉ አልቀረም ፤ እንዲያውም በቋንቋው በኩል የሄድን እንደ ሆን ግዕዙ ጠፍቶ አማርኛ ሊፈጠር የቻለው በዚሁ ምክንያት እንደሆነ ይገመታል ። አማርኛ መቼ ተጀመረ ሲባል በአክሱም ፤ በሥነ ጽሑፍም በኩል የፊደል ቅርጽ ድምፅ ሊለውጥ የቻለው በዚያኑ ጊዜ ነው ፤ ይኸ ዓይነት ጥፋት በግራኝ ሞሐመድ ጊዜም ተደጋግሞ ተደርጓል ፤ ብዙ ነገሮች ከመሬት በታች ተደፍነው ቀርተዋል ፤ ብዙ መጻሕፍት ንዋየ ቅድሳት ተቃጥለዋል ። በጠቅላላም የጥፋቱ ሁኔታ ተመሳሳይ ስለሆነ ታሪኩም ተመሳሳይ ሁኖ እናገኘዋለን ። በፊተኛውም ሆነ በ፪ኛው ጥፋት ጊዜ እንዲሁም በሌላ በሀገር ውስጥ በየጊዜው በሚደረገው የርስ በርስ ግጭት የጠፉ ብዙ ጥበብ ሲኖር ፤ ሊቃውንቱ ግን ተስፋ ባለመቍረጥ በየጊዜው እየተነሡ ሕይወታቸውን ለጥበብ መሥዋዕት አድርገው ቢሰጡና በጥናት ቢወስኑ ጥበባትን ለማስገኘት በመጠኑም ቦታ ለመስጠት መልክ ለማውጣት ችለዋል ። ባለፉት የዘረዘርናቸው ልዩ ልዩ የትምህርት ዓይነትና ጥበባት የነርሱ ድካም ውጤት መሆኑን የሚዘነጋው የለም ። አበው አልቀው ውሉድ ሲተኩ ይኸው ዓይነት ግዴታ እንዳለባቸው በመቍጠር ስለሚያጠኑትና ለተተኪዎች ስለሚያስተላልፉት እስከኛ ለመድረስ ቻለ ።

ይኸም ሁሉ ችግር እያለ ትምህርት በኢትዮጵያ የተወደደና ከፍተኛውን ደረጃ ይዞ ይገኝ እንደነበር የታወቀ ነው ። የአገሯ ነፃነት የሕዝቡም መብት ቅሉ ሊከበርና ወዲያው ሊቋቋም የቻለው በዚሁ ረገድ ነው ፤ ማለት ሕዝቡ የራሱን ጥቅምና ጉዳት የለየ በመሆኑ ከሌላው ሥራ ይልቅ ሕይወቱን ለትምህርት የሰጠ በመሆኑ በኢትዮጵያ ጥፋት የደረሰ ብዙ ነገር የተቋረጠ ሳያስመስል ይዞ ይገኛል ። ትምህርቱም ሲጠበቅና በሚገባም ሲካሄድ የነበረው ሕዝቡ መምህራኑን ጊዜው በፈቀደው መልክ ሲቀጥርና ሲረዳ ፤ መምህራኑም በጸጋ ያገኙትን በጸጋ ፤ በከንቱ ያገኙትን በከንቱ ሲያካፍሉ በመኖራቸው ነው ። ተማሪዎቹም በመምህራኑ እግር ለተመካት የነበራቸው ጥረት እጅግ ከፍ ያለ ስለነበር ለሕይወታቸው ሳያስቡ የትምህርት ስደተኞች ሁነው የሚወስዱትም ጥናት እንዲሁ ከፍተኛ ስለ ነበር ነው ።

ስለዚህም ይኸን ሁሉ ትምህርት እያንዳንዱ ደቀ መዝሙር በተወሰነው ጊዜ ተምሮ አጥንቶ ከመሔዱም በላይ ራሱ ወደ ምርምር እየገባ ብዙ ጥበብ ይቀምር ለሌላውም ለማስተማር በጣም ይጥር ነበር ። ይኸ ሁሉ ብሔራዊ ዕውቀትም ለጊዜው ይገመት የነበረው መንፈሳዊ ተግባር አንድም መንፈሳዊ ግዴታ እንደሆነ ነበር ፤ በ፩ኛው በኩል በጥንት ዘመን በየትኛውም ዓለም መንፈሳዊ ነገር ይከበር ስለነበር ክብርን በመሻት ሲሆን ፤ በ፪ኛው በኩል ደግሞ መንፈሳዊ ነገር በመሆኑ በምድር ባንጠቀም በሰማይ እንጠቀማለን የማለት ግምት ስለነበር ነው ። መምህራኑ ቅሉ ራቡንና ጥሙን ታግሠው ያስተምሩት የነበር ፤ [illegible]

www.ethiopianorthodox.org

ዘመን እንዲሁ እየተቸገሩ ይማሩት የነበር የሃይማኖት ትምህርት አድርገው ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን እናገኛለን የማለት ስሜት ስለነበራቸው ነው ። በእርግጥም አምላክ ኃይሉን እየሰጣቸው ብዙ ጸዋትወ መከራን በቀላሉ እያሳለፉ ከሕማም ከኀዘን እየተጽናኑ ብዙ ዘመንም የሚፈጀውን ዕውቀት በቅርብ ጊዜ እንዲፈጽሙ ሲያደርጋቸው ይገኝ የነበር በዚሁ ስሜት በመነሣታቸው ነበር ። ሕዝቡ ስሜቱ ሥራው መንፈሳዊ ነበር ፤ ውድድሩም መንፈሳዊ ተግባርን ለመሥራትና ለመፈጸም ብቻ ነበር ፤ ቢያጠፉም ቅጣቱ ከመንፈሳዊ ተግባር መለየት ነበር ፤ ስለዚህ በጥዋት በማታ ዕረፍትን ሳይሹ በማስተማራቸው ተማሪዎችም ያለ ረዳት ችግሩን ሁሉ ተቋቁመው ያልፉት ነበር ።

ሕዝቡም ተማሪዎችን በአንዳንድ ቦታ ይረዳቸው ይደግፋቸው የነበር እንዲሁ መንፈሳዊ አቅዋም ያለው በነፍስም በሥጋም የሚጠቅም መሆኑን በመመርመርና በማመን ነበር ። ነገር ግን እየዋለ እያደረ ፤ ጊዜው የተለወጠውን ያህል ነገሩም መልኩን ለወጠ ፤ በተለይም ከጠላት ወረራ ወዲህ ሕዝቡ የተለያየ አስተያየት ሊያድርበት በመቻሉ ተማሪዎች የራስን ጥበብ ብቻ ፈላጊ እንደሆኑ የሚገመቱና የሚናገሩ የሚተቹም ብዙዎች ሆኑ ፤ ስለዚህም የተማሪዎቹ ቍጥር ቢያንስም ለነርሱ እንኳን የሚደረገው ርዳታ የሕዝቡ ስጦታ እየተቀነሰ ከመሔዱም በላይ ትምህርቱ ሥጋዊ ዕውቀት ያውም ዝቅተኛ ፣ እንጀራም የማያበላ ነው እየተባለ በመገመቱ ተማሪዎች የማይማሩት መምህራንም የማያስተምሩት ሁኖ ተገኝቷል ፤ በዚህም ምክንያት ያ ሁሉን ያኰራ የነበረው ጥንታዊው ጥበባችን ለመውደቅ አዘንብሎ ይገኛል ።

ለማንኛውም ሞያ ዋጋ የሚሰጠው ሕዝብ ነው ፤ የሚደግፈውም መንግሥት ነው ፤ በየጊዜው መልክ የሚሰጡት ደግሞ ሊቃውንት ናቸው ። ስለዚህ የነዚህ ሁሉ ድጋፍ የተለየውን ያህል ለመውደቅ አዘንብሎ ይገኛል ፤ አሁን ግን ይኸ ሞያ በማንም ሳይደገፍ ባለቤት አጥቶ እንዲሁ ወድቆ ቢሰበር የደረሰበትም ጠፍቶ ቢቀር ተወቃሹ አሁን ያለው ትውልድ እንደሆነ መዘንጋት የለብንም ። በየትኛውም ዓለም ቢሆን እንኳን የነበረውንና ያለውን ሊኖርም የሚችለውን ቀርቶ በነበር ብቻ የሚያገለግለውን ጥበብ በመፈለግና በማጥናት ይገኛል ፤ እንዲሁም ለወደፊት ሌላ ለመፈልሰፍ ከሕሊናው ጋር ይታገላል ። ከዚህም ጋር የውጭ አገር ሊቃውንት ተራ በተራ እንደጥናታቸው ልዩነት በዚህ ጽሑፍ የሚገኙትን ዕውቀቶች ሁሉ ለማጥናት ሲጣጣሩ በአንድ ቦታ እንኳን አጠቃሎ የሚነግራቸው ባይገኝ በየጠቅላይ ግዛቱ ሲራራጡ ይገኛሉ ።

ጥበባችን ብዙ ፤ ዓይነቱም ልዩ ሁኖ ለኛ ምንም ባይመስለን ፤ ወይም ርዝራዡ ገና ያልጠፋ ሁኖ በየቤተ ክርስቲያኑ ያለ መስሎ ቢታየንም መሠረቱን ሲለቅ ከጥቂት ጊዜ በኋላ እንዳልነበር ሊሆን እንደሚችል የአሁኑ አያያዝ ያስገምታል ። እስካሁን ከፍተኛ ጥበብ ተብሎ ከዘመን ወደዘመን ሲሸጋገር የኖረው አሁንም በመጠኑ ያለው የመጀመሪያው ጥበብ የቅ/ ያሬድ ድርሰት ዜማ የተባለው ነው ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፩ኛ ዜማ ።

የዜማው ትምህርት ከፍ ያለ የፍልስፍና ዕውቀት ያለው፤ አሁንም በብዛት ሁሉ ለጥናት የሚፈልገው ነው፤ የግጥሙም አሰካክ ከፍ ያለ ርቀት ያለው ብሔራዊ ሥልጣኔን በጕላ የሚመሰክር ነው ። የዜማ መዝገቡ ድጓ ሲሆን ሌላውም ቢሆን በመላ የያሬድ ድርሰት ነው፤ በኋላም የተደረሱ አንዳንድ ቢኖሩ ያነኑ ተከትለው የሄዱ ስለሆነ ሁሉን ወደ አድናቆት የሚስብ ኃይል ያለው ትምህርት ሁኖ ተገኝቷል ። እንዲሁም ሲሆን ጥቅሙን ዐውቆ ተከታትሎ ያሻሻለውና ብሔራዊ መልክ የሰጠው ባለመኖሩ ለዘመናዊው ትውልድና ለሰሚው ሁሉ አስቸጋሪ መስሎ ይገኛል ። ይኸ ጥበብ አሁንም የጠፋ መስሎ ይታይ አንድም ይገመት እንጂ የውጭ አገር ሊቃውንት ለጥናት በር የከፈቱበት ልዩም ወጭ ያደረጉበት ጊዜ ነው ። የውጭ ሰዎች በሚፈልጉት መንገድ የሚገልጥ በመጥፋቱ ግን በውጭ ሰው የዜማው ስልት ይኸን ያህል ምሥጢር ያዘለ፤ ትርጕምና ምልክት ያለው መሆኑ ግልጥ የሆነ አይመስልም፤ የቀረው ቀርቶ በንብረት ሲባል የሚያምረው ዜማ ኀብረት አጥቶ ሁሉም እንዳገኘ ሲጮኸው እንኳን ለሰው ሀገሩ ለሀገሩም ተወላጅ እጅግ የሚያስቀይም ሆኗል። አሁንስ ባለቤቱ አንድም ኃላፊው ማነው ? ሁል ጊዜም የሚጠፋው ባለቤት ያጣ ነገር ነው ። ይኸን የመሰለው ጉዳይ ሁሉ የቤተ ክህነት ብቻ ወይም የመንግሥት ብቻ አይደለም፤ ሁሉም ቢያስብበት ሁሉም ኃላፊነት እንዳለበት ቢያውቅ ሊቃና በቻለ ነበር ።

## ፪ኛ የቅኔ ግጥም ።

የቅኔም ግጥም እንዲሁ እንደዜማው ተወዳጅና ተፈላጊ ነው ፤ የአእምሮ መክፈቻ የዕውቀት መገመቻ የንግግር ስልት መልመጃ ሁኖ ከጥንት ጀምሮ በኢትዮጵያችን ተከብሮ ይኖር ነበር፤ የሊቃውንቱ ችሎታ የሚታወቅ ሥውሩ ነገር ሁሉ የሚገለጥ በዚሁ ነው ። ቅኔ በኢትዮጵያ ታላቅ ፍልስፍና እንደሆነ በመታወቁ የማንኛውም ትምህርት ተማሪዎች ሁሉ በመጀመሪያ ወደዚያ እየሄዱ ይማሩት ነበር፤ በአሁኑ ጊዜም ቢሆን ቅኔ ራሱን የቻለ ሞያ ሁኖ ሌላውን የሚያብራራ፤ ለሌላውም ምሥጢር ሁሉ ትርጕም የሚሰጥ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ግን ታላቁ ሞያ እንኳን ለሌላው ሊሆን ለራሱም ትርጕሙ እየጠፋ ከመሔዱ የተነሣ አዲሱ ትውልድ ከግዕዙ ቋንቋ ከቅኔውም ግጥም ይልቅ የውጭ ቋንቋ ማጥናት የውጭም ሥልጣኔን መከተል አስፈላጊ መሆኑን አምኖበታል ። የመጽሐፉም ትርጕም ብዙ የረቀቀ አማርኛ የሚፈጠርበት የተሠወረው ምሥጢር የሚተረጐምበት አዳዲስ አስተያየት የሚፈጠርበት ትምህርት ሲሆን ፤ መምህራኑ እያለቁ ደቀ መዛሙርቱም ባለመተካታቸው ዕውቀቱ እየተቀነሰ ክብሩ እየወነሰ ሄዷል ። እውነት ነው፤ የቅኔ ሞያ አስፈላጊ መሆኑን ሁሉም ሳያምንበት አልቀረም፤ እንዲያውም ማንኛ

www.ethiopianorthodox.org

ውንም የአማርኛ ግጥም ቅኔ እያሉ መጥራታቸውና የቅኔ ደራሴ እያሉ ሰዎችንም ማሞገሳቸው አልቀረም ፤ ይሁን እንጂ ያ ተስማሚ መንገድ ያለው ፤ ብዙ ምሥጢር ያዘለው የግዕዙ ጥንታዊ ቅኔ ቦታ የለውም ። ቋንቋውም ቢሆን በየትኛውም ዓለም የታወቀ ብዙ ሥራ የተሠራበት ፤ መጻሕፍት የተጻፉበት ፤ ከሴማውያን ቋንቋዎች ጋር ብዙ ግንኙነት ያለው ስለሆነ እንዲሁ እንደዋዛ ዕቃ ሊታይ የሚገባው አይደለም ፤ ሁሉም እንዲማረው ደረጃ እንዲኖረው በር እንዲከፈትለት በግድ ያስፈልጋል ። ይኸ ሳይሆን ግን ስለኢትዮጵያ የሚደረገው ጥናት ሁሉ የዓይነ ሥውር ደበሳ ይመስላል ፤ እንደርሱም ይቈጠራል ፤ ስለዚህ ኢትዮጵያን በበለጠ ለማወቅም ለማሳወቅም ቢሆን ግዕዙን በሚገባ ማስተማር ይጠቅማል ።

## ፫ኛ የዘመን አቈጣጠር ።

የዘመን መቍጠሪያ የሰዓት መሥፈሪያ የነበረው ዕውቀት በኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ የሠራ ቀደም ብሎም የታወቀ ጥበብ ነው ። በአሁኑ ጊዜ ግን እየተቀነሰ በመሔዱ ዘመናት ፤ በዓላት ፤ ሥፍረ ሰዓት ሁሉ እንዴት እንደሚገኙ ለማወቅ በብዙዎች ዘንድ ችግርን ፈጥሯል ። መምህሮቻችን ይኸን ሁሉ የፈለሰፉ ፤ ይኸን ሁሉ ለትውልድ ያስተላለፉ ሲሆኑ በሞት ይለዩ እንጂ አሁንም ቢሆን ሕያዋን ናቸው ። ሞቱ የሚባሉ ይኸ ዕውቀታቸው ተቀባይ አጥቶ ልጅ ሳይተካ የቀረ እንደሆን ነው ፣ እስካሁን ግን ሕያው ሥራቸው ለታሪክ ሰፊ ገጽን ሰጥቶ በጨለማው ላይ ሲያበራ ይገኛል ። የቍጥር ትምህርት የተባለው ለሞያው ሁሉ ፤ ለጥበባትም ሁሉ መልክን የሚሰጥ ፤ በዓላትን አጽዋማትን ለይቶ ቦታ ሰጥቶ የሚያስተምር ሞያ ከመሆኑ ጋር ሌላው ሥጋዊ ጥበብ ሁሉ በርሱ ይመጠን ይለካ ነበር ፤ ለምሳሌ የኮከብ አቈጣጠር የትምህርት አመራር በዚሁ ይፈጸም ነበር ።

የኢትዮጵያ መምህራን የቀለም ትምህርት ብቻ በማስተማር አልተወሰኑም ነበር ፤ ነገር ግን ዘመናቸው የፈቀደውን አስፈላጊም መስሎ የታያቸውን ትምህርት ሁሉ በሚገባ ያስተማሩ ነበሩ ። የአሁን የቍጥሩ ስልት ቀስ በቀስ እየጠፋ ሄዷል ፤ በቅርብ ያለው በያመቱ የሚታወጀው የአጽዋማትና የበዓላት ማውጫ ብቻ እንጂ ረቂቁ ምርምር የምሕዋረ ፀሐይ ፤ የምዕዛረ ፀሐይ አቈጣጠር ቦታውን ለቆ ይገኛል ። እርግጥ ነው ምናልባት በያንዳንዱ ገዳም የተለዩ መምህራን ይኖሩ ይሆናል ፤ እነርሱን ሰብስቦ የነበረውን መጠየቅ ፤ እንዴት ሊስፋፋ እንደሚችል መረዳት መጽሐፉንም ሰብስቦ ማሳተም ተገቢ ነበር ።

## ፬ኛ የቁም ጽሕፈት ።

አባቶቻችን የፊደሉን ቅርፅና ድምፅ በመጠበቅ በየጊዜው እያጻፉ ብዙ መጻሕፍት አቆይተውናል ። በየዘመኑ የተለያየ መልክ ያላቸው ጽሑፎች ሊያቆዩልን የቻሉ ዘመናቸውን ተከትለው ፍጹም ለውጥ እንኳ ባይኖረው የፊደሎችን አጣጣል መልካቸውንም ቢሆን በመለዋወጥ በቁም ጽሕፈት ጽፈው ያቆዩልን እነርሱ ናቸው ።

www.ethiopianorthodox.org

አባቶች የቁም ጽሕፈት ሲያስተምሩ ከርሱ ጋር በማያያዝ ቀለም መበጥበጥን ብራና መፋቅን አብረው ያስተምሩ ነበር ፤ በዚህም ምክንያት እስካሁን ድረስ የቁም ጽሕፈት ዕውቀት ሳይቋረጥ የብራና ማውጣቱ ተግባር ሳይጠፋ ለመቆየት ቻለ ። አሁንም ዓለምን ወደ አድናቆት የሚስቡ በዘመን ጥንታውያን ፤ በሥራቸው ደግሞ አስደናቂዎች ፤ በብዛትም ከግምት በላይ የሆኑ የብራና መጻሕፍት በሀገራችን ይገኛሉ ። በአሁኑ ጊዜ የዚህን ሥራ የሚከታተሉ በቍጥር ያነሱ ናቸው ፤ እነርሱም ስለሞያው ፍቅር ሳይሆን የእንጀራ መፈለጊያ ብቻ በማድረግ ስለሚጽፉ በፊደሉ አቀማመጥ በነጥብ አጣጣል የተጠበቀ ጽሑፍ ሊያቀርቡ አልቻሉም ።

ከጽሑፉ ጋርም የሥዕል ሥራ በኢትዮጵያ የተወደደና ቅዱስም ተግባር ሁኖ ከዘመን ወደ ዘመን እየተሻሻለ የሄደ ጥበብ ነው ፤ በመጽሐፉ ውስጥ በየገጹ እያስገቡ ፤ አንድም ልዩ ልዩ ታሪክ በሚጀምርበት ገጽ ሁሉ ይሞሉት ነበር ። በአሁኑ ዘመንም በቍጥር ይነሱ እንጂ በተሻለ መልክ የሚሠሩ ሠዓሊዎች አሉን ፤ ሁኖም የቀድሞውን መልክ ሳይጠብቁ ከውጭ ባህል ጋር የሚያደባልቁ ናቸው ። የጥንት ሠዓሊዎች በቅዱሳን ሥዕል ብቻ ያልተወሰኑ ልዩ ልዩ ምሳሌዎችን ከራሳቸው እያፈለቁ እንደመሰላቸው ይሥሉ ነበር ፤ ስለዚህም የኢትዮጵያ ሥዕል የተለየ ጠባይ ያለው ሁኖ ይገመታል ፤ ከማንም ያልተወረሰ ራሱን የቻለ የምርምር አርእስት ለመሆን የቻለ ጥበብ ነው ። ሥዕልም የሚሣልበት ቀለም ብዙውን ጊዜ ብሔራዊ ስለሆነ ፤ በቀለሙ አገባብ በአርእስቱ አመራረጥ የነበራቸው ጥንቃቄና ችሎታ የአሁኖችን የሚያስንቅ ሁኗል ። የሥዕሉም አቀማመጥ የአሁኑን ዘመን ሠዓሊዎች ወደ አድናቆት የሚስብ ሁኖ ይገኛል ። ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ ብቸኛ ሁና የምትኖር አገር ስትሆን ከማንም ጋር ግንኙነት የሌለው ራሱን የቻለ ባህል እንዲኖረው እያደረጉ የሣሉና ያስተማሩ መምህራን ብዙዎች ናቸው ። የሚሥሉትም በቤተ ክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በመጻሕፍት ላይ በልዩ ልዩ ቤቶች ዕቃዎችና እነዚህንም በመሳሰሉ ነገሮች ላይ ነበር ። የሠዓሊዎች ሐሳብ በብዙ ሲገናኝ በብዙ ደግሞ ይለያይ ነበር ፤ ይኸም ቅሉ አንዱ ከአንዱ ቅጅ ሊያደርግ አለመፈቀዱን ያመለክታል ።

## ፳ኛ ቅርጻ ቅርጽ ።

ኢትዮጵያውያን መምህራን ራሱን የቻለ የቅርጽ ሞያ ስለነበራቸው ሀገራቸውን በነዚሁ ቅርጾች አበልጽገው ይገኛሉ ፤ ለምሳሌ እንደመስቀል ፤ እንደ አይኮን ያሉና ለልዩ ልዩ አገልግሎት የሚውሉ ከብረት ከእንጨቶች ከደንጋይ የተሠሩ ብዙዎች ይገኛሉ ። ይኸም ሥራ በየቦታውና በልዩ ልዩ ሰዎች ቢሠራ ብዙ ጊዜ አንድም በብዛት የሚሠራው በገዳማት በመነኮሳት እጅ ነበር ፤ አሁንም ቢሆን ርዝራዡ ሳይጠፋ ይገኛል ። ለተማሪዎችም በማስተማር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ሳይቋረጥ እስካሁን ይገኛል ።

www.ethiopianorthodox.org

## ፮ኛ ድጕሥ ።

ድጕሥ ማለት ለመጻሕፍት ጥራዝ መልክ መስጠት ገበታውን በቆዳ ጠርዞ ልዩ ልዩ ጌጥ መስጠት አንድም ማውጣት ነው ። እርሱም ሐረጉ ልዩ ልዩ የሆነ በስሙ በመልኩ እንዲሁም በቍጥሩ የተለያየ ጌጥ መስጠት ሲሆን በኢትዮጵያ ተስፋፍቶ ያለ ራሱንም የቻለ ሞያ ነበር ፤ በዚህም መልክ ሐረግ መሳብ ፤ ሱማን ወርድ ማውረድ ፤ ሌላም ልዩ ልዩ ጌጥ በዕቃው ላይ መጣል የተለመደ ተግባር ነበር ፤ ከዚህም ሌላ የጊዜ ማሳለፊያ የሚሆነውን ነገር ሁሉ ይሠሩት ያስተምሩትም ነበር ።

በገና ! ማለት ነቢዩ ዳዊት ይደረድረው የነበር ለአምላክ ምስጋና ያቀርብበት የነበር መሣሪያ ነው ። አሁንም የዜማው ቃና ልቡና የሚመስጠውን ምሥጢሩ ኀብረት ያለውን ግጥም በመግጠም ነው ፤ ይኸነኑ በገና ይጠቀሙበት የነበር ፤ በጥንት ጊዜ ታላላቅ ሕዝቦች ሁሉ አንዳንድ በገና መች በቤታቸው ይዘው እነርሱም ይጫወቱ ሌላውንም እንዲጫወትላቸው ያደርጉ ነበር ፤ እርሱም በዜማው ቃና ከማስደሰቱ ጋር ምሥጢሩ የዚህን ዓለም ጣዕም የሚለውጥ በመንፈስ የሚሸነፍጥ እገሌ ፈጸማት የማትባለውን የዓለምን ከንቱነት ያስረዳ ነበር ። መኳንንቱና የሴት ወይዛዝርቱ እንደዛሬው ሁሉ ከዓለም ጋር በጣም አልተጣበቁም ነበርና ስለዚህ ይኸን የመሰለውን ነገር ሁሉ አተኩረው ይመለከቱት ነበር ።

## ፯ኛ ሠንጠረዥ ጨዋታ ።

ጥንታውያን ወገኖቻችን በቁም ነገር የተወሰኑትን ያህል የዕረፍት ጊዜያቸውን የሚያሳልፉበት ፤ እንዲሁ ከፍተኛ ጥበብ እየተባለ ይገመት ወይም ይጠራ የነበረውን ይሠሩ ፤ በዚያውም ጊዜያቸውን ያሳልፉ ነበር ። ይኸውም ሠንጠረዥ ጨዋታ እንዲጫወቱ ይገፋፉ እንዲያውም ያስተምሩ ነበር ። ለምሳሌ ከቤተ ክርስቲያን መምህራን ውስጥ ብዙዎቹ ከሥጋዊ ጥበብ አስፈላጊ ጥበብ አድርገው ሲገምቱ ፤ ሁሉም ሊሠራው እንደሚገባ አድርገው ሲናገሩ ከሥጋዊ ጥበብ ውስጥ ውኃ ዋና ፤ ሠንጠረዥ በገና ፤ ፈረስ ግልቢያ ፤ ጸናጽል ፤ ከበሮ ፤ እርሻ ፤ ቁፋሮ ፤ ጽሕፈት ፤ ድጕሠት ሽለላ ፤ ሙግት ፤ ሊማሩ ያስፈልጋል በማለት ሲናገሩ ፤ ተግባረ ነፍስን ደግሞ በመለየት የሃይማኖት ትምህርት ነው በማለት ሥነ ፍጥረትን ማወቅ ፲ቱ ቃላትን ፤ ፮ቱ ቃላትን ፤ ፭ቱ አዕማደ ምሥጢራትን መማርና ጠንቅቆ ማወቅና በዚያውም መሠረት መሥራት ተገቢ መሆኑን በልዩ ልዩ ምዕዳናቸው ይነግሩ ያስተምሩም ነበር ።

ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሞያዎች በከፊልም ሆነ በጠቅላላ የሚያውቅ ሰው ታላቅ ተብሎ ይገመት ከፍተኛም ማዕረግ ይሰጠው ነበር ፤ ሌሎችንም ወደ ስደት ወደችግር በፈቃዳቸው ይሰዳቸው አገር ለአገርም ያንከራትታቸው የነበር

www.ethiopianorthodox.org

ቅሉ ፩ኛው ጥበቡን ማወቅ ሲሆን ፪ኛው ማዕርጉን ለማግኘት እንደነበር የታወቀ ነው ። እንደዚህ ብሎ የተማረውን በዕውቀትም የበሰለውን ሰው ሁሉ ይፈልገው ነበር ። ሞያን በማፍቀር ብቻ ወገኑ ማን ሀገሩ የት ተብሎ አይጠየቅም ነበር ፤ ስለ ዚህ ጐሣ ሳይለይ ሁሉም ይኸን ጥበብ ለመማር ኢትዮጵያዊ የሆነ ሁሉ ከሀገር ወደ ሀገር ይጐርፍ ነበር ። በዚህ መልክ ጥበብ ከዘመን ወደዘመን ሊሸጋገር ቻለ ። አሁንሳ ምን አቋረጠው ? ያልን እንደሆነ ፤

፩ኛ/ የተማሩት ሰዎች ቦታ የላቸውም ፤ ዋጋም አይከፈላቸው ፤
፪ኛ/ ትምህርቱ ከባድ ነው ጊዜ ይፈጃል ፤
፫ኛ/ ዕውቀቱ ብሔራዊ ብቻ እንጂ ለሌላ ሊተርፍ እንደማይችል ተገመተ ።

እንግዲህ ይኸንና ይኸን የመሰለ ነገር ስለተፈጠረ ለሌላ ሊተርፍ የሚችለው ጥበባችን ለኛው እንኳን ሊጠፋ ተቃርቧል ። ከዚህም ሁሉ ምክንያት ጋር የኛ ቤተ ክርስቲያን በመድከሟ ልትደግፈው አልቻለችም ፣ ሌሎች አብያተ ክርስቲያን ደግሞ ሰውን እንጂ ባህሉን አይፈልጉም ፤ እንዲያውም ባህሉን የጠበቀው የማይመስላ ቸው የማይከተላቸውም ስለሆነ አስቀድሞ ባህሉ እንዲጠፋ ልዩ ልዩ ፕሮፓ ጋንዳ ያደርጋሉ ።

www.ethiopianorthodox.org

# ማ ው ጫ ።

## በውስጡ የሚገኙ ።


ገጽ

መቅድም ። . . . . . . . . . . . . . . ፱—፲፫
መግቢያ ። . . . . . . . . . . . . . . ፲፭—፲፯

ክፍል ፩ ፊደል ከነጓዙ ፤

ምዕራፍ ፩ የፊደል ትምህርት ፤ . . ፲፯—፳፯

፩ኛ የፊደል የት መጣው ፤ . . . . . . . . . . ፲፯—፲፰
፪ኛ » ቊጥር ፤ . . . . . . . . . . ፲፰—፳፩
፫ኛ » መለወጥ ፤ . . . . . . . . . . . ፳፩—፳፪
፬ኛ » የአማርኛ ፊደል ፤ . . . . . . . . ፳፪—፳፫
፭ኛ » የፊደሎች ድምፅ ፤ . . . . . . . ፳፫—፳፬
፮ኛ » የፊደል ትርጕም ፤ . . . . . . . ፳፬—፳፮
፯ኛ » ጥንታዊ የፊደል ቅጽ ፤ . . . . . . ፳፮—፳፯
፰ኛ » ሥርዓተ ትምህርት ፤ . . . . . . ፳፯—፳፰

ምዕራፍ ፪ አቡጊዳ ፤ . . . . ፳፯—፴

፩ የአቡጊዳ ትርጕም ፤ . . . . . . . . . . ፳፯—፳፰
፪ የፊደሉ አቀማመጥ ፤ . . . . . . . . . ፳፰—፳፱
፫ የአቡጊዳ ሥርዓተ ትምህርት ፤ . . . . . . ፳፱—፴

ምዕራፍ ፫ የሒሳብ ትምህርት ፤ . . ፴፩—፴፫

፩ኛ የቊጥር ስልት ፤ . . . . . . . . . . . . ፴፩
፪ኛ በአሁኑ ፊደል ሲቆጠር ፤ . . . . . . . . ፴፩—፴፪
፫ኛ በአቡጊዳ ሲቆጠር ፤ . . . . . . . . . ፴፪—፴፫

ምዕራፍ ፬ ፊደለ ሐዋርያና ገብተ ሐዋርያ ፤ ፴፫—፴፬

፩ኛ የፊደለ ሐዋርያ ታሪክ ፤ . . . . . . . . ፴፫
፪ኛ በብዛት የሚጠቀሙበት አገሮች ፤ . . . . . ፴፬

ምዕራፍ ፭ የጽሕፈት ትምህርት ። . ፴፬—፴፰

፩ኛ የፊደልን መልክ በመጠበቅ ፤ . . . . . . . ፴፭
፪ኛ የነጥቦችን አቀማመጥ በመጠበቅ ፤ . . . . ፴፮
፫ኛ የጽሕፈት ተቃውሞ ፤ . . . . . . . . . ፴፯


www.ethiopianorthodox.org

## ክፍል ፪ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ።

ገጽ


### ምዕራፍ ፩ የንባብ ትምህርት ። . . ፴፱—፵

፩ኛ የንባብ መጻሕፍት ፤ . . . . . . . . . . ፴፱
፪ኛ የንባቡ ዓይነት ፤ . . . . . . . . . . ፴፱—፵

### ምዕራፍ ፪ ዳዊት መድገም ። . . . . ፵—፵፪

፩ኛ የትምህርቱ ዓይነት ፤ . . . . . . . . . ፵፩
፪ኛ ዳዊት ሲደገም የሚሰጠው ሽልማት ፤ . . . ፵፪

### ምዕራፍ ፫ የሃይማኖት ትምህርት ። . . ፵፪—፵፱

፩ኛ የሥነ ፍጥረት ትምህርት ፤ . . . . . . . ፵፫—፵፬
፪ኛ የአሥርቱ ቃላተ ኦሪት ትምህርት ፤ . . . ፵፬—፵፭
፫ኛ የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ትምህርት ፤ . . . ፵፭
፬ኛ የአምስቱ አዕማደ ምሥጢር ትምህርት ፤ . . ፵፮—፵፯
፭ኛ የምግባረ ሠናይ ትምህርት ፤ . . . . . . ፵፱

### ምዕራፍ ፬ የቃል ትምህርት ። . . ፵፱—፶፮

፩ኛ ከበስመ አብ እስከ በሰላመ ቅዱስ ገብርኤል ፤ . ፵፱
፪ኛ ከጸሎተ ሃይማኖት እስከ ጸሎተ እግዝእትነ ማርያም፤ ፶—፶፪
፫ኛ ውዳሴ ማርያም በመላ ፤ . . . . . . . . ፶፫
፬ኛ አንቀጸ ብርሃን ፤ . . . . . . . . . . ፶፬
፭ኛ መልክዓ መልክዕ ፤ . . . . . . . . . ፶፬—፶፮
ልዩ አስተያየት ፤ . . . . . . . . . . . ፶፮

## ክፍል ፫ የዜማ ቃል ትምህርት ።

### ምዕራፍ ፩ ዜማ በጠቅላላው ። . . ፶፯—፷፯

፩ኛ የውዳሴ ማርያም ዜማ ። . . . . . . . ፶፯
፪ኛ መስተጋብዕ ፤ . . . . . . . . . . . ፶፰
፫ኛ አርባዕት ፤ . . . . . . . . . . . . ፶፱—፷፩
፬ኛ አርያም ፤ . . . . . . . . . . . . ፷፩—፷፫
፭ኛ ሠለስት ፤ . . . . . . . . . . . . ፷፫—፷፰
፮ኛ ክስተት ፤ . . . . . . . . . . . . ፷፰

### ምዕራፍ ፪ መወድስ ። . . . . ፷፰—፸፩

፩ኛ ስብሐተ ነግህ ። . . . . . . . . . . ፸—፸፩


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ

ምዕራፍ ፫ የፍትሐ ነገሥት እውነተኝነት ። . ፪፻፴፫—፪፻፴፭

ልዩ አስተያየት ፤ . . . . . . . . . . . . . ፪፻፴፭

ክፍል ፲፩ የቊጥር ትምህርት ።

ምዕራፍ ፩ የዘመን አቈጣጠር ስልት ። . ፪፻፴፮—፪፻፴፰

፩ የመጻሕፍቱ ቊጥር ፤ . . . . . . . . ፪፻፴፮
፪ የትርጕም ስልት ፤ . . . . . . . . ፪፻፴፯
፫ የቊጥር ትምህርት ደረጃ ፤ . . . . . . . ፪፻፴፯

ምዕራፍ ፪ ባሕረ ሐሳብ ። ፪፻፴፰—፪፻፵

፩ የቃላት ትርጕም ፤ . . . . . . . . ፪፻፴፱
፪ የባሕረ ሐሳብ ትምህርት ፤ . . . . . . ፪፻፵

ምዕራፍ ፫ ሐሳበ አሬት ፤ ፪፻፵—፪፻፵፩

፩ አሬታውያን አጽዋማትና በዓላት ፤ . . . . ፪፻፵፩

ምዕራፍ ፬ ሐሳበ ነቢያት ፤ ፪፻፵፩—፪፻፵፭

፩ ሱባዔ አዳም . . . . ፤ . . . . . . ፪፻፵፪
፪ ሐሳበ ሄኖክ ፤ . . . . . . . . . . ፪፻፵፪
፫ ኢዮቤልዩ ዘሙሴ ፤ . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፬ ሱባዔ አብርሃም ፤ . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፭ ቀመረ ዳዊት ፤ . . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፮ ሱባዔ ኤርምያስ ፤ . . . . . . . . . ፪፻፵፫
፯ ሱባዔ ዳንኤል ፤ . . . . . . . . . ፪፻፵፬
፰ ሱባዔ ዕዝራ ፤ . . . . . . . . . ፪፻፵፭

ምዕራፍ ፭ አቡሻክር ። ፪፻፵፭—፪፻፶፰

፩ የዓመተ ዓለም መስፈሪያና መቊጠሪያ ፤ . . ፪፻፵፭
፪ የአበቅቴና የመጥቅዕ አወጣጥ ፤ . . . . ፪፻፵፮
፫ የዕለታት ተውሳክ ፤ . . . . . . . . ፪፻፵፯
፬ የዘመነ ብሉይ አጽዋማትና በዓላት . . . ፪፻፵፰
፭ የቀመር አወጣጥ . . . . . . . . . ፪፻፶—፪፻፶፫
፮ የአበቅቴና የፍስሕ አወጣጥ . . . . . . ፪፻፶፫
፯ የመጥቅዕ አወጣጥ . . . . . . . . ፪፻፶፬—፪፻፶፮


www.ethiopianorthodox.org

ገጽ

፪ የመድጐስ ዓይነት ስምና ቍጥር . . . . . ፪፻፸፭

<u>ክፍል ፲፫ የመምህራን ሕይወት</u>

ምዕራፍ ፩ የመምህራን ታሪክ . . . . . ፪፻፸፯—፪፻፹፪

፩ኛ/ የዜማ . . . . . . . . . . . . . ፪፻፸፯—፪፻፹

፪ኛ/ የቅኔ . . . . . . . . . . . . . ፪፻፹

፫ኛ/ የትርጓሜ . . . . . . . . . . . . ፪፻፹፩

ምዕራፍ ፪ የትምህርት አሰጣጥ ዘዴ . ፪፻፹፩—፪፻፹፭

፩ኛ/ የዜማ . . . . . . . . . . . . . ፪፻፹፫

፪ኛ/ የቅኔ . . . . . . . . . . . . . ፪፻፹፫

፫ኛ/ የመጽሐፍ . . . . . . . . . . . . ፪፻፹፬

ምዕራፍ ፫ መምህራን ይገኙባቸው የነበሩ ቦታዎች ፪፻፹፭—፪፻፹፯

<u>ክፍል ፲፬ የተማሪዎች ሕይወት</u>

ምዕራፍ ፩ የተማሪዎች ታሪክ . . . . . ፪፻፹፰—፪፻፺፩

ምዕራፍ ፪ የተማሪዎች ችግር . . . . . ፪፻፺፩

ምዕራፍ ፫ የተማሪዎች ዘዴኛነት . . . . ፪፻፺፭

ምዕራፍ ፬ የተማሪዎችና የሕዝቡ ግንኙነት ፪፻፺፯

<u>ክፍል ፲፭ የኢትዮጵያ የካህናት የማዕርግ ስም</u>

<u>ምዕራፍ ፩ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች መዓርጋት</u> ፫፻—፫፻፪

<u>ምዕራፍ ፪ የካህናት የክብር ስም</u> . . ፫፻፪—፫፻፬

<u>ምዕራፍ ፫ የአድባራትና የገዳማት የክብር ስሞች ።</u> ፫፻፬—፫፻፭

ማጠቃለያ . . . . . . . . . . . . . ፫፻፯—፫፻፲፫

ምስጋና . . . . . . . . . . . . . ፫፻፳፭

www.ethiopianorthodox.org

# ምስጋና ።

አንድ ሥራ ለመሥራት ሲፈለግ የከፍተኛም የዝቅተኛም ሰው ርዳታ በግድ ያስፈልጋል ፤ ጥሩ ውጤትም የሚገኘው ብዙዎች ያሰቡበት የተመካከሩበት እንደ ሆን ነው ። በዚህም መሠረት እኔ ይኽን ሥራ ልጀምረው እንጅ ብቻዬን ብሆን ልፈጽመው አልችልም ነበር ፤ ነገር ግን ከላይ እንደጠቀስኩት ሁሉ ስማቸው ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ሊቃውንት በሰጡኝ ምክርና ርዳታ በቀላሉ ልወጣው ቻልኩ ፤ ስለዚህ ስማቸውን በመጥራት ከፍ ያለ ምስጋናዬን አቀርብላቸዋለሁ ።

## ( በድጓ ጥናት ለረዱኝ )

፩/ ለሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ወልደ ቂርቆስ ፤
፪/ ለአለቃ ጥበቡ መንግሥቱ ፤
፫/ ለርእሰ ደብር መስፍን ፤

## (በሥዕል ለረዱኝ)

፩/ ለአቶ ሠረቀ የማነ ብርሃንና ለአቶ አሰፋ የማነ ብርሃን ፤

## (በቅኔው መንገድ ፍለጋ ለረዱኝ )

፩/ ለአለቃ ዕንባቆም ( ቃለ ወልድ ) ፤
፪/ ለአለቃ ልሳነ ወርቅ ፤
፫/ ለአለቃ አስተአ በረከት ጌጡ ፤

## (በአቋቋሙና በዝማሬ መዋሥዕት ለረዱኝ)

፩/ ለቀኝ ጌታ ከብካብ ፤
፪/ ለግራ ጌታ አሥራት ፤
፫/ ለሊቀ ጠበብት አክሊለ ብርሃን ፤
፬/ ለአባ ተክለ ድንግል በቊጥር ትምህርት ለረዱኝ ፤

፩/ ለአለቃ ደስታ ሀብተ ገብርኤል በእርማት ለረዱኝ ፤
፪/ ለወይዘሮ ሰብለ ወንጌል ጸጋዬ ፤ በታይፕ ጽሕፈት ለረዱኝ ምስጋና አቀር ባለሁ ። እንዲሁም በአንዳንድ ሐሳብ አቀራረብና ልዩ ልዩ አስረጅ በመስጠት የረዱኝን ሁሉ ስማቸውም ባይጠቀስ ሁሉንም ከልብ አመሰግናለሁ ።

www.ethiopianorthodox.org

## ከዚህ ቀደም የታተሙ

፩. ዜና ሕይወቱ ለቅዱስ ጳውሎስ ፤
፪. ስለ እግዚአብሔር መኖር ፤
፫. ትምህርተ አበ ነፍስ ፤
፬. ክብረ ድንግል ፤
፭. ድንግልናዊ ሕይወት ፤
፮. የእግዚአብሔር ሕገ መንግሥት ፤
፯. እንጸልይ ፤
፰. ማኅበራዊ ኑሮ በኢትዮጵያ ፤
፱. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ትምህርት ።
፲. ጥንታዊ የኢትዮጵያ ሥርዓተ ትምህርት ።

www.ethiopianorthodox.org